## የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣1ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም

አመልካች፦ ወ/ሮ ሐሳይ ደዬ

ተጠሪዎች፦ እነ አቶ ትንሳኤ ኩታሌ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

### ውሳኔ

የዚህ አቤቱታ መነሻ አመልካች ጥቅምት 27 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ያቀረቡት የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲሆን አቤቱታቸው ባለቤቴ ከሞቱ በኋላ ለተጠሪዎች በቃል ስምምነት በአካባቢ ባህል መሰረት በጋራ አርሰን ምርቱን በጋራ ለመጠቀም ተዋውለን ድርሻዬን በማስቀረታቸው የእርሻ መሬት ይዞታዬን እንዲለቁልኝ በፍ/ቤቶች ክስ ብመሰርትም ለተጠሪዎች የተወሰነ በመሆኑና በውሳኔውም ከይዞታዬ ያለመነቀል ሕገ-መንግሥታዊ መብቴ ስለተጣሰ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጠኝ የሚል ነው፡፡

የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

በጉዳዩ ላይ በገዜ ጎፋ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ልጆች በአምስት ሰዎች ላይ የመሰረቱት ክስ ይዞታቸውን ከተጠሪዎች ጋር በጋራ ለመጠቀም ተስማምተው ከያዙ በኋላ አሁን አንለቅም በማለታቸው ፍ/ቤቱ ይዞታውን እንዲለቁ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች በተናጠል ባቀረቡት መልስም ከፊሉን ይዞታ በግዥና ሌላውን በኪራይ ይዘውት ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙበት እንደቆዩ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመመዘን የሰጠው ውሳኔ ተከሳሾች ለረጅም ጊዜ

ሲጠቀሙ በመቆየታቸው ግብር ሲከፍሉበት የቆዩ ስለሆነና የአመልካች ልጆች በይዞታው ሲጠቀሙ ስላልቆዩ ይዞታው የተከሳሾች ነው ሲል ወስኗል፡፡

በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ ጉባዔው አጣርቷል፡፡ በዚህም መሰረት ከስምምነቱ በፊት ወ/ሮ ሐሳይ ደዮ እና ባለቤታቸው ክርክር ያስነሳው የእርሻ መሬት ባለይዞታ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን በፍርድ ቤት የቀረቡትም ምስክሮች ይህንኑ አረጋግጠዋል፡፡ በፍርድ ቤት በተደረገ የቃል ክርክር ከፊሎቹ ተጠሪዎች መሬቱን ከአመልካች ከብዙ ዓመታት በፊት በኪራይ እና አትክልት ያለበትን ቦታ ደግሞ በግዥ መረከባቸውን ሲገልፁ የተቀሩት ደግሞ ከሌላ ሶስተኛ ወገን በኪራይ መያዛቸውን ገልፀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የመሬት ሽያጭ ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር መሆኑን ገልፆ ይህንን ሕገ ወጥ ተግባር የፈፀሙት ሁለቱም ወገኖች ስለሆኑና ተጠሪዎች ከ10 ዓመት በላይ ግብር እየከፈሉ የቆዩትን መንጠቅ ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ ስለሚያስከትል በፍ/ሕ/ቁ 1845 መሰረት በይርጋ የሚታገድ እና በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀጽ 2(7) መሠረት ወራሾች (የአመልካች ወኪል) መሬቱን እየተጠቀሙ የቆዩ ስላልሆኑ ተጠሪዎች ይዞታቸውን መልቀቅ የለባቸውም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በጥልቀት ስንመረምረው አመልካች ከፊሉን ይዞታ ለተጠሪዎች በሽያጭ ማስተላለፋቸውን የሚያሳይ ማስረጃ በፍርድ ቤት መቅረቡን መረዳት የተቻለ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የደረሰበት መደምደሚያ ሕገ-ወጥ ድርጊቱን የፈጸሙት ሁለቱም ወገኖች በመሆናቸውና ተጠሪዎች በይዞታው ለረጅም ጊዜ በመጠቀም ቋሚ አትክልቶችን በማፍራታቸው ይዞታውን እንዲለቁ ቢደረግ ከሚያመጣው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ አንጻር ተጠሪዎች ሊለቁ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40(3) መሬት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና የመንግሥት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ መሬት መሸጥና መለወጥ በሕገ መንግሥቱ የተከለከለ ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቱ ይህንን ጭብጥ ትኩረት ሳይሰጥ ማለፉ አግባብ አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቶች በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ9(2) እና 13(1) መሰረት ሕገ-መንግሥቱን የማስከበር ግዴታ ስለተጣለባቸው የመሬት ሽያጭ ግልጽ ሆኖ ሲታይ ፍርድ ቤቱ በእራሱ ተነሳሽነት ተገቢውን ማጣራት ማድረግና መወሰን ሲገባው ሕገወጥ ለሆነ የመሬት ሽያጭ ውል ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ውሳኔ ማሳለፍ ሕገ-መንግሥቱን የሚፃረር ውሳኔ ሆኖ

አግኝተነዋል፡፡ ሕገ-መንግሥቱን የሚፃረሩ ሕጎች፣ ደንቦች፣ የሕግ አስፈፃሚ አካላት ውሳኔዎችና ሌሎች ድርጊቶች ከመጀመሪያውም እንዳልተፈፀሙ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በሽያጭ ለተጠሪዎች የተላለፈው መሬት ላይ ያስተላለፈው ውሳኔ ሕገ-መንግሥታዊ ባለመሆኑ የሕገ-መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው ይህ ክርክር የተነሳበት ይዞታ መሬት የአመልካች መሬት መሆኑንና ልጆቻቸውም በቤተሰብ አባልነት የተመዘገቡበት መሆኑን በፍርድቤት ተያይዞ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ከማረጋገጡም በላይ ይህ እውነታ በተከሳሾችም አልተካደም፡፡አራቱ ተከሳሾች በስር ፍርድ ቤት በግልጽ ባቀረቡት መቃወሚያ በቀን 15/6/95 ዓ.ም በተጻፈ ውል ክስ የተመሰረተበትን የይዞታ መሬት እና አትክልት ከአመልካች ወ/ሮ ሐሳይ ደዮ በገንዘብ የገዙ መሆናቸውን የሚያስረዳውን የጽሁፍ ማስረጃ በማያያዝ አቅርበው እንደተከራከሩ የቀረበው ሰነድ ያስረዳል፡፡ሌላው ተከሳሽ ደግሞ የአመልካችን መሬት ከማይመለከተው ግለሰብ በ8 ዓመት ኮንትራት ወስደው መያዛቸውን ገልጸው ማስረጃዩ ነው ብለው ያቀረቡት በቀን 6/3/94 ዓ.ም የተጻፈው መሬቱን በብር 225 ላልተወሰነ ጊዜ ሊጠቀሙበት የወሰዱ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ይህም በተጠሪዎች የታመነ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች መሬቱን ገዝተው ለአመታት የያዙት በመሆኑ ይዘው ይጠቀማሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ከተደነገገው ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የገዜ ጎፋ ወረዳ ፍርድቤት የሕገመንግስቱን አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎችን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

በገዜ ጎፋ ወረዳ ፍርድቤት ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገ መሆኑን እንዲያውቁት ለፍርድቤቶቹ የውሳኔው ግልባጭ እንዲደርሳቸው ይደረግ።

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት።

የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋም ይሰጥ።

2

# የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣5ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ አልይ ዳዌ

ተጠሪ፡- አቶ ሙመድ አደም

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

የዚህ ክርክር መነሻ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ሃብሮ ወረዳ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ የእርሻ መሬት ይዞታ ሲሆን በስር የወረዳ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው የነበሩት የአሁን አመልካች የእርሻ መሬታቸውን ለልጃቸው በኮንትራት ሰጥተውት እየተጠቀሙበት እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የአሁን ተጠሪ ያለአግባብ መያዙን በመቃወም እንዲያስረክባቸው ክስ መስርተው ነበር፡፡በዚሁ መሰረት ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የሀብሮ ወረዳ ፍርድቤት መሬቱን ልጃቸው ለአሁኑ ተጠሪ እንደሸጠለት ተረጋግጧል በማለት መሬቱን መጠየቅ እንደማይችሉና ሊመለስላቸው እንደማይገባ በመወሰኑ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶችም ሆነ ለኦሮሚያና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት በማጣታቸው የፍርድቤቶቹ ውሳኔ በሕገ መንግስቱ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ስለመሆኑ ጥበቃ የተደረገለትን ድንጋጌ የሚጥስ በመሆኑ ትርጉም እንዲሰጥበት ለአጣሪ ጉባኤው ማቅረባቸውን ምክርቤቱ ተረድቷል፡፡

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤውም የቀረበለትን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ ከመረመረ በኋላ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት የእርሻ መሬታቸው የአሁን አመልካች ልጅ ለነበረው መሀመድ አልይ ለተባለው ሰጥተውት ወደ ሰፈራ ሔዶ በመሞቱ መሬቱ ለሚች ወንድም እንደተላለፈና ይህኛው ልጅ ለተጠሪው እንደሸጠለት ፍርድቤቱ አረጋግጫለሁ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ማለቱንና ይህም ለውሳኔው መሰረት መሆኑን በመረዳት ውሳኔው መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ሀብት መሆኑን ከሚደነግገው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/3/ ጋር የማይጣጣምና የአመልካችን ሕገመንግስታዊ መብት የጣሰ በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የሚል የውሳኔ ሃሳብ ለምክርቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የምክርቤቱ የሕገመንግስት እና የክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ እና በምክርቤቱ ባለሙያዎች አስተያየት ላይ ከተወያየ በኃላ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክርቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ምክርቤቱም አቤቱታውን ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር በማጣመር መርምሯል፡፡እንደመረመረውም ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሃብሮ ወረዳ ፍርድቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው መሬቱ ለአሁን ተጠሪ የተሸጠ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች ሊጠይቁ አይችሉም የሚለውን ጭብጥ መሆኑን ምክርቤቱ መረዳት ችሏል፡፡ መሬት ደግሞ በግልጽ የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ሀብት እንደሆነና የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ስለመሆኑ በሕገ መንግስታችን አንቀፅ 40/3/4/ ስር በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይህንን ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም ውሳኔ  በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደማይችል የህገመንግስቱን የበላይነት በሚደነግገው እና አንዱ መሰረታዊ መርህ በሆነው ድንጋጌ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

ስለሆነም ፍርድ ቤቶች በግለሰቦች የተፈፀመውን የመሬት ሽያጭ ድርጊት በዝምታ ማለፋቸው ብሎም ያለማረማቸው እንዲሁም ሕገመንግስቱን የማስከበር ኃላፊነት ተሰጥቷቸው እያለ የሕገመንግስቱን ድንጋጌ የሚጥስ ውሳኔ መስጠታቸው ሊታረም የሚገባው በመሆኑ በፍርድቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው መደረግ ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም ክርክር የተነሳበት የእርሻ መሬት በሽያጭ ከአንዱ ወደ ሌላው ተላልፏል በማለት በሃብሮ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠውና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1.በሃብሮ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠውና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች እንዲጸና የተደረገው እና የአመልካችን ሕገመንግስታዊ የመሬት ባለይዞታነት እና የተጠቃሚነት መብት የሚጻረረው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን አውቀው እንዲያስፈጽሙ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ይተላለፍ፡፡

2.የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

3

ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም

## የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የስራ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

የፌ/ም/መ/ቁ.017/08

አመልካች፡- አቶ ሙየዲን ዮኒስ

ተጠሪዎች፡- 1አቶ ናዚ አሊይ

2. አቶ አሊይ አብዶ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ-መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች ለተጠሪዎች የሰጠሁት ይዞታ መሬት እንዲለቀቅልኝ በፍ/ቤት ስጠይቅ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ ይዞታውን ማስለቀቅ ሲገባው ተጠሪዎች የሰጡትን መልስ ተመልክቶ ይዞታው ሊመለስልህ አይገባም ብሎ መወሰኑ ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 40 ጋር ይቃረናል በማለት የሕገመንግስት ትርጉም እንዲሰጥ ለሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 26 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ ማመልከቻ ለጉባኤው አቅርበዋል፡፡ በማመልከቻቸውም ለተጠሪዎች የሰጠሁት ይዞታ መሬት እንዲለቀቅልኝ በፍ/ቤት ስጠይቅ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ ይዞታውን ማስለቀቅ ሲገባው ተጠሪዎች የሰጡትን መልስ ተመልክቶ ይዞታው ሊመለስልህ አይገባም ብሎ መወሰኑ ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 40 ጋር ይቃረናል በማለት የሕገመንግስት ትርጉም ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡



4 8

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች 1ኛ ተጠሪ ከሚስቱ ጋር በመሆን በአላባው እንዲጠቀም የሰጡትን የጫት ተክል የሚገኝበት 6 ሄክታር የገጠር መሬት ይዞታ ለ2ኛ ተጠሪ ሸጧል በማለት በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የመሬት ሽያጭ ውል ፈርሶ ይዞታው እንዲመለስላቸው በፍ/ቤት ክስ መስርተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን ይዞታ አመልካች በአደራ ይዞ እንዲጠቀም የሰጠሁት ሲሆን ኑሮ ሲከብደው ለ2ኛ ተጠሪ በኪራይ መልክ በብር 1000.00 /አንድ ሺ ብር/ የሰጠ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ ይዞታውን ለመመለስ ፈቃደኛ አይደለም ብሎ ሲከራከር 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ክርክር የተነሳበትን የመሬት ይዞታ 1ኛ ተጠሪ ከሚስቱ ጋር በመሆን በ1988 ዓ.ም በብር 1400.00 /አንድ ሺ አራት መቶ ብር/ የሸጠላቸው በመሆኑ እና ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ይዞታውን መመለስ አይገባኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው የመሬት ይዞታ የማን እንደሆነ ተጣርቶ ለምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበው ሪፖርት ላይ ክርክሩን ያስነሳው ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ሚስት አባት መሆኑን፤ የ1ኛ ተጠሪ ሚስትም ክርክሩን ያስነሳውና በውርስ ከአባትዋ የተላለፈላትን የመሬት ይዞታ ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠች ሲሆን ክርክር የተነሳበት ይዞታ የአመልካች እንዳልሆነ ተረጋግጧል፡፡

በኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ መሰረትም ቋሚ ንብረት ሽያጭን የሚከለክል ቢሆንም የመሬት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ የሚጠይቀው ወገን ከውሉ መፍረስ የተነሳ ጥቅም ያለው ሰው ብቻ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1808 ንዑስ አንቀጽ 2 ስለሚደነግግ አመልካች የመሬት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ አይችልም በማለት የተወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

መዝገቡ አመልካች ካቀረቡት አቤቱታ ጋር ተጣምሮ ተመርምሯል፡፡ ጉዳዩ ለጉባኤው የቀረበው አመልካች የፍ/ቤቱ ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ላይ ከንብረት መብታቸው ጋር የሚቃረን መሆኑን በመግለጽ የሕገመንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው በጠየቁት አቤቱታ መነሻነት ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት አመልካች እንዲመለስላቸው የሚጠይቁት በገጠር የሚገኝ የመሬት ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ሚስት ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠች መሆኑ ቢረጋገጥም አመልካች በዚህ ይዞታ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን አላስረዱም በማለት የወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ሲመለከት ክርክር የተነሳበትን የመሬት ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ሚስት ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠች መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የመሬት ሽያጭ ውሉም መፍረስ አይገባውም ያለው አመልካች ከውሉ መፍረስ የሚያገኙትን ጥቅም አላረጋገጡም በሚል ምክንያት ነው፡፡

ነገር ግን የሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ በገጠርም ሆነ በከተማ መሬት እና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው የሚለውን ድንጋጌ ስንመለከት በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የመሬት ሽያጭ ውል መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ከሚከለክለው የሕገመንግስቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ አመልካች ከመሬት ሽያጭ ውሉ መፍረስ የሚያገኙትን ጥቅም አላረጋገጡም ብሎ የመሬት ሽያጭ ውሉ ሳይፈርስ እንዳለ እንዲቀጥል የወሰነው ውሳኔ ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 ጋር የሚቃረን መሆኑን ጉባኤው በሙሉ ድምጽ የተስማማ ስለሆነ ይህ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው ክርክር የተነሳበት ይዞታ መሬት የአመልካች የይዞታ መሬት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ ሚስት ከአባቷ በውርስ ተላልፎላት ለ2ኛ ተጠሪ በብር 1400.00 /አንድ ሺ አራት መቶ ብር/ የሸጠችለት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ መብትና ጥቅም የለህም ተብሎ የአመልካች ጥያቄ በፍ/ቤቱ ውሳኔ ውድቅ መደረጉን ነው፡፡ይህም ቢሆን የመሬት ሽያጭ ውል መኖሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ ውሉ ሳይፈርስ መታለፉ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በገጠርም ሆነ በከተማ መሬት እና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው የሚለውን ድንጋጌ የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ሆኖ ስለተገኘ በፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ አመልካች በይዞታው ላይ መብት የለውም መባሉ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ቢሆንም የመሬት ሽያጭ ውሉ ሳይፈርስ እንዳለ እንዲቀጥል ጉዳዩን የተመለከተው የዶባ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውና በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የጸናው ውሳኔ የሕገ-መንግስቱን አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 የሚቃረን በመሆኑ በሕገ-



6

2

መንግስቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የውሳኔውን ውጤት በተመለከተ በአጣሪ ጉባኤው የተባለ ነገር ባይኖርም ከክርክሩ ሒደት አመልካች ክርክር በተነሳበት መሬት ላይ ባለመብት እንዳልሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡የመሬት ይዞታው በፍ/ቤቱ በማስረጃ ተረጋግጧል በተባለው መሰረት የ1ኛ ተጠሪ ሚስት ቢሆንም ባለመብቷ በሕገወጥ የሽያጭ ውል የተላለፈው መሬት እንዲለቀቅላቸው ባለመጠየቃቸው ምክንያት 2ኛ ተጠሪ በሕገወጥ የሽጭ ውል ገዝተው በያዙት መሬት ተጠቃሚ ሊሆኑ ስለማይገባ በመሬቱ ላይ መብት አለኝ የሚል ወገን ጠይቆ እስኪረከብ ድረስ መሬቱ በሚመለከተው የመሬት አስተዳደር ስር እንዲቆይ ተወስኗል፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

1. በዶባ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በየደረጃው ባሉ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 102452 የጸናውና የመሬት ሽያጭ ውሉን እንዳይፈርስ ያደረገው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን እንዲያውቀው የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲደርሰው ይደረግ፡፡
2. በምክርቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲደርሰው ይደረግ፡፡
3. የፌዴራሉ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

4

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣1ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም

አመልካች፡- እማሆይ ባንቺ አምላክ ደርሶልኝ ፣ወኪል የአማራ ብ/ክ/መንግስት የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ

ተጠሪ፡- አቶ አበባው ሞላ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የዚህ አቤቱታ መነሻ ጉዳይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ንኡስ አንቀፅ 3 እና 4 የተደነገገውን መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነው፤ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው ተብሎ የተደነገገውን ሕገ መንግስታዊ መብትን የሚጥስ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሆኖ በአመልካች አቤቱታ ላይ በየደረጃው የሚገኙ ፍርድቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የውሳኔ ሐሳብ በማቅረቡ ነው፡፡

የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ሚየዚያ 29 ቀን 2004 ዓ.ም.በወኪላቸው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ አማካኝነት ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ተጠሪው በአማራ ክልል በደቡብ ጎንደር ዞን በምስራቅ እስቴ ወረዳ የሚገኝ የመሬት ይዞታዬን በመያዝ 900 ብር(ዘጠኝ መቶ ብር) ካበደረኝ በኋላ የተበደርኩትን ብር መልሼ ይዞታዬን እንዲመልስልኝ ብጠይቀው እምቢተኛ በመሆኑ በሚል ሰኔ 10 ቀን 1996 ዓ.ም. በአመልካች የቀረበለትን ክስ በመጀመሪያ የተመለከተው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ



15

ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጥር 23 ቀን 1997 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አመልካች ልጆቼን ለመፈለግ ስል ከተጠሪ ብር 900 ተብድሬ በመያገኘት ቤቱንና አትክልቱን አስይዤ ሄድኩኝ ትበል እንጂ ቤቱንና አትክልቱን ለመሸጧ በቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ አረጋግጧል፡፡ ከዚያም በኋላ ሐምሌ 18 ቀን 1990 ዓ.ም አመልካች ብሩን ከጥቅምት 30 ቀን እስከ ጥር 30 ቀን 1990 ዓ.ም ድረስ ልትመልስ፣ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሆነው በሽማግሌዎች እርቅ ያደረጉና ገንዘብ አመልካች ባትመልስ ግን ተጠሪ ቤቱንና አትክልቱን ሊረከብ ተዋውለው ከዚያም አመልካች እንደ እርቁ ባለመፈፀሟ የተነሳ የካቲት 5 ቀን 1991 ዓ.ም የሽማግሌ ዳኞች እንደ እርቁ እንዲፈፀም ውሳኔ መስጠታቸው ታውቋል፡፡ ክሴን ለደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀርብም ፍ/ቤቱ መሬትሽን እና አትክልቱን ከሸጥሽ በኋላ እንደገና በመያገኘት ነው የሰጠሁት ብለሽ ከተጠሪ ጋር ሽምግልና ይዘሽ ገንዘቡን የምትመለሽበት ጊዜ ቢሰጥሽም መመለስ ስላልቻልሽ በሽማግሌዎች ላይ በፈፀምሽው ስምምነት መሰረት መሬቱ አይገባሽም በሚል ጥር 23 ቀን 1997 ዓ.ም. ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡

ውሳኔው የሕገ-መንግሥት ጥሰት ያለው በመሆኑ ክሴን በወኪሌ የምስራቅ እስቴ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት የፍትህብሔር ዐቃቤ ሕግ አማካኝነት እንደ አዲስ ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ለምስራቅ እስቴ ወረዳ ፍርድቤት ባቀርብም ጉዳዩ ቀደም ብሎ በፍርድ ያለቀ ነው በሚል ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡ በውሳኔው ላይ ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ባቀርብም በተመሳሳይ በብይን የተዘጋ በመሆኑ በውሳኔው ላይ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቤ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በሚል በመወሰኑ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 እና ንኡስ አንቀጽ 4 ተጥሷል ሲሊ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካች ተጥሷል ሲሉ የጠቀሷቸው የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌዎች አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 ናቸው፡፡የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 ‹‹የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው መሬት የማይሸጥ የማይለወት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው፡፡›› በሚል ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 ‹‹የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈፃፀሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል›› በሚል ተደንግጓል፡፡



14

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በገጠማቸው ጊዜያዊ ችግር ምክንያት ልጆቻቸውን ለመፈለግ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄዱ በይዞታቸው ላይ ያለውን ቤት እና አትክልቱን ለተጠሪ አስይዘው ብር 900(ዘጠኝ መቶ ብር) ተበድረው የነበረ ሲሆን ከሄዱበት ሲመለሱ ይዞታቸውን ተጠሪ እንዲመልስላቸው ጠይቀው ተጠሪ እምቢተኛ በመሆኑ ክሳቸውን ለፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም አመልካች በይዞታቸው ላይ ያለውን ቤት እና አትክልት ሸጠው ስለመሄዳቸው የቀረበው የሰነድ ማስረጃ እንደሚያስረዳ በመጥቀስ በሌላ በኩል አመልካች አከራካሪውን ይዞታ በተመለከተ ከተጠሪ ጋር በሽማግሌዎች ፊት ተደራድረው የተበደሩትን ገንዘብ የሚመልሱበት ጊዜ ተቆርጦ ተሰጥቷቸው በተሰጣቸው ጊዜ ገንዘቡን የማይመልሱ ከሆነ ይዞታውን ሊያስረክቡ ተስማምተዋል በማለት ስምምነቱ እንዲፈፀም ወስኗል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት በአንድ በኩል አከራካሪው ይዞታ መሸጡን ያረጋገጠ ሲሆን በሌላ በኩል በይዞታው ላይ የተደረገውን የመያዣ ውል ስምምነት አፅድቋል፡፡ ይህን የፍ/ቤቱን ውሣኔ ይዞታው ከተወሰነለት አጠቃቀም፣ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ እንደዚሁም ከላይ ከተጠቀሰው የሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች አንፃር መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

አመልካች ቅሬታቸውን ለጉባኤው ሲያቀርቡ አያይዘው ያቀረቡት ኅዳር 3 ቀን 2001 ዓ.ም የታደሰ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ የይዞታው አጠቃቀም ለእርሻ የተወሰነ መሆኑን ያሰረዳል፡፡የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 በአንቀጽ 19 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የገጠር መሬት ይዞታን የመጠቀም መብት በዋስትና ማስያዝ የተፈቀደው የገጠር መሬት ይዞታን ለማልማት በሊዝ የያዘን ሰው የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም በወረዳው አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ጽ/ቤት በተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንደተጠቀሰው አከራካሪው ይዞታ ለእርሻ የሚውል (የተመደበ) ሲሆን በዚህ ዓይነት ይዞታ ላይ አትክልት እና ቤት አለው በሚል ምክንያት የሚደረግ የሽያጭም ሆነ የመያዣ ውል መሬቱን ከመሸጥ ወይም ከማስያዝ የተለየ ውጤት አይኖረውም፡፡

ከላይ በተጠቀሰው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ድንጋጌ መሰረት ደግሞ በአከራካሪው የመሬት ይዞታ ላይ ያለን የመጠቀም መብት በመያዣነት ማስያዝ ለአመልካች የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ይህ የአዋጁ ድንጋጌ መሬት በመያዣ ሰበብ እንዳይሸጥ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ፣አርሶ አደሩ



13

ከይዞታው እንዳይፈናቀል የሚከለክል እና ሕገ-መንግሥቱ በአንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ያስቀመጠውን ዓላማ የሚያሳካ ነው፡፡ በመሆኑም አከራካሪውን መሬት መሸጥ በግልጽ የተቀመጠውን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ የሚፃረር ሲሆን በመያዣ ውል መስጠትም ቢሆን በአዋጁ ያልተፈቀደ እና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚደረግ ሽያጭ በመሆኑ በውጤቱ የሕገ-መንግሥት ጥሰት ያለው ነው፡፡

በመሆኑም ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት ሕገ-መንግሥቱን የሚፃረር ስምምነት በመቀበል የሰጠው ውሳኔ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በሚል የተደነገገውን ሕገ-መንግሥታዊ ክልከላ የጣሰ እና አመልካችን ከይዞታቸው ያፈናቀለ በመሆኑ የሕገ-መንግስቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የጣሰ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ-መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው በዚህ ጉዳይ የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኗ አመልካች ከሳሽነት እና በአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽነት መነሻነት ለቀረበለት የሁከት ይወገድልኝ (የመሬት ይዞታዬን ይልቀቅልኝ) እና የመሬት አላባ ይከፈለኝ ክስ ፍርድ ቤቱ በተከሳሹ በኩል የቀረበለትን በአመልካችና ተጠሪ መካከል በቀን 04/06/89 ዓ.ም ተደርጓል ተብሎ የቀረበውን የሽያጭ ውልና ሐምሌ 18 ቀን 1990 ዓ.ም ተፈፅሟል ተብሎ የቀረበውን የዕርቅ ስምምነት ተቀብሎ በማፅደቅ ከሳሽ (የአሁኗ አመልካች) ቤቱንና የአትክልቱን ቦታ አስይዤ ብር 900 (ዘጠኝ መቶ ብር) ገንዘብ ተበድሬ ሄድኩኝ ትበል እንጂ ቤቱንና አትክልቱን ለመሸጧ የቀረበው የፅሑፍ ማስረጃ አረጋግጧል፤ ከዚያም በኋላ በመያዣነት ነው የሰጠሁት በማለት በእርቅ እንዲፈፀም ድርድር ገብታ በሽማግሌዎች እርቅ ተፈፅሞ በዕርቁ መሰረትም በተወሰነው ጊዜ ገንዘቡን ለተከሳሽ (የአሁኑ ተጠሪ) መልሳ ቤቱንና አትክልቱን መረከብ ስላልቻለች በእርቁ መሰረት እንዲፈፀም በማለት የሰጠው ውሳኔ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ ዓንቀፅ 3 እና 4 ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግስቱ ዓንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም።



12

በመሆኑም በደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት የሕገመንግስቱን አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 ድንጋጌዎችን በሚቃረን መልኩ የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

በደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት ተሰጥቶ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገ መሆኑን እንዲያውቁት ለፍርድቤቶቹ የውሳኔው ግልባጭ እንዲደርሳቸው ይደረግ፡፡

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡

የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ወኪል ይሰጥ፡፡



11

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣5ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ቀለቤ ተስፋ

ተጠሪ፡- አቶ አየልኝ ደርበው

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የሕገመንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት የቀረበው ጉዳይ መነሻ የሆነው አመልካች ወ/ሮ ቀለቤ ተስፋ ከተጠሪ አቶ አየልኝ ደርበው ጋር በ13/11/2002 ዓ.ም. የፈፀምኩት የመሬት መያዣ ውል ተገድጄ የፈፀምኩት ውል ስለሆነ እንዲፈርስልኝ በማለት ለደንቢያ ወረዳ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው የነበረ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ውሉን እንድትፈርም ያልተገደደች ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ አይገባውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳውን ፍርድቤት ውሳኔ ያፀናው ሲሆን በውሳኔው ላይ በአመልካች የቀረበውን የሰበር አቤቱታም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በውሳኔው የሕግ ስሕተት የለበትም በማለት ውድቅ አድርጎ የስር የወረዳ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማጽናት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካችም በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ አማካኝነት የፍርድቤቱ ውሳኔ የሕገመንግስቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 ትን በመጣስ የተሰጠ ስለሆነ የሕገመንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ለሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አመልክተዋል፡፡

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበለትን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ በመመርመር መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የህዝብና የመንግስት ሀብት እንደሆነ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ተደንግጓል፡፤በክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 5/1/ እና በፌዴራሉ የገጠር የመሬት አስተዳደርና 10



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደሬሽን ምክር ቤት

አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 በመግቢያቸው ይህንኑ በማጠናከር ደንግገዋል፡፡መንግስት የሚያወጣቸው ሕጎችና በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት የሚወስኗቸው ውሳኔዎች ሕገመንግስታዊ ዋስትና የተሰጣቸውን መብቶች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚረዱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ለፍርድቤቶቹ ውሳኔ ምክንያት የሆነው ውል በተዘዋዋሪ መንገድ የመሸጥ የመለወጥ ተግባር የተፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ከመነሻው በሕገመንግስቱና እርሱን ተከትለው በወጡ ሕጎች አርሶ አደሩን ከመፈናቀል በመታደግ በመሬት የመጠቀም መብቱን ተግባራዊ በማድረግ ዋስትና በመስጠት የተቀመጡ ድንጋጌዎችን የሚቃረን ነው፡፡ በፌዴራሉ የገጠር የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀጽ 8/4/ እና በክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 19/1/ የገጠር ይዞታ መሬትን በዋስትና ማስያዝ የተፈቀደው ባለሀብት ሆኖ የገጠር ይዞታ መሬትን ለማልማት በሊዝ ይዞታ የተከራዩትን እንጂ በግብርና ስራ ተሰማርቶ የሚገኘውን ገበሬ ይዞታውን በዋስትናና በእዳ በመያዣነት እንዲያውል የሚፈቅዱ ሕጎች አለመሆናቸው በፍርድቤቶቹ ውሳኔ ያልተዳሰሰ ነጥብ ነው ካለ በኃላ ተጠሪ የአመልካችን መሬት በመያዣነት፣አመልካችም ለተጠሪ የይዞታ መሬቷን በመያዣነት መስጠት የማትችል ስለሆነ ፍርድቤቶችም ይህን አይነት ሕገወጥ ውል ሲቀርብላቸው በራሳቸው ተነሳሽነት ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው ይህን በማለፍ የሰጡት ውሳኔ የሕገመንግስቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት የውሳኔ ሀሳብ ለምክርቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የምክርቤቱ የሕገመንግስት እና የክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ እና በምክርቤቱ ባለሙያዎች አስተያየት ላይ ከተወያየ በኃላ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክርቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ምክርቤቱም አቤቱታውን ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር በማጣመር መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም የዚህ ክርክር መነሻ አመልካች የሆኑት ፈራሽ እንዲሆን አቤቱታ ያቀረቡበትና በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶች ሊፈርስ አይገባም በማለት ውሳኔ የሰጡበት በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ13/11/2002ዓ.ም. የተደረገው የዕርቅ ወይም የስምምነት ውል 9



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ሲሆን ይህ ውል ቀደም ሲል በአመልካችና የተጠሪ አውራሽ በሆኑት ሟች አቶ ይመር ቸኮል መካከል በ26/10/88ዓ.ም. ተደርጎ የነበረውን ውል ለማሻሻል ወይም ለመተካት የተደረገ ውል መሆኑን ምክርቤቱ ተረድቷል፡፡

በምክርቤቱ እይታ እነዚህ ውሎች ማለትም ቀደም ሲል በአመልካችና በአቶ ይመር ቸኮል መካከል በ26/10/88ዓ.ም የተደረገውና ወ/ሮ ቀለቤ ተስፉ ከአቶ ይመር ቸኮል ብር 270.00 (ሁለት መቶ ሰባ ብር) ተበድራ በልታ የምትከፍለው በማጣቷ ከቦታዋ ቀንሳ የቦታዋን ግማሽ ለባለገንዘቡ አስረክባለች... በሚል ያደረጉት እንዲሁም ይህን ውል ለማሻሻል ወይም ለመተካት በአመልካችና የአሁኑ ተጠሪ አቶ አየልኝ ደርበው መካከል በ13/11/2002ዓ.ም. ... ወ/ሮ ቀለቤ ተስፋና አቶ አየልኝ ደርበው በቤት ቦታ ተጣልተው በዛሬው ቀን በሽማግሌ ሲስማሙ... የመጀመርያው ውላቸው ፈርሶ ወ/ሮ ቀለቤ ተስፉ ለ42 ዚንጎ ቆርቆሮ መስሪያ 8x9 ሜትር ቦታ ለአቶ አየልኝ ደርበው አስረክባለች፤... በሚል የተደረገው የዕርቅ ወይም የስምምነት ውል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መሬትን ለመሸጥና ለመለወጥ የተደረጉና ባለይዞታዋን የሚያፈናቅሉ በመሆናቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 እንዲሁም ይህን ተከትለው በወጡት የፌዴራሉና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጆች የተደነገገውን መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነው፤ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፤... ተብሎ ዋስትና የሰጠውን ድንጋጌ የሚቃረኑ መሆናቸውን ግልጽ ነው፡፡

ይህ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንን ተገንዝበው ውሉ ከመጀመርያው ጀምሮ ከሕገመንግስቱ ጋር የሚቃረን፣ሕገ ወጥና ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው ይህንን በማለፍ ውሉ በመገደድ ሳይሆን በተዋዋዮቹ ፈቃድ የተፈፀመ ስለሆነ ሊፈርስ አይገባውም በማለት የሰጡት ውሳኔ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀፅ 40 ንኡስ ዓንቀፅ 3 እና 4 መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነው፤የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው በማለት የተደነገገውን የሚቃረን መሆኑን ምክርቤቱ አምኖበታል፡፡

በመሆኑም በደንቢያ ወረዳ ፍርድቤት ተሰጥቶ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ መብት የሚጥስ ሆኖ 8



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ስለተገኘ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1.በደንቢያ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠውና በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ የመሬት ባለይዞታነት እና የተጠቃሚነት መብት የሚጻረር በመሆኑ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን አውቆ እንዲያስፈጽም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ይተላለፍ፡፡

2.የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው አካል ይሰጥ፡፡

6

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣1ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ አለሚቱ ገብሬ

ተጠሪ፡- አቶ ጫኔ ደሳለኝ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

**ውሳኔ**

የዚህ አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ የሆነው ግለሰብ የአመልካች ይዞታ የሆነውን የእርሻ መሬት ለሃምሳ ዓመታት በኪራይ የያዝኩት ነው በማለት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያወጣበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የስር ፍርድቤት በአመልካች የቀረበውን ክስ የይርጋ ጊዜን መሰረት በማድረግ ውድቅ በማድረጉ ለአጣሪ ጉባኤው የሕገመንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት በመቅረቡ ነው፡፡

የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በ1989 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ባደረኩት የኪራይ ውል ስምምነት በገጠር የሚገኝ 2 ሄክታር የእርሻ መሬት ይዞታዬን ለ5 ዓመት እንዲጠቀም ያከራየሁት ቢሆንም ተጠሪ ግን ከአመልካች ጋር የኪራይ ውሉን የተፈራረምነው ለ5 ዓመት ሳይሆን ለ50 ዓመት ነው፣ በማለት በይዞታው ላይ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቶ ግብር እየከፈለ የሚጠቀምበት በመሆኑ የዚህ ይዞታ ባለመብት መሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰንለት በወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ሲሆን አመልካች በ1989 ዓ.ም. በተደረገ የውል ስምምነት 2 ሄክታር የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታቸውን ለተጠሪ ያከራዩት ለ50 ዓመት ሳይሆን ለ5



8

ዓመት በመሆኑ እና የኪራይ ጊዜውም ያለቀ ስለሆነ መሬቱ ይመለስልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤትም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው የገጠር መሬት ኪራይ ውል ለ5 ዓመት ሳይሆን ለ50 ዓመት ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች በኪራይ ባገኘው የገጠር መሬት ይዞታ ላይም ለ16 ዓመት ግብር በመገበር የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር ወስዶበታል በማለት የአመልካች ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168(1) እና 1845 በይርጋ ይታገዳል በማለት ወስኖ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አያስቀርብም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ውሳኔው ከሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌዎች ጋር ይቃረናል በማለት ትርጉም እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤው በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች እና ተጠሪ ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝና ግብሩም በማን እንደሚገበር በተደረገው ማጣራት መሰረት የከፋ ዞን የጊምቦ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት በቁጥር 3443/Q-32 በቀን ሰኔ 11 ቀን 2007 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ ክርክር ከተነሣበት 2 ሄክታር የመሬት ይዞታ ውጪ 6.4 ሄክታር የመሬት ይዞታ ለአመልካች የተሰጣቸውና የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር በስማቸው የተመዘገበ እና ግብርም የሚገብሩት እኚሁ አመልካች መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ክርክር የተነሳበትን 2 ሄክታር ጨምሮ 4.2 ሄክታር የመሬት ይዞታ ያለው እና በዚህ ይዞታ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቶበት ግብር የሚገብር መሆኑን አረጋግጦ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን 2 ሄክታር ይዞታ ጨምሮ በ4.2 ሄክታር ላይ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር ሊሰጠው የቻለውም ክርክር የተነሳበት ይዞታ በ1997 ዓ.ም. ሲለካ አመልካች ተቃውሞ ባለማንሳታቸው መሆኑን ገልፆአል፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ላይ በ1989 ዓ.ም በኪራይ የወሰደው የገጠር መሬት ይዞታ ላይ በስሙ የባለይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የወሰደበት መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡የኢፌዴሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ የተደነገገ ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ዋና ዓላማ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸውን ለማረጋገጥ የተደነገገ መሆኑን ስንመለከት ምንም እንኳ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው የ50 ዓመት የእርሻ

መሬት የኪራይ ውል የሽያጭ ውል ነው ባይባልም አንድ አርሶ አደር ለ50 ዓመት ያህል መሬቱን ማከራየቱ በእራሱ አርሶ አደሩን ከመሬቱ የሚያፈናቅለው ተግባር ነው፡፡

በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል(ሀ) ላይ አርሶ አደር ለአርሶ አደር መሬቱን ሲያከራይ እስከ 5 ዓመት ይሆናል የሚለውን ድንጋጌ ስንመለከት አርሶ አደሮች መሬታቸውን በማከራየት ሰበብ ከመሬታቸው እንዳይፈናቀሉ ጥበቃ ለማድረግ የተደነገገ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የፍ/ቤቱ ውሳኔ ሲታይ ተጠሪ በ1989 ዓ.ም ከአመልካች ላይ ለ50 ዓመት በኪራይ በወሰደው የገጠር መሬት የእርሻ ይዞታ ላይ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቼበታለሁ በማለቱ አመልካች በኪራይ የሰጡትን የእርሻ መሬት ይዞታ እንዲያጡ የሚያደርጋቸው ስለሆነ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማገኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡ ከሚለው የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን በመሆኑ በአመልካች የቀረበው አቤቱታ የሕገ-መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ የውሳኔ ሐሳቡ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል የሚል ነው፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው የፍርድቤቱ ውሳኔ ተጠሪ ከአመልካች ላይ ለሃምሳ ዓመታት በኪራይ የእርሻ መሬት ተከራይቻለሁ በማለት የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ከሚደነገገው ውጪ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቼበታለሁ በማለቱ ብቻ ይዞታቸውን እንዲያጡ እና እንዲፈናቀሉ የሚያደርጋቸው ነው፡፡

በመሆኑም የጊምቦ ወረዳ ፍርድቤት በአመልካች ጉዳይ የሰጠው ውሳኔ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማገኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው ከሚለው የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ነው ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡



6

## ትዕዛዝ

በጊምቦ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠውና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገ መሆኑን እንዲያውቁት ለፍርድቤቶቹ የውሳኔው ግልባጭ እንዲደርሳቸው ይደረግ፡፡

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡

የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ፡፡



5

# የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣5ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ወ/ሮ ማሚቴ ሰብለ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሙሉ ጉርሙ

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን በሙሉ ወረዳ ፍርድቤት የነበረ የእርሻ መሬት ይዞታ ክርክር ሲሆን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.131212፣ መጋቢት 10 ቀን 2004ዓ.ም በዋለው ችሎት ለክርክሩ መነሻ የሆነው የመሬት ይዞታን አስመልክቶ የበታች ፍርድ ቤቶች የአሁኗ ተጠሪ ለአሁኗ አመልካች እንድትለቅላት በማለት የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የአሁኗ ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን መሬት ለአስራ ሁለት ዓመት ይዛ ስትጠቀምበት የነበረ በመሆኑ የአሁኗ አመልካች በዚህ የመሬት ይዞታ ላይ ክስ ለማቅረብ መብት የሌላት መሆኑን በመግለፅ ውሳኔ በመስጠቱ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ውሳኔ በማጽናቱ ነው፡፡

አመልካች ለፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረቡት የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መነሻነት አጣሪ ጉባኤው አቤቱታውን ተመልክቶ አመልካች ክርክር ያስነሳውን መሬት ልጃቸው እያረሰላቸው በጋራ ሲጠቀሙበት ቆይተው ልጃቸው ሲሞት የልጃቸው ሚስት የአሁን ተጠሪ በመሬቱ እንዳይጠቀሙ በመከልከሏ በተነሳ ክርክር የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይርጋን መሰረት አድርጎ አመልካች መሬቱን የመጠየቅ መብት የላቸውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በውሳኔውም አመልካች ተሸናፊ ሆነዋል በሚል ምክንያት ብቻ ከእርሻ መሬት እንዲፈናቀሉ መደረጉ ሕገመንግስቱ ከቆመለት ዓላማ ውጪ ነው በማለት የሕገመንግስቱን አንቀጽ 35/7/ በመጥቀስ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ

የአመልካችን ሕገመንግስታዊ መብት የሚጥስ በመሆኑ የሕገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት የውሳኔ ሀሳቡን ለምክርቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የምክርቤቱ የሕገመንግስት እና የክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ እና በምክርቤቱ ባለሙያዎች አስተያየት ላይ ከተወያየ በኃላ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክርቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ምክርቤቱም አቤቱታውን ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር በማጣመር መርምሯል፡፡እንደመረመረውም አንደኛ የአሁኗ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የመሬት ይዞታ ለአስራ ሁለት ዓመት ይዘው ሲጠቀሙበት የነበረው በባለይዞታነት መብት ነው ወይስ በሌላ መንገድ ሁለተኛ የአሁኗ አመልካችስ በዚህ የመሬት ይዞታ ሳይጠቀሙበት ቆይተው የባለይዞታነት መብት አቤቱታ ያቀረቡበት አግባብ አለ ወይስ የለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ አቤቱታውን ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ጭብጥ ማለትም የአሁኗ ተጠሪ ለክርክር መነሻ የሆነውን የመሬት ይዞታ ለአስራ ሁለት ዓመት ያህል ይዘው ሲጠቀሙበት የነበረው በምን አግባብ ነው የሚለውን በተመለከተ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የመሬት ይዞታ የአሁኗ አመልካች ከሟች ባለቤታቸው ጋር በመሆን በ1971 ዓ.ም ተሰጥቷቸው በጋራ ሲጠቀሙበት ቆይተው ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ መጀመሪያ ሌላ ሰው በኋላም የአሁኗ ተጠሪ ባለቤት የነበረው ሟች ልጃቸው መሬቱን እያረሰ ከመሬቱ ከሚገኘው ምርት እኩል እንዲያካፍላቸው በኦሮሚያ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 130/99 ዓንቀፅ 6/14/ በተደነገገው መሠረት በኪራይ መልክ ሰጥተውት በሞት እስኪለይ ድረስ እያረሰላቸው ሲጠቀሙበት እንደቆዩና በሞት ከተለየ በኋላ ግን ባለቤቱ የአሁኗ ተጠሪ የመሬት ይዞታውን አልለቅም ብለው እንደከለከሏቸው በስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ምክርቤቱ ተረድቷል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁኗ ተጠሪና ሟች ባለቤቷ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የመሬት ይዞታ ለአስራ ሁለት ዓመት ይዘው ሲጠቀሙበት የነበረው በባለይዞታነት መብት ሳይሆን በተከራይነት እንደሆነ ምክርቤቱ መረዳት ችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት



9

3

በሁለተኛ ደረጃ የተነሳውን ጭብጥ በተመለከተ የአሁኗ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የመሬት ይዞታቸውን የአሁኗ ተጠሪ ባለቤት ለነበረው ልጃቸው በኪራይ መልክ ሰጥተውት ከመሬቱ ከሚገኘው ምርት እኩሌታውን እየተቀበሉ ልጃቸው በሞት ተለይቶ ይህ ክርክር እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ በመሬት ይዞታቸው ሲጠቀሙበት እንደነበረ በስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአሁኗ አመልካች መሬቱን ለአስራ ሁለት ዓመታት በይዞታቸው አድርገው ሲጠቀሙበት እንደቆዩና መሬቱም ከሟች ባለቤታቸው ጋር ከተሰጣቸው ከ1971ዓ.ም ጀምሮ ክርክር እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ በይዞታ መብታቸው ስር የነበረ መሆኑን ምክርቤቱ ማረጋገጥና መረዳት ችሏል፡፡ የፌዴራሉንና የክልሉን ሕግጋተ-መንግስት እና የፌዴራሉን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ተከትሎ በወጣው በኦሮሚያ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀፅ 6/16/ መሰረት ደግሞ አንድ የመሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ በይዞታ የመጠቀም መብቱን የሚያጣው በመሬቱ ሳይጠቀምበት ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ የቆየ እና በራሱ ፈቃድ ይዞታውን የተወ እንደሆነ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክሩ መነሻ የሆነውና የአሁኗ ተጠሪ በሟች ባለቤታቸው አማካይነት በተከራይነት መብት በአጋጣሚ በእጃቸው የገባው የመሬት ይዞታ ላይ ሕጋዊ የመሬት ባለይዞታነት መብት እንዳላቸውና የአሁኗ አመልካች ግን ለአስራ ሁለት ዓመታት ያህል በመሬት ይዞታ መብታቸው ሳይጠቀሙበት እንደቆዩ በመቁጠር፣ የባለይዞታነት መብታቸውን እንዳጡና በሕግ መጠየቅ እንደማይችሉ በመግለጽ የሰጠውና የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያፀናው ውሳኔ አንደኛ፡- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገውን ማለትም የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው የሚለውን ድንጋጌ ሁለተኛ በአንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 7 ሴቶች በተለይ መሬትን በመጠቀም፣በማስተላለፍ፣በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው የሚለውን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ የሚቃረንና ተፈጻሚ መሆን የሌለበት ውሳኔ መሆኑን ምክርቤቱ አምኖበታል፡፡

በመሆኑም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ መብት የጣሰ በመሆኑ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1.በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ የመሬት ባለይዞታነት እና የተጠቃሚነት መብት የጣሰው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን አውቀው እንዲያስፈጽሙ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይተላለፍ።

2.የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታው አቅራቢዋ ይሰጥ።

# የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፤5ኛ ዓመት፤2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሚያዚያ 22 2010 ዓ.ም

አመልካች፡- እነ ከተፎ ገ/የስ /2 ሰዎች/

ተጠሪ፡- ወጣት በሱፍቃድ አየለ

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

አመልካቾች ዕድሚያቸው የገፋ በመሆኑና ጧሪ ስላስፈለጋቸው የይዞታ መሬታቸውን ታህሳስ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የስጦታ ውል ለተጠሪ ካስተላለፉለት በኋላ ተጠሪው ስጦታ አድራጊዎቹን ባለመጦሩ በዘመድ ቤት ተጠግተው እየኖሩ መገኘታቸውን ገልፀው የስጦታ ውሉ ፈራሽ ይሁንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀው ጉዳዩን ያዩት ፍርድ ቤቶች የስጦታ ውሉ አይፈርስም በማለት በመወሰናቸው አመልካቾች ውሳኔው ሕገ መንግስታዊ መብታችንን የሚቃረን ነው በማለት የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥ አቤቱታ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቅርበው ጉባኤው ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ ለመጨረሻ ውሳኔ ልኳል፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን አመልካቾች ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በሆኑበት በአማራ ብ/ክ/መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በእንሳሮ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የክሱ ፍሬ ሀሳብም አመልካቾች እድሜያቸው የገፋ በመሆኑና ጧሪ ስላስፈለገን ለተጠሪ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ባዋሳኝ የተጠቀሰውን ይዞታ መሬታችንን ታህሳስ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ውል በስጦታ ካስተላለፍንለት

በኃላ በስሙ የይዞታ ማረጋገጫ አውጥቶ እኛን ባለመጠሩ በዘመድ ቤት ተጠግተን እየኖርን ስለምንገኝ ስጦታው ፈራሽ ይሁንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ቀርበው መልስ እንዲሰጡ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በሰጡት መልስ ውሉ ከተደረገበት ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ከሁለት አመት በላይ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል መቃወሚያ እና ባማራጭ በሰጡት መልስ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ከግራ ቀኙ የቀረበለትን ክርክር ሰምቶ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 244 ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት በማድረግ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከፍተኛው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በይርጋ ሊታገድ አይገባም በማለት የወረዳው ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ማስረጃ በመስማት አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 341(1) መሠረት መዝገቡን መልሷል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት አከራክሮ አመልካቾች ለተጠሪው ያደረጉት የይዞታ መሬት ስጦታ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የሌለ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም፤ ተጠሪው በስጦታ ውሉ መሠረት እየተጠቀመ እስካሁን የሚያደርገውን እንክብካቤ ይቀጥል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካቾች በወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤትም ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ካከራከረ በኋላ ተጠሪ በራሱ መኖሪያ ቤት ተቀምጦ እያለ ጦሬያለሁ እየተንከባከብኩ ነው ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት አመልካቾች ያደረጉት የይዞታ መሬት ስጦታ ውል ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ በቅሬታቸውም በስር ፍ/ቤት ያቀረብኳቸው ምስክሮች አመልካቾችን እየጦርኩ እንዳለሁ በሚገባ አስረድተው እያለ የስጦታው

ውል ግዴታዬን እንዳልተወጣሁ ተቆጥሮ ፈራሽ ነው በሚል የተወሰነው ውሳኔ አግባብ ባለመሆኑ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል።

ጠቅላይ ፍ/ቤቱም የይግባኝ ቅሬታውን መርምሮ የከፍተኛው ፍ/ቤት የስጦታ ውሉ ፈራሽ ይሆናል በማለት የሰጠው ምክንያት አሳማኝ ነወይ? ይግባኝ ባይ የውል ግዴታውን አልተወጣም ከተባለ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉትን ነጥቦች ለማየት ያስቀርባል በማለት መልስ ሰጭዎች መልስ እንዲሰጡ አድርጓል።

በዚሁ መሠረት ተከራካሪ ወገኖች መልስ አቅርበው ፍ/ቤቱ ማስረጃ ከመረመረና የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ይግባኝ ባይ ስጦታ አድራጊዎችን እየጦረና እየተንከባከበ መሆኑን፣ ወደፊትም በዚሁ መልኩ ድጋፍ እንደሚያደርግ በስር ፍ/ቤት ባደረጉት ክርክር መጠቀሱን በመግለፅ በስጦታ ውሉ ውስጥ ግዴታ ያለው ከሆነ ማስገደድ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2462/1/ ላይ የተደነገገ መሆኑን በመግለፅ የስጦታ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፤ ይኸው ውሳኔ በአብክመ እና በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎቶች ፀንቷል።

አመልካቾች መጋቢት 22 ቀን 2008 ዓ.ም ፅፈው ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረቡት አቤቱታ በፍርድ ቤቶች የፀናው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ መብታችንን የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልን በማለት ጠይቀዋል።

የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔውም ጉዳዩን በጥልቀት ከመረመረ በኋላ አመልካቾች የመሬት ይዞታቸውን ሙሉ በሙሉ በስጦታ ውል ማስተላለፋቸው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 እና 4 የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ እንደሆነ፤ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት

ሆኖ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው የተከበረ መሆኑ በመግለፅ አመልካቾች የመሬት ይዞታቸውን ሙሉ ለሙሉ በስጦታ ወደ ተጠሪ እንዲተላለፍ እና ከይዞታቸው እንዲፈናቀሉ ያደረገው ውል ሊፈርስ አይገባም በማለት ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 እና 4 ጋር የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንገስት ትርጉም ያስፈልገዋል የሚል የውሳኔ ሀሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ ልኳል።

የሕገ መንግስት ትርጉማና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የፍ/ቤቶችን ውሳኔ፣ የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ እና የኢፌዴሪ ሕገ መንግስትን በማጣመር መርምሮታል።

እንደመረመረውም ተጠሪ የአመልካቾችን የመሬት ይዞታ በስጦታ ውል በህጋዊ መንገድ የተረከበ መሆኑን ተጠሪ አመልካቾችን በቅርብ በመሆን የማይጦራቸውና የማይንከባከባቸው በመሆኑ አመልካቾች የስጦታ ውሉ ይፍረስ በማለት ፍ/ቤቱን መጠየቃቸውን፣ ተጠሪ በበኩሉ የስጦታ ውሉ ላይ ለመጦርና ለመንከባከብ ግዴታ አልገባሁም በማለት በመከራከሩ ብቻ ፍርድ ቤቶች የስጦታ ውሉ እንዲፀና ውሳኔ መስጠታቸው አርሶ አደሮች ከመሬት ይዞታቸው ላይ አለአግባብ እንዲፈናቀሉ የሚያደርግ ውሳኔ መሆኑን አጣሪ ጉባኤው ተገንዝቦ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 እና 4 ጋር ይቃረናል ስለሆነም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

## ትዕዛዝ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ አግባብ አለመሆኑን ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ተቀባይነት

የለውም በማለት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲያውቁትና እንዲያስፈጽሙ ይድረሳቸው፡፡

2. የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የውሳኔ ሀሳብ ም/ቤቱ በሰጠው የሕገ መንግስት ትርጉም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን እንዲያውቁት ውሳኔው ይድረሳቸው፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካቾች ይድረሳቸው፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ 4ኛ ዓመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

<u>የመ/ቁ. 70/11</u>

አመልካች፡- አቶ አብዱራህማን ኡርጌሳ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሐሊማ ቶላ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዶዶታ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ የጉዳዩ ይዘትም የአመልካች ወላጅ እናትና አባት ሲሞቱ አመልካች የእንጀራ እናታቸው ከሆኑት ከተጠሪ ጋር ለክርክር ምክንያት በሆነው የገጠር ይዞታ መሬት ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ አብረው ሲጠቀሙ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን የእናትና አባታቸው መሬት ይዞታ ድርሻ እንዲያካፍሉአቸው ተጠሪን ጠይቀው ፍቃደኛ ስላልሆኑ በሕግ ተገደው እንዲያካፍሏቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም በሰጡት መልስ የአመልካች አባት እና እናት ከሞቱ 25 ዓመት እና 50 ዓመት መሆኑን አመልካችም እራሳቸው ስላልካዱ ከዚህ ጊዜ በኋላ የውርስ ይዞታ መሬት ለመጠየቅ አመልካች በይርጋ ይታገዳሉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካች ወላጅ እናትና አባት ሲሞቱ አመልካች የእንጀራ እናታቸው ከሆኑት ተጠሪ ጋር ለክርክር ምክንያት በሆነው የገጠር መሬት ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ አብረው ሲጠቀሙ ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን የውርስ ንብረት ማጣራት ሳይደረግ አመልካች ከተጠሪ ጋር በይዞታው እየተጠቀሙ መቆየታቸው የአመልካች አባት ከሞቱ ከ25 ዓመት እና እናታቸው ከሞቱ ከ50 ዓመት በኋላ ይህንን ይዞታ ለመካፈል ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ከመሆን ስለማያግደው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ባለመቅረባቸው የአመልካችን ክርክር በመስማት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት ወስኗል፡፡ ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም ሲሉ መዝገቡን ዘግተዋል፡፡

አመልካች ለአጣሪ ጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ ለክርክር መነሻ የሆነውን የቤተሰቦቼን የገጠር ይዞታ መሬት ከተጠሪ ጋር በጋራ ስንጠቀም ከቆየን በኋላ ተጠሪ ያለ ምንም ምክንያት ይዞታውን እንዳልጠቀም ስላደረጉኝ ክስ ባቀርብም በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶች ከሕግ ውጭ ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40(3) ጋር የሚጋጭ እና ከይዞታዬ ያፈናቀለኝ ስለሆነ ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤው የአመልካችን አቤቱታ ከፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ እና በንዑስ አጣሪ ጉባዔ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት በተደረገው ማጣራት ከተገኘው መረጃ እንዲሁም አመልካችና ምስክሮች በጉባኤው ስብሰባ ቀርበው ከሰጡት ቃል ጋር ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም ጉባኤው በሰጠው አቅጣጫ መሰረት በተደረገው ማጣራት የዶዶታ ወረዳ ገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በቁጥር WLBEN/675/9-1/2007 በቀን 26/10/2007 ዓ.ም ለወረዳው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ምላሽ እና በምክትል የወረዳው አስተዳደር እና የገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ ሰብሳቢነት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙና ሌሎች የሚመለከታቸው ወገኖች ተገኝተው የሰጡት ቃል እና ቃለ-ጉባኤ እንዲሁም የገጠር ይዞታ መሬት ማረጋገጫ ደብተር ተመልክተናል፡፡ እነዚህም ማስረጃዎች የሚያስረዱት ለክርክር ምክንያት የሆነው የገጠር ይዞታ መሬት የአመልካች ወላጆች ይዞታ እንደነበር ነው፡፡ የአመልካች ወላጅ እናት ቀድመው ሲሞቱ ወላጅ አባቱ ተጠሪን በማግባት በመሬቱ በመጠቀም አብረው እየኖሩ እርሳቸውም መሞታቸው ተረጋግጧል፡፡

የአመልካች ወላጆች ከሞቱ ረጅም ጊዜ እንደሆናቸው ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ ተጠሪም ባለቤታቸው የሆኑት የአመልካች አባት ከሞቱ በኋላ በ1996 ዓ.ም መሬቱን በስማቸው አስመዝግበው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዳወጡበት እና በዚህ ጊዜ አመልካች ደግሞ የቤተሰብ አባል ተብሎ መመዝገባቸውንም ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

በመሰረቱ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ 130/99 አንቀፅ 6 እና 9 መሰረት የገጠር መሬት የውርስ ጥያቄ ከሌላው ንብረት የውርስ ጥያቄ ይለያል፡፡ ለዚህም አንዱና ዋነኛው ምክንያት የመሬት ባለቤትነት መብት የሕዝብ እና የመንግስት በመሆኑ ግለሰብ በመሬት ላይ ያለው መብት በመሬት የመጠቀም መብት ብቻ መሆኑ ነው፡፡

ይህንኑ የሕገ መንግስቱን መርህ ለማስፈፀም በፌዴራልም ሆነ በክልል የወጡት ሕጎች ይህንኑ በመሬት የመጠቀም መብትን ብቻ መሰረት አድረገው የተቀረፁ ናቸው፡፡ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ እና ደንብ መሰረት የገጠር መሬት የውርስ ጥያቄ አውራሽ ከሞተ በኋላ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በግልፅ የደነገገው ጊዜ የለም፡፡ ከዚህ ባለፈ ወራሽ በሆነ እና ወራሽ ባልሆኑ ግለሰቦች መካከል በተለይም በይዞታው በጋራ አብረው ሲጠቀሙበት የነበሩ ሰዎች መካከል የውርስ ይዞታ መሬት ጥያቄን ለማቅረብ የይርጋ ጊዜ የሚያግድ ስለመሆኑ የሚደነግግ አንቀፅ የለም፡፡ ለመሬት ይዞታ የውርስ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የውርስ ጥያቄ አቤቱታዎች በተለይም ውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ በውርስ ንብረቱ በጋራ ሲጠቀሙ በነበሩ ሰዎች መካከል የይርጋ ተፈፃሚነት ስለመኖሩ የውርስ ሕጉም የሚደነግገው ነገር የለም፡፡ በተለይም በንብረቱ በጋራ ሲጠቀሙ ከነበሩ ግለሰቦች መካከል አንዱ ግለሰብ ሌላኛው ግለሰብ በንብረቱ እንዳይጠቀም እገዳ ሲያደርግበት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው አንደኛው ወገን በንብረቱ እንዳይጠቀም ከተከለከለበት ጊዜ አንስቶ በሚቆጠር የይርጋ ጊዜ ከሚሆን በቀር ወደ ኋላ ተመልሶ አውራሾች ከሞቱበት ጊዜ አንስቶ የይርጋ ጊዜ የሚቆጠርበት አግባብ አይኖርም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፍ/ቤት በነበረው ክርክርም ሆነ በጉባኤው በተደረገው ማጣራት እንዲሁም በጉባኤው ቀርበው ከተሰሙት ምስክሮች ማረጋገጥ እንደሚቻለው አመልካች ለክርክር ምክንያት በሆነው ይዞታ ክስ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ከተጠሪ ጋር በይዞታው አብረው ይጠቀሙ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም ያልካዱት ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች ሟች አባታቸው ከሞቱ በኋላ ከተጠሪ ጋር በይዞታው እየተጠቀሙ መኖራቸው የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ደግሞ አመልካች ይህን መብት ሊያገኙ የቻሉት ከላይ ከተጠቀሰው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ይህ ሕግ ያጎናፀፋቸውን መብት ለፍርድ ቤት አቅርበው የውርስ ሃብት እንዲጣራላቸው ወይም ክፍፍል እንዲደረግላቸው ባይጠይቁም በይዞታው ግን ለረዥም ጊዜ ሲጠቀሙ በመቆየታቸው ብቻ ከይርጋ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ነፃ እንደሚያደርጋቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ውስጥ አመልካች በቤተሰባቸው ይዞታ ረዥም ጊዜ ሲጠቀሙ እንደነበር ተጠሪ ራሳቸው ባልካዱበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች የገጠር መሬት ይዞታን ሲጠቀም በቆየ ሰው ላይ ይርጋን ተፈፃሚ ማድረጋቸው በተለይም የፍ/ሕ/አንቀፅ 1000(3)ን ተፈፃሚ ማድረጋቸውና ሟች ከሞተበት ጊዜ አንስቶ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ውርስ እንዲጣራ አመልካች ለፍርድ ቤት ማመልከት ነበረባቸው በሚል ምክንያት ጉዳዩን በይርጋ መዝጋታቸው ሕገ መንግስቱ ለአርሶ አደሮች ካደረገው ጥበቃና ይህንኑ ለማስፈፀም ከወጣው ከክልሉ ሕግ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

በመሰረቱ የይርጋ ደንብ ተፈፃሚ የሚሆነው ከፊታድ፣ ከውል ወይም ከሕግ ውጭ ግንኙነት ተይዞ በሚቆይበት ጊዜ እንጂ የንብረቱ ባለቤት በንብረቱ በጋራ እየተጠቀመ ከቆየና ፍቃዱ ባለበት ሁኔታ አይደለም፡፡ አንድ ሰው በይርጋ ምክንያት መብቱን የሚያጣው በንብረት መብቱ መጠቀም ሲያቆም እንጂ በንብረቱ እየተጠቀመ የቆየን ባለመብት ይርጋ የሚያግደው አይሆንም፡፡ ይህ መርህ ለሁሉም ንብረቶች ተፈፃሚነት ያለው ሲሆን ለመሬት ይዞታ የውርስ ክርክርም ተፈፃሚነት የሚያጣበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም በመሬት ይዞታ መብቱ ይጠቀም የነበረ ግለሰብ በይርጋ ምክንያት መብቱን ሊያጣ የሚችለው በይዞታው መጠቀም ሲያቆም እንጂ በመሬቱ እየተጠቀመ የቆየን ባለመብት ይርጋ የሚያግደው አይሆንም፡፡

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የይርጋ ድንጋጌ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳያርመው መቅረቱ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(4) ለአርሶ አደሮች የተረጋገጠው ከመሬት ይዞታ ያለመፈናቀል መብት ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

ስለዚህ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለሰበር አያስቀርብም ተብሎ የተዘጋው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰ/መ/ቁጥር 89385 ላይ በተመሳሳይ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ በትዕዛዝ የተዘጋው ይህ ጉዳይ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(4) ጋር የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባኤው ለፌደሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባኤውንና የምክር ቤቱ ባለሙያዎች የሰጡትን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውንና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት የአመልካቹን ሕገ መንግስታዊ መብት የሚቃረን መሆን አለመሆኑን በዝርዝር ለመመርመር

የአመልካቹን አቤቱታ፣የፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሁም በአጣሪ ጉባኤ በተጨማሪ የተደረገው የማጣራት ሥራ ተመልክቶ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የመሬት ይዞታ የአመልካች ወላጆች ይዞታ እንደነበርና የአመልካቹ ወላጅ እናት ቀድመው ሲሞቱ ወላጅ አባቱ ተጠሪን በማግባት በመሬቱ በመጠቀም አብረው እየኖሩ እሳቸው መሞታቸውን፣ተጠሪም በ1996ዓ.ም መሬቱን በስማቸው አስመዝግበው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዳወጡበትና በዚህ ጊዜ አመልካቹም የቤተሰብ አባል ተብለው መመዝገባቸው በፍ/ ቤቶች መረጋገጡን አጣሪ ጉባኤው ከተረዳ በኋላ የመሬት ባለቤትነት መብት የሕዝብና የመንግስት በመሆኑ ግለሰብ በመሬት ላይ ያለው መብት በመሬት የመጠቀም መብት ብቻ ሲሆን ይህም መርህ የሕገ መንግስቱ መርህ እንደመሆኑ መጠን በፌደራልም ሆነ በክልል የሚወጡ ማናቸውም ሕጎች የሕገ መንግስቱን መርህ በተከተለ አግባብ መቀረጽ አለባቸው ሲል ተችቶ በክልሉ የገጠሪ መሬት አዋጅ መሰረት የገጠር መሬት ውርስ ጥያቄ አውራሽ ከሞተ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በግልፅ የተደነገገ ጊዜ በሌለበት፣በይዞታው በጋራ ሲጠቀሙ የነበሩ ሰዎች መካከል የውርስ ይዞታ ጥያቄን ለማቅረብ የይርጋ ጊዜ የሚያግድ ስለመሆኑ የሚደነግግ አንቀጽ በሌለበትና አመልካቹ በቤተሰባቸው ይዞታ ረዥም ጊዜ ሲጠቀሙ እንደነበረ ተጠሪ ራሳቸው ባልካዱበት ሁኔታ ፍ/ቤቶች የገጠር መሬት ይዞታን ሲጠቀሙ በቆዩት አመልካች ላይ ይርጋን ተፈጻሚ ማድረጋቸው በሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 40 ላይ ተደንግጎ ለአርሶ አደሮች ከተረጋገጠው መብት ጋር የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባኤውና ቋሚ ኮሚቴው ያቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(4) ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና በየደረጃው ያሉ የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ይቃረናል በማለት ምክር ቤቱ የሻረው ስለሆነ ውሳኔውን አውቀው በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲጸሙ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካቹ ይሰጥ፡፡

# የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፤5ኛ ዓመት፤2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ወደሬ ታችበሌ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ልኬ ጉርሙ

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የዚህ አቤቱታ መነሻ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ሸዋ ዞን፣በሎሜ ወረዳ ፍርድቤት በአመልካችና ተጠሪዎች መካከል የነበረ የእርሻ መሬትና ሌሎች ንብረቶች ክርክር ሲሆን የአሁን አመልካች ባለቤታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አብረው ሲጠቀሙበት የነበረውን አስራ አራት ቀርጥ የእርሻ መሬት የሟች ልጆች እንዳይጠቀሙ በመከልከላቸው እንዲያካፍሏቸው ጠይቀው የወረዳው ፍርድቤትም እንዲካፈሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ውሳኔውም እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድቤት ደርሶ የጸና ቢሆንም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.117802 ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የመሬት ይዞታና ሌሎች ንብረቶችን አስመልክቶ የበታች ፍርድ ቤቶች የአሁኗ አመልካች፣ ተጠሪና የሟች የአቶ ማሙዬ ባደግ ልጆች እንዲከፋፈሉት የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በውሳኔውም የአሁኗ አመልካች ከሟች ከአቶ ማሙዬ ባደግ ጋር በጤና ችግር ምክንያት በስምምነት ተለያይተው አስራ ስምንት ዓመት ከቆዩ በኋላ ባለቤታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ሟች እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ በጋራ ባለይዞታነት የተመዘገቡበትንና እየተጠቀሙበት ያለን የመሬት ይዞታ በይርጋ ይታገዳል በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡አመልካችም ውሳኔው ከይዞታዬ እንድፈናቀል የሚያደርግ ስለሆነና በሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 የተደነገገውን ስለሚቃረን ሊታረምልኝ ይገባል በማለት ለፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አመልክተዋል፡፡

የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች አርሶ አደር ሆነው በአካባቢው እየኖሩና ሟች በሕይወት እያሉ ክርክር ካስነሳው መሬት ከሚገኝ ምርት በሟች ባለቤታቸው ቀለብ እየተሰፈረላቸው ሲጠቀሙ መቆየታቸውና ቋሚ መኖሪያቸው ከዚያው አካባቢ መሆኑ በግልጽ እየታወቀ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይርጋን መሰረት አድርጎ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ከእርሻ መሬታቸው እንዲፈናቀሉ መደረጉ ሕገመንግስቱ ከቆመለት ዓላማ ውጪ በመሆኑ ጉዳዩ የህገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት የውሳኔ ሀሳቡን ለምክርቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የምክርቤቱ የሕገመንግስት እና የክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ እና በምክርቤቱ ባለሙያዎች አስተያየት ላይ ከተወያየ በኃላ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክርቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ምክርቤቱም አቤቱታውን ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር በማጣመር መርምሯል፡፡እንደመረመረውም የአሁኗ አመልካች ባለቤታቸው ከነበሩት ሟች አቶ ማሙዬ ባደግ ጋር በሕመም ምክንያት ቢለያዩም በመሬት ይዞታ መብታቸው መጠቀማቸው ግን አልተቋረጠም ነበር፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የአሁኗ አመልካች አርሶ አደር ሆነው በአካባቢው እየኖሩና ሟች በህይወት እያሉ አሁን ክርክር ካስነሳው መሬት ላይ ከሚገኝ ምርት በሟች ባለቤታቸው አማካኝነት ቀለብ እየተሰፈረላቸው በመሬት ይዞታውም ሲጠቀሙና ቋሚ መኖሪያቸውም እዚያው መሆኑ በግልፅ ቢታወቅም ባለቤታቸው የነበሩት ሟች ከሞቱ በኂላ ግን የአሁኗ ተጠሪና ልጆቻቸው መሬቱንና ከመሬቱ ከሚገኘው ምርት እንዳይጠቀሙ እንደከለከሏቸው በስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ምክርቤቱ ተረድቷል፡፡በዚህም መሰረት ምክርቤቱ አቤቱታውን ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ካለው የኦሮሚያ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 6/16/ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደተመለከተው አንድ የመሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ የሆነ ሰው በይዞታ የመጠቀም መብቱን የሚያጣው በመሬቱ ሳይጠቀምበት ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ የቆየ ወይም በራሱ ፈቃድ ይዞታውን የተወ እንደሆነ መደንገጉን ተረድቷል፡፡ከዚህ ሁኔታ በመነሳት ምክርቤቱ የአሁኗ አመልካች ለክርክሩ መነሻ

በሆነው አስራ አራት ቀርጥ የእርሻ መሬት ይዞታ የመጠቀም መብታቸውን የሚያሳጣ ሁኔታ የተፈጠረ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

በጉዳዩ ላይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው እና የህጉ ድንጋጌ ይህ ሆኖ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አግባብነት የሌለውን ድርጋን መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የሰጠው እና የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም በማለት ያፀናው ውሳኔ በምክርቤቱ በኩል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፣እንዲሁም በአንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 7 ሴቶች በተለይ መሬትን በመጠቀም፣በማስተላለፍ፣በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው የሚለውን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡በሕገመንግስታችን አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተደነገገው ማናቸውም ሕግ፣ልማዳዊ አሰራር፣የመንግስት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከሕገመንግስቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

በመሆኑም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ መብት የጣሰ በመሆኑ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**ትዕዛዝ**

1.በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ የመሬት ባለይዞታነት እና የተጠቃሚነት መብት የሚጥስ በመሆኑ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን አውቀው እንዲያስፈጽሙ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡

2.የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታው አቅራቢ.ዋ ይሰጥ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት



6

11

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን

# 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ ደፋር አሰፋ

ተጠሪ፡- አቶ ድሪባ አያኔ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

## ውሳኔ

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ክርክርን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁን አመልካች ከሳሽ በመሆን በኦሮሚያ ክልል ኩዩ ወረዳ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ወላጅ አባቴ ከሞቱ ጀምሮ ከእንጀራ እናቴ ጋር ስጠቀምበት የነበረውን የቤተሰብ ይዞታ መሬት አዋሳኙን በመጥቀስ የእንጀራ እናቴ ወ/ሮ ጥሩ አያኔ በ2006 ዓ.ም ሲሞቱ ተጠሪ አላግባብ ስለያዙብኝ በህግ ተገደው እንዲመልሱልኝ በማለት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡

የአሁን ተጠሪም ባቀረቡት መልስ የሟች ወ/ሮ ጥሩ አያኔ ወንድም በመሆናቸው ሟችን እየደገፉ ይዘዋቸው የኖሩት እሳቸው መሆናቸውን፣ አመልካች ከሟች ጋር መሬቱን ይጠቀሙበት ያልነበረ መሆኑንና የሟችም ቤተሰብ ስላልሆኑ ይዞታው ለአመልካች አይገባም ብለው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ ከወረዳው መሬት አስተዳደር መረጃ እንዲሰጠው ጠይቆ በቀን 17/4/2008 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አመልካች ከ10 ዓመት በፊት በመሬቱ ይጠቀም እንደነበረና በቀን 3/05/ 2008 ዓ.ም በተጻፈ ሌላ ደብዳቤም መሬቱን ይጠቀምበት የነበረ መሆኑን ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ የክልሉን የመሬት አዋጅ ተከትሎ የወጣውን ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 32ን ጠቅሶ አመልካች አባታቸው ከሞተ 30 ዓመት ስለሆነውና በ12 ዓመት ጊዜ ውስጥ ባለመጠየቃቸው የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ወራሽ ባልሆነ ሰው እጅ ከ10 ዓመት በላይ የቆየ ንብረትን መጠየቅ እንደማይቻል የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ በመጥቀስ አመልካች የመሬት ይዞታው አይገባቸውም የሚል ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በቀን 19/11/2008 ዓ.ም በተጻፈ ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ባቀረቡት አቤቱታ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 128255 የሰጠው ውሳኔ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 40 ድንጋጌዎችን የሚቃረን በመሆኑ ትርጉም እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች የሟች አባታቸው እና የእንጀራ እናታቸው ይዞታ ከአባታቸው ሞት በኋላ በእንጀራ እናታቸው ስም ሆኖ የቆየ መሆኑን ጉባኤው ተረድቷል፡፡ አመልካች ለወረዳ ፍ/ቤቱና ለጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ መሬቱን ከአባታቸው ሞት በኋላ ከእንጀራ እናታቸው ጋር በጋራ ይጠቀሙ እንደነበር የገለጹ ሲሆን ፍ/ቤቱም መሬቱ ከሚገኝበት ወረዳ ካለው መሬት አስተዳደር ማስረጃ እንዲሰጠው ጠይቋል፡፡ መሬት አስተዳደሩ ለፍ/ቤቱ በላካቸው ሁለት ደብዳቤዎች አመልካች ከሟች እንጀራ እናታቸው ጋር በመሬቱ ይጠቀሙ የነበረ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በቀረበው የሰው ማስረጃ መሰረት ተጠሪ ሟችን እሳቸው ወደሚኖሩበት ሌላ ወረዳ ወስደው መሬቱን በሌላ ሰው እያሳረሱላቸው እስከሚሞቱ ድረስ ከእሳቸው ጋር ይኖሩ የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ጉባዔው ጉዳዩ በጽ/ቤቱ በኩል እንዲጣራ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲሰጠው የኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ኩዩ ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ተጠይቆ በቁጥር 1116/99135 በቀን 26/03/2010 ዓ.ም በላከው ደብዳቤ ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ሁለቱም አርሶ አደር መሆናቸውን፣ ይዞታውን ከሟች ጥሩ አያኔ ጋር በመሆን ሲጠቀሙ የነበሩት አመልካች መሆናቸውን በአካባቢው ካሉ ሰዎች ያረጋገጡ መሆኑንና ይዞታውን ክርክር ተጀምሮ እስከተወሰነበት ቀን 21/01/2007 ዓ.ም ድረስ በአመልካችና በሟች ጥሩ አያኔ እጅ የነበረ መሆኑን በመጥቀስ ማስረጃ ልኳል፡፡

አመልካች ከሟች የእንጀራ እናታቸው ጋር በመሆን በመሬት አስተዳደር ፖሊሲውና በክልሉ መሬት አዋጅ መሰረት በቀጥታ ከመሬቱ ሲጠቀሙ የነበረ መሆኑን ከዚህ የጽሁፍ ማስረጃ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ውሳኔ አመልካች የመሬቱ የቅርብና ቀጥተኛ ተጠቃሚ ሆነው እያለ ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ያልተያያዙ የይርጋ ጊዜና ሌሎች ምክንያቶች በመጥቀስ አመልካች ከይዞታቸው እንዲነቀሉ ተደርጓል፡፡

በአንድ የመሬት ይዞታ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ከሰው ማስረጃ ይልቅ የሰነድ ማስረጃ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከወረዳው መሬት አስተዳደር ለፍ/ቤቱ የተጻፉት ሁለት ደብዳቤዎች አመልካች ከመሬት ይዞታው ተጠቃሚ የነበሩ መሆኑን ስለሚጠቅሱ በክልሉ መሬት አዋጅ 130/99 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 10 እና አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረትም የሟች ወንድም ከሆነው ተጠሪ ይልቅ አመልካች ከሟቾች ጋር ጥገኛ በመሆን ከመሬቱ ይጠቀሙ ስለነበር ለሟች የቀረበ ቤተሰብ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሕግ በመሬት አጠቃቀም ዙሪያ ቅድሚያ የሚሰጠው በመሬቱ ተጠቃሚ የነበረን ሰው በመሆኑ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ ያነሳው የይርጋ ጉዳይ ከሰው ማስረጃ መነሻነት እንጂ የሰነድ ማስረጃን መሠረት አለማድረጉ ይርጋውም መሰረት ያደረገው መጠቀምን ሳይሆን የአመልካች አባት የሞቱበትን ጊዜ መሆኑ የውሳኔውን አግባብ አለመሆን ያሳያል፡፡ የተጠቀሰውም የይርጋ ጊዜ ሕገ መንግስታዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ይህ ውሳኔ አመልካችን ከይዞታ መሬታቸው የሚነቅልና የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ሲል ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ በኢ.ፌ.ዲ..ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአዋጅ ቁጥር 798 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ ጉዳዩ በሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ታይቶ እንዲቀርብ መርቶት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የአመልካች ወላጅ አባት አቶ አሰፋ ገመዳ በ1978 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ በመሆኑ የአሁን አመልካች ከእንጀራ እናታቸው ወ/ሮ ጥሩ አያኔ ጋር በመሆን ክርክር በተነሳባቸው የእርሻ መሬቶች በጋራ ሲጠቀሙ የቆዩ መሆኑ በቀጥታ ጉዳዩ ከሚመለከተው የወረዳው መሬት አስተዳደር በመረጋገጡ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 እና በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ቅድሚያ መሰጠት ያለበት በመሬቱ ሲጠቀሙ ለቆዩት ለአሁን አመልካች እንደሆነ እና ተጠሪው ደግሞ ሟች ወ/ሮ ጥሩ አያኔ እህታቸው በመሆናቸው ብቻ የእርሻ መሬቱ ለእኔ ይገባል በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ እንደሆነ ምክር ቤቱ ተገንዝቧል፡፡

ይሁንና ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በአመልካች ክርክር የተነሳበት የእርሻ መሬት በተጠሪ የተያዘው ያለአግባብ ስለሆነ እንዲለቁልኝ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት የቀረበውን ክስ በሚገባ ሳይመረምሩና ሳያጣሩ የአሁን ተጠሪ የእርሻ መሬቱን ሊለቁ አይገባም ሲሉ የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስቱን የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፌዴራል ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ ውሳኔው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ወስኗል፡፡

ትእዛዝ

1. በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ኩዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የጸናው ውሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም ሲል ምክር ቤቱ የወሰነ በመሆኑ ውሳኔውን አውቀው በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይተላለፍላቸው፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለባለጉዳዩ ይሰጥ፡፡
3. የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይላክ፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ 39/09

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አመልካች፡-** ወ/ሮ እናት በለጠ አድራሻ በአ/ብ/ክ/መ/ ምዕራብ ጐጃም ዞን ጃቢ ጠህናን ወረዳ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መብራት ቤዛ በአ/ብ/ክ/መ/ ምዕራብ ጐጃም ዞን ጃቢ ጠህናን ወረዳ፣

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ይመለከታል፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምዕራብ ጎጃም ዞን በጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ከሳሽነት ሲሆን የክሱ ይዘትም በአጭሩ ባለቤቴ እና የባለቤቴ እናት ሲሞቱ ተጠሪ ከሕግ ውጭ መሬቱን ስለያዘችብኝ ትልቀቅልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪም በበኩላቸው በይዞታው ላይ በቤተሰብ አባልነት የተመዘገብነው እኔ እና ልጆቼ ስለሆንን ይዞታውን የእኔ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት የወረዳውን አካባቢ ጥበቃ እና መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤትን አዟል፡፡ የአካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤትም በሰጠው ምላሽ በይዞታው ላይ በቁ. 4 (አራት) የሚሆኑ ሰዎች የተመዘገቡ ቢሆንም ስም ዝርዝራቸውን በሚመለከት በጽሕፈት ቤቱ በኩል ምንም ማስረጃ እንደሌለ ተገልጿል፡፡

ፍርድ ቤቱ ይህንን በማድረግ በስም ዝርዝር ያልተጠቀሱ አራት ሰዎችን ማንነት በተመለከተ በተጠሪ በኩል የቀረበ የሰው ምስክሮችን ከሰማ በኋላ በይዞታው ላይ የቤተሰብ አባል የሆኑት ተጠሪና ልጆቻቸው በመሆናቸው ይዞታውን ሊለቁ አይገባም በማለት

ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በይግባኝ ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡

አመልካች በወረዳው ዐቃቤ ሕግ አስወክለው እንደገና 10/02/2005 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በሀሰት ምስክሮች የተሰጠ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ይሻርልኝ በማለት ከወረዳው አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የተሰጠ ማስረጃ በመያዝ አመልክተው የጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍርድ ቤትም የቀድሞውን ውሳኔ በመሻር እንደገና አከራክሮ ይዞታው የአመልካች ነው ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ለምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ባይ በፍትሀ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.6 መሠረት መስፈርቱን ማሟላታቸውን ሳያስረዱ የቀድሞ ውሳኔ መሻሩ አግባብ አይደለም በማለት ለተጠሪ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፀንቷል፡፡ ጉዳዩን በሰበር ስልጣናቸው የቀረበላቸው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ መሠረታው የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ወስነዋል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የካቲት 5 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ ለጉባኤው ያቀረቡት ጥያቄ ከሟች ባለቤቴ እናት ጋር በ1989 ዓ.ም በተደረገው የመሬት ሽግሽግ በቤተሰብ አባልነት ተመዝግቤ እስከ 2001 ዓ.ም የተጠቀምንበትን መሬት የሟች ባለቤት እህት የሆነችው ተጠሪ ይዞታዬን ያለአግባብ ስለያዘች እንድትልቅልኝ በፍርድ ቤት ክስ ብመሰርትም ፍርድ ቤቶች ለተጠሪ ወስነዋል፡፡ ይህ ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(3) እና 40(4) በመጣስ ከይዞታዬ ያፈናቀለኝ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጠኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3) እና 40(4) በማጣመር ሲመረመር አከራካሪው ነጥብ በመሬት ሽግሽግ ወቅት በይዞታው ላይ በቤተሰብ አባልነት የተመዘገቡት አራት ሰዎች እነማን ናቸው? የጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍርድ ቤት እነዚህን አራት ሰዎች እነማን ናቸው? የሚለውን ፍሬ ነገር በሰው ምስክር አጣርቶ ለተጠሪ ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 መሠረት የቀድሞ ውሳኔ እንዲሻር ያቀረቡት ምክንያት ተጠሪ ቀድሞውኑ ያሰወሰኑት በሀሰት የምስክርነት ቃል እና የወረዳው የአካባቢ

ጥበቃ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አዲስ ማስረጃ ከማህበረሰቡ አግኝቻለሁ ያሉትን በመያዝ ሲሆን ይህንን አዲስ ማስረጃ መሠረት በማድረግ የዞኑና የወረዳ ፍርድ ቤት በድጋሚ ማስረጃዎችን ከመረመሩ በኋላ መሬቱ ለአመልካች ተወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ውሳኔው እንደተገለጸው ምስክሮቹ በሀሰተኛ ምስክርነታቸው በመወንጀል ያልተቀጡ በመሆናቸውና አዲስ ማስረጃ የቀረበው በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ የቤተሰብ አባልነትን አጣርቶ የመወሰን ስልጣን ያልተሰጠ አካል በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት  የቀድመው ውሳኔ የሚሻርበት ምክንያት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አጣሪ ጉባኤው ይህንን ጉዳይ መርምሮ ለመወሰን እንዲችል ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ አዋሳኙን በመጥቀስ ቀድሞ ይዞታው የማን እንደነበር? ማን ሲጠቀምበት እንደቆየና የአመልካችና ተጠሪ መተዳደሪያ ምን እንደሆነ? አመልካችና ተጠሪ አርሶ አደር መሆን አለመሆናቸውን፣ እንዲሁም የየግል የመሬት ይዞታ ያላቸው ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ተጣርቶ እንዲቀርብ ባዘዘው መሠረት በአማራ ክልል ምዕራብ ጐጃም ዞን ጃቢ ጠህናን ወረዳ የአካባቢ ጥበቃና መሬት አስተደደር ጽሕፈት ቤት መረጃ እንዲሰጥ ተጠይቋል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በምዕራብ ጐጃም አስተዳደር ዞን የፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር የግብርና አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የሥራ ሂደት የካቲት 24 ቀን 2009 ዓ.ም በቁ.097/13/2009 አንድ ገጽ ሽኚ ደብዳቤና አራት የጽሑፍ ማስረጃዎች ሰጥቷል፡፡

በዚሁ ማስረጃ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው አዋሳኝ የተጠቀሰው ይዞታ ቀድሞውኑ የአመልካች ባለቤት እናት የሆኑት የወ/ሮ አስላ ገ/እግዚእ ሲሆን ሲጠቀሙበት የቆዩትም ወ/ሮ አሰላ ገ/እግዚእ ከነቤተሰቦቻቸው መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ተጠሪዋ በ1989 ዓ.ም 20 በ25 የሆነ መሬት በራሷ ስም የተደለደለች መሆኑን፣ በ1989 ዓ.ም ከወ/ሮ አሰላ ገ/እግዚእ ጋር አሁን ክርክር ያነሳነው የገጠር መሬት ላይ በቤተሰብነት የተቆጠሩት ወ/ሮ እናት በለጠ ከሟች ባለቤታቸው እና ከልጆቻቸው ጋር መሆኑን አረጋግጧል፡፡

አመልካች በፍኖተ ሰላም ግብርና ጽሕፈት ቤት ለአካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር የሥራ ሂደት እና ለመልካም አስተዳደር ኮሚቴ በተሳሳተ ማስረጃ በተሰጠ ውሳኔ መሬቱን

ያለአግባብ ተነጠቅሁ በማለት በተደጋጋሚ በአመለከቱት መሠረት የዞኑ የመልካም አስተዳደር ኮማንድ ፖስት አቤቱታቸውን በማየት የቀረበውን አቤቱታ ወደ ቀበሌው ህዝብ ወርዶ ተጣርቶ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ለጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍትህ ጽሕፈት ቤት ቀርቦ ክስ እንዲመሠረትና መሬታቸውን በህግ ውሳኔ የሚመለስበት ሁኔታ እንዲመቻች የፍኖተ ሰላም ከተማ አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር አጠቃቀም የሥራ ሂደት ባለሙያዎችና የሚመለከታቸው አመራሮች ወደ ቀበሌው ወርደው መረጃውን አጣርተው እንዲያቀርቡ በማለት ትዕዛዝ አስተላልፎ የምዕራብ ጐጃም ዞን የመልካም አስተዳደር ኮሚቴ 07/11/2007 ዓ.ም 7 አባላት ያሉት ኮሚቴ ቀበሌ ወርዶ በርካታ ህዝብ ከአወያየ በኋላ በ1989 ዓ.ም አዋሳኙ የተጠቀሰውን መሬት አመልካች በቤተሰብ አባልነት የተቆጠሩና በኋላም የተመሩት ወ/ሮ እናት በለጠ እና ቤተሰቦቻቸው እንጂ ተጠሪ በወቅቱ ራሷን ችላ የምትኖር በራሷ መሬት የተመራች መሆኑን በህዝቡ በማረጋገጥ ነገር ግን ይህንን ጉዳይ ህጋዊ አድርጎ ወደህግ አካል ለማቅረብ እና ለመከራከር መረጃው ህዝብ በተገኘበት ተጣርቶ ለሚመለከተው የህግ አካል ቀርቦ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዲመቻች ለፍ/ሰላም አስተዳደር ግብርና ጽሕፈት ቤት ደብዳቤ ተጽፎላቸው መረጃው እንዲጣራ በማለት ልዩነት በሌለው ድምጽ የወሰነበትን ሰነድ ልኳል፡፡

በዚሁ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት እያረሱ ሲጠቀሙበት የነበሩት እንዲሁም ይዞታው ላይ የተቆጠሩት ወ/ሮ እናት በለጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም የራሷ 20*25 የሆነ መሬት በራሷ መደልደሏ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም በቁ.በአ2734/04/09 በቀን 24/06/2009 በአ.ብ.ክ.መ ምዕራብ ጎጃም ዞን በፍኖተሰላም ከተማ አስተዳደር የባህል አባጥር የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በሰጠው ምላሽ አመልካችና ተጠሪ አርሶ አደር መሆናቸውን አረጋግጦ ጽፏል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3-4) መሠረት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የመንግሥትና የህዝብ መሆኑ በተደነገገው መሠረት የክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ሕጎች የገጠር መሬት ይዞታ የሚተላለፍባቸው ሁኔታዎች ደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከባለቤታቸው እና ከባለቤታቸው እናት ከወ/ሮ አስላ ገ/እግዚ ጋር በባለቤትነት የተቆጠሩት ለመሆናቸው የዞኑ የአካ/ጥ/ የመሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በሰጠው ማስረጃ የሚያረጋግጥ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ በ1989 ዓ.ም አመልካችና ቤተሰባቸው አርሶ

አደር መሆናቸውና መሬቱን ሲጠቀሙበት እንደነበረ ተረጋግጦ በፍርድ ቤት የሰው ማስረጃ በመስማት ብቻ የሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ከመሬት ያለመነቀል ሕገ መንግሥታዊ መብት ይቃረናል፡፡

ስለዚህ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

13

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ አምስተኛ ዓመት አንደኛ መደበኛ ስብሰባ

መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ.ቁ. 51/10

አመልካች፡- ወ/ሮ በሰጡ ባሩዳ

ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ሮ ወይንሸት ኃይሌ (6 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

አመልካች መጋቢት 9 ቀን 2007 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ 125263 የሰጠውና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የጸናው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/4/ ከእርሻ መሬቴ ያለመነቀል መብቴን የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ የሚች አባታችን አቶ ኃይሌ ከበደ ልጆችና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች በመሆናችን የአሁን አመልካች ይዘው የሚገኙትን የተለያዩ ንብረቶችና የመሬት ይዞታ የአባታችን ድርሻ ያካፍሉን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በውርስ አጣሪው በቀረበለት ሪፖርት መሠረት ሁለት ቆርቆሮ ቤቶችን፣ ሁለት የሳር ቤቶችን፣ አንድ የከብቶች መኖ ማስቀመጫ ቤትን፣ 3647 በማሳው ላይ ያሉ ተክሎች እና አመልካች 298 ባህርዛፎችን ቆርጠው ስለተጠቀሙበት የተቀረጠው በገንዘብ ሲሰላ 52150 /ሃምሳ ሁለት ሺ አንድ መቶ ሃምሳ/ ብር የሚያወጣ፣ 413 ተክሎች፣ ፣ አንድ ላም፣ አንድ ወይፈንና አንድ በሬ፣ ሁለት ሄክታር የእርሻ መሬት፣ 7 ኩንታል ገብስ፣ 4.5 ኩንታል ባቄላ፣ 3.5 ኩንታል አተር በገንዘብ ሲገመት ብር 10,025.00 (አስር ሺ ሃያ አምስት ብር) የአሁን ተጠሪዎች የሚችን ድርሻ አመልካች ከወለዱት ሕፃን መረከብ ሀይሌ ጋር እኩል እንዲካፈሉ እንዲሁም ግማሹን የሚች ሚስቶች የነበሩት የአሁን አመልካች እና ወ/ሮ ንጋቷ ፍቃዱ እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

የአመልካች ዋና ቅሬታ ተጠሪዎች የአ/አ ከተማ ነዋሪ በመሆናቸዉ በመሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ. 89/89 አንቀጽ 2 መሰረት የይዞታ ባለመብቱን ገቢ በመጋራት በቋሚነት አብረው የሚኖሩ ባለመሆናቸዉ እንዲሁም እኔ የመሬት ይዞታውን በራሴ በአርሶ አደርነት ተመዝግቤ ያገኘሁት በመሆኑ ውሳኔው ከመሬት ይዞታዬ እንድፈናቀል የሚያደርገኝ ነው የሚል ነው፡፡

የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የመሬት ይዞታውን በተመለከተ ከሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ተጨማሪ ማጣራት እንዲደረግ ባዘዘው መሠረት ጉዳዩ በጉባኤው ጽ/ቤት እንዲጣራ ተደርጓል፡፡ እንደተጣራውም በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የሰንዴ ሶዶ ወረዳ ገጠር መሬት እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት፡-

በሰጠው መረጃ መሠረት የአሁን ተጠሪዎች የመሬት ይዞታው የሚገኝበት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ የማይኖሩና አድራሻቸው እንደማይታወቅ እና አመልካች ወ/ሮ በሰጡ ባሩዳ አሁን ክርክር ከተነሳበት መሬት ይዞታ ውጪ ሌላ በራሳቸው ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ እንደሌላቸው እንዲሁም ቀበሌ ገበሬ ማህበሩ በቀን 26/07/2010 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አመልካቿ ሌላ የመሬት ይዞታ የሌላቸው መሆኑን አረጋግጧል፡፡

አመልካች እንደተጨማሪ ማስረጃ የተጠሪዎችን አድራሻ የሚገልጽ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ለፍርድ አፈፃፀም ያመለከቱት አንድ ገጽ ማመልከቻ ግልባጭ የፍ/ቤት ማህተም ያረፈበት አቅርበው የ1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ ወይንሸት ኃይሌ አድራሻ አሜሪካ፣ የ2ኛ ተጠሪ ወ/ሮ ፍቅርተ ኃይሌ ካናዳ፣ የ3ኛ ተጠሪ ወ/ሮ አስቴር አ.አ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ ከተማ የ4ኛ ተጠሪ ወሪ/ት እጥፍወርቅ ኃይሌ አ.አ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ የ5ኛ ተጠሪ ወጣት ጌታቸው ኃይሌ ካናዳ የ6ኛ ተጠሪ መቅደላዊት ኃይሌ ካናዳ የሚል አቅርበው ከአቤቱታቸው ጋር አያይዘዋል፡፡

ጉባኤው ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻለው የአሁን ተጠሪዎች የሟች ኃይሌ ከበደ ልጆች እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸዉ ተረጋግጧል፡፡ ከመሬት ይዞታ ውጪ ያሉ ሌሎች ንብረቶችን ተጠሪዎች የአባታቸዉን ድርሻ እንዲካፈሉ መወሰኑ በሕግ አግባብ በመሆኑ ከሕገ መንግስቱ ጋር ይቃረናል የሚባልበት ምክንያት አይኖርም፡፡

የመሬት ይዞታውን በተመለከተ አመልካች በአቤቱታቸው ላይ እንደገለፁት የአሁን ተጠሪዎች በአዲስ አበባ ከተማ ሲኖሩ የነበሩና ከሌላ እናት የተወለዱ ሆነው ከመሬት ይዞታው ሲጠቀሙ እንዳልነበሩና የከተማ ነዋሪ በመሆናቸው በኦሮሚያ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ

መሠረት የእርሻ መሬቱ እንደሌላ ንብረት ተቆጥሮና በውርስ ንብረት ውስጥ ተካትቶ ለተጠሪዎች ሊከፋፈል የሚችል አይደለም የሚል ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ተጠሪዎች የመሬት ይዞታው የሚገኝበት ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ ነዋሪ እንዳልሆኑና የአሁን አመልካችም አሁን ክርክር ከተነሳበት የመሬት ይዞታ ውጪ ሌላ በራሳቸው ስም የተመዘገበ መሬት እንደሌላቸው የወረዳው የመሬት አስተዳደር አረጋግጧል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው የተከበረ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ አመልካች ከሟች ባለቤታቸው ጋር የነበራቸው የመሬት ይዞታ ሁለት ሄክታር ሲሆን ይህንን ሁለት ሄክታር የመሬት ይዞታ በሌላ ገቢ በሚተዳደሩና ከመሬቱ ተጠቃሚ ካልሆኑ ተጠሪዎች ጋር ይካፈሉ ማለት አመልካችን ከእርሻ መሬት ከማፈናቀል ያላነሰ ውሳኔ ነው፡፡

ስለዚህ በጉዳዩ ላይ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት የአሁን ተጠሪዎች በእርሻ ስራ የማይተዳደሩና የከተማ ነዋሪ ስለሆኑ በመሬቱ ሲጠቀሙ የነበሩ ባለመሆኑ በኦሮሚያ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሠረት የእርሻ መሬቱ እንደሌላ ንብረት በውርስ ንብረት ውስጥ ተካትቶ ለተጠሪዎች ሊከፋፈል የሚችል ባለመሆኑ በፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሕገመንግስቱን አንቀጽ 40/4/ ድንጋጌን ስለሚቃረን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9/1 መሰረት ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የእርሻ መሬቱን በተመለከተ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ተወስኖ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የፌዴራሉ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የምክር ቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

## 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ ዓመት 2ኛ መደበኛ ጉባኤ

ሰኔ/2013 ዓ.ም

የመዝገብ ቁጥር 100/13

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘመድ ዋጋው

ተጠሪዎች፡- እን አቶ ሀብታሙ ዋጋው (4 ሰዎች)

የኢፌዴሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል።

ውሳኔ፤

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን መስከረም 20 ቀን 2010 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው። የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.144043 በቀን 27/10/2009 ዓ.ም ያፀናው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው።

ክርክሩ የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግሥት ላስታ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በመሠረቱት ክስ ሲሆን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል። የክሱ ይዘትም በአጭሩ ከአያቶቼ ሟች አቶ ዋጋው ተፈራ እና ጎዳዳ በራቸው ጋር አብሬ ያደግኩና የቤተሰብ አባል ሆኜ ስኖር ነበር። በትዳር ምክንያት ከሄድኩ በኋላም ቢሆን ከባለቤቴ ጋር የአያቶቼን መሬት እየተጠቀምኩ እኖር ነበር።

ከባለቤቴ ጋር ከተለያየን በኋላ በላሊበላ ከተማ በመኖር ላይ እያለሁ ወንድ አያቴ በ2004 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ እና የቤተሰብ አባል በመሆኔ ተከሳሾች የውርስ መሬቱን እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው። የአሁን





ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን በሰጡት መልስ አመልካች የሟቾች የቤተሰብ አባል አይደሉም። በ1997 ዓ.ም በቤተሰብ አባልነት ያለተመዘገቡና በትዳር ምክንያት ሲሄዱ ሁለት ጥማድ መሬት የተሰጣቸው ስለሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት ጠይቀዋል።

የግራ ቀኙን የሰማው የወረዳው ፍ/ቤትም አመልካች የሟቾች የቤተሰብ አባል መሆናቸው እና ሌላ መሬት የሌላቸው መሆኑን ስለተረጋገጠ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ11 /7/ (ለ) መሠረት ከተጠሪዎች ቅድሚያ መብት ያላቸው ስለሆነ መሬቱን ለመውረስ መብት ያላቸው አመልካች እንጂ ተጠሪዎች አይደሉም በማለት ተጠሪዎች የያዙትን መሬት ለአመልካች እንዲለቁ ወስኗል።

በጉዳዩ ላይ ተጠሪዎችም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም።

ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበለት የአ/ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 2/6/ መሠረት የተሰጠው ትርጉም ከመሬት ባለይዞታው ጋር በቋሚነት የሚኖር የራሱ የሆነ ቋሚ መተዳደሪያ የሌለው፣ የይዞታ ባለመብቱን አርሶ አደር ገቢ በመጋራት የሚተዳደር ስለመሆኑ ይደነግጋል። ነገር ግን አመልካች ባል አግብተው በመሄዳቸው በአዋጁ መሠረት ከቤተሰብ አባልነት አስተዳደር የተቋረጠ ከመሆኑም በላይ ሟቾች ጎጆ መውጫ በሚል መሬት የሰጧቸው ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አመልካች የመሬት ይዞታውን ለመውረስ መብት የላቸውም በማለት ወስኗል።

በመጨረሻም ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ በጉዳዩ ላይ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ተዘግቷል።

በዚሁ ውሳኔ መነሻነት አመልካች ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ ከሟች አያቶቹ ጋር የቤተሰብ አባል ሆኜ መመዝገቢ በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለና በትዳር ምክንያት ከሄድኩ በኋላ ከመሬቱ በሚገኝ ገቢ እንተዳደር ነበር። እንዲሁም በስጦታ መሬት አገኘች የተባለውም ፍ/ቤቶች ይህ እውነት መሆኑን ሳያረጋግጡ በመወሰናቸው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ስር የተረጋገጠውን ከመሬት ይዞታ አለመፈናቀል መብቱ ስለተጣሰ በጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል።

ጉባኤው ጉዳዩን መርምሮ የፍ/ቤት ውሳኔው የአመልካችን ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

በግራ ቀኙ መካከል በነበረው ክርክር አመልካች ከሟች አያታቸው ጋር የቤተሰብ አባል ሆነው ይኖሩ እንደነበር በፍ/ቤቶች ተረጋግጧል። በ1999 ዓ.ም በተደረገው የአርሶ አደሮች የይዞታ ምዝገባ ሰነድ ላይም አመልካች የቤተሰብ አባል ሆነው መመዝገባቸው ተረጋግጧል። የስር ፍ/ቤቶች ይህንን መሠረት በማድረግ አመልካች በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሠረት የቤተሰብ አባል መሆናቸው ስለተረጋገጠ ለክርክር ምክንያት የሆነውን የሟች አያታቸውን ይዞታ መውረስ ይችላሉ የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል።

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ውሳኔ ቀይሮታል። ፍ/ቤቱ ውሳኔውን የቀየረበት ዋናው ነጥብ አመልካች በጋብቻ ምክንያት ከሟች አያታቸው ዘንድ ተለይተው ስለሄዱ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና





አጠቃቀም አዋጅ መሠረት የቤተሰብ አባል የሚለውን መስፈርት አያሟሉም በሚል ምክንያት ነው።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34/1/ መሠረት በሕግ ለተወሰነው የጋብቻ እድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት መብት አላቸው ተብሎ ተደንግጓል።

ከዚህ በተጨማሪ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 35/7/ መሠረት ደግሞ ሴቶች ንብረት በማፍራት፣ በማስተዳደር፣ በመቆጣጠር፣ በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች እኩል መብት አላቸው ተብሎ ተደንግጓል።

ከነዚህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ሴቶች ጋብቻን የመመሥረትና መሬትን በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑን ነው። ሴቶች ይህንን ሕገ መንግሥታዊ መብት በመጠቀም ረገድ ገደብ የሚጥልባቸው ሕጎችም ሆነ አሠራሮች እንዲሁም ባህሎች ተፈጻሚነት ሊኖራቸው አይገባም። ስለሆነም እነዚህን ጉዳዮች የሚመለከቱ ማናቸውም ሕጎች ሲወጡ ሆነ ሕጎቹ ተግባራዊ ሲደረጉ እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ተግባራዊ በሚያደርግ መልኩ መተርጎምና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል።

የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በሚመለከት የፌዴራል መንግሥትም ሆነ የክልል መንግሥታት ሕግ አውጥተው ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በነዚህ ሕጎች ከሚገዙት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የገጠር መሬት በውርስ ስለሚገኝበት ሁኔታ ነው።

አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው የአ/ብ/ክ/መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 2/6/ የገጠር

መሬት በውርስ የሚተላለፈው ለቤተሰብ አባል ብቻ ሲሆን በአዋጁ ድንጋጌ መሠረት የቤተሰብ አባል ማለት ከመሬት ባለ ይዞታው ጋር በቋሚነት የሚኖር የራሱ የሆነ ቋሚ መተዳደሪያ የሌለው ሰው፣ ይዞታ ባለመብቱን አርሶ አደር ገቢ በመጋራት የሚተዳደር እንደሆነ ተደንግጓል።

በሕጉ ድንጋጌ ላይ በመሠረታዊነት ሕግ ሊያሳካ ያሰበው ዓላማ በግጠር በአርሶ አደርነት የሚተዳደሩና ከባለይዞታው ጋር በቋሚነት የሚኖሩ ሰዎች ሌላ ገቢ ስለሌላቸው የይዞታው ባለቤት በሚሞትበት ጊዜ በዚህ መሬት መጠቀማቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግና ሌላ ገቢ ያለው ሰው ገቢ የሌላቸውን አርሶ አደሮች ከይዞታው እንዳያፈናቅል ለመከላከል ነው። ከባለይዞታው ጋር ገቢ በመጋራት ይኖር የነበረ ሰው ይህንን መብት እንዲጎናፀፍ ሕጉ ሲያስቀምጥ ሌሎች ማኅበራዊ ኑሮዎቹን በሚጎዳ መልኩ ከባለ ይዞታው በአካል እንዳይለይ ሳይሆን ከይዞታው በሚገኝ ገቢ እየተዳደረ መሆኑን መሠረት በማድረግ ነው።

አንድ የቤተሰብ አባል የሆነ ሰው ከባለይዞታው በአካል ወይም በትዳር ምክንያት ቢለይም ሌላ የመተዳደሪያ ገቢ የሌለውና ከባለይዞታው በሚገኝ ገቢ የሚኖር ከሆነ በሕጉ የተደነገገውን የቤተሰብ አባል ትርጉም አያሟላም ማለት አይቻልም። የቤተሰብ አባልነትና በቤተሰብ መካከል የሚኖረው መረዳዳት ወይም ጥገኝነት ትዳር በመያዝ የማይቋረጥ ማኅበራዊ መስተጋብር መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

በአብዛኛው የሀገራችን የኅብረተሰብ ባህል ሴቶች ሲያገቡ የሚኖሩት ባላቸው በሚመርጥላቸው መኖሪያ አካባቢ ነው። ያገቡ ሴቶች በተለይም አርሶ አደር አካባቢ ከባላቸው ጋር የመሄድና ከቤተሰቦቻቸው የመለየት ባህልና ልምድ አለ። በተቃራኒው ወንዶች ሲያገቡ ሚስታቸውን ይዘው በቤተሰቦቻቸው አካባቢ የመኖርና በአብዛኛውም የቤተሰቦቻቸውን የእርሻ መሬት በመውሰድ በዚያ የመተዳደር ልምድ ስለመኖሩ የታወቀ ነው። ለምሳሌ የአርሶ አደር ሴት





ልጅ ስታገባ አካባቢዋን በመልቀቅ ወደ ባሏ መኖሪያ አካባቢ የመሄድና ወንዱ ሲያገባ ደግሞ ሚስቱን ይዞ በመምጣት በቤተሰቦቹ አካባቢ የመኖር ባህልና ልምድ አለ።

አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀድሞ የቤተሰብ አባል የነበሩ መሆኑ ተረጋግጧል። አመልካች ባል አግብተው ከአካባቢው ቢሄዱም በነበሩበት አካባቢም ከሟች አያታቸው ይዞታ ከሚገኝ ገቢ ይተዳደሩ እንደነበር ተከራክረዋል። ከዚህ ባለፈም አመልካች ትዳራቸው በ2004 ዓ.ም የፈረሰ መሆኑን ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል።

አንድ ሰው በትዳርም ይሁን በሌላ ምክንያት ከቤተሰብ ዘንድ ርቆ የነበረ ቢሆንም ሌላ ጊዜ ተመልሶ ከቤተሰቦቹ ጋር እንዳይኖር የሚከለክል ሕግ የለም። አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ባል አግብተው መሄዳቸው በራሱ ከቤተሰብ አባልነት ሊያፈናቅላቸው አይገባም። በተጨማሪም አመልካች ባል አግብተው ከሄዱ በኋላ ትዳራቸው በመፍረሱ ተመልሰው ከሟች ይዞታ ገቢ በመጋራት ይተዳደሩ እንደነበር ያቀረቡትን ክርክር ፍ/ቤቶች ሳያረጋግጡና አንድ ጊዜ በትዳር ምክንያት ከቤተሰቡ በአካል የተለየ ሰው ተመልሶ የቤተሰቡ አባል መሆን እንደማይችል በሚመስል መልኩ በፍ/ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ በመርህ ደረጃ የተሳሳተ ነው።

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ባል አግብተው ስለሄዱ ብቻ ከቤተሰብ አባልነት ውጪ ሆነዋል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የአርሶ አደር ሴቶች የትዳር ሁኔታን ያላገናዘበና ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃውን ወደ ጎን የተወ ነው። አመልካች አሁን ያሉበት ሁኔታ ከግምት ያላስገባና ትዳራቸው ከፈረሰ በኋላ እንኳን ተመልሰው በጥገኝነት መኖራቸው ሳይረጋገጥ አግብተው ስለነበር ብቻ የቤተሰብ አባልነት መስፈርት አያሟሉም መባሉ አግባብነት ያለው አይደለም።

ስለሆነም ከላይ በተገለጸው አግባብ አመልካች ሴት አርሶ አደር መሆናቸው እና የሟች የቤተሰብ አባል የነበሩ መሆኑ አግብተው በመኖራቸው ብቻ ከቤተሰብ አባልነት ውጪ ናቸው በማለት ከውርስ ውጭ እንዲሆኑ በፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥቱ ለሴቶችና ለጋብቻ ያስቀመጠውን መርህ የሚጥስ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል::

ስለሆነም 1ኛ. በአ/ብ ክ/ መንግሥት ላስታ ወረዳ ፍ/ቤት ተጀምሮ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 144043 ላይ የፀናው ውሳኔ ኢሕገመንግሥታዊ ስለሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ9/1/ መሠረት ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ፣

2ኛ. የአ/ብ ክ/ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በጋብቻ ምክንያት ከሟች አያታቸው ዘንድ ስለሄዱ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሠረት የቤተሰብ አባል የሚለውን አያሟሉም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ኢሕገመንግሥታዊ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን እንደገና በማየት በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ መሠረት አመልካች የቤተሰብ አባል ለመሆን ሌሎች ሕጋዊ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆን አለመሆናቸውን በማረጋገጥ አግባብነት ያለው ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ84/1/ መሠረት ይህን የውሳኔ ሃሳብ በሙሉ ድምጽ አቅርቧል።

ስለሆነም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ በጥልቀት እና በስፋት መርምሮ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ አግባብ መሆኑን ተቀብሎ በሙሉ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል።

16

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ አመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የፋ/ቁ.74/11

አመልካች፡- አቶ ታዬ ዳብሱ

አድራሻ ፡- ኦሮሚያ ብ/ክ/መ ምእራብ ሸዋ ዞን ጀልዱ ወረዳ

ተጠሪ፡- ሳጅን ተስፋዬ ታዬ

አድራሻ ፡- ኦሮሚያ ብ/ክ/መ ምእራብ ሸዋ ዞን ጀልዱ ወረዳ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 15 ቀን 2008 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩም የገጠር መሬት ይዞታ ክርክርን ይመለከታል፡፡

የጉዳዩ ፍሬ ሀሳብ ከሣሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ ለጀልዱ ወረዳ ፍ/ቤት በቀን 22/12/2005 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ አመልካች እና እናቴ ወ/ሮ ብርቄ ገመቹ ባል እና ሚስት የነበሩ ሲሆን እናቴ በ1983 ዓ.ም ሲሞቱ አመልካች እጅ የነበረ በጀልዱ ወረዳ በቱሉ ቡለቱማ መንደ ተብሎ በሚታወቀውና 4 በተለያዩ ቦታዎች የሚገኝ በጠቅላላው 2.4555 ሄክታር የሚሆን መሬት አመልካች የእናቴን ድርሻ በቀን 15/01/1995 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል የሰጡኝ ሲሆን መሬቱን ተካፍዬ በእጄ እያለ አመልካች ከ14/08/2005 ዓ.ም ጀምሮ በጉልበት ስለያዙብኝ እንዲለቁልኝ በማለት ክሳቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካችም በሰጡት መልስ ለተጠሪ አካፍዬ የሰጠሁት የመሬት ይዞታ የለም፣ የመሬት ስጦታ ውል የሀሰት ውል ስለሆነ ፎርማዩ ይመርመርልኝ፣ ውል የለም እንጂ ቢኖር እንኳን ህግን የሚቃረን ውል ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፣ የተጠሪ እናት ወ/ሮ ብርቄ ገመቹ ሳይሆኑ ወ/ሮ እልፌ ቱራ ናቸው፣ ተጠሪ የስጋ ዝምድና ወይም የቤተሰብ አባል ባለመሆናቸው ሊካፈሉ አይችሉም፡፡ ይዞታው በደርግ ጊዜ የተሰጠኝ ሲሆን ከእጄ ወጥቶ የማያውቅ በመሆኑ የተጠሪ ክስ ውድቅ እንዲሆንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የጀልዱ ወረዳ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ የቤተሰብ አባል እንዳልነበረ፣ ከሟች ወ/ሮ ብርቄ ገመቹ እና ከአመልካችም የማይወለድ መሆኑ እንዲሁም ሕጋዊ የሆነ ጉዲፈቻ የሌለ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ፣ አመልካች እና ተጠሪ በ15/01/1995 የተፈራረሙት የስጦታ ውል የማይንቀሳቀስ ንብረት በሆነው የመሬት ይዞታ ላይ ሆኖ ነገር ግን ሕጉ በሚያስቀምጠው መሰረት የተፈራረሙት ውል ሳይሆን የውል ረቂቅ ሆኖ ከኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ጋር የሚቃረን ስለሆነ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታውን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካች የተጠሪን የውርስ ድርሻ በ15/01/1995 ዓ.ም በተደረገ ውል ለተጠሪ ሰጥቶት እንደነገና በ2005 ዓ.ም በጉልበት መሬቱን ይዟል ወይስ አልያዘም የሚለውና ሌሎች ነጥቦችን በመለየት ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለወረዳ ፍ/ቤት በመመሪያ መልሶታል፡፡

አመልካችም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመመሪያ ወደ ወረዳ ፍ/ቤት በመመለስ የወሰነውን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ከጀልዱ ወረዳ የመሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ተጨማሪ ማጣራት ካደረገ በኋላ የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

ተጠሪም የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ቅሬታቸውን ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ከስር ጀምሮ ሲከራከር የነበረው አመልካች በ15/01/1995 ዓ.ም በተደረገ ስጦታ አከራካሪውን ይዞታ እንደሰጡኝ በሌላ መዝገብ በመ.ቁ 34190 የስጦታ ውል አለ ተብሎ ተወስኖልኝ እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በመ.ቁ 173745 ላይ አያስቀርብም ተብሎ አመልካች ላይ ውሳኔው የጸና በመሆኑ ክርክር ያስነሳው ይዞታ የእኔ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ ፍ/ቤትም ክርክር ያስነሳውን ይዞታ አመልካች ከሌላ ሰው ጋር የባለይዞታነት መብት ክርክር ላይ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ሲከራከር አመልካች ለተጠሪ በ15/01/1995 ዓ.ም ባደረገው ስጦታ የሰጠ መሆኑን፤ ነገር ግን ተጠሪ አልጠርም ስላለውና ሃሳቡን ለውጦ ሲከራከር እንደነበረ መዝገቡ ውስጥ ከሰፈረው ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ክርክር ያስነሳው ይዞታ አመልካች በቀን

15/01/1995 ዓ.ም ለአሁኑ ተጠሪ የሰጠ ስለሆነ ከሳሽ /ተጠሪ/ በተጻፈ የስጦታ ውል ተሰቶኛል በማለት በክሱ ላይ አዋሳኙን ጠቅሶ ያቀረበው የመሬት ይዞታ የተጠሪ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔም በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትእዛዝ ፀንቷል፡፡

አመልካችም ይህ የፍ/ቤት ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ የሆነውን የመሬት ይዞታ ባለቤትነት መብቴን ጥሷል በማለት ቅሬታቸውን ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ያቀረቡ ሲሆን፣ በዋናነት ያነሱት ቅሬታም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመቁ. 28394 ላይ አምኗል ብሎ የሰጠው ውሳኔ አላመንኩም ከክሱ ጋርም አይገናኝም፣ ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 173745 ውሳኔ ተሰጥቶበታል የተባለው ከዚህ መሬት በተገኘው አላባ ላይ እንጂ በአከራካሪው ይዞታ ላይ ስላልሆነ ከመሬቱ ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ እኔ አመልካች የ102 ዓመት ሽማግሌ እና ከ45 ዓመት በፊት አይኔና ጆሬዬ መስማት እና ማየት የተሳነው ሲሆን የወረዳው ፍ/ቤት በማስረጃ አረጋግጦ የወሰነውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የአመልካች የቤተሰብ አባል እና ዝምድና ሳይኖረው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለተጠሪ የወሰነው ውሳኔ አመልካች በዚህ እድሜዬ ከይዞታዬ የሚያፈናቅለኝና ከዚህ ይዞታ በስተቀር ሌላ ምንም ምትክ መሬት የሌለኝ በመሆኑ የተወሰነው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ጋር የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ተሰጥቶት ወደነበረበት እንዲመለስልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ጉባኤውም ጉዳዩ ላይ ተወያይቶ የውሳኔ ሀሳብ ከመስጠቱ በፊት በአዋጅ ቁ. 798/2005 አንቀፅ 9(2) መሰረት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ አድርጎ ጉዳዩን መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት የጀልዱ ወረዳ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት አጣርቶ በቀን 10/03/2011 ዓ.ም ለጉባኤው ጽ/ቤት በላከው ደብዳቤ፣ አመልካች ለተጠሪ መሬት መስጠቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በቀበሌም ሆነ በወረዳው አስተዳደር የመሬት ስጦታ ውል የሌለ መሆኑ፣ አከራካሪው መሬት አመልካች እና ተጠሪ እንደ አባት እና ልጅ እስከ 2005 ዓ.ም በጋራ አብረው ሲጠቀሙበት መቆየታቸውን እና ከ2005 ዓ.ም በኋላ በፍ/ቤት መከራከር የጀመሩ መሆኑ፣ አመልካች አርሶ አደር ሆነው ክርክር ያስነሳው በተለያዩ 4 ቦታዎች ያለውን መሬት ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን፣ ከዚህ መሬት በስተቀር ሌላ የእርሻ መሬት የሌላቸው መሆኑ፣ ይህ መሬትም በፍ/ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ከተወሰደባቸው በኋላ በአሁኑ ግዜ አመልካች ከ0.1 ሄክታር የባህርዛፍ መሬት በስተቀር ሌላ የእርሻ መሬት



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የሌላቸው መሆኑ፣ አመልካች እና ሟች ባለቤታቸው ተጠሪን በግምት ከ2 እስከ 6 ዓመት እድሜ ያለውን ህፃን ወስደው በአገሩ ባህል መሰረት ከ40 አመት በፊት ሽማግሌዎች ፊት ለፊት ቃለ መሃላ ፈፅመው ያሳደጉት መሆኑ እና ሳጅን ተስፋዬ ታዬ ከአመልካች አቶ ታዬ ዳብሱ በስተቀር ሌላ ወላጅ አባትም ሆነ አሳዳጊ የሌላቸው መሆኑን እንዲሁም የአመልካች ባለቤትም እስከሞቱበት ግዜ ድረስ በገቡት ቃል መሰረት እናት ሆነው ተጠሪን አሳድገው ያስተማሩ መሆኑን አጣርቶ ለጉባኤው መላኩን በመግለጽ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በፍ/ቤት ውሳኔ የአመልካች ሕገ መንግስታዊ መብት ስለተጣሰ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና የምክር ቤቱ ባለሙያዎች የሰጡትን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡ በዚህም መሰረት ምክር ቤቱ አመልካች ሙሉ በሙሉ ከመሬቴ እንድፈናቀል አድርጎኛል በማለት ቅሬታ ያቀረቡበት የፍ/ቤቱ ውሳኔን መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪው አመልካች በ15/01/1995 ዓ.ም አከራካሪው የመሬት ይዞታ የእናቴን ድርሻ አካፍሎኝ እየተጠቀምኩበት እያለ መልሶ በጉልበት በ2005 ዓ.ም ስለያዙብኝ አመልካች መሬቱን ይልቀቅልኝ የሚል ሲሆን አመልካችም ለተጠሪ በስጦታ ያካፈልኳቸው መሬት የለም፣ የቀረበው የስጦታ ውልም የሀሰት ነው በማለት ከተከራከሩ በኋላ የወረዳውና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ሕጋዊ የስጦታ ውል የለም በማለት አመልካች ላይ የቀረበውን ክስ ውድቅ ሲያደርጉ ነገር ግን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች መሬቱን ለተጠሪ መስጠቱ ከሌላ 3ኛ ወገን ጋር በሌላ መዝገብ ላይ በሚከራከሩበት ወቅት አምኗል በማለት የወረዳው እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር አመልካች 4ቱም ቦታ ያለውን 2.4555 ሄክታር መሬት ለተጠሪ እንዲለቁ በማለት ወስኗል ውሳኔውም በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡ ይህ ፀንቶ ያለው የፍ/ቤቱ ውሳኔ የአመልካችን ከመሬታቸው ሙሉ በሙሉ ያፈናቀላቸውና ሕገ መንግስታዊ የመሬት ባለ ይዞታነት መብታቸውን ጥሷል አልጣሰም? የሚለው ሲታይ፣ 1ኛ/ አመልካች አርሶ አደር ሆነው ከሟች ባለቤታቸው ጋር ሲጠቀሙበት የነበረው የመሬት ይዞታ በተለያዩ 4 ቦታዎች ያለው

በአጠቃላይ 2.4555 ሄክታር መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ተጠሪ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ የጠየቁት የዳኝነት ጥያቄ ደግሞ "አመልካች የእናቴን ድርሻ አካፍሎኝ መልሶ በጉልበት የያዙብኝን መሬት ይልቀቅልኝ" የሚል ሲሆን ተጠሪ የእናታቸውን ድርሻ ከአጠቃላይ መሬቱ 2.4555 ሄክታር ውስጥ 1.275 ሄክታር ሲሆን ግማሹ 1.275 ሄክታር ደግሞ የአመልካች ድርሻ ነው፡፡ ነገር ግን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተጠሪ ክሱ ላይ የጠቀሳቸውን 4ቱም ቦታዎች ያሉትን በአጠቃላይ 2.4555 ሄክታር መሬት የአመልካችን ድርሻ ጭምር ተጠሪ እንዲወስዱ የወሰነ ሲሆን ይህ ደግሞ ፍ/ቤቱ ተጠሪ የእናቴን ድርሻ በማለት የመሬቱን ግማሽ ከጠየቁት ዳኝነት ላይ 50% ያልተጠየቀውን ዳኝነት በመጨመር ለተጠሪ የተወሰነ ውሳኔ ሲሆን በዚህ ውሳኔ መሰረትም አመልካች አርሶአደር ሆነው ሲተዳደሩበት የነበረው አከራካሪው የእርሻ መሬት ሙሉ በሙሉ ከአመልካች እጅ ወጥቶ ተጠሪ እጅ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

2ኛ/ ተጠሪ በ1995 ዓ.ም አመልካች የእናቴን ድርሻ አካፍሎኝ በመሬቱ እየተጠቀምኩ እያለ እንደገና በ2005 ዓ.ም በጉልበት ያዙብኝ በማለት ቢከራከሩም፣ የቀረበው ማስረጃ የሚያመላክተው ይህ አከራካሪው መሬት አመልካች እና ተጠሪ እንደ አባት እና ልጅ ሆነው አብረው እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ ከመጠቀም ውጭ አመልካች ለተጠሪ መሬቱን እንደሰጠው የሚያረጋግጥ የሰውም ሆነ የፅሁፍ ውል ወይም ማስረጃ እንደሌለ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ደግሞ ተጠሪ መሬቱን ከሰጡኝ በኋላ በጉልበት ያዙብኝ በማለት አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ የሀሰት ክስ መሆኑ እንዲሁም ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔም አመልካች ለተጠሪ የሰጡት ሕጋዊ የሆነ የስጦታ ውል በሌለበት የተሰጠ ውሳኔ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡

3ኛ/ አመልካች ከአከራካሪው መሬት በስተቀር ሌላ የመሬት ይዞታ የለኝም በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ በተመለከተ መሬቱ ያለበት የወረዳው መሬት አስተዳደር አጣርቶ ለጉባኤው በላከው ማስረጃ ተጠሪ አከራካሪውን እና በአይነት የተለያየ ቦታ የሚገኘውን መሬት አራቱም ቦታ ያለውን 2.4555 ሄክታር ሙሉ በሙሉ በፍ/ቤት ተወስኖለት ይዞ እንደሚገኝ የሚገልጽ ሲሆን ነገር ግን አመልካች ከ0.1 ሄክታር የባህርዛፍ መሬት በስተቀር ሌላ የእርሻ መሬት ወይም መተዳደሪያ የሌላቸው እና በአሁኑ ጊዜ ጥገኛ ሆነው እየኖሩ መሆኑን ከቀረበው ማስረጃ መረዳት ተችሏል፡፡

ከላይ በተቀመጠው መሰረት አመልካች አርሶአደር መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን፣ አርሶ አደሮች የመሬት ይዞታ ላይ ያላቸውን መብት ለማስከበር በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40



የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ንዑስ አንቀፅ 4 ስር "የኢትዮጵያ አርሶአደሮች ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው የተከበረ ነው ዝርዝሩም በህግ ይወሰናል በማለት" ተደንግጓል፡፡ አመልካች መሬታቸው ሙሉ በሙሉ ከእጃቸው የወጣው ሕግን በተከተለ በፍ/ቤት ውሳኔ ሳይሆን አመልካች አራቱም ቦታ ያለውን መሬት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተደረገው ሕጋዊ የሆነ የጽሁፍም ሆነ የሰው ማስረጃ በሌለበት ነው፡፡

አመልካች በሌላ መዝገብ ላይ ከሌላ 3ኛ ወገን ጋር ሲከራከሩ ለተጠሪ መሬቱን መስጠቱን አምኗል በማለት እንዲያውም ተጠሪ የእናቱን ድርሻ ብቻ ጠይቆ እያለ ፍ/ቤቱ ግን የአመልካችንም ድርሻ ጨምሮ ተጠሪ ያልጠየቀው ዳኝነት ላይ 50% በመጨመር ሁሉንም አመልካች የያዙትን የመሬት ይዞታ ለተጠሪ እንዲለቁ የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ አይደለም፡፡

በመሆኑም በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(4) የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው በማለት የተደነገገውን የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብት የሚቃረን ስለሆነ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ትእዛዝ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን በምክር ቤቱ መወሰኑን አውቀው ተገቢውን እንዲፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የፌዴራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

18

1. የፌ/ም/መ/ቁ 34/09

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አመልካቾች፡-** እነ አቶ ረጋሳ ስዩም (17 ሰዎች)

**ተጠሪዎች፡-** እነ አቶ ሙስጠፋ ከድር (10 ሰዎች)

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የግጦሽ መሬትን ከመጠቀም መብት ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክር ሲሆን የክሱ ይዘትም ጪሞ ኡስማን ቀበሌ የሚገኝና ክርክር የተነሳበት 6 ሄክታር መሬት አዋሳኙን በመጥቀስ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ከተጠሪዎች ጋር ለግጦሽ በጋራ ስንጠቀምበት ቆይተን ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪዎች ስለያዙብን ይልቀቁልን በማለት ክስ ስላቀረቡ ነው፡፡

ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳውን የይዞታ መሬት ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በኛ እጅ የሚገኝ፣ ስንጠቀምበት የቆየንና የይዞታ ማረጋገጫ የወሰድንበት በመሆኑ በይዞታው ላይ መብት አለን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመመዘን

ተጠሪዎች ባለይዞታ መሆናቸውንና ያለተቃውሞ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆናቸውን ጠቅሶ ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ይዞታውን በሕጋዊ መንገድ ስለመያዛቸው በማስረጃ ባለማረጋገጣቸው እንዲሁም አመልካቾች ይዞታውን ሲጠቀሙ መቆየታቸውን በማስረጃ በኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁ.130/99 አንቀጽ 25 መሠረት ይዞታውን አመልካቾችና ተጠሪዎች በጋራ እንዲጠቀሙበት ሲል ወስኗል፡፡

ይህም ውሳኔ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦ የፀና ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ያላቸው መሆኑን በማስረዳታቸው በይዞታው ላይ ባለመብት ናቸው በማለት የዞኑን ፍርድ ቤት እና የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ስልጣኑ ተመልክቶ ጉዳዩ አያስቀርብም ብሏል፡፡

አመልካቾች ሰኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለጉባኤው ባቀረቡት ጥያቄ እኛ አመልካቾች ከፊል አርብቶ አደር በመሆን ለረጅም ጊዜ ለግጦሽ ስንጠቀምበት የቆየነውን የወል መሬት ፍርድ ቤቶች የተጠሪዎች የግል ይዞታ ናቸው በማለት መወሰናቸው የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 9፣ 40(5) እና 50 ስለሚጥስ ትርጉም እንዲሰጥልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቶች የሰጧቸውን ውሳኔዎች ከተጠቀሰው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡

አመልካቾች ተጣሰብን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በጋራ በመያዝ ለግጦሽ ሲጠቀሙበት የቆዩትን የገጠር መሬት ያለአግባብ አጥተናል የሚል ነው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ከፍርድ ቤቶች ውሳኔ ጋር በማጣመር እንደመረመርነው አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የመሬት ይዞታ በተመለከተ ጉባኤው በደብዳቤ ቁ.አጠ1436/03/08 በቀን 08/03/08 ዓ.ም ለክልሉ የገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ቢሮ በጻፈው ደብዳቤ በአንድ ይዞታ ላይ ሁለት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዴት እንደተሰጠ አስተያየት እንዲሰጥበት ጠይቋል፡፡ በዚሁ መሠረት የክልሉ የገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ቢሮም በቀን 02/06/08

ዓ.ም በቁ.BLBE-/1451/108 በጻፈው መልስ ክርክር ወደ አስነሳው ስፍራ ባለሙያዎችን በመላክ ማጣራት አድርጓል፡፡

በዚሁም መሠረት ክርክር የተነሳበት መሬት በ1996 ዓ.ም በተደረገ የመሬት ልማት የጋራ መሬት ተብሎ መለካቱን በተለያየ ወቅት ከነበሩ የቀበሌው የመሬት ልማት ኮሚቴዎችና የአካባቢ የሰፈር ሽማግሌዎች አነጋግረው ያረጋገጡ መሆኑን በሌላ በኩል እነ አቶ ሙስጠፋ ከድር (10 ሰዎች) አለን ብለው ያቀረቡት የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግባብ ባለው የገጠር መሬት ምዝገባ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያላለፈ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

በተጨማሪም በእጃቸው ይዘውት የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ስርዝ ድልዝ ያለው ተፍቆ የተሞላበት እና በወረዳው የገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽሕፈት ቤት የሚገኘው ቀሪ ማለትም የገጠር መሬት የሚመዘገብበት መዝገብ ላይም በተመሳሳይ መልኩ ተፍቆ የተሞላ እና የመሬት ልኬት ኮሚቴዎች በቀበሌው ደረጃ የሚዘጋጅ ቅጽ ላይ ያልፈረሙበት በመሆኑ ይህ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በዚህም መሠረት የተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሲታይ የገጠር መሬት ልኬትና ምዝገባ በዚሁ በኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁ.130/99 አንቀጽ 15 መሠረት የሚከናወነው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬትና የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ ነው፡፡ ነገር ግን በያዝነው ጉዳይ የክልሉ የገጠር መሬትና አካባቢ ቢሮ የተጠሪዎች ማስረጃ ተቀባይነት እንደሌለው አረጋግጧል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(5) መሠረት የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበትን መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀም እና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው በማለት ይደነግጋል፡፡ የክልሉ የገጠር መሬት አካባቢ ጥበቃ ቢሮ በዚህ ጉዳይ ላይ ለአጣሪ ጉባዔው ከላከው ማስረጃ መረዳት እንደሚቻለው በይዞታው ላይ በተሰጠው ሁለት የይዞታ ማረጋገጫ ለተጠሪዎች በሕጉ መሠረት ያልተሰጠ እና ተፍቆ የተሞላ መሆኑን ስለሚያመለክት እንዲሁም ይዞታው በመሬት ልኬት ወቅት ለአካባቢው ህብረተሰብ በጋራ ለግጦሽ የሚውል መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

አመልካቾች ከፊል አርብቶ አደሮች በመሆናቸውና ክርክር ያስነሳው ይዞታ የወል የግጦሽ መሬት መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶች ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ የአመልካቾችን ሕገ መንግሥታዊ መብትን በሚጥስ መልኩ ይዞታው የተጠሪዎች የግል ይዞታ ነው በማለት መወሰናቸው አመልካቾች ከጋራ የግጦሽ መሬት ይዞታቸው የሚያፈናቅልና ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(5) ጋር የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ 131/07

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አመልካቾች፡-** እነ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ተስፋጽዮን (2 ሰዎች)

**ተጠሪ፡-** የቦሌ ክ/ከ/ማ አስተዳደር

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

አመልካቾችና ተጠሪ ክርክር ውስጥ ሊገቡ የቻሉት 1ኛ አመልካች ባለቤታቸው ከሆኑት 2ኛ አመልካች ጋር ጋብቻ መስርተው በጋራ ካፈሯቸው ንብረቶች ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 17 ቀበሌ 19 የቤት ቁ.309 መኖሪያ ቤት፣ ሞዴል 190 የሰሌዳ ቁ.2-32548 አ.አ የሆነ ቶዮታ እና የሰሌዳ ቁ.2-35568 አ.አ የሆኑ መኪናዎችን 1ኛ አመልካች በባለቤትነት በመጠቀምና በማስተዳደር ላይ እያሉ ሌላ ሰው በመወከል ለህክምና ጉዳይ ከኢትዮጵያ ሲወጡ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ከሁለቱም አመልካቾች እና ከተወካያቸው ፈቃድ ውጭ ንብረቶችን ስለወሰዱ እንዲመልሱ ወይም ሸጠው ከሆነም ለመሸጥ የሚያስችል ስልጣን ስለሌላቸው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ወይም ለመሸጥ ህጋዊ

19

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን

## 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም

አመልካች:- ሃለቃ ተአረ ደስታ ወኪል ወ/ሮ ጥበቡ ተአረ

ተጠሪ:- ወ/ሮ ገነት አስነ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

ውሳኔ

ጉዳዩ የገጠር መሬት ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች ለኦፍላ ወረዳ ስምሪት ጣቢያ መሬት ዳኝነት ባቀረቡት አቤቱታ የቀበሌው መሬት አስተዳደር በስሜ የተመዘገበውን መሬት በህዝብ ተተችቶ ሊነጠቅ አይገባውም ከተባለ በኂላ በሌላ ጊዜ እኔ በሌለሁበት ማስታወቂያ አውጥተው ተጠሪ እንድትወስድ ማድረጋቸው አግባብ አይደለም በማለት ጠይቀዋል። ተጠሪም ባቀረቡት መልስ በተለመደው አሰራር በቀበሌው ማስታወቂያ ወጥቶ የአመልካችና የባለቤታቸው መሬት ይዞታ በእጣ ለእኔ ተሰጥቶኛል በማለት ተከራክረዋል። የመሬት ዳኝነት አካሉም የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን በማስቀረብ የአመልካች መሬት ከ1 ዓመት በፊት ተጠንቶ አመልካችም እድሜያቸው ከ80 ዓመት በላይ የሆነና አቅመ ደካማ ስለሆኑ ይህንኑም ከወረዳው መሬት ዴስክ በቀረበ ማስረጃ መሠረት መሬቱን ሊነጠቁ አይገባም በማለት ውሳኔ አስተላልፏል።

ጉዳዩ በተጠሪ ለኦፍላ ወረዳ ማይማዶ ምድብ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ በማቅረብ መሬቱ በ2005 ዓ.ም ለህዝብ ቀርቦ የተተቸና አመልካችም ዕድሜያቸው 86 አመት የሆኑ አዛውንት ናቸው ተብሎ የታለፈ ቢሆንም ይህ የህዝብ ውሳኔ ለካቢኔና ለአስፈጻሚ ያልቀረበ በመሆኑ እንደገና በ2006 ዓ.ም ተጠንቶና ለካቢኔ ቀርቦ በእጣ ለእኔ ስለደረሰኝ ይዞታው ለእኔ ይገባል በማለት ተከራክረዋል። የወረዳው ፍ/ቤት ምስክሮችን በመስማት አመልካች ኮረም ከተማ ቢገቡም አዛውንት ስለሆኑና በ2005 ዓ.ም. ጉዳዩ ለህዝብ ቀርቦ ሊነጠቁ እንደማይገባ ህዝቡ የተስማማ መሆኑን ከምስክሮች በማረጋገጥ በ2006 ዓ.ም አመልካች በሌሉበትና ለህዝብ ሳይቀርብ ማስታወቂያ በማውጣት ብቻ ይዞታቸውን ሊነጠቁ አይገባም ሲል ውሳኔ ሰጥቷል።



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

በአሁን ተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ቀርቦ አመልካች ወደ ኮረም ከተማ ከገቡ 8 ዓመት ስለሆናቸውና ተጠሪም መሬቱን ያገኙት ብዙ ሂደቶችን አልፈው በመሆኑ በህጋዊ መንገድ ያገኙትን መሬት ሲነጠቁ አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩ ለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ቢቀርብም የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም በማለት አያስቀርብም ተብሎ ተወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በወኪላቸው በኩል ግንቦት 9 ቀን 2008 ዓ.ም ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ውሳኔው በ1983 ዓ.ም በድልድል ያገኘሁትን የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ስላሳጣኝ ውሳኔው ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40፤ 37 እና 79 ንኡስ አንቀጽ 3 አንፃር ታይቶ ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤውም የአመልካችን አቤቱታ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 አንጻር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ ክርክር የተነሳበት ይዞታ ቀድሞ የአመልካች እንደነበረ፣ ከዚያም አመልካች ወደ ከተማ በመሄዳቸው መሬቱን ለሌላ ግለሰብ ለመስጠት በ2005 ዓ.ም ተጠንቶና ለህዝብ ቀርቦ አመልካች የ86 ዓመት ሽማግሌ በመሆናቸው ይዞታው ለሌላ ሰው ተላልፎ መሰጠት እንደሌለበት ህዝቡ አስተያየት ሰጥቶበት የታለፈ መሆኑን ነገር ግን በ2006 ዓ.ም አመልካች በሌሉበት ለተጠሪ በእጣ ድልድል የተሰጣቸው መሆኑን፣ እንዲሁም ውሳኔው አመልካችን ከይዞታ መሬታቸው ያለመፈናቀል ሕገ መንግስታዊ መብት ጋር የሚፃረር መሆን አለመሆኑ እና የአመልካች ይዞታ መሬት ለተጠሪ የተሰጠው በህጋዊ መንገድ መሆን አለመሆኑ የተመረመረ ሲሆን ክርክር ከመነሳቱ በፊት ይዞታው የማን እንደነበር ለማወቅ በጉባኤው ጽ/ቤት በኩል መረጃ ተጠይቆ የኦፍላ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 659/መ-2/09 በቀን 24/10/09 ክርክር የተነሳባቸው አራት በተለያየ ቦታ የሚገኙ የመሬት ይዞታዎች ከ1983-2007 ዓ.ም ድረስ በሃለቃ ተአረ ደስታ ስም ሆኖ 7 የቤተሰብ አባላትን የሚያስተዳድሩበት የነበረ መሆኑን በመግለፅ ለጉባኤው ልኳል፡፡

የጉባኤው ጽ/ቤት የአመልካችን ዕድሜና የኑሮ ሁኔታ ይኖሩበታል ከተባለው ኮረም ከተማ በደብዳቤ ባደረገው ማጣራት የከተማ አስተዳደሩ በቀን 24/06/09 በቁጥር 4126/ኮም/09 በሆነ ደብዳቤ አመልካችን በአካል ሄደው በማነጋገር አመልካቹ የሚተዳደሩት በግለሰብ ወፍጮ ቤት ተቀጥረው በሚያገኙት ገቢ መሆኑን፤ ከሚኖሩበት ኦፍላ ወረዳ ከለቀቁ 10 ዓመት የሆናቸውና ዕድሜያቸውም 86 ዓመት እንደሆነ በመግለጽ መረጃ ልኳል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው

አመልካች በጊዜያዊነት አነስተኛ ገቢ ሊባል በሚችል ሁኔታ በግለሰብ ወፍጮ ቤት ተቀጥረው የሚሰሩና በዕድሜያቸውም አዛውንት መሆናቸውን ነው፡፡

የትግራይ ክልል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 136/2000 በአንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ ማንም ሰው ያለ በቂ ምክንያት የይዞታ መሬቱ የሚገኝበትን ቀበሌ ከ2 ዓመት በላይ ለቆ የሄደ እንደሆነ መሬቱ ሊወሰድ እንደሚችል ጠቅሶ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 /ቀ/ ላይ ጧሪና ተንከባካቢ አጥተው መስራት የማይችሉ አዛውንቶች ቀበሌያቸውን ቢለቁም መሬቱ ሊወሰድ እንደማይገባ ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል ህዝቡ አመልካች አዛውንት እንደሆኑ ተስማምቶ መሬቱ መወሰድ የሌለበት መሆኑን እየገለፀ በተቃራኒው በሌላ ጊዜ ደግሞ ለህዝብ ሳይቀርብ በማስታወቂያ ብቻ ለሌላ ሰው በድልድል የተላለፈበትን ሂደት ፍ/ቤቱ ተቀብሎ በውሳኔ ማጽደቁ በክልሉ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ በዝርዝር ህግ ጥበቃ የተደረገለትን ከመሬት ያለመነቀል መብት እንዲሁም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ የሚጥስ ነው፡፡

ስለዚህ የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ሲል ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለመጨረሻ ውሳኔ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ በሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩ ታይቶ እንዲቀርብ መርቶት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት አድርጓል፡፡ ከጉዳዩ አመጣጥ መረዳት እንደተቻለው አመልካች የመሬት ይዞታቸውን እንዲያጡ በፍርድ ቤት የተወሰነው በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት አንድ የመሬት ባለይዞታ ከአካባቢ ለቆ ለሁለት አመት ከቆየ የይዞታ መብቱን ያጣል የሚለውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ አዋጅ የተጠቀሰው ይዞታ መብት ሊታጣበት የሚችል ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ አዋጅ ልዩ ድንጋጌ (exception) ደግሞ ባለይዞታው አቅመ ደካማ ከሆነ ይህ ገደብ ተፈጻሚ እንደማይሆን ይገልጻል፡፡

በመሆኑም አመልካች በሕጋዊ መንገድ ተሰጥቷቸው በርካታ ቤተሰቦቻቸውን ይዘው የሚጠቀሙበትን ይዞታ መሬት እድሜአቸው በመግፋቱ ምክንያት አቅማቸው የሚፈቅደውን አነስተኛ ስራ እየሰሩ ለመኖር ከተማ የሚኖሩ በመሆኑና የክልሉ የመሬት አዋጅም አዛውንቶች ቀበሌአቸውን ለቀው ወደ ሌላ ቦታ ቢሄዱም ይዞታ መሬታቸውን እንደማይነጠቁ በሕግ በተፈቀደላቸው መብት እና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 ከመሬት ይዞታ ያለመነቀል መብታቸውን የሚቃረነው የፍርድ ቤቱ የመጨረሻው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ወስኗል፡፡

## ትእዛዝ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተወስኖ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስህተት የለበትም ተብሎ የጸናው የመጨረሻ ውሳኔ ተፈጻሚነት አይኖረውም ሲል ምክር ቤቱ የወሰነ ስለሆነ ውሳኔውን አውቀው እንዲያስፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይድረሳቸው፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለባለጉዳዩ ይሰጥ፡፡
3. የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቁት ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይላክ፡፡

6

18

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣3ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ
መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ ኪዳነማርያም ተክሉ አድራሻ ትግራይ ክልል

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ገ/ሚካኤል እንደያ አድራሻ ትግራይ ክልል

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ በገጠር ከሚገኝ መሬት ይዞታ ጋር ተያይዞ የተጀመረ ክርክር ሲሆን አመልካች በአቤቱታቸው ተጠሪዎች ይዘው የሚጠቀሙበት በገጠር የሚገኝ የእርሻ መሬት ይዞታው የኔ ነው በማለት ይዞታው እንዲለቀቅላቸው ተጠሪዎች በዶግዓ ተምቤን ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪዎችም አመልካች ክርክር የተነሣበትን የገጠር ቀበሌ ለቀው በመሄዳቸዉና የነሱ የመሬት ይዞታ በልማት ምክንያት ለመንገድ ስራ ተብሎ በመንግስት በመወሰዱ በሕጋዊ መንገድ የተሰጣቸውን ምትክ የመሬት ይዞታ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤትም ክርክር በተነሣበት በገጠር መሬት ይዞታ ላይ ማን ባለመብት እንደሆነ በቀበሌው መስተዳድር ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማዘዝና በማጣራት ክርክር የተነሣበትን የገጠር መሬት ይዞታ አመልካች ለቀው በመሄዳቸዉ ይዞታው በሕጋዊ መንገድ ለተጠሪዎች የተሰጣቸዉ ነው፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የትግራይ ክልል የደቡብአዊ ምስራቅ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ያጸናው ሲሆን ጉዳዩ በሰበር የቀረበላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች ታህሣሥ 7 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ ማመልከቻ ለጉባኤው በማቅረብ ጧሪ የሌለኝ የ78 ዓመት ሽማግሌ ስሆን እኔ መቀሌ ከተማ ብቀመጥም ክርክር የተነሳበትን የገጠር መሬት እንድጠቀም የወጣውን አዋጅ በሚቃረን ሁኔታ ይዞታዬን ለተጠሪዎች

9

እንዲሰጥ በፍ/ቤት መወሰኑ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ጋር ይቃረናል በማለት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡

የፍቤቱ ውሳኔ አመልካች ተጣሰብኝ በማለት ከጠቀሱት የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 ጋር የሚቃረን መሆን ያለመሆኑ በጉባኤው ተመርምሯል፡፡ ጉዳዩን አጣርቶ ሕገ መንግስታዊ ትርጉም ለመስጠት እንዲቻል አመልካች ክርክር የተነሳበትን በገጠር የሚገኝ የእርሻ መሬት ይዞታ በምን ምክንያት እንደተወሰደባቸው፣ ይዞታው በማን እጅ ተመዝግቦ እነደሚገኝ እና የአመልካች መተደደሪያ ምን እንደሆነ በሚመለከተው አካል ተጣርቶ ውጤቱ እንዲገለጽ በጉባኤው ታዟል፡፡

በዚሁ መሰረት በትግራይ ክልል በመቀሌ ከተማ አይደር ክፍለ ከተማ በቀን 28/07/08 ዓ.ም በቁጥር 562/4/ደ/11/08 በተፃፈ ደብዳቤ አመልካች በቀበሌያቸው ውስጥ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ ነዋሪ መሆናቸውን፣ መተዳደሪያቸዉም የቀን ሰራተኛ እና እድሜያቸውን 75 ዓመት መሆኑን ሲገልጽ የትግራይ ክልል የዶግዓ ተንቤይን የስነ አካባቢና የገጠር መሬትና አጠቃቀም ጽ/ቤት ደግሞ በቀን 09/02/09 ዓ.ም ቁጥር 752/መ2.01 በተፃፈ ደብዳቤ ክርክር የተነሳበት የገጠር መሬት ይዞታ ከ2005 ዓ.ም በፊት የአመልካች ይዞታ እንደነበር ከ2005 ዓ.ም በኋላ የተጠሪዎች ይዞታ በልማት ምክንያት በመንግስት ሲወሰድ የአመልካች ይዛታ የነበረው በምትክ ለተጠሪዎች መስጠቱንና አሁን ይዛታው በተጠሪሪዎች ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

አመልካች ክርክር የተነሳበት የእርሻ መሬት ይዛታ የሚገኝበትን የገጠር ቀበሌ ለቀው መቀሌ ከተማ የገቡት በ1981 ዓ.ም ቢሆንም እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ በዚሁ ይዞታቸው ይጠቀሙ የነበረውና አመልካች በ75 ዓመታቸው የቀን ስራ እየሰሩ የሚተዳደሩ ጧሪና ተንከባካቢ የሌላቸው አቅመ ደካማ መሆናቸውን ከደብዳቤዎቹ ይዘት መረዳት ተችሏል፡፡

የተሻሻለው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር239/2006 አንቀጽ 11 ንኡሰ አንቀጽ 1 በዚህ አዋጅ ከተፈቀዱ ምክንያቶች ውጪ ከሚኖሩበት ቀበሌ ከሁለት ዓመት በላይ ወደ ሌላ ቀበሌ ወይም ከተማ የለቀቀ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን ያጣል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል ብሎ የሚደነግግ ቢሆንም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 5 (በ) ላይ ጠዋሪና ተንከባካቢ አጥተው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ቀበሌአቸውን ቢለቁም በነበራቸው የመሬት ይዞታ የመጠቀም መብታቸው የተጠበቀ እነደሚሆን ከድንጋጌው መረዳት ተችሏል፡፡

አመልካች ክርክር በተነሳበት የገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብታቸው የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈፃፀሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል በማለት ከተደነገገው እና ከሕገ መንግስቱ ጋር በሚጣጣም መልኩ አመልካች ጠዋሪና ተንከባካቢ የሌላቸው አቅመ ደካማ ሰለሆኑ የነበራቸውን በገጠር የሚገኝ የመሬት ይዞታ ቢለቁም በልዩ ሁኔታ በነበራዉ የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚደነግገው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ውጪ ተጠሪዎች የመሬት ይዞታ በልማት ምክንያት በመወሰዱ የአመልካችን ይዞታ በምትክነት ይዘው እንዲጠቀሙ የተወሰነው የፍ/ቤቱ ውሳኔ ከሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንኡስ ቁጥር 4 ጋር ይቃረናል፡፡በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. ከትግራይ ክልል የሥር ፍ/ቤት እስከ ክልልና ፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ሽሮታል፡፡አመልካች አቅመ ደካማ ስለሆኑ ከይዞታቸው እንዳይፈናቀሉ ተወስኗል፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የውሳኔ ሀሳብ ም/ቤቱ በሰጠው የሕገ መንግስት ትርጉም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን እንዲያውቁት ውሳኔው ይድረሳቸው፡፡
3. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ም/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ እንዲያስፈጽም ይድረሰው፡፡
4. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ም/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ እንዲያስፈጽም ይድረሰው፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካች ይድረሳቸው፡፡

6ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባኤ

ሰኔ/2013 ዓ.ም

የመዝገብ ቁጥር 97/13

አመልካች፡- ወ/ሮ መንፀገባ ግርማይ

ተጠሪ፡- አቶ ይሕደጎ ንጉሥ

የኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል።

ውሳኔ፣

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 19/10/2010 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው። ጉዳዩ የገጠር መሬት ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ነው።

ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ክልል ደቡብ ዞን እንባ አላጀ ወረዳ በፋና ቀበሌ አስተዳደር የአሁን ተጠሪ በፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበሩት በአቶ መንግሥቱ ግርማይ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው። የክሱ ይዘትም በአጭሩ ለሕዝብ ጥቅም ወይም ለመንገድ ሥራ መሬቴ ተወስዶብኛ፣ በዚህ መሬት ምትክ መንግሥቱ ግርማይ የሚያርሱት መሬት ቢሰጠኝም አቶ መንግሥቱ መሬቱን ለመልቀቅ ፍቃደኛ ስላልሆኑ በሕግ ተገደው እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው።

በፍርድ ቤቱ ተከሳሽ የነበሩት አቶ መንግሥቱ ግርማይ በሰጡት መልስ ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት የወ/ሮ መንፀገባ ግርማይ፣ የአሁን አመልካች ሲሆን አመልካች እህታቸው ስለሆኑ የሚያርሱላቸው መሆኑን

በመጥቀስ አመልካች በመድኅንነት ወደ ክርክሩ እንዲገቡላቸው ጠይቀዋል።

በዚሁ መሠረትም የአሁን አመልካች ወደ ክርክሩ ገብተው መልስ ሰጥተዋል። በሰጡት መልስም ትውልዳቸው መሬቱ በሚገኝበት ቀበሌ መሆኑን ከገለጹ በኋላ፣ መጀመሪያ በትምህርት ምክንያት ከአካባቢው ርቀው ከሄዱ በኋላ የመከላከያ ሰራዊት አባል ባል አግብተው እየኖሩ ሲሆን በአሁን ሰዓት የፌስቱላ በሽተኛ መሆናቸው በሦስት ዶክተር የተረጋገጠ ማስረጃ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ከመሬታቸው ሊፈናቀሉ እንደማይገባ ተከራክረዋል። ከዚህም በተጨማሪ መሬቱ ከዚህ በፊት ለሌላ ሰው ሊሰጥ ዕጣ ውስጥ ሲገባ ቀርበው በመከራከራቸው ምክንያት እንደታለፈላቸው በመግለጽ አሁንም ለሌላ ሰው ሊሰጥ አይገባም በማለት ተከራክረዋል።

የግራ ቀኙን ክርክር የሰማው የቀበሌው መሬት አስዳደር ኮሚቴ በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ውሳኔ አመልካች መሬቱን ለረዥም ጊዜ ለሌላ ሰው ሰጥተው እየተጠቀሙ በራሳቸው ከተማ የሚኖሩ ሲሆን የገጠር መሬት ሕጉ ደግሞ ይህን ስለማይፈቅድ መሬቱን ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል ሲል ወስኗል።

ክርክሩ በይግባኝ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤት አይስቀርብም ሲል ዘግቷል። ቀጥሎ በሰበር አቤቱታ ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በሽተኛና ባለትዳር በመሆናቸው በከተማ እንደሚኖሩ አረጋግጠዋል። ነገር ግን በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 239/2006 አንቀጽ 11/5/(ሰ) መሠረት በከተማ የሚኖሩ የገጠር መሬታቸውን እያከራዩ መጠቀም የሚችሉት ከባድ የስነ አእምሮ ችግርና የአካል ጉዳት ያለባቸው ዜጎች ብቻ እንደሆኑ ይደነግጋል። የአመልካች በሽታ ከዚህ አንፃር በአዋጁ ላይ



የተደነገገ
ምክንያት

በመጨረሻ ክ
ሰበር ሰሚ ች
በማለት መዝገቡ

አመልካች ለጉባኤ
የሆነው መሬት የራሴ
የሰጠኝ ነው። ከልጅ
መጀመሪያ በትምህርት
እየኖርኩ ሳለሁ በ2002
የህክምና ማስረጃ በመረጋገጠ
እንዳልሄድ በሃኪሞች ታዝዤለ

አሁንም በዚህ በሽታ እየታመ
በሽታውን እንደ ቀላል በሽታ በማ
ማለታቸው በሕገ መንግሥቱ አን
ሕገመንግሥታዊ መብት የሚጥስ
ትርጉም ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል።

ጉባኤው አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ
ካላቸው ሕጎችና ከሕገ መንግሥቱ ፍትሐ
መሬት ካለመፈናቀል መብት አንፃር መርምሯ
ውስጥ በዋናነት መፍትሄ ማግኘት የሚገባቸው ነ

1ኛ. አመልካች በትግራይ ብ/ክ/መንግሥት የገጠር መሬት አዋጅ መሠረት የደረሰባቸው በሽታ በከተማ ሆነው የገጠር መሬት ይዞታቸውን እንዲያሳርሱ የሚፈቅድ ነው ወይስ አይደለም?

2ኛ. ይህ በሕጉ የተደነገገው መስፈርት ከሕገ መንግሥቱ የሴቶችና ከገጠር መሬት ያለመፈናቀል ሕገ መንግሥታዊ መብት አንፃር እንዴት ይታያል? የሚል ነው

አመልካች በፍርድ ቤቶች በነበረው ክርክር የፌስቱላ ተጎጂ መሆናቸው በዶክተሮች የተረጋገጠ ማስረጃ ቀርቦ ከመዝገባቸው ጋር ተያይዞ ይገኛል። በተጨማሪም አጣሪ ጉባኤው የበሽታውን ምንነት የሚያስከትለውን አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ እንዲሁም ማኅበራዊ ጉዳቶችን በተመለከተ ሙያዊ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ለሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ ፌስቱላ ሆስፒታል ተጠይቆ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

በማብራሪያውም ፌስቱላ በሴቶች እናቶች ላይ የሚያደርሰው ስነ ልቦናዊ ጉዳት ቀላል እንዳልሆነና አንዲት እናት በፌስቱላ ተጎጂ ስትሆን ተያይዞው ከሚመጡ ችግሮች መካከል የስነ ልቦናና የአእምሮ መታወክ ችግሮች ዋነኞቹ ችግሮች ናቸው። ጉዳቱ ከሚያደርሰው ማኅበራዊ ችግር ከፍተኛ መገለል አንዱ ሲሆን በአጠቃላይ ጉዳቱ የደረሰባት ማንኛውም ሴት ከግብርና ሥራ ጋር በተያያዘ እንደ አረም፣ ጉልጓሎ፣ እንዲሁም ረዥም መንገድ ለመሄድ ሊያስቸግራት እንደሚችል ተገልጿል።

በአጠቃላይ ለፍርድ ቤቶች በቀረበው ማስረጃም ሆነ አሁን በአጣሪ ጉባኤው በተጣራውና በተገኘው መረጃ መሠረት አመልካች የፌስቱላ ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ እንደ ሌሎች ሴቶች የግብርና ሥራን በአግባቡ ለመሥራት አስቸጋሪ እና ጉዳቱ ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ሁኔታ ሲያጋጥም ከመሬት ይዞታቸው ላይ ተፈናቅለው ለበለጠ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር እንዳይጋለጡ በማድረግ መሬቱን በማሳረስ ሊጠቀሙበት ይገባል የሚል ሃሳብ ያለው ነው።

በመሠረቱ የገጠር መሬት ይዞታ ለአርሶ አደር፣ ለአርብቶ አደር እና ለከፊል አርብቶ አደር መሰጠት እንዳለበት የሚደነግገው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌም መሠረት ያደረገው ሌላ ሥራ መሥራት የሚችሉ፣ ከግብርና ሥራ ውጪ በሌላ ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች በከተማ ሆነው የአርሶ አደርን መሬት በመያዝ ሰፊ የሆነው የሀገራችን አርሶ አደር ከሀገራዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቱ እንዳይገለል ለማድረግ ነው። ነገር ግን በአርሶ አደርነት ሥራ ተሰማርተው መኖር እየፈለጉ በበሽታና በተለያዩ ምክንያቶች አቅመ ደካማ የሆኑ አርሶ አደሮች ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል።

በተመሳሳይ ሴት አርሶ አደሮችም በግብርና ሥራ መተዳደር እየፈለጉና ለመተዳደሪያነት የገጠር መሬት ይዞታ እያላቸው በተለያዩ ምክንያቶች በተለይም ሴቶችን በብዛት የሚጎዱ እንደ ፌስቱላ ዓይነት ጉዳት ስለደረሰባቸውና የግብርና ሥራውን መሥራት ስላልቻሉ ከገጠር ይዞታ መሬታቸው እንዲፈናቀሉ ማድረግ የሕገ መንግሥቱን መርህና ዓላማ መሠረት ያደረገ አይደለም። ስለሆነም ፍርድ ቤቶች እንዲህ ዓይነት ጉዳይ ሲያጋጥማቸው በሕገ መንግሥቱ ለሴቶች የተረጋገጠውን ሕገ መንግሥታዊ መብት ሊረጋገጥ በሚችል አግባብ ውሳኔ ወይም ፍርድ መስጠት ይገባቸዋል።

ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሲሰጡ ይህንኑ ሴቶች ለበሽታው ያላቸውን ተጋላጭነትና በሽታው የግብርና ሥራ ላይ የሚኖረውን የስነ አእምሮ ችግር እና የአካል ጉዳት ከግንዛቤ ባለማስገባት ውሳኔ መስጠት ተገቢነት የለውም። ከዚህ በተጨማሪ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 41/5/ መሠረት መንግሥት የአካል እና የአእምሮ ጉዳተኞችን ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ አቅም



በፊቀደው ደረጃ እን
አካል ውሳኔ አመልካች
ዙርያ ሲያሳካው ካሰበ

ስለሆነም አመልካች የ
የአካል ጉዳት የሚያደ
ለመሥራት የማያስችል
ይዞታቸው ሊፈናቀሉ አይ

በመሆኑም ፍርድ ቤቶች
አንቀጽ 35/7 እና 40 /4/
ትርጉም ያስፈልገዋል በ
አቅርቧል።

ስለዚህ በትግራይ ክልል
አስተዳደር ኮሚቴ ክርክር ተ
ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14
ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አ
ይቃረናል በማለት ከኢፌዴሪ
ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የኢ
እንዲሰጥበት የሕገ መንግሥት

ለክርክር ምክንያት የሆነው የገ
ተወስዶባቸው ከሆነም ፍርዱን
ለአመልካች እንዲመልስላቸው የ
መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ
ሀሳብ አቅርቧል።

ስለሆነም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ በጥልቀት እና በስፋት መርምሮ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ አግባብ መሆኑን ተቀብሎ በሙሉ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል።

80

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን
# 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

**መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም**

አመልካች፡- አቶ ጀማል ሰይድ

ተጠሪ፡- አቶ ገራድ ጉዲሳ ቡሽራ

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።**

**ውሳኔ**

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ክርክርን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጉራጌ ዞን በሀሳባ ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት ነው። የጉዳዩ አመጣጥ የአሁን ተጠሪ በ26/05/2007 ዓ.ም ለሀሳባ ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት ከአመልካች ጋር በነበረን የጋብቻ ዝምድና ምክንያት በደርግ ዘመን ከታወጀው የመሬት ላራሹ አዋጅ ጊዜ ጀምሮ ስጠቀምበት የነበረውን 0.18 ሄክታር መሬት በጋራ ለመጠቀም ተስማምተንና ሰጥቻቸው ይዞታውን በስማቸው ሲያደርጉ ሲሉ ስለደረስኩ ይዞታውን እንዲለቁልኝ በማለት ክስ በማቅረባቸው ነው። አመልካችም መሬቱን ከ20 ዓመት በላይ ይዘው ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን፣ ጉዳዩም በከፍተኛ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል።

ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ላይ ካከራከረ በኋላ የኪራይ ውሉ በክልሉ የመሬት አስተዳደር አዋጅ መሠረት አለመሆኑ፣ በከፍተኛ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑና ከወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የተገኘን ማስረጃ መሠረት አድርጐ መሬቱ ለአመልካች ይገባል ብሎ ወስኗል።

ግራቀኙ ተከራካሪዎች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ይግባኝ እያቀረቡና በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች አንድ ጊዜ ለተጠሪ ሌላ ጊዜ ለአመልካች እየተወሰነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት ለተጠሪ ይገባል በማለት በመወሰኑ፣ አመልካች ለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ጊዜው በማለፉ ምክንያት ተጠሪ የአፈጻጸም መዝገብ ከፍተው ካስፈፀሙ በኋላ በአፈጻጸም መዝገቡ ላይ የታዘዘውና ውሳኔ የተሰጠበት ነጥብ ስለሚለያይ ማለትም ውሳኔ የተሰጠው በ0.18 ሄክታር ላይ ሲሆን አፈጻጸሙ ግን በ2.5 ሄክታር ላይ ነው በማለት አመልካች የስር ፍ/ቤቱን ቢጠይቁም

ፍ/ቤቱ እንደጥያቄያቸው ስላልፈፀመላቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት አመልክተዋል፡፡ ከፕሬዝዳንቱም በተጻፈ ደብዳቤ ሌላ የአፈጻጸም መዝገብ ተከፍቶ በዚህም የአፈጻጸም መዝገብ ሊፈፀም የሚገባው 0.18 ሄክታር እንጂ 2.5 ሄክታር አይደለም ተብሎ ስለተወሰነ ይህም ውሳኔ ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ በክልሉና ሰበር ሰሚ ችሎት ስነ ስርዓታዊ አካሄድ አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡

የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በአፈጻጸሙ ሳቢያ ውሳኔ ያላረፈበት ይዞታዬ አብሮ ተወስዶብኛል የሚሉ ከሆነ በዚህ ረገድ ያላቸውን አቤቱታ በዚያው የአፈጻጸም መዝገብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 349 ድንጋጌ መሠረት አቅርበው መስተናገድ ይችሉ የነበረ ከመሆኑ ውጭ በፍርድ ኃይል ተገደው ያስረከቡትን ይዞታ ከክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት በተጻፈ ደብዳቤ መነሻ አድርገው በሌላ አፈጻጸም መዝገብ መልሰው ሊረከቡ የሚችሉበት ሥነ ሥርዓት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ሰኔ 3 ቀን 2008 ዓ.ም ለፌደራል ሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ በእኔ እና በተጠሪ መካከል በነበረው የመሬት ይዞታ ክርክር አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 113960 በቀን 28/7/2008 በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከ25 ዓመታት በላይ ስጠቀምበት ከነበረው የእርሻ መሬቴ የሚያፈናቅለኝ በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የቀረበው አቤቱታ ከውሳኔው ጋር ሲመረመር ክስ የቀረበበትና ክርክር የተካሄደበት ይዞታ በአፈጻጸም ከተፈፀመው ጋር የተለየ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በዚህም መሠረት ክርክር የተካሄደበትና የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ ያረፈበት 0.18 ሄክታር መሬት ነው፡፡ ይሄው የክርክር ነጥብ በሌሎች ውሳኔዎችም ላይ የተለወጠ መሆኑ አይታይም፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያው የአፈጻጸም መዝገብ ውሳኔ ከተሰጠበት ይዞታ ጋር የተለየ ነው፡፡ ይህም በሁለተኛው አፈጻጸም ክርክር መዝገብ ላይ አልተስተባበለም /ክርክር አልተካሄደበትም/፡፡ አመልካችም ከተወሰነባቸው 0.18 ሄክታር ውጭ ያለው የእርሳቸው ይዞታ መሆኑን እና ከአራት ቤቶች በላይ የሰሩበትና ብዙ ቤተሰብ የሚያስተዳድሩበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ይኸው ጉዳይ በጽ/ቤቱ በኩል ተጨማሪ ማጣራት እንዲደረግበት ጉባኤው ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ማጣራት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የደቡብ ክልል ሀላባ ልዩ ወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጽ/ቤት በቁጥር 1048/2010 በቀን 11/04/2010 በላከው ደብዳቤ አመልካችና ተጠሪ 0.18 ሄክታር መሬት አብረው በጋራ ይጠቀሙ የነበረ መሆኑን፣ በፍ/ቤት በነበረው ክርክር ተጠሪ ክሳቸው ላይ አቅጣጫ ሲጠቅሱ የአመልካች ይዞታን ጨምረው ጠቅሰውት ስለነበር በፍ/ቤቱ ውሳኔ አመልካች ከ2 ሄክታር በላይ ከሆነው ይዞታቸው ላይ ተነስተዋል፡፡ በዚህም ውሳኔ አመልካች ከነልጆቻቸው ከይዞታቸው የተነሱና በአሁኑ ጊዜም ሌላ ይዞታ የሌላቸው መሆኑን ጽ/ቤቱ ጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች በእርሻ ስራ የሚተዳደሩ መሆናቸውንና ተጠሪ ክርክር ከተነሳበት ይዞታ ውጭ ሌላ ከ10 ሄክታር በላይ መሬት ያላቸው መሆኑን በደብዳቤው ላይ ተገልጿል፡፡ ከዚህ ማስረጃ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ክስ ሲመሰርቱ የአመልካችን የግል ይዞታ በመጨመር አቅጣጫ የጠቀሱ በመሆኑ ክርክሩ በተጨባጭ በ0.18 ሄክታር ላይ ቢሆንም የአመልካች ቀሪ ይዞታ በአፈጻጸም ወቅት የተወሰደባቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ ውሳኔ መሰረት አመልካች ከነቤተሰባቸው ከይዞታቸውና ንብረታቸው የተፈናቀሉ መሆኑና ክርክር ከተነሳበትና በውሳኔው ከተወሰደባቸው ይዞታ ውጭ ሌላ ይዞታም አለመኖሩን ተረድተናል፡፡

ስለሆነም በመጀመሪያው የአፈጻጸም መዝገብ ላይ የሚስተዋለው ችግር ፍ/ቤቱ በስነ ስርዓት ህጉ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉንና በተጨባጭ ያለውን ሀቅ ወደ ጎን በመተው ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡ ውሳኔውም አርሶ አደርን ከህግ ውጭ ከይዞታው የሚነቅልና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 ጥበቃ የተደረገለትን ከይዞታ መሬት ያለመነቀል ሕገ መንግስታዊ መብት የሚነፍግ መሆኑን ያሳያል፡፡

ስለዚህ የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ሲል ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአዋጅ ቁጥር 798 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለመጨረሻ ውሳኔ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ በሕገመንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩ ታይቶ እንዲቀርብ መርቶት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የጉዳዩ መነሻ የእርሻ መሬት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተከራካሪ ወገኖች ተከራክረው በፍ/ቤት ውሳኔ የተሰጠበትና በአፈጻጸም የአሁን ተጠሪ ሊረከቡት የሚገባ 0.18/ዜሮ ነጥብ አስራ ስምንት/ ሄክታር መሬት ላይ መሆን ሲገባው በተፈጠረው የአፈጻጸም ስህተት የአሁን አመልካች ቤተሰቦቻቸውን ይዘው የሚተዳደሩበትንና ውሳኔ ያልተሰጠበትን የእርሻ መሬት ጨምሮ ጠቅላላ 2.5/ሁለት ነጥብ አምስት/ ሄክታር በአፈጻጸም እንዲያስረክቡ መደረጉ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ስለሆነ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ወስኗል።

## ትእዛዝ

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ስለሚቃረን ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት ምክር ቤቱ የወሰነ ስለሆነ በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ይተላለፍላቸው፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለባለጉዳዩ ይሰጥ።
3. የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይላክ።

21

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ 4ኛ ዓመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ
ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

የመ/ቁ. 64/10

አመልካች፡- ወ/ሮ ፋንታዬ ሌጂሳ

ተጠሪ፡- አቶ አዱኛ ደምሴ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በዳዎ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የጉዳዩ ይዘትም ተጠሪ ከአባቴ በውርስ ያገኘሁትን መሬት በ2004 ዓ.ም በጉልበት ስለያዘብኝ እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን በሰጡት መልስ ለክርክር መነሻ የሆነውን መሬት ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ለ24 ዓመታት ይዤ እየተጠቀምኩበት ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ አመልካችም ልትጠይቀኝ አትችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት የአሁን አመልካች አባት መሬት እንደሆነና አመልካች በ1998 ዓ.ም በውርስ ክርክር ወንድሟን ከሳ በእጅ አስገብታ ከተጠሪ ጋር በ2001 ዓ.ም መሬት ተቀያይረው ስትጠቀምበት ከቆየች በኋላ አመልካች የተጠሪን መሬት እንደመለሰችለትና ተጠሪ ግን የአመልካችን መሬት አልመልስም ብሎ ይዞ እንደሚገኝ የአመልካች ማስረጃ ማረጋገጡን ገልጿል፡፡

በሌላ በኩል የተጠሪ ማስረጃዎች ደግሞ አንዱ ምስክር ተጠሪ መሬቱን በ1982 ዓ.ም እንደያዘ ሌላው ደግሞ ተጠሪ መሬቱን በ1998 ዓ.ም እንደያዘው መስክረዋል፡፡ በተጨማሪም ጉዳዩን ከወረዳው መሬት አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃ ለማጣራት በታዘዘው መሰረት ፅ/ቤቱ ከአካባቢው ሽማግሌዎች ቃል ሰምቶ እንደ መለሰና በይዞታው ላይ ማን የይዞታ ማረጋገጫ እንዳለው ማወቅ እንዳልተቻለ በመግለፅ መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ተጠሪ የያዘው የመሬት ይዞታ የአመልካች አባት ይዞታና በውርስ ያገኘችው መሆኑ ስለተረጋገጠ ተጠሪ ይዞታውን ሊለቅ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ክሷን ስታቀርብ ተጠሪ በ2004 ዓ.ም መሬቱን በጉልበት እንደያዘባት ብትገልጽም የቀረቡት ማስረጃዎቿ ግን ይህን ጭብጥ ስላላረጋገጡ ተጠሪ መሬቱን ሊለቅ አይገባም በማለት የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

የአሁኗ አመልካች በውሳኔው ላይ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ መነሻው የአመልካች አባት ይዞታ የነበረ፣ አመልካች አባቷ ከሞቱ በኋላ የአሁኑን አንድ ቀርጥ መሬት ጨምሮ ሌላ 3 ቀርጥ መሬት ላይ በፍ/ቤት ከወንድሞቿ ጋር ተከራክራ በ1998 ዓ.ም ተወስኖላት እስከ 2004 ዓ.ም በይዞታው ስትጠቀምበት ከቆየች በኋላ ተጠሪ የያዘባት ለመሆኑ ቀድሞ ውሳኔ ካገኘው የፍ/ቤት ውሳኔና አመልካች ካቀረበችው የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሁም ሌሎች ማስረጃዎች መገንዘብ መቻሉን ገልጿል፡፡

በሌላ በኩል ግን የተጠሪ ክርክር ያተኮረው ይዞታውን ከ1982 ዓ.ም አንስቶ መያዙን በመግለፅ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ከሚል በቀር ቀድሞ ይዞታው የእርሱ መሆኑን እና እንዴት እና ከማን እንዳገኘው ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ የቀረቡት የአይን ምስክሮችም ተጠሪ ይዞታውን የያዘበት ጊዜ በትክክል ስላላረጋገጡ እና ተጠሪ በይዞታው ላይ ያቀረበው የይዞታ ማረጋገጫ ስለሌለ ተጠሪ ለአመልካች ይዞታውን ሊለቅ ይገባል በማለት የዞኑን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች መጀመሪያ ክሷን ስትመሰርት ተጠሪ በ2004 ዓ.ም በጉልበት ይዞታዬን ወስዶብኛል የሚል ጭብጥ አቅርባለች፡፡ አመልካች ይህን ጭብጥ በምስክሮች ሳታረጋግጥ ወደ ተጠሪ ማስረጃ ታልፎ የተጠሪ ማስረጃ የሚተችበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ ተጠሪ ለአመልካች ይዞታውን መልቀቅ አይገባውም በማለት የጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር የዞን ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች ለአጣሪ ጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ዋና ቅሬታቸው ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ የአባቱ መሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 7 ላይ የተረጋገጠውን መብት በሚቃረን መልኩ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ኢ-ሕገ መንግስታዊ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለጉባኤው ያቀረቡት አቤቱታ ከፍ/ቤቶቹ ውሳኔና አመልካች ከጠቀሷቸው የሕገ መንግስቱ አንቀጾች ጋር ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔን የሕግ ስህተት የለውም በማለት ያለፈው መሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ለክርክር መነሻ የሆነው የገጠር ይዞታ መሬት ከመነሻው የአመልካች አባት ይዞታ እንደሆነ እና ይህንኑ መሬትም አመልካች በፍርድ ቤት ከወንድሞቿ ጋር ተከራክራ በውሳኔ ያገኘች መሆኑ፣ በይዞታው ላይም አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዳላት ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራት ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነው፡፡

ስለዚህ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ በትዕዛዝ ተዘግቶ የተሰጠው ውሳኔ ከላይ ከተጠቀሱት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር ስለሚቃረን ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባኤው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት የሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና የምክር ቤቱ ባለሙያዎች አስተያየትን በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውንና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡በዚህም መሰረት የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ አከራካሪው መሬት የአመልካች አባት እንደሆነ እና አመልካች በ1998 ዓ.ም በውርስ ክርክር ወንድማቸውን ከሰው በእጅ ካስገቡ በኋላ ከተጠሪ ጋር በ2001 ዓ.ም መሬት ተቀያይረው ሲጠቀሙበት ከቆዩ በኋላ አመልካች የተጠሪን መሬት እንደመለሱለትና ተጠሪ ግን የአመልካችን መሬት አልመልስም ብሎ ይዞ እንደሚገኝ የአመልካች ማስረጃ የሚያረጋግጥ መሆኑን፣ በሌላ በኩል ተጠሪ መሬቱን በ1982 ዓ.ም እንደያዘ ገልጾ ቢከራከርም የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ መሬቱን የያዘው በተለያየ ጊዜ መሆኑን መመስከራቸው ሲታይ የአመልካች ማስረጃ በተሻለ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ አከራካሪውን ይዞታ ለአመልካች እንዲለቅ ብሎ መወሰኑ ባግባቡ ሲሆን የዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት ግን ተጠሪ አከራካሪውን መሬት የአመልካች አባት ካረፉ በኋላ እና እናቷ በህይወት እያሉ ከ1982 ዓ.ም አንስቶ እስካሁን ይጠቀምበት ነበር በማለት ተጠሪ መሬቱን ሊለቅ አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ያሳለፈውና በሰበር ችሎቶች የፀናው ውሳኔ ሲታይ አመልካች በፍ/ቤት ውሳኔ ያገኙትን የንብረት መብት የሚጥስ ውሳኔ ሆኖ የተገኘ በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤውና ቋሚ ኮሚቴው ያቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጡት ውሳኔ በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(4) እና(7) ድንጋጌዎችን የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች የሰጡት ውሳኔ በምክር ቤቱ የተሻረ መሆኑን አውቀው በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽሙ የውሳኔው ግግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካቹ ይሰጥ፡፡

ፀ2

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የ/መ/ቁ. 101/13

አመልካች፡- አቶ ቦርጩ ገናኖሬ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ብጹአን አማረ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሀሴ 19 ቀን 2009ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ጉዳዩ የከተማ ቦታ ምትክ መሬትና የካሳ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ከሳሽ በመሆን በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በሃድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡የክሱ ይዘትም በአጭሩ 67 ቆርቆሮ ቤትና የተለያዩ አትክልቶች ያሉበት የግል ይዞታዬን መንግስት ልማት ምክንያት ወስዶ ለአሁን ተጠሪ ሰጥቷል ፡፡ሆኖም በህጉ መሰረት ምትክ ቦታ እና ተገቢው ካሳ ስላልተከፈለኝ የቤቱንና የአትክልቶቹን ግምት በድምሩ ብር 585,000.00 (አምስት መቶ ሰማንያ አምስት ሺ) ብር እንዲከፈለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን በሰጡት መልስ ከመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተጨማሪ አመልካች በይዞታው ላይ የነበረውን የቤት ቆርቆሮ አራሳቸው አፍርሰው የሸጡ በመሆኑ አትክልቶቹንም ሸጠው የሄዱ መሆኑን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

የሃድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎችን ከመዘነ በኋላ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች በአካል ባለመኖራቸው ምክንያት መገመት እንዳለተቻለ ጠቅሶ የካሳ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ይህ ውሳኔ ቀጥሎ ባሉት ፍ/ቤቶች ከፀና በኃላ የለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩን በሰበር አቤቱታ ተመልክቶ እና መርምሮ ውሳኔ በመስጠት ጉዳዩ ተመልሶ በስር ፍ/ቤት እንደገና እንዲታይ ሲል ወስኗል፡፡ለውሳኔውም መሰረት የሆነው የህግ ጭብጥ በወረዳም ሆነ በከተማ አስተዳደር ለህዝብ ጥቅም ሲባል በመንግስት አካላት ለግል ባለሀብቶች ወይም በህጉ ላይ ለተጠቀሱት ሌሎች አካላት ቦታ ሲለቀቅ በቅድሚያ ካሳ እንዲከፈል በማድረግ የማስለቀቅ ስልጣን ያለው የመንግስት አካል ስለመሆኑ ተደንግ1ል፡፡በአዋጅ ቁጥር 455/2007 አንቀፅ10(1) እና (2)፣11(1) እና (2) መሰረት በገጠር ወይም በከተማው አስተዳደር በሚቋቋምና ተገቢው ሙያ ባላቸው ኮሚቴ ንብረቱ ተገምቶ ካሳው መከፈል እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ የህጉ ድንጋጌ መሰረት አሁን በክርክር ላይ ባለው ጉዳይ ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት የሚገኘው በከተማ ይሁን በገጠር ሳይጣራ ፣አመልካች ጉዳያቸውን ለሚመለከተው አስተዳደር አካል ማቅረብ አለማቅረባቸው ሳይረጋገጥ፣ያላቀረቡም ከሆነ በምን ምክንያት ማቅረብ እንዳልቻሉና በተጨማሪም በክርክር ውስጥ ተካፋይ መሆን ያለባቸው አካላት በመጥራት እነዚህን ነጥቦች ካጣራ በኃላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ ውሳኔ መስጠት ይገባዋል በሚል ነጥብ ነው፡፡

ጉዳዩ በነጥብ የተመለሰለት የሃድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚሁ በሰበር ሰሚ ችሎት ትእዛዝ መገገቡን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 455/2007 መሰረት አመልካች በልማት ምክንያት ለተወሰደባቸው መሬት ምትክ መሬት ለማግኘትም ሆነ የካሳ ጥያቄ ማቅረብ ያለባቸው ወይም ጉዳዩ እልባት ሊያገኝ የሚገባው በአስተዳደር ክፍል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ዘግቷል፡፡ ውሳኔው እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በየደረጃው ላሉ ፍ/ቤቶች ቀርቦ አያስቀርብም ተብሎ ተዘግቷል፡፡

አመልካች ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ ዋና ቅሬታቸው ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት በ1989 ዓ.ም በልማት ምክንያት ሲወሰድብኝ የአሁን ተጠሪ በመሬቱ ላይ የነበረውን ቆርቆሮ ሲፈርስ ወስደውብኛል፡፡ መሬቱ ከተወሰደበት ማለትም ከ1989 ዓ.ም አንስቶ እስከ 2000ዓ.ምድረስ ለቀበሌውና ለከተማ ማዘጋጃ ቤቱ በተደጋጋሚ አመልክቼ መፍትሄ በማጣቴ በ2000ዓ.ም አቤቱታዬን ለመደበኛ ፍ/ቤት አቀረብኩ እስካሁንም መፍትሄ አላገኘም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲመልስ ቀድሞ በዚህ ጉዳይ ለሚመለከተው አስተዳደር መስሪያ ቤት ማመልከት አለማመልከቴ ተጣርቶ ውሰኔ እንዲሰጥ ነበር ነገር ግን ፍ/ቤቱ ይህንን በአግባቡ ሳያጣራ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም

በማለት ውሳኔ መስጠቱ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠውን ፍትህ የማግኘት መብቴን የሚጥስ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤውም አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ከፍርድ ቤቶች ውሳኔ ፣ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህጎችና ከሕገ መንግስቱ ፍትህ የማግኘት መብት አንፃር መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ውስጥ በዋነኝነት መፍትሄ ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች ፦

1. አመልካች በ1989 ዓ.ም የነበራቸው መሬትና በመሬቱ ላይ የነበራቸው ቤትና ሌሎች አትክልቶች በልማት ምክንያት እንበተወሰደባቸው ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል ወይስ አላረጋገጡም?
2. በነጥብ አንድ ላይ የተቀመጠው ፍሬ ነገር በፍ/ቤቶች ተረጋግጦ ከሆነ አመልካች በልማት ምክንያት በተወሰደባቸው ቦታ ሌላ ምትክ ቦታና ካሳ ማግኘት ነበረባቸው ወይስ አልነበረባቸውም?
3. አመልካች የምትክ ቦታ አቤቱታቸውን በሕግ አግባብ ማቅረብ የነበረባቸው ለየትኛው የመንግስት አካል ነው? የሚለው ነው፡፡

አመልካች በ1989 ዓ.ም የነበራቸው የመሬት ይዞታ እና በይዞው ላይ የነበረው 67 ቆርቆሮ ቤትና አትክልቶችየፈረሰባቸውና የወደመባቸው መሆኑን የሃድያ ወረዳ ፍ/ቤት ለአመልካች ተጽፎ ከነበረው የድጋፍ ደብዳቤ መረጋገጡን፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች ይዞታ፣ቤትና አትክልቶች በልማት ምክንያት የወሰደባቸው መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ በአግባቡ በፍርድ ቤት ተለይቶ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑን፡፡

የሚቀጥለውን ጭብጥ በሚመለከት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 (8) መሰረት፦ መንግስት ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከግለሰቦች የመሬት ይዞታን ሲወስድ ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያ በቅድሚያ ሊከፍል እንደሚገባ የተደነገገ መሆኑን፡፡ በተመሳሳይ በአዋጅ ቁጥር 455/2007 አንቀፅ 3 (1) በልማት ምክንያት የሚወሰዱ ይዞታዎችን በሚመለከት መሬቱን የሚወስደው የክልል ወይም የፌዴራል መንግስት የበላይ አካል በቅድሚያ ካሳ እንዲከፍል በማድረግ መሬቱን ማስለቀቅ እንዳለበት መደንገጉን፡፡

ከዚህ የአዋጁ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው በሕገ መንግስቱ የተደነገገው ካሳብ በቅድሚያ መክፈል የመንግስት ግዴታ መሆኑን ነው፡፡ይህ ድንጋጌም የራሱ የሆነ ሰፊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ያሉት ነው፡፡በተለይም አንድ ሰው የራሱ የነበረውን ንብረት በሚለቅበት

ጊዜ ሌላ ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ችግር እንዳየደርስበትና እራሱን በቅድሚያ እንዲያቋቁም ለማደረግ ነው፡፡

ይህንን የመንግስት ሀላፊነት በሚመለከት አመልካች ከ1989 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ምትክ ቦታ እና ካሳ እንዲከፈላቸው አቤቱታ አቅረበው መልስ ያላገኙ መሆኑን ቀበሌው ለከተማው ማዘጋጃ ቤት ከፃፈውና በፍ/ቤቱ መዝገብ ላይ ከሰፈረው ማስረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ አግባብ ለክርክሩ ጭብጥ አድረጎ ጉዳዩን መመርመር የነበረበት የካሳ ግምት ባልተሰራበት ሁኔታ አመልካችም ይህንኑ ጠይቀው መልስ ካላገኙ ለማን አቤቱታ ማቅረብ ይጠበቅባቸውል? እንዲ አይነት ክርክር የማየት ስልጣን የፍ/ቤቱ መሆን አለመሆኑን መመርመር ሲገባው የሚከፈለው የካሳ መጠን እንደተገመተ በመውሰድ በካሳ ግምት መጠን ላይ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ክፍል መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠቱና ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱ አላግባብ ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መጀመሪያ ወደ ዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲመልሰው ይህንን ጉዳይ እንዲጣራ አዞ የነበረ ቢሆንም ሰበር ሰሚ ችሎቱ ክርክሩ ተመልሶ ሲመጣለት ግን ለምን ጉዳዩ ሳይጣራ እንደተወሰነ ሳያረጋግጥ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡በዚህ ምክንያት አመልካች ከላይ በተገለፀው አግባብ ማግኘት የነበረባቸውን ሕገ መንግስታዊ ፍትህ ሳያገኙ ቀርተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር እንደተቀመጠው አመልካች በህገ መንግስቱና በህግ የተቀመጠላቸውን መብት ሳያገኙ የቀሩት የሚመለከተው የመንግስት አካል ሃላፊነቱን ባለመወጣቱ ሲሆን ይህንንም ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በአግባቡ መርምረው ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማረጋቸው ሕገ መንግስታዊ ፍትህ የማግኘት መብታቸውን በእጅጉ የጣሰና አላግባብ ለረጅም ጊዜ የፍርድ ቤት ክርክር ውስጥ እንዲገቡ ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት በሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጀምሮ እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሰውና በመጨረሻ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 140503 በቀን 30/09/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ1 እና 40 ንዑስ አንቀጽ 8 የሚጥስ ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ውሳኔው ተፈፃሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣1ኛ ዓመት፣3ኛ መደበኛ ስብሰባ

ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ.ም

አመልካቾች እነ ወ/ሮ ብርቄ ለገሰ

ተጠሪዎች 1.ብላክ ዳይመንድ ኃ/የተ/የግል ማህበር

2.ቦሌ ክ/ከተማ፣የወረዳ 11 አስተዳደር

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካቾች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

## ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ ከመሬት ይዞታ መፈናቀልን የሚመለከት ሆኖ ለምክርቤቱ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ለፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሚያዝያ 24 ቀን 2006 ዓ.ም ጽፈው ባረቡት ማመልከቻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በመ፣ቁ.203179 የሰጠውና በይግባኝ ሰሚ ፍርድቤቶች የጸናው ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተውን ድንጋጌ የሚጥስ ስለሆነ የሕገመንግስት ትርጉም ይሰጥልን በማለት በማመልከታቸው ጉባኤው ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሀሳብ በማቅረቡ ነው፡፡

የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካቾች ሚያዝያ 24 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 203179 የሰጠውና በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የፀናው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 የተመለከተውን ድንጋጌ የሚጥስ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልን

በማለት አመልክተዋል፡፡ የጉዳዩም ፍሬሃሳብ የአሁን አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ከሳሽ በመሆን በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ ከአያት ቅድመ አያት ጀምሮ በዘር ሀረግ በመተካካት ይዘነው በእርሻ መጠቀሚያነት የምንገለገልበትን በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ክልል የነበረ የእርሻ ይዞታ መሬት የመንገዶች ባለስልጣን መ/ቤት ለልማት ስራ በእርሻ ይዞታው ላይ ያለውን የድንጋይ ምርት ተጠቅሞ ድንጋዩን ከጨረሰ በኋላ ይዞታውን አፈር ሞልቶ ባለመመለሱ እኛ አፈር ሞልተን ለማልማት ዝግጅት ላይ እያለን 1ኛ ተጠሪ ካሣ ሳይከፍል ወይም ምትክ ቦታ ሳናገኝ ማዕድን ለማውጣት ፈቃድ አለኝ በማለት በይዞታው ላይ ሁከት ፈጥሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ይዞታው የራሳችን መሆኑን እያወቀ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ሕጋዊ እርምጃ አልወሰደም በማለት የሁከት ይወገድልን ክስ አቅርበዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በበኩሉ መልስ ሲሰጥ አመልካቾች የመሬት ይዞታው በዘር ሀረግ በመተካካት አገኘን ከማለት ውጪ መሬቱ የራሳቸው ስለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ የላቸውም፡፡ 2ኛ ተጠሪም በ1ኛ ተጠሪ ድርጊት አስፈላጊውን እርምጃ አልወሰደም ከማለት በስተቀር ሁከት መፍጠሩን ስላልገለፁ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት የመጀመሪያ መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ 2ኛ ተጠሪ በሃይል ወይም በሌላ ሁኔታ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር አመልካቾች ይዞታ ላይ ሁከት ማድረጉን ክሱ ስለማያስረዳ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ በመሬት ይዞታው ላይ ማዕድን የማውጣት ስራ ከመጀመሩ በፊት የመሬት ይዞታው በአመልካቾች እጅ ያልነበረ በመሆኑ አመልካቾች ክስ ለማቅረብ መብትና ቅጥም የላቸውም በማለት የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ በአጭሩ እንደተገለጸው ሲሆን ለክርክሩ መነሻ በሆነው የመሬት ይዞታ ላይ የአመልካቾች መብት እስከየት ነው የሚለውንና በመሬት ይዞታው ላይ ባለመብት ከሆኑ ደግሞ ሕገ-መንግስታዊ መብታቸው ተጥሷል ወይ የሚለውን ነጥብ ጉባኤው መርምሯል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካቾች ዋና ጥያቄ የመሬት ይዞታው ከአያት ቅድመ አያቶቻችን ተላልፎልን ባለመብት ሆነን እያለን የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ከይዞታው ላይ ለግንባታ ሥራ የሚያገለግል ድንጋይ ሲያወጣ ቆይቶ ስራውን ከጨረሰ በኋላ ይዞታው ተመልሶልን እያለ 1ኛ ተጠሪ ማዕድን የማውጣት ፍቃድ አለኝ በማለት በሕገወጥ መንገድ ይዞብናል፡፡ ካሣም ሆነ ምትክ የእርሻ መሬት አልተሰጠንም የሚል ነው፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ለክሱ መልስ ሲሰጥ የአሁኑ ተጠሪዎች ጉዳዩ በአስተዳደራዊ መንገድ እንዲታይላቸው



21

በጠየቁን መሰረት ስናጣራ አውራ ጎዳና ቦታውን ለልማት ፈልጎት ሲጠቀምበት ቆይቶ ከጨረሰ በኋላ ለአርሶ አደሮች ማስረከብ ሲገባው ጥሎ ሲሄድ ለአመልካቾች ምንም ዓይነት ካሣ ሳይከፍላቸው 1ኛ ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ይዟል፡፡ ለዚህም 1ኛ ተጠሪ በተለያዩ ጊዜያት ይዞታውን ለአሁን አመልካቾች እንዲለቅ ለአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ደብዳቤ ብንፅፍም እልባት ሊያገኝ አልቻለም በማለት ገልፆአል፡፡

አመልካቾች አሁን ክርክር ያስነሳው መሬት የኛ መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች በማለት ያቀረቧቸው ሰነዶች፡-

1. ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ እስከ 2004 ዓ.ም በተለያዩ ጊዜያት ግብር የከፈሉበት 5 ገጽ ደረሰኞች፡

2. የአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ማለትም የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በቁጥር በቦ/ክ/ከ/ወ/11/0/2/153/04 በቀን 26/8/2004 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ የአሁኑ አመልካቾች ይዞታ እንደነበርና አውራ ጎዳና ለልማት ሲባል በፈቃደኝነት ድንጋይ ሲያወጣ ቆይቶ ስራውን ከጨረሰ በኋላ ትቶ ሲሄድ የአሁኑ 1ኛ. ተጠሪ ያለ አግባብ በጉልበት ገበሬዎቹን በማስፈራራትና በተለያዩ ጊዜያት በማሳሰር ከወረዳው አስተዳደር እውቅና ውጪ በይዞታው እየተጠቀመ እንደሚገኝ ገልፆአል፡፡

3. የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በቁጥር ቦ/ክ/ከ/ወ/11/0.2/957/05 በቀን 01/06/2005 በተፃፈ ደብዳቤ ክርክር የተነሳበት የመሬት ይዞታ የአሁኑ አመልካቾች በአፅመ-ርስትነት ከቤተሰቦቻቸው ያገኙና አሁን ደግሞ በእነሱ እጅ ያለ ግብር እስከ 2004 ዓ.ም. የገበሩበት ቦታ ቀደም ሲል አውራ ጎዳና ለልማት ፈልጎት እያለም አመልካቾችም ጠጠር በመፍጨት ሲጠቀሙበት ኖረው መ/ቤቱ ስራውን ጨርሶ ለቆ ሄዷል፡፡ ግለሰቦች ከይዞታው ላይ ማዕድን የማውጣት ስራ እየሰሩ ስለሆነ ቦታው ከባድ ድልድይ የሚያልፍበት በመሆኑ መልሶ በአፈር ሞልቶ ማልማትን



20

ስለሚጠይቅ ይዞታውም የአመልካቾች መሆኑን ስላረጋገጥን ቦታውን መልሶ አፈር በመሙላት እንዲያለሙ ቢፈቀድላቸው የሚል ድጋፍ ደብዳቤ ፅፎል፡፡

4. በደብዳቤ ቁጥር በቦ/ክ/ከ/ወ/11/0/2/888/2005 በቀን 23/4/2005 ዓ.ም. የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ለአ/አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በፃፈው ደብዳቤ ብላክ ዳይመንድ የተባለ ድርጅት የጠጠር ድንጋይ ማምረት ሥራ የፈቃድ ጊዜው በ2005 ዓ.ም. የሚያበቃ በመሆኑና ቦታው የቦሌ ለሚ ዞን የአስፋልት መንገድ ከባድ ድልድይ ስላለ ሥራው በቀጣይነት ቢሰራ በድልድዩ ላይ ጉዳት ስለሚያድርስ ፍቃድ እንዳይታደስለት በማለት ገልፆል፡፡

5. የወረዳ 11 የወጂ አካባቢ የሀገር ሽማግሌዎችና የአካባቢ ኮሚቴዎች የጋራ ስብሰባ በ08/04/05 በተፃፈ ቃለ ጉባኤ ክርክር የተነሳበት ቦታ የአሁኑ አመልካቾች መሆኑን አረጋግጦ አመልካቾች ካሣ ያልተከፈላቸው ወይም ምትክ የእርሻ ቦታ ያልተሰጣቸው መሆኑን አረጋግጦ በቃለ ጉባኤው ላይ አምስት ሰዎች የፈረሙበትን አያይዘዋል፡፡

6. የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ዋና ሥራ አስፈፃሚ በቁ.ቦ/ክ/ከ/ወ.11/29/07 በቀን 15/11/2007 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ አሁን ክርክር የተነሳበት የመሬት ይዞታ የአመልካቾች መሆኑን እና በስማቸውም ግብር እየተገበረበት መሆኑን አረጋግጦ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ስንመለከት ክርክር የተነሳበት የመሬት ይዞታ ለአመልካቾች ከወላጆቻቸው ተላልፎ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑንና የመንገዶች ባለሥልጣን በመሀል ከይዞታቸው ላይ ድንጋይ ለማውጣት ፈልጎ በፈቃደኝነት ስራውን ጀምሮ የሚፈልገውን ያህል ተጠቅሞ ከጨረሰ በኋላ ለአመልካቾች ትቶ መሄዱን አመልካቾች ከአቤቱታቸው ጋር አያይዘው ካቀረቧቸው ሰነዶች መረዳት ይቻላል፡፡ 2ኛ ተጠሪ የቅርብ የመንግሥት አስተዳደር አካል እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ በተለያዩ ጊዜያት ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አረጋግጧል፡፡ በፍ/ቤቱም ተከሶ መልስ ሲሰጥ ይህንኑ አጠናክሮ



19

ገልጧል፡፡ የ1ኛ ተጠሪን ሕጋዊነት 2ኛ ተጠሪ አለማወቁንና ለአመልካቾች በይዞታው ላይ በመንግሥት መመሪያ መሰረት የሚገባቸው ካሳ ወይም ምትክ የእርሻ መሬት ያልተሰጣቸው መሆኑንም መስክሯል፡፡ በጉዳዩ ላይ በፍ/ቤቱ የተሰጠ ውሳኔን ስንመለከት አመልካቾች ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብትና ምክንያት የላቸውም የሚል ነው፡፡ ነገር ግን የቅርብ የመንግሥት አስተዳደር አካል ይዞታው የአመልካቾች ነው ብሎ የሚሰጠው ማረጋገጫ ከውሳኔው ጋር ይጋጫል፡፡

የመሬት ይዞታው የአመልካቾች መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ መንግሥት መሬቱን ለሌላ ልማት ከፈለገው ወይም ለሌላ አልሚ አካል ሲያስተላልፍ ለአመልካቾች ተገቢው ካሳ ሊከፈል ወይም ምትክ የእርሻ መሬት ሊሰጣቸው ይገባ ነበር፡፡ ይህ አለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብት እንዳላቸው የሚደነግገውንና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ እንደሚችል የሚደነግገውን ይቃረናል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው መሆኑን ጉባኤው በሙሉ ድምፅ የተስማማ ሲሆን ይህ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው ጉዳዩን ለማጣራት እንዲቻል ክርክር የተነሳበትን መሬት አጠቃላይ ሁኔታ ለማወቅ ከሚመለከተው የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ማስረጃ እንቀርብ ተደርጎ በቁጥር ቦ/ክ/ከ/ወ.11/ 856/08 በቀን 28/08/2008 ዓ.ም በተጻፈ ማስረጃ ክርክር የተነሳበት ይዞታ መሬት የወ/ሮ ብርቄ ለገሰ ሆኖ የቦታ ስፋት 20161.21 ሜትር ካሬ ሲሆን በአዋሳኝ በሰሜን መንገድ፤ በደቡብ ወሰኔ የሱፍ፤ በምእራብ ይገዙ ቢራ እና በምስራቅ መንገድ መካከል የሚገኝ እንደሆነ እንዲሁም የአቶ ይገዙ ቢራ ይዞታ ስፋት 23368.24 ሜትር ካሬ ሲሆን አዋሳኙ በሰሜን መንገድ፤ በደቡብ ወሰኔ የሱፍ፤ በምስራቅ ብርቄ ለገሰ እና በምዕራብ ሀይሉ ካሳ መካከል እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡



18

በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ለአመልካቾች ተገቢውን ካሳ ሳይከፍል ወይም ምትክ የእርሻ መሬት ሳያገኙ ይዞታቸውን የያዘ መሆኑን እና የመሬት ይዞታውም የአመልካቾች ስለመሆኑ በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጦ እያለ እና ሁለተኛው ተጠሪ የወረዳው የመንግስት አስተዳደርም ይህንኑ አረጋግጦ እያለ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በሃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በአመልካቾች ይዞታ ላይ ሁከት መፈጠሩን ክሱ ስለማያስረዳ እና 1ኛ ተጠሪ በመሬቱ ላይ ማዕድን የማውጣት ስራ ከመጀመሩ በፊት የመሬት ይዞታው በአመልካቾች እጅ ስላልነበረ አመልካቾች ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት የሰጠውና በይግባኝ ሰሚ ፍርድቤቶች ጸንቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ስህተት አልተሰራበትም በማለት የተሰጠው ውሳኔ የኢፌዴሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4 አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት እንዳላቸው ከሚደነግገውንና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ ቅድሚያ መከፈል እንዳለበት ከተደነገገው ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም ምክርቤቱ አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በሚል ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተቀብሎ ከላይ እንደተገለጸው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት የተሰጠውና በይግባኝ ሰሚ ፍርድቤቶች የጸናው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ጥሰት ያለበት እና የአመልካቾችን ሕገመንግስታዊ የመሬት የይዞታ መብት የሚጥስ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም። አመልካቾች ክርክር በተነሳበት የይዞታ መሬታቸው ላይ ያላቸው ሕገመንግስታዊ መብት ሊጠበቅላቸው ይገባል በማለት በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

## ትዕዛዝ

በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት የተሰጠውና በየደረጃው በሚገኙ የፌዴራል ፍርድቤቶች የጸናው ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገ ስለሆነ የሚመለከታቸው በዚሁ መሰረት እንዲያስፈጽሙ ታዟል።

የምክርቤቱን ውሳኔ እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤቶች እንዲደርሳቸው ይደረግ።

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡

የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዎችም ይሰጥ፡፡

16

96

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ. 98/13

አመልካች ፡- አቶ ድሪባ ገላ

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ በቆጂ ነጌሶ ቀ/ገ/ማህበር

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ የሲሙና ቢልቢሎ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት

2ኛ የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት

አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን በቆጂ ከተማ 01 ቀበሌ

የ.ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሃሴ 9 ቀን 2009 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

አቤቱታውም በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ አስተዳደር አመልካች የእርሻ መሬታቸው እና በመሬቱ ላይ ያለውን ቋሚ ንብረቶችን ለሃይማኖት ተቋም እንዲለቁ የወሰነው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 136999 የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ከይዞታቸው ያለመፈናቀል እና ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብታቸውን ይጥሳል የሚል ነው፡፡

አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ፅፈው ባቀረቡት ክስ የአሁን ተጠሪዎች 1.20 ሄክታር የሚሆን የመሬት ይዞታዬን ከኔ ፈቃድ ውጭ ለሀይማኖት ተቋም እንድለቅ ወስነው በተለያየ ጊዜ ደብዳቤ ጽፈውልኝ እንድለቅ አስገድደውኛል፡፡ አመልካችም በተጠሪዎች ውሳኔ ቅር

በመሰኘት ለ1ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት እና ለዞን አስተዳደር ጽ/ቤት አመልክቻለሁ። ይሁን እንጂ ቅሬታዬን ባለመቀበል 2ኛው ተጠሪ በቀን 30/01/2007 ዓ.ም ብር 235.000.00 /ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ሺ / ካሳ ተቀብዬ የመሬት ይዞታዬን ለቅቄ የመሬት ባለቤትነት ማስረጃዬን እንድመልስ መኖሪያ ቤቴ ላይ ደብዳቤ በመለጠፍ እያስገደዱኝ ነው። ስለሆነም ተጠሪዎች ለወሰዱብኝ የመሬት ይዞታ ሌላ ምትክ መሬት እንዲሰጡኝና የይዞታ ማፈናቀያ ካሳ ግምት ብር 683.840.000 /ስድስት መቶ ሰማንያ ሶስት ሺ ስምንት መቶ አርባ ብር /እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል።

ተጠሪዎቹም ለአመልካች ክስ በሰጡት መልስ የአመልካች ይዞታ በህግ መሰረት ለህዝብ ጥቅም ተወስዶ ብር 235.000.00 ካሳ ተገምቶላቸው ብሩ ባንክ ገብቶላቸዋል። በቀረበላቸው የካሳ ግምት ላይ ቅሬታ ካላቸው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀፅ 3 እና11/2 መሰረት ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሳያቀርቡ ጉዳዩ በቀጥታ ለፍ/ቤት መቅረቡን እንቃወማለን በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል። በዋና ፍሬ ጉዳይ ላይም የአመልካች የመሬት ይዞታ በአዋጅ ቁ. 455/97 መሰረት የካሳ ግምት በመወሰን መሬቱ የተወሰደ እንጂ ከሕግ ውጭ የተወሰደበት አይደለም ኮሚቴው የገመተላቸው የካሳ ግምት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዝግ ሂሳብ ቁጥር 1000131572682 ገቢ ቢሆንላቸውም አመልካች የራሳቸውን ግምት በማቅረብ ለመውሰድ ፍቃደኛ ስላልሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል።

ከፍተኛው ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ.455/97 አንቀፅ 11 ንዑስ 2 እና 4 የተቀመጠውን ሁኔታዎች ሳያሟላ በፍ/ቤት ክስ መመስረት ተገቢ አይደለም ፣ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የአመልካችን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ወስኗል።

በአመልካች ቅሬታ አቅራቢነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ አመልካች በ15/10/2007 ዓ.ም ለሴሙና ቢልቢሎ ወረዳ የመሬት አስተዳደር እና በ19/12/2007 ዓ.ም ለአርሲ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ቅሬታቸውን በቅድሚያ ያቀረቡ መሆኑን እየታወቀ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ስልጣን የለኝም ሲል መወሰኑ አግባብነት የለውም ሲል ፍ/ቤቱ ወደ ክርክሩ መሰረታዊ ጉዳይ ገብቶ አከራክሮ

የመሰለውን ውሳኔ ይስጥበት በማለት ጉዳዩን በመመሪያ ወደ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

የአሁን ተጠሪዎችም ውሳኔውን በመቃወም ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም አመልካች የተወሰነለት የካሳ ግምት ብር 235,000.00 ላይ ቅሬታ ካለው በቅድሚያ ይግባኝ ለሚሰማው የአስተዳደር ኮሚቴ ማቅረብ ሲገባቸው ካሳው አንሶኛል በማለት በቀጥታ ክስ ለፍ/ቤት ማቅረብ ስለማይችል የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን አፅንቶ ወስኗል፡፡

አመልካች በውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን ብያቀርቡም የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በመቀጠልም አመልካች ውሳኔው ሕገ መንግስታዊ መብቴን ጥሷል በማለት ለጉባኤው ባቀረቡት ቅሬታ፤

1ኛ አመልካች አርሶ አደር ሆኜ ከ1.20 ሄክታር የእርሻ መሬቱ ውስጥ በሁለት ጥማድ መሬት ላይ ባህር ዛፍ እና የተለያዩ ቋሚ ተክሎችን በማልማት ፣ የቀረውን መሬት ደግሞ በየአመቱ የግብርና ምርቶችን እያመረትኩ 10 የቤተሰብ አባላትን እያስተዳደርኩ እያለ የአሁን ተጠሪዎች ምትክ መሬት እና በቂ የመፈናቀያ ካሳ ሳይሰጡኝ ፣ በቂ መውጫ እና መግቢያ ላለው እንዲሁም ከ15 ሄክታር መሬት በላይ የመሬት ይዞታ ባለቤት ለሆነው ለሃይማኖት ተቋም ለመውጫና መግቢያ በሚል ሰበብ ቋሚ ተክሎች እና ባህርዛፎቹን ጨምሮ ሙሉ በሙሉ መሬቱን እንድለቅ መወሰናቸው በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንኡስ 1፣ 4 እና 7 ስር የተደነገገውን ከእርሻ መሬት ያለመፈናቀል እና ንብረት መብቴን ይጥሳል፣

2ኛ አመልካች ይዞታዬን አለአግባብ እንድለቅ መወሰኑን በመቃወም ቅሬታዬን በየደረጃው ስልጣን ላላቸው የአስተዳደር አካላት ማለትም የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ አስተዳደር እና አርሲ ዞን አስተዳደር አቅርቤ መፍትሄ ባለማግኘቴ ጉዳዩን ወደ ፍ/ቤት ባቀርብም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ስልጣን የለኝም በማለት ጉዳዩበመደበኛ ፍ/ቤት እንዳይታይ መወሰኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ስር የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብቴን ጥሷል፡፡

3ኛ በፌዴራሉ የመሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ.455/1997 አንቀፅ 11 /1 የገጠር መሬት ነክ አቤቱታ አስተዳደራዊ አካል ባልተቋቋመባቸው ከተሞች የካሳ መጠንን አስመልክቶ አቤቱታ የሚቀርበው ስልጣን ላለው መደበኛ ፍ/ቤት ነው በማለት ተደንግጎ እያለ እና አመልካች ይህንን ሳልጠብቅ በራሴ ተጨማሪ ጥረት በማድረግ ወደ ፍ/ቤት ከመሄዴ በፊት ለሚመለከታቸው የዞን እና የወረዳ አስተዳደር አካላት ቅሬታዬን አቅርቤ መፍትሄ ባለማግኘቴ ጉዳዩን ለፍ/ቤት ሳቀርብ ስልጣን የለኝም ማለቱ በሕግ በግልጽ የተጠበቀልኝን መብት ባለማክበር በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት መብቴን ጥሷል በማለት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የአመልካች ቅሬታ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩን ለመመርመር እንዲመች የአመልካች ቅሬታን መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ጭብጦች ተይዘዋል

1. አመልካች ከእርሻ መሬታቸው ሙሉ በሙሉ ተፈናቅለዋል ወይስ አልተፈናቀሉም ተፈናቅለው ከሆነ ያለመፈናቀል ሕገ መንግስታዊ መብታቸው ተጥሷል ወይስ አልተጣሰም?
2. ፍ/ቤቱ አመልካች ጉዳያቸውን መጀመሪያ ለቅሬታ ሰሚ አካል አላቀረቡም በማለት በቀጥታ ለማየት ስልጣን የለኝም ሲል መወሰኑ የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብት ይጥሳል? ወይስ አይጥስም? የሚሉ ናቸው ፡፡

በጉዳዩ አመጣጥ ውስጥ የተገለፁት ፍሬ ነገሮች ፣ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ እና የቀረቡ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም፡- 1ኛ አመልካች ከመሬቱ ሙሉ ለሙሉ ተፈናቅለዋል ወይስ አልተፈናቀሉም? የሚለውን ነጥብ ከመመልከታችን በፊት በመሰረቱ አመልካች የገጠር መሬት ይዞታ ለእምነት ተቋሙ ለህዝብ ጥቅም ይፈለጋል በሚል ምክንያት እንደሆነ ከፍርድ ቤቶች ውሳኔ መረዳት ይቻላል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 455/97ም ሆነ በሊዝ አዋጅ ቁ. 721/2004 መሰረት መሬትን ከባለይዞታ ተቀብሎ ለእምነት ተቋማት መስጠት ለሕዝብ ጥቅም እንደተሰጠ ይቆጠራል ወይ የሚለውን ለግንዛቤ ማስገባት ተገቢ ነው፡፡ ለእምነት ተቋም የሚሰጥ መሬት ለሕዝብ ጥቅም እንደተሰጠ የሚቆጠር አይደለም እንጂ ለሕዝብ ጥቅም የተሰጠ ነው ቢባል እንኳን ለአመልካች በሕጉ አግባብ ተተኪ መሬትና ካሳ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

አመልካች ለፍ/ቤቱ እና ለጉባኤው ባቀረቡት ቅሬታ አርሶአደር ሆነው በ1.20 ሄክታር የእርሻ መሬት ላይ የእርሻ ስራ እየሰሩ የሚተዳደሩ መሆኑን ፣ ይህ የእርሻ መሬታቸውም ምንም አይነት ምትክ የእርሻ መሬት እና በቂ መፈናቀያ ካሳ ሳይሰጣቸው ተጠሪዎች ሙሉ በሙሉ መሬቱን ወስደው ለእምነት ተቋሙ እንደሰጡት ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በጉባኤው ትእዛዝ ተጣርቶ የቀረበው መረጃም አመልካች ከዚህ በፊት እያረሱ ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩበት የነበረው የእርሻ መሬት ሙሉ ለሙሉ ስለተወሰደባቸው በአሁን ጊዜ በሌላ ቦታ የሚገኝ የእርሻ መሬት ሳይሆን የመኖሪያ ቤት እና ባህርዛፍ ያረፈበት 0.25 ሄክታር መሬት በስተቀር ሌላ አርሰው በዘላቂነት ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩበት ይዞታ እንደሌላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ የወረዳ አስተዳደሩ የአመልካችን መሬት ወስዶ ለእምነት ተቋም በሚሰጡበት ለተወሰደው መሬት ሌላ ምትክ መሬት መስጠት ሲገባው ያልሰጣቸው በመሆኑ አመልካች ከአሁን በፊት ከነበራቸው እርሻ መሬታቸው ሙሉ በሙሉ በመፈናቀላቸው ለከፍተኛ ማህበራዊ ችግር መዳረጋቸው ተረጋግጧል፡፡

በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 ስር የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘት ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው የተከበረ መሆኑን፣ አፈፃፀሙ በተመለከተም ዝርዝር ሕግ እንደሚወጣ ደንግጓል፡፡ ሕገ መንግስቱን መሰረት በማድረግ የወጣው የኦሮሚያ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1 ደግሞ ሕብረተሰቡ ማህበራዊ አገልግሎት ሲያገኝ የሚችልበትና ለመኖሪያ የሚሆብ መሬት ሊይዝ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ በሕብረተሰቡ ስምምነት ለመንደር ወይም ለከተማ የሚውል መሬት ለተወሰደባቸው ባለይዞታዎች ተመጣጣኝ ምትክ መሬት ወይም ካሳ የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል በክልሉ ሕግም ሆነ በፌዴራል ሕጎች ላይ የአንድ አርሶ አደር መተዳደሪያ የሆነውን የእርሻ መሬት እና ባህርዛፎች ለሕዝብ ጥቅም በሚል ሰበብ በሙሉ ወስዶ ለሀይማኖት ተቋም እንዲሰጥ የሚፈቅድ ድንጋጌ የለም፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካችን ጉዳይ ስንመለከት ከወረዳው መሬት አስተዳደር ተጣርቶ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የሃይማኖት ተቋሙ በቀን 24/06/2007 ዓ.ም በቁጥር ጨ.መ.28/2007 በተፃፈው ደብዳቤ የወረዳ አስተዳደሩን የመግቢያ እና መውጫ መንገድ እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሰረት አመልካች የእርሻ መሬት እና በእርሻ መሬቱ ጫፍ ላይ ያለውን ባህር ዛፍ እና ቋሚ ተክሎቹን ሙሉ በሙሉ ወስዶ ለሀይማኖት ተቋሙ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን የአንድን አርሶ አደር መሬት ለሕዝብ ጥቅም በሚል ወስዶ ለሀይማኖት ተቋም

መስጠት እንደሚቻል በግልፅ የተደነገገ ድንጋጌ ቢኖር እንኳን አስተዳደሩ ሃይማኖት ተቋሙን ለመውጫ እና መግቢያ የማያገለግለውን በእርሻ መሬቱ ጫፍ ላይ ያለውን ባህርዛፍ እና አትክልቶችም ጨምሮ የአመልካችን መብት ፣ ጥቅምና ፍላጎት በሚጋፋ ሁኔታ አመልካች የያዙትን የእርሻ መሬት ሙሉ ለሙሉ ወስዶ ለሀይማኖት ተቋሙ መስጠቱ ተረጋግጧል፡፡

ከዚህም ሌላ አመልካች አርሶ አደር ሆነው ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩት ከአከራካሪው የእርሻ መሬታቸው ከሚያገኙት ገቢ መሆኑ ነው፡፡ አመልካች ከዚህ መሬት በስተቀር ሌላ የእርሻ መሬት የላቸውም፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች አመልካች መሬቱን ሙሉ ለሙሉ እንዲለቁ ሲወስኑ ከተሰጠው የካሳ ግምት ብር 235.000.00 በስተቀር ሌላ አመልካች በዘላቂነት የሚተዳደሩበት ምትክ የእርሻ መሬት ሳይሰጣቸው አመልካች ከመሬታቸው ሙሉ በሙሉ ለቀው እንዲነሱ አስተዳደሩ ውሳኔ መስጠቱ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(4) እና 40(7) የተደነገገውን አመልካች ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት ይጥሳል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ መጀመሪያ ለቅሬታ ሰሚ አስተዳደር አካል ስላልቀረበ በቀጥታ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብትን ይጥሳል ወይስ አይጥስም? የሚለው ነው፡፡ በጉዳዩ አመጣጥ ውስጥ እንደተገለፀው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የካሳ ክፍያውን እና ምትክ መሬቱን አስመልክቶ ቅሬታቸውን መጀመሪያ የፌዴራል መንግስት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ. 455/97 መሰረት ለወረዳው አስተዳደር ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሳያቀርቡ ጉዳዩን በቀጥታ ለፍ/ቤት ያቀረቡ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ነገር ግን አመልካች መሬቱን እንዲለቁ ከተወሰነባቸው በኋላ ውሳኔውን በመቃወም ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ከመሄዳቸው በፊት በ15/10/2007 ዓ.ም ለሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ አስተዳደር አቅርበዋል፡፡ የወረዳው አስተዳደርም የአመልካችን ቅሬታ በወረዳው አስተዳደር ስር በተቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በመምራት እንዲታይላቸው ባለማድረጉ ምክንያት አመልካች በ19/12/2007 ዓ.ም ለአርሲ ዞን አስተዳደር ቅሬታቸውብ አቅርበዋል፡፡ የአርሲ ዞን አስተዳደር የአመልካችን ቅሬታ ተመርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ለአርሲ ዞን መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት መርቶት ጽ/ቤቱም የአመልካችን ቅሬታ በአስተዳደሩ ስር በተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንዲታይ በማድረግ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ባለማድረጉ ምክንያት አመልካች ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸውን ለማስከበር ወደ ፍ/ቤት የሄዱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በክርክሩ ወቅትም ጉዳዩ ይህ መሆኑን የተገነዘበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ቅሬታቸውን ለሚመለከተው አስተዳደር አካል በቅድሚያ ያቀረቡ ቢሆንም ውሳኔ አለማግኘታቸውን ገልጸ አመልካች ጉዳዩን ለፍ/ቤት ማቅረብ ይችላሉ ሲል አመልካች ሕገ መንግስታዊ ፍትህ የማግኘት እና ከእርሻ መሬታቸው ያለመፈናቀል መብትን ሲያስከብሩ በሚችሉበት ሁኔታ መወሰኑን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡ ነገር ግን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች አቤቱታቸውን በአስተዳደሩ ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አላቀረቡም ሲል ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ወስኖ ይህ ውሳኔም በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትእዛዝ ጸንቷል፡፡ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ፍሬ ነገር የማጣራት ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ጉዳዩን እንዳይወስን የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ በመጨረሻ ፀንቶ ያለው የክልሉ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ስር የተደነገገውን የአመልካች ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብታቸውን ይጥሳል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በፌዴራል የመሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ. 455/1997 አንቀፅ 11 (1) የገጠር የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አስተዳደራዊ አካል ባልተቋቋመባቸው ከተሞች የካሳ መጠንን አስመልክቶ አቤቱታ የሚቀርበው ስልጣን ላለው መደበኛ ፍ/ቤት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ቅሬታቸውን ለማቅረብ የሚችሉበት የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አካል ያልተቋቋመ በመሆኑ በየደረጃው ስልጣን ከተሰጣቸው የመንግስት አካላት የካሳ ክፍያ ቅሬታቸው እንዲፈታላቸው በመጠየቅ ተጨማሪ ጥረት ያደረጉ መሆናቸው ከቀረበው መዝገብ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስለሆነም በፌዴራሉ የመሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 455/1997 አንቀፅ 11(1) መሰረት አመልካች የካሳ መጠንን አስመልክቶ ያላቸውን ቅሬታ በቀጥታ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት የማቅረብ መብት የተሰጣቸው በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት አለመቀበሉ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን ፍትህ የማግኘት መብትን ይጥሳል፡፡

በመሆኑም አመልካች የነበራቸው የእርሻ መሬት ሙሉ በሙሉ በአስተዳደር አካል ውሳኔ መወሰዱ እና ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ የአመልካችን የካሳ መጠን ቅሬታ ተቀብሎ አለማስተናገዱ አመልካች በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 (4) እና 37 የተረጋገጠላቸውን ሕገ መንግስታዊ መብት የሚጥስ በመሆኑ ውሳኔው የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን መረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 241160 በቀን 20/02/2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 136999 የጸናው የካሳ መጠንን አስመልክቶ በአመልካች የቀረበውን ቅሬታ ለመመልከት ስልጣን የለኝም ማለታቸው አመልካች በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 (1) የተረጋገጠላቸውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚጥስ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 (1) መሠረት ውሳኔው ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ወስኗል።

<u>ትእዛዝ</u>

1. የኦሮሚያ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እና ይህን ውሳኔ ያጸኑት የክልሉና የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎቶች ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ይቃረናል ተብሎ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን እንዲያውቁት፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወሰነው መሰረት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ጉዳይ ተቀብሎ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሳቸው።
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት።
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ።

25

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣1ኛ ዓመት፣3ኛ መደበኛ ስብሰባ

ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ.ም

ይግባኝ ባይ 1.ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ

ተጠሪ የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በይግባኝ ባይ የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ዩግባኝ ቅሬታ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

## ውሳኔ

1.የይግባኝ ቅሬታው በአጭሩ

ይ/ባይ ሰኔ 8 ቀን 2003 ዓ.ም ለምክር ቤቱ የፃፉት የይግባኝ ቅሬታ ጠቅለል ባለመልኩ ሲቀመጥ ለረጅም አመታት ከኢትዮጵያ ውጭ ያፈራሁትን ሀብት ወደ አገሬ ይዤ ከገባሁ በኃላ ለአካባቢው ሕብረተሰብም ሆነ ለመንግስት እገዛ ያደርጋል በሚል እሳቤ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ካፋ ዞን ቦንጋ ከተማ ውሰጥ በኢንቨስትመንት ሆስፒታል ለመገንባት ቦታ ተረክቤ ከ70% በላይ ከገነባሁ በኃላ የከተማው ማዘጋጃ ቤት የግንባታው ቦታ ላይ የኮንቴይነር ሱቆች በመደርደሩ የተነሳ የግንባታ አቃዎች ለማስገባት ባለመቻሌ ግንባታው እንዲቆም ተደርጓል፡፡

በዚሁ መነሻነት ማዘጋጃ ቤቱ ክስ አቅርቦ የተለያዩ ፍ/ቤቶች የተለያየ ውሳኔ የሰጡ ቢሆንም የፌደራሉ ጠ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ቀሪው ግንባታ መጠናቀቅ ያለበትን ጊዜ ወስኖ እንዲያሳውቅና ለግንባታ ስራው እንቅፋት የሆኑትን የደረደራቸውን የኮንቴነር ሱቆች በየደረጃው በመለየት እንዲያፈርስ፣ በዚሁ ሁኔታ በሚሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታ ካላጠናቀቁ ማዘጋጃ ቤቱ ግንባታውን ባለበት ሁኔታ የመረከብ መብት እንዳለው ወስኗል፡፡

ይህ ቢሆንም ማዘጋጃ ቤቱ ግዴታውን ሳይወጣና ከ70% በላይ ግንባታ የተፈፀበት በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 /7/ እና ስለኢንቨስትመንት ዋስትና የተቀመጠውን አዋጅ ቁጥር 280/94- አንቀጽ 21ን በመተላለፍ ለንብረቱ ካሣ እንዲከፈል ሳይደረግ መወሰኑ ኢ-ሕገ መንግስታዊ በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ለህገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ ባቀርብም ውድቅ በመደረጉ ያለአግባብ የተደረደሩት የኮንቴይነር ሱቆች ተነስተው ግንባታውን ተረክቤ እንዳጠናቅቅ ወይም ተገቢው ካሳ የማግኘት መብቴ እንዲጠበቅልኝ የሚል ነው፡፡

2.የጉዳዩ አመጣጥ

በዚህ ጉዳይ ክርክሩ የተጀመረው በካፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከሣሽ የነበረ ሲሆን የአሁን ይ/ባይ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ ።ማዘጋጃ ቤቱም ባቀረበው ክስ ይግባኝ ባይ ዘመናዊ ሆስፒታል ለመገንባት ቦታ ጠይቀው 1931 ካ.ሜ ተሰጥቷቸው ግንባታውን ስላቋረጡ ውሉ ተሰርዞ ግንባታውን በራሳቸው ውጭ አፍርሰው ቦታውን እንዲያስረክቡ የቦታና የቤት ግብርም እንዲከፍሉ እንዲወስንባቸው ጠይቋል፡፡ የአሁን ይግባኝ ባይ ለክሱ በሰጡት መልስ ግንባታው የተቋረጠው በፕሮጀክቱ ሳይት ላይ ከሣሽ የኮንቴይነር ሱቆች በማቆሙና ይህም የግንባታ እቃዎች በመኪና ተጭነው እንዳይገቡና እንዳይራገፉ እንቅፋት በመሆናቸውና የግንባታ እቃ ዋጋም በመናሩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ክርክሩን ከመረመረ በኃላ የግንባታ ዕቃዎች ወደ ግቢው በመኪና ተጭኖ እንዳይገባ ያገደው ነገር የለም ። ከዲዛይኑ አኳያ ከግማሽ በላይ የተከናወነ በመሆኑ ውሉ ተሠርዞ ለጅምር ግንባታው ግምቱን ከሣሽ ለተከሣሽ ከፍሎ ግንባታውን ከነይዞታው ይረከብ በማለት ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ላይ ግራ ቀኙ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ክርክር ተመልክቶ ግንባታው የተቋረጠው ማዘጋጃ ቤቱ ባቆማቸው የኮንቴነር ሱቆች ችግር ስለመሆኑ እስከ ቦታው ድርስ ሂዶ ተመልክቶ እንዳረጋገጠ ገልጾ እና የግንባታ እቃ ዋጋ ጭማሪም ለግንባታ መቆሙ አስተዋጽ ስላለው ውሉ ሊሰረዝ አይገባም፡ ሊሰረዝ ይገባል ቢባል እንኳን ከ55% በላይ ግንባታ ስለተከናወነ ወደ ነበሩበት ለመመለስ አስቸጋሪ ስለሆነ ውሉ ሊሠረዝ አይገባም። ስለሆነም ማዘጋጃ ቤቱ ለግንባታ እንቅፋት የሆኑትን ኮንቴነሮችን እንዲያነሳ ግንባታውም እንዲቀጥል ሲል ወስኗል። ማዘጋጃ ቤቱ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ

አድሮበት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል ይ/ባይ ግንባታውን በወቅቱ ላለማጠናቀቅ በምክንያትነት ያቀረቡትን በሳይቱ መግቢያ የኮንቴነር ሱቆች ስላልተነሱ ነው የሚል መከራከሪያ ፍርድ ቤቱ በመመርመር ይግባኝ ባይ ቦታውን ከተረከቡበት ከ 1993 ዓ.ም እስከ 1995 ዓ.ም ድረስ ያለችግር ግንባታውን ሲያካሒዱ እንደነበርና በግንባታ እቃዎች እጥረት ምክንያት ግንባታውን አቋርጠው ቆይተው የኮንቴነር ሱቆች ተደረደሩ የሚል ምክንያት ያነሱት በ 1997 ዓ.ም መጨረሻና በ 1998 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ እንደሆነ በማረጋገጥ ቀሪ ግንባታውን ሊያጠናቅቁ የሚገባበትን ጊዜ በተመለከተ በክልሉ ደንብ ቁጥር 41/1997 በተመለከተው መሰረት ማዘጋጃ ቤቱ ወስኖ እንዲያሳውቃቸው፣ ማዘጋጀ ቤቱ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ማጠናቀቅ ካልቻሉ ውሉ ተሰርዞ ማዘጋጃ ቤቱ ቦታውንና ግንባታውን ባለበት ሁኔታ የመረከብ መብቱን ጠብቆ ለግንባታ ስራው እንቅፋት የሆኑት ኮንቴነር ሱቆች ማዘጋጃ ቤቱ በየደረጃው በመለየት እንዲያፈርስ በማለት ወሰኗል። ይግባኝ ባዩ በጠቅላይ ፍርድቤቱ ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት ተሰርቷል በማለት ለሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው የነበረ ቢሆንም የሰበር ችሎቱም የተፈጸመ የህግ ስሕተት የለም በማለት ውሳኔውን አጽንቶታል፡፡

ከዚህ በኃላ ይግባኝ ባዩ መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም ለሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገመንግስት ትርጉም አቡቱታ አቅርበው የነበረ ሲሆን በአቤቱታቸው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 ስር የተመለከተውን በመጣስ የተሳሳተ ትርጓሚ የሰጡ በመሆናቸው ጉባኤው የፍርድቤቶቹን ውሳኔ እንዲያርመው እና ግንባታውን ተረክቤ እንዳጠናቅቅ ወይም ተገቢውን ካሳ የማግኘት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩን ከተመለከተ በኃላ በአብላጫ ድምጽ አመልካች በግንባታው ላይ ያላቸው መብት ከማዘጋጃ ቤቱ ጋር በገቡት ውል ምክንያት የተጎናፀፉት በሁኔታ ላይ የተመሠረተ መብት ነው፣ይህም ሁኔታ ቀድሞውኑ አመልካች በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ለማጠናቀቅ የማይችሉ ቢሆን ግን ውሉ ሲፈርስ በገደብ የተሠጠ መብት ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ መሠረት የመንግስት አካል የዜጎችን ንብረት መውረስ የሚችለው በቅድሚያ ከግለሰቡ ጥቅም ላቅ ላለ የማህበረሰብ ጥቅም አስገዳጅ ሁኔታን ሲፈጠር ነው፣

በዚህ ጉዳይ ግን ማዘጋጃ ቤቱ ከግማሽ ደርሶ ያልተጠናቀቀውን ግንባታ እንዲረከብ ሆነ እንጂ ከፍ ላለ የሕዝብ ጥቅም ሲባል ከባለሀብቱ ለመውረስ የሚያስገድድ ሁኔታ አልተከሰተም። ማዘጋጃ ቤቱ የባለሀብቱን ንብረት ለሕዝብ ጥቅም ለመውረስ አልወሰነም። ባለሀብቱ እንደውላቸው ግንባታውን ቢያጠናቅቁ ኖሮ ንብረቱ ከባለሀብቱ እጅ የሚወጣበት ሁኔታ አይኖርም ነበር። ማዘጋጃቤቱ ግንባታውን የተረከበው አመልካች እንደ ውሉ ባለመፈጸማቸው ምክንያት ግንባታው ከሚፈርስ ማዘጋጃ ቤቱ ቢረከበው ይሻላል ከሚል ሚዛን ነው። ስለሆነም አመልካቹ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ7 መሠረት ተመጣጣኝ የካሣ ክፍያ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ የሕገ መንግስት ትርጉም የማያስነሳ ነው በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

የጉባኤው አነስተኛው ድምጽም በበኩሉ በአመልካች ላይ የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 /7/ መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ሊሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማወረስ ፣የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ወይም የካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብት አለው የሚለውን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ የሚጥስና የኢንቬስትመንት እንቅስቃሴንም የሚገታ በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት በሀሳብ ተለይቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባዩ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ባዩ የይግባኝ ቅሬታቸውን ለምክርቤቱ ያቀረቡ ሲሆን ምክርቤቱ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የግንባታውን ሁኔታ ለመረዳት እንዲቻል ሁለት ቡድኖች በተለያየ ጊዜ በቦታው በመገኘት ምልከታ አድርገው እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ በምልከታቸውም ይግባኝ ባዩ የግንባታ ስራ ጀምረውበት የነበረው ሕንጻ የካፋ ልማት ማህበር ተረክቦት እየተጠቀመበት እንደሆነ፣ማህበሩ ሕንጻውን ሰርቶ ግማሹን ለተለያዩ ድርጅቶች ባንኮች ያከራየ መሆኑን ቡድኑ ተመልክቷል፡፡ቀሪውን ግንባታ ልማት ማህበሩ እያከናወነ እንደሚገኝ አረጋግጧል። በወቅቱ ግንባታው ሲቋረጥ የሕንጻ ስራው የነበረበትን ደረጃ በተመለከተ ፕላኑ G+2 እንደነበረ፣ በወቅቱ ይግባኝ ባዩ መሰረት እና ኮለን እንዳቆሙ፣የአንዱ ወገን ስላቭ እንደተሰራና ሐምሌ 8 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የርክክብ ሰነድ ቦታውንና ግንባታውን ማዘጋጃ ቤቱ ያለክፍያ ለካፋ ልማት ማህበር እንዳስረከበ ከቡድኑ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ከላይ የተመለከቱት ሲሆኑ ምክርቤቱም የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን ከስር ጀምሮ ማለትም የይግባኝ ባይን አቤቱታ፣የአጣሪ ጉባኤውን ውሳኔ፣በተለያዩ ወቅቶች በተደረገው ማጣራት የተገኙ ጉዳዮችን፣የህገመንግስቱንና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ድንጋጌዎች በማገናዘብ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ በአግባቡ ተመልክቷል፡፡በዚህም መሰረት የይግባኝ ባዩ ጥያቄዎች በዋነኛነት ሁለት ሲሆኑ እነዚህም ግንባታውን ተረክቤ እንድሰራ ይደረግ ወይም ተገቢውን ካሳ የማግኘት መብቴ ይጠበቅልኝ የሚሉ ናቸው፡፡

ምክርቤቱም ከጉዳዩ አመጣጥ፣በፍርድቤቶች ከተሰጡ ውሳኔዎችና ከይግባኝ ባይ አቤቱታ በመነሳት ሁለት ጉዳዮች ተከፋፍለው መታየት እንዳለባቸው ተገንዝቧል፡፡አንደኛው የውሉ መሰረዝ እና ለዚህ ጉዳይ በፍርድቤቶች የተሰጡት ምክንያቶች ከዚሁ ጋር ተያይዞ ይግባኝ ባዩ ቦታውንና ግንባታውን ተረክቤ እንዳጠናቅቅ በሚል ያቀረቡት ጥያቄ ሲሆን ሁለተኛው ይግባኝ ባዩ በአማራጭ ተገቢው ካሳ የማግኘት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ነው፡፡

አንደኛውን ጉዳይ በተመለከተ በይግባኝ ባይና በማዘጋጃ ቤቱ መካከል የነበረው ውል በጠቅላይ ፍርድቤት ውሳኔ መሰረት ይግባኝ ባዩ ማዘጋጃ ቤቱ ወስኖ በሰጣቸው የጊዜ ገደብ ግንባታውን ባለማጠናቀቃቸው ውሉ ተሰርዞ ማዘጋጃ ቤቱ ቦታውን ከእነግንባታው ተረክቧል፡፡ ለውሉ መሰረዝ ምክንያት ለሆነው የግንባታ መጓተት በተለያዩ ፍርድቤቶች የተለያዩ ትንተናዎች የተሰጡ ሲሆን ውሉ የተሰረዘው በአግባቡ ነው አይደለም?ለውሉ መሰረዝ እና ለግንባታው በጊዜ ያለመጠናቀቅ ምክንያቶች ምንድናቸው? የሁለቱ ወገኖች ድርሻ ምን ነበር?ቀሪ የግንባታ ጊዜ ማዘጋጃ ቤቱ ወስኖ እንዲሰጥ መደረጉ በአግባቡ ነው አይደለም? የሚሉት ሀሳቦች ከላይ በጠቅላይ ፍርድቤቱ የውሳኔ ሐተታ የተረጋገጡ፣ምላሽ ያገኙና ውሳኔ የተሰጠባቸው የህግ እና የፍሬ ነገር ክርክሮች በመሆናቸው ምክርቤቱ የሚመለከታቸው አይሆኑም፡፡ማዘጋጃ ቤቱም መሬቱን ሲረከብ ግንባታውንም አብሮ የተረከበበትን አግባብነትንም በተመለከተ ይህ ምክርቤት የሚያየው ጉዳይ አይደለም፡፡ከዚህም በመነሳት ይግባኝ ባዩ ግንባታውን ተረክቤ እንድቀጥል በሚል ያቀረቡት ጥያቄ ይህን ምክርቤት የሚመለከት ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተነሳው እና በይግባኝ ባዩም የተጠየቀው ተገቢው ካሳ የማግኘት ጥያቄን በተመለከተ ጥያቄው ሕገ-መንግስታዊ በመሆኑ በምክርቤቱ በኩል የታየው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ያለምንም ተመጣጣኝ ክፍያ ማዘጋጃ ቤቱ መሬቱን ከእነ ግንባታውን እንዲረከብ ውሳኔ ሲሰጥ በመሬቱ ላይ አመልካች የገነቡት ግንባታ ጉዳይ እንዴት ይታያል የሚለው ነው፡፡

በምክርቤቱ በኩል ይህ ጥያቄ እንደታየው በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ በግልጽ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው፡፡ይህ መብት የመሸጥ፣የመለወጥ፣የማውረስ፣የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል በሚል ተደንግጎ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ እንደሚወሰን አስቀምጧል፡፡በሌላ በኩል ለንብረት ካሳ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 455/1997 ዓ.ም አንቀጽ 7 የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ የሚደረግ ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ መሻሻል ካሳ እንደሚከፈለው ተደንግጓል፡፡

በዚህ ጉዳይ ይግባኝ ባይ የመሬት ተጠቃሚነታቸው ተቋርጧል፡፡ሆኖም በመሬቱ ላይ ግንባታ ማከናወናቸው የግንባታውም ደረጃ ጭምር በእራሱ በማዘጋጃ ቤቱ የታመነ በመሆኑ ማዘጋጃ ቤቱ ያለምንም ክፍያ ንብረቱን እንዲረከብ ተብሎ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት የተሰጠው ውሳኔ የቦታውንና ግንባታውን ርክክብ የተመለከተው ውሳኔ ሳይሆን ተመጣጣኝ ክፍያን በሚመለከት ምንም ነገር ያለማለቱ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ የተደነገገውን መብት የሚጻረር በመሆኑ ጥያቄው የምክርቤቱ የህገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በሚል ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡

በመሆኑም ይግባኝ ባዩ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 7 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ሊሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማወረስ ፣የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ወይም የካሣ ክፍያ

የመጠየቅ መብት አለው በሚለው ድንጋጌ መሰረት በመሬቱ ላይ የተገነቡትን ሀብት ግምት የመጠየቅ መብት አላቸዉ በማለት ምክርቤቱ በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ምክር ቤቱ ባብላጫ ድምፅ ይግባኝ ባይ በመሬቱ ላይ የገነቡትን ሀብት ግምት የመጠየቅ መብት አላቸው በማለት የወሰነውን ውሳኔ እንዲያስፈፅም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የፌዴራል ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያውቀው ይላክለት፡፡
3. የምክር ቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለይግባኝ ባይ ይሰጥ፡፡

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣5ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሚያዚያ 22 2010 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ

ተጠሪ፡- የወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን ተተኪዎች (እነ አቶ ገ/መድህን አባይ)

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

## ውሳኔ

የጉዳዩ መነሻ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 የተደነገገውን የንብረት መብትን የሚጥስ ነው በማለት አመልካች ባመለከቱት መሰረት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩን መርምሮ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የቀረበ ነው።

የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ያቀረበው የውሳኔ ሐሳብ ክርክር ያስነሳው የመሬት ይዞታ ወ/ር አባይ ግፋው (የአሁኑ ተጠሪዎች አውራሽ) ቤት ለመስራት በማለት በ1973 ዓ.ም በምሪት ተሰጥቶአቸው አንደነበረ መረዳት ተችሏል።በ16/04/1974 ዓ.ም በ6 ወር ጊዜ ውስጥ በኘላኑ መሰረት ቤት እንዲሰሩና ግብር እንዲገብሩ ደብዳቤ ተፅፎላቸው (ውል ገብተው) ቢፈርሙም በውላቸው መሰረት በይዞታው ላይ ግንባታ ማድረግ አለመቻላቸው።

የአሁኑ አመልካች እናት የነበሩት እማሆይ ፀሐይነሽ ገ/ማርያም በ14/07/1974 ዓ.ም ክርክር ያነሳነውና የወ/ር አባይ ግፋው ይዞታ የነበረው 500 ካ.ሜ ቦታ

እሳቸው መስራት ባለመቻላቸው ለእኔ ይሰጠኝ ብለው ባመለከቱት መሰረት የከተማው አስተዳደር ሰኔ 18 ቀን 1974 ዓ.ም ካርታና ፕላን ሰርቶ በርስት መዝገብ ቁጥር 159 መዝግቦ እንደሰጣቸው ታውቋል፡፡

ግንባታውን ለማካሄድ ፈቃድ አውጥተው እንደወሰዱ፣ ቦታውን ከተመሩበት ጊዜ ጀምሮ ለልጃቸው ለአሁኗ አመልካች እስካስተላለፉበት ጊዜ ድረስ በየአመቱ በስማቸው ግብር ሲከፍሉ እንደነበረ፣ በቀን 26/12/1992 ዓ.ም በሕጋዊ መንገድ ለልጃቸው ለአሁኗ አመልካች ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ በስጦታ (ሰጥተው) እንዳስተላለፉ ታውቋል፡፡

የከተማው አስተዳደርም በርስት መዝገብ ቁጥር 158 ለአመልካች ስም መዝግቦ አመልካች ካርታና ፕላን በማውጣት ተጨማሪ ክፍሎችን በመገንባትና በስማቸው ግብር በመክፈል የንብረቱ ባለቤት በመሆን በመብታቸው እየተጠቀሙበት መቆየታቸውን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ቀርበዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች አባት (ለክርክር መነሻ በሆነው) የመሬት ይዞታ ላይ የነበራቸው መብት የተቋረጠው በ1974 ዓ.ም በተሰጣቸው የ6 ወር ጊዜና ፕላን መሰረት ግንባታ ለማድረግ ውል ገብተው በውሉ መሰረት መፈጸም ባልቻሉበት ጊዜ ሆኖ እያለ (የአሁኑ ተጠሪዎች) አባታቸው በህይወት በነበሩበት ወቅት የተዉትን መብት የአሁን ተጠሪዎች ማንሳታቸውን አግባብነት የለውም፡፡

መሆኑም የአሁኑ አመልካች በህጋዊ መንገድ ባለቤት የሆኑበትን ቤትና ይዞታ የአሁኑ ተጠሪዎች ከ21 ዓመት በኂላ ወደ ኂላ ተመልሰው ያቀረቡትን ክስና የቀድሞ የመሬት ይዞታ ታሪክን መነሻ በማድረግ ፍርድ ቤቱ (የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሐድነት ክፍለ ከተማ ምድብ ችሎት) የሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 40 የተደነገገውን የአመልካች ሕገ መንግስታዊ የንብረት ባለቤትነት መብት የሚቃረን በመሆኑ አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ

መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

የሕገ መንግስት ትርጉማና የማንነት ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ የፍ/ቤቶችን ውሳኔ፣ የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ እና የኢፌዴሪ ሕገ መንግስትን በማጣመር መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም ለክርክር መነሻ የሆነው በመቀሌ ከተማ፣ የግንቦት 20 ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኘው አዋሳኙ ተጠቅሶ የቀረበው የመሬት ይዞታ ቀደም ሲል በ1973 ዓ.ም የአሁኑ ተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት ሚች ወ/ር አባይ ግፋው ቤት ሊሰሩበት የከተማው አስተዳደር በምሪት ሰጥቷቸው በይዞታነት ይዘውት የነበረ ቢሆንም የከተማው አስተዳደር በ1974 ዓ.ም በመሬት ይዞታው ላይ በተሰጣቸዉ ኘላን መሰረት በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ቤት እንዲሰሩበትና ግብር እንዲከፍሉበት ውል ገብተው እንዲፈርሙ በማድረግ የሰጣቸውን ዕድል አለመጠቀማቸውን ተከትሎ ይሄው ቦታ እንዲሰጣቸው ለጠየቁት ለአሁኗ አመልካች እናትና ስጦታ አድራጊ እማሆይ ፀሐይነሽ ገ/ማርያም የከተማው አስተዳደር ሰኔ 18 ቀን 1974 ዓ.ም የቦታውን ካርታና ኘላን ሰርቶና በርስት መዝገብ መዝግቦ በመስጠት ቤት እንዲሰሩበት በማድረግ በሕጋዊ መንገድ የይዞታው ባለቤት እንዲሆኑ ማድረጉና ቤትና ይዞታውን ወደ ከተማው ውልና ማስረጃ ምዝገባ (የፍትሕ) ፅ/ቤት ቀርቦ በተመዘገበና በሚፀና የስጦታ ውል ወደ ልጃቸዉ - የአሁኗ አመልካች ባለቤትነት እንዲተላለፍ መደረጉን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በከተማው አስተዳደር በሚገኘው የቤቱ ማህደር ውስጥ ተያይዞ እያለ ይህንን ችላ በማለት በጉዳዩ ላይ የተነሳውን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የመቐለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሐድነት ምድብ ችሎት የአሁኗ አመልካች ለክርክር መነሻ ከሆነውና በይዞታቸው ስር ከሚገኘው 500 ካ.ሜ ይዞታ ውስጥ ግማሹ 250 ካ.ሜ ለአሁኑ ተጠሪዎች አውራሽ የሚገባ በመሆኑ ለቀው እንዲያስረክቡአቸው በማለት የሰጠውና እስከ

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች እንዲፀና የተደረገው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 40 የተደነገገውን የአመልካችን የንብረት ባለቤትነት ሕገ መንግስታዊ መብትን የጣሰ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ትዕዛዝ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የሰጡት ውሳኔ ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ተቀባይነት የለውም በማለት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት እና የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ም/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ እንዲያውቁትና እንዲያስፈጽሙት ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የውሳኔ ሀሳብ ም/ቤቱ በሰጠው የሕገ መንግስት ትርጉም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን እንዲያውቁት ውሳኔው ይድረሳቸው፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካች ይድረሳቸው፡፡

97

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ. 86/12

አመልካች፡- ቄስ ወ/ጊዮርጊስ ኪዳኔ

አድራሻ ፡- ት/ብ/ክ/መ/ወ/ታ/ማይጨው ማይበራዝዬ ቀበሌ

ተጠሪ ፡- 1. አቶ መረሳ ወ/ማርያም

2. አብረኸት ገ/ጻድቃን

አድራሻ፡- ት/ብ/ክ/መ/ወ/ታ/ማይጨው ማይበራዝዬ ቀበሌ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

## ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 25 ቀን 2011 ዓ.ም ለሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው። ጉዳዩ የይዞታ ይገባኛል ክርክር ሲሆን ሲጀመር አመልካች ተከሳሽ ተጠሪዎች ከሳሽ ሆነው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው።

የክሱም ይዘት በትግራይ ክልል በታች ማይጨው በማይበራዝዬ ቀበሌ አዋሳኞቹ በክሱ በተጠቀሱት የኢንቨስትመንት ቦታ ላይ የሚገኝ ስድስት የእህል ወፍጮ ከነ ሙሉ መሳርያው በብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ) ለአመልካች ሸጠናል። ሆኖም አመልካች ወፍጮውን ከቦታው እንዲያነሱልን ብንጠይቅም እንዲሁም አስፈላጊውን ማስጠንቀቂያ ብንሰጥም ሊለቁልን ፍቃደኛ አልሆኑም። በመሆኑም በኢንቨስትመንት ቦታችን ላይ ምንም መብት ስለሌላቸው ወፍጮውን አንስተው ቦታውን እንዲለቁ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ይህንኑ ክስ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ማቅረባቸውን፣ ጉዳዩን አይቶ የይዞታ ማረጋገጫ ለእኔ በመስጠቱ ክሱ በተመሰረተበት ሀብት ላይ ጥቅም ስለሌላቸው የመክሰስ መብት የላቸውም ብለዋል። በፍሬ ነገር መልሳቸው ተጠሪዎች ወፍጮውን ከእነ ይዞታው በመሸጣቸው ይዞታው ለአመልካች ይሰጥ በማለት በቀበሌ መስተዳደር በሦስት ምስክር ፊት በመፈረማቸው የመጠቀም መብት የይዞታ ማረጋገጫ

በ40×30 ሜ መሬት ላይ በቀን 12/1/2007 ዓ.ም ማግኘታቸውን፣ ማረጋገጫው እንዳልተሰረዘ እና ተጠሪዎች በኢንቨስትመንት ያገኙት መሬቱን ከአምስት ዓመት በኋላ ማሳደስ ቢኖርባቸውም የታደሰ የኢንቨስትመንት ውል አለመኖሩ ይዞታውን ለእኔ እንዳስተላለፉት ያሳያል በማለት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገሩ ተጠሪዎች የሸጡት ወፍጮ ብቻ ነው ወይስ መሬቱንና ሌላ ንብረቶችንም ጭምር ነው? የሚል ጭብጥ በመያዝ በግራ ቀኙ የቀረቡትን የሠው እና የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ የሰው ማስረጃዎች ሽያጩ ወፍጮን፣ 4 ክፍል ቤት ከዙርያ መለስ የግንብ አጥር ጋር ማካተቱን እና ውሉ በውልና ማስረጃ እንደጸደቀ በማስረዳታቸው፣ የጹሁፍ ማስረጃዎች፤ ተጠሪዎች ቦታውን ለኢንቨስትመንት እንደተረከቡት እና ወፍጮ ተክለው ሲሰሩበት ቆይተው ወፍጮውን እና ቤት እና ግቢውን በብር 270.000.00 (ሁለት መቶ ሰባ ሺ.ህ) እንደሸጡት ያስረዳል፡፡ በመሆኑም ሽያጩ ይዞታውን በማጠቃለሉ አመልካች ሊለቁ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም አያስቀርብም ተብሎ መዝገቡ በትዕዛዝ ተዘግቷል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ለሰበር ያስቀርባል በማለት ሽያጩ የኢንቨስትመንት የኪራይ መሬቱን ያጠቃልላል? አያጠቃልልም? የሚለውን ከትግራይ ክልል የኢንቨስትመንት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ 239/2006 እና ከግራ ቀኙ ውል አንጻር መርምሮታል፡፡

በምርመራው ውሉ በግልጽ የወፍጮ ቋት ሽያጭ የተፈጸመ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 239/2006 መሠረት የእርሻ ኢንቨስትመንት የወፍጮ ሥራ ኢንቨስትመንትን የሚያካትት ነው፡፡ በአዋጁ ኢንቨስትመንት መብት ከሚተላለፍበት ስርዓት ውጪ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ መሆኑን፣ በዚህም አግባብ የመሬት አስተዳደር ይህንኑ ለተጠሪዎች በመግለጹ በኪራይ ለኢንቨስትመንት ስራ የተገኘን መሬት መሸጥ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ የኪራይ መሬት ሽያጩ በውሉ ያልተመላከተ እና በአዋጁ አንቀጽ 22/5/ እና 26/4/ መሠረት በኪራይ ለኢንቨስትመንት ስራ የተገኘ መሬት መሸጥ የተከለከለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮ ሽያጩ የኢንቨስትመንት መሬቱን አያካትትም በማለት ወስኗል፡፡



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

አመልካች ለሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ብሎ ሳይጠየቅ ቀሪ ይሁን ማለቱ የክርክር ነጥብ ያልሆነ ጉዳይ አንስቶ ለመወሰን ስልጣን ሳይኖረው መወሰኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 25፣ 80(3) የተደነገገውን መብቴን ጥሷል፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእጄ እያለና ካርታው ሳይመክን የእርሻ ኢንቨስትመንት መብት ከስርዓት ውጪ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/6/ እና /7/ እንዲሁም 79(3) መሠረት ንብረት የማፍራት እና የመጠቀም መብቴን የጣሰ ነው በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ጉባኤውም የአመልካችን አቤቱታ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ እና ተጣሰብኝ ካሉት ሕገ መንግስታዊ መብት አንጻር መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም ተጠሪዎች ቤቱን ለኢንቨስትመንት ብለው ከክልሉ መንግስት ተረክበው ሲሰሩ ቆይተው ወፍጮአቸውን ለአመልካች መሸጣቸውን ነው፡፡ በዚህ አግባብ በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች ሽያጩ የኢንቨስትመንት መሬቱን ያጠቃልላል ብለው ቢወስኑም የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ ሕግ አዋጅ ቁጥር 239/2006 ለኢንቨስትመንት የተሰጠን መሬት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ ስለተከለከለ እና ውሉም የእህል ወፍጮ ሽያጭ ስለሚል ሽያጩ የወፍጮ ብቻ ነው በማለት መወሰኑን ነው፡፡ አመልካች ይህ ውሳኔ በሕገ መንግስቱ የተደነገጉትን መብቶቼን ይጥሳል በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ሰበር ሰሚው አዋጁን እና ውሉን የተረጎመበትን መንገድ ሕገ መንግስታዊነት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህ አግባብ በፍርድ ቤት የነበረው ክርክር በግራ ቀኙ መካከል በቀን 18/11/2005ዓ.ም በብር 20,000 (ሃያ ሺ.ህ) የእህል ወፍጮ ሽያጭ ውል መደረጉን፣ በቀን 22/11/2005 ዓ.ም ግራ ቀኙ ባደረጉት የስምምነት ውል 40 ሚትር በ30 ሜትር የሆነውን የእህል ወፍጮ ቦታ፣ አራት ክፍል ቤት፣ መጋዘን፣ ግንብ አጥርና ብረት መዝጊያ ያለው ቦታ በብር 270,000.00 (ሁለት መቶ ሰባ ሺ.ህ ብር) በመሸጥ ውሉን እንዳሻሻሉት ማስረጃ የመመዘን ስልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች መረጋገጡን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ይህንን ተከትሎ ሐምሌ 28 ቀን 2005 ዓ.ም የወረዳ ታህታይ ማይጨው አስተዳደር ኮሚቴ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን 40 × 30 ሜትር የሆነ ቦታ የወፍጮ ድርጅት ስም ለአመልካች እንዲዛወርላቸው የድጋፍ ማስረጃ የጻፈላቸው ሲሆን መስከረም 12 ቀን 2007 ዓ.ም የታህታይ ማይጨው ወረዳ አመልካች ወፍጮውን በውል እና ማስረጃ እንደገዙት በመጥቀስ እና የቀበሌው መሬት አስተዳደር ወፍጮ የነበረበትን 40×30 ሜትር የሆነው መሬት ለአመልካች ሲዛወርላቸው

ይገባል በማለት በመወሰኑ መሬቱን ለአመልካች መስጠታቸውን አረጋግጠው ጽፈውላቸዋል፡፡ ይህን ተከትሎ በአዋጁ አንቀጽ 17 /1/ መሠረት በክልሉ የገጠር መሬትን የማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው የትግራይ ክልል የአካባቢ ስነ ጥበቃ ኤጀንሲ የገጠር መሬት አስተዳደር በ04/04/2009 ዓ.ም የገጠር መሬት የይዞታ ካርታ ሰጥቷቸዋል፡፡ በቦታው ላይ ካርታ እንጂ የኢንቨስትመንት ፍቃድ አለመሰጠቱ ከኢንቨስትመንት ሕጉ አንጻር ሲታይ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12 የኢንቨስትመንት ፍቃድ ስለሚያስፈልጋቸው ባለሃብቶች ሲደነግግ በእርሻ ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ባለሃብቶች ፍቃድ ከሚያስፈልጋቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ውስጥ አያካትታቸውም፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ምንም እንኳን የእህል ወፍጮ ሽያጩ የተደረገው በግራ ቀኙ በተደረገው ውል ቢሆንም መሬቱን ለአመልካች ያስተላለፈው የወፍጮ ሽያጩን እና የተሻሻለውን ውል መሰረት አድርጎ የቀበሌው አስተዳደር እንጂ ቀጥታ ተጠሪዎች አለመሆናቸውን ነው፡፡ በመሆኑም የፌደራል ሰበር ሰሚው ችሎት በውሳኔው ሽያጩ በውሉ ያልተመላከተ ነው በማለት ለውሳኔው መነሻ ምክንያት ቢያደርግም በክልሉ ፍ/ቤቶች ማስረጃዎችን መዝነው ያረጋገጡት እና መዝገቡም የሚያስረዳው ግራ ቀኙ ውላቸውን በማሻሻል ተጠሪዎች ወፍጮውን እና ጊቢው ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶች ለአመልካች እንደሸጡላቸው ነው፡፡

በዚህ አግባብ በሕገ መንግስቱ መንግስት ለኢንቨስትመንት የሰጠውን መሬት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ ሕገ መንግስታዊነቱ እና የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለኢንቨስትመንት የተሰጠን መሬት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም ብሎ የመወሰኑን ሕገ መንግስታዊነት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 6 መሬት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ለግል ባለሃብቶች የመሬት መጠቀምን መብት እንደሚያስከብርላቸው ደንግጓል፡፡ ይህም የሚያስረዳው የመሬት ባለቤትነት የሕዝብና የመንግስት በመሆኑ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል መሬትን የማስተዳደር፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ከግምት ውስጥ በማስገባት መሬት የመጠቀምን መብት ለባለሃብቶች ማስተላለፍ፣ ማከራየት፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሕጋዊውን ስነ ስርዓት ተከትሎ የኪራይ ውሉን ማቋረጥ መሬቱን ለሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ መብት ይኖረዋል፡፡

መሬቱን የተከራዩት ባለሃብቶች በአንጻሩ የመሬቱ ተጠቃሚ እንጂ ባለቤት ባለመሆናቸው ባለቤት ከሆነው ከመንግስት እውቅና ውጪ የተከራዩትን መሬት ማስተላለፍ አይችሉም የሚል ትርጓሜ ይኖረዋል፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ የክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 22/5 እና 26/4/ ከመንግስት የገጠር መሬት ተከራይቶ የሚጠቀም ባለሃብት የተከራየውን የእርሻ ኢንቨስትመንት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ መሆኑን እና ባለሃብቱ ከሚመለከተው አካል እውቅና ውጪ የተከራየውን መሬት ለሦስተኛ ወገን አስተላልፎ ሲገኝ የኪራይ ውሉ እንደሚቋረጥ ይደነግጋል፡፡

ይህም የሚያስረዳው ባለሃብቱ ለኢንቨስትመንት የተከራየውን መሬት ከሚመለከተው አካል እውቅና ውጪ ማስተላለፍ የማይችል መሆኑን እንጂ በአጠቃላይ ለኢንቨስትመንት የተሰጠ መሬት ለሦስተኛ ወገን አይተላለፍም የሚል እንድምታ አይኖረውም፡፡ አዋጁ ማስተላለፍን በጠቅላላው ባለመከልከሉ የግራ ቀኙን ስምምነት መነሻ በማድረግ የትግራይ ክልል የአካባቢ ስነ ጥበቃ ኤጀንሲ የገጠር መሬት አስተዳደር ታህሳስ 4 ቀን 2009 ዓ.ም የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለአመልካች መስጠቱ ለሽያጩ እውቅና የሰጠው መሆኑን ያሳያል፡፡

ባለሃብቱ ንብረቱ ላይ ሊኖረው የሚችለውን መብት ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40(1) አንጻር ስንመለከተው ንብረትን የመሸጥ መብት የሚገደበው የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ፣ ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር ሲቃረን ወይም በሕግ በተወሰነ ጊዜ ብቻ መሆኑን በድንጋጌው ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ሽያጩ በሕግ ያልተከለከለ፣ የሕዝብ ጥቅምን የማይጋፋ እና የሌሎችን መብት እና ጥቅምን የማይቃረን በመሆኑ ንብረቱን በጠቅላላው ማስተላለፍ አይቻልም ተብሎ መተርጎሙ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ድንጋጌ ይቃረናል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትርጓሜው በጠቅላላው /መንግስትም ሆነ ባለሃብቱ/ ለኢንቨስትመንት በኪራይ የተሰጠን መሬት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም ማለቱ በሕገ መንግስቱ የመሬት ባለሃብትነት ለመንግስት እና ለሕዝብ ከመሰጠቱ እና መንግስት በባለቤትነት መብቱ የተለያዩ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ በመሬት የመጠቀም መብትን የሚያስተላልፍበትን አግባብ የሚገድብ ነው፡፡

በዚህም መሰረት በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 ጋር የሚጋጭ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ

84(1) እና በአዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀፅ 3 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/1/ ስር የተቀመጠውን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አውቆ ተገቢውን እንዲፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የፌዴራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

28

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣1ኛ ዓመት፣

# 3ኛ መደበኛ ስብሰባ

ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ.ም

አመልካቾች አቶ እሸቱ ይማም

ተጠሪ፦ ወ/ሮ የተመኘ አሊ ሀሰን

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካቾች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች ከተጠሪ ባለቤት ጋር የሽርክና ንግድ ስራ ሲሰሩ ቆይተው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ሽርክናው ፈርሶ በንግድ ስራቸው ያፈሯቸውን ንብረቶች እንዲካፈሉ ተጠሪ ለፍ/ቤት አመልክተው ፍ/ቤቱም በዚሁ መሰረት ንብረቶቹን በዓይነትና በገንዘብ እንዲካፈሉ ወስኖ በአፈፃፀም ሂደቱ ፍርድ ያልተሰጠበትን ቤት በጨረታ እንዲሸጥ ፍ/ቤቱ በመወሰኑ የእኩልነት እና ንብረት የማፍራት መብቴ ስለተጣለ የሕገመንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በሚል ጥያቄ ቀርቦ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው በመሆኑ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በሙሉ ድምጽ የውሳኔ ሐሳብ ለምክር ቤቱ በመላኩ ነው፡፡

የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

ከፍ/ቤቱ ውሳኔዎች መረዳት እንደተቻለው በአመልካችና በተጠሪ ባለቤት መካከል የነበረው ሽርክና በሞት በመፍረሱ የጋራ ንብረት መሆናቸው የታመኑ አራት መኪኖችና ጥሬ ገንዘብ ሁለቱም እኩል በዓይነት ወይም ዋጋቸው እየተተመነ አንዱ ለአንዱ ገንዘብ እየሰጠ ሊከፋፈሉ ይችላሉ በማለት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወስኗል፡፡ ይህ የፍ/ቤት ውሳኔ አመልካች ለተጠሪ ምን ያክል

እንደሚከፍል ያስቀመጠው የገንዘብ መጠን ባይኖርም የጋራ ናቸው ተብለው የታመኑ እና ማስረጃ የቀረበባቸው ንብረቶች እና እዳዎችን በሙሉ እኩል እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

በዚህም መሰረት የአፈፃፀም ክስ ተመስርቶ አመልካችና ተጠሪ  የሽርክና ንግድ ሥራው የጋራ ንብረት የሆኑትን በአይነትና በገንዘብ ተካፍለዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ጥሬ ገንዘብ፣ የእህል ሚዛን፣ ባዶ ኬሻ እና የጭነት መኪና መካፈላቸውን መዝገቡ ያስረዳል፡፡  የሽርክና ስራው የጋራ ንብረት መሆናቸው ከተረጋገጡ መኪኖች መካከል ሁለቱ የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ሀገር ውስጥ የገቡና ጅግጅጋ የሚገኙ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ በአመልካች እጅ እንደሚገኙ በመውሰድ ተገቢውን ቀረጥ ከፍለው መኪኖቹን እንዲያስለቅቁ ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ቢያስተላልፍም አልተፈፀመም፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው አመልካች መኪኖቹ በአደራ የተቀመጡት በእሳቸው አማካኝነት መሆኑን በማመናቸው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ለአመልካች በሰጠው ተደጋጋሚ ትእዛዝ መኪኖቹ ባለመቅረባቸው ለሶማሌ ክልል የትራ/መ/ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ደብዳቤ ጽፎ ቢሮውም ለፍርድ ቤቱ በደብዳቤ ቁጥር XGGW//24/64/98 የገለፀው አንድ ላንድክሩዘር እና አንድ ጂፕ መኪኖች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው መኖራቸውን እና በአንድ ግለሰብ ግቢ ውስጥ የሚገኙ መሆኑን ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ እንደገና ጥቅምት 11 ቀን 2008 ዓ.ም ለሶማሌ ክልል ፖሊስ መኪኖቹ ካሉበት ተይዘው እንዲላኩ በፃፈው ደብዳቤ የክልሉ ፖሊስ 09/03/2003 ዓ.ም በፃፈው መልስ መኪኖቹ አሉ በተባለበት ቦታ ሲደርስ ያገኘው አንድ ጂፕ ቸሮኪ መኪና ብቻ ሲሆን መኪናውም መንቀሳቀስ የማይችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሳኔው እንደገለፀው አመልካች በመኪናዎቹ ላይ በትእዛዙ መሰረት አፈፃፀም እንዲቀጥል ያደረጉት ጥረት ስለሌለና በፍርዱ መሰረት ስላልፈፀሙ ለአፈፃፀም ክስ መያገ እንዲሆን  ተከብሮ የነበረው የአመልካች መኖሪያ ቤት (የቤት ቁጥር 386) በጨረታ እንዲሸጥና ፍርዱ እንዲፈፀም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ጨረታውም ከተካሄደ በኋላ አመልካች የመኪናዎቹ ዋጋ ሳይተመንና የተጠሪ ድርሻ ሳይታወቅ ቤቱ የተሸጠበት ዋጋ በሙሉ መከፈሉ ተገቢ አይደለም ከፍርዱ ውጭ የማይገባኝን እንድከፍል ተደርጓል የሚል ቅሬት አቅርበዋል፡፡ ሌላው በአመልካች የተነሳው ጥያቄ የጭነት መኪናው በጨረታ ከተሸጠ በኋላ ለተጠሪ ግማሽ ተከፍሏቸው ቀሪው በሞዴል 85 ተቀምጦ ፍርድ ቤቱ ያለአግባብ ቀሪውን በሙሉ እንዲሁም ከኪሴ ተጨማሪ 5,000 ብር መክፈሉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ በሰጠው ፍርድ ላይ እንደገለፀው አመልካችና ተጠሪ የሽርክና ንግድ ስራው የጋራ የሆኑትን ንብረቶች እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወሰነ እንጂ አመልካችን ባለዕዳ አላደረገም፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ የሽርክናው ዕዳ የጋራ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ በሌላ በኩል ተገቢው ታክስና ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ መኪኖችን አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በመንግሥት

ሊወረሱ የሚገባቸው እንጂ አመልካች መኪኖቹ እንዲቀርቡ ሊያደርጉ አይችሉም፡፡ ይህንንም ባለማድረጋቸው እንደባለዕዳ ተቆጥረው የግል መኖሪያ ቤታቸው እንዲሸጥ መደረጉ የአመልካችን የንብረት መብት የሚፃረር ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40 መሰረት የግል ንብረት ባለቤትነት ከለላ ያገኘ መብት ሆኖ ይህ መብትም በሕግ ሊገደብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ መኪኖቹ ሕገ-ወጥ በመሆናቸው በመንግስት ሊወረሱ የሚገባቸው እንጂ አመልካች መኪኖቹን ባለመቅረባቸው ቤታቸው በጨረታ ተሸጦ የመኪኖቹን ዋጋ እንዲከፍሉ መደረጉ የግለሰቡን የንብረት መብት የሚፃረር ነው፡፡ ምክንያቱም ፍርዱ በዓይነት እና በገንዘብ እኩል ይካፈሉ ባለበት ሁኔታ ሕጋዊ ላልሆኑት መኪኖች አመልካች ለተጠሪ ዋጋቸውን እንዲከፍሉ መደረጉ አግባብ አይደለም፡፡

ፍርድ ቤቱ መኪኖች ሕጋዊ ያለመሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ የቀረበለት በመሆኑ በዚሁ መሰረት ትዕዛዝ ማስተላለፍ ነበረበት፡፡ ምንም እንኳን አመልካች በተደጋጋሚ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባለማክበር አፈፃፀሙን ቢያጓትቱም አመልካች ባለዕዳ ሳይሆኑ የሽርክና ንግዱ የጋራ መሆናቸው ከታመነባቸው ንብረቶች ውጭ የሆነውን የአመልካች የግል ቤት እንዲሸጥ መደረጉ የአመልካችን የባለቤትነት መብት ይፃረራል፡፡ ስለሆነም የቀረበው አቤቱታ የሕገ-መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ የውሳኔ ሃሳቡ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው ክርክሩ የሚያጠነጥነው በሕገ መንግሥቱ አንቅጽ 40 ስር በተደነገገው ንብረት የማፍራት መብት ዙሪያ ሲሆን በአመልካች እና በተጠሪ ባለቤት መካከል ያለው የሽርክና ንግድ ስራ በሞት ምክንያት በመፍረሱ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድቤት አመልካችና ተጠሪ የሽርክና ንግድ ስራው የጋራ የሆኑትን ንብረቶች እኩል እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡ከዚህ ውሳኔ መረዳት የሚቻለው ተጠሪ ባለመብት አመልካች የፍርድ ባለእዳ ሳይሆኑ ሁለቱ የሽርክናውን ንብረቶች እኩል የሚካፈሉ መሆናቸውን ነው፡፡ከሽርክና ንብረቶቹ መካከል ሌሎቹን አመልካች ለተጠሪ በአይነትና በገንዘብ ካካፈሉ በኃላ በአመልካች ቤት ላይ ጨረታ እንዲወጣ ምክንያት የሆኑት ተገቢው ታክስና ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ መኪኖች ጉዳይ ነው፡፡መኪናዎቹ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በአንድ ግለሰብ ግቢ ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል የትራንስፖርት መገናኛ፣ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በጻፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡ መኪኖቹ

የጋራ ንብረታቸው እስከሆኑ ድረስ እንዲሁም ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ማስለቀቅ የሁለቱም ወገኖች ግዴታ መሆን አለበት፡፡ቀረጥና ታክስ ካልተከፈለባቸው ውጤቱ በመንግስት መወረስ ነው፡፡በዚህ ምክንያት ከአመልካች ቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በነበሩና የሁለቱም የጋራ ንብረት በሆኑ መኪናዎች መነሻነት እንደ ባለእዳ ተቆጥረው የግል ንብረታቸው የሆነው ቤት እንዲሸጥ እና የመኪናዎቹን ዋጋ እንዲከፍሉ የሚያደርግ ውሳኔ በፍርድቤቶች መሰጠቱ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን የንብረት መብት ጥበቃና ዋስትና የሚጻረር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም ምክርቤቱ አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በሚል ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተቀብሎ ከላይ እንደተገለጸው በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት የተሰጠውና በክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድቤቶች የጸናው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ጥሰት ያለበት እና የአመልካችን ሕገመንግስታዊ የንብረት መብት የጣሰ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት በአመልካች ጉዳይ የተሰጠውና በየደረጃው በሚገኙ ፍርድቤቶች የጸናው ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገ መሆኑን እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት፣ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት እና ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት እንዲደርሳቸው ይደረግ፡፡

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡

የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣5ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሚያዚያ 22 2010 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ መሰረት ታዬ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዛብሽ ገላው

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

## ውሳኔ

ጉዳይ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ጉዳዩ የንብረት ክርክርን መነሻ ያደረገ ሲሆን፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የማቻክል ወረዳ ፍ/ቤት ከተጠሪ ከቄስ ታዬ ምህረቴ ጋር በነበራቸዉ የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በአማኑኤል ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጨረታ ገዝቼ ስመ ንብረቱን በስሜ ያዞርኩት አንድ ክፍል ቤት እንደዚሁም የግሌ የነበሩ የቀንድ ከብቶች የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ናቸው በሚል የወረዳው ፍ/ቤት በመወሰኑ ነው፡፡በወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ መብቴ ስለተነካ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት ወደ ክርክሩ ገብቼ ተከራክሪአለሁ፡፡

በዚህ ክርክር ቄስ ታዬ ምህረቴ በሰጡት መልስ አምነው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ግን አከራካሪዎቹ ንብረቶች ከጋራ ንብረት ወጪ ተደርጎ የተገዙ በመሆኑ የቀድሞ ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ተጠሪ ከቄስ ታዬ ምህረቴ ጋር በነበራቸው የጋብቻ የንብረት ክፍፍል ክርክር በአማኑኤል ከተማ ቀበሌ የሚገኝ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጨረታ ገዝቼ ስመ ሀብቱን በስሜ ያዞርኩትን አንድ ደጃፍ ቤት እንደዚሁም የግሌ የነበሩት የቀንድ ከብቶችን የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በሚል የማቻከል ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊሰርዝ ይገባል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቄስ ታዬ ምህረቴ በሰጡት መልስ አምነው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ግን አከራከሪዎቹ ንበረቶች ከጋብቻችን የጋራ ንብረት ወጪ ተደርጎ የተገዙ በመሆኑ ንብረቶቹ የጋራ ሊባሉ ይገባል፣ የቀድሞ ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙንክርክር እና የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች የተመለከተው ይኸው የወረዳ ፍ/ቤት አመልካች አከራካሪውን ቤት በገዛበት ወቅት ለአካለ መጠን ያልደረሰ መሆኑ በመጥቀስ በራሱ የሽያጩ ውሉን ሊዋዋል እንደማይችል በመጥቀስ ውሉ ከመሰረቱ ፈራሽ ነው ብሏል፡፡ እንደዚሁም የሽያጭ ውሉ የ3ኛ ወገን መብት የነካ በመሆኑ ፈራሽ ነው ብሏል፡፡

እንደዚሁም አመልካች አከራካሪውን ቤት ለመግዛት የሚያስችል ሀብት ኖሮት ንብረቱን ስለመግዛቱ አላስረዳም በማለት ንብረቱን ተጠሪ እና ከላይ በስም ተጠቃሹ የቀድሞ ባለቤታቸው በእዳ ምክንያት ንብረታቸውን ባንክ ሲይዝባቸው በአመልካች ስም ከራሣቸው የጋራ ሀብት አውጥተው ያስገዙት የጋራ ንበረታቸው እንጂ የአመልካች የግል ሊባል አይችልም በማለት አከራካሪዎቹን የቀንድ ከብቶችም በተመለከተ ከተጠቃሹ ጋብቻ የጋራ ሀብት ውጭ ተደርጎ የተገዙ በመሆኑ የባልና ሚስቱ የጋራ ናቸው በማለት ቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

በጉዳዩም ላይ በአመልካች ይግባኝ የቀረበለት የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት አመልካች የደረገውን የቤት ግዢ ውል በተመለከተ የደረሰበትን ድምዳሜ በመንቀፍ ውሉ ፈራሽ ሊሆን የሚችለው አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ጥቅም በሚጎዳ መልኩ በተደረገ ጊዜ መሆኑን በመጥቀስ በሌላ በኩል አመልካች ባቀረባቸው

በሰነድ ሆነ በሰው ማስረጃዎች በሚገባ ያስረዳ መሆኑን በመጥቀስ እንደዚሁም አከራካሪዎቹን የቀንድ ከብቶችም በተመለከተ አመልካች ባቀረባቸው ሁለት የውል ሰነዶች እና የሰው ማስረጃዎች በሚገባ ያስረዳ መሆኑን በመጥቀስ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በጉዳዩ ላይ በተጠሪ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል በተጠሪ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር እና የወረዳው ፍ/በት ውሣኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

በጉዳዩ ላይ አመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌደራሉ ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለመግዛት የራሱን የሃብት ምንጭ የተጠቀመ መሆኑ በስር ፍ/ቤት አልተረጋገጠም እንደዚሁም አንድ ሰው የንብረት ባለሃብት የሚሆነው በጉልበቱ በፈጠራ ችሎታው ወይም በገንዘቡ ንበረት ያፈራ ሲሆን እንጂ በስሙ ስለተመዘገበ ብቻ የግሉ ሊሆን አይችልም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

ከላይ ጸንቶ ባለው የአመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ሃሣብ ተጠሪ ከቁስ ታዬ ምህረቴ ጋር በነበራቸዉ የጋብቻ የንብረት ክፍፍል ክርክር በአማኑኤል ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጨረታ ገዝቼ ስመ ሀብቱንም በስሜ ያዞርኩት አንድ ደጃፍ ቤት እንደዚሁም የግል የነበሩት የቀንድ ከብቶችን የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በሚል የማቻከል ወረዳ ፍ/ቤት ወስኖ ነበር፡፡

ውሳኔውን መብቴን ነክቷል በሚል በፍ/ሥ/ይ/ሕ/ቁ 358 ወደ ክርክሩ ገብቼ እንድከራከር ጠይቆ ብከራከርም አመልካች በወቅቱ እጻን በመሆኑ ውል መዋዋል አይችምል እንደሁም ንብረቶቹ የተገዙት በባልና ሚስቱ ገንዘብ ነው በማል

ንብረቶቹን የባልና ሚስቱ የጋራ በማድረግ የተሰጠውን ውሣኔ በመጨረሻ በመጽናቱ በሕገ መንግስቱ ያለኝን የንብረት መብት ይጥሳል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉባኤው በቀረበለት አቤቱታ መነሻ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፍ/ቤቶች በነበረ ክርክር ተጠሪ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ቤቱ በባንክ ዕዳ ምክንያት ሲሸጥ ወጪው ከቀድሞ ባለቤታቸው አቶ ታዬ ምህነቴ ጋር ከነበራቸዉ የጋብቻ ሀብት ወጪ በማድረግ በአመልካች ስም ቤቱ የተገዛ መሆኑን እንደዚሁም በተመሳሳይ አከራካሪዎቹ የቀንድ ከብቶችም ከተጠቀሰው የጋብቻ የጋራ ሀብት ወጪ ተደርጎ የተገዙ መሆናቸውን በመጥቀስ ንብረቶቹን በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ ስለሆነ የጋራ ይባሉልኝ የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቶችም ግራ ቀኙን አከራክረው በዋናነት አመልካች አከራካሪዎቹን ንብረቶች ከራሱ የሀብት ምንጭ ወጪ አድርጎ ስለመግዛቱ አላስረዳም በሚል ምክንያት ላይ በመመስረት ንብረቶቹን የተጠሪና የቀድሞ ባለቤታቸው አቶ ታዬ ምህነቴ በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ የጋራ ሀብት ናቸው በማለት መወሰናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን ፍ/ቤቶች ተጠሪ የቀድሞ ባለቤታቸው አቶ ታዬ ምህረቴ በአንድ በኩል የሚፈለግባቸውን የባንክ ዕዳ መክፈል አቅቷቸው አከራካሪው ቤት በጨረታ ሊሸጥ የቻለ መሆኑን አረጋግጠው በሌላ በኩል አከራካሪውን ቤት ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ አቅም ኖሯቸው ከጋራ ሀብታቸዉ ወጪ አድርገው አከራካሪውን ቤት ገዝተዋል ሲሉ መደምደማቸውን ስንመለከት የተጠቀሰው ምክንያትና ድምዳሜ አብረው የሚሄዱ አለመሆናቸውን መረዳት የሚቻል ሲሆን ይልቁንም ፍ/ቤት የተጠቀሱት አከራካሪው ቤት ከተጠቃሹ የጋብቻ ሀብት ወጪ ተደርጎ ያልተገዛ መሆኑን ያስረዳል ለሚል ድምዳሜ የቀረበ ነው፡፡

በተጨማሪም ፍ/ቤቶች በተለይ አከራካሪው ቤት ከተጠቃሹ ጋብቻ የጋራ ሀብት ወጪ ተደርጎ የተገዛ ነው ብለው እንደወሰዱት ግምት እንኳ ቢሆን ዕዳዉን ቀድሞውኑ

በቀጥታ መክፈል እየቻሉ ባለመክፈል ንብረታቸውን እንዲሸጥ በመፍቀድ በተዘዋዋሪ በአመልካች ስም ቤቱን የመግዛታቸው ድርጊት ተጠሪ ከቀድሞ ባለቤታቸው ጋር በመሆን ህግን በተቃረነ መልኩ አንዳች ኃላፊነት ለመሸሸ ወይም ለሕገ ወጥ አላማ ሲሉ የከወኑት ተግባር ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ ከቀድሞ ባለቤታቸው ጋር በመሆን በፈጸሙት ህግን የተቃረነ ተግባራቸው ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባ አይደለም፡፡ ተጠሪና የቀድሞ ባለቤታቸው ህግን ባልተቃረነ መንገድ አከራካሪዎቹን ንብረቶች በፈቃዳቸው ከጋራ ንብረታቸው ወጪ በማድረግ አካለመጠን ባልደረሰ በአመልካች ስም ገዝተዋል፡፡ ብሎ መነሳት ከምክንያታዊነት እና ሕገ መንግስታዊ መሰረት ካለው የሕፃናትን ጥቅም በቀደምትነት ከማክበር መርህ ጋር የሚቃረን ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በተለይ አከራካሪውን ቤት ስመ ሀብቱን በስሙ አድርጎ ማስረጃውን ይዞ የሚገኝ ሆኖ እያለ በዚህም በፍ/ሕ/ቁ 1195 መሰረት አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ስመ ሀብቱን በስሙ በማድረግ ማስረጃውን በእጁ ያደረገ ሰው የንብረቱን ባለቤት እንደሆነ የሚገመት ስለመሆኑ ተደንግጎ እያለ፣ እንደዚሁም ይህንኑ ድንጋጌ ተከትሎ በሚገኘው አንቀጽ 1196 መሰረት የቀረበ ግምቱን ሊያስተባብል የሚችል ክርክርም ሆነ ማስረጃ በሌለበት አልያም ሌላ ሕጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ፍ/ቤቶች አከራካሪዎቹ ንብረቶች አንድ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ንብረት ከሚያፈራባቸው መንገዶች በአንዱ የተገኙ ንበረቶች ስለመሆናቸው መነሻ ግምት በመያዝ በተቃራኒው ሕግ በሚፈቅደው አግባብ ተጠሪ ማስተባበሪያ ማቅረብ አለማቅረባቸውን መመርመር ጉዳዩን መመልከት እየተገባቸው በተቃራኒው አመልካች ስለሙብታቸው እንዲያስረዱ ግዴታን በመጣል መወሰናቸውን የሕፃናት የተሻለ ጥቅም ለማስጠበቅ በሚረዳ መልኩ ውሳኔ የሰጡ አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ በመሆኑ ፡፡

8

ውሳኔው በኢ..ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትተ አንቀጽ 36 (2) ሕፃናት የሚመለከቱት እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ መንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጊነት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕገ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት፣በሚል የሰፈረው ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ እንደዚሁም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 የሰፈረውን የንብረት መብት ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ  አግባብ አለመሆኑን ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲያውቁትና እንዲያስፈጽሙ ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የውሳኔ ሀሳብ ም/ቤቱ በሰጠው የሕገ መንግስት ትርጉም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን እንዲያውቁት ውሳኔው ይድረሳቸው፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካች ይድረሳቸው፡፡

# የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት 6ኛ የፓርላማ ዘመን 2ኛ አመት

## 2ኛ መደበኛ ጉባኤ

የመ/ቁጥር 106/15

ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ አለበል ሲሳይ

ተጠሪ፡- መምሬ ሲሳይ አካለ

የኢ.ፌዲሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ባቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ የሚከተለው ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 06/10/10 በተጻፈ ማመልከቻ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩ የመኖሪያ ቤት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በአጭሩ በአዲስ አበባ በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ መኖሪያ ቤት በስሜ ተመዝግቦ የሚገኝ ነው፡፡

በቤቱ ውኃና መብራት በስሜ ያስገባሁበት ሲሆን ተጠሪ አባቴ ስለሆኑ ከክፍለ ሀገር ሲመጡ እንዲኖሩበት ፈቅጄላቸው እንዲያስተዳድሩትም ውክልና ሰጥቻቸው ነበር፡፡በዚህ መሰረት ግቢ ውስጥ ያሉትን ቤቶችም እያከራዩ ነበር፡፡ ተጠሪ አሁን ቤቱን አላስረክብም ስላሉኝ ቤቱን እንዲያስረክቡኝ እና የኪራዩን ገንዘብ እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች በ1981 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት አቶ ባዬ አካሌ የሚባሉ ግለሰብ ቤት አዋሳኝ ላይ ቤት እና ግቢ የነበረው ሲሆን በወሰን ግጭት

ምክንያት ቤቱን አፍርሶ ንብረቱን ወስዷል፡፡ እኔ ከሌሎች ልጆቼ ጋር በ1984 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ግጭት ከተነሳበት ይዞታ በመራቅ በመንግስት ቦታ ላይ በራሴ ወጪ አሁን ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ሰርቻለሁ፡፡

አመልካች ልጄ ስለሆነ የግብር ደረሰኞች በስሙ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡በኋላም ይዞታው ነባር ይዞታ ስለነበር ተጠሪ ተከታትሎ ካርታ እንዲያወጣበት የካርታ ማውጫ 11000.00 (አስርአንድ ሺህ) ብር ሰጥቸው በስሙ ካርታ አውጥቷል፡፡ የቤቱ ስመ ሃብት በተጠሪ የተመዘገበ ቢሆንም ቤቱን ግን የሰራሁት እኔ ነኝ፡፡

የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት በስሙ የተመዘገበ ሰው የቤቱ ባለቤት ነው ተብሎ የሚገመት ቢሆንም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 መሰረት አንድ ሰው በገንዘቡ እና በጥረቱ ያፈራው ንብረት ለመሆኑ በሌላ ማስረጃ ማስረዳት ሲቻል ግን ይህ ተቀባይነት የማይኖረው እንደሆነ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አግባብ ውሳኔ ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር የሰማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የማን ነው የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምሯል፡፡ በዚህ መሰረት ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ላይ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የከተማ ቦታ እና ቤት ግብር እንዲሁም መብራት እና ውሃ የገባው በአመልካች ስም ነው፡፡በፍ/ሕግ አንቀጽ 1195 መሰረት ለአመልካች በሚመለከተው አካል የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በፍ/ሕጉ አንቀጽ 1196 መሰረት በሕገ ወጥ መንገድ የተሰጠ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡

የአመልካች ምስክሮች እንዳረጋገጡት አመልካች በ1981 ዓ.ም የመንግስት የሆነ ቦታ አጥረው ይዘው በ1983 ዓ.ም ደግሞ በቦታው ላይ 3 ክፍል ቤት ሰርተዋል፡፡ በ1997 ዓ.ም ደግሞ ትልቁ ቤት መስራቱን እና ተጠሪ ደግሞ በ1988 ወደ አዲስ አበባ የመጡ ሲሆን ትልቁ ቤት ሲሰራ ተጠሪ ከልጆቻቸው ጋር የነበሩ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

በሌላ በኩል የተጠሪ ምስክሮች ደግሞ ትልቁ ቤት በ1991 ዓ.ም ቀድሞ የነበሩት ትንሽ ቤቶች ፈርሰው የተሰራ መሆኑን ተጠሪ ቤቱን ሲያሰሩ ማየታቸውን እና ገንዘብ እራሳቸው ይከፈሉ እንደነበር ሆኖም ገንዘቡ ከየት እንደመጣ የማያውቁ መሆኑን መስክረዋል፡፡

ተጠሪ ቤቱ በራሳቸው ገንዘብ የተሰራ መሆኑን ቢከራከሩም ተጠሪ በ1988 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ከመምጣታቸው በፊት አመልካች ቦታውን ቀድመው ይዘው ሶስት ቤቶችን የሰሩ መሆኑን፣ ትልቁ ቤትም ቢሆን በ1991 ዓ.ም ሲሰራ ቤቱ በተጠሪ ገንዘብ የተሰራ መሆኑ ስላልተረጋገጠ ቤቱ የአሁን አመልካች ንብረት ነው ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት መጀመሪያ ተጠሪ ወደ አዲስ አበባ ሳይመጡ በፊት ተሰርተው የነበሩት ትንሽ ቤቶች ፈርሰው አዲስ ትልቅ ቤት የተሰራ መሆኑን፣ ቤቱ የተሰራውም በተጠሪ ገንዘብ ጭምር መሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡

አመልካችም በቤቱ መሰራት ሂደት ውስጥ የገንዘብ እና የጉልበት አስተዋጽኦ አልነበራቸውም ማለት ስለማይቻል ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

ቀጥሎ በአሁን አመልካች የይግባኝ ቅሬታ ክርክሩ የቀረበለት ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አከራካሪው ቤት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያለው እና ከበፊትም ጀምሮ ይዞታውን ይዞ ያለው አመልካች በመሆኑ አላከራከረም፡፡

ነገር ግን ይህ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አመልካች ብቸኛ የቤቱ ባለሃብት ያደርጋል ወይ የሚለው ጭብጥ በመያዝ እንደተመረመረ ተረድተናል፡፡ በዚህ መሰረት ቀድሞ በይዞታው ላይ የነበረው የአመልካች ቤት በ1991 ዓ.ም የፈረሰ መሆኑ እና አዲስ ቤት ሲሰራ የአሁን ተጠሪ ቤቱ የተሰራበትን ገንዘብ የግንባታ ዕቃዎችን ሲገዙ እንደነበረ በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ስለሆነም ምንም እንኳን የቤቱ ስመ ንብረት ተመዝግቦ ያለው በአመልካች ቢሆንም ተጠሪ በቤቱ መሰራት ሂደት የገንዘብ እና የጉልበት አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ተረጋግጧል በማለት የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡በመጨረሻ ጉዳዩን በሰበር አቤቱታ የተመለከተው ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔው የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ዘግቷል፡፡

አመልካች ለጉባኤ ባቀረቡት አቤቱታ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ተጠሪ አባቴ ወደ አዲስ አበባ ሳይመጡ በፊት በ1983 ዓ.ም ጀምሮ ግብር እየከፈልሁ በስሜ ተመዝግቦ

የሚገኝ ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስተዳድሩ ውክልና ሰጥቼያቸው ያስተዳደሩት እንጂ የእራሳቸው ጉልበትም ሆነ ገንዘብ የለበትም፡፡

ቤቱ የተሰራው በእኔ ለመሆኑ የቤት መስሪያ ዕቃዎች የተገዙበት ደረሰኝ፣ ቤቶቹን ሳከራይ የነበርሁት እኔ ለመሆኔ እና በገቢዎች እና የግብር ከፋይ መለያ የተሰጠኝ፣ ውሃ እና መብራት በራሴ ስም ያስገባው መሆኑ እና ሌሎችንም ማስረጃዎች በመጥቀስ ቤቱ የግል ሀብቴ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ፍ/ቤቶች ከዚህ ውጪ በመውጣት የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ የንብረት መብቴን የሚጠስ ስለሆነ በውሳኔው ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤው አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ካጣራ እና ከመረመረ በኋላ በጉድዩ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልጋል የሚል እምነት የሚያሳድር ሆኖ በማግኘቱ ለትርጉም አሰጣጡ መሰረት የሆኑትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጭብጦች በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ 4 ገጽ መልስ አቅርበዋል፡፡

የተጠሪ ዋና ክርክር አከራካሪው ቤት የተፈራው በግራ ቀኙ ጉልበት፣ ገንዘብ እና ካፒታል መሆኑን ፍርድ ቤቶች በማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡የጋራ ባለሃብትነት ከሚፈጠርበት መንገድ አንዱ በጋራ ጉልበት፣ ካፒታልና ጥረት ነው፡፡ ምንም እንኳን ንብረቱ ተመዝግቦ ያለው በአንድ ሰው ቢሆንም አከራካሪው ንብረት የተፈራው በጋራ ጥረት፣ ካፒታልና ጉልበት መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ንብረቱ የጋራ ይሆናል፡፡ስለሆነም የግልም ሆነ የጋራ ንብረት የሚፈራው በጥረት፣ በጉልበት እና በካፒታል እስከ ሆነ ድረስ ንብረቱ በበአድኛው ሰው መመዝገብ የንብረቱን መፈራት ለአንድ ሰው ብቻ የሚሰጥ አይደለም፡፡

የይዞታ ማረጋገጫን በተመለከተም አከራካሪው ጉዳይ ቤቱ የተሰራበት ይዞታ የማን ነው የሚል ሳይሆን በይዞታው ላይ በጋራ ጉልበት የተፈራው ቤት የጋራ ነው የሚል ነው፡፡ ይይዞታ ማረጋገጫ የሚያረጋግጠው ይዞታውን እንጂ በይዞታው ላይ የተፈራ ቤትን ስላልሆ የይዞታ ማረጋገጫ በአመልካች ስም መሆኑ ብቻ በይዞታው ላይ ያለውን ቤት የግል አያደርገውም፡፡

መተጨማሪም በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1199 (1) መሰረት ባለቤቱ በሌላ ሰው መሬት ላይ ቤት የሰራ የሚለው የመሬት ባለቤትነት የግለሰብ በነበረበት ጊዜ የወጣ እና የኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግስት መሬትን የመንግስት ካደረገ በኋላ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ስለሆነም በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ገንዘቡን አፍስሶ ቤት የሰራ ሰው የዚሁ ቤት ባለቤት ስለሚሆን የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብት አይጥስም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በፍ/ቤቶች የነበረው ክርክር፣ የአመልካች የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ይዘትና የተጠሪ መልስ ከላይ የተገለጸው ሲሆን መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው የውሳኔ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ተመዝግቦ የሚገኘው በአሁን አመልካች ስም እንደሆነ በፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡አመልካች ክስ ሲያቀርቡ አከራካሪው ቤት የተሰራበት ይዞታ በ1983 ዓ.ም ጀምሮ በእጃቸው የነበረና ሶስት ክፍል ቤት የተሰራበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ተጠሪ አከራካሪው ቤት የራሳቸው መሆኑን የሚከራከሩት ቤቱ እና ይዞታው በስማቸው ስለተመዘገበ ሳይሆን አከራካሪው ቤት የተሰራው በእኔ ገንዘብ ነው በሚል ነው፡፡

ፍ/ቤቶችም ከተጠሪ ምስክሮች ያረጋገጡት አከራካሪው ይዞታ ቀድሞ በአመልካች የተሰራ ቤት የነበረው ሲሆን በኋላ ግን ትልቁ ቤት ሲሰራ ብቻ ተጠሪ ቤቱን ያሰሩ እና የቤቱን መስሪያ ገንዘብ ሲከፍሉ እንደነበር በምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡

በአጠቃላይ በፍ/ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠው አከራካሪው ይዞታ ቀድሞ አመልካች የነበረ ስለመሆኑ፣ በፊት የተሰሩት ቤቶችም በአመልካች ተሰሩ መሆኑን፣በኋላ ትልቁ ቤት ሲሰራ ብቻ ተጠሪ ቤቱን ያሰሩ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አመልካች አከራካሪውን ቤት እንዲያስተዳድሩ የውክልና ስልጣን ለተጠሪ የሰጡ መሆኑን ነው፡፡ከዚሁ ሁሉ መረዳት የሚቻለው አከራካሪው ቤት እና ይዞታ በአመልካች ስም ከመመዝገቡ እና ግብር በስሙ ከመከፈሉ በላይ ተጠሪ ቤቱን በውክል እና ስልጣን ያስተዳድሩ የነበረ መሆኑን ነው፡፡

በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) መሰረት አንድ ሰው በጉልበቱ ፣ በፈጠራ ችሎታውና በገንዘቡ ላፈራው ንብረት ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡የንብረት መብት መጠን እና ስፋቱ በሕገ መንግስቱ ያልተገለጸ ቢሆን በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ

1204 እና ቀጣይ ቁጥሮች ላይ እንደተደነገገው ሀብት ማለት በአንድ ግዙፍ ንብረት ላይ የሰፋ መብትን የያዘ ማለት ሲሆን ይህ ሰፊ መብት በማይቀሳቀስ ንብረት ላይም የሚገኝ ነው፡፡

በማይቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚገኘው ሰፊ የንብረት መብት ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን ይህ ሕገ መንግስታዊ መብትም ተገቢው ጥበቃ እንዲኖረው ከሚያስችሉ መንገዶች ውስጥ አንዱ ዜጎች በንብረት ላይ ያላቸውን መብት የሚያረጋግጡበት ማስረጃቸውን በመስጠት ነው፡፡ በማይቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ወይም ማስረጃ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1195 በልዩ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ይህ በልዩ ሁኔታ የተደነገገው ማስረጃም እንዲሁ ሳይሆን የራሱ ልዩ ዓላማ ያለው ነው፡፡

በተለይም ህጉ ለማይቀሳቀሱ ንብረቶች ልዩ ጥበቃ መስጠት የፈለገበት ምክንያት እነዚህ ንብረቶች ባለይዞታው መብቱን ሲያገኝ ወይም በሆነ ምክንያት ወደ ሌላ ሶስተኛ ወገን በሚያስተላልፍበት ወቅት የመመዝገብ ስልጣን በተሰጠው መንግስታዊ አካል ካልተመዘገበ በህግ ፊት የሚጸና መብት እንዳይኖረው በማድረግ ዜጎች በማይቀሳቀስ ንብረት ላይ ያላቸው መብት ከፍላጎታቸው ውጪ በሆነ መንገድ ንብረቱን እንዳያጡ ጥበቃ ለመስጠት ነው፡፡በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚሰጠው ይህ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድም በሕገ ወጥ መንገድ ቢሰጥም በምን አግባብ ሊስተባበል እንደሚችል በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1196 ላይ ተደንግጓል፡፡

ይህም ዜጎች በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን የማይቀሳቀስ ንብረት ላይ ያላቸውን መብት በጥብቅ ሁኔታ የሚያረጋግጡበትን መንገድ ለመግለጽ የተቀመጠ ነው፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው ይዞታ በአመልካች ስም በከተማ መስተዳደሩ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ይዞታው ነባር ይዞታ እንደ መሆኑ መጠን ይዞታው ቀድሞ የተመዘገበው እና ግብርም ሲከፈል የነበረው በአመልካች ስም ነው፡፡አመልካች በዚህ መልኩ በከተማ መስተዳደሩ በስማቸው ተመዝግቦ ያለውን ይዞታ ያገኙት በሕገ ወጥ መንገድ ስለመሆኑ ፍ/ቤቶች በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1196 መሰረት ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ይልቁንም ፍ/ቤቶች አከራካሪው ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ነው ለማለት ምክንያት ያደረጉት ተጠሪ ትልቁን ቤት ሲያሰሩ በቤቱ ግንባታ ላይ ገንዘብ ስለማዋጣታቸው ባልተረጋገጠበት እና ማዋጣታቸው ተረጋግጧል ቢባል እንኳን ምን ያህል የገንዘብ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ በግልጽ በማስረጃ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ይህ ባልሆነበት ሁኔታ አከራካሪውን ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ነው መባሉ በአግባቡ አለመሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

የጋራ ሀብትነት ስለሚመሰረትበት ሁኔታ በፍተሐብሔር ሕግ አንቀጽ 2258 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች ተቀምጧል፡፡ በፍተሐብሔር ሕግ አንቀጽ 2258(1) መሰረት የጋራ ባለሃብቶች መብትና ግዴታዎች የሚወስኑት የጋራ ሀብቱ በተቋቋመበት የውል ስምምነት ወይም በሕግ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው የጋራ ባለሃብትነት የሚቋቋመው ወይም የሚመሰረተው 1ኛ በጋራ ባለሃብቶች መካከል በሚደረግ የውል ስምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በህግ በግልጽ የጋራ ሃብትነት ሲቋቋም ብቻ ነው፡፡

ፍ/ቤቶች በሕገ መንግስቱ እና በሕግ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ለቀረበባቸው ጉዳይ ሕግን በመተርጎም ውሳኔ ወይም ፍርድ ይሰጣሉ፡፡ በተለይም ግልጽ ሕግ ሲኖር ያንኑ ተፈጻሚ ከማድረግ ባሻገር አዲስ ሕግ በትርጉም ምክንያት ሊፈጠሩ እንደማይችሉ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በተያዘው ጉዳይ ፍ/ቤቶች በሕግ በግልጽ ካልተቀመጠ በውሳኔው ወይም በፍርድ የጋራ ባለሃብትነትን ሊያቋቁሙ አይችልም፡፡

ተጠሪ ለጉባኤው ባቀረቡት መልስ የጋራ ባለሃብትነት በፍርድ ሊፈጠር ይችላል በማለት ክርክር ቢያስቀርቡም ይህ በሕግ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ፍ/ቤቶች በሕግ ወይም በውል በተፈጸመ የጋራ ባለሃብትነት አግባብ ውሳኔ ከሚሰጡ በስተቀር በሕግ ባልተደነገገ እና ባልተፈቀደ ሁኔታ የጋራ ባለሃብትነትን በፍርድ ብቻ ሊፈጥሩ አይችሉም፡፡

ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ በተመለከተም ባቀረቡት ክርክር በአከራካሪው ይዞታ ላይ የተገነባው ቤት በጋራ ጥረት የተገነባ ስለሆነ ይዞታው በአመልካች ስም መመዝገቡ ብቻውን አመልካችን የቤቱ ባለሃብት አያደርገውም ቢሉም ክርክሩ ከፍተሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1195 አንጻር ተቀባይነት የለውም፡፡

አንድ ሰው በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ንብረት ሊያፈራ እና በተፈራው ንብረት ላይም ሕገ መንግስታዊ እና ሕገዊ መብት ሊያገኝ የሚችለው ከባለይዞታው ጋር በሚደረገው ስምምነት

መሰረት ነው፡፡በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) መሰረት ንብረት የሚፈራው በጥረት እና በገንዘብ ቢሆንም ጥረቱ መደረግ ያለበት በሕጋዊ መንገድ ነው፡፡

በሕገ መንግስቱ መሰረት መሬት የመንግስት እና የሕዝብ ሲሆን ዜጎች ደግሞ በመሬት የመጠቀም ሕገ መንግስታዊ መብት አላቸው፡፡ በመሬት የመጠቀም መብት ያለው ሰው በቅድሚያ መሬቱን በሕጋዊ መንገድ ያገኘ ስለመሆኑ ለዚህም ማረጋገጫ ከአስተዳደር አካል የባለይዞታነት ማረጋገጫ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፡፡በዚህ ሁኔታ ባገኘው እና በተመዘገበው መሬት ላይ በጉልበት፣ በመፍጠር ችሎታ እና በካፒታል የሚፈራ ማናቸውም ንብረትም ሕገ መንግስታዊ እና ሕጋዊ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

አንድ ሰወው በሕገ ወጥ መንገድ ባገኘው ወይም የራሱ የመጠቀም መብት በሌለው ይዞታ ላይ ንብረት ቢያፈራ፣ ንብረቱ የተፈራው በጉልበቱ፣ በገንዘቡ፣ ወይም በፈጠራ ችሎታው ቢሆንም በቤቱ ላይ ሙሉ የባለሃብትነት ሕገ መንግስታዊ መብት እና ጥበቃ የሚያገኘው ቀድሞ በመሬቱ የመጠቀም መብት ከመንግስት ወይም ከባለይዞታው ሲያገኝ ነው፡፡አንድ ሰው በራሱ ባል ሆነ ይዞታ ላይ ቤት አፍርቶ ከተገኘም ከባለይዞታው ጋር ባለው ህጋዊ መሰረት ጉዳዩ መፍትሄ የሚያገኝ እና ያወጣውን ገንዘብ ከሚጠይቅ በቀር የቤቱ ባለሃብት ሊሆን አይችልም፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው ይዞታ እና ቤት መነሻው የአመልካች ንብረት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ፍ/ቤቶች ቤቱ የጋራ ሃብት ነው ብለው ለመወሰን ምክንያት ያደረጉት ትልቁ ቤት ሲሰራ ተጠሪ በቤቱ ግንባታ ላይ የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርገዋል በሚል ሲሆን ይህንንም ያረጋገጡት በሰው ምስክሮች ነው፡፡

ነገር ግን የፍተሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1195 በግልጽ እንደሚደነግገው የመሬት ባለይዞታነት መብት እንዲሁም እንዲሁም የቤት ባለሃብትነትን መብት ማረጋገጥ የሚቻለው በሰነድ ማስረጃ ብቻ ነው፡፡ተጠሪ በመሬቱ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ያላቸው ሲሆን ቤቱን በሚመለከትም የጋራ ሃብት ወይም ቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ወይም ማረጋገጫ ሰነድ የለም፡፡

የፍ/ቤቶች የፍተሐብሔር ሕግ አንቀጽ 2258 እና ተከታዮቹን ሲተረጉሙ ሕገ መንግስታዊ በሆነ መልኩ መተርጎም ይጠበቅባቸዋል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት የጋራ ባለሃብትነት ሊቋቋም የሚችለው በውል እና በህግ ብቻ መሆኑ በግልጽ ተደንግጓ እያለ ህጉ ካስቀመጠው

መስፈርት ውጪ ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ስራ ላይ የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርገዋል በሚል የጋራ ሃብትነት መፍጠር በሕገ መንግስቱ ለአመልካች ተጠብቀውን የንብረት መብት መሰረት በማድረግ ጋራ ባለሃብትነት ሊፈጠር የሚችለው በግራ ቀኙ መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም በሕግ ብቻ መሆኑን በሚደነግገው ሕግ ብቻ በመመራት ጉዳዩ መታየት የሚገባው ሆኖ እያለ ፍ/ቤቶች የጋራ ባለሃብትነትን የፈጠሩበት መንገድ ሕገ መንግስታዊ አይደለም፡፡

ተጠሪ በተፈራው ቤት የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርገዋል የሚባልም ከሆነ ተጠሪ ለቤቱ ያወጡትን ገንዘብ ከሚጠይቁ በቀር የቤቱ የጋራ ባለሃብት ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረውን የውክልና ውል መሰረት በማድረግ ተጠሪ ቤቱን ያሰሩት በውክልና ውሉ መሰረት መሆን አለመሆኑ እና ይህን የውክልና ውል ቀሪ የሚያደርግ እና ቤቱን የጋራ የሚያደርግ ሌላ ስምምነት በግራ ቀኙ መካከል በሌለበት ሁኔታ የጋራ ባለሃብትነትን መፍጠር በሕግ የሚቻል አይደለም፡፡

ከዚህ ቀደም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቦበት በፌደሬሽን ም/ቤት በመዝገብ ቁጥር 022/08 ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም የሕገ መንግስት ትርጉም የተሰጠበት ውሳኔ በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1195 አግባብ በአንድ ንብረት ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ያለው ሰው ማስረጃው ሊስተባበል የሚችለው በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1196 በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡፡በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠው ባለሃብትነት ለምሳሌ በሰው ምስክሮች ሊስተባበል የማይችል ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቶች ግን ሕጉን ከሕገ መንግስቱ የንብረት መብትን የሚጥስ በመሆኑ ተገልጾ ተወስኗል፡፡

በተመሳሳይ በዚህ ጉዳይ ጉዳይ አመልካች በይዞታው ላይ በህጋዊ መንገድ የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያላቸው ስለሆነ የይዞታው ባለመብት አመልካች ናቸው፡፡በይዞታው ላይ የተሰራውን ቤትም በሚመለከት ከሚመለከተው የከተማ መስተዳደር የቤቱ ባለ፤ሃብት ከአመልካች ውጪ ስለመሆኑ ወይም ከተጠሪ ጋር በቤቱ ላይ የጋራ ባለሃብት በመሆናቸው በተመሳሳይ የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በቤቱ መፈራት ላይ የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርገው ከሆነ ይህንኑ ገንዘባቸውን ሕግ የሚፈቅድላቸው ከሆነ ከሚጠይቁ በስተቀር በአመልካች ስም በተመዘገበ ንብረት ላይ የጋራ ባለሃብት የሚሆኑበት አግባብ የለም፡፡

አመልካች ባላቸው ነባር ይዞታ ከላይ ቤት ገንብተው ቤቱም የራሳቸው መሆኑን በህግ አግባብ የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አቅርበው እያለ ፍ/ቤቶች ከዚህ ውጪ በመውጣት የሰጡት ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ የንብረት መብት የሚጥስ ስለሆነ ውሳኔው ተፈጻሚነት የለውም፡፡

ስለሆነም በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጀምሮ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 143686 በቀን 23/12/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (1) የሚጥስ ስለሆነ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው እና አከራካሪው ይዞታ በአመልካች ስም ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 84 (1) መሰረት የፌደሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ትርገም ያስፈልገዋል በማለት እንዲሰጥ የውሳኔ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

ከላይ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ሲታይ አንድ ሰው የመጠቀም መብት በሌለው ይዞታ ላይ ንብረት ቢያፈራ፣ ንብረቱ የተፈራው በጉልበቱ፣ በገንዘቡ፣ ወይም በፈጠራ ችሎታው ቢሆንም በቤቱ ላይ ሙሉ የባለሃብትነት ሕገ መንግስታዊ መብት እና ጥበቃ የሚያገኘው ቀድሞ በመሬቱ የመጠቀም መብት ከመንግስት ሲያገኝ ነው፡፡አንድ ሰው በራሱ ባል ሆነ ይዞታ ላይ ቤት አፍርቶ ከተገኘም ከባለይዞታው ጋር ባለው ህጋዊ መሰረት ጉዳዩ መፍትሄ የሚያገኝ እና ያወጣውን ገንዘብ ከሚጠይቅ በቀር የቤቱ ባለሃብት ሊሆን አይችልም የሚለው መሰረታዊ ነጥብ ነው፡፡

ተጠሪ በተፈራው ቤት የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርገዋል የሚባልም ከሆነ ተጠሪ ለቤቱ ያወጡትን ገንዘብ በሕግ አግባብ በሚለከተው የፍትህ አካል ከሚጠይቁ በቀር የቤቱ የጋራ ባለሃብት ሊሆኑ የሚችሉበት የሕገ መንግስት አግባብ አላገኘንበትም፡፡ ቤቱን በጋራ ለማድረግ የተስማሙበት የውል ሰነድ እስከሌለ ድረስ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40(1) መሰረት መብታችን ተጣሰ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

በመሆኑም የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (1) እና (2) ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ትዕዛዝ

1. በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፍርድ ተሰጥቶ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ተብሎበት ቤቱ የጋራ ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ እስከ ፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የጸናው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን በምክር ቤቱ መወሰኑን አውቀው በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽሙ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

31

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት 6ኛ የፓርላማ ዘመን 2ኛ አመት

2ኛ መደበኛ ጉባኤ

የመ/ቁጥር 105/15

ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ ጎዳና ጎዴቦ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አይናለም ጌታቸው

የኢ.ፌዲሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ባቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ የሚከተለው ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 06/10/10 በተጻፈ ማመልከቻ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ባቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩ የመኖሪያ ቤት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል መንግስት ሀድያ ዞን በሾኔ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ የክሱይዘትም የአሁን ተጠሪ የሚች ባለቤቴ እህት ስትሆን ተጠሪዋ የመኖሪያ ቤት ችግር ስላጋጠማት ካለን ዝምድና አንጻር በእህትነት እንድትኖርበት አሁን ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ሰጠኋት፡፡

ተጠሪ በዚህ ቤት ለረጅም ጊዜ ስትኖርበት ቆይታ ቤቱን ለመስራት ስለፈለግሁ እንድትለቅልኝ በ2006 ዓ.ም ስጠይቃት ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልሆነች በሕግ ተገዳ እንድትለቅልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የአሁን ተጠሪ አሻሽለው ባቀረቡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሲያነሱ አከራካሪው ቤት የአመልካች የግል ቤት ሳይሆን የአመልካች ሚስት ከሞተች ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ከ 20 አመት በኋላ ያቀረበው ክስ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል፡፡

ቤቱ ሰነድ አልባ ሳይሆን በምሪት አግኝቼ የመንግስት ግብር እየከፈልኩ የኖርኩበት ሲሆን አሁን ደግሞ በገጠመኝ የገንዘብ እጥረት ምክንያት ግብር አለመክፈሌን ምክንያት በማድረግ አመልካች በተጭበረበረ መንገድ ከከተማው መስተዳድር መሀንዲሶች ጋር በመመሳጠር ሰነድ አልባ ይዞታ ነው በማለት በሀሰት የይዞታ ማረጋገጫ ያወጣበት ነው፡፡ አከራካሪው ቤት የእኔ በመሆኑ በስሜ መብራትና ውሀ ያስገባሁበት ነው፡፡ በቤቱ የአመልካች ባለቤት ከነበረች እህቴ ጋር በጋራ የኖርንበት እንጂ የአመልካች አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ የሰማው የወረዳው ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩ ክርክር ላይ ማስረጃ ሰምቷል፡፡ የአሁን አመልካች የሰው ምስክሮች እንዳረጋገጡት አከራካሪውን ይዞታ አመልካች በሀይለ ስላሴ ዘመን ተመርተው ቤት የሰሩ ስለሆኑ ከተጠሪ ጋር ባላቸው ዝምድና በቤቱ እንድትኖር የፈቀዱ ስለመሆኑ ነው፡፡ አከራካሪው ንብረት የማይንቀሳቀስ ንብረት እንደመሆኑ መጠን በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት መብት ማረጋገጥ የሚቻለው ከክፍሉ መስተዳደር በሚቀርብ ማስረጃ ነው፡፡

አከራካሪው ቤትና ይዞታ የአመልካች ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ከሾኔ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በስማቸው የተመዘገበ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ ይህ የይዞታ ማረጋገጫ የተገኘው በተጭበረበረ መንገድ ነው ቢሉም ማስረጃው በተጭበረበረ መንገድ ስለመሰጠቱ አላረጋገጡም፡፡ የይዞታው ማረጋገጫ በሕግ የተመለከተውን ስርአት ሳይከተል የተሰጠ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡

ስለሆነም ከአመልካች የሰውና የሰነድ ማስረጃ መረዳት የሚቻለው አከራካሪው ቤትና ይዞታ የአመልካች መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አከራካሪው ቤት የግሌ ነው ቢሉም ይህን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አላቀረቡም፡፡ የሰው ምስክሮች ምቢሆኑ ተጠሪ አከራካሪውን ይዞታ የያዙት ተመርተው ነው ቢሉም በዚህ ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ እስካላወጡ ድረስ ተቀባይነት የለውም፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ተጠሪ በቤቱ መብራትና ውሀ ማስገባታቸው ብቻ የቤቱ ባለቤት አያደርጋቸውም፡፡ ፍ/ቤቱ በግራቀኙ ፈቃድ ግራቀኙ በሽማግሌዎች እንዲታረቁ ቀጠሮ ሰጥቶ ሽማግሌዎች ባቀረቡት ሪፖርት ተጠሪ አከራካሪው ይዞታ የአመልካች መሆኑን በሽማግሌዎች ፊት አምነው በቤቱ ረጅም አመት ስለኖሩ አመልካች ለተጠሪ 60000 ብር ሰጥተው ቤቱን እንዲለቁ ወይም በከተማው ውስጥ ሌላ ቤት እንዲሰሩላቸው በሚለው ሀሳብ ብቻ ባለመስማማታቸው እርቁ ሊፈርስ ችሏል፡፡ ከዚህ ሁሉ የክርክር ሂደትና ማስረጃ ማረጋገጥ የሚቻለው አከራካሪው ይዞታና ቤት የአመልካች መሆኑ፤ አመልካች በይዞታው ላይ ያላቸው የይዞታ ማረጋገጫም በሕጋዊ መንገድ የተሰጠ መሆኑን ነው፡፡ በማለት ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ሊለቁ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ሊለቁ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ጸንቷል፡፡

የአሁን አመልካች በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የጸናው ውሳኔ የንብረት ሕገ መንግስታዊ መብቴን የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አጣሪ ጉባኤውም ጉዳዩን አጣርቶ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሀሳብ በማዘጋጀት ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ ልኳል፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ የሕገ መነግሰት አጣሪ ጉባኤ አከራካሪውን ይዞታ እና ቤት በተመለከተ ለአሁን አመልካችከከተማ ማዘጋጃ ቤቱ የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በህገ ወጥ መንገድ ስለመስጠቱበፍርድ ቤቱ የተረጋገጠበት መንገድ የፍ/ህጉ አንቀፅ 1196 የተከተለ አይደለም፡፡

ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫውን ሰነድ የሰጠው የከተማ መስተዳደሩ በፅሁፍም ሆነበችሎት ተገኝቶ በህጋዊ መንገድ ስለመስጠቱ እያረጋገጠ ፍርድ ቤቶች ግን ይህን ወደ ጎንበመተው የተመዘገበ ሰነድ ውድቅ አድርገዋል። አንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚሰጥየይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ከመመሪያ ውጪ የተሰጠ መሆኑን መጀመሪያ ሰነዱን ከሰጠውአካል በአግባቡ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

ይህን ሊያረጋግጥ የሚችል የወረቀት ሰነድለጊዜው ባለመገኘቱ ብቻ ፍርድ ቤቶች በግምት ማስረጃው የተሰጠው መመሪያንባልተከተለ መንገድ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍትሐብሔር ህጉን አንቀፅ 1195 እና1196 አላግባብ እና ሕገ መንግስታዊ ባልሆነ መንገድ ከመተርጎም የመጣ ነው፡፡

ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ህጉ አንቀፅ 1196 በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠውን የንብረት መብትበተለይም የማይንቀሳቀስ የንብረት መብት አንፃር በጥብቅ መተርጎም ይገባቸዋል።በዚህም ለአመልካች የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መመሪያን በጣሰ መልኩ የተሰጠመሆኑን ሳያረጋግጡ መመሪያን የጣሰ ነው በማለት መወሰናቸው የፍ/ብ/ህጉን ጥብቅ የማስረጃ መርህ አላግባብ ከመተርጎም የመጣ ሲሆን ይህም የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ የማይንቀሳቀስ የንብረት መብት የጣሰ ነው፡፡

ከዚህ ቀደም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የውሳኔ ሃሳብ አቅርቦበት በፌዴሬሽን ምክር ቤት በመዝገብ ቁጥር 022/08 ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ/ም የሕገ መንግሥትትርጉም የተሰጠበት ውሳኔ በፍ/ህግ አንቀፅ 1195 አግባብ በአንድ ንብረት ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ያለው ሰው ይህ ማስረጃው ሊስተባበል የሚችለው በፍ/ህጉ አንቀፅ 1196 በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡፡

ይህ በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠው ባለሃብትነት ለምሳሌ በሰው ምስክሮች ሊስተባበል የማይችል ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶች ግን ህጉን ከሕገ መንግስቱ የንብረት መብት ድንጋጌ ጋር በሚቃረን መልኩ በመተርጎም የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ የንብረት መብትን የሚጥስ መሆኑ ተገልጾ ተወስኗል፡፡

በተመሳሳይ በዚህም ጉዳይ አመልካች በይዞታው እና በቤቱ ላይ በህጋዊ መንገድ የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዳላቸው ከወረቀት ሰነድ ይልቅ ብዙ ጠቃሚአላማ ባለው በካደስተር የተመዘገበ መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ የወረቀት ሰነዱ ለጊዜውባለመገኘቱ ብቻ የይዞታ ማረጋገጫው በፍ/ህግ አንቀፅ 1196 መሰረት በህገ ወጥ መንገድየተሰጠ መሆኑን ያመለክታል የተባለበት አግባብ ኢ-ሕገ መንግስታዊ ነው፡፡

ፍርድ ቤቶች የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማስረጃን ወይም ሰነድን በፍ/ህጉ አንቀፅ1195 መሰረት ሲተረጉሙ በህጉ አንቀፅ 1196 ስር ከተዘረዘረው መስፈርት ውጪ በሌላበማናቸውም መስፈርት የሰነድ ማስረጃን ውድቅ ማድረግ የለባቸውም፡፡ ስለሆነም ከላይበተጠቀሱት ምክንያቶች የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ የንብረት መብት የሚጥስ ስለሆነ ውሳኔው ኢ-ሕገ መንግስታዊ ነው፡፡

ስለሆነም ጉባኤው፡-

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ሃዲያ ዞን በሾኔ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትተጀምሮ የፌ/ጠ/ፍ/ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 147703 በቀን23/02/2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የኢ.ፌ..ድ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀጽ አንድን የማይጥስ ስለሆነ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት፡-
አከራካሪው ቤት እና ይዞታ በአመልካች ስም በሃዲያ ዞን በሾኔ ከተማ የመሬትልማትና ማኔጅመንት ዋና የስራ ሂደት የከተማ ቦታ ኪራይ ይዞታ ቋሚ የይዞታማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊሰረዝ ወይም ሊመክን አይገባም ተብሎ የመጨረሻ
ውሳኔ እንዲሰጥበት ለኢ..ፌ..ዲ..ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳሜኔ ሃሳብ አቅርቧል።
በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የጸናው ማለትም ተጠሪ አከራካሪውን ቤትና ይዞታ ለአመልካች ሊለቁ አይገባም በማለት የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን የንብረት ሕገ መንግስታዊ መብት የሚቃረን መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (1) እና (2) ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. በደ/ቡ/ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል መንግስት ሀድያ ዞን በሾኔ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ተሰጥቶ ለሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ተብሎበት የተሻረውና እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የጸናው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን በምክር ቤቱ መወሰኑን አውቀው በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

32 (2727)

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ አመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የፋ/ቁ.75/11

አመልካች፡- ወ/ሮ አሰለፈች ከበደ

አድራሻ፡- በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማ ለኩ ከታ ቀበሌ የቤ.ቁ 1356

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ ጅማ

አድራሻ፡- በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማ ለኩ ከታ ቀበሌ የቤ.ቁ አዲስ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 3 ቀን 2010 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ፣ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 145772 በቀን 13/03/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩም የንብረት እና የይዞታ ክርክርን የተመለከተ ነው፡፡

የጉዳዩ ፍሬ ሀሳብ አመልካች በቡራዩ ከተማ ለኩ ከታ ቀበሌ ውስጥ የቤት ቁጥሩ 1356 የሆነና በስማቸው ተመዝግቦ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ግብር የሚከፍሉበት ቤት አላቸው፡፡ አመልካች ይህን ቤት መያዝ የቻሉት በ1994 ዓ.ም ተጠሪ በተጠቀሰው አድራሻ ካለው 800 ካ/ሜ ይዞታ ላይ 500 ካ/ሜ ቦታ በመቁረጥ በብር 85,000.00 በይዞታው ላይ ከነበረው አንድ ሰርቪስ ቤት ጋር ለአመልካች ስለሸጠላቸው ነው፡፡ የሽያጭ ውሉ በውል ክፍል አልተመዘገበም፡፡ ተጠሪ ይዞታውን በሸጠበት ወቅት ይዞታው የሚገኝበት ቀበሌ በቡራዩ ከተማ ክልል ውስጥ ነበረ፡፡

ሁኔታው ይህ ሆኖ እያለ የአሁን ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በፍንፍኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ሊዩዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ለገሰ ጅማ፣ 2ኛ ጸሃይ ገማ፣ 3ኛ ከበደ ንጋቱ እና 4ኛ ሰብለ ነጋሽ በሆኑት ላይ ክስ ይመሰርታል፡፡ የክሱ ፍሬ ጉዳይም 1ኛ ተከሳሽ /የተጠሪ/ የኔ ወንድም ሆኖ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ባለቤቱ ስትሆን በቡራዩ ከተማ ለኩ ከታ ቀበሌ ውስጥ በሚገኝ አዋሳኞቹ በተጠቀሰው 800 ካ/ሜትር ይዞታ ላይ በጊዜያዊነት እንዲኖሩ ብሰጣቸውም በሌላቸው መብት ይዞታውን በላዩ ላይ

ካሉ ባህር ዛፎች እና ቤቶች ጋር ለ3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች አሳልፈው የሸጡብኝ በመሆኑ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን በይዞታው ላይ ያሉኝም ንብረቶች ግምት እንዲከፍለኝ እና ይዞታውን እንዲያስረክቡኝ ሲሉ ክሳቸውን አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በተጠሪ ቅሬታ አቅራቢነት ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ በይርጋ መቋረጥ የለበትም በማለት ወስኖ የስር ፍ/ቤት አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት በመመሪያ መልሶታል፡፡ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤትም ጉዳዩን እያከራከረ እያለ የአሁን አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጥያቄ አቅርበው ፍ/ቤቱም ፈቅዶላቸዋል፡፡

አመልካች በጣልቃ ገብ ክርክራቸው 500 ካ/ሜ ላይ ያለውን ንብረት እና ይዞታ በ1994 ዓ.ም ከተጠሪ በብር 85,000.00 መግዛታቸውን እና በ2002 ዓ.ም የቀድሞውን የሰርቪስ ቤት በማፍረስ በምትኩ 14 ክፍል ቤት እና በዙሪያው ያለውን አጥር ጭምር በ3,000,000.00 /ሶስት ሚሊዮን ብር/ በማውጣት የሰሩት መሆኑንና በስማቸው የቤት ቁጥር 1356 የተሰጠ መሆኑን በመግለፅ በዚህ ጊዜ ውስጥ ተጠሪ አጎራባቻቸው ሆኖ ሳለ ምንም አይነት ተቃውሞ ያላቀረበ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የአመልካች ክርክር ተቀብሎ ንብረቱ ከክርክሩ ውስጥ እንዲወጣ በማለት ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን፣ የክልሉ ሰበርም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ከተጠሪ ይዞታውን እና ንብረቱን የገዙበት ውል አልተመዘገበም፣ ተከራካሪዎቹ ውሉን በሚያደርጉበት ወቅት ይዞታው የነበረበት ቦታ የከተማ ክልል ውስጥ አልነበረም በሚሉ ምክንያቶች የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር አመልካች ንብረቱንና ይዞታውን ለቀው እንዲወጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካች ይህ የፍ/ቤት ውሳኔ የሕገ መንግስት ጥበቃ የተደረገበትን የንብረት መብቴን ጥሷል በማለት የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ጉባኤውን የጠየቁ ሲሆን ጉባኤው ጉዳዩን መርምሮ የፍ/ቤት ውሳኔው የአመልካችን የንብረት ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ የሕገ

መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለምክር ቤቱ በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና የምክር ቤቱ ባለሙያዎች የሰጡትን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በዋናነት ያነሱት ቅሬታም ተጠሪ በአከራካሪው 500 ካ/ሜ ይዞታ ላይ ያለውን ቤት ህዳር 7 ቀን 1991 ዓ.ም እና ህዳር 7 ቀን 1994 ዓ.ም ሸጦልኝ እኔም የገዛሁትን ነባር ቤት አፍርሼ ከሶስት ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማውጣት 14 ክፍል ቤቶች በድንጋይ እና በብሎኬት እንዲሁም በድንጋይ አጥር ያስምንም ተቃውሞ የአሁን ተጠሪም ጎረቤቱ ሆኖ እያወቀና እያየ ሰርቼ፣ የሚመለከተው የመንግስት አካልም የቤት ቁጥር ሰጥቶኝ፣ በስሜ የቤት ግብር እና የይዞታ ኪራይ እየከፈልኩ፣ ውሉንም የሚመለከተው የመንግስት አካል እውቅና ሰጥቶት ተመዝግቦ ያለ መሆኑ በሰነድ ተረጋግጦ እያለ፣ እንደዚሁም ይህንኑ የራሱ አጥር ግቢና ወሰን ያለውን ቤት ከ18 ዓመት በላይ በእኔ እጅ የሚገኝ ስለመሆኑ ተጠሪም ሳይክድ፣ ቤቱን ከመግዛቴም በፊት ይዞታው በከተማ የሚገኝ ሆኖ እያለ፣ ይህንንም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በማስረጃ ሳያረጋግጥ እንደዚሁም ተጠሪ ራሱ ህዳር 7 ቀን 1991 ያደረግነውን ውል ከመከላከያ መልስ ጋር አቅርቦ እያለ ለተጠሪ ሀብትና ንብረቴን እንድለቅ የተሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ይጥሳል የሚል ነው፡፡

ጉባዔው በጽ/ቤቱ በኩል በጻፈው ደብዳቤ አከራካሪው ቤት በቡራዩ ከተማ አስተዳደር ውስጥ መቼ እንደተካተተ እንዲጣራ ባደረገው ጥረት የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ጽ/ቤት ከከተማ አስተዳደሩ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት በቀን 12/02/2011 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ከተማዋ ከ1983 በፊት የገጠር ቀበሌ እንደነበረች እና ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በቡራዩ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ስር መተዳደር የጀመረች መሆኑን አረጋግጠዋል።

አመልካች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍ/ቤቱ ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አንፃር ተመርምሯል። እንደተመረመረው በመጨረሻ ፀንቶ ላለው ውሳኔ መሰረት የሆነው ነጥብ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የማይንቀሳቀስ ንብረትን የተመለከተ ውል አልተመዘገበም እንደዚህም ውሉ የተደረገው በከተማ ይዞታ ላይ አይደለም የሚሉ ናቸው፡

በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ከመነሻ ጀምረን ስንመለከተው አመልካች ንብረቱ ያለበት አካባቢ በ1988 ዓ.ም ከከተማ ቀበሌ ወደ ማዘጋጃ ቤት ካደገ በኋላ አመልካች ህዳር 7 ቀን 1991 እና 1994 ዓ.ም በተደረገው ውል ከተጠሪ ላይ 500 ካ/ሜትር አራት በአራት የተሰራ ሰርቪስ ቤት እና በመሬቱ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ታዳጊ ዛፎችም ጭምር ከገዙ በኋላ ተጠሪ እያየ ሳይቃወማቸው ከተጠሪ የገዙትን 500 ካ/ሜ መሬት ላይ የነበረውን ቤት አሻሽለው 14 ክፍል የያዘውን 5 ቤቶች ሰርቶ ቤቱም በመንግስት እውቅና አግኝቶ የቤት ቁጥር 1356 በአመልካች ስም ተሰጥቶት ተመዝግቦ ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም አመልካች በራሳቸው ስም የባለቤትነት ሰነድ አውጥተውበት ግብር እየገበሩ የቆዩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተደረገው ውል አልተመዘገበም በማለት ፍ/ቤቱ ቢወስንም ተጠሪ ግን በክርክሩ ወቅት አልተመዘገበም ከማለት ውጭ በግልፅ ውሉን ያልካደ በመሆኑ፣ ተጠሪ ውሉን በግልፅ አለመካዱ ደግሞ ውሉ ባይመዘገብም ተዋዋዮቹ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የፀና ውል በመሆኑ አመልካች አከራካሪውን ንብረት በሕጋዊ መንገድ ያፈሩት መሆኑን ያመላክታል፡፡

አመልካች ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ንብረቱን ከተጠሪ ከገዙ በኋላ የገዙትን ቤትም አሻሽለው ሌላ ቤት ሰርተው ለረጅም አመት ግብር እየገበሩበት ተጠሪ ምንም ሳይቃወማቸው ንብረቱን ይዘው መቆየታቸው አመልካች የንብረቱ ሕጋዊ ባለቤት ሆነው በንብረቱ ላይ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(7) መሰረት ‹‹ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው›› በማለት የደነገገውን ሕገ መንግስታዊ የንብረት ባለቤትነት መብት የተጎናፀፉ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡ አመልካች የንብረቱ ባለቤት መሆናቸው ከተረጋገጠ ደግሞ ይህ ሕገ መንግስታዊ የንብረት ባለቤትነት መብት እንደሚከበርላቸው በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(1) ስር ‹‹ማንኛውም የኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆን ይከበርለታል›› በማለት የተደነገገውን ሕገ መንግስታዊ ዋስትና አላቸው፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 13(1) ደግሞ የመንግስት አካላት የሕግ አውጭው፣ የሕግ አስፈፃሚው እና የሕግ ተርጓሚው ማለትም ፍ/ቤቶች በሕገ መንግስቱ ላይ የተደነገጉት መብቶችን ማክበር፣ ማስከበር እና ስራ ላይ መዋል ግዴታ እንዳለባቸው አስቀምጧል፡፡ ይህ ማለት ሶስቱም የመንግስት አካላት በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት በሚሰጡት ውሳኔ በሕገ መንግስቱ ላይ ከተቀመጡት መብቶች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ውሳኔ ማስተላለፍ እንደሌለባቸው ግዴታ የጣለባቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ነገር ግን በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 13(1) መሰረት የመንግስት

አካላት በሕግ መንግስቱ ምእራፍ 3 የተቀመጠውን ድንጋጌዎች የሚጥስ ውሳኔ የሚያስተላልፉ ከሆነ ደግሞ የተወሰነው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9(1) መሰረት ተፈፃሚነት እንደማይኖረው ተደንግጓል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች አከራካሪውን ንብረት የከተማ ክልል ውስጥ በነበረበት ወቅት ከተጠሪ ገዝተው፣ በመንግስት አስተዳደር አካል ፍቃድ እና እውቅና መሰረት ተጠሪ ጎረቤት ሆነው እየኖሩና እያዩ ሳይቃወማቸው አስፋፍተው ብዙ ገንዘብ በማውጣት 14 ተጨማሪ ክፍል በድንጋይና በብሎኬት ሲሰሩና አጥሩንም በግንብ በሰሩት ቤት የቤት ቁጥር ተሰጥቷቸው ግብር እየከፈሉ ለረዥም ጊዜ ይዘው የሚገኙበት እና በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(1) እና (7) ስር የተቀመጠውን ሕገ መንግስታዊ የንብረት መብት የተጎናፀፈበትን ቋሚ ንብረት ላይ ፍ/ቤቱ አመልካች መብት የላቸውም በማለት የጣልቃ ገብ አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረግ መወሰናቸው፣ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ የንብረት ባለቤትነት መብቶች በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(1) እና (7) ስር የተቀመጠውን የሚጥስ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ተብሎ በትዕዛዝ የተዘጋው የፍ/ቤት ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር ስለሚቃረን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትእዛዝ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን በምክር ቤቱ መወሰኑን አውቀው ተገቢውን እንዲፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የፌዴራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ፡፡

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ አምስተኛ ዓመት አንደኛ መደበኛ ስብሰባ

መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ.ቁ. 76/11

የጉዳዩ አቅራቢ፦ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ተጠሪ ፦ የለም

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

### ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 150818 ሰኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም በአመልካች አቶ አለማየሁ ተሰማ እና በተጠሪ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ መሀከል ሲካሄድ ከነበረው የኮንደሚኒየም ቤት ዕጣ ጋር የተያያዘ ክርክርን ሲመለከት ቆይቶ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለተጠቃሚዎችና ለልማት ተነሺዎች ለማስተላለፍ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀፅ 44 ሕገ መንግስታዊነቱ እንዲመረመር በመላኩ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ በብይኑ እንዳሰፈረው የጉዳዩ አጀማመር ችሎቱ በያዘው መዝገብ ላይ አመልካች የነበሩት አቶ አለማየሁ ተሰማ ተጠሪ በሆነው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት እናታቸው ሚች በለጡ መርሻ በአዲስ አበባ ከተማ የጋራ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ዝርዝር ተመዝግበው አስፈላጊውን ክፍያ እየቆጠቡ ቆይተው የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣው ከመውጣቱ አስቀድሞ ጥቅምት 11 ቀን 2007 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ቢሆንም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች አስተዳደር ኤጀንሲ በ2008 ዓ.ም ለነዋሪዎቹ የ11ኛ ዙር የ20/80 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ባለቤት ለማድረግ ባወጣው ዕጣ ሚች ወ/ሮ በለጡ መርሻ በምዝገባ መለያ ቁጥር BO 13Y0005202005 ቦሌ አራብሳ በተባለው የግንባታ ሳይት ውስጥ ብሎክ ቁጥር 041 የቤት ቁጥር 041/14 የሆነ ባለ ሦስት መኝታ የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ ወጥቶላቸዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች በኢትዮጵያ የውርስ ህግ መሠረት

ከሟች እናታቸው የሚተላለፍላቸውን መብት ለመውረስ የወራሽነት ማስረጃ አውጥተው ለከተማ አስተዳደሩ ጥያቄ ሲያቀርቡ ለህግ የሚቃረኑ መመሪያዎችን በመጥቀስ ሊፈፅሙላቸው አለመቻላቸውን ገልፀው የጋራ መኖሪያ ቤት ወራሽነት መብት ተከብሮ ለአመልካች ይተላለፍላቸው ዘንድ በመጠየቅ ያቀረቡት ክስ መሆኑን ችሎቱ ጠቅሷል።

ተጠሪም በሰጠው መልስ በአዋጅ ቁ. 35/2004 አንቀፅ 25 መሰረት ግንባታቸው የተጠናቀቁ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለተጠቃሚዎች የማስተላለፍ ሥልጣን ያለው ሲሆን ቤቶችን ለተጠቃሚዎች በማስተላለፍ ሂደት ሕግን መሠረት አድርጎ የሚሠራ ነው። በመሆኑም ቤት ፈላጊዎችን የመመዝገብ፣ የማጣራትና የቤት ርክክብ ሥርዓት እንዲሁም የማስተላለፍ ሂደቱ የሚመራው ለዚህ ተብሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 19/1997 እና መመሪያ ቁጥር 1/2008 መሠረት ነው። ስለሆነም መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀፅ 44 የቤት ዕድለኛ በሞተ ጊዜ ዕድሜያቸው 18 ዓመት የሞላቸው የሟች ልጆች በሟች ስም የወጣውን ዕጣ አይወርሱም በሚል ይደነግጋል። ከዚህም አንጻር የአመልካች አቤቱታ ህግን መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ክርክር አቅርበዋል ሲል ችሎቱ በብይኑ አስፍሯል።

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለትም የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጠቃሹን መመሪያ አንቀፅ 44(ሠ) በመጥቀስ አመልካች የሟች እናታቸውን የጋራ የመኖሪያ ቤት ዕጣ ሊወርሱ አይችሉም ሲል ወስኖ በውሳኔው ላይ አመልካች ይግባኝ ቢያቀርቡም በይግባኝ ሰሚው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀባይነት አለማግኘታቸውን እና በዚሁ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት መሆኑን ችሎቱ በብይኑ ጠቅሷል።

ሠበር ሰሚ ችሎቱም የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 40(1) እና 40(2) በመጥቀስ ከሕገ መንግስቱ የንብረት ትርጓሜና የንብረት ማፍራት መብት አንፃር ጉዳዩን በመመልከት የአመልካች እናት ሟች በለጡ መርሻ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የጋራ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ተርታ ተመዝግበው ገንዘባቸውን ሲቆጥቡ ቆይተው የሞቱ ቢሆንም ዕጣው ከሞት በኋላ የደረሳቸው መሆኑን በመጥቀስ ዕጣው እንደሟች ንብረት ተቆጥሮ በውርስ ሊተላለፍ እንደሚገባ አመልካች የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ከላይ የተጠቀሰውን መመሪያ መሠረት በማድረግ የኮንዶሚኒየም ቤት ዕጣ ከ18 ዓመት በላይ ለሆናቸው የሟች ልጆች እንደማይተላለፍ በመጥቀስ ተከራክረዋል። አመልካችም 18 ዓመት የሞላቸው መሆኑን ሳይክዱ የዚህን መመሪያ ሕገ መንግስታዊነት ጥያቄ ውስጥ በማስገባት መከራከራቸውን ችሎቱ ጠቅሷል።

በመጨረሻም ችሎቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ያወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀፅ 44 የህገ መንግስቱን አንቀፅ 40(1) የሚቃረን ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ላይ ተጣርቶ ትርጉም እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው እንዲላክ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመመሪያው ላይ የተጠቀሰው ይህ አንቀፅ ከሕገ መንግስቱ ጋር ይቃረናል ወይስ አይቃረንም በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተመርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ ተጠቃሹ መመሪያ ያካተተው ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የሟች ልጆችን የኮንደሚኒየም ዕጣ እንዳይተላለፍላቸው ያደረገውን ድንጋጌ ሕገ መንግስታዊነቱን ለመፈተሽ 1ኛ የድንጋጌው ዝርዝር ይዘት ምንድን ነው? 2ኛ ኮንዶሚንየም ቤት ላይ የሚፈጠር የባለንብረትነት/የባለቤትነት መብት በአፈጣጠሩ እና ከተፈጠረም በኋላ እንደማንኛውም ሌላ ንብረት ከባለቤቱ በቀር መንግስት ሊያሳካው የሚሻው ፍላጎት የሌለበት መሆን አለመሆኑ፣ ፍላጎት ካለም ከየት እንደሚመነጭና ከግለሰቦች መብት ጋር እንዴት ተጣጥሞ ሊከበር እንደሚችል በመጨረሻም ሟች የሚጠበቅባቸውን ቁጠባ ሲቆጥቡ ቆይተው በመጨረሻ ዕጣው ሳይወጣ ህይወታቸው ቢያልፍም ከህልፈታቸው በኋላ ዕጣው በወጣው የኮንዶሚንየም ቤት ላይ ለወራሾች ሊተላለፍ የሚችል መብት የላቸውም ወይስ አላቸው? የሚሉትን በመፈተሽ ለተያዘው ጉዳይ መቋጫ መስጠት ይገባል፡፡

ለእነዚህ ጉዳዮች መልስ ለመስጠት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበበትን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለተጠቃሚዎች እና ለልማት ተነሺዎች ለማስተላለፍ የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀፅ 44 መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፊደል ተራ 'ሀ' እስከ ፊደል ተራ 'ሰ' የተዘረዘሩ ሰባት ንዑስ አንቀጾች ያሉት ሲሆን እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡-

አንቀጽ 44 <u>ዕጣ የማይወረስ ስለመሆኑ</u>

ሀ) ማንኛውም ሰው በዕጣ ተጠቃሚ መሆን የሚችለው በህይወት እስካለ ድረስ ብቻ ነው፤

ለ) የቤት ዕድለኛው ምዝገባ በባል ወይም በሚስት ስም ሲሆንና ባለዕድሉ በሞት ቢለይ ወይም ቢጠፋ በህይወት ያለው ባል ወይም ሚስት በምዝገባ ቅፁ አማካኝነት ወይም ከፍርድ ቤት በሚያቀርበው ማስረጃ መሰረት ተጠቃሚ የመሆን መብት አለው፤

ሐ) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ “ሀ” ቢኖርም በምዝገባ ወቅት ዕድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው የሟች ልጆች ወራሽነታቸውን በመደበኛ ፍ/ቤት አረጋግጠው ሲመጡ ብቻ የዕጣው ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፤

መ) በፍ/ቤት የወራሽነት መብት የተረጋገጠላቸው ግለሰቦች ተጠቃሚ የሚሆኑት በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ ድንጋጌዎች የሚያሟሉ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው፤

ሠ) በዚህ አንቀጽ በፊደል “ሐ” መሰረት ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ የሟች ልጅ(ልጆች) የዕጣውን ውርስ ተጠቃሚ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ይኖሩበት የነበረውን የቀበሌ ቤት በምዝገባው ወቅት ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የሟች ልጆች ዕጣውን መውረስ ስለማይችሉ በመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2007 መሰረት ቤቱን እንደያዙ ይቆያሉ፤

ረ) ባልና ሚስት በጋራ ምዝገባ አካሂደው ቤቱ ሳይደርስ በፍቺ ቢለያዩ በፍ/ቤት ውሳኔ መሰረት ቁጠባው እንዲቀጥል ተደርጎ ቤቱ በዕጣ ሲደርስ በውሳኔው መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፣ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ቅድመ ሁኔታውን አሟልተው ቤቱን ካልተረከቡ ዕጣው ይሰረዛል፤

ሰ) በፍርድ ቤት ክርክር ምክንያት መደበኛው የቤት ሽያጭ የውል ጊዜው ካለፈ በኋላ ዘግይተው ለሚመጡ ዕድለኞች ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ መሆኑን በቤት ማስተላለፍ ውል ጊዜ ገደብ ውስጥ ለኤጀንሲው አስቀድሞ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ጉዳዩ በፍ/ቤት ውሳኔ እንዳገኘ በ10 ተከታታይ የሥራ ቀን ውስጥ በአካል ቀርበው ሊስተናገዱ ይችላል። ከዚህ ውሳኔ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተቀባይነት የላቸውም።

ከዚህ በላይ ተዘርዝረው ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው በፊደል ተራ ሀ፣ ሐ እና ሠ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ግልፅ ንባብ እንደሚያስረዳው የኮንዶሚንየም ዕጣ ከመውጣቱ በፊት የሞተ ሰው በምዝገባ ወቅት የሟች የ18 ዓመት እና ከዛ በላይ የሆኑ ልጆች የዕጣው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መደረጋቸውን መረዳት የሚቻል ነው።

ጉባኤው የከተማው አስተዳደር ቤቶች ኤጀንሲን አንድ ሃላፊና አንድ ባለሙያ አስቀርቦ በመስማት ተጨማሪ ማብራሪያ ተቀብሏል። በዚህም የጋራ መኖሪያ ቤቶች በመንግስት የሚሰሩና ቤት ለሌላቸው የከተማዋ ነዋሪዎች የቀረበ እድል ሲሆን ነዋሪዎቹ በምዝገባው ወቅት 18 አመትና ከዚያ በላይ መሆን እንዳለባቸው ገልፀዋል። እነዚህ ሰዎች እጣን መውረስ

እንደማይችሉ በመመሪያ መደንገግ ያስፈለገው በቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ወቅት መመዝገብና የእድሉ ተጠቃሚ መሆን ይችሉ ነበር ብለዋል፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው የቤት ባለቤት የሚሆነው እጣ ስለወጣለት ብቻ ሳይሆን ከኤጀንሲው ጋር የሽያጭ ውል ሲገባ ስለሆነ እጣ ሃብት/ንብረት ሊሆን አይችልም በማለት ገለፃ አድርገዋል፡፡

መንግስት ለኮንዶሚንየም ቤቶች ወጪ በመመደብ ግንባታ ሲያካሂድ የገቢ አቅማቸው አነስተኛ የሆነ ዜጎችን የቤት ባለቤት ማድረግና ፍትህዊ የሀብት ክፍፍልን ማሳካት በዋናነት ታሣቢ ያደረገ በመሆኑ በዚህ ሀብት አፈጣጠር ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦና ፍላጎት ያለው መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ቤቶች ላይ ዜጎች የባለቤትነት መብት በሚፈጥሩበት አግባብ ላይ ልዩ ልዩ ህጎችን ማውጣቱ የሚጠበቅ በመሆኑ ለትርጉም የቀረበው መመሪያም የዚሁ አካል ነው፡፡ ዜጎች መንግስት በገነባቸው ኮንዶሚንየም ቤቶች ላይ የባለቤትነት መብትን ለመፍጠር የሚችሉት ቤቶቹን በዕጣ ለማግኘት መንግስት በሚያወጣቸው አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት የሚጠበቅባቸውን ምዝገባ፣ አስፈላጊውን ቁጠባ እና መሰል ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው በመገኘት ነው፡፡

በሌላ በኩል ዜጎችም የኮንዶሚንየም ቤት ተጠቃሚ ለመሆን ቁጠባ የሚያካሂዱ በመሆኑ መጠነኛ በሆነ መልኩ በካፒታላቸው ሀብቱን ለራሳቸው ለመፍጠር ጥረት የሚያደርጉ መሆኑ ከግንዛቤ ሊወሰድ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም ዜጎች በኮንዶሚንየም ቤት ላይ የሚፈጥሩት ባለሀብትነት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40(2) ስር ከተዘረዘሩት የግል ንብረት መፍጠሪያ መንገዶች ከሆኑት በጉልበት፣ በመፍጠር ችሎታ ወይም በካፒታል የግል ንብረት መፍጠሪያ መንገዶች ውስጥ ከሚቆጥቡት መጠነኛ ካፒታል በተጨማሪ የዚሁ አንቀጽ ተደማሪ የግል ንብረት መፍጠሪያ መንገድ በሆነው የሕገ መንግስቱ ክፍል በመታገዝ ነው፡፡

በሕገ መንግስቱ በምዕራፍ አስር ከሰፈሩት የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች ውስጥ በአንቀጽ 89 ስለ ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ሲደነግግ በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ (1) *"መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሀገሪቱ የተጠራቀመ እውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት"* እና በንዑስ አንቀጽ (2) *"መንግስት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት"* ተብሎ መደንገጉ እንደዚሁም ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 90 ስለ ማኀበራዊ ነክ ዓላማዎች ሲደነግግ በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት *"የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና*

አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል" በሚል መደንገጉን ስንመለከት መንግስት ያለበትን ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን የማረጋገጥ እና ለዜጎች አቅም በፈቀደ መልኩ የመኖሪያ ቤት የማቅረብ ግዴታውን ሲወጣ ለዜጎች አንዱ የግል ንብረት መፍጠሪያ መንገድ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መነሻነት ዜጎች የሚፈጥሩት የግል ንብረት ባለቤትነት፣ መብቱን የፈጠሩትን ድንጋጌዎች መሰረታዊ ዓላማ ያከበረ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ የሚፈጠር የንብረት ባለቤትነት የተጠቃሾቹን ድንጋጌዎች መሰረታዊ ዓላማ እስካሳካ ድረስ ባለቤትነቱን ለፈጠረው ዜጋ ሙሉ የንብረት መብት ሊፈጥር የሚገባ መሆኑ ትኩረት የሚሻ ነው፡፡ ሙሉ የንብረት መብት ደግሞ ንብረት ማውረስን የሚጨምር መሆኑ አያከራክርም፡፡

በያዝነው ጉዳይ የንብረት ባለቤትነትን መብት ለመወሰን በመመሪያው የኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤትነት መብት የሚገኝበትን ወይም የሚጀምርበትን ሁኔታ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶችን የማስተላለፍ ሃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 5(3) መሰረት በቤት ፈላጊነት የተመዘገበ ሰው ኤጀንሲው ባስቀመጣቸው መመዘኛ መሰረት አስፈላጊውን የማጣራትና የምርመራ ስራ ከተሰራ በኋላ በቤት ፈላጊነት በፅ/ቤቱ እንደሚመዘገብና ስሙ በማስታወቂያ ሰሌዳ ይፋ እንደሚደረግ፤ በዚህም የመኖሪያ ቤት የመግዛት መብት እንደሚያገኝ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይህም የሚያሳየው የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ መውጣት የሚያስፈልገው በህግ አግባብ ተመዝግበው አነስተኛውን የገንዘብ መጠን ከቆጠቡ ነዋሪዎች መካከል በቅድሚያ ማን ያግኝ፣ በእጣው ከተካተቱትስ የትኛውን ቤት ያግኝ (የት አካባቢ የተሰራውን ቤት፣ ብሎክ፣ ፎቅ፣... ወዘተ) እና መሰል ጉዳዮች ለመወሰን የሚረዳ እንጂ በህጉ አግባብ ሲቆጥብ የነበረ ነዋሪ ቤት ላያገኝ/ሊከለከል የሚችልበት መንገድ መኖሩን ለማሳየት ያለመ ሊሆን እንደማይችል መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ ቤት ፈላጊዎች ተገቢውን ቁጠባ መቆጠብ እስከቀጠሉ ድረስ እጣው እንደሚወጣላቸውና ቤቱን እንደሚያገኙ እርግጥ ነው፡፡

ሟችም በመጀመሪያ በቤት ፈላጊነት በህጉ አግባብ ተመዝግበዋል፣ ኤጀንሲውም ባስቀመጣቸው መመዘኛዎች መሰረት አስፈላጊውን ማጣራት አድርጎና መዝግቦ የቤት ፈላጊ መታወቂያ ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህም ሟች በህይወት ቢኖሩ ኖሮ ከእጣ ሊወጡ እንደማይችሉ እንዲያውም ሟች ቀድሞውኑ የጋራ መኖሪያ ቤት የመግዛት መብት እንዳገኙ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በኋላም ሟች  በህጉ የሚጠበቅባቸውን ክፍያ ሲፈፅሙ ቆይተው እጣ ደርሷቸዋል፡፡ ከእጣው መውጣት በኋላ የሚቀጥለው ግዴታ የሚጠበቅባቸውን ቅድመ ክፍያ በመክፈል ከኤጀንሲው

ጋር የቤት ሽያጭ ውል መግባትና ቤቱን መግዛት ነበር፡፡ ስለሆነም ቤቱን የመግዛት ፍላጎትና አቅም እስካለ ድረስ ሟች የቤት ባለቤት ሳይሆኑ የሚችሉበት አሰራር አለ ለማለት አያስችልም፡፡ በተጨማሪም ምንም እንኳን መንግስት በራሱ ተነሳሽነት በጀት በመያዝና ገንዘብ ወጪ በማድረግ የጀመረው የቤት ልማት ፕሮግራም ቢሆንም ሟች ለቤት ብለው የሚያደርጉት ቁጠባ ሙሉ የቤት ባለቤት ለመሆን(በውርስ የማስተላለፍ መብትን ጨምሮ) በማሰብ ኢንቨስት እያደረጉት ያለው ገንዘብ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህም የተነሳ ሟች የሚጠበቅባቸውን ሁሉ አሟልተው እስከተገኙ ድረስ ከላይ በተጠቀሱት አንቀጽ 89(1)(2) እና አንቀጽ 90(1) የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መሰረት የተፈጠረላቸው የንብረት መብት የድንጋጌዎቹን መሰረታዊ ዓላማ እስካሳካ ድረስ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ የተከበረ ሙሉ የንብረት መብት ተከብሮ የሟች ወራሾችም ተጠቃሚ ሲሆኑ የሚገባ ነው፡፡ ወራሾች ሟች ያላቸውን የጋራ መኖሪያ ቤት የመግዛት መብት የተሟላ ለማድረግ ቀሪውን ግዴታ ማለትም ከእጣው በኋላ የሚጠበቅባቸውን የቅድመ ክፍያ እስከሬፀሙ ድረስ የመብቱ ሙሉ ተጠቃሚ ከመሆንና ቤቱን ከመረከብ የሚከለክላቸው መሆን የለበትም፡፡ በተለይም ሟች እጣው ሳይደርሳቸው በመሞትና እጣው ከደረሰው በኋላ በመሞት መካከል የሚኖረው ልዩነትና የተለየ ውጤት በሌለበት ሁኔታ ከ18 አመት በታች እና በላይ የሚል ልዩነት መፍጠሩ ምክንያታዊ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

በመጨረሻም ከላይ ለማየት እንደተቻለው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ አላማ መንግስት ቤት የሌላቸውን የከተማዋ ነዋሪዎች ቤት እንዲኖራቸው ለማድረግ ያቀደ ቢሆንም መመሪያው በኮንዶሚኒየም ቤት ምዝገባ ወቅት ያልተመዘገቡ የቤት እጣ መውረስ አይችሉም በሚል የያዘው አቋም አግባብነት የሌለው ነው፤ በወቅቱ በቤት ፈላጊነት ባይመዘገቡም ቤት የሌላቸው ግለሰቦች በውርስ መልክ ሊያገኙ ከሚችሉት የቤት ባለቤትነት መብት መነፈጋቸው በህገ መንግስቱ የተከበረላቸውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ በተጨማሪም መመሪያው ለሟች አካለመጠን ላልደረሱ ልጆች ክልከላ አለማድረጉ የሚደገፍ ቢሆንም በእድሜ ልዩነት በመፍጠር ሟች ከልጆቻቸው መሀከል አካለ መጠን ያልደረሱ ባይኖሩም አካለ መጠን የደረሰ ወራሽ የቤት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚፈቅድ አለመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40(1) እና (2) የተደነገገውን የዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ በመሆኑም በእነዚህ የሟች ወራሾች መካከል ልዩነት መፍጠር በህገ መንግስቱ የተሰጣቸውን በህግ እኩል ጥበቃ የማግኘት መብት የሚሸራርፍ ነው፡፡

ስለዚህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንደሚኒየም ቤቶች ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 44(ሐ) እና (ሠ) የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልጋቸዋል በማለት ጉባኤው በአብላጫ ድምፅ በአንድ የልዩነት ሀሳብ ጉዳዩ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት እንዲተላለፍ የውሳኔ ሀሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት ወራሾች ሟች ያላቸውን የጋራ መኖሪያ ቤት የመግዛት መብት የተሟላ ለማድረግ ቀሪውን ግዴታ ማለትም ከእጣው በኋላ የሚጠበቅባቸውን የቅድመ ክፍያ እስከፈፀሙ ድረስ የመብቱ ሙሉ ተጠቃሚ ከመሆንና ቤቱን ከመረከብ የሚከለክላቸው መሆን የለበትም፡፡ በተለይም ሟች እጣው ሳይደርሳቸው በመሞትና እጣው ከደረሰው በኋላ በመሞት መካከል የሚኖረው ልዩነትና የተለየ ውጤት በሌለበት ሁኔታ ከ18 አመት በታች እና በላይ የሚል ልዩነት መፍጠሩ ምክንያታዊ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ከላይ ለማየት እንደተቻለው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ አላማ መንግስት ቤት የሌላቸውን የከተማዋ ነዋሪዎች ቤት እንዲኖራቸው ለማድረግ ያቀደ ቢሆንም መመሪያው በኮንዶሚኒየም ቤት ምዝገባ ወቅት ያልተመዘገቡ የቤት እጣ መውረስ አይችሉም በሚል የያዘው አቋም አግባብነት የሌለው ነው፤ በወቅቱ በቤት ፈላጊነት ባይመዘገቡም ቤት የሌላቸው ግለሰቦች በውርስ መልክ ሊያገኙ ከሚችሉት የቤት ባለቤትነት መብት መነፈጋቸው በህገ መንግስቱ የተከበረላቸውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ በተጨማሪም መመሪያው ለሟች አካለመጠን ላልደረሱ ልጆች ክልከላ አለማድረጉ የሚደገፍ ቢሆንም በእድሜ ልዩነት በመፍጠር ሟች ከልጆቻቸው መሀከል አካለ መጠን ያልደረሱ ባይኖሩም አካለ መጠን የደረሰ ወራሽ የቤት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚፈቅድ አለመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40(1) እና (2) የተደነገገውን የዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ በመሆኑም በእነዚህ የሟች ወራሾች መካከል ልዩነት መፍጠር በህገ መንግስቱ የተሰጣቸውን በህግ እኩል ጥበቃ የማግኘት መብት የሚሸራርፍ ነው፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንደሚኒየም ቤቶች ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 44(ሐ) እና (ሠ) ድንጋጌ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1)እና(2) ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ትእዛዝ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መመርያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 44(ሀ እና ሰ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40(1) እና (2) ድንጋጌን የሚቃረን እንደሆነ ምክር ቤቱ ውሳኔ ስለሰጠ ውሳኔውን አውቆ ያሳደረውን መዝገብ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ የምክር ቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የፌዴራሉ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በምክር ቤቱ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

34 ( ~~3383~~ 5590)

# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 6ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

የመ/ቁጥር 108/15

መስከረም 29 ቀን 2016 ዓ.ም

አመልካች፡- የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- ዶ/ር አብርሃም መድኔ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከክት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡

የክሱ ይዘትም በአዲስ አበባ በቀድሞ አጠራር ወረዳ 17 ቀበሌ 20 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር 29252 ተመዝግቦ የሚገኝ የቤት ቁጥር 677 የሆነ መኖሪያ ቤት በደርግ ዘመን በቤቱ ውስጥ ከነበረው ንብረት ጋር ለቤት ሰራተኛ እና ለጥበቃ በአደራ ሰጥቼ ወደ ውጭ ሃገር ልሄድ ችያለሁ፡፡ በወቅቱ የደርግ መንግስት ሰራተኞቹን በማባረር ከአዋጅ 47/67 ድንጋጌ ውጪ ቤቱን ይዞ ማስተዳደር ጀመረ፡፡

ከደርግ መንግስት ዘመን በኋላ ጉዳዩን ለፕራይቬታይዘሽን ኤጀንሲ ባቀርብም ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ዘግቷል፡፡ ይሁንና የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በ16/03/86 ለኪራይ ቤቶች አስተዳደር በፃፈው ደብዳቤ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቁጥር 677 ቤት የእኔ መሆኑን አረጋግጦ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲሰጠኝ ወስኖ 1985 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት እንዲፈፀምና ከቤቱ ከሚገኘው ኪራይ ላይ 60% እንዲከፈለኝ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል አሏል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

በዚሁ መሰረትም ከቤቱ የሚገኘውን ኪራይ ሲከፈለኝ ነበር፡፡ በኋላም በ2005 ዓ.ም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጥናት አድርጎ ቤቱ የእኔ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ነገር ግን የቤቱ የኪራይ ዘመን ሲያልቅ አመልካች ቤቱን ሊያስረክበኝ ስላልቻለ በፍርድ ተገዶ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ተከሳሽ በመሆን በሰጠው መልስ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 (2) መሰረት መብቱ በሚኒስቴሩ ፀድቆ በተጠሪ ስም የታደሰ የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ካርታ እስካልተሰጠ ድረስ ከአዋጁ በፊት የነበረውን ካርታ ከክሱ ጋር አያይዘው ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ተቀባይነት የላቸውም፡፡ ተጠሪ በስማቸው ውሃና መብራት መክፈላቸውም የቤቱ ባለቤት አያደርጋቸውም፡፡ ተጠሪ ቤቱን በአደራ ለሰራተኛቸው ሰጥተው ስለሄዱ ቤቱን መጠየቅ የሚችሉት ከሰራተኛቸው እንጂ ከአመልካች ስላልሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ የሰማው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዘግቶት የነበረ ቢሆንም ክርክሩን በሰበር አቤቱታ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ተጠሪ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ለተባለው ለፕራይቬይታይዜሽን ኤጀንሲ አቅርበው ኤጀንሲው ስልጣን የለኝም ማለቱ እየታወቀ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው እና የቤት ባለሃብትነት ጥያቄን ፍርድ ቤቱ ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱ ተገቢነት የሌለው ስለሆነ ጉዳዩ እንደመሩለም ክስ እንዲመረመር ሲል ለስር ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

በዚህ መልኩ ጉዳዩ የተመለሰለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች ከሰማ በኃላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ውሳኔውም የፕራይቤታይዜሽን ኤጀንሲ በ1992 ዓ.ም የተጠሪን አቤቱታ መርምሮ ጉዳዩን ለማየት ሰልጣን የለኝም ብሎ ውድቅ አድርጓል፡፡ ኤጀንሲው ጉዳዩን ውድቅ ያደረገው አከራካሪው ቤት በአዋጅ አስፈፃሚ እንዲመለስ አልተፈቀደም እንዲሁም የኮብላይ ቤት ተብሎ መወሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የለም በሚል ምክንያት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ከእነዚህ ማስረጃዎች መረዳት የሚቻለውም ቤቱ በአዋጁ የተወረሰ አለመሆኑን ነው፡፡ አመልካች ከሀገር አስከወጡበት ጊዜ ድረስ የቤቱ ስመ ሃብት የራሳቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ካርታ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም አመልካች በዚሁ ቤት እስከ 1999 ዓ.ም በስማቸው መብራትና ውሃ ይከፍሉ ነበር፡፡
አመልካች በመልሳቸው በቤቱ ላይ የነበራቸው ካርታ በድሮ ሰርዓት የተሰራ ነው የሚሉት መከራከሪያዎች ተቀባይነት የላቸውም ይልቁንም አመልካች ቤቱን በአዋጅ 47/67 ሂደት በመንግስት የተወረሰ መሆኑን የማስረዳት ሃላፊነት እያለበት አላስረዳም፡፡ ቤቱ በአዋጁ የተወረሰ መሆኑን የሚገልፅ ቅፅ በአመልካች በኩል አልቀረበም::

ተጠሪ ከ40 ዓመት በኋላ ቤቱን በአደራ ጥለው ስለመሄዳቸው፤ ኮብላይ ስለመሆን አለመሆናቸው ወይም ቤቱ በወቅቱ ትርፍ ቤት ስለመሆን አለመሆኑ ምስክር መስማቱ ከተያዘው ጭብጥ ጋር አይገናኝም፡፡ ዋናው ጭብጥ ቤቱ በአዋጁ መሰረት ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም የሚል ሲሆን ይህን ጭብጥ ደግሞ ከቀረቡት ማስረጃዎች አንፃር ቤቱ እንዳልተወረሰ ተረጋግጧል በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ቅሬታ የመረመረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔውን በማፅናት ወስኗል፡፡ በመጨረሻም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በቤቱ ላይ የከተማ ልማት ሚኒስቴር አከራካሪውን ቤት የተጠሪ መሆኑን አምኖ ደብዳቤ የፃፉላቸው መሆኑን ማስረጃን ለመስማት እና ለመመዘን ስልጣን ባላቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ በውሳኔው የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ዘግቷል፡፡

አመልካች ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታና ቅሬታቸው በአቀጅ 47/67 የተወረሱ ቤቶችን በሚመለከት በተለይም ከአዋጁ ውጪ በህገ ወጥ መንገድ በመንግስት የተወሰዱ ቤቶችን አጣርቶ ለመመለስ በአዋጅ ቁጥር 110/88 መሰረት ስልጣን የተጠሰው ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው፡፡ ይህ ስልጣን በግልፅ ከፍርድ ቤቶች ተወስዶ ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ላለው ለመንግስት አካል የተሰጠ ስልጣን ስለሆነ እንዲህ ዓይነት ጉዳዮችን ተቀብለው ለማየት ፍርድ ቤቶች ስልጣን የላቸውም፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤቶች ይህን ጉዳይ ተቀብለው ማየታቸው እና ውሳኔ ወይም ፍርድ መስጠታቸው በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 (1) የተረጋገጠውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚጥስ ነው፡፡

በሌላ በኩል አከራካሪው ቤት በመንግስት የተወረሰ መሆኑን አመልካች በማስረጃ ማረጋገጥ አለበት የሚለው የፍርድ ቤቶች አቋም እና ውሳኔም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀደም ከሰጣቸው በርካታ ውሳኔዎች ጋር የሚቃረን እና መንግስት ቤቶችን በአዋጅ አግባብ መውረሱን ለማሳየት የግድ ቅፅ 003 የተባለውን ሰነድ ማቅረብ እንደሌለበትና ሰነዱ ባለመቅረቡ ብቻ ቤቱ አልተወረሰም ማለት የማይቻል መሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎቱ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም ተጠሪ ለክርክር ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አለኝ የሚሉት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በፊት የተሰጠ ካርታ ሲሆን ይህ የይዞታ ማረጋገጫ በአዋጅ 47/67 መውጣት ምክንያት የመከነ፤ ዋጋ ያጣ መሆኑን የፌ/ጠ/ፍ/ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት ውሳኔ ሰጥቶ እያለ በዚህ ጉዳይ ዝም ብሎ ማለፉ ሕገ መንግስታዊ የንብረት መብታችን ጥሷል፡፡ ስለሆነም በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጠን የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው በጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስ እና የሕገ መንግስት ትርጉም አስተያየት ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በመንግስት የተወረሰ ስለመሆኑ አመልካች ማስረጃ አላቀረበም፡፡ በቤቱ ላይ የተሰጠኝ የባለቤትነት ማስረጃ አልመከነም፤ የሚመክንበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ቤቱ ለተጠሪ እንዲመለስ ተወስኗል፡፡

አመልካችም ቢሆን ይህንኑ አምኖ ኪራይ ለተጠሪ ሲከፈል ነበር፡፡ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ በተገቢው ማስረጃ በማጣራት ቤቱ የተጠሪ ያልተወረሰ ቤት መሆኑን አረጋግጠው የወሰኑት ውሳኔ ስለሆነ የአመልካች የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት አቅርበዋል፡፡

ጉባኤው የአመልካችን የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ እና የተጠሪን መልስ ተገቢነት ካላቸው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አንፃር መርምሯል፡፡በዚሁ መሰረት ለውሳኔ ሃሳብ አቀራረብ በጉዳዩ ውስጥ ምላሽ የሚሹት ጭብጦች፡-

1ኛ. ከአዋጅ 47/67 ውጪ በህገ ወጥ መንገድ በመንግስት የተያዙ ቤቶችን እያጣራ ለባለቤቶቹ የመመለስ ስልጣን የማን ነው ? በአዋጅ መሰረት ቤቱ ለተጠሪ እንዲመለስላቸው ስልጣን ያለው አካል ወስኗል ወይ ?

2ኛ. ከአዋጅ 47/67 ጋር ተያይዞ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከዚህ ቀደም ከሰጠው ውሳኔ አንፃር አመልካች ቤቱ እንዲመለስላቸው ያልተፈቀደ እና በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንዲመለስላቸው ሳይወሰን ቤቱን ሊመለስ ይገባል በማለት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስታዊነት እንዴት ይታያል ? የሚል ነው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ከአዋጅ 47/67 ጋር በተያየዘ አንድ ቤት በአዋጁ መሰረት የተወረሰ ነው ወይስ የተወረሰ አይደለም የሚለውን ለመዳኝት ስልጣን ያለው ማን ነው የሚል ሲሆን አመልካች እንዲህ ዓይነት ክርክሮችን ፍርድ ቤቶች ለመዳኘት ስልጣን የላቸውም በማለት አጥብቆ ተከራክረዋል፡፡

በኢ..ፌ..ዲ..ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37 (1) እና 79 (1) መሰረት የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ነው፡፡ ይህ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 (1) መሰረት ለሌላ የዳኝነት አካል በህግ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን በዚህ አግባብ ለሌላ የዳኝነት አካል እስካልተሠጠ ድረስ ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን የሚኖራቸው ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡

ከአዋጅ 47/67 ጋር ተያይዞ በአዋጅ 110/1989 ተለይቶ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ተሰጥቶ የነበረው የዳኝነት ስልጣን ከአዋጅ 47/67 ውጪ በህገ ወጥ መንገድ በቀላጤ፣ በመመሪያ እና በቃል ትዕዛዝ የተወሰዱ ቤቶችን እያጣራ መመለስ ነው፡፡ በአዋጅ 110/89 ለኤጀንሲው ተሰጥቶ የነበረው ይህ ስልጣን እንዴት መተርጎም አለበት የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአዋጅ ቁጥር 110/89 ዋነኛው ዓላማ ከአዋጅ ቁጥር 47/87 ውጪ በህገ ወጥ መንገድ በመንግስት የተያዙ ቤቶችን እያጣራ መመልስ ነው፡፡

አዋጁ ከአዋጅ 47/867 ውጪ መንግስት በህገ ወጥ መንገድ አንድን ቤት ሊይዝ ስለሚችልበት ሁኔታ የዘረዘረ ሲሆን ይህም በቀላጤ፣ በመመሪያ እና በቃል ትዕዛዝ የሚሉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ አንዱ የሚነሳው አከራካሪ ነጥብ በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩት እነዚህ ሁኔታዎች ተዘርዝረው ያለቁ ሁኔታዎች ናቸው ወይስ ያልተዘረዘሩ ሌሎች ሁኔታዎችን ይጨምራል የሚል ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ፍርድ ቤቶች ማየት ይችላሉ ያለው በአዋጁ ከተዘረዘሩት እነዚህ ሁኔታዎች ውጪ በሌላ መንገድ ቤቱቶቹ ከአዋጅ 47/67 ውጪ ሊያዙ ይችላሉ በሚል ምክንያት ነው፡፡

ነገር ግን በአዋጁ ላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጪ ያለውን ወይም ሊኖር የሚችለው ሌላ ሁኔታ ምን እንደሆነ አልተገለፀም፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ በድፍኑ ከአዋጅ 47/67 ውጪ ቤቶች በአዋጁ ላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጪ በሌላም ሁኔታ በመንግስት ሊያዙ ይችላሉ የሚለው ሃሳብ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም በአዋጅ 110/89 ለፕራቬታይዜሽን ኤጀንሲ ተሰጥቶ የነበረው እና ከአዋጅ 47/67 ውጪ በመንግስት የተያዙ ቤቶችን የማጣራት እና የመመለስ ስልጣን የኤጀንሲው እንጅ የፍርድ ቤቶች አይደለም፡፡

ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ከአዋጅ 47/67 ውጪ በህገ ወጥ መንገድ በመንግስት የተያዙ ቤቶችን በሚመለከት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብለው ለማየት ስልጣን የላቸውም፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይም አመልካች አከራካሪው ቤት ከአዋጅ 47/67 ውጪ በመንግስት የተያዘባቸው መሆኑን ለኤጀንሲው አመልክተው ኤጀንሲው አላግባብ በመንግስት የተያዘ አለመሆኑን ተረጋግጦ እና ፍርድ አግኝቶ እያለ ፍርድ ቤቶች እንደ አዲስ ጉዳዩን ተቀብለው ማየታቸው አለግባብ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌላው አከራካሪ ነጥብ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 በመንግስት ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም፤ ቤቱ በአቀጅ ለመወረሱ ወይም ላለመወረሱ በምን ማስረጃ መረጋገጥ አለበት፤ ማስረጃውን የማቅረብ ግዴታ የማን ነው የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ 47/67 የተወረሱ ቤቶች የተወረሱት በአስፈፃሚው ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይሆን በሕግ አውጪ አካል በወጣ ህግ ነው፡፡ በህግ አውጭው አካል በወጣ ህግ የተወረሰ ቤት በፍርድ ቤት ወይም በአስፈፃሚ አካል ውሳኔ እንዲመለስ በአዋጁ የተደነገገ ነገር የለም፡፡ ይመለስ ቢባል እንኳን በዚህ መልክ የተወረሰ ቤት ሊመለስ የሚችለው ሕግ አውጪው በሚያወጣው ሌላ ሕግ ወይም በአዋጁ ይህ ስለመፈቀዱ በግልፅ ሲደነገግ ብቻ ነው፡፡

በአዋጅ 47/67 ለስራና ቤት ሚኒስቴር የተሰጠው ስልጣንም ቢሆን ከአዋጁ ውጪ አላግባብ በመንግስት ሳይወረሱ ነገር ግን በመንግስት የተያዙ ቤቶች ካሉ እነርሱን እያጣራ እንዲመልስ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 110/89 የተሰጠው ስልጣንም ቢሆን በአዋጅ 47/67 በመንግስት ያልተወረሱ ቤቶች እንዲመልስ

ሳይሆን ከአዋጁ ውጭ አላግባብ በተለያዩ ምክንያቶች በመንግስት የተያዙትን እያጣራ እንዲመልስ ነው፡፡
አሁን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው ቤት በአዋጁ መሰረት በመንግስት ሳይወረስ በህገ ወጥ መንገድ በመንግስት የተያዘ ስለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰውም ቤቱ በህገ ወጥ መንገድ በመንግስት የተያዘ ስለመሆኑ ጉዳዩን ለማጣራት ስልጣን ለተሰጠው ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ቤቱ አላግባብ በመንግስት የተያዘ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ተብሎ ውሳኔ የተሰጠበት ነው፡፡

ቤቱ በአዋጁ መሰረት በመንግስት ሳይወረስ አላግባብ በመንግስት የተያዘ ቢሆን ኖሮ አመልካች እደገለፀው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቤቱ በምን አግባብ ከአዋጁ ውጪ በሌላ ህግ ወጥ መንገድ በመንግስት እንደተያዘ የማረጋገጥ ስልጣን ነበረው፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች ቤቱ ከአዋጁ ውጪ በምን አግባብ በመንግስት ከህግ ውጪ እንደተያዘ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ቤቱ በአዋጅ 47/67 የተወረሰ አይደለም የሚለው መደምደሚ ላይ መድረሳቸው አላግባብ ነው፡፡

በአዋጅ 47/67 የተወረሱ ቤቶች ለመመዝገብ እና መረጃቸውን ለመያዝ የተለያዩ ቅፆች ስራ ላይ እንዲውሉ አዋጁን ለማስፈፀም ከወጣው መመሪያ መረዳት ይቻላል፡፡
በመመሪያው መሰረት የሚሞሉት እነዚህ ቅፆች ዓላማቸው የቤቶቹን መረጃዎች መያዝና መሰል እንጂ የቤት ባለቤትነትና ቤቱ ስለመወረስ አለመወረሱ እንደ በቂ እና ብቸኛ ማስረጃም የሚያገለግል አይደለም፡፡
ነገር ግን ፍርድ ቤቶች ቅፆቹን አከራካሪውን ቤት በመንግስት ለመወረሱ ወይም ላለመወረሱ እንደ በቂ እና የመጨረሻ ማስረጃ በመውሰድ የሰጡት ውሳኔ የተሳሳተ ነው፡፡ ስለሆነም ቤቱ በመንግስት ከዛሬ 40 ዓመት በፊት በህግ ስለመወረሱ ለማረጋገጥ ቅፅ አልቀረበም ፤ ቅፅ አለመቅረቡ ደግሞ የቤቱን አለመወረስ ያመለክታል የሚለው ድምዳሜ የተሳሳተ ነው፡፡
ሌላው መታየት ያለበት ጉዳይ አክራካሪው ቤት በመንግስት በአዋጅ መወረሱን ወይም አለመወረሱ ማስረዳት ያለበት ማን ነው የሚለውን ነው፡፡ ተጠሪ በመንግስት የተያዘባቸው ቤት አላግባብ የተያዘባቸው እና በአዋጅ ያልተወረሰ መሆኑን ክስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

አመልካች ደግሞ ቤቱ በአዋጅ የተወረሰ ስለሆነ ለተጠሪ ሊመለስ አይገባም በማለት ተከሳሽ ሆነው ተከራክሯል፡፡በዚህ በግራ ቀኙ ክርክር ውስጥ አከራካሪው ቤት በአዋጅ 47/67 ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም የሚለው ጭብጥ የማስረዳት ሸክሙ በሥነ-ሥርዓት ህግ መሰረት በምን ምክንያት ከከሳሽ ወደ ተከሳሽ እንደሚተላለፍ አልተገለፀም፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ቤቱ በመንግስት በአዋጅ ያልተወረሰ ስለመሆኑ ማስረጃ አቅርበው ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡

ይልቁንም ፍርድ ቤቶች አከራካሪው ቤት በመንግስት የተወረሰ መሆኑን የአሁን አመልካች ማለትም ተከላሽ በቅድሚያ ማስረጃ አቅርቦ ማረጋገጥ አለበት በማለት ቀድሞ ጉዳዩን በማስረጃ የማረጋገጥ ግዴታን ከተጠሪ ወደ አመልካች ማዞራቸው አላግባብ ነው፡፡

በአከራካሪው ቤት ላይ የባለሃብትነት ማረጋገጫ ሰንድን በሚመለከትም በፍ/ሕግ አንቀፅ 1195 መሰረት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ያለው አካል የቤቱ ባለሀብት እንደሆነ ግምት የሚወሰድ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ጉዳይ ውስጥ ተጠሪ ቤቱ በመንግስት ያልተወረሰ የግል ንብረታቸው መሆኑን ቢከራከሩም ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለማቅረባቸው ፍርድ ቤቶች አላረጋገጡም፡፡

አመልካች በአቤቱታው እንደገለፀው በአዋጅ 47/67 መውጣት በኋላ የቤት ባለሃብትነት መብትን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማስረጃ መሰጠት እንዳለበት እና ከዚያ በፊት የተሰጠው የሰነድ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ከአዋጁ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ሳይኖር ወይም ማስረጃው በፍ/ህግ አንቀፅ 1195 መሰረት ህጋዊ ያልሆነ፤ ማለትም በአዋጅ 47/67 ቀሪ የተደረገ፤ ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ መሆኑን እየታወቀ ፍርድ ቤቶች ቤቱ የተጠሪ መሆኑን ያስረዳል በማለት ይህን ማስረጃ መሰረት አድርገው የሰጡት ውሳኔ አላግባብ ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የተያዘው ጭብጥ በአዋጅ 47/67 በመንግስት የተወረሱ ቤቶችን በሚመለከት ከዚህ ቀደም የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ በጫት እርሻ እርባታና ኢንዱስትሪ ውጤቶች አምራችና ላኪ አክስዮን ማሕበር እና በመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ መካከል በነበረ ጉዳይ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባኤ በቀን 29/01/2011 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በሰጠው ውሳኔ በአገር አቀፍ ደረጃ ከአዋጅ ውጭ በመንግሥት የተያዙ ቤቶችን አስመልክቶ ወደ ባለንብረቶቹ ለመመለስ ኤጀንሲ የተቋቋመ መሆኑን፣ ከአዋጅ 47/67 ውጭ ቤት ተወስዶብኛል የሚል ሰው ቤቱ የተፈቀደለት ከሆነ ወይም ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቤቱ እንዲመለስለት ካልተወሰነ በስተቀር ለረዥም ግዜ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ ሲተዳደር የነበረ ንብረት ለአመልካች እንዲመለስ መወሰን ከጊዜ ርዝመት ጋር ተያይዞ ተአማኒነት የሌለው ማስረጃ እንዲቀርብ የሚያበረታታ በመሆኑ እንዲህ ዓይነት ቤቶች የመንግሥት እንደሆኑ ይቆጠራሉ ሲል ወስኗል፡፡

ስለሆነም በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት ከዛሬ 40 ዓመት በፊት በመንግስት እጂ የገባን ቤት በሚመለከት አመልካች ቅፅ ካላቀረበ ቤቱ በመንግስት እንደተወረሰ አይቆጠርም የሚለው ከቅሁ ዓላማ እና ቆይታ አንፃር በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠሪ የቤቱ ባለሀብት መሆናቸውን የሚያሳይ ካርታ አለኝ በማለት ያቀረቡትም ካርታው የተሰጠው ከአዋጅ 47/67 በፊት በመሆኑ በፍ/ህግ አንቀፅ 1195 መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

አከራካሪው ቤትም በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ እየተዳደረ የሚገኝ ስለሆነና ተጠሪ ከአዋጅ ውጭ የተያዙ ቤቶች እያጣራ እንዲመልስ ስልጣን ወደ ተሰጠው የፕራይቬታይዜሺን ኤጀንሲ ጉያቸውን አቅርበው ቤቱ እንዲመለስላቸው ያልተወሰነላቸው በመሆኑ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ለረዥም ግዜ በመንግሥት ቁጥጥር ስር የነበሩ ቤቶች አጣ ፈንታ አስመልክቶ ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ጉዳዩን ስንመረምረው የፍ/ቤቱ ውሳኔ ከምክር ቤቱ ውሳኔ እና ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37 (1) ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር በመዝገብ ቁጥር 189707 ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37 (1) የሚጥስ ስለሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 9 (1) መሰረት ተፈፃሚነት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢ ስለሆነ ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ በማጽደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ... የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ትዕዛዝ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም አስታውቃለሁ፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የጸደቀ መሆኑን እንዲያውቀው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ውሳኔው ደርሶት ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ይድረሰው፡፡

35 (1966)

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 4ኛ ዓመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

የመ/ቁ. 65/11

አመልካች፡- አቶ አብርሃም ኃ/ጊዮርጊስ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ መሃሪ መኮንን

2. የአራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር

3. የአራዳ ክ/ከተማ የወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤት

4. የአራዳ ክ/ከተማ ኮንስትራክሽን ቤቶች ልማት ጽ/ቤት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ የንብረት ኪራይ ክርክር የሚመለከት ሲሆን አመልካች ለአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 146 የሆነውን የንግድ ቤት ከወረዳው አስተዳደር ላይ ተከራይቼና የንግድ ስራ ፈቃድ አውጥቼ የምሰራበትን የንግድ መደብር የወረዳው አስተዳደር ለሌላ ሰው አከራይቶኛል በሚል መነጠቁ አላግባብ ነው፣ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ቤቱን ከፋፍዬ የተለያየ በር አድርጌ ባዶውን ክፍል ያላከራየሁ በመሆኑ በመመሪያው ስለማይሸፈን ቤቱ እንዲመለስልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበረን ግንኙነት በሽርክና ተስማምተን ከሚገኘው ጥቅም በወር ብር 4500 /አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ የሚሰጠኝ እንጂ ግንኙነታችን የአከራይና ተከራይ አይደለም፡፡ በተጨማሪም ዕድሜዬ 65 /ስልሳ አምስት/ ዓመት በላይ የሆንኩ አዛውንት ስለሆንኩና በአዋጁ ስለማልሸፈን ቤቱ ሊወሰድብኝ አይገባም በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ ባቀረቡት መልስ አመልካች ቤቱን በመከፋፈል ለራሳቸው ሌላ መውጫና መግቢያ በር በማበጀት ለእኔ ሌላ በር አዘጋጅተው ያከራዩኝ ስለሆነ በመመሪያው ተጠቃሚ መሆናቸውን፣ ቤቱን በወር ብር 4500 /አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ያከራዩኝ በመሆኑና የሽርክና ውሉ ከዚህ በፊት በፍ/ቤት ክርክር ተደርጎበት በፌዴራል መጀ/ደ/ፍ/ቤት ህጉን ተከትሎ ያልተፈፀመ ስለሆነ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተወሰነ በመሆኑ ቤቱ ለእኔ መከራየቱ በመመሪያው መሰረት አግባብ ስለሆነ ከክሱ በነጻ ልሰናበት በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በቀረቡት ማስረጃዎች መሰረት የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ ግንኙነት የአከራይና ተከራይ ሳይሆን የሽርክና ግንኙነት መሆኑ ስለተረጋገጠ፣ አመልካች አዛውንት በመሆናቸው መመሪያው አዛውንቶችን



የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ስለማያጠቃልል ተጠሪዎች ያደረጉትን የኪራይ ውል አቋርጠው ቤቱን ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አመልካች ከአሁኑ ክርክር በፊት በ1ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ በሽርክና ውሉ መሠረት ያልከፈለኝን ብር እንዲከፍለኝ የሚል ሲሆን ክሱን የተመለከተው ፍ/ቤት የሽርክና ውሉ ህገ ወጥ ነው የሚል ውሳኔ የሰጠ ስለሆነ ይህም ውሳኔ ፀንቶ ያለ በመሆኑ የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ ግንኙነት የሽርክና አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በ23/02/2009 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 98003 የሰጠው ውሳኔ ህገ መንግስታዊ መብቱ የሆኑትን አንቀጽ 40/1/፣ 37፣ 41/5/ የሚጥስ ስለሆነ ህገ መንግስታዊ ትርጉም እንዲሰጥ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቤቱን ያላከራዩና እድሚያቸውም አዛውንት መሆኑ ተጠቅሶ ውሳኔ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ይህም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ጸንቷል፡፡

አመልካች አከራይተው በመገኘታቸው ምክንያት ፍ/ቤቱ መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6ን መሰረት በማድረግ በጊዜው ለተከራየው 1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡ ተገደዋል፡፡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/1/ እንደተገለፀው እራሱ ሳይሰራበት ለ3ኛ ወገን ቤቱን በማከራየት በሚገኘው ገቢ ብቻ የሚተዳደር ተከራይ አቅመ ደካማ አዛውንት ወይም ወላጅ ያጡ ህጻናት፣ የኤች አይ ቪ ህመምተኞችና የአካል ጉዳተኛ የሆኑ በሽተኞች ከሆኑና ሌሎች የገቢ ምንጮች እንደሌላቸው በሚመለከተው ህጋዊ ተቋም ማስረጃ ካቀረቡ እንደ ቤቱ ሁኔታ ታይቶ በልዩ ሁኔታ ተከራይነታቸው ሊረጋገጥላቸው ይችላል በማለት ተደንግጓል፡፡
አመልካች ባያያዙት የልደት የምስክር ወረቀት የተወለዱበት ቀን ነሐሴ 28 ቀን 1937 ዓ.ም መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህ በመነሳት የአመልካች ዕድሜ መመሪያው እስከወጣበት ህዳር 7/2004 ድረስ እንኳ 67 /ስልሳ ሰባት/ አመት የሞላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ዕድሜ ደግሞ አዛውንት ወይም ደካማ የሚባል ነው፡፡

ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 41/5/ መንግስት የአካል እና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሃገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል በማለት ደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መንግስት ባለው የኢኮኖሚ አቅም ለአረጋውያን አስፈላጊውን ጥበቃ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው መመሪያ ይህን የህገ መንግስት ድንጋጌ የሚያስከብርና ወደ አፈጻጸም የሚያመጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ውሳኔው አመልካች አባውንት መሆናቸውን ግምት ውስጥ ሳያስገባ የተሰጠና አመልካች በዚህ እድሜያቸው ለአረጋውያን በህገ መንግስቱ የተሰጠውን ክብርና እንክብካቤ እንዳያገኙ ያደረገ ነው፡፡ ውሳኔው ለአመልካች በመመሪያውና በህገ መንግስቱ የተከበረላቸውን ከመንግስት እንክብካቤ የማግኘት መብት ያገናዘበ አይደለም፡፡ ክርክር የተነሳበት ቤት የመንግስት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ውሳኔው አመልካችን በአረጋዊነታቸው የተከበረላቸውን ከመንግስት እንክብካቤ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት የሚጻረር ነው፡፡ በዚህም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 41/5/ ድንጋጌ በመተላለፍ የተወሰነ ነው፡፡

ስለዚህ የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 5 የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ሲል አጣሪ ጉባኤው ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት ቋሚ ኮሚቴው የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና የምክር ቤቱ ባለሙያዎችን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውንና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ግራ ቀኙ በስር በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባደረጉት ክርክር የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት የአከራይ ተከራይ ሳይሆን የሽርክና ግንኙነት መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን፣ አመልካች 67 (ስልሳ ሰባት) ዓመት የሞላቸው፣ መሆኑን፣ ይህ ዕድሜ ደግሞ አባውንት የሚያስብል መሆኑን በመግለጽ እንዲሁም መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6(1) የሚደግፋቸው መሆኑን በመዘርዘር ተጠሪዎች ያደረጉትን የኪራይ ውል አቋርጠው ቤቱን ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ በጥልቀት በመመርመርና የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጠናከር ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባኤውና ቋሚ ኮሚቴው ያቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 41(5) ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሻሩን አውቆ የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካቹ ይሰጥ፡፡

36 | 1866)

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣3ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም

አመልካች፡- ሲክስ ኮንቲነንስት ሆቴል ኢ.ንክ (six Continents Hoteles inc.)

ተጠሪ፡- ክራውን (ባለቤት ወ/ሮ ዘውዲቱ መስፍን)

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ጋር ተያይዞ የተነሳን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሊጀምር የቻለው ተጠሪ በሄራልድ ጋዜጣ " CROWNE PLAZA" የሚለውን የንግድ ምልክት በመመለከተ ተቃውሞ ያለው እንዲቀርብ የወጣውን ማስተወቂያ መነሻ በማድረግ "CROWNE PLAZA" በሚል መጠሪያ የተመዘገበው ንግድ ምልክት የቀዳሚነት መብት ባለው "CROWN HOTEL" ከሚለው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ መሆኑ "ክራዉን " ከሚለው ቃል በኋላ አንዲት ፊደል በመጨመር "ክራውኔ" በማለት ተጠቃሚውን ህብረተሰብ በሚያሳስትና በሚያሳክር ሁኔታ በመቅረጽ የተጠሪን ሆቴል መልካም ስም የሚጎዳና ከፍተኛ ቁሳዊ ጉዳት የሚያደርስ ስለሆነ የአመልካች የንግድ ምልክት ሊፈርስ ይገባል ሲሉ ተጠሪ ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ከሃምሌ 07 ቀን 1987 ዓ/ም ጀምሮ የተጠሪ የንግድ ምልክት በንግድ ሚኒስቴር ተቀምጦ ሲታደስ የቆየ ቢሆንም፣ ለመጨረሻ ጊዜ የታደሰው ሃምሌ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በመሆኑ በሰርተፍኬቱ ላይ እንደተገለጸው የህግ ጥበቃው ሃምሌ 06 ቀን 2003 ዓ.ም ስላበቃን የCPROWNE PLAZA የንግድ ምልክት እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡ የአመልካች የንግድ ምልክት በዓለም አቀፍ ደረጃ እና በኢትዮጵያ የሚታወቁ ሆቴሎች የሚጠቀሙበት በመሆኑ እንዲሆም CROWN HOTEL የንግድ ምልክት በያዘው የጀበናና የጎጆ ቤት ምስል ምክንያት ሊመሳሰልና ሊያሳስት ስለማይችል የተለያዩና የማያሳክሩ ናቸዉ ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡

በኢ..ፌ.ዴ.ሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የአእምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ 501/98 አንቀጽ 24 መሰረት የንግድ



20

ምዝገባ ጸንቶ የሚቆየው የምዝገባ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን ጀምሮ ለ7 አመታት ነው፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በንግድ ምልክቱ ላይ እስከ ሃምሌ 06 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ የህግ ጥበቃ ስላላቸው በሰርተፍኬቱ ላይ ያለውን የ2 ዓመት ገደብ መሰረት በማድረግ የቀረበው ተቃዎሞ ተቀባይነት ስለሌለው ታልፏል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የአእምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የተጠሪን መዝገብ አስቀርቦ ሲመለከት CROWNE PLAZA እንዲመዘገብ በቀረበ ጥያቄ የካቲት 18 ቀን 2005 በንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና ስራ ሂደት በተዘጋጁ ደብዳቤ የንግድ ምልክቱ CRON HOTEL በሚል መጠሪያ በጽ/ቤቱ ከተመዘገበ የንግድ ምልክት ጋር በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 7(1) መሰረት ተመሳሳይ ስለሆነ ሊመዘገብ እንደማይችል ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ በንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር ld218-9-05 ጸሚክስ ግሎባል አንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግ/ማ ድርጅት በጻፈው ደብዳቤ ላይ እነደተጠቀሰው ድርጅቱ ከሚሰራው ባለ 5 ኮከብ ሆቴል ኢንቨስትመንት ጋር በቀጥታ የተገናኘ መሆኑን በመጥቀስ የንግድ ምልክቱ በድጋሚ እንዲታይ በተጠየቀው መሰረት ምዝገባው እንዲቀጥል የተወሰነ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የንግድ ምልክትና እንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና ስራ ሂደት CROWNE PLAZA የንግድ ምልክት ቀደም ሲል በጽ/ቤቱ ከተመዘገበው CROWN HOTEL የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ነው በሚል ውድቅ ካደረገው በኋላ በአመልካች ማመልከቻ መነሻነት የንግድ ምልክቱ ምዝገባ እንዲቀጥል ማድረግ ተገቢነት የሌለው አሰራር በመሆኑ በቀጣይ እንዳይደገም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የአእምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በኩል ኮሚቴው የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪይዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት ዕለት ከዕለት በሚያከናውናቸው ስራዎች ከንግድ ምልክትና ምዝገባ ጠበቃ አዋጅ ባሻገር ሌሎች በአገሪቱ የሚገኙ ህጎችንም ጭምር መሰረት በማድረግ መወሰን እንደሚገባ ያምናል፡፡ ከዚህ አንጻር የስራ ሂደቱ የሀገሪቱ የኢንቨስትመንት አዋጅ እና የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅን መነሻ በማድረግ CROWNE PLAZA የንግድ ምልክት



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

19

ከኢንቨስትመንት አኳያ ለአገር የሚሰጠው አስተዋጽዖ ግምት ውስጥ በማስገባት የሰጠው ውሳኔ መልካም ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የአእምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ተጠሪ በጽ/ቤቱ ያስመዘገቡት የንግድ ምልክት በአመልካች ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር በዕይታ፣ በንባብና በድምጸት የሚለያዩ ናቸው፡፡ ሁለቱም ለሆቴል አገልግሎት የሚውሉ በመሆኑ የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከሌሎች አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች አኳያ ሲታይ የኢኮኖሚ አቅም፣ የትምህርት ደረጃ እና የማገናዘብ አቅማቸው ከፍተኛ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚጠቀሚቸው አገልግሎቶች በመሆናቸው ሁለቱ የንግድ ምልክቶች መሳከር የመፍጠር አቅማቸው በጣም አነስተኛ መሆኑን ተረድቷል፡፡

ስለዚህ በግራ ቀኙ ስም የተመዘገቡት የንግድ ምልክቶች በተመሳሳይ ሁኔታ የህግ ጥበቃ አግኝተው ስራ ላይ ቢውሉ አንዱ በሌላው አገልግሎት ላይ ጉዳትን የማያስከትል እና በተጠቃሚው ላይ የሚፈጥረው መሳከር ስለሌለ CROWNE PLAZA የንግድ ምልክት በአዋጅ ቁጥር 501/98 ፈራሽ ሊደረግ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

ክርክሩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሌሎች የተቃውሞ ክርክሮች ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ከዋና ክርክሮች ውስጥ በንግድ ምልክትና ኢንድስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት አመልካች በመጀመሪያ ያቀረበው የንግደ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በተጠሪ ስም ከተመዘገበ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይነት አለው በሚል ውድቅ ከተደረገ በኋላ እንደገና እንዲቀጥል የተደረገው ከኢንቨስትመንት አንጻር ሊከበርለት የሚችለው ከፍተኛ አስተዋጽዖን ከግንዛቤ በመውሰድ እንደሆነ ከውሳኔው ተገንዝበናል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከጀምሩ በህጉ መሰረት የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ ይገባል ወይም አይገባም በሚለው ነጥብ ላይ የንግድ ምዝገባ፣ ጥበቃ አዋጅ፣ ዓላማና ግብ ከማሳካት አንጻር ሊታዩ የሚችሉት የጎንዮሽ ጉዳትና ጥቅሞች ላይ በቂ ጥናት ሳያደርግ በመወሰኑ የመነጨ በመሆኑ፣ መጀመሪያ ውድቅ ያደረገውን የንግድ ምልክት ምዝገባ ጉዳይ በድጋሚ ተመልክቶ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 320/95 አንቀጽ 6 እና በደንብ ቁጥር 273/2005 አንቀጽ 19(1) እና (3) መሰረት በአመልካች የቀረበን የእንደገና ይታይልኝ ጥያቄ ተቀብሎ የመመርመር ስልጣን ስላለው ነው፡፡

ሌላው ስለንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የወጣው አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 2(12) የንግድ ምልክት ማለት የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያስችል የሚታይ ምስል ነው፡፡ ምልክቱም ቃላቶችን ፣ ዲዛይኖችን፣ ፊደሎችን፣ ቁጥሮችን፣ ቀለሞችን፣ ዕቃዎችን፣ የመያዣዎቻቸውን ቅርጽ ወይም የነዚህን ቅንጅት ሊይዝ ይችላል በማለት ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ስለዚህ ክርክሩ መነሻ የሆነው የንግድ ምልክት በተጠሪ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር ስለንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የወጣው አዋጅ ቁጥር 501/1998 እና ደንብ ቁጥር 273/2005 የምዝገባ ጥያቄ ከቀረበለት የንግድ ምልክት ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ነው የሚባለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲኖሩ እንደሆነ በግልጽ የተደነገገ ነገር የለም፡፡

በመሆኑም አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ መመዘን የሚቻለው የንግድ ምልክቱ እንዲያመላክት (እንዲያስተዋውቅ) ወይም እንዲገለጽ ከተፈለገው ዕቃ ወይም አገልግሎት አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ከመሆን አለመሆን አንጻር አያይዞ በመመዘን እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 501/199 አንቀጽ 6 እና 7 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ አንጻር ተጠሪ በስሙ ያስመዘገበው የንግድ ምልክት CROWN HOTEL በሚል ጹሑፍና ዘውድ የተሳለበትና የጣሪያው ክዳን የጀበና ቅርጽ የሆነ መለስተኛ አዳራሽ ፎቶ ግራፍ የሚወክለው በክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነው ባለ 4 ኮከብ ሆቴል የሆነ የንግደ ስሙ CROWN HOTEL የተባለ የሆቴል አገልግሎት ሲሆን፣ አመልካች ያስመዘገበውና የይፍረስ ተቃውሞ የቀረበበት CROWNE PLAZA የሚል የንግድ ምልክት እንዲወክል የተፈለገው የአገልግሎት አይነት ባለ 5 ኮከብ ሆቴል የሆነ የንግድ ስሙ ሲክስ ኮንቲነንትስ ሆቴልስ ኢ.ንክ (Six Continents Hotels inc) የተባለ የሆቴል አገልሎት በመሆኑ፣ እንዲሁም አመልካች CROWNE PLAZA የሚለውን ሀረግ የሚጠቀመው ለንግድ ምልክትነት ስም CROWN HOTEL የሚል ዘውድ የተሳለበትና ጣሪያው ክዳን የጀበና ቅርጽ የሆነ መለስተኛ አዳራሽ ፎቶ ግራፍ በጣምራ በንግድ ምልክትንት የሚጠቀምበት እንደሆነ መገንዘብ በመቻሉ የንግድ ምልክቶቹ በንባብ፣ በጹሑፍ እና በድምጽ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ናቸዉ ለማለት የሚቻል አይደለም ሲል ወስኗል፡፡

ክርክሩን በሰበር የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 መግቢያ ላይ ለንግድ ምልክቶች ጥበቃ ማድረግ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ መዳበር በተለይም ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ልማት አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው በመታመኑ ኢንቨስትመንት የሚያበረታታው ለንግድ ምልክቶች ጥበቃ ሲደረግ ነው በማለት አቅጣጫን የሚያሰይ ነው፡፡

አዋጁ ከወጣባቸው ምክንያቶች መካከል ዕቃ በማምረት፣ ማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መልካም ስምና ዝና ለመጠበቅ፣ በተመሳሳይ ዓቃዎች ወይም አገልግሎቶች መካከል መሳከርን ለማስወገድ የንግድ ምልክት ጥበቃ ለማድረግ፣ በነጻ ገበያ ስርዓት ውስጥ የሸማቾችን ምርጫ በመምራት እና ጥቅማቸውን በማስጠበቅ ረገድ የሚጫወቱትን ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት እንጂ ክርክር የተነሳበት የንግድ ምልክት ለኢንቨስትመንት ተግባር እስከሆነ ድረስ አስቀድሞ የህግ ጥበቃ የተደረገለት የንግድ ምልክትና አገልግሎት ዘርፍ ጋር የተመሳሰለ ሆኖ ቢገኝም ደርቦ ለመስጠት እንዲያስችል አይደለም፡፡

ለንግድ ምልክት የህግ ጥበቃ እንዲያገኝ ማድረግ ኢንቨስትምንት የማበረታታት ፋይዳ አለው በሚል ያላቸውን ቁርጠኝነት ከመግለጽ በቀር ለኢንቨስትመንት ለታሰብ የአገልግሎት ዘርፍ አዋጅ ቁጥር 501/98 ስለ ንግድ ምልክት ጥበቃ ጉዳይ የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች አፈጻጸም ወደ ጎን ለማስቀረት የሚያስችል አይደለም፡፡

ኢንቨትስመንትን አስመልክቶ የወጡት ህጎችም ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያለውን የአዋጅ ቁጥር 501/98 ዝርዝር ድንጋጌ የተፈጻሚነት ኃይሉን የሚያስቀር ስልጣን ሰጭ ድንጋጌ የላቸውም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 6 የንግድ ምልክቶች ለምዝገባ ብቁ ከማይሆንባቸው ውስጥ የአንድ ሰው አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች አገልሎቶች በግልጽ ለመለየት የማያስችል ከሆነ፣ የምልክቱን ባህሪ የሚቀንስ ወይም የሌላውን ሰው መብት የሚጥስ ከሆነ፣ ህዝቡን የንግዱን ህብረተሰብ ሊያሳስት የሚችል ንግድ ምልክት ስለሆነ ሊመዘገብ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን ከአዋጁ ዓላማና ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዘት አንጻር እየታየ ጉዳዩን በሚመለከተው አስተዳደራዊም ሆነ የዳኝነት ሰጭ አካል አስፈላጊው ውሳኔ በህግ ከሚሰጥበት በቀር ኢንቨስትመንት በራሱ የአዋጁን ዓላማና ዝርዝር ድንጋጌዎች እዲሁም ለተቋሙ በህግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለማስለወጥ የሚያስችል አይደለም፡፡



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራሽን ምክር ቤት

16

በአዋጁ አንቀጽ 7 መሰረት የአመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄን በጀመሪያ የተመለከተው የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት የስራ ሂደት የካቲተ 18 ቀን 2005 ዓ.ም ከተጠሪ የንግድ ምልክት ተመሳሳይ በመሆኑ ሊመዘገብ አይችልም በማለት ጥያቄውን ውድቅ ያደረገ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

በሌላ ጊዜ ፀሚክስ ግሎባል ኢንተርፕንራይዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ስላመለከተ ምዝገባው እዲቀጥል ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያ ለቀረበው ጥያቄ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው ክፍል ሙያዊ ትንትናን መሰረት አድርጎ የሰጠውን ውሳኔ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ለውሳኔው መለወጥ መሰረት አድርጎ ከሰጠው ምክንያት ጋር ሲታይ፣ የመጀመሪያው በሙያዊ ትንተና የተደገፈ ምክንያት በመስጠት "CROWNE PLAZA የሚለው የንግድ ምልክት በጽ/ቤቱ አስቀድሞ ተመዝግቦ ከሚገኘው CROWN HOTEL ከሚለው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በመገኘቱ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ከዚህ በኋላ አስቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስለወጥ በምክንያትነት ተጠቅሶ የተገኘው የአመልካች' "CROWNE PLAZA የሚለውን የንግድ ምልክት ምዝገባ ሂደት ቢቀጥል ከኢንቨስትመንት አንጻር ሊያበረክት የሚችለው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ብቻ ከመሆኑ በቀር ሌላ የተለየ ምክንያት እንደሌለው ተገንዝበናል፡፡

ኢንቨስትመንትን ማበረታታት ተገቢ ቢሆንም ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ሲባል ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ምልክት እንዲመዘገብ እንደ መሥፈርት በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 ሆነ በኢንቨስትመንት አዋጅ ወይም በሌሎች ህጎች ስልጣን ሰጭ ድንጋጋዎች በሌለበት ሁኔታ በደፈናው ኢንቨስትመንት ከማበረታታት አንጻር በሚል መወሰኑ የህግ መሰረት የለውም፡፡

ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ህግ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 5፣ 6 እና 7 የተደረጉት ናቸው፡፡ ሲጠቃለል የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሀገሪቱ ኢንቨስትመንት አዋጅና የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጆች መነሻ በማድረግ 'CROWNE PLAZA" የንግደ ምልክት ለሀገር ከሚሰጠው አስተዋጽኦ በማለት አዋጅ ቁጥር 501/98 ለማውጣት መነሻ ግብ ሆነው በህጉ ሰለንግድ ምልክቶች ጥበቃ አስፈላጊነት ከመግቢያው ላይ እና ዝርዝር ድንጋጌዎች ትክክለኛ ይዘትና አፈጻጸም በመውጣት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት

የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል በማለት ውሳኔአቸው መሻሩን ገልጾ፣ የአመልካች "CROWNE PLAZA" የንግድ ምልክት ከተጠሪ "CROWN HOTEL" በሚል መጠሪያ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ መገኘቱ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 7(1) መሰረት የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ እና ህጋዊ ጥበቃ ሊሰጠው አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ሃምሌ 29 ቀን 2008 ዓ/ም ለጉባኤው በጻፈው አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) መሰረት መሰረታዊ የህገ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ከማረም የስልጣን ገደብ በማለፍ፣ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ሙያዊ እና አለም አቀፋዊ አሰራሮች ተፈትሾ የሁለቱ የንግድ ምልክቶች እንደ ማይመሳሰሉና እንደ ማያሳክሩ ተወስኖ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀባይነት ያገኘ ፍሬ ነገር በመመልከት መወሰኑ ከተጠቀሰው የሕግ መንግስቱ ድንጋጌ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥ ጠይቋል፡፡ጉባኤውም በአመልካች አቤቱታ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን ሲመለከት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ የሰጠውን ውሳኔ ከተሰጠው የሕገ መንግቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን መሆኑ አለመሆኑ መርምሯል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ሲመለከቱ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክትና ኢንዱስትራያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት ውሳኔ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚባል ስለሆነ ጉዳዩን በድጋሚ ማየቱ እንደግድፈት እንደማይወሰድ ተመልክተዋል፡፡

በተለይም ከተያዘው ጉዳይ አንጻር ሲታይ "CROWNE PLAZA" የሚለው የንግድ ምልክት በጽ/ቤቱ አስቀድሞ ተመዝግባ ከሚገኘው "CROWN HOTEL" የሚለው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ነው ተብሎ ውድቅ የተደረገው ውሳኔ መለወጥ የዚህ ውሳኔ መሰረት የነበሩት ፍሬ ነገሮች ሁሉ በመለወጥ የንግድ ምልክቶቹ እንደማይመሳሰሉ መደምደም የሚያስችል ነው፡፡

በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪ "CROWNE PLAZA" የሚለውን የንግድ ምልክት CORWN HOTEL የሚል ጹሑፍ ዘውድ የተሳለበትና የጣሪያው



14

ክዳን የጀበና ቅርጽ የሆነ መለስተኛ አዳራሽ ፎቶ ግራፍ በጣምራ በንግድ ምልክትነት የሚጠቀም እንደሆነ መገንዘብ መቻሉ የንግድ ምልክቶቹ በንባብ፣ በጽሑፍ፣ እና በድምጽ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ናቸዉ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ስለዚህ በግራ ቀኙ ስም የተመዘገቡ የንግድ ምልክቶች በተመሳሳይ ሁኔታ የህግ ጥበቃ አግኝተው ስራ ላይ ቢውሉ አንዱ በሌላው አገልግሎት ላይ ጉዳትን የማያስከትል እና በተጠቃሚው ላይ የሚፈጥረው መሳከር ስለሌለ CROWNE PLAZA የንግድ ምልክት በአዋጅ ቁጥር 501/98 ፈራሽ ሊደረግ እንደማይገባ መወሰናቸዉ እነደ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ አገላለጽ ጉዳዩን ከኢንቨስትመንት አስተዋፆ ብቻ ሳይሆን ከንግደ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብት ጋር በጥልቀት መታየቱን የማያረጋግጥ ነው፡፡

በተጨማሪም በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት በተለያየ ወቅት ሁለት ውሳኔዎች ምክንያት የግራ ቀኙ የንግድ ምልክቶች ተመሳሳይ መሆናቸዉ ወይም ያለመሆናቸዉ የፍሬ ነገር ክርክር ሆኖ በማስረጃ እና በሙያዊ ትንተና የሚጠራ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ አግባብ የንግድ ምልክቶች ተመሳሳይ መሆኑ ወይም ያለመሆን እንደ ፍሬ ነገር አልተጣራም ከተባለ አግባብ ባለው አካል ተጣርቶ እንዲወሰን ወደስር ፍ/ቤት መመለስ ሲገባው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህግ በመንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) ከተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን በማለፍ የአመልካች,,CROWNE PLAZA,, የንግድ ምልክት ከተጠሪ,,CROWN HOTEL,, በሚል መጠሪያ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በመገኘቱ በአዋጁ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 7(1) መሰረት የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ እና ህጋዊ ጥበቃ ሊሰጠው አይገባም ሲል መወሰኑ የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ማከናወኑን ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች የሰላም የዲሞክራሲ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና የማህበራዊ እድገት በማሳካት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት አላማዎችና እምነቶች መያዛቸው እና የእነዚህን ማሰሪያም የኢፌዴሪ ህገ መንግስት መሆኑን በመግቢያው ላይ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ እነዚህን ዓላማዎችና እምነቶች ለማሳካት መንግስት የሚከተለውን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ፍልስፍና መነሻ ህገ መንግስቱን ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት



13

ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ዕድገት በማሳካት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት ዓላማዎች እና እምነቶች እውን የሚሆኑት በላይ ሥር ሰዶ ያለውን ድህነት በመዋጋት እና በመቅረፍ እንደሆነ ሕገ መንግስቱን ይገልጻል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ በማምጣት ድህነትን ከማስወገድ ጎን ለጎን ተጨማሪ ስራዎችን መስራት እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት የድህነት መቀረፍ ለሌሎች ዓላማወች እና እምነቶች መሳካት ዋና መሳሪያ ነው፡፡

በሃገራችን እየታየ ባለው ለውጥ እና ባደጉ አገሮች እንደታየው አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት ዓላማ እና እምነት የኢኮኖሚያዊ ዕድገት በመገንባት ለውጥ ለማምጣት በተለይ እንደ ኢትዮጵያ የአገር ውስጥ ባለሃብቱ አቅምና ብዛት አነስተኛ በሆነበት ሁኔታ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ድህነትን ለመቅረፍ መሰረት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 41 (4-7) እና 43 (1) የተጣለውን ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለህዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት የመመደብ እና ለዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር የሚያስችል ፕሮጀክት የማካሄድ እንዲሁም በአጠቃለይና በተናጠል የአገሪቱ ዜጎች የኑሮ ሁኔታ የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸውን መንግስት እንደ ግዴታ ሊወጣ የሚችለው በተመሳሳይ አዳዲስ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በማስፋፋት ዓመታዊ ግብር በመሰብሰብ፣ ተጨማሪ የስራ መስኮች እንዲፈጠር በማድረግ፣ የቱሪዝም ፍሰቱን እና የውጭ ምንዛሬ ማግኛ መንገዶችን ማመቻቸት እንዲሁም ከቴክኖሎጂ አንጻር ያለውን ውስንነት ለመፍታት የቴክኖሎጂና የዕውቀት ሽግግር በማድረግ ነው፡፡

ስለዚህ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥበቃ ህጎች ስለንግድ ምልክት መመሳሰል ግልጽ ምላሽ ከሌላቸው የብሄራዊ ኢኮኖሚ የሚዳብርባቸውን በኢንቨስትመንት ሲሆን ከአገር ውስጥ ባለሃብቶች በተጨማሪ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ትልቅ ሚና እንዲኖረው በማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም ሕገመንግስቱ ዓላማዎችና እምነቶች ጋር በማጤን ለኢንቨስትመንት ሰፊ በር የሚከፍት ትርጉም መስጠቱ ይበልጥ ሕገ መንግስታዊነት የሚያረጋገጥ ሆኖ እያለ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ህጉን በጠባብ የተረጎበት አግባብ ከሕገ መንግስቱ ውሳኔ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ይህም ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ትዕዛዝ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ከፍ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አግባብ አለመሆኑን ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ሽሮታል፡፡ት የተሰጠው ውሳኔ በም/ቤቱ በተሰጠ የሕገ መንግስታዊ ተትርጉም ተሽሯል፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የውሳኔ ሀሳብ ም/ቤቱ በሰጠው የሕገ መንግስት ትርጉም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን እንዲያውቁት ውሳኔው ይድረሳቸው፡፡
3. ፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ም/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ እንዲያስፈጽም ይድረሰው፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካች ይድረሳቸው፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት



11

ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የስራ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

የፌ/ም/መ/ቁ.018/08

አመልካች፡- አቶ ታሪኩ መኮንን

ተጠሪዎች፡- 1.በአ/አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ

2. በአ/አበባ ትምህርት ቢሮ የየካ ክ/ከተማ ት/ጽ/ቤት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ-መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት አቤቱታዬን ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው አልቀበልም በማለቱ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ተብሎ ከተደነገገው ጋር የሚቃረን ስለሆነ የህገ-መንግስት ትርጉም እንዲሰጥላቸው አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉደዩ ላይ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም.የተፃፈ አቤቱታ ለጉባዔው አቅርበዋል፡፡ በአቤቱታቸውም በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ቀጣሪነት ከጥቅምት 1 ቀን 1999 ዓ.ም.እስከ መጋቢት 19 ቀን 2004 ዓ.ም.ድረስ በኮከበ ጽባህ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በፊዚክስ መምህርነት ተቀጥሬ ሳገለግል የየካ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር

6/2000 እና የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 24/2000 ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ በቀን 19/07/2004 ዓ.ም.በተፃፈ ደብዳቤ ከስራ አሰናብቶኛል፡፡

ስነ-ስርዓቱን ሳይጠብቅ በጽሑፍ የተሰጠኝን የስንብት ደብዳቤ በመቃወም ይግባኝን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ፍ/ቤት ባቀርብም የፍ/ቤቱ ሬጅስትራር ቅሬታዬን በቃል አልቀበልም በማለቱ አቤቱታዬን ለሲቪል ሰርቪስ ዳይሬክተር፣ ለከንቲባ ጽ/ቤት እና ለአቅም ግንባታ ቢሮ ባቀርብም ተገቢው ምላሽ ያልተሰጠኝ በመሆኑ በመጨረሻ አቤቱታዬን ለሕዝብ እንባጠባ ተቋም አቅርቤያለሁ፡፡

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በቁጥር 231/48-81/482/4 በቀን 07/05/05 ዓ.ም.በተፃፈ ደብዳቤ አመልካች የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽመዋል የሚባል ከሆነ አዋጅና ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት የዲሲፕሊን ክስ ተመስርቶባቸው መልስ የመስጠት እና የመከራከር መብታቸው ተጠብቆ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ የሚቀጡ ከመሆኑ በስተቀር በደብዳቤ ብቻ ከስራ መሰናበታቸው አግባብ ያለመሆኑን ገልፆ ስነ-ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ ጉዳዩ ታይቶ ውጤቱን በ30 ቀን ውስጥ እንዲያሳውቅ ለየካ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ቢፅፍም እስካሁን መፍትሔ ያላገኘሁ ስለሆነ ፍትህ የማግኘት ሕገ-መንግሥታዊ መብቴ ተጥሷል በማለት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በኮከበጽባህ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በፊዚክስ መምህርነት እያገለገሉ ባሉበት ወቅት ከየካ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት በቁጥር የካ/ት/ጽ/434/2004 በቀን 19/07/2004 ዓ.ም.በተፃፈ ደብዳቤ በት/ቤት ያሉ መምህራንን በማስተባበር የስራ ማቆም እንዲመታና የመማር ማስተማሩ ሥራ እንዲቆም ተማሪዎች እንዲበተኑ በማድረግ ተማሪዎች ለጉዳት እንዲዳረጉ፣ የትምህርት ቤቱ ሃብት እንዲባክን በማድረጋቸው ከዚህ በፊት ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ከጥፋታቸው ሊታረሙ አልቻሉም በሚል ምክንያት ከስራ እንዲሰናበቱ በተፃፈባቸው ደብዳቤ መነሻነት የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

አመልካቹም የዲስፕሊን ጥፋት ፈፅመዋል የሚባሉ ከሆነ ሰርዓቱ ተጠብቆ የዲስፕሊን ክስ ተመስርቶባቸው ለተከሰሱበትም የዲስፕሊን ክስ መልስ በመስጠት የመከራከር መብታቸው ሳይጠበቅ በአንድ ግለሰብ ውሳኔ ብቻ ከስራ መሰናበታቸው እና ይኸው የመብት ጥሰትና የሥነ-ሥርዓት አካሄድ እንዲታይላቸው ጉዳያቸውን ለሚመለከተው አካል ማለትም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ የአመልካችን ጉዳይ በመቀበል ፋይል ያልከፈተላቸው በመሆኑ አመልካች በየደረጃው ላሉ ለክቡር ከንቲባ ጽ/ቤት እና ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ካመለከቱበት እና የሕዝብ የዕንባ ጠባቂ ተቋምም ለአመልካች መፍትሔ እንዲሰጣቸው ከፃፈው ደብዳቤ መረዳትይቻላል፡፡

የሕዝባ እንባ ጠባቂ ተቋም ለየካ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት አመልካች የሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሰረት በማድረግ ለሚቀርብባቸው ክስ የመከራከርና መልስ የመስጠት መብታቸውን ጠብቆ ውሳኔ በመስጠት የተደረሰበትን ውጤት እንዲገለፅለት ለየካ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የመፍትሔ ሀሳብ ፅፏል፡፡

የየካ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የሕዝባ እንባ ጠባቂ ተቋም ለፃፈው ደብዳቤ ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን ጉዳዩን ለማጣራት ያመች ዘንድ ትምህርት ጽ/ቤቱ ለአመልካች የስንብት ደብዳቤ ከመሰጠቱ በፊት ጉዳያቸው በዲስፕሊን ኮሚቴ ታይቶ የተወሰነ መሆን ያለመሆኑ ተረጋግጦ ምላሽ እንዲሰጥ ተጠይቋል፡፡

የየካ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤትም ነሐሴ 04 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከአመልካች ጋር የተሰናበቱ መምህራን ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ስለጠየቁ ወደ ስራቸው የተመለሱ ሲሆን አመልካችም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቤት በኩል ከሙያ ማህበሩ ጋር በመሆን ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ተደርጎላቸው ከተላኩ ክፍት ቦታና በጀት ካለ ብቻ ለመቀበል ፈቃደኛ መሆናችንን እንገልፃለን የሚል ደብዳቤ ልኳል፡፡

ከዚህ ደብዳቤም መረዳት የሚቻለው አመልካች የዲስፕሊን ክስ ሳይመሰረትባቸውና ሳይከራከሩ በትምህርት ቤቱ ጽ/ቤት ኃላፊ በተፃፈ ደብዳቤ ብቻ ከስራ የተሰናበቱ መሆናቸውን ነው፡፡

በጉባኤው በኩል ጉዳዮን አጣርቶ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ያመች ዘንድ አመልካች በወቅቱ ለነበረው የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር የይግባኝ ማመልከቻውን ማቅረብ ያለማቅረባቸውን እና አንድ ጉዳይ በዲስፕሊን ኮሚቴ ሳይታይ በስራ ኃላፊ በተፃፈ ደብዳቤ ብቻ የተሰናበተ ሰራተኛ የስንብት ደብዳቤውን በመያዝ የይግባኝ ፋይል ለማስከፈት ቢፈልግ የይግባኝ መዝገብ መክፈት አለመክፈቱ ተጣርቶ ምላሽ እንዲሰጥበት ተጠይቆ ኅዳር 8 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በወቅቱ የነበረው ሬጅስትራር የለቀቀ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ምላሽ መስጠት የማይቻል መሆኑን እንዲሁም አንድ ጉዳይ በዲስፕሊን ኮሚቴ ሳይታይ በስራ ኃላፊ በተፃፈ ደብዳቤ ብቻ የተሰናበት ሰራተኛ የስንብት ደብዳቤውን በመያዝ የይግባኝ ፋይል ለማስከፈት ቢፈልግ የይግባኝ መዝገብ የሚከፈትለት መሆኑን በመግለጽ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

አመልካችም የስንብት ደብዳቤ በተሰጣቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻውን ለአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ ፍ/ቤት ያቀረቡ መሆናቸውን ለጉባኤው ካቀረቡት አቤቱታ ጋር በማስረጃነት ካያያዟቸው ሰነዶች መረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ ፍ/ቤት የአመልካችን ጉዳይ ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው ‹‹አንቀበልም›› ማለቱ አመልካች በጠቀሱት የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37 ላይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ተብሎ ከተደነገገው ድንጋጌ ጋር የሚቃረን መሆኑን ጉባኤው በሙሉ ድምፅ የተስማማ ስለሆነ ይህ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክርቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስናል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ አመልካች የስንብት ደብዳቤ በተሰጣቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤት ያቀረቡ መሆናቸውን ለጉባኤው ካቀረቡት አቤቱታ ጋር በማስረጃነት ካያያዟቸው ሰነዶች በግልጽ ተረድቷል፡፡

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤት የአመልካችን ጉዳይ ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው ‹‹አንቀበልም›› ማለቱ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37 ላይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ተብሎ የተደነገገውን የሚቃረን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ነው በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

1. አመልካች ጉዳያቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ የአስተዳደር ፍርድ ቤት የማቅረብ ሕገ-መንግስታዊ መብት አላቸው ብሎ ምክርቤቱ ወስኗል፡፡
2. የፌዴራሉ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡



6

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣3ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ አንድነት ከበደ አድራሻ አፋር ክልል ሰመራ ከተማ

ተጠሪ፡- የአፋር ብሔራዊ ክልል ፍትህ ቢሮ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ በዲሲፕሊን ምክንያት ከተሰጠ የስራ ስንብት ውሳኔ ጋር በተያያዘ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን መነሻውም አመልካች በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ በዐቃቤ ሕግነት በቋሚነት ተቀጥረው በክልሉ የሰነዶች፣ ጠበቆችና ማህበራት ምዝገባ ዓቃቤ ህግ በመሆን ሲያገለግሉ የክልሉ ዓቃቢያን ህግ አስተዳደር ጉባኤ በሥነምግባር ጥፋት ምክንያት ከስራ እንዲሰናበቱ የወሰነ መሆኑን በመግለፅ በቁጥር 1769/75 በቀን 10/10/2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አመልካችን ከስራ በማገዱ ነው፡፡

አመልካችም ጉዳዩ እንደገና እንዲታይላቸው ለክልሉ ፍትህ ቢሮ ዐቃብያን ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ቢያመለክቱም ጉባኤው በክልሉ ዐቃቢያን ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አንድ ጊዜ የሰጠውን ውሳኔ በድጋሚ የማየት ስልጣን የለውም በማለት ዘግቶታል፡፡ አመልካች አሁንም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢጠይቁም የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል በማለት ይግባኙን አልተቀበለውም፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የአመልካች ዋና ቅሬታም በክልሉ ዐ/ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ጥፋት ቢኖርብኝም ክስ ቀርቦብኝና ክሱ ደርሶኝ መልስና መከላከያዬን አቅርቤ ሳልከራከር በቀላጤ ደብዳቤ ብቻ ከስራ ተሰናብተሃል ተብዬ መታገዴ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37፣41 እና 42 የተመለከቱትን መብቶቼን የሚቃረን ነው የሚል ነው፡፡

12

ጉባዔውም የቀረበውን አቤቱታና የተሰጠውን ውሳኔ እንደተመለከተው አመልካች የዲስፕሊን ክስ ቀርቦባቸው ክሱ ደርሷቸው ተከራክሮ ውሳኔ ስለመስጠቱ የሚገልፅ ነገር ባለመቅረቡ አመልካች ከስራቸው የተሰናበቱት በአግባቡ ነው ወይስ ሕገ መንግስቱን በሚቃረን መልኩ ነው የሚለውን ጉዳይ ለማጣራት የክልሉ ፍትህ ቢሮ ይህንን መረጃ እንዲልክ በደብዳቤ ቁ አጠጉ/148/12/07 በቀን 01/12/2007ዓ.ም በደብዳቤ ቁ 1351/07 በቀን 01/06/2008 ዓ.ም እና በደብዳቤ ቁ 1351/07 በቀን 09/03/2009 ዓ.ም የጠየቀ ሲሆን የክልሉ መንግስት ፍትህ ቢሮ በደብዳቤ ቁጥር 491/09 በቀን 20/03/2009 ዓ.ም የተጻፈ 7 ገጽ የያዘ የውሳኔ ግልባጭ ያለውን ለጉባዔው ልኳል፡፡

ከተላከው መረጃ መረዳት እንደተቻለው የክልሉ ፍትህ ቢሮ የዐቃቢያን ሕግ አስተዳደር ጉባዔ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ፣ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ውሳኔ ላይ 6 ሰዎች አመልካች በማስጠንቀቂያ እንዲታለፍ፣ ሰባት ሰዎች ደግሞ እንዲባረር ድምጽ የሰጡና አንድ ሰው በድምጽ ተአቅቦ የወሰኑ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ከዚህ ስብሰባ በኋላ የክልሉ ፍትህ ቢሮ ደብዳቤ ቁ 1769/05 በቀን 10/10/2005 አመልካች በፈፀሙት የሥራ ኃላፊነት በአግባቡ አለመወጣት እና በታየባቸው የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት የዓቃቢያን ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ከሥራ እንዲሰናበቱ የወሰነባቸው መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፏል፡፡

በተጨማሪም በደብዳቤ ቁ 101153/2006 በቀን 26/7/2006 ዓ.ም አመልካች ጉዳዩ እንደገና እንዲታይላቸው ለዓቃቢያን ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ያቀረቡት አቤቱታ ጉባዔ አንድ ጊዜ የወሰነውን ነገር በድጋሚ የማየት ስልጣን ስለሌለው አቤቱታው ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ተያይዟል፡፡ አመልካች በክልሉ ዓቃቢያን ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢጠይቁም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አላቀረቡም ተብሎ በይርጋ ውድቅ ተደርጓል፡፡

የአፋር ክልል አቃቢያን ሕግ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 12/2004 አንቀጽ 80/1/ መሠረት የዲስፒሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም ዐቃቢ ሕግ መከላከያ መልሱን አዘጋጅቶ መቅረብ እንዲችል የቀረበበትን ክስ በዝርዝር የሚገልጽ የክስ ጽሑፍ፣ ክሱን ለማረጋገጥ የቀረበበትን ማስረጃ፣ መልስ የሚሰጥበትን ቀንና ቦታ ከሚያመለክት መጥሪያ ጋር እንዲደርሰው ማድረግ የመ/ቤቱ ኃላፊነት እንደሆን ይገልጻል፡፡

ከጉዳዩ ለመረዳት እንደተቻለው የአቃቢያን ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ቃለ ጉባዔ አመልካች መከሰሳቸውንም ሆነ ክሱ በአግባቡ ደርሷቸው ቀርበው መከራከራቸውን አይገልጽም፡፡ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይላቸው አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በማያውቁትና ክስ ባልቀረበባቸው እንዲሁም የመከላከል መብት ባልተጠበቀላቸውና ከውሳኔ በጀመረው ስነ ስርዓት ከስራ እንዲታገዱ መደረጋቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

ስለዚህ የአፋር ክልል ፍትህ ቢሮ አቃቢያን ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም አመልካች ከስራ እንዲታገዱ ወስኖ በደብዳቤ ቁ 1769/05 በቀን 10/10/2005 ዓ.ም አመልካችን ያሳወቀው የክልሉን የአቃቢ ሕግ አስተዳደር ደንብ ቁ 12/2004ን ያልተከተለና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 መሠረት ፍትህ የማግኘት መብትን የሚቃረን ነው፡፡የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የአፋር ክልል ፍትህ ቢሮ ዐቃቢያን ህግ አስተዳደር ጉባኤ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም አመልካች ከስራ እንዲታገዱ በደብዳቤ ቀ. 1769 በቀን 10/1/2005 ዓ.ም አመልካችን ያሳወቀው የክልሉን የዐቃቢያን ህግ አስተዳደር ደንብ ቀ. 12/2004ን ያልተከተለና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 መሰረት ፍተህ የማግኘት መብትን የሚቃረን በመሆኑ ይህ አስተዳደርአዊ ውሳኔና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔን ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ተትርጉም በመስጠት ሽሮታል፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የውሳኔ ሀሳብ ም/ቤቱ በሰጠው የሕገ መንግስት ትርጉም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን እንዲያውቁት ውሳኔው ይድረሳቸው፡፡
3. የአፋር ክልል ፍትህ ቢሮ ውሳኔው መሻሩን እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡
4. የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ም/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ እንዲያስፈጽም ይድረሰው፡፡
5. ፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ም/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ እንዲያስፈጽም ይድረሰው፡፡
6. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካች ይድረሳቸው፡፡

10

BM 39

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ 5ኛ ዓመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ
ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

የመ.ቁ. 72/11

አመልካች፡- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
2ኛ/ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት በ05/07/2009 ዓ.ም ለጉባኤው በላከው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ በአቶ አብዮት ዘለቀ በይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤቱ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረውን ክርክር ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ለጉባኤው ልኳል፡፡

የጉዳዩ ይዘትም በፍርድ ቤቱ ይግባኝ ባይ የሆኑት አቶ አብዮት ዘለቀ ተጠሪዎች በጋራ በመሆን ያስተላለፉት የዲስፒሊን የጥፋተኝነትና የስራ ስንብት ቅጣት ውሳኔ ምንም ዓይነት ክስ ያልቀረበበትና በጉዳዩ ያልተከራከሩበት መሆኑን በመግለፅ በተጠሪዎች የተላለፈው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20(4) ጋር ይጋጫል በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 515/99፣ በደንብ ቁጥር 77/94 አንቀፅ 8 አንቀፅ 13 አንቀፅ 17(1) እና (5) በተዘረዘሩት የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች ለቅጣት ውሳኔ ያበቃውን ክስ የመመልከት፣ የመከራከር፣ የመከላከል፣ በጉዳዩ ላይ ማስረጃዎች ቀርበውም ከሆነ ማስረጃዎችን የማወቅ፣ የመመርመር እንዲሁም መስቀልኛ ጥያቄ የመጠየቅና በጉዳዩ የሕግ ባለሙያዎች የማማከር መብት ሕጉ ያጎናፀፋቸዋል፡፡

ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒው ተጠሪዎች በጋራ በመሆን በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀፅ 37 መሰረት መጋቢት 26 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር EA-164/2/08 በተፃፈ ደብዳቤ በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትና የስራ ስንብት ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀጽ 4

ድንጋጌ ፅንስ ኃሳብ ጋር የሚጣረስ ስለሆነ ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ እንዲላክላቸው ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች ከስራ እንዲሰናበት የተደረገው በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀፅ 37 መሠረት ለ1ኛ መልስ ሰጪ መ/ቤት ዋና ዳይሬክተር በተሰጠ ልዩ ስልጣን መሆኑን እና ሠራተኛውም በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ስራ የመመለስ መብት የማይኖረው መሆኑን በመግለፅ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ሊዘጋ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ለአመልካች የስራ ስንብት ውሣኔ መሰረት የሆነው ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀፅ 37 ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 ጋር ተገናዝቦ ትርጉም እንዲሰጥበት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቱ ለሕገ መንግስት ትርጉም በላከው የትርጉም ጥያቄ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሰራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀፅ 37 የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር በሙስና የጠረጠረውንና እምነት ያጣበትን ማንኛውንም ሰራተኛ መደበኛውን የዲስፕሊን እርምጃ አፈፃፀም ስርዓት ሳይከተል ከስራ ማሰናበት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ከስራ የተሰናበተው ሰራተኛም በተላለፈበት ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ስራ የመመለስ መብት የለውም፡፡ ይህ ድንጋጌ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37(1) እና ሃገራችን ከተቀበለቻቸው የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 14(3)(ለ) እና (ረ) አንፃር ሲታይ ማንኛውም የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ክስ የመመልከት፤ የመከራከር፤ የመከላከል፤ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች የማወቅና ብሎም የመመርመር መብት አለው ከሚለው ድንጋጌ ጋር የማይጣጣም ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚሻው መሆኑን በማመን ለጉባኤው ልኳል፡፡

ጉባኤው ፍርድ ቤቱ የላከውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ለትርጉም ከተላከው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሰራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀፅ 37 ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37(1) እና 25 እንዲሁም ሃገራችን ከተቀበለቻቸው የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 14(3)(ለ)(ረ) አንፃር መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37(1) መሰረት ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚችል ማንኛውንም ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ በዚህ የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው ፍርድ ወይም ውሳኔ ለማግኘት በሕገ መንግስቱና በሕግ

የተቀመጠውን የክርክርና የፍርድ ሂደትን በተከተለ አካሄድ ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ ወይም ፍርድ ማግኘት እንዳለበትም ከዚሁ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህን የፍርድ ወይም የክርክር ሂደትን ሳይከተል የሚሰጥ ውሳኔ ወይም ፍርድ ወይም ይህንኑ የክርክር ሂደት እንዲቀር የሚፈቅድ ሕግ፣ መመሪያ ወይም ደንብ ከዚሁ የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ ይሆናል፡፡ በተለይም አንድ ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል እንዳያቀርብ የሚከለክል ወይም አቅርቦ ውሳኔ ማግኘት እንዳይችል ክልከላ የሚያደርግ ማንኛውም ሕግ፣ መመሪያ ወይም ደንብ ከዚሁ ግልፅ ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሃገራችን ከተቀበለቻቸው የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ) እና (ረ) መሰረት ማንኛውም የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ክስ የመመልከት፤ የመከራከር፤ የመከላከል፤ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ማስረጃ የማወቅና ብሎም የመመርመር መብት እንዳለውም ተደንግጓል፡፡

በተጨማሪም ሌሎች የመንግስት ሰራተኞችን የዲሲፕሊን የጥፋተኝነትና የስራ ስንብት ቅጣት ውሳኔ አሰጣጥን ስንመለከት የሕገ መንግስቱን መርህ የተከተለና የዜጎችን የመከራከር መብት የጠበቀ እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 515/99፣ ከደንብ ቁጥር 77/94 አንቀፅ 8፣ 13፣ 17(1) እና (5) ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ማንኛውም ሰው የዲሲፕሊን ክስ ሲቀርብበት የቀረበበትን ክስ የመመልከት፣ የመከራከር፣ የመከላከል፣ በጉዳዩ ላይ ማስረጃዎች ቀርበውም ከሆነ ማስረጃዎችን የማወቅና ብሎም የመመርመር እንዲሁም መስቀልኛ ጥያቄ የመጠየቅና በጉዳዩ የሕግ ባለሙያዎችን የማማከር መብቶች እንዳሉት ይደነግጋል፡፡

ይህን የሕገ መንግስቱን መርህ ተከትለው የወጡ ሕጎች በማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ሲሆን ከዚህ በተለየና የሕገ መንግስቱን መርህ ባልተከተለ መልኩ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች ብቻ ተብሎ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀፅ 37 የባለስልጣኑን የመንግስት ሰራተኞች ከሌሎች የመንግስት ሰራተኞች ጋር እኩል እንዳይዳኙ ወይም በሕግ ፊት እኩል የመከራከር መብት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ የደንቡ ድንጋጌ መሰረት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚሰሩን ሰራተኛ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር በሙስና የጠረጠረውና እምነት ያጣበት እንደሆነ መደበኛውን የዲሲፕሊን እርምጃ አፈፃፀም ሥርዓት ሣይከተል ከስራ ማሰናበት እንደሚችል መደንገጉና በተጨማሪም በዚህ ሁኔታ ከስራ የተሰናበተው ሰራተኛም በተላለፈበት ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ስራ የመመለስ መብት እንደሌለው መደንገጉ ከላይ ከተጠቀሱት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር የሚጋጭ በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም ሊሰጥበት የሚገባው ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሰራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀፅ 37 ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37(1) እና 25 ጋር የሚጋጭ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሃሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት የቀድሞው ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኛ አቶ አቢዮት ዘለቀ ክስ ሳይቀርብባቸው፣ እራሳቸውን የመከላከል እድል ሳይሰጣቸውና ማስረጃ ሳያቀርቡ በዋና ዳይሬክተሩ ጥርጣሬ ብቻ ከስራ እንዲሰናበቱ የሚፈቅደውና በየትኛውም ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ወደ ስራ የመመለስ መብት እንደሌላቸው የሚደነግገው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 ከሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣ 37(1) እንዲሁም ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች አለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 14(3) /ለ/ እና /ረ/ ጋር የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ እና ቋሚ ኮሚቴው የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሰራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣ 37(1) ጋር የሚቃረን በመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1) መሰረት ድንጋጌው ተፈፃሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሰራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37 ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣ 37(1) ጋር ይቃረናል በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ የሰጠ ስለሆነ የሚንስትሮች ምክር ቤት ውሳኔውን አውቆ ከላይ የተጠቀሰውን የደንቡን አንቀጽ እንዲያሻሽል የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
2. የፌዴራሉ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካችና ለተጠሪዎች ይድረሳቸው፡፡

BM 40

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ.95/13

አመልካች:- አቶ ተስፋዬ በለጠ መኩሪያ

አድራሻ:- ኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ ቀበሌ 13

ተጠሪዎች:- 1ኛ. የኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን

አድራሻ:- አዲስ አበባ

2ኛ. የኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ሸዋ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን

አድራሻ:- ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ/ም ለጉባኤው ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ሲሆን የስራ ክርክርን ይመለከታል፡፡

የጉዳዩ ይዘት አመልካች ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ከሁለት አመት በላይ በኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን ምስራቅ ሸዋ ዞን ቅ/ፅ/ቤት ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም ቅ/ጽ/ቤቱ ባደረገው ምርመራ አመልካች በ2004 ዓ.ም ከኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ከስራ በመቅረት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ከስራ መሰናበታቸውን እያወቁ በጽ/ቤቱ ቅጥር እንደተፈጸመላቸው አረጋግጧል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን የሰራተኞች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 160/2005 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ከማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት በዲስፕሊን ጥፋት የተሰናበተ ሰራተኛ የባለስልጣኑ ሰራተኛ ሆኖ መቀጠር አይችልም፤ አመልካችም በባለ ስልጣን መስሪያ ቤቱ መቀጠራቸው ጥፋት ነው በሚል ተከሰውና በቅ/ፅ/ቤቱ ስነ ምግባር ኮሚቴ ጉዳያቸው ሲመረመር ቆይቶ ጥፋተኛ ተብለዋል፡፡ አመልካችም በደንብ ቁጥር 160/2005 አንቀፅ 31 ንዑስ አንቀፅ 1(ሠ) መሰረት በቀን 27/3/2009 ዓ.ም በቁጥር A/T/G/A/Go/sh/Ba/4839/2009 በጽ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ በተፃፈ ደብዳቤ ከስራ ተሰናብተዋል፡፡

አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ክልል የገቢዎች ባለስልጣን ይግባኝ አቅርበው ባለስልጣን መስሪያ ቤቱም በቅ/ፅ/ቤቱ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ቅሬታ የማይቀርብበት ነው ሲል ውሳኔውን አጽንቶታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍ/ቤት የይግባኝ ማመልከቻ ይዘው ቢቀርቡም ፍ/ቤቱ በተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን ሰራተኞች ስነ ምግባር መመሪያ ቁጥር 8/2008 መሰረት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለሆነ የቀረበውን ማመልከቻ ተቀብለን ፋይል ከፍተን ልናስተናግድ አንችልም ሲል የይግባኝ ማመልከቻውን አልቀበልም ብሏል፡፡

በቀጣይ አመልካች አስተዳደር ፍ/ቤቱ የይግባኝ ማመልከቻውን ተቀብሎ አለማስተናገዱን በመቃወም ወደ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ቅሬታቸውን አቅርበውና ተቋሙም የአመልካች አቤቱታ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ካላቸው የክልሉ ህጎች አንፃር በመመርመር አመልካችን ካልተከፈለ ደመወዛቸው ጋር ወደ ስራቸው እንዲመለሱ በማለት የመፍትሄ ሃሳብ ሰጥቶ ለተጠሪ ተቋማት ቢያሳውቅም ተፈፃሚ አልሆነላቸውም፡፡ አመልካች አስተዳደራዊ መፍትሄ ለማግኘት ወደ ክልሉ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት እና ሌሎች መስሪያ ቤቶች አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም መፍትሄ ማግኘት አልቻሉም፡፡

አመልካችም ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ የኦሮሚያ ክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቢቀርብለትም በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ መመሪያ ቁጥር 08/2008 ተከልክያለሁ በሚል የቀረበለትን የይግባኝ ማመልከቻ ተቀብሎ ፋይል ከፍቶ ማስተናገድ አለመቻሉ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20(6)፣ እና 37(1) የተቀመጡትን ህገ መንግስታዊ የይግባኝ እና ፍትህ የማግኘት መብቶቼን የሚጥስ ስለሆነ የህገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥልኝና ወደ ስራዬ እንድመለስ እንዲደረግ በማለት ጉባኤውን ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤውም የኦሮሚያ ክልል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ ማመልከቻ ተቀብሎ አለማስተናገዱን ጠቅሰው ያቀረቡትን አቤቱታ ከተጠቀሱት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት ድንጋጌዎች አንፃር መርምሯል፡፡

አመልካች የፈፀሙት የዲስፕሊን ጥፋት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የስነ ምግባር ኮሚቴ ታይቶና በበላይ ሃላፊው ፀድቆ የተሰናበቱ መሆኑን መስሪያ ቤቱ ለአመልካች ከፃፈው የስንብት ደብዳቤና በክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን መስሪያ ቤት ከጸናው ውሳኔ መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች ከስራ መሰናበታቸውን በመቃወም የይግባኝ አቤቱታቸውን ለክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስና

እንደቆየና ከመመሪያ ቁጥር 8/2008 መምጣት በኂላ ግን ይህን አሰራር ለባለ ስልጣን መስሪያ ቤቱ ሰራተኞች መከተል እንዳቆመ ከፍ/ቤቱ ምላሽ መገንዘብም ተችሏል። ይህ ደግሞ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱን ሰራተኞች ይግባኝ የማለት መብት የሚያጣብብ ነው።

አመልካች ከአቤቱታቸው ጋር አያይዘው ባቀረቡት የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የህዝብ እንባ ጠባቂ የኦ/ቅ/ጽ/ቤት በቀን 07/07/09 ዓ.ም በቁጥር- MM20/T-305484/1/1 በፃፈው ደብዳቤም ሆነ ጉባኤው አስተዳደር ፍ/ቤቱን በጉዳዩ ላይ ማብራርያ እንዲሰጥ ጠይቆ ፍ/ቤቱ በደብዳቤ ቁጥር- BPSMQN2W-G3-3/114/561 በቀን 17/02/13 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የአመልካች የይግባኝ አቤቱታ ተቀብሎ ለማስተናገድ እንደማይችል ምላሽ ሰጥቷል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው አመልካች ከተጠሪ ተቋም በዲስፕሊን ጥፋት ከስራ መሰናበታቸውን በመቃወም የተፈጸመባቸው የመብት ጥሰት እንዲታይላቸው ለሚመለከተው አስተዳደር ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ተቀብሎ የይግባኝ ፋይል ከፍቶና ተራ አስይዞ ማስተናገድ ሲገባው አንቀበልም በማለት መመለሱን እና ከፍ/ቤቱ ለጉባኤው ከተጻፈው ደብዳቤ ለመረዳት እንደተቻለው አሁንም ድረስ የሚቀርቡላቸውን ተመሳሳይ ጉዳዮች ተቀብለው እያስተናገዱ እንዳልሆነ ነው። አስተዳደር ፍ/ቤቱ በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 61/1994 አንቀፅ 70(1) እና 71 የመንግስት ሰራተኞች የሚያቀርቡት ይግባኝ ተቀብሎ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው ቢሆንም አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀብሎና መርምሮ በፅሁፍ ምላሽ ባለመስጠቱ አመልካች ጉዳያቸውን አቅርበው መፍትሄ ማግኘት አልቻሉም።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከዚህ በፊት በመ.ቁ 018/08 በአቶ ታሪኩ መኮንን እና በአዲስ አበባ የትምህርት ቢሮ በነበረው ጉዳይ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ ተቀብሎ የመመርመር እና ውሳኔ የመስጠት ግዴታ እያለው የአመልካችን አቤቱታ 'አልቀበልም' ማለቱ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ጋር የሚቃረን መሆኑን ገልጾ ወስኗል። በያዝነው ጉዳይም በተመሳሳይ የኦሮሚያ ክልል የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍ/ቤት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው የይግባኝ አቤቱታውን አልቀበልም ማለቱ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ጋር የሚቃረን ነው።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ላይ 'ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው' ተብሎ ተደንግጓል። በመሆኑም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት

አንቀፅ 78/4/ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ 61/1994 መሰረት የመንግስት ሰራተኞች የስራ ክርክሮችን በይግባኝ አይቶ የመዳኘት ስልጣንና ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳይ ሆኖ እያለ በመመሪያ ተከልክያለው በማለት የይግባኝ አቤቱታቸውን ተቀብሎ ፋይል ከፍቶ አለማስተናገዱ አመልካች በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍ/ቤት በተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን ሰራተኞች ስነ ምግባር መመሪያ ቁጥር 8/2008 ተከልክያለው በሚል ምክንያት የአመልካችን አቤቱታ ተቀብሎ አለማስተናገዱ ኢ-ህገ መንግስታዊ በመሆኑ የኦሮሚያ ክልል የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍ/ቤት የተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን ሰራተኞች ስነ ምግባር መመሪያ ቁጥር 8/2008 ተፈፃሚነት የሌለው እንደሆነ አውቆ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት እና በኦሮሚያ ክልል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ለአመልካች የተጠበቀላቸውን የይግባኝ መብት በማክበር አቤቱታቸውን ተቀብሎ፣ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶና የሚቀርቡለትን ማስረጃዎች መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የቀድሞ የኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ባለሥልጣን ሠራተኞች ሥነ ምግባር መመሪያ ቁጥር 3/2006 አንቀፅ 27(1)ን ለመሻር የወጣው መመሪያ ቁጥር 8/2008 በኢ.ፌ.ዶ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ይህ የምክር ቤቱ ውሳኔ ከተላለፈት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚነት የሌለው በመሆኑ የክልሉ ገቢዎች ባለሥልጣን መመሪያውን እንዲያሻሽል የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የኦሮሚያ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ ተቀብሎ ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን ታዟል፤ የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

# የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤1ኛ ዓመት፤2ኛ መደበኛ ስብሰባ

መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም

አመልካች፡-፡- አቶ ሚልክያስ አየለ

ተጠሪ፡- የደምቢዶሎ ከተማ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ድርጅት

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

## ውሳኔ

የዚህ አቤቱታ መነሻ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37 (1) "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ፡፡" በሚል ተደንግጎ የሚገኘው ድንጋጌ ተጥሷል በማለት በአቶ ሚልክያስ አየለ አቤቱታ አቅራቢነት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ በማቅረቡ ነው፡፡

የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ኅዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ሃሳብ ተጠሪ ድርጅት ከመንግሥት መ/ቤትነት ተለውጦ በቦርድ የሚተዳደር ኢንተርፕራይዝ ሆኖ እያለ ካለአንዳች ምክንያት ከስራዬ እና ደሞዜ ስላፈናቀለኝ ክሴን ወረዳ ፍ/ቤት አቅርቤ ነበር፡፡ ፍ/ቤቱም ወደ ስራዬ እንድመለስ እና የተለያዩ ክፍያዎችን በጥቅሉ ብር 19,630(አስራ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሰለሳ) ብር እንዲከፍለኝ ወስኖ ውሣኔውን የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያፀናውም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ተጠሪ መ/ቤት የመንግሥት መ/ቤት ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የላቸውም በማለት ውሳኔያቸውን በመሻር የሰጠው ውሳኔ በሕገ-መንግሥቱ የተሰጠኝን ፍትህ የማግኘት እና የመስራት መብቴን ይጥሳል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ በአመልካች ክስ አቅራቢነት የተመለከተው የሰዩ ወረዳ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር በመ.ቁ. 13251 መጋቢት 8 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በኦሮሚያ ክልል የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 61/94 አንቀጽ 70 እና 71 መሰረት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድቤት ነው በሚል ያቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡ፍርድቤቱ የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር ጽ/ቤት ከአመልካች በቀረበለት ቅሬታ መሰረት በደብዳቤ ቁጥር 375/SSBG-55/03 ታህሳስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ አስፈላጊውን መመሪያ ለተጠሪ መስጠቱን በመጥቀስ ይህ አካል ‹‹ የመንግሥት አካል እና ከኦሮሚያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እና መልካም አስተዳደር ባገኘው ውክልና ለሰራተኞች መብት የተቋቋመ ከሆነ ይህ የአሁን ከሳሽ(ተጠሪ) ከሕግ አግባብ ውጪ ከስራ የተገለለው እልባት እንዲያገኝ የሰጠው መመሪያ ይህ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 61/1994 አንቀጽ 73/2/መሰረት ለማስፈፀም ስልጣን አለው፡፡›› በማለት ተጠሪ በጥቅሉ ብር 19,630(አስራ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሰለሳ ብር) ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል እና አመልካችን ወደ ስራው እንዲመልስ ሲል ወስኗል፡፡ ውሳኔውን የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አጽንቶታል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 128890 የካቲት 19 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አዋጅ ቁጥር 61/94 አንቀጽ 73/2/ በሚያዘው መሰረት የወረዳው ፍ/ቤት ስልጣን የኦሮሚያ ክልል የመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ማስፈፀም እንጂ የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር የፃፈውን ደብዳቤ የሚመለከት አለመሆኑን በመጥቀስ በተጠሪ ድርጅት ስነ ምግባር ኮሚቴ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት ባለመሻሩ እና የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን በቀጥታ መመልከትም የማይችል መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር ቢሮ ለቄለም ወለጋ ዞን አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር አመልካችን ይመለከታል በሚል በቁጥር BA18/M-



21

98318/1/2 በቀን 30/11/2004 የአስተዳደር ፍ/ቤት ዳኛ በሚል በተፈረመ ደብዳቤ፣ ተጠሪ ድርጅት ‹‹በራሱ በጀት የሚተዳደር እና መዋቅሩም ከመንግሥት መ/ቤት የተለየ እና በቦርድ የሚተዳደር ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 16/89 የመንግሥት ኢንተርፕራይዝ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ የሚተዳደር መሆኑን ተረድተናል፡፡›› በማለት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን እንደሌለው ገልፆአል፡፡

አመልካች ከላይ የተጠቀሰውን ደብዳቤ በመያዝ ክሳቸውን ለቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ በመ.ቁ.090319 በቀን 20/02/05 በሰጠው ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለው የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ነው ቢልም የአስተዳደሩ ፍ/ቤቱ ግን ከላይ በተጠቀሰው ደብዳቤ ስልጣኑ የኔ አይደለም ማለቱን በመጥቀስ ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በመሆኑ ስልጣኑ የወረዳው ፍ/ቤት ነው በማለት የአመልካችን መብት በመጠበቅ ወስኗል፡፡

የሰዮ ወረዳ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ለአመልካች ‹‹ ባሉበት›› በሚል ኅዳር 6 ቀን 2005 ዓ.ም በፃፉት ደብዳቤ አንደኛ ቀደም ሲል ፍ/ቤታችን አመልካች ወደ ስራ እንዲመለሱ ወስኖ የነበረ በመሆኑ መልሰን ጉዳዩን ለማየት የሚደግፈን ሕግ የለም፣ሁለተኛ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እስካልተሻረ ድረስ የኦሮሚያ ክልል ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር ቢሮ በስሩ ለተዋቀረው መ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ በማሳወቁ ብቻ ጉዳዩን ተቀብለን ለማየት አንችልም በማለት እንደዚሁም አመልካች በጉዳዩ ላይ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድቤት መመሪያ እንዲሰጥበት መጠየቅ እንደሚችሉ በማስገንዘብ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀደም ሲል ውሳኔውን በሰጠበት በመ.ቁ. 128890 ላይ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 6 መሰረት አዲስ ማስረጃ እንዳገኙ ጠቅሰው ያቀረቡትን ማመልከቻ በመቀበል ጥር 20 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች አገኘሁ ብለው ያቀረቡት ማስረጃ‹‹ የሲቪል ሰርቪስ ፍ/ቤት እና መልካም አስተዳደር የመልስ ሰጪውን (የአሁን አመልካች) እና የአሁን ተጠሪን ጉዳይ በተመለከተ የሚታየው በወረዳ ፍርድቤት ላይ ነው እንጂ እኔ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን መመሪያ መሆኑን ይህ ችሎት አይቷል፡፡›› በማለት ማስረጃውን ከፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 6 አንፃር በመመርመር አመልካች እና ተጠሪ ፍርድ ቤቱ ስልጣን አለው የለውም በሚለው ሲከራከሩበት የነበረ እና የሚያውቁት ነገር መሆኑን በመጥቀስ እንዲዚሁም የተጠሪ ሕገወጥ ድርጊት ስለመኖሩ



20

የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ስልጣን የለኝም ማለቱ የራሱ ውሳኔ ከመሆኑ ባሻገር የሚሰጠው መመሪያ ይህ ችሎት ከዚህ በፊት ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ መሰረቱን የሚያስለውጥ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ በተጨማሪም አመልካች አግኝቻለሁ ያለውን አዲስ ማስረጃ ማስረጃውን ባገኘ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያላቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡አመልካች ተጣሰብኝ ሲሉ የጠቀሱት የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌ አንቀጽ 37/1/ ን የተመለከተ ፍትህ የማግኘት መብት ነው፡፡

ፍትሕ የማግኘት መብት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37/1/ "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡ ›› በሚል ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች፣ ተጠሪ ከስራ ገበታዬ አፈናቅሎኛል ሲሉ ክሳቸውን ለፍ/ቤት አቅርበው ጉዳዩን የተመለከቱት የወረዳና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች አመልካች ወደ ስራ ገበታቸው እንዲመለሱ እና ያልተከፈላቸው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉዋቸው ሲሉ ወስነዋል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የመንግሥት ሰራተኛ መሆናቸውን ጠቅሶ የስር ወረዳ ፍ/ቤት የመንግሥት ሰራተኛን በተመለከተ የመንግሥት መ/ቤቱ የስነ-ምግባር ኮሚቴ የሚሰጠው ውሳኔ ለመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት ቀርቦ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ለአፈፃፀም ሲቀርብለት ከማስፈፀም በቀር ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ መወሰን እንደማይችል በመግለፅ የወረዳና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶቹን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች የኦሮሚያ ክልል ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር ቢሮ ለቄለም ወለጋ ዞን አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር አመልካችን በሚመለከት በፃፈው ደብዳቤ ጉዳያቸውን ማየት እንደማይችል መግለፁን በመረዳታቸው ጉዳዩን ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለው የመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት ነው ቢልም የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ግን ስልጣኑ የመደበኛ ፍ/ቤት ነው ማለቱን በመጥቀስ ጉዳዩን አስቀድሞ ማየት ያለበት የወረዳው ፍ/ቤት ነው በማለት ወስኗል፡፡

18

አመልካች ጉዳዩን ለወረዳው ፍ/ቤት ይዘው ቢቀርቡም የወረዳው ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት በፃፉት ደብዳቤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ባልተለወጠበት እንደዚሁም ጉዳዩን በድጋሚ ለማየት የህግ አግባብ በሌለበት ጉዳዩን ማየት አንችልም በማለታቸው አመልካች በደብዳቤ ጉዳያቸው እንዳይታይ ተከልክሏል፡፡አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሰረት የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ስልጣን የለኝም ማለቱን በመጥቀስ አዲስ ማስረጃ እንዳገኙ በመግለፅ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይላቸው ቢያቀርቡም አቤቱታቸው የድንጋጌውን መስፈርት አያሟላም በሚል ተቀባይነት አላገኙም፡፡

ተጠሪ መ/ቤት "የኦሮሚያ ክልል ም/ቤት " የከተሞች የመጠጥ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 78/1996›› ተብሎ በሚጠቀስ አዋጅ እንደዚሁም አዋጁን ተከትሎ በወጣ‹‹ የኦሮሚያ ከተሞች የመጠጥ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 40/1997›› ተብሎ በሚጠቀስ ደንብ አንቀጽ 3 ስር በተራ ቁጥር 57 ላይ ተጠቅሶ የተቋቋመ እና በአዋጁ አንቀጽ 20 የፋይናንስ /የገንዘብ/ ምንጮች በሚለው ርዕስ ስር "ድርጅቱ በራሱ ገቢ ይተዳደራል፣የድርጅቱ የገቢ ምንጮች፣ከውሃ ሽያጭና ከፍሳሽ አገልግሎት ስራዎች የሚገኝ፣በብድር የሚገኝ፣በእርዳታና እና በስጦታ የሚገኝ ንብረትና ገንዘብ፣በከተማው አስተዳደር የሚመደብለትና ከማናቸውም ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሚገኝ ውሃ፣አገልግሎቶችን ለማቋቋምና ለማስፋፋት የክልሉ መንግስት አቅማቸውን አጥንቶ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይችላል"

በሚል ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ከድንጋጌው መረዳት እንደሚቻለው ድርጅቱ በሙሉ ወይም በከፊል ሊባል በሚችል መልኩ ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር አይደለም፡፡ በክልሉ የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 61/94 አንቀጽ 2/2/ መሰረት አንድ ድርጅት የመንግሥት መ/ቤት ሊባል የሚችለው በሙሉ ወይም በከፊል ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ሲሆን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በአደረጃጀቱ ጭምር በመንግስት መ/ቤትነት የሚመደብ አይደለም፡፡ አመልካችም በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ የሚሸፈኑ የመንግሥት ሰራተኛ ተብለው ሊጠቀሱ የማይችሉ በመሆኑ የክልሉ የመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ያለመዳኘቱ ባግባቡ የሆነ ነው፡፡የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር ጽ/ቤት አመልካችን እንደ የመንግሥት ስራተኛ በመቁጠር ለተጠሪ መመሪያ መስጠቱ በተሳሳተ መነሻ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ 18

የሰዮ ወረዳ ፍ/ቤትም አመልካችን እንደ የመንግሥት ሰራተኛ በመቁጠር የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር ጽ/ቤት የሰጠውን መመሪያ እያስፈፀምኩ ነው በሚል የአመልካችን ክስ በቀጥታ በመቀበል የሰጠው ውሳኔ፣ እንደዚሁም የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳን ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በተሳሳተ መነሻ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎች ናቸው፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች በሕግ የመንግሥት ሰራተኛ ሊባሉ የማይችሉ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶችን የተሳሳተ መነሻ ባለማረም አመልካችን እንደ መንግሥት ሰራተኛ በመቁጠር የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በሌላ አግባብ በመሻር የሰጠው ውሳኔ አመልካችን ላልተገባ ውጣ ውረድ የዳረገ እና ፍትህ የማግኘት መብታቸውን ያጣበበ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳያቸውን ለመደበኛው ፍ/ቤትም ሆነ ለክልሉ መንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት አቅርበው ማስወሰን ያልቻሉ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37/1/ የተጠቀሰው ፍትህ የማግኘት መብታቸው ተጥሷል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው በዋናነት የሰዮ ወረዳ ፍ/ቤት የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር ጽ/ቤት የሰጠውን መመሪያ እያስፈጸምኩ ነው በሚል የአመልካችን ክስ በቀጥታ በመቀበል ያሳለፈው ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ማጽናቱ በተሳሳተ መነሻ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ መሆኑን እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች በሕግ የመንግሥት ሠራተኛ ሊባሉ የማይችሉ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶችን ስህተት ባለማረም አመልካችን እንደ የመንግሥት ሠራተኛ በመቁጠር የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ የግለሰቡን ፍትሕ የማግኘት መብት ያጣበበ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካችም በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳያቸውን ለመደበኛ ፍርድቤትም ሆነ ለመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድቤት አቅርበው እንዳያስወስኑ መደረጉን መረዳት ይቻላል፡፡

17

ስለሆነም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(1) "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው " በሚል የተደነገገው ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው በመጣሱ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም።

በመሆኑም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕገመንግስቱን አንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

## ትዕዛዝ

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገ መሆኑን እንዲያውቁት ለፍርድቤቶቹ የውሳኔው ግልባጭ እንዲደርሳቸው ይደረግ።

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት።

የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ።

16

42

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ. 85/12

አመልካች፡- ጎንደር ዩንቨርስቲ

ተጠሪዎች፡- እነ አድና አባተ (121 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 12/07/2011 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥም ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን በአማራ ክልል ጎንደር ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ነው፡፡

ተጠሪዎች ለወረዳው ፍ/ቤት ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከ2002 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም በቀን ሰራተኝነት በአመልካች ተቋም ስር በሚተዳደሩ የተለያዩ ግቢዎች ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት በእንጀራ ጋጋሪነት፣ በወጥ ቤት ሰራተኝነት፣ በመስተንግዶ ስራ፣ በእንጨት ፈላጭነት ወዘተ ተቀጥረው በየወሩ 1740 ብር (አንድ ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር) እየተከፈላቸው ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ በቀን 08/02/2010 ዓ.ም በህገ ወጥ መንገድ ከስራ የተሰናበቱ መሆናቸውን በመግለጽ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ወይም ወደ ስራቸው መመለስ የማይቻል ከሆነ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ተገቢ የስንብት ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ባቀረበው መልስ ለትርፍ ያልተቋቋመ የመንግስት መስሪያ ቤት መሆኑ ገልጾ ተጠሪዎች ክሳቸው ማቅረብ ያለባቸው በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 መሰረት በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ስለሌለው በመጀመርያ ደረጃ መቃወምያ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም በቀረበው የመጀመርያ ደረጃ መቃወምያ ውሳኔ ለመስጠት ከግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የህግ ክርክር እንዲቀርብ ከፈቀደ በኋላ በመጨረሻ አመልካች የመንግስት ተቋም

በመሆኑ እና በመንግስት በጀት የሚተዳደር በመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እንደ ድርጅት ስለማይቆጠር በተጠሪዎች የቀረበው ክስ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ወስኗል።

ተጠሪዎች የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ያስቀርባል በማለት ከመረመረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(2)(ሠ) መሰረት የመንግስት ሰራተኞች ጉዳይ በልዩ ህግ እንደሚታይ ቢገልጽም የተጠሪዎች ጉዳይ የቀን ሰራተኞች በመሆናቸው እንደ መንግስት ሰራተኛ እንደማይቆጠሩ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 2(2) የተገለጸ በመሆኑ ጉዳያቸው በአዋጁ አልተሸፈነም። በመሆኑም ተጠሪዎች የመንግስት ሰራተኞች ባለመሆናቸው እና በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የተጠሪዎች ጉዳይ በሌላ ልዩ ህግ እንደሚታይ ያልተገለጸ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው በማለት በፍሬ ነገር ደረጃ አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ሲል መዝገቡ መልሶታል።

አመልካች የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል። በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ የቀን ሰራተኞች የመንግስት ሰራተኞች አይደሉም የሚል ድንጋጌ ሳይኖረው የስር ፍ/ቤት የመንግስት ሰራተኞች አይደሉም ማለቱ፣የቀን ሰራተኞች የመንግስት ሰራተኞች አይደሉም ቢባል እንኳ ጉዳያቸው በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ይታያል ማለት እንዳልሆነ እና ፍ/ቤቱ የተጠሪዎች ጉዳይ በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ስለማይሸፈን በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ይታያል ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻርልን የሚል ነው። ተጠሪዎች በበኩላቸው የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም ሲሉ ውሳኔው እንዲጸናላቸው ጠይቋል።

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አንቀጽ 3(2)(ሠ) መሰረት የመንግስት ሰራተኞች ጉዳያቸው በአዋጁ እንዳይታይ የተፈጻሚነት ወሰን ያስቀመጠ ቢሆንም የአዋጁ ዓላማ በስራ ሁኔታቸው ምክንያት ልዩ ህግ ለወጣላቸው መንግስት ሰራተኞች በልዩ ህጉ እንዲተዳደሩ ለማድረግ ታስቦ የወጣ መሆኑን፤ በሌላ በኩል የተጠሪዎች የስራ ሁኔታ በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ የማይታይ ከመሆኑ በተጨማሪ ጉዳያቸው ለማየት ሌላ ልዩ ህግ የሌለ በመሆኑ የተጠሪዎች የስራ ሁኔታ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እንዲታይ የስር ፍ/ቤት መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ውሳኔውን አጽንቶታል።

አመልካች የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል። የሰበር ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መርምሮ አመልካች ከተቋቋመበት የማስተማር እና ምርምር ስራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እና ዘላቂነት ባህሪ ያለው የስራ መስክ ቀጥሮ የስራ ቅጥር ግንኙነታቸው በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ይሁን በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የማይሸፈን በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰራተኞች በቀን ሰራተኝነት መደብ በመቅጠር ስንብቱ ተጠያቂነት በማያስከትልብኝ ሁኔታ ማድረግ እችላለሁ በሚል ዓይነት የሚያቀርበው ክርክር ህጋዊ መሰረት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል።

አመልካች ለህገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ ባቀረበው የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ተጠሪዎች በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 515/99 እና አዋጁን ተክቶ በወጣው አዋጅ ቁ.1064/10 የማይሸፈኑ ቢሆንም ጉዳያቸው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 ይታያል በማለት በመጨረሻ ጉዳዩን የተመለከተው ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ በህገ መንግስቱ ለህግ አውጪውና ለፍ/ቤቶች የተቀመጠው የስልጣን ክፍፍል የሚጥስ ነው፤ ፍ/ቤቱ የተጠሪዎች ጉዳይ በአዋጅ ቁ. 515/99 አይታይም የሚል መደምደምያ ከደረሰ መፍትሔው ጉዳዩ በአዋጅ ቁ. 377/96 እንዲታይ መወሰን ሳይሆን የህግ አውጪው የተጠሪዎች ሁኔታ የሚገዛ ህግ እንዲያወጣ ለህግ አውጪው መተው ነበረበት እንጂ ፍ/ቤቱ በውሳኔ ሰበብ የራሱን ፍላጎት በህገ መንግስቱ ከተቀመጠው ስልጣን በላይ የተገበረ በመሆኑ ውሳኔው ከህገ መንግስቱ ይቃረናል ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል።

የአመልካች የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ከፍ/ቤቱ ውሳኔና አግባብ ካላቸው የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አንጻር ተመርምሯል።

አመልካች ለጉባኤው ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪዎች በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 515/99 እና አዋጁን ተክቶ በወጣው አዋጅ ቁ.1064/10 የማይሸፈኑ ቢሆንም ጉዳያቸው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 ይታያል በማለት በመጨረሻ ጉዳዩን የተመለከተው ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ በህገ መንግስቱ ለህግ አውጪውና ለፍ/ቤቶች የተቀመጠው የስልጣን ክፍፍል የሚጥስ ነው፤ ፍ/ቤቱ የተጠሪዎች ጉዳይ በአዋጅ ቁ. 515/99 አይታይም የሚል መደምደምያ ከደረሰም መፍትሔው ጉዳዩ በአዋጅ ቁ. 377/96 እንዲታይ መወሰን ሳይሆን ህግ አውጪው የተጠሪዎች ሁኔታ የሚገዛ ልዩ ህግ እንዲያወጣ ለህግ አውጪው

መተው ሲገባው ፍ/ቤቱ በውሳኔ ሰበብ የራሱን ፍላጎት በህገ መንግስቱ ከተቀመጠው ስልጣን በላይ የተገበረ በመሆኑ ውሳኔው ከህገ መንግስቱ ይቃረናል እንዲባልለት ነው።

በሌላ በኩል ተጠሪዎች በመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤት ተቀጥረው ሲሰሩ የነበሩ መሆኑን ያልተካደ ሲሆን የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.1064/10 የተፈጻሚነት ወሰን በቋሚነት ተቀጥረው ለሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች ስለመሆኑ በአዋጁ በግልጽ በመደንገጉ አዋጁ ለተጠሪዎች አግባብነት የሌለው መሆኑን መረዳት እንችላለን። በመሆኑም ፍ/ቤቱ የተጠሪዎች ስንብት ህጋዊነት እና ተያይዞ የሚነሳው የካሳ ጥያቄ አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክር ላይ ውሳኔ ለመስጠት እንዲችል አግባብነት ያለው ህግ አዋጅ ቁ. 377/1996 ነው ሲል መወሰኑ ከመዝገቡ ለመረዳት ይቻላል።

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 መሰረት ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ ተደንግጓል። ከዚህ አንጻር ተጠሪዎች ጉዳያቸው በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሰረት የዳኝነት ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት በአዋጁ በተዘረጋው መንገድ ፍትህ የማግኘት መብታቸው ለማረጋገጥ እንዳይችሉ አዋጁ ለቋሚ ሰራተኞች ብቻ የሚመለከት በመሆኑ ሊስተናገዱ ባለመቻላቸውና የተጠሪዎች ጉዳይ የሚመለከት ልዩ ህግ የሌለ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የስር ፍ/ቤት የተጠሪዎች ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ይሸፈናል ሲል ወስኗል።

ይሁን እንጂ የተጠሪዎች ክስ ይዘት ስንብቱ ህገ ወጥ በመሆኑ ወደ ስራችን ልንመለስ ይገባል ወይም ወደ ስራችን ለመመለስ የማይቻል ከሆነ ደግሞ በህጉ መሰረት የሚገባን ካሳ ሊከፈለን ይገባል የሚል በመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/1996 ከቀን ሰራተኞች የስራ ሁኔታ አንጻር ተፈጻሚነቱ ማብራራት ያስፈልጋል። በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አንቀጽ 9 እና 10 መሰረት አዋጁ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን አንድ ሰራተኛ የሚቀጠርበት ሁኔታ፣ በቅጥር ወቅት ስላለው መብቶች እና ከስንብት ጋር ተያይዞ የአሰሪውና የሰራተኛው መብቶችና ግዴታዎች በዝርዝር ተደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ ለሰራተኞች የተለያዩ የእረፍት ቀናት፣ የስራ ላይ ጉዳት ሲደርስ የህክምና የማግኘት፣ የጉዳት ካሳ የማግኘት መብቶች፣ የጡረታ መብት እና ሌሎች ሰፋ ያሉ የህግ ጥበቃዎች ያደርጋል።

ከላይ በአዋጁ የተቀመጡት መብቶችና ግዴታዎች በተለይ ረዥም ጊዜ ከአሰሪው ጋር ለመቆየት የሚያስችል የስራ ግንኙነት ላላቸው ሰራተኞች ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ታስቦ የወጣ ህግ መሆኑን ከተዘረዘሩት መብቶችና ግዴታዎች ይዘት አንጻር እንረዳለን፡፡ በሌላ በኩል የቀን ሰራተኞች በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ አንቀጽ 2/2/ሀ/ የቀን ሂሳብ እየተከፈላቸው ዕለታዊ የሆነ ስራ ለመስራት የሚቀጠሩ መሆናቸው የተገለጸ ስለሆነ በአዋጁ የተዘረዘሩት መብቶችና ግዴታዎች በቀን ሰራተኞቹ ላይ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስቸግር መሆኑን ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሊያሳኩት ከታሰበው አላማ አንጻር በመንግስት በየጊዜው በጀት የሚመደብላቸውና በጀቱ ለታለመለት አላማ ስለማዋላቸው ቁጥጥር የሚደረግባቸው ናቸው፡፡ ህግ አውጪውም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሊያሳኩት ከታሰበው አላማ ጋር አብሮ የሚሄድ ልዩ የአሰሪና ሰራተኛ ህግ እንደሚያስፈልጋቸው በማመን የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ማውጣቱ ከአዋጁ መግቢያ ለመረዳት እንችላለን፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለሚቀጥሯቸው ጊዜያዊ ሰራተኞችም የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 1064/10 አንቀጽ 21/3/ የጊዜያዊ ሰራተኞች አቀጣጠር፣የሚኖራቸው መብትና ግዴታዎች እንዲሁም ስለሚጠበቁላቸው የስራ ሁኔታዎች አስመልክቶ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንዲያወጣ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የጊዜያዊ ሰራተኞች ደንብ አውጥቶ በስራ ላይ አውሏል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅም በአንቀጽ 3/2/ሠ/ መሰረት በልዩ ህግ ለሚተዳደሩ የመንግስት አስተዳደር ሰራተኞች ተፈጻሚ እንደማይሆን ተደንግጓል፡፡

ከላይ ባስቀመጥናቸው ምክንያቶች በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚቀጠሩ ሰራተኞች የሚተዳደሩበት ልዩ ህግ እንደሚያስፈልግ በህግ አውጪው የታመነበት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የቀን ሰራተኞች ቅጥር በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ከሚቀጠሩ የመንግስት ሰራተኞች አንጻር ልዩ የቅጥር አላማ ያለውና የሚኖራቸው መብቶችና ግዴታዎችም የተለየ በመሆኑ ሰራተኞቹ የሚተዳደሩበት ልዩ ህግ እንደሚያስፈልግ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በመንግስት መስሪያ ቤት የተቀጠሩ የቀን ሰራተኞች በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/1996 ጉዳያቸው ሊታይ ይገባል ማለቱ በህገ መንግስቱ በተሰጠው የህግ መተርጎም ስራ የሚወድቅ ተግባር ባለመሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 79/3/ ጋር ይቃረናል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠሪዎች በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸው ፍትህ የማግኘት መብት እንዲረጋገጥ ህግ አውጪው በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተጠሪዎች የአቀጣጠር ሁኔታና ሊኖራቸው ስለሚገባ መብቶችና ግዴታዎች የሚመለከት ህግ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 55/1/ እና 55/3/ መሰረት በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንደአስፈላጊነቱ ማውጣት ይጠበቅበታል። ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች የስር ፍ/ቤት አዋጅ ቁ. 377/1996 ለተጠሪዎች ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት መወሰኑ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 55/1/፣55/3/ እና 79/3/ ጋር ስለሚቃረን ውሳኔው የህገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ ለመጨረሻ ውሳኔ ማቅረቡን መረዳት ተችሏል።

በመሆኑም ከሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ፌ.ጠ.ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የተሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 79(3) ስለሚቃረን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል።

## ትእዛዝ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጀምሮ ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ስለሚቃረን ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ የሰጠ ስለሆነ ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እንዳይታይ ለስር ፍርድ ቤቶች መመሪያ እንዲሰጥ የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው።
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት።
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ.ቁ. 81/12

አመልካች፡- የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ እርገጤ መድበው ጆፊ (22 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ የጡረታ መብት ተጠቃሚነትን የተመለከተ ጥያቄ ሲሆን የተጀመረውም 1ኛ ተጠሪ በሆኑት አቶ እርገጤ መድበው የሰው ለሰው መረዳጃ ዕድር ም/ሊቀመንበር የዕድሩን አባላት በመወከል ለአመልካች ባቀረቡት ጥያቄ መነሻነት ነው፡፡

ተጠሪዎች ለአመልካች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ቀደም ሲል በመንግስት ሰራተኛነት ተቀጥረው ከ10 ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ በፅኑ እስራት ምክንያት አገልግሎታቸውን ያቋረጡ በመሆኑ አሁን የጡረታ መብታቸው እንዲከበር ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የካቲት 9 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቀደም ሲል በፅሑፍ እና በቃል ምላሽ የሰጠ መሆኑን በማስታወስ በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀፅ 27 እና በመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀፅ 63 ተራ ቁ 3 መሰረት አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የሚወሰንላቸው የአንድ ጊዜ የዳረጎት አበል ወይም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ወይም የዘለቄታ ጡረታ አበል የለም ሲል ወስኗል፡፡

በውሳኔው ላይ ይግባኝ የቀረበለት የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ከላይ በተጠቀሱት የጡረታ ባለመብት በሆኑት 1ኛ ተጠሪ አማካኝነት በተከፈተ ማህደር የቀድሞ የመንግስት ሰራተኛ የነበሩ በመንግስት ለውጥ አብዛኛዎቻችን ከአስር ዓመት በላይና እስከሞት ተፈርዶብን የነበረ ለእያንዳንዳችን የዕድሜ ልክ ጡረታ ተፈቅዶልን የምንኖር ሲሆን ከማረሚያ ቤት ከወጡ አባሎቻችን የተወሰኑት የዘለቄታ የጡረታ መብት አጥተው የሞት ጥላ ያጠላባቸውና ለልመና

ጎዳና የወጡ አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች አሉን፤ በአዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀፅ 5(2) መሰረት ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ ዕድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል በሚል ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን ኤጀንሲው አዋጁ ከ20 ዓመት በላይ ያገለገሉትን ብቻ የሚመለከት ነው በሚል መወሰኑ ተገቢ እንዳልሆነና ብዛታቸው ከ150-200 የሚሆኑ ከ18-19 ዓመት አገልግሎት ያላቸው ጭምር ያሉበት ቢያንስ 10 ዓመት አገልግሎት ያላቸው አባላት የዘለቄታ ጡረታ መብት እንዲከበርልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ከ20 ዓመት በታች አገልግሎት ያላቸው ሰዎች መብታቸው የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ቢሆንም በአዋጅ ቁ 907/2007 መሰረት የሚወሰንላቸው አበል የለም በማለት የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

በይግባኝ ሰሚው ጉባኤ በተሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስቀርቦ አመልካችም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ለውሳኔያቸው መሰረት ያደረጉት መሰረታዊ ነጥብ የተጠሪዎች አገልግሎት ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ የጡረታ አበል ይገባቸዋል አይገባቸውም? የሚለውን ከአዋጅ ቁ 907/2007 አንቀፅ 5(2) አንፃር ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በምርመራውም አመልካች ለችሎቱ ባቀረበው መልስ በአዋጅ ቁጥር 209/55፣ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 5/67 እና አዋጅ ቁጥር 714/2003 ላይ የተደነገገውን ከ20 ዓመት በላይ አገልግሎት እያነሳ የተከራከረ መሆኑን በመጥቀስ በእነዚህ አዋጆች ላይ የተደነገገው እና የአሁኑ ተጠሪዎች ስለመብታቸው የሚከራከሩበት የአገልግሎት ዘመን በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 መተካቱን ገልጸዋል፡፡ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5/2 ላይ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሠራተኛ ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 18 /1/ በተደነገገው መሠረት የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልክ ይከፈለዋል ሲል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት ቢያንስ አስር ዓመት ማገልገል ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 18/1/ መሠረት



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጡረታ እድሜ መድረስ ነው። የአመልካቾች እድሜ ከ60 ዓመት በላይ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ አልተገኘም። አመልካች ሲከራከር የነበረው አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ ጡረታ አበል አይገባቸውም በማለት ነው። ይህ ክርክር ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19/2/ ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ሲሆን ይህ ደግሞ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 5/2/ የተተካ በመሆኑ የአመልካች የ20 ዓመት አገልግሎት ክርክር ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም። ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 63/3/ ድንጋጌም ቢሆን አዋጁን ሊጻረር አይችልም። ምክንያቱም መመሪያው አዋጁን ማስፈጸሚያ እንጂ በአዋጁ የተደነገገውን ድንጋጌ ሊቃረን የሚችልበት የህግ አግባብ የለም።

ሌላው የአመልካች ክርክር የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 5/2/ አዋጁ በሚወጣበት ጊዜ በሥራ ላይ ያሉትንና ከአዋጁ በኋላ የጡረታ እድሜያቸው ሲደርስ ጡረታ የሚወጡን የመንግስት ሰራተኞችን የሚመለከት ነው የሚል ነው። ይህ ክርክር የማሻሻያ አዋጁን አንቀጽ 5/2/ 'ን' መሠረት ያደረገ አይደለም። የአሁኑ አመልካቾች የዘለቄታ የጡረታ አበል እየጠየቁ ያሉት በገዛ ፈቃዳቸው ሥራ ለቀው ሳይሆን ታስረው በመቆየታቸውና እድሜያቸው ለጡረታ የደረሰ በመሆኑ ነው። ይህም ከተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 11/9 አንጻር ሲታይ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል በማለት ተጠሪ የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከፀናበት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ የጡረታ አበል ክፍያ ለአመልካቾች እንዲከፍላቸው ሲል ወስኗል።

ከላይ ፀንቶ ባለው ውሳኔ ላይ የአመልካች ቅሬታ ፍሬ ሃሳብ ሁሉም ተጠሪዎች ከስር ጀምሮ አልተከራከሩም፣ የተጠሪዎች አገልግሎት ከ10-19 ዓመት በመሆኑ በመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ 714/2003 (በአዋጅ ቁ 907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀፅ 59(9) መሰረት የዘለቄታ የጡረታ አበል ለማግኘት አይችሉም፣ በዚህ ማሻሻያ ተጠቃሚ የሆኑት የዘለቄታ የጡረታ አበል በመጠቀም ላይ እያሉ በጽኑ እስራት ምክንያት የጡረታ አበላቸው ተቋርጦባቸው ለነበሩና ከመታሰራቸው በፊት 20 ዓመትና በላይ አገልግሎት የነበራቸውን የሚመለከት ሆኖ ሳለ ይህን ግልጽ አዋጅ በመተው ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሠጠው ውሳኔ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 79(3) ይቃረናል የሚል ነው።

የአመልካች አቤቱታ ከህገ መንግስቱና ከፍ/ቤቱ ውሳኔ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል። በጽኑ እስራት ምክንያት የጡረታ አበል የተቋረጠባቸው ወይም ደግሞ የጡረታ አበል ሳይወሰን አገልግሎታቸው 20 ዓመትና ከዛ በላይ አገልግሎት የሠጡ፣ በፅኑ እስራት ምክንያት አገልግሎታቸው ውድቅ የተደረገባቸው የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 907/2007 አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የጡረታ አበል የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ደንግጓል።

በአዋጅ ቁጥር 714/2003 ላይ አንድ የመንግስት ሰራተኛ ከ20 አመት ያላነሰ 25 አመት ያልሞላ አገልግሎት ፈጽሞ በራሱ ፈቃድ ወይም ደግሞ በተለያየ ምክንያት አገልግሎቱን ካቋረጠ፣ እድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አበል ተጠቃሚ ይሆናል የሚል ነበር። ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 907/2007 የተሻሻለ ሲሆን አዋጁ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በመንግስት ስራ ላይ ያሉና አዋጁ ከፀና በኋላ ከመንግስት ስራ ለሚለቁ ሰራተኞች አገልግሎቱ 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነና እድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አበል ይወሰንለታል በሚል ተሻሽሏል። ነገር ግን ይህ ማሻሻያ ወደ ኋላ እንዳይሄድ ተደርጎ አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በመንግስት ስራ ላይ የነበረ ሰራተኛ ስራውን የሚለቅ ከሆነ የጡረታ እድሜው ሲደርስ የዘለቄታ የጡረታ አበል ያገኛል በሚል ተደንግጓል። አዋጁ ላይ እንደተጠቀሰው ቀደም ሲል በነበሩ አዋጆችና መመሪያዎች መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል ይላል። የተጠሪዎች ጉዳይም በዚሁ መሰረት መታየት አለበት።

ጉባኤው አመልካች ጉዳዩን ቀርቦ እንዲያስረዳ ባዘዘው መሰረት የኤጀንሲው ተወካዮች ቀርበው ስለሁኔታው አስረድተዋል። በዚህም መሰረት *"ጉዳዩ በዚህ መልኩ ተፈጻሚ ከሆነ በትክክል የፖሊሲ መናጋትን እንደሚያመጣ፣ በተሻሻለው ድንጋጌ መሰረት ድሮ በጽኑ እስራት ታስሩ ተብሎ መከልከል ጥሩ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ሁሉንም እንቀበል ብንል የጡረታ መዋጮው ውስጥ ልንሸከመው የማንችለው ችግር ይፈጠራል። በአዋጁ መሰረት ከ2007 ሐምሌ በኋላ ያሉትን መንግስት ዘላቂ የጡረታ አበል መክፈል እንደሚችል ታስቦ የወጣ አዋጅ ነው። የአዋጁ ድንጋጌ ሕግ ብቻ ሳይሆን ፖሊሲም ነው፣ ውሳኔው የተወሰነው ህግን መሰረት አድርጎ አይደለም፣ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሳኔ ህግንና ህገ መንግስትን ጥሷል"* በማለት ለጉባዔው አስረድተዋል።

ማሻሻያ አዋጁ ስራ ላይ የሚውለው አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ነው። የ10 አመት አገልግሎት የተሰጠው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሚሆነው ሰራተኛ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በራሱ ምክንያት ወይም ደግሞ በሌላ ምክንያት ስራን ለሚለቅ ሰራተኛ ነው ። ይህ ድንጋጌ ስራ መልቀቅን አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ እንደ አንድ ግዴታ ስለሚያስቀምጥ ከዚያ በፊት የለቀቀን ሰራተኛ አያካትትም ።

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ስራ የለቀቁት አዋጁ ከመታወጁ በፊት ነው ። ከአዋጁ መታዎጅ በፊት የለቀቀ ሠራተኛ ደግሞ ከአዋጁ የ10 ዓመት አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም

የጡረታ አበል በፖሊሲና በህግ መሰረት መመራት አለበት። በዚህ ውሳኔ መሰረት ሁሉም 10 አመት ያገለገለ ሰራተኛ አበል የሚሰጠው ከሆነ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ የሰበር ሰሚ ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ ተፈጻሚ ቢሆን የጡረታ ፈንዱ ከሚሸከመው በላይ ስለሚሆን ኤጀንሲውና መንግስትን ብሎም መላውን የጡረታ አበል ተጠቃሚዎች ችግር ውስጥ ያስገባቸዋል። ይህ የገንዘብ መጠን ደግሞ ለአገሪቱ ችግር ይፈጥራል። በዚህ መሰረት የፖሊሲ መቃወስ ያስከትላል። ስለዚህ በውሳኔው ህግ በትክክል ባለመተርጎሙ የፖሊሲ ችግር ስለሚያመጣ የህገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል።

ህገ መንግስቱ በአንቀጽ 79(3) ዳኞች ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም በማለት ደንግጓል። ግልፅ የሆነ ሕግ እያለ ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ሕግ ተላልፏል። ስለዚህ ፍርድ ቤቶች መስራት ያለባቸው በሕግ መሰረት ነው። አዋጅ ቁጥር 907/07 በግልጽ ያስቀመጠው ሰራተኛው አዋጁ ከጸደቀ በኋላ ሲለቅ ብቻ የዘለቄታ የጡረታ መብት ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ነው። የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የአዋጁን አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 የተረጎመበት መንገድ ትክክል አይደለም። ማንኛውም ሰራተኛ 10 አመት ካገለገለ የጡረታ መብት ይከበርለታል ብሎ ውሳኔ መስጠት ከአዋጁ ድንጋጌና እሳቤ ውጭ ነው። በዚህም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በትክክል ህጉን ያላከበረና ዳኞች ከህግ ውጭ አይመሩም የሚለውን የህገ መንግስት ድንጋጌ ያከበረ አይደለም ። በዚህም ውሳኔ ዳኞች በህግ መሰረት እንዲመሩ የሚያዘው የህገ መንግስት ድንጋጌ ተጥሷል። ስለዚህ የፍ/ቤቱ ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 3፣ የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት

ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአዋጅ ቁጥር 798 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 79 (3) ድንጋጌን የሚቃረን በመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አውቆ ተገቢውን እንዲፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው።
2. የፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት።
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ።

19

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣5ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሚያዚያ 22 2010 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ ብርሀኑ አሰፋ

ተጠሪ፡- የፍቼ ከተማ ቀበሌ 04 አስተዳደር

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች በፍቼ ከተማ በ860 ካ.ሜ ላይ ያረፈውን የአውራሽ አያታቸው የአቶ በድኬ ዲነግዴ የሆነውን እና አውራሻቸው እስከ ነሐሴ 23 ቀን 1983 ዓ.ም ድረስ የኖሩበትን ቤት አውራሻቸው ከሞቱ በኋላ አመልካች ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክባቸው ክስ መስረተው ጉዳዩን የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤት ያልተወረሰ መሆኑን በማረጋገጥ ተጠሪ እንዲያስረክባቸው ቢወስንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር በመወሰኑ ውሳኔውም በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባለመለወጡ ቅር በመሰኘት ጉዳዩን ለክልሉ ቅረንጫፍ የዕንባ ጠባቂ ተቋም አቅርበው ተቋሙ ጉዳዩን መርምሮ የአስተዳደር በደል እንደደረሰብኝ አረጋግጦ ቤቱን ተጠሪ ለአመልካች እንዲያስረክብ ቢወስንም የፌዴራል የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በየትኛውም የፍርድ አካል ያልተነሳ ነገር በማንሳት ወስኖብኛል፡፡

ባጠቃላይ ፍ/ቤቶችና የፌዴራል ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሕገ መንግስታዊ መብቶቼን የጣሱ በመሆኑ ትርጉም እንዲሰጠኝ ሲሉ አቤቱታ ለሕገ መንግስት

ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቅርበው ጉባኤው ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ ልኳል፡፡

አመልካች የአውራሽ አያታቸው የአቶ በድኬ ዲነግዴ ሀብት የሆነ በፍቼ ከተማ በ860 ካ.ሜ ላይ ያረፈውን ቤት ተጠሪ እንዲያስረክባቸው በግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ክስ መስርተው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ካከራከረና የምስክሮችን ቃል ካዳመጠ በኋላ አከራካሪው ቤት ያልተወረሰ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም ተጠሪ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ አመልካች የእህቴ ልጅ ሲሉ የሚጠቅሱት ግለሰብ ከአጎራባች ግለሰብ ጋር የነበራቸው አለመግባባት መፍትሄ ያገኝ ዘንድ ለሰሜን ሸዋ ዞን የከተማ ስራና ልማት ፅ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ እና ጥር 21 ቀን 1986 ዓ.ም በቁጥር 730/595/86 በተጻፈ ደብዳቤ ባገኘው ምላሽ የአከራካሪው ቤት ወራሽ እስኪታወቅ ድረስ ይዞታው እንዳለ ተከብሮ እንዲቆይ ቀበሌው /ተጠሪ/ ክትትል እንዲያደርግ መገለጹን» በመጥቀስ ይኸው አከራካሪው ቤት እስከ 1987 ዓ.ም ድረስ በአዋጅ ቁ 47/67 ያልተወረሰ የግለሰብ ቤት መሆኑን ያሳያል በማለት ቤቱን ተጠሪ ለአመልካች ያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አያስቀርብም ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ ጉዳዩ በስር ፍ/ቤት ለሶስት ጊዜ የቀረበ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች በመጀመሪያው ጊዜ የወረዳው ፍ/ቤት ስልጣኔ አይደለም በማለቱ ወደ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ሄደን የነበረ ቢሆንም ኤጀንሲው ቤቱ እንዳልተወረሰ ሲገልፅልን ወደ ፍ/ቤት ተመለስን ቢሉም የአንድን ጉዳይ ክርክር አስቀድሞ የሚቀርብበትን አካል በመለየት ክስ መመስረት የተከራካሪ ወገኖች ግዴታ ሆኖ ፍ/ቤቱ ስልጣን አለው ቢባል እንኳ በመ.ቁ 06441 የተከፈተውን ፋይል የወረዳው ፍ/ቤት ሲዘጋው በይግባኝ ማሻር ሲገባቸው ይህ ሳይሆን ሌላ ክስ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ተቀባይነት ሊኖረው

እንደማይችል በመጥቀስ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በውሳኔው ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል ወስኗል፡፡

የሕገ መንግስት ጥሰት ተፈፅሟል በማለት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የፍርድ ቤቶች ውሳኔን ከሕገ መነግስቱ ድንጋጌዎች ጋር አጣምሮ መርምሯል በዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች ቀደም ሲል በመጀመሪያ በመዝገብ ቁጥር 83/96 ያቀረቡትን ክስ የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ስልጣን የለኝም በማለት ሲዘጋው ወደ ፕራይቭታይዜሽን ኤጀንሲ ሄደው ጉዳያቸው በመደበኛ ፍ/ቤት የሚታይ መሆኑ ተገልጾላቸው ለሁለተኛ ጊዜ በመዝገብ ቁጥር 06441 አዲስ ክስ በተጠቃሹ ወረዳ ማቅረባቸውንና ይኸውም ክስ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ ነው በሚል ፋይሉን መዘጋቱን በመጥቀስ ፍ/ቤቱ አመልካች ክርክራቸውን በመጀመሪያ ማቅረብ ያለባቸውን አካል ለይተው ማቅረብ ይገባቸው ነበር በማለት በተጨማሪም ለሁለተኛ ጊዜ ክስ አቅርበው ክሱ በፍ/ቤቱ ሲዘጋ ይህንኑ በይግባኝ ማሳረም ሲገባቸው ለሦስተኛ ጊዜ አሁን ለተያዘው ጉዳይ መነሻ የሆነውን ክስ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ተቀባይነት የለውም በሚል መወሰኑን እና ውሳኔውም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ መፅናቱን ጉባዔው ተረድቶ ጉዳዩን በጥልቀት ከመረመረ በኋላ ውሳኔው ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37(1) የተከበረውን ፍትሕ የማግኘት መብት ይቃረናል በማለት ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ሲል ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የላከ መሆኑን ከቀረበው ሰነድ መረዳት ተችሏል፡፡

የሕገ መንግስት ትርጉማና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የፍ/ቤቶችን ውሳኔ፣ የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ እና የኢፌዴሪ ሕገ መንግስትን በማጣመር መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም አመልካች በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳያቸውን በመጀመሪያ ለመደበኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ስልጣን የለኝም ሲል በመወሰኑ ጉዳያቸውን ወደ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ወስደው ኤጀንሲው ጉዳያቸውን ሊመለከት የማይችል ስለመሆኑ የተገለፀላቸው መሆኑን ጠቅሰው በድጋሚ ለመደበኛ ፍ/ቤት ጉዳያቸውን ቢያቀርቡም ጉዳዩ የቀረበለት መደበኛ ፍ/ቤት ቀደም ሲል በተሳሳተ መነሻ የሰጠውን ውሳኔ በማስታወስ ጉዳዩ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ ነው በማለት የቀረበለትን ክስ ውድቅ በማድረግ የወሰነ መሆኑን፤አመልካችም ለሦስተኛ ጊዜ ያቀረቡትን ክስ ፍ/ቤቶች ሲመለከቱ ቆይተው በመጨረሻ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል ለሁለተኛ ጊዜ በቀረበው ክስ ላይ በተሳሳተ መነሻ ላይ ተመስርቶ የተሰጠን ውሳኔ መሰረት በማድረግ አመልካች ውሳኔውን በይግባኝ አላሳረመም በሚል ምክንያት ብቻ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ያሳለፈው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ መፅናቱ አመልካች በየትኛውም አካል ጉዳያቸውን አቅርበው ማስወሰን የከለከላቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም የፍ/ቤቶች ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 (1) ላይ ማነኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን ሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው በሚል የተደነገገውን የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብት የሚጥስ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. አመልካች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37/1 መሰረት ፍትህ የማግኘት መብት እንዲከበርላቸው ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ማየት ያለበት ፕራይቨትአይዜሽን ኤጀንሲ እንደሆነ እና በዚያው በኩል እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ፕራይቨትአይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ እንዲከራከርና የመሰላችሁን ውሳኔ እንድትሰጡ ይደረግ፡፡ የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት እና የሆሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ም/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ እንዲያውቁትና እንዲያስፈጽሙ ይድረሳቸው፡፡
2. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የላኩት የውሳኔ ሀሳብ በም/ቤቱ በሰጠው የሕገ መንግስት ትርጉም ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካች ይድረሳቸው፡፡

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣3ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሚያዚያ 22 2010 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ ብርሃኑ በላይ ዲነግዲ

ተጠሪ፡- የቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 አስተዳደር ጽ/ቤት

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

## ውሳኔ

የጉዳዩ መነሻ አመልካች በቀን 24/09/2008 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ባቀረቡት አቤቱታ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት የአመልካች አውራሽ ብቸኛ ንብረት እና በአዋጅ ቁ 47/67 ያልተወረሰ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ እንዲሁም ጉዳዩ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ቤቱ በመመሪያ፣ በቀላጤና በቃል ትዕዛዝ ያልተወሰደ በመሆኑ ከኤጀንሲው ስልጣን ውጪ ነው ተብሎ የተወሰነ ሆኖ ሳለ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ቤቶች እንዲመለስልኝ የሰጡትን ፍርድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መመለስ የለበትም በማለት በመዝገብ ቁጥር 107520 ላይ የሰጠው ፍርድ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 እና 40 ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው።

ይህ ጉዳይ የተጀመረው የአሁን አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ ሲሆን የክሱ ይዘት እንደሚያስረዳው የኑዛዜ አውራሼ ወ/ሮ አስካለ ጎሹ በቦሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 5 የሚገኘው 1000 ካሬ ሜትር ቦታ ባለቤት መሆናቸው ተረጋግጦ በ1964 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የካርታ ቁጥር 32087 ተሰጥቷቸው በዚሁ ቦታ ላይ ሰርቪስ ቤት ሰርተው

ዘመዳቸው እንዲጠብቁላቸው አድርገው በ1966 ዓ.ም ከሐገር ወጥተው ለ17 ዓመታት ሲኖሩ ይህ ብቸኛ ቤታቸው አልተወረሰም፡፡

የቤት ቁጥር ለውጥ ሲደረግ ቤቱ 188 እና 189 ተብሎ ተሰጥቷል፡ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ባለመወረሱ ወ/ሮ አስካለ ጎሹ ይህን ይዞታና ቤት በ25/11/1997 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ከሰጡኝ በኂላ በ10/7/2003 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆን ተከሳሾች 1ኛ በቦሌ ክ/ከተማ የወረዳ 5 አስተዳደር ጽ/ቤት፣ 2ኛወ/ሮ ቀነኒ ቀዲዳ፣3ኛ ወ/ሮ ብዙነሽ አባሳ ቤቱን እንዲለቁልኝ ብጠይቅም ፈቃደኛ ስላልሆኑ በፍ/ቤት ተገደው እንዲለቁልኝ በማለት ክስ መስርተዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት ተከሳሾች መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቶ 1ኛ፣ 2ኛና 3ኛ ተከሳሾች መልስ ሰጥተዋል::

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር እና የሰው ምስክር ከሰማ በኂላ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት አመልካች ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በፊት ገዝተው የይዞታ ማርጋገጫ ካርታ አውጥተው ዘመደቻቸውን ቤት ውስጥ በማስቀመጥ ወደ ጅቡቲ ሄደው ይኖሩ እንደነበር ቤቱ በአዋጅ ለመወረሱ የቀረበ ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ በ1984 ዓ.ም ከአመልካች ዘመዶች ጋር የነበሩት አቶ ገመቹ ቤቱን አለቅም በማለታቸው ከቀበሌው ጋር ክርክር እንደተጀመረ በማስረጃ በመረጋገጡ፣ በአጠቃላይ ከሳሽ ባቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ ለክሱ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ከተከሳሾች የተሻለ መብት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ተከሳሾች ቤቱን ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለይግባኙ ምክንያት የሆነውን የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ መርምሮ ጉድለት የሌለበት ነው በማለት መልስ ሰጪን (የአሁኑ አመልካችን) መጥራት ሳያስፈልግ ይግባኙን የዘጋ ሲሆን ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ

ለረጅም ዓመታት በመንግሥት እጅ የቆየ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 አልተወረሰም ይመለስልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄን የማየት ስልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በመሆኑ ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የላቸውም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በአስተዳደራዊ መልኩ በፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ኤጀንሲ እንዲሁም በፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔዎች ከተጠቀሱት የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

አመልካች ጉዳያቸውን ለመዳኘት በሕግ ሥልጣን አለው ለተባለው ለኤጀንሲው አቅርበው ኤጀንሲው ማየት የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀጽ 2(3) ስር በተደነገገው መሠረት የተወረሱ ቤቶችን ብቻ መሆኑን በመግለጽ የአመልካችን ጉዳይ አላይም ማለቱን ጉባዔው ከቀረበው ማስረጃ ተረድቷል፡፡

የቀረበው ጉዳይ የኤጀንሲው ስልጣን ካልሆነ አመልካች ጉዳዩን ለማየት በሕግ ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ፍርድ ወይም ውሳኔ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት አላቸው በማለት ጉዳዩን ለፍ/ቤቶች ቢያቀርቡም ሰበር ችሎቱ ስልጣኑ የኤጀንሲው ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር መዝጋቱ አመልካች ጉዳያቸውን የሚያቀርቡበት እና ፍርድ ወይም ውሳኔ የሚያገኙበት ዕድል ካልተፈጠረ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 ጋር ስለሚቃረን አቤቱታው የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

የሕገ መንግስት ትርጉማና የማንነት ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ የፍ/ቤቶችን ውሳኔ፣ የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ እና የኢፊዴሪ ሕገ መንግስትን በማጣመር መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አጣሪ ጉባዔው ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(1) ጋር አገናዝቦ በመመርመር አመልካች ጉዳያቸውን በአስተዳደራዊ መልኩ ለኤጀንሲው አቅርበው ኤጀንሲው ከስልጣኑ ውጭ በመሆኑ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የአመልካችን አቤቱታ መዝጋቱን፣ የሰበር ችሎቱ ደግሞ የቀረበውን ጉዳይ መርምሮ ይህን አይነት ጉዳይ የማየት ስልጣን የኤጀንሲው ነው በማለት ጉዳዩ በሁለቱም በኩል እንዳይታይ መደረጉ የአመልካችን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 (1) ላይ የተደነገገውን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጥስ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በአባላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

- አመልካች ፍትህ የማግኘት መብቱ እንዲከበርላቸው ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በአዋጅ 47/67 ካልተወረሰ በአዋጅ 110/87 ማየት ያለበት ኘራይቨትአይዜሽን ኤጀንሲ እንደሆነ እና በዚያው በኩል እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ቀርቦ እንዲከራከርና የመሰላችሁን ውሳኔ እንዲሰጡ ይደረግ፡፡
- ፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ም/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ እንዲያውቀውና እንዲያስፈጽም ይድረሰው፡፡
- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ የውሳኔ ሀሳቡ በም/ቤቱ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው ይድረሰው፡፡
- የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካች ይድረሳቸው፡፡

7

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ. 88/12

አመልካች፡- አቶ ጌታቸው ተድላ ኃ/ጊዮርጊስ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 07

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 8

2ኛ/ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን

አድራሻ፡ አዲስ አበባ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 20/11/2010 ዓ.ም ለጉባኤው ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ አቤቱታውም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15468 ሰኔ 25 ቀን 2010 ዓ.ም ተወስኖ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ.142430 ላይ የፀናው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ፍትህ የማግኘት መብቴን ስለሚጥስ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥልኝ የሚል አቤቱታ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ የአሁን አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ተጠሪዎች የግል ቤቴን ይዘው ስለሚገኙ ይልቀቁልኝ የሚል የክስ አቤቱታ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ እንዲሁም በየደረጃው ላሉት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት አቅርቤ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለንም በማለት ስለወሰኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 35(2) መሰረት የትኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንዳለው ለይቶ ትእዛዝ እንዲሰጥልኝ በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎችም በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው በሰጡት አስተያየት አመልካች ጉዳያቸውን ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 57680 ስልጣኔ አይደለም በማለት መዝገቡን ሲዘጋው ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሳይጠይቁ

በቀጥታ ለአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ክስ ማቅረባቸው ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ በከተማው አስተዳደር ያሉት ችሎቶችም ሥልጣን የለንም ቢሉም እስከ መጨረሻው ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በመሄድ በመብታቸው አለመጠቀማቸው የራሳቸው ስህተት ነው፣ ጉዳዩን እንደገና ለፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 44662 አዲስ ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮና ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ብይን በመስጠት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይህ ብይንም በይግባኝ አልተሻረም፡፡ ስለዚህ አመልካች በተለያየ ጊዜ ያጡትን መብት ይግባኝ ጠይቀው ሳያሽሩ በሥልጣን ይለይልኝ ሰበብ እንደገና አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢነት ስለሌለው የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጠቅላይ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 35 (2) ድንጋጌ ሥር እንደተመለከተው አንድ ጉዳይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ፍ/ቤቶች ሥልጣናችን አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በአሁኑ ጉዳይ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ሁሉም ፍ/ቤቶች ስልጣን የለንም በማለታቸው ሳይሆን ለአንድ ፍ/ቤት ጉዳያቸውን ሁለት ጊዜ በማቅረባቸው እና በጉዳዩ ላይ መብት እና ጥቅም ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የላቸውም ተብሎ በተሰጠ ብይን በመሆኑና በየጊዜው ፍ/ቤቶች በሰጧቸው ብይኖች ላይ ይግባኝ በመጠየቅ መብታቸውን እስከ መጨረሻ አሟጠው መጠቀም ሲገባቸው ይህንን ሳያደርጉ በመቅረታቸው ያጡትን መብት በስልጣን ይለይልኝ ሰበብ ለማግኘት ያቀረቡት አቤቱታ በመሆኑ ጉዳዩ በስልጣን ይለይልኝ ስር የሚሸፈን አይደለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

በአመልካች ቅሬታ አቅራቢነት ጉዳዩን በሰበር ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ የአመልካች ክርክርና ማስረጃ ታይቶ መብት እንዳላቸው አላሳዩም ተብሎ ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን የተሰጠበት ስለመሆኑ ፍሬ ጉዳይን በተመለከተው ፍ/ቤት በተረጋገጠበት እና የስር ፍ/ቤት ባሳለፈው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለም በይግባኝ ማሳየት ሲቻል አመልካች በሕግ የተዘረጋውን ሥርዓት በመተው ስልጣን ያለው ፍ/ቤት ይለይልኝ በማለት አቤቱታ ማቅረባቸው የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 35(2) ድንጋጌን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም በማለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

አመልካችም የሰበሩ ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ መብቴን ይጥሳል በማለት ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 08 በቀድሞ አጠራር ወረዳ 5 ቀበሌ 12 በአንድ ግድግዳና ጣራ ሥር በአራት ክፍሎች ተከፋፍሎ በቁጥር 1387፣ 1388፣1389 እና 1390 የሚታወቀውን አከራካሪውን ቤት በቀን 22/10/1968 በተፃፈ ቅፅ 004 እና በቁጥር 892/ቀ/12/68 ቀን 04/01/1969 ዓ.ም በተፃፈው ደብዳቤ የግል ንብረቴ መሆኑ ተረጋግጦ የቦታ ኪራይና የቤት ግብር እንዲከፍሉበት ተፈቅዶልኝ ነበር። አመልካችም በዚህ ንብረት ላይ ያለኝን መብት ለማስከበር በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እና በየደረጃው ላሉት ፍ/ቤቶች አቅርቤ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት መልሶብኛል።

በዚህ ምክንያት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የትኛው ፍ/ቤት ስልጣን እንዳለው እንዲለይልኝ አቤቱታ ባቀርብለትም ፍ/ቤቱ ግን ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ብሎ የወሰነውን ጉዳይ በድጋሚ ለዛው ፍ/ቤት ማቅረብ መብትና ጥቅም እንዳለኝ ተረጋግጧል በማለት ክርክሩን በይግባኝ መቀጠሉ ውጤት እንደማይኖረው በግልፅ እያወቀ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱ አመልካች በይግባኝ መብት ሳይጠቀሙ የቀሩትን ጉዳይ በፍ/ቤት ሥልጣን ሰበብ ለማግኘት መሞከር የሕግ አግባብነት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 እና 40 የተደነገገውን የአመልካችን ፍትህ የማግኘት እና የንብረት መብትን የሚጥስ በመሆኑ ለጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ተሰጥቶ አከራካሪው ንብረት ላይ ተከራክሬ ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብቴ እንዲከበርልኝ በማለት አመልክተዋል።

የጉዳዩ ፍሬ ሀሳብ እና የአመልካች ቅሬታ ከላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍ/ቤቱ ውሳኔ በጉባኤው ተመርምሯል። እንደተመረመረውም:-

1ኛ አመልካች ተጠሪዎች ከሕግ ውጪ ቤቱን ይዘው እየተጠቀሙ ስለሆነ ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቅርበው ኤጀንሲውም በቀን 09/08/1999 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ‹‹አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት የመኖሪያ ቤት የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን ለመውረስ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 ውጭ በመመሪያ በቀላጤ የተወሰዱ ወይም በአዋጅ አስፈፃሚ አካል ስለመፈቀዱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመቅረቡ የኤጀንሲው ሥልጣን አይደለም›› በማለት መመለሱን፣

2ኛ/ አመልካች ጉዳዩን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በመዝገብ ቁጥር 57680 በቀን 20/10/1999 ዓ.ም ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም፣ ስልጣን ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ነው በማለት ክሱን በመጀመሪያ ተቃውሞ ውድቅ ማድረጋቸው፣



* የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን *

3ኛ አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አቅርበው ፍ/ቤቱም በመዝገብ ቁጥር 06179 በቀን 29/02/2009 ዓ.ም አመልካች ያቀረቡት ክስ የባለቤትነት ጥያቄ ስለሆነ ይህ ፍ/ቤት አከራክሮ ጉዳዩን ለመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ክሱን መሰረዙን፣

4ኛ አመልካች የአሁን ተጠሪዎች እና ሌሎች 12 ሰዎች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በድጋሚ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካች አስቀድሞ በጉዳዩ ላይ በዚህ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 57680 ላይ ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም በማለት የተወሰነ ውሳኔ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ ቁ. 5 መሰረት የአመልካችን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ አመልካች አከራካሪው ንብረት ላይ መብት እና ጥቅም የለውም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 33 ንኡስ ቁጥር 2 መሰረት ሌላ አማራጭ ውሳኔ በመስጠት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎ መወሰኑን መዝገቡ ያስረዳል።

በዚህ ምክንያት አመልካች የክስ አቤቱታ ያቀረቡላቸው ሁሉም የዳኝነት አካላት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለንም በማለት ክሳቸውን ስላልተቀበሉት አመልካች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የትኛው ፍ/ቤት ስልጣን እንዳለው ለይቶ እንዲወስንላቸው አቤቱታቸውን አቅርበዋል። የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ፣ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስልጣን የለኝም ሳይሆን አመልካች አከራካሪው ቤት ላይ መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት ስለወሰነ ይህ የፍ/ቤት ስልጣን የሚለይበት ጉዳይ አይደለም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል።

ከፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ መረዳት እንደሚቻለው ፍ/ቤቱ ሁለት ጭብጦች ላይ ውሳኔ በመስጠት የአመልካችን ክስ ውድቅ እንዳደረገው ያመለክታል። የመጀመሪያው ጭብጥ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚል ሲሆን ሁለተኛው ጭብጥ ደግሞ አመልካች አከራካሪው ንብረት ላይ መብት እና ጥቅም አለው? ወይስ የለውም? የሚሉ ናቸው።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ፣ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ እንደሚያሳየው አመልካች አሁን ያቀረቡት ጉዳይ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ሁኔታ ለዚህ ፍ/ቤት አቅርበው ይህ ፍ/ቤትም ስልጣን የለኝም በማለት የዘጋው ጉዳይ ነው። አመልካች ከዚህ በፊት ስልጣን የለኝም በማለት የተወሰነውን ጉዳይ በድጋሚ ያቀረቡ ስለሆነ የአመልካች ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 5 መሰረት ውድቅ አድርገናል በማለት ወስኗል። ይህም በሌላ አረዳድ ፍ/ቤቱ አመልካች ከዚህ በፊት ጉዳዩን ለዚህ ፍ/ቤት



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

አቅርበው የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቷል በማለት የወሰነው ቀድሞ ፍ/ቤቱ ስልጣን የለኝም በማለት የወሰነውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ለሁለተኛ ጊዜ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የወሰነ መሆኑን ያሳያል።

አመልካች አከራካሪው ንብረት ላይ መብት እና ጥቅም አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ፣ የክስ አቤቱታው ለ2ኛ ጊዜ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን የለኝም ካለ በኋላ እንደገና አመልካች ንብረቱ ላይ መብት እና ጥቅም አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ንብረቱ ላይ መብት እና ጥቅም የለውም በማለት በዋናው የፍሬ ነገር ላይ የዳኝነት ውሳኔ እንደሰጠ ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል።

ይህ ደግሞ አንድ የዳኝነት አካል ጉዳዩን ለማየት በህግ ስልጣን አልተሰጠኝም የሚል ከሆነ ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን እንደሌለው ጠቅሶ መዝገቡን መዝጋት ሲገባው እንደገና በአንድ በኩል ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን የለኝም እያለ በሌላ በኩል ደግሞ ስልጣን እንዳለው አድርጎ የጉዳዩ ፍሬ ነገር ውስጥ በመግባት የመጨረሻ የዳኝነት ውሳኔ መስጠቱ ህጋዊ እና ተገቢ ባለመሆኑ እንዲሁም የመጀመሪያው የውሳኔ ክፍል እና የሁለተኛው ውሳኔ ክፍል እርስ በርስ የሚጣረስ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የወሰነው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተግባራዊ ይሆናል ማለት ነው። ከዚህ ውሳኔ እና ከአጠቃላይ መዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች የክስ አቤቱታውን ያቀረቡላቸው ሁሉም የዳኝነት አካላት ማለትም የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት እና ለ2ኛ ጊዜ ክሱ የቀረበለት የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የአመልካችን ክስ እንደመለሱት ያመላክታል።

በሌላ በኩል እንዲህ አይነት ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 35(2) ስር እንደተደነገገው ‹‹አንድ ጉዳይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የክልል ወይም የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ነው ብለው የያዙት ወይም ሥልጣናችን አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የትኛው ፍ/ቤት ስልጣን እንዳለው በመለየት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት ይችላል›› በማለት ደንግጓል።

አመልካችም በዚህ ድንጋጌ መሰረት ክሳቸውን ያቀረቡባቸው ሁሉም የዳኝነት አካላት ስልጣን የለንም በማለት ክሱን ስላልተቀበሉት የትኛው ፍ/ቤት ስልጣን እንዳለው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

## የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 2ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም

ይግባኝ ባዮች፡ የሟች አቶ ዋሲሁን መኮንን ሚስትና ወራሾች (10 ሰዎች)

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 250/1993 ዓ.ም. በአንቀፅ 18 መሠረት የቀረበለትን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የይግባኝ አቤቱታ አመልካቾች ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም. የተፃፈ የይግባኝ ቅሬታ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ በአቤቱታቸውም ከአዋጅ ቁጥር 47/67 ድንጋጌ ውጪ የተወረሰብንን እና በአሁኑ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ፣ ቀበሌ 13/15 የቤት ቁጥር 703 የሆነው የንግድ ቤት እንዲመለስልን በአዋጅ ቁጥር 110/1987 ዓ.ም. ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አመልክተን ኤጀንሲውም የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ መልስና ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ ካዘዘ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ ቤቱ ከአዋጅ ውጪ የተወረሰ ስለሆነ ይመለስላቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በውሳኔው ላይ ይግባኝ በማቅረቡ ማመልከቻው ከቦርዱ መጥሪያ ጋር ደርሶን የክርክሩ ተከፋይ እናደርጋልን ብለን ብንጠብቅም ቦርዱ የይግባኝ ባይን አቤቱታ ብቻ መርምሮ ውሳኔ በመስጠቱ መልስ የመስጠት ሕገ መንግስታዊ መብታችን ተጥሶብናል

በማለት አቤቱታ ብናቀርብለትም ሊያስተናግደን ፍቃደኛ አልሆነም:: በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር የዳኝነት ስልጣኑ የመከራከር መብታችንን ሳይጠበቅ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ እንዲያርምልን አቤቱታ ብናቀርብም የቦርዱ ውሳኔ አስተዳደራዊ ስለሆነ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶ አሰናበተን::

ውሳኔው ሕገ መንግስታዊ የመሰማት መብታችንን የጣሰ ነው በማለት ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ ብናቀርብም ጉባኤው ጥያቄያችንን የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ሳይቀበለው ስለቀረ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ ይህን ይግባኝ ለማቅረብ ተገደናል::

ሕገ መንግስት በአንቀፅ 37(1) ሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል በሚል ታሳቢ ከሚያደርጋቸው ፍ/ቤት መሰል አካላት መካከል የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አንዱ ነው:: እነዚህ አካላት የሚሰጡትን የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ለማረም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር የዳኝነት ስልጣን ያለው በመሆኑ ኤጀንሲው ፍ/ቤት ... እንዳልሆነ በመቁጠር በተሰጠው ውሳኔ ላይ ተገቢውን የሕገ መንግስታዊ ትርጉም እንዲሰጥልን በማለት አመልክተዋል::

ለምክር ቤቱ የቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ከላይ በአጭሩ የተመለከተው ሲሆን ምክር ቤቱም የሕገ መንግስትና የክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበለት የውሳኔ ሀሳብ ላይ በስፋት ተወያይቷል:: በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በአስፈፃሚው ስር የተደራጀ አካል ቢሆንም ከጉዳዩ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቾች ጥያቄ ሲያቀርቡ ኤጀንሲው አቤቱታውን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር ll0/87 አንቀፅ 2/3/

ስልጣን ያለው ከመሆኑም በላይ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲም እንደ ፍ/ቤት መሰል አካል ይወሰዳል ከተባለ ጉዳዩ አስተዳደራዊ ነውና የማየት ስልጣን የለኝም ማለት ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37(1) ላይ የተቀመጠውን የዜጎችን በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል አቅርቦ የማስወሰን መብት የሚጋፋ ነው፡፡

በመሆኑም በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37/1/ ፍትሕ የማግኘት መብት እና በአንቀፅ 80 /3/ (ሀ) የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስልጣንን የሚመለከተው ድንጋጌ ተዛምደው በዚህ አግባብ ጉዳዩ ሊስተናገድ ስለሚገባ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በሰበር በማየት ስልጣኑ እንዲመለከተው ምክር ቤቱ በሙሉ ድምፅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በፌዴሬሽን ምክር ቤት ፅ/ቤት
የሕገ መንግሥት ትርጉምና መብቶች ዳይሬክቶሬት
The Secretariat of the House of Federation
Constitutional Interpretation and Rights Directorate

የውስጥ መፃፃፊያ
*Inter-Office memo*

ለ፡ ሕገ መንግስትና ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

ከ፡ ሕገ መንግስት ትርጉምና መብቶች ዳሬክቶሬት

ቀን፡ ታህሳስ 26 ቀን 2005 ዓ.ም.

አመልካች------ 1. ወ/ሮ ሁለመናዬ ጌታሁን
2.አቶ ኤፊሬም ዘ/ሚካኤል

ተጠሪ 1. አቶ ሠረት መኮንን
2.አቶ እርቁ ጎዳ
3,የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የውልና ክብር መዝገብ ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት

1. <u>የአቤቱታው ፍሬ ሓሳብ</u>

አመልካች በ25/10/2002 ዓ.ም በተፃፈ ለጉባኤው ያቀረቡት አቤቱታ ጊዜውን ጠብቆ በ90 ቀናት ውስጥ ባለመቅረቡ ውድቅ ተደርጎባቸው የነበረ ቢሆንም ለተከበረው ምክር ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች በይር.ጋ ሊታገዱ ስለማይገባ እንዲታይላቸው በመወሰኑ ነው ። በመሆኑም አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ሰፋ ያለ ቢሆንም በአጭሩ ሲታይ, በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03/05 የቤት ቁጥር 743 የሆነውን ቤታችን በብድር ምክንያት ለአቶ እርቁ ጎደ ለ1ኛው ተጠሪ ከቤቱ ማስረጃ ጋር ቤቱን በዋስትና እንዲይዝ በ23/12/95 ዓ.ም አስረክበነዋል። የብድሩ ገንዘብም ብር

300000/ሶስት መቶ ሺ. ብር/ሲሆን 200 /ሺ.ብሩ/ ለቀድሞ ዕዳችን - ለቀድሞ አበዳራያችን ለአቶ ገ/ኪዳን ሀይሉ አስረክበናል። ቀሪውን 100/አንድ መቶ ሺ. ብር /እና ተረክበናል። ተጠሪዎች ግን ውክልና ሳንሰጣቸው በተጭበረበረ መንገድ መኖ/ቤታችንም እግድ እያለበት ጥር 3 ቀን 96 ዓ.ም ተሻሽጠዋል፡፡

የሽያጭ ውሉ የተፈፀመው በቤቱ ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ፀንቶ ባለበት ወቅት በመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጇለኪያ ምድብ ችሎት ውሉ ሊፀና አይገባም በማለት የሰጠወን ውሳኔ, በአሁን 2ኛ ተጠሪ ስም የተሰጠው ካርታ የተሰረዘ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ, ከክፍሉ ቀበሌ የወሰደው መታወቂያ እንዲመልስ የተሰጠውን ትዕዛዝ በማያያዝ ቤቱን እንዲያስረክቡን ክስ ብመሠርትም ከአቀረብኩት አቤቱታ ውጭ ውሳኔ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠ በመሆኑ በይግባኝም ሆነ በሰበር የተመለከተው ፍ/ቤት ማጽደቁ ስህተት ነው፡፡ የመጇለኪያ ምድብ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ቀርቦ ፀንቶ እያለ ይህ ውሳኔ ሳይሻር የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሉ ሊጸና ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው።

ስለሆነም እግድ ተሰጥቶ በነበረበት ወቅት የተፈጸመው ህገወጥ ውል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሉ ሊፀና አይገባም ብሎ ወስኖ እያለና ለተጠሪ ተሰጥቶ የነበረው ካርታም ተሰርዞ እያለ ከጠየቅሁት ዳኝነት ውጭ የቤቱ ሽያጭ ገንዘብ ልትቀበሉ ይገባል ውሉ ሊጸና ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ የፍ/ህ/ቁ 1195 ን የሚቃረንና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነው።

## 2 <u>አስተያየት</u>

እኛም በአመልካች የቀረበው አቤቱታ የህገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የያዘ ነው ወይ? የሚል ነጥብ በመያዝ ጉዳዩን ተመልክተናል።መዝገቡን እንደተመለከትነው የአሁን አመልካቾች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪዎች በመያዣነት በመስጠት ገንዘብ ተበድረው የነበረ በመሆኑ ቤቱ ሊረከቡ ይገባ በነበረበት ወቅት ቤቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸውና ብሎም በሰጡት ውክልና መሰረት ቤቱ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ መሸጡን በመረዳታቸው ውክልና ያልሰጡና ፊርማቸውን አጭበርብረው ሊሆን በሚችል መልኩ ተሻሽጠው ሊሆን ስለሚችል ህጋዊ ባልሆነ ውክልና ተሸጠ የተባለው ውል እንዲፈርስላቸውና ቤቱን እንዲያስረክቡአቸው, ውሉ ሊፈርስ አይገባም ከተባለም የአሁን ተጠሪዎች የቤቱን ዋጋ በወቅቱ የገበያ ዋጋ እንዲከፍሉአቸው ,ውክልናው በትክክል ተሰጥቷል የሚባል ከሆነ ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ /ወኪሉ/ከተሸጠበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ ህጋዊ ወለድ የሽያጬን ዋጋ እንዲከፍል እንዲወሰንበት በማለት ተጠሪዎችን በፌደራሉ ከፍ/ፍ/ቤት በ1998ዓ/ም ከሰዋል።

1ኛ ተጠሪ ጉዳዩ በሌሉበት የታየ ሲሆን ሌሎች ተጠሪዎች የየበኩላቸው ክርክር አቅርበው ተከራክረዋል።የክርክራቸው ይዘትም አመልካቾች ህጋዊ ውክልና ስለመስጠታቸውና ወኪላቸውም በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት አከራካሪውን ቤት ስለመሸጡ በመግለጽ ተከራክረዋል።ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም አመልካቾች ህጋዊ ውክልና አልሰጠንም ፊርማችን ተጭበርብሯል የሚል ክርክር በማቅረባቸው ፊርማቸው በባለሞያ እንዲመረመር አዞ ውክልና ሰጡበት በተባለው የውክልና ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የአመልካቾች ነው በማለት ሙያዊ አስያየት በመስጠቱ አመልካቾች የቤት ሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሽያጭ ውሉ በህጋዊ የውክልና ስልጣን መሰረት የተሸጠ በመሆኑ

ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኖ በአመልካቾች አማራጭ ዳኝነት ጥያቄ መሰረት ቤቱ የተሸጠበት ዋጋ ብር 1700,000 አመልካቾች ከወኪላቸው/ከ1ኛ ተጠሪ/እንዲቀበሉ በማለት ወስኗል።ይህ ውሳኔም በይግባኝም ሆነ በሰበር ሰሚ ችሎት የፀና መሆኑን ተመልክተናል።አመልካቾች ቤቱ በፍ/ቤት ታግዶ እያለ ተሸጧል ይህም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጀለኪያ ምድብ ችሎት አረጋግጦ ውሉ ፍርስ ነው በማለት ወስኗል። በግዥ ውሉ መሰረት የቤቱ ካርታ ስመንብረት በገዥ ስም ተዛውሮ የነበረ ቢሆንም ተሰርዟል።ይህንን ሁሉ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ብናቀርብም ተቀባይነት አለገኘንም በማለት ቅሬታ ያቅርቡ እንጂ ክርክሩ ለፍርድ ቤት አልቀረበም ። ቀርቦም ቢሆን ማስረጃ በአግባቡ አልታየልኝም የሚለው ክርክር ህገመንግስታዊ ክርክር ሊሆን አይችልም።ከዚህም በተጨማሪ ኮሜት ትራንስፖርት የፍርድ ባለመብት, አላይደ ኢንተርናሽናል ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ሆነው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጀለኪያ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ 00871 በሆነ ሲከራከሩ የአሁን አከራካሪው ቤት ለፍርድ ማስፈጸሚያነት በሀራጅ ለመሸጥ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ስለነበረ ይህው ቤት የገዙት ግለሰብ/የአሁን 2ኛ ተጠሪ/ በሽያጭ ውል የገዛሁት በመሆኑ በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው ትዕዛዝ ይነሳልኝ የሚል አቤቱታ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ቤቱን የገዙት ታግዶ በነበረበት ወቅት በመሆኑ አቤቱታቸው ተቀባይነት የለውም ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል።

አመልካቾች በሰጡት ውክልና መሰረት ክርክር ያነሱበት ቤት ተሸጧል።ህጋዊ ውክልና ሳንሰጥ ቤታችን ስለተሸጠ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ይህ ባይሆን ደግሞ የሽያጩ ገንዘብ እንድናገኝ ይወሰንልን የሚል ክስ መስርተው ህጋዊ ውክልና ስለመስጠታቸው ተረጋግጦ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ተወስኖ የቤቱ ሽያጭ ገንዘብ እንዲያገኙ ተወስኗል።ነገር ግን የተሸጠው ቤት በፍርድ ቤት በታገደበት ወቅት ስለመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጀለኪያ ምድብ ችሎት አረጋግጦ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ወስኗል በማለት ቅሬታ ያቅርቡ እንጂ ፍርድ ቤቱ ከፍ ሲል እንዳመለከትነው በጠቀሱት መልኩ አከራክሮ ውሳኔ አልሰጠም። አመልካቾችም ቢሆኑ ለፍርድ ቤቶች የተለያየ ማስረጃ አቅርበን ሊታይልን አለመቻሉ መሰረታዊ የህግ ትርጉም ስህተት ስለሆነ በጉባኤው በኩል ይታረምልን የሚል እንጂ የጉባኤውን ስልጣን አገናዝበው የህገመንግስት ትርጉም አላቀረቡም።በአጠቃላይ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ጉባኤው የፍርድ ቤቶቹን ውሳኔ እንደይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንዲያርምላቸው የሚያመለክት እንጂ የህገመንግስት ትርጉም ጥያቄ ያላቀረቡ ከመሆኑም በላይ በውሳኔው የተጣሰ ህገመንግስታዊ ድንጋጌ ስለሌለ አቤቱታው የህገመንግስት ትርጉም አያስፈልገውም የሚል አስተያየት አቅርበናል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ 4ኛ ዓመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

<u>የመ.ቁ. 69/11</u>

አመልካች፡- ወ/ሮ ቀመርያ አህመድ (ወኪል) ነቢል አህመድ

ተጠሪ፡- አቶ በድረዲን አብዱልዋሃብ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ዝርዝርም በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ የሚገኝና የቤት ቁጥር 2399 የካርታ ቁ. መል / ም12459 በባለቤቱ አቶ ዩሱፍ ፈሲህ ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤቱን ለተጠሪ ለጊዜው እንዲኖርበት ፈቅጄለት ሰጥቼው ሲጠቀምበት ቆይቶ አሁን ቤቱን እንዲለቅልኝ ብጠይቀው ሊለቅልኝ ፍቃደኛ ስላልሆነ ለቆ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ቀርበው በሰጡት መልስ ክርክር የቀረበበት ቤት የአመልካች ነው፣ የተሰጠኝና የያዝኩት ግን ለጊዜው አይደለም፣ በ1959 ዓ.ም ተሰጥቶኝ እስከ ዛሬ ድረስ ለ47 ዓመታት የኖርኩበትና ትዳር ይዤ ፤ ልጆች ወልጄና አሳድጌ እኔም በጡረታ ላይ ሆኜ እየተጠቀምኩበት ያለ ነው፡፡ አመልካች የወላጅ እናቱ እናት ወይም አያቱ ናቸው፡፡ በ2002 ዓ.ም 100ኛ ልደት በዓላቸውን አክብረው አሁን 105 አመታቸው ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በእድሜያቸው መግፋት የተነሳ ትክክለኛ አስተሳሰብ ላይ የሚገኙ ባለመሆናቸው ምክንያት ይህን ክስ ያቀረቡ ስለሆነ አመልካች ያቀረቡት ክስ በትክክለኛ አዕምሮዋቸው ያቀረቡት ጥያቄ መሆኑ ይረጋገጥልኝና ይህ መሆኑ ከተረጋገጠ ቤቱን ለቅቄ እወጣለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ያከራከረ ሲሆን ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ አመልካች እንዲቀርቡ ባዘዘው መሰረት አመልካች ቀርበው እድሜያቸው 100 ዓመት መሆኑን ገልጸው *"ተጠሪ ጥፋት አላጠፋም ቤቱን ለቆ እንዲወጣ ስለፈለግኩኝ ነው"* ብለዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ቤቱ የአመልካች መሆኑንና ጥያቄያቸው በዕድሜ ምክንያት ያልመጣና በትክክለኛ አዕምሮ የተጠየቀ ከሆነ ፍ/ቤት አጣርቶ ቤቱን እለቃለሁ በማለት ከሰጡት ቃል በመነሳት ፍርድ ቤቱ አመልካችን ሲመረምር በትክክለኛ አእምሮና አስተሳሰብ የዳኝነት ጥያቄ ማቅረባቸው ተረጋግጧል በማለት ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ይልቀቁ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የአመልካች የእድሜ መግፋት ብቻ የህግ ችሎታቸውን አያሳጣም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ጉዳዩን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንደሰጧቸው የታመነ ጉዳይ ነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2441/1/ ስር እንደተመለከተው ስጦታ የሰጠ ሰው ስጦታው ከተደረገበት ቀን አንስቶ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ስጦታው እንዲሻር ጥያቄው ለዳኞች ካልቀረበ በስተቀር ዋጋ የለውም የሚል መሆኑን ችሎቱ አብራርቷል፡፡

በአርግጥ ተጠሪ በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለቀረበባቸው ክስ የይርጋ ጉዳይን አስመልክቶ ያነሱት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሌለ ቢሆንም ክርክሩ ቤት ከተሰጣቸው 47 ዓመት የሞላው መሆኑን ገልጿል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 1 በሰ/መ/ቁ.14047 ላይ ተከራካሪዎቹ ባያነሱትም ከቀረበው ክርክር በመነሳት የህግ ግምት ሊወሰድ የሚቻልበት አግባብ መኖሩን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ክርክሩ በይርጋ ይታገዳል የሚል መከራከሪያ ባያቀርቡም ቤቱን ለ47 ዓመት ይዘው መቆየታቸውን በመግለጽ ክርክሩን እስካቀረቡ ጊዜ ድረስ የይርጋ ጥያቄ ማቅረባቸው የህግ ግምት ተወስዶበታል፡፡

አመልካች በዚህ ላይ ያነሱት መከላከያ የለም፡፡ በመሆኑም ከላይ በተመለከተው የህግ አንቀጽ መሰረት ተጠሪ በቤቱ ላይ ለ47 ዓመት መኖራቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በህጉ በልዩ ክፍሉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ከማለፉም በተጨማሪ በጠቅላላ ህጉ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 ስር ተደንግጎ የሚገኘውን የአስር አመት የይርጋ ጊዜም አልፏል በማለት ካብራራ በኋላ አመልካች ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ተጠሪ ለአመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በቀን 23/05/09 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/119714 ከህግ ውጭ የይርጋ ጥያቄን በራሱ በማንሳት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ዳኞች በህግ ብቻ መመራት እንዳለባቸው ሕገ መንግስቱ የደነገገውን በመተላለፍ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ መብቴን የጣሰ ነው በማለት የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ ጥያቄን በራሱ በማንሳት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ እና በህግ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ነው የሚል አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱ ለውሳኔው አስገዳጅ የሰበር አቤቱታን የጠቀሰ ሲሆን በዚህ ውሳኔ ተከራካሪው በግልጽ መቃወሚያ ባያቀርቡም ከቀረበው ክርክር በመነሳት የህግ ግምት እንደሚወሰድ በመጥቀስ ተጠሪ በክርክራቸው ስጦታ ተደርጎላቸው ለ47 ዓመት በቤቱ መኖራቸውን ስለጠቀሱ በዚህም ይርጋን እንዳነሱ የህግ ግምት መወሰዱን አብራርቷል፡፡

ተጠሪ በቀረበባቸው ክስ ላይ መልስ ሲያቀርቡ አመልካች ጥያቄውን ያቀረቡት በትክክለኛ አእምሯቸው ከሆነ ቤቱን ለመልቀቅ ዝግጁ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ በዚህ አነጋገር ተጠሪ ንብረቱ የአመልካች መሆኑን አለመካዳቸውን ያሳያል፡፡ በጥያቄያቸውም መሰረት ፍ/ቤቱ አመልካችን በአካል አስቀርቦ ያነጋገራቸው መሆኑንና አመልካችም በክሱ ላይ የተጠቀሰውን በመናገር ተጠሪ ቤቱን እንዲለቁላቸው የፈለጉ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ አመልካች በአካል ቀርበው መናገራቸው ክሱን ያቀረቡት በትክክለኛ አዕምሮአቸው መሆኑን ፍ/ቤቱ አረጋግጧል፡፡ በዚሁ አግባብ በተጠሪ መልስ መሰረት የስር ፍ/ቤቱ አመልካችን አስቀርቦ ከጠየቀ በኋላና ጥያቄውም በትክክለኛ አዕምሮአቸው አስበውበት ያቀረቡ መሆኑን አረጋግጦ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

ምንም እንኳን ተጠሪ ለ47 ዓመታት በቤቱ ውስጥ ኖሬበታለሁ በማለት ቢከራከሩም ቤቱ ከአመልካች በቋሚነት የተሰጣቸው መሆኑን በማስረጃ አስደግፈው አላስረዱም፡፡ አመልካችም ቤቱን ለጊዜው ነው የሰጠሁት በማለት ክርክር ማቅረባቸውን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ያስረዳል፡፡ ለፍ/ቤቶቹም የቀረበ የስጦታ ውል የለም፡፡ በዚህም ስጦታው ስልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠሪም በመልሳቸው ቤቱን ለመልቀቅ ፍቃደኛ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ውሳኔ የቀለበሰው ተጠሪ በግልፅ የይርጋ ጥያቄውን ባያነሱም ከክርክሩ ጠቅላላ ይዘት በመነሳት የይርጋ ጥያቄን በራሱ ጊዜ በማንሳት ክሱ በይርጋ መታገድ አለበት በማለት የሰጠ መሆኑን አብራርቷል፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 245(2) በተከራካሪ ወገኖች መቃወሚያ ለፍ/ቤት በሚቀርብ ጊዜ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን እንደሚመረምር ደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ፍ/ቤት በራሱ ጊዜ መቃወሚያውን ማንሳት አይችልም፡፡



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በግልፅ በህግ ለሰበር ሰሚ ችሎትም ሆነ ለፍርድ ቤቶች ባልተሰጠ ስልጣን ላይ የድርጋ ጥያቄ በተከራካሪዎች መነሳት ሲገባው ችሎቱ በራሱ ማንሳቱ በሕገ መንግስቱና በአዋጅ የህግ ስህተቶችን ብቻ እንዲያርም ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ነው፡፡ ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 79(3) ዳኞች በህግ ብቻ ሊመሩ እንደሚገባ ያዛል፡፡ በተጨማሪም ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3 (ሀ) መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን የመጨረሻ ውሳኔ እንደሚያይ ደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት የሰበር ችሎቱ የስር ፍ/ቤቶች በስልጣናቸው ስር ሆነው የወሰኑትን ውሳኔ ባልተሰጠው ስልጣን በመግባት ከሕገ መንግስቱ ድንጋጌ ውጭ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ያልሆነ እና ሕገ መንግስቱን የሚጥስ ነው፡፡

ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 41/5/ መንግስት የአካል እና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሃገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል በማለት ደንግጓል፡፡

ውሳኔው አመልካችን በአረጋዊነታቸው የተከበረላቸውን እንክብካቤ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት የሚጻረር ነው፡፡ በዚህም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 41/5/ ድንጋጌ በመተላለፍ የተወሰነ ነው፡፡ ውሳኔው አመልካች አባውንት መሆናቸውን ግምት ውስጥ ሳያስገባ የተሰጠና አመልካች በዚህ ዕድሜያቸው ለአረጋውያን በሕገ መንግስቱ የተሰጠውን ክብርና እንክብካቤ እንዳያገኙ ያደረገ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ በመፍጠር ችሎታው ወይም በካፒታሉ ያፈራው ንብረት ባለቤት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ አመልካች በባለቤታቸው ስም ተመዝግቦ የሚታወቅና የራሳቸው የሆነን ቤት ለተጠሪ ለጊዜው እንዲኖሩበት የሰጡ መሆኑ በፍርድ ቤቱ ተረጋግጧል፡፡ይህ ባለበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ ያላግባብ የንብረት ሕገ መንግስታዊ መብታቸውን በመጣስ መወሰኑ ሕገ መንግስቱን ያከበረ አይደለም ፡፡

ስለዚህ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 3፣ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 እንዲሁም አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 5 የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች የልጅ ልጃቸው እንዲጠቀምበት የሰጡትን ቤት እንዲለቅላቸው ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት አግኝቶ የአሁን ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክብ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠና ውሳኔውም በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የጸና ሲሆን የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን በስር ተከሳሽ (በአሁን ተጠሪ) ያልተነሳን የይርጋ መቃወሚያ በማንሳት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ሊለቁ አይገባም ሲል የሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ የንብረት መብትን የሚጋፋ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች እድሜያቸው ከ100 አመት በላይ ስለሆነ በንብረታቸው ተጠቅመው ራሳቸውን መንከባከብ ይችሉ ዘንድ ተጠሪው ለጊዜው እንዲኖሩበት የሰጧቸውን ቤት እንዲለቁ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብ ሆኖ እያለ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን በስር ተከሳሽ ያልተነሳን የይርጋ መቃወሚያ በማንሳት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ውሳኔውን መሻሩ ሕገ መንግስቱን የሚቃረን



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የ/መ/ቁ. 93/13

አመልካች፡- ወ/ሮ ገነት አበበ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሮማን ደስታ

2ኛ. አቶ ግርማ ሩምቻ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 15/02/2010 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.138602 በቀን 28/11/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩም የፍቺ ውጤት የሆነ የንብረት ክርክርን ይመለከታል፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በ2ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ከሐምሌ 20 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ሁለት ልጆችን መውለዳቸውን ነገር ግን ተግባብተው ለመቀጠል ባለመቻላቸው እንደባልና ሚስት የነበረው ግንኙነት መቋረጡን ገልጸው በአዲስ አበባ ከተማ በሶስት ቦታ የሚገኙ ቤቶች፣ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች፣ በተለያዩ ባንኮች በ2ኛ ተጠሪ ስም ያለ ገንዘብ እና የአክስዮን ድርሻዎች የጋራ ናቸው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት አብረው መኖር የጀመሩት ከሐምሌ 20 ቀን 1993 ዓ.ም ሳይሆን ከጥቅምት ወር 1994 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑን፤ በዚህ ግንኙነት ውስጥ ሁለት ልጆችን መውለዳቸውን፤ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ከወ/ሮ በየነች አባይነህ ተገዛ የተባለውና በአቃቂ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ክልል ያለ ቤት 1ኛ ተጠሪ የጋራ ናቸው ያሉዋቸውን ቤቶች እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ያላፈሩ እና ያልተገዙ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በቦሌ ክ/ከ/ ያለው ቤት በ2ኛ ተጠሪ ገንዘብና ስም የተገዛ መሆኑን ገልጸው ከጋብቻ

በፊት የተፈራውን ንብረት ከተካፈሉ በኋላ በመለወጥ ያገኙት የግል ንብረት መሆኑን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

አሁን አመልካች ጣልቃ ገብ ሆነው ወደ ክርክሩ በመግባት ለገባኤው በቀረበው አቤቱታ የተገለጸው እና በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የሚገኘው ቤት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ፍቺ ከፈፀሙ በኋላ መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም የገዙትና የግል ንብረቴ ስለሆነ የጣልቃገብ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም አመልካች የጠቀሱትን ቤት በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት መግለጫ እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል ሰምቶና ክርክራቸውንም መርምሮ በኮልፌ ቀራኒዎ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የሚገኘውን ቤት 2ኛ ተጠሪ ከመጀመሪያው የቤቱ ባለቤት ባገኙት ውክልና መሠረት ለአመልካች የሸጡላቸው በመሆኑ ቤቱ የአመልካች ነው፣ ሌሎቹ በዝርዝር የተጠቀሱት የማይንቀሳቀሱ እና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች የጋራ ናቸው ሲል ወስኗል፡፡

1ኛ ተጠሪ በኮልፌ ቀራኒዎ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የሚገኘው ቤት ላይ የተወሰነውን በመቃወም ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በመቀጠልም 1ኛ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በውሳኔ ዝርዝሩም ግራ ቀኙን የሚያከራክራቸውና በኮልፌ ቀራኒዎ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የአመልካች ነው ተብሎ የተወሰነውን ቤት በተመለከተ 2ኛ ተጠሪ ከሻጭ በተሰጣቸው ውክልና መሠረት መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም ለአመልካች መሸጣቸውን፣ ጋብቻቸው ጥቅምት 12 ቀን 1994 ዓ.ም እንደፈረሰ አድርገው በመ/ቁ/ 19249 ላይ የካቲት 18 ቀን 2007 ዓ.ም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማስወሰናቸውን በማስረጃ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ መሆኑን ገልጿል፡፡

ጋብቻ ፈረሰ የሚባለውም የፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡ እውነቱ ይህ ሆኖ እያለ የ1ኛ ተጠሪን በንብረት የመጠቀም መብት ለማስቀረት ሲባል ክርክር የተነሳበት ቤት ከተገዛበት ከመጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም በፊት የአመልካችና 2ኛ ተጠሪ ግንኙነት እንደተቋረጠ አድርጎ ማቅረብ በህግ ፊት እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ 2ኛ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን ቤት ለአመልካች ሸጠው በ2005 ዓ.ም ሺላ ቤት ተሰርቶበታል፡፡ ቤቱ በአመልካች ስም መመዝገቡና የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ያላቸው መሆኑ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1195/1/ መሠረት የቤቱ ባለሃብት ናቸው የሚል ግምት ሊያሳድር የሚችል ማስረጃ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1196/ሀ/ እና /ለ/

የተደነገጉትን ሁኔታዎች በማስረዳት የባለቤትነት ማስረጃው ትክክል አለመሆኑን በበቂ ሁኔታ ስላስተባበሉ ቤቱ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው በማለት ወስኗል።

በዚሁ ውሣኔ መነሻነት አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 138602 ከጋብቻ ውጭ ያፈራሁትን ንብረት በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ህገ መንግስታዊ የንብረት መብት የሆነውን አንቀጽ 40 /1/ እና የፍ/ቤቶች የጣምራነት ስልጣን አንቀጽ 80 /3/ /ሀ/ የጣሰ ነው በማለት ህገ መንግስታዊ ትርጉም እንዲሰጥበት ጉባኤውን የጠየቁ ሲሆን ጉባኤው ጉዳዩን መርምሮ የፍ/ቤት ውሳኔው የአመልካችን ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

የአመልካች አቤቱታ ከሕገ መንግስቱ ድንጋጌ ጋር ተመርምሯል። እንደተመረመረውም ለዚህ አቤቱታ መነሻ የሆነው በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 5 የሚገኘው ቤት ነው። ይህ ቤት በፍርድ መዝገቡ ላይ እንደተጠቀሰው በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ ነው። ቤቱ የተገዛው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በሁኔታ ተፋተናል ካሉበት ከ1994 ዓ.ም በኋላ በ2005 ዓ.ም ነው።

የሰበር ሰሚ ችሎቱ ስመ ንብረቱ በአመልካች የተመዘገበ መሆኑ ቢታወቅም 1ኛ ተጠሪ ይህን ማስተባበል ከቻሉ ግምቱ ፈራሽ መሆኑን የፍትሐብሔር ህጉን በማጣቀስ አብራርቷል። ይህ መነሻ ከህግ አንጻር ተገቢ ቢሆንም በዚህ ውሳኔ 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን የባለቤትነት ማስረጃ ያስተባበሉበት ሂደት አልተጠቀሰም። ችሎቱ ሃሳባዊ በሆነ መነሻ የጋብቻ ፍቺው በቅን ልቦና ያልተከናወነ ነው። ጋብቻቸው ጥቅምት 12/1994 ዓ.ም ፈርሷል ተብሎ መወሰኑ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው በማለት ድርጊቱ የ1ኛ ተጠሪን መብት ለመጉዳት የታሰበ መሆኑን ጠቅሷል። ጋብቻ በሁኔታ ካልፈረሰ በስተቀር በፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ እንዳለ የሚገመት መሆኑን ችሎቱ አትቷል።

በዚህ መነሻነት ችሎቱ የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ ድርጊት የ1ኛ ተጠሪን በንብረት የመጠቀም መብት ለማስቀረት ሲባል ክርክር የተነሳበት ቤት ከተገዛበት ከ2005 ዓ.ም በፊት ግንኙነታቸው እንደተቋረጠ አድርጎ ማቅረብ በህግ ፊት ተቀባይነት የለውም በማለት አብራርቷል። ከፍርድ ሃተታ መረዳት የሚቻለው የአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ግንኙነት የተቋረጠው በ2007 ዓ.ም መሆኑን ነው። ምክንያቱም በችሎቱ ማብራሪያ መሰረት ጋብቻው ፈረሰ የሚባለው ለፍ/ቤት ጥያቄ በቀረበበት ቀን መሆኑ ነው።

የፌ.ዴ.ሪ. ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ነገር ግን የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ አከራክሮ በሚወስንበት ጊዜ በአመልካች እና ተጠሪ መሀከል የነበረው ጋብቻ መች ተፈጽሞ መች በፍቺ እንደፈረሰ የፍቺ ውሳኔ የተሰጠበትን ውሳኔ በመጥቀስ በዝርዝር አስፍሯል። ይህ ውሳኔ በይግባኝ ያልተሻረ እና ጸንቶ የሚገኝ ውሳኔ ነው። በዚሁ መሰረት በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መሀከል በታህሳስ 1 ቀን 1969 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመው እየኖሩ ቆይተው ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት ጋብቻቸው ተለያይተው ከኖሩበት ጊዜ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ የፈረሰ ነው በማለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት በከ/መ/ቁ/ 19249 ላይ የካቲት 18 2007 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቶበታል። ይህ የወረዳ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ጸንቶ ባለበት ሰበር ሰሚ ችሎቱ የአመልካችና 2ኛ ተጠሪ ተግባር 1ኛ ተጠሪን ለመጉዳት እንደሆነ በማሰብ ብቻ የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የጋራ ሃብት ነው በማለት እና አመልካችን ሙሉ በሙሉ ከንብረቱ ተካፋይነት በማስወጣት ወስኗል። ይህ ውሳኔ ከህገ መንግስታዊ መብቶች አንጻር ሲታይ፦

1ኛ/ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔው በአንድ በኩል የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ ግንኙነት እስከ 2007 ዓ.ም እንዳለ ከቆጠረ በኋላ አከራካሪው ቤት በ2005 ዓ.ም የተገዛ መሆኑን እያረጋገጠ አመልካችን ከንብረቱ በማስወጣት መወሰኑ እራሱ በፍርድ ሀተታው የዘረዘራቸው ነጥቦችን በሚቃረን እና ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁ 43988 እና 14290 የተወሰኑት የሰበር ሰሚ ችሎቱ አስገዳጅ ውሳኔዎችን ሁሉ ባልተከተለ መንገድ የተወሰነ ውሣኔ መሆኑን ያሣያል። ከዚህ በተጨማሪም በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መሀከል ግራ ቀኙ የተማመኑበት እና የፀና ጋብቻ የነበረ መሆኑን የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር የማከራከር እና ማስረጃን በመመዘን ስልጣናቸው አረጋግጠው ይህን ጋብቻ ስለመኖሩ 1ኛ ተጠሪ ባልካዱበት እና ባላስተባበሉበት ሁኔታ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79/3/ ስር እንደተደነገገው ዳኞች በሕግ ብቻ በመመራት ውሣኔ ይሰጣሉ የሚለው ድንጋጌ ወደ ጎን በመተው በማስረጃ ሣይደገፍ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መሀከል የተደረገው የጋብቻ ፍቺ ውሳኔ 1ኛ ተጠሪን ለመጉዳት በማሰብ ሊሆን ይችላል በሚል ሀሣብ ብቻ አመልካችን ከተጠቀሰው ቤት ተካፋይነት ሙሉ በሙሉ እንዲወጡ ማድረጉ የአመልካችን በሕገ መንግስቱ የተደነገገውን የእኩልነት ፣ ፍትህ የማግኘት እና የንብረት መብት የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል።

2ኛ/ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በክርክሩ የተገለፀው ቤት በመጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ/ም 2ኛ ተጠሪ በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ለአመልካች የሸጡላቸው መሆኑን በውሣኔ ሀተታው ዘርዝሯል። ይህ የሚያሣየው አከራካሪው ቤት የተገዛው በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መሀከል የነበረው

ጋብቻ በፍ/ቤት ውሣኔ ከፈረሰ ከአስራ ሶስት አመታት በኂላ እንደሆነ እና ስመ ሀብቱ በአመልካች ስም የተመዘገበ የግል ንብረታቸው መሆኑ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ላይ አከራክረው ፤ ማስረጃን መዝነው እና ህጉን ተርጉመው ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት ነው ብለው ወስነው እያለ ሰበር ሰሚ ችሎቱ አመልካችን ሙሉ በሙሉ ከንብረቱ በማስወጣት ቤቱ የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ንብረት ነው ብሎ መወሰኑ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በህገ መንግስቱ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 ከተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተት ከማረም ስልጣኑ ውጪ የወሰነው እና የሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣ 40 እና 79 ድንጋጌዎች የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 /2/ መሰረት ማንኛውም ሰው በጉልበቱ፣ በእውቀቱ ወይም በገንዘቡ የግል ንብረት የማፍራት መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ንብረት ያፈራ ሰው ደግሞ በሕግ አግባብ በንብረቱ የመጠቀም እና የማስተላለፍ መብት እንዳለው በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ተደንግጐ እናገኛለን፡፡ አንድ ሰው በሕግ አግባብ ያፈራው የግል ንብረት መብቱን ሊያጣ የሚችለው ሕግ በዘረጋው ስርዓት ብቻ መሆን እንዳለበት የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡ ነገር ግን በክርክሩ ላይ የተጠቀሰው ቤት አመልካች በግላቸው ገዝተውት በስማቸው ተመዝግቦ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ይዘውበት በእርግጥም እያስተዳደሩት መሆኑን የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠውት እያለ እና ይህንን ማስረጃ የሚያስተባብል ተጨባጭ ማስረጃ ሳይገኝ አመልካችን ከንብረቱ ባለመብትነት ሙሉ በሙሉ በማስወጣት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ የአመልካችን ንብረት የማፍራት ህገ መንግስታዊ መብት የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን መረዳት ተችሏል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 138602 ላይ የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ፤ 25 እና 79 ጋር የሚቃረን በመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 138602 ላይ የሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚነት የለውም ተብሎ በምክር ቤቱ የተሻረ መሆኑን አውቆ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የሚገኘውን ቤት በተመለከተ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች አስቀርቦ በማከራከር ተገቢውን ውሳኔ እንዲወስን የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡

2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡



## የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ
## ግንቦት 13 ቀን 2009 ዓ.ም

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ያይኔአበባ አዳሙ /5 ሰዎች/

ተጠሪዎች፡- ተጠሪ ወ/ሮ መሰረት ገ/መድህን

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

አመልካቾች ጥቅምት 18 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለጉባኤው ያቀረቡት ጥያቄ ተጠሪ የሟች አባታችን አቶ አዳሙ ዘገዬ ልጅ ነኝ በማለት ለፍ/ቤት ጥያቄ አቅርበው ፍ/ቤቶቹም በዘረመል (DNA) ምርመራ ውጤት ተጠሪ የሟች ልጅ ያለመሆናቸው እየታወቀ ልጅ ናቸው በማለት መወሰናቸው ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 25፣ 37፣ እና 40 ጋር ስለሚቃረን ትርጉም ይሰጥልን የሚል ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሟች አቶ አዳሙ ዘገዬ ልጅ ነኝ በማለት ካስወሰኑ በኋላ አመልካቾች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ በአቤቱታቸውም ተጠሪ የሚጠሩበት የአባት ስም የሌላ ሰው መሆኑ የሟች ልጅ ያለመሆናቸውን ስለሚያሳይ እና ሟች አቶ አዳሙ ዘገዬ የተጠሪ እህት የሆኑትን ወ/ሪት ብርቱካን አዳሙን ልጄ ናት በማለት በመስሪያ ቤታቸው እና በዕድር ውስጥ ሲያስመዘግቡ ተጠሪን መተዋቸው ልጅ ያለመሆናቸውን ስለሚያመለክት ውሣኔው ይሻርልን የሚል ነው፡፡ ተጠሪም በበኩላቸው ያቀረቡት ክርክር የሚጠሩት በአያታቸው ስም መሆኑን፣ ሟች በሕይወት በነበሩበት ወቅት አባትነታቸውን ተቀብለው ይረዷቸው እና ይንከባከቧቸው የነበሩ በመሆኑ እንዲሁም ሟች እና እናቴ እንደባልና ሚስት ወይም በህግ የታወቀ ግንኙነት ባይኖራቸውም በፆታዊ ግንኙነት ለአራት አመታት በቆዩበት ጊዜ የተወለድኩ በመሆኔ የተሰጠው ውሣኔ ሊሻር አይገባውም የሚል ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሟች ልጅ ናቸው በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህም ውሣኔ መሰረታዊ የህግ

ስህተት አለበት በማት አመልካቾች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ቢያቀርቡም ለሰበር አያስቀርብም በማለት ውሣኔ ተላልፏል፡፡ አመልካቾች እንደገና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 መሰረት ከዚህ በፊት የተሰጠው ውሣኔ ሀሰተኛ የምስክርነት ቃልን መሰረት በማድረግ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በማግኘታችን እንዲሁም የዘረ-መል ምርመራ ውጤቱ ሟች የተጠሪ አባት ያለመሆናቸውን የሚያሳይ ስለሆነ ጉዳዩ በድጋሚ ይታይልን በማለት የድጋሚ ዳኝነት ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አቤቱታው በህጉ ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ስለማያሟላ ተቀባይነት የለውም ሲል ወስኗል፡፡ ይህም ውሣኔ እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ አያስቀርብም በማለት ተወስኗል፡፡

አመልካቾች በአቤቱታቸው ተጣሰብን በማለት የጠቀሷቸው መብቶች የእኩልነት፣ ፍትህ የማግኘት እና የንብረት መብቶች ናቸው፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው በአመልካቾችና ተጠሪ መካከል የነበረው ክርክር ልጅነትን ስለማረጋገጥ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ሟች አቶ አዳሙ ዘገዬ ልጅ ነኝ በማለት ካስወሰኑ በኋላ አመልካቾች መቃወሚያ አቅርበው ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙን አከራክረው ውሣኔ የሰጡ ሲሆን አመልካቾች የድጋሚ ዳኝነት ቢጠይቁም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

አመልካቾች ካቀረቡት ቅሬታ አንደኛው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት የዘረ-መል (DNA) ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጥቶ ውጤቱን በመጠባበቅ ላይ ሳለ ዳኛ በመቀየራቸው ምክንያት ስለ ዲ.ኤን.ኤ ምርመራው አንድም ነገር ሳይጠቅስ ለይግባኝ አያስቀርብም በማለት መወሰኑ የእኩልነት መብታችንን ያጣብባል የሚል ነው፡፡ አጣሪ ጉባዔውም በጽ/ቤቱ በኩል በደብዳቤ ቁጥር 1507/08 በቀን 04/09/2008 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መ/ቁ 102036፣ የመዝገቡ ግልባጭ እንዲቀርብ ጠይቆ ሙሉ መዝገቡ ቀርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት በመ/ቁ 102036 ሲመለከት ቆይቶ ሰኔ 9 ቀን 2003 ዓ.ም በአመልካቾች ጥያቄ መሠረት በወ/ሮ መሠረት ገ/መድህን እና የሟች አቶ አዳሙ ወንድም አቶ ዳኛቸው ዘገየ መሀል ዝምድና ስለመኖሩ የዲ.ኤን.ኤ. ምርመራ በማድረግ ውጤቱን እንዲገልጽ ለኢንተርናሺናል ክሊኒካል ላቦራቶሪስ ትዕዛዝ መስጠቱን መረዳት ችለናል፡፡ ኢንተርናሺናል ክሊኒካል ላቦራቶሪስ ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ ምርመራው በተጠሪ እና በሟች ወንድም መካከል ዝምድና ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ አይደለም የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም

ምላሹ ደርሶት መዝገቡን መርምሮ ለመወሰን ለነሐሴ 10 ቀን 2003 ዓ.ም ቀተሮ ቢሰጥም ነሐሴ 20 ቀን 2003 ዓ.ም ጉዳዩን አዲስ በማድረግ ለይግባኝ አያስቀርብም በሚል ፎርም ትዕዛዝ በመስጠት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሕግም ይሁን የፍሬ ነገር ግድፈት የለበትም በማለት እና ይግባኙን አለመቀበሉን በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የዲ.ኤን.ኤ. ምርመራ አዝዞ ውጤቱ ለፍ/ቤቱ ከቀረበ በኋላ ወደ ኋላ ተመልሶ አያስቀርብም ማለቱ ፍ/ቤቱ ሕገ መንግሥቱን ያልተከተለ መሆኑን መረዳት የሚያስችል ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25 መሠረት ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን እና በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ፍ/ቤቱ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ተደርጎ ውጤቱ ከቀረበለት በኋላ ማስረጃዎችን በመመዘን ውሳኔ ሊያስተላልፍ ሲገባው ወደኋላ በመመለስ የሰጠው ትዕዛዝ ሕግን ያልተከተለ እና ለተጠሪ እንደክርክራቸው የተሻለ እድል የፈጠረ በአንጻሩ የአመልካቾችን መብት ያጣበበ በመሆኑ ውሳኔው የአመልካቾችን በሕግ ፊት እኩል የመታየት መብት ይቃረናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍ/ቤቱ ያስተላለፈው ውሳኔ መሠረት ያደረገባቸውን ምክንያቶች ሳይጠቅስ እና በጉልህ መልኩ የሥነ ሥርዓት ሕጉን ሳይከተል መወሰኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 12 ላይ የተደነገገውን የግልጽነት መርህ እንዲሁም በአንቀጽ 79 ላይ ዳኞች ከሕግ ውጭ በሌላ ሁኔታ እንደማይመሩ የሰፈረውን ድንጋጌ ይቃረናል፡፡

በተጨማሪ ፍ/ቤቱ በተያዘው ጉዳይ የዘረ-መል ውጤቱን መሰረት በማድረግ ትክክል ነው ብሎ ያመነበትን ውሳኔ መስጠት የሚችል ቢሆንም በአንጻሩ ግን በትዕዛዙ ያስቀረበውን የምርመራ ውጤት ከግምት ባለማስገባት የሰጠው ውሳኔ ያልተገባ አባት እና ልጅ ግንኙነትን የመፍጠር ዕድል ያለው በመሆኑ ይኸውም የቤተሰብን ህልውና የሚፈታተን እና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 3 "ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መነሻ ነው፡፡ ከኅብረተሰብና ከመንግስት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡" የሚለውን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ የሚጋፉ ነው፡፡

በመጨረሻም አመልካቾች ያቀረቡትን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ትዕዛዝ ሰጥቶበት የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ውጤቱ ከቀረበ በኋላ በውጤቱ ላይ ተመስርቶ የተላለፈ ምንም አይነት ውሳኔ

ወይም ትዕዛዝ አለመኖሩ ለአመልካቾች ጥያቄ ምላሽ በመንፈግ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ አንድ ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳይን ለፍ/ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት እንዳለው የሚደነግገውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚጋፋ ነው፡፡

አመልካቾች ካቀረቡት ቅሬታ አንደኛው እና ዋናው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ ቀርቦለት የዘረ-መል (DNA) ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጥቶ ውጤቱን በመጠባበቅ ላይ ሳለ ዳኛ በመቀየራቸው ምክንያት ስለ ዲ.ኤን.ኤ ምርመራው አንድም ነገር ሳይል መወሰኑ አግባብ አለመሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶችም በዘረ-መል ምርመራው ላይ ምንም ሳይሉ ማለፋቸው የግለሰቡን አባት የማግኘት መብት የሚጋፋ እንዲሁም አላግባብ አባት ያልሆነ ሰውም አባት የማድረግ ፕሪስደንት የሚያስከትል በመሆኑ፣ ምክንያቱም የፌደራል ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሳኔ እንደ ሕግ የሚያገለግል በመሆኑ በተመሳሳይ ጉዳዮች ሊጠቀሱ (ሊወሰኑ) ስለሚችሉ እና መከራከሪያ ነጥብ ስለሚሆኑ ይህን አይነት ለማስቀረት እና የዲ.ኤን.ኤ ምርመራው ለፍትሕ አሰጣጥም አመች ስለሚሆን ሊታለፍ የማይገባው የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ መታለፉ ተቀባይነት የለውም፡፡

ስለሆነም ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ የአጣሪ ጉባኤው የውሳኔ ሀሳብን ተቀብሎ ፍ/ቤቱ የዘረ-መል ምርመራ ውጤትን ፈትሾ እና መዝኖ የመጨረሻ ውሳኔ ስላልሰጠ እንደገና ተመልክቶ የመሰለውን የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥ ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1.በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውና በጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ መብት የሚጻረር በመሆኑ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን አውቆ የዘረ-መል ምርመራን ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ የተመለሰ መሆኑን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይድረሰው፡፡

2.የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

13 68/2007

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ
ግንቦት 13 ቀን 2009 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ አዳነች ልሳነወርቅ

ተጠሪዎች፡- አቶ ሽብሩ አስናቀ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

አመልካች ባለቤታቸው ከነበሩት ተጠሪ ጋር ከተፋቱ በኋላ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ መሆኑ የተረጋገጠው እና በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ መኖሪያ ቤት በልማት ስራ ምክንያት በመፍረሱ በምትክ ለቤት መስሪያ የተሰጣቸውን የመሬት ይዞታ ከተጠሪ ጋር ካልተስማሙ መካፈል አይችሉም ብሎ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 13ኛ ፍትሐብሄር ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ጋር ይቃረናል በማለት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩም አመጣጥ አመልካች እና ተጠሪ በጅማ ዞን ጎማ ወረዳ ፍ/ቤት በነበራቸው የባልና ሚስት ክርክር ጋብቻቸው በፍ/ቤት ውሳኔ ከፈረሰ በኋላ የጋብቻ መፍረስ የሚያስከትለውን ውጤት በተመለከተ ፍ/ቤቱ ማስረጃን መሰረት በማድረግ በጋራ ያፈሩትን ንብረት ካካፈለ በኋላ የአመልካች እና የተጠሪ መሆኑ የተረጋገጠው በአዲስ አበባ ከተማ በቤት ቁጥር 904 ተመዝግቦ በ75 ካ.ሜ ላይ የሰፈረው መኖሪያ ቤት አመልካች እና ተጠሪ እንዲካፈሉ በመወሰን አፈፃፀሙን ቤቱ በሚገኝበት ለሚያስችለው አዲስ አበባ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 13ኛ ፍትሐብሄር ችሎት እንዲያስፈፅም ልኳል፡፡

ፍርዱን እንዲያስፈፅም የተላከለት የልደታ ምድብ ችሎትም ጉዳዩን ተቀብሎ ግራ ቀኙን አስቀርቦ እንደ ፍርዱ ለማስፈፀም ጉዳዩን ሲያጣራ ቤቱ በልማት ስራ ምክንያት የፈረሰ መሆኑን እና ምትክ 75 ካ.ሜ ባዶ ቦታ እና ብር 43,000.80 (አርባ ሶስት ሺ ከሰማኒያ ሳንቲም) ካሳ ለተጠሪ የተከፈለ መሆኑን በማጣራት ተጠሪ በልማት ስራ ለፈረሰው ቤት ከተከፈለው ካሳ አመልካች ግማሹን እንድትካፈል በማድረግ ለፈረሰው ቤት መስሪያ ምትክ

8

የተሰጠው 75 ካ.ሜ ባዶ የመሬት ይዞታ እንዲያስፈፅም በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ጽ/ቤት የይዞታ አስተዳደር አገልግሎት የሽግግር ጊዜ መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ጽ/ቤቱም ይዞታው ላይ ንብረት ያልሰፈረበት ስለሆነ ባዶ የመሬት ይዞታው ሊካፈል አይችልም ብሎ አፈፃጽሙን ለያዘው ፍ/ቤት ምላሽ ሰቷል፡፡

ፍ/ቤቱ የጽ/ቤቱን ደብዳቤ መሠረት አድርጎ አመልካች እና ተጠሪ ተስማምተው ካልጨረሱ ይዞታውን ማካፈል አይቻልም በማለት መዝገቡን የዘጋው ሲሆን ፍ/ቤቱ የሰጠው ትእዛዝ እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ አያስቀርብም ተብሎ የተዘጋ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ምክር ቤቱ የአመልካችን አቤቱታ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ፍርድ አስፈፃሚው ፍ/ቤት የባል እና ሚስት የጋራ መሆኑ የተረጋገጠው በአዲስ አበባ ከተማ ክልል የሚገኘው የመሬት ይዞታ አመልካች ከተጠሪ ጋር ካልተስማማች ማካፈል አይቻልም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ጋር ይቃረናል በማለት የጠየቁት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲታይ ፍርድ አስፈፃሚው ፍ/ቤት ይዞታው ላይ ግንባታ ያልሰፈረና የይዞታው መጠን 75 ካ.ሜ ስለሆነ መካፈል አይችልም በማለት የሰጠውን ምላሽ መሰረት አድርጎ ንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

ፍርድ አስፈፃሚው ፍ/ቤት በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት የይዞታ አስተዳደር አገልግሎት የሽግግር ጊዜ መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽ/ቤትን ምላሽ መሰረት አድርጎ አመልካች እና ተጠሪ ካልተስማሙ ይዞታውን ማካፈል አይቻልም በማለት ትዕዛዝ ከመስጠቱ ፊት ይዞታውን ለሁለት ማካፈል የማይቻል ከሆነ አንደኛው ወገን ለሌላው ወገን በእጣ እንዲያስቀር የሚል አማራጭ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ፍ/ቤቱ ፍርዱን ለማስፈፀም ያስቀመጠው አማራጭ ላይ አመልካች እና ተጠሪ ባለመስማማታቸው መዝገቡን የዘጋው ቢሆንም የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን ፍርድን ከማስፈፀም አንጻር ለፍ/ቤቶች ትልቅ ስልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ተብሎ የውሳኔ ሐሳብ ከመቅረቡ በፊት ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ ካልተስማሙ ማስፈፀም አይቻልም በማለት የዘጋውን መዝገብ

በማንቀሳቀስ አመልካች እና ተጠሪን በድጋሚ አስቀርቦ ሕጋዊ ነው ብሎ ያመነበትን ትዕዛዝ በመስጠት ፍርዱን አስፈፅሞ ውጤቱን ለጉባኤው እንዲገልጽ ለፍ/ቤቱ ደብዳቤ የተፃፈ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በዚህ ሁኔታ ለመፈጸም ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡

ምክር ቤቱ ፍ/ቤቱ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርአት ሕጉ ላይ ፍርድን ከማስፈፀም አንፃር የተደነገጉትን የሕግ ድንጋጌዎች በመከተል እና ስልጣኑን በመጠቀም ሕጋዊ ነው ብሎ ያመነበትን አማራጭ በመከተል ትዕዛዝ በመስጠት ፍርዱን ማስፈፀም ሲገባው አመልካች ከተጠሪ ጋር ካልተስማማች ይዞታውን ማካፈል አይቻልም የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ መዝገቡን መዝጋቱ በሕገ መንግስቱ አንቀፀ 35 ንኡስ አንቀፅ 7 ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀም እና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይም መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደር እና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው የሚለው እና በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ከሚለው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ነው፡፡

በህግ አግባብ መሰረት የተፈረደ ፍርድ መፈጸም ስላለበት እና ፍርድ እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ የተላለፈለት ወይም ውክልና የተሰጠው ፍርድ ቤት በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በፍተሐ ብሔር ሥነ ስርዓት ህግ ስለ ፍርድ አፈጻጸም የተደነገጉትን የሕግ ድንጋጌወች በመከተል ፍርድን ለማስፈጸም አስፈላጊ ከሆኑት የተለያዩ ህጋዊ አማራጭ መንገዶች አንዱን በመምዘዝ ትእዛዝ ሰጥቶ ተከራካሪ ወገኖች ቢስማሙም ባይስማሙም ፍርዱን ማስፈጸም ሲገባው አመልካች ከተጠሪ ጋር ካልተስማማች ይዞታዋን ማካፈል አይቻልም ነገር ግን አመልካች ከተጠሪ ጋር ከተስማማች ይዞታውን ማካፈል ይቻላል የሚል ትርጉም የሚሰጥ ምክንያት በመስጠት የሰጠው የአፈጻጽም ትእዛዝ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 37 የተደነገጉትን የአመልካችን ማለትም የሴቶችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚገድብ እና የሚጥስ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን የአፈጻጸም ትእዛዝ በመሆኑ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

ስለሆነም የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚ እንዳይሆን ም/ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፤

**ትዕዛዝ**

1.በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ልደታ ፍትሐብሄር ችሎት የተሰጠው እና በጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ የንብረት ባለቤትነት እና ተጠቃሚነት መብትን የሚጻረር በመሆኑ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን አውቆ ንብረቷን እኩል የመካፈል መብቷ እንዲከበር እና እንዲፈጸም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይድረሰው፡፡

2.የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የስራ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

የፌ/ም/መ/ቁ.016/08

አመልካች፡- ወ/ሮ ሃና አድማሱ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የሻረግ ከበደ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ-መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ ቁ.79679 ሚያዚያ 17 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 103454 በ15/07/2007 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የፀናው ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 37፣ 25 እና 78 የተመለከተውን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ የሕገመንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ለአጣሪ ጉባኤው አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉደዩ ላይ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ሚያዚያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ ቁ.79679 ሚያዚያ 17 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው እና እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 103454 በ15/07/2007 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የፀናው ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9፣ 37፣ 25 እና 78 የተመለከተውን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ የሕገመንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ጉዳዩም የፍትሐብሔር ፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የአሁን አመልካች በስር ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ የቤት ቁጥር 423 አካል የሆነው ማዕድ ቤት ተጠሪ ይዘው ስለሚገኙ ይልቀቁልኝ፣ ኪራዩንም ይክፈሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ቤቱን በስጦታ

ውል አግኝቻ ማዕድ ቤቱን አፍርሸ ሁለት ክፍል ዛኒጋባ ቤት ስለሰራሁ ቤቱ የራሴ ነው ልለቅ አይገባኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን ቤት ለአሁን አመልካች እንዲለቁ፤ ማዕድ ቤቱን አስፋፍተው ለመስራት ያወጡት ወጪ ካለ ዳኝነት ከፍለው የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካችም የፍርድ አፈጻጸም ክስ አቅርበው ግራቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፍርድ አፈጻጸም መምሪያው በውሳኔው መሰረት ለአሁን አመልካች አስረክቧል፡፡ ተጠሪም በፍርድ አፈጻጸም መምሪያው ውሳኔ ላይ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቅሬታ በማቅረባቸው የፍርድ አፈጻጸም መምሪያው ያስረከበው ቤትና ንብረት በዋናው ፍርድ ያልተመለከተ ንብረት ስለሆነ ተጠሪ አዲስ የተሰሩትን ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ለአመልካች እንዲያስረክቡ መደረጉ ትክክል አይደለም በማለት ተጠሪ ለአመልካች ማዕድ ቤቱን እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

ፍሬ ሃሳቡ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ሲሆን አመልካች የፍርድ ባለመብት የሆንኩትን ንብረት በአፈጻጸም ጊዜ ያጣሁ በመሆኑ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 25 እና 37 መሰረት የእኩልነትና ፍትህ የማግኘት መብቴ ተጥሷል በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ ከጉዳዩ አመጣጥ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት ቁጥር 423 በውርስ አግኝተዋል፡፡ አመልካች በመሰረቱት ክስ የቤቱ አካል የሆነውን ማዕድ ቤት ተጠሪ በስጦታ ውል አግኝቼዋለሁ በማለት ይዘው ስለሚገኙ ይልቀቁልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ክርክሩን ሰምቶ ተጠሪ በዋናው ክስ ክርክር ቤቱን በስጦታ ስላገኘሁ በቦታው የነበረውን ማዕድ ቤት በማፍረስ አስፋፍቸ አዲስ ዛኒጋባ ቤት ሰርቻለሁ ቢሉም ይህ የስጦታ ውል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.00691 በፍርድ ስለተሰረዘ ተቀባይነት የለውም በማለት ተጠሪ ያወጡትን ወጪ ከፈለጉ ዳኝነት ከፍለው መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን ገልጾ ክርክር የተነሳበትን ቤት ግን ለአሁኗ አመልካች እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በዋናው ውሳኔ በመ. ቁ. 22011 የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክር ያስነሳውን ቤት በአራቱም አቅጣጫ አዋሳኞቹን በመግለጽ የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ይልቀቁ በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የዚህ ውሳኔ ክፍልም እስከ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ድረስ ስለፀና አመልካች የፍርድ አፈፃፀም ክስ መስርተዋል፡፡ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ የቤት ቁጥር 423 አካል በሆነ የመሬት ይዞታ በፍርዱ በተገለፀው በምስራቅ መንገድ፤ በምዕራብ የመንግስት ቤት፤ በደቡብ ወንዝ፤ በሰሜን ቁ.423 የሆነው ዋና ቤት እና መንገድ የሚያዋስኑትን አዲስ የተሰሩ ቤቶችንና ዛፎችን ተጠሪ ለአመልካች እንዲያስረክቡ ወስነው አስፈፅመዋል፡፡

ተጠሪ በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ውሳኔ ላይ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቅሬታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱም የአፈፃፀም መምሪያው በዋና ውሳኔ ያልተካተተውን ንብረት ከተጠሪ ወስዶ ለአመልካች ማስረከቡ ስህተት ነው በማለት ተጠሪ ማዕድ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡

ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔም ስንመለከት በዋናው ውሳኔ ተጠሪ ማዕድ ቤቱን አፍርሰው የሰሩትን አዲስ ቤት ለአመልካች ለቀው ከፈለጉ ያወጡትን ወጪ ዳኝነት ከፍለው መጠየቅ ይችላሉ ተብሎ የተወሰነውን ፍርድ የሚቃረን ይሆናል፡፡ ተጠሪ ማዕድ ቤቱን ያስረክቡ በማለት የተሰጠውም የአፈፃፀም ውሳኔ ማዕድ ቤቱ ፈርሶ አዲስ ቤት በመሰራቱ ምክንያት በተጨባጭ መሬት ላይ ያለው ሌላ ነገር በመሆኑ ሊፈፀም የማይችል ውሳኔ ያደርገዋል፡፡ በዚህ የአፈፃፀም ውሳኔ በሰ.መ.ቁ. 103454 በሀሳብ የተለዩት አንድ ዳኛ እንዲህ በማለት የልዩነት ሃሳባቸውን አስቀምጠዋል፡፡ *"ተጠሪዋ በስረ ነገር ክርክር ጊዜ በተከሳሽነት ቀርበው በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ተገቢ ነው የሚሉትን ክርክር ሁሉ አቅርበው በይዞታው ላይ አስፋፍቸ ሰርቻለሁ በሚሉት ዛኒጋባ ቤት ላይ ያጡትን መብት ባለዕዳ ሆነው በተከራከሩበት በአፈፃፀም ክርክር እንዲጎናፀፉ ማድረጉ በሕጉ አግባብ የተሰጠውን የሥረ ነገር ፍርድ ዋጋ አልባ የሚያደርገው በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አላገኘሁትም"* ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል እንዲጣራ ለጽ/ቤቱ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ለጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ማኔጅመንት ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር አጠጉ392/2008 በቀን 29/02/08ዓ.ምበተጻፈ ደብዳቤ የተጠየቀ ሲሆን፤ የጉለሌ ክ/ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀግት ጽ/ቤት በቁጥር ጉ/ክ/ከ/ው/ይ/ሬ/ፕ/ዴስክ 197/2008 በቀን 28/7/2008 ዓ.ም ለጉባኤው በላከው መረጃ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ማዕድ ቤትና ሰርቪስ ቤት 6 ክፍል ተጠሪ የሰሩ መሆኑንና ቤቶቹ ግን የሚገኙት በአመልካቿ 530 ካ.ሜ. የመሬት ይዞታ ውስጥ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

ተጠሪ ማዕድ ቤቱን አፍርሰው ሰዲስ ቤት ሰርቻለሁ ብለው የተከራከሩት ማዕድ ቤቱን በስጦታ ውል አግኝቻለሁ በሚል ሲሆን ይህ ክርክር በዋናው ፍርድ የስጦታ ውሉ በሌላ መዝገብ ሕገወጥ ውል ነው ተብሎ ስለተሰረዘ ክርክሩ ውድቅ ተደርጓል፡፡ የዋናው ቤት አካል በሆነው ይዞታ ላይ ተጠሪ መብት የላቸውም ከፈለጉ ቤቶችን ለማስፋፋት ያወጡትን ወጪ ዳኝነት ከፍለው መጠየቅ ይችላሉ ተብሎ በፍርድ የተወሰነውንና አመልካች በፍርድ ባለመብት ሆነው በአፈጻጸም የተረከቡትን ቤት እንዲመልሱ መወሰኑ በዋናው ፍርድ የተወሰነውን ውሳኔ ዋጋ አልባ የሚያደርገው ነው፡፡

ስለዚህ አመልካች በፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ንብረት በአፈፃፀም ውሳኔ ማጣታቸው በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40/1/ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ



10

ይከበርለታል የሚለውን ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ የቀረበው አቤቱታ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የተስማማ ሲሆን የውሳኔ ሃሳቡ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንድቀርብ በሙሉ ድምጽ ተስማምቷል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው ክርክር የተነሳበት ቤትና ቤቱ የተሰራበት ቦታ አመልካች ከእናቷ በውርስ ተላልፎላቸው ያገኙት መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪ ግን በቤቱ እና በቦታው ላይ መብት እንደሌላቸው በፌደራል ፍ/ቤቶች በማስረጃ ተጣርቶ ተወስኗል፡፡

ምክርቤቱም የደረሰበት መደምደሚያ አመልካች በዋናው ክርክር የፍርድ ባለመብት በመሆን እንደ ፍርዱ እንዲፈጸምላቸው ለፍርድ አፈጻጸም መምሪያ አመልክተው እንደ ፍርዱ ከተፈጸመላቸው በኋላ በተጠሪ ቅሬታ አቅራቢነት በየደረጃው የሚገኙ የፌደራል ፍ/ቤቶች ከፍርዱ ውጪ የሰጡት የአፈጻጸም ትዕዛዝና ውሳኔ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በዋናው ፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ንብረት በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ እንዲያጡ ያገረገበት ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውንና ዋስትና ያገኘውን የዜጎች የንብረት መብት የሚጥስ ስለሆነ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝና ውሳኔ ይህን ተከትሎም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.103454 የሰጠውና አመልካችን በአፈጻጸም ክርክር የንብረት ባለቤትነታቸውን ያሳጣው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲደርሰው ይደረግ፡፡

2. የፌዴራሉ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

3. የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ፡፡

5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባኤ

ሰኔ/ 2013 ዓ.ም

የመዝገብ ቁጥር 89/13

አመልካች፡- አቶ ሐጎስ አብርሃ

ተጠሪ፡- የጋምቤላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል።**

ውሳኔ

አመልካች በቀን 28/03/1999 ዓ.ም ለጋምቤላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በወ/ሮ ታደለች ታረቀኝ እና ጊታቸው ለማ ላይ በመሠረቱት ክስ በ1988 አንድ ሳር ክዳን ቤት 8 በ17 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ቤትና ቦታ በ1500 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ሸጠውልኝ እኔም ከተማ አስተዳደሩን ጠይቄ፣ በስሜ አድርጌና ልዩ ልዩ አትክልት ተክየ እየተጠቀምኩ እየኖርኩ እያለ አጥሩን በመስበር፣ እሳት በማቃጠል በንብረቴ ላይ ጉዳት ስላደረሱብኝና ቤቱንም ስለወሰዱብኝ እንዲመልሱልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀረበው ማስረጃ መሠረት ተከሳሾች የወሰዱትን ይዞታ መሬት ለአመልካች እንዲመለስ ወስኗል። በተጨማሪም ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች በአመልካች ንብረት ላይ ላደረሱት ጉዳት፣ የሞራል ካሳና የክርክር ወጪ እንዲከፍሉ ወስኗል። ይህም ውሳኔ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ተሻሽሎ በጠ/ፍ/ብ/ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 202787 ፀንቷል።

ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በመ.ቁ 01310 በቀን 18/05/2001 ዓ.ም የወሰነው ውሳኔ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 00818 በካሳው መጠን ብቻ ተሻሽሎ የተወሰነው

ውሳኔ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰ/ሰ/ችሎት በተሻሻለ በዐናው ውሳኔ አመልካች ለጋምቤላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአፈጻጸም ክስ አቅርበዋል። በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 32,150 (ሰላሳ ሁለት ሺ. አንድ መቶ አምሳ ብር) እንዲከፍሉ ወስኗል።

ይህም ውሳኔ ይግባኝ ተጠይቆበት የከፍተኛ ፍ/ቤቱ የካሳ መጠኑ ብር 13,568 (አሥራ ሦስት ሺ. አምስት መቶ ስልሳ ስምንት ብር) የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ወደ ብር 5,000 (አምስት ሺ. ብር) ዝቅ በማድረግ ሲወስኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለሰበር አያስቀርብም በማለት ወስኖ የነበረ መሆኑን መዝገብ ቁጥር 102787 ላይ ያለው የሰበር ውሳኔ ያሳያል።

በዚህ የሰበር ውሳኔ እንደተጠቀሰው አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ የስር ፍ/ቤት ቁጥሩና ቀኑ ተለይቶ በታወቀ የአፈጻጸም ውሳኔ ሳይሆን በደፈናው ተጠሪዎች ፍርድ ያረፈበትን ይዞታ አላስረከቡኝም በማለት ብቻ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ፍርዱ የተፈጸመ መሆንና ያለመሆኑን እንዲገለጽለትና ክርክር የተነሳበት ይዞታን የማን እንደሆነ ከከተማ ማዘጋጃ ቤት ጋር በመሆን አጣርቶ እንዲወስን በማለት የሰጠው ውሳኔ አመልካችን የሚጠቅም መሆኑን በመጠቆም አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል።

አመልካች በተደጋጋሚ ለስር ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም የቀረበው የአፈጻጸም መዝገብ ተመልክቶ የእኔ ሥልጣን አይደለም በማለት ለከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲላክ አድርጓል። የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ የስር ፍ/ቤት በእንደዚህ ዐይነት ጉዳይ ላይ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሊሰጠኝ አይችልም በማለት ጉዳዩን ራሱ እንዲያይ ለስር ፍ/ቤት ልኮለታል። አመልካች አሁንም ሊፈጸምላቸው ባለመቻሉ አስተዳደራዊ በሆነ መልኩ





ጭምር እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት ድረስ አቤቱታ አቅርበዋል።

አመልካች ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ ለጋምቤላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መብቱ እንዲከበርልኝ ክስ መስርቼ እንደ ክሱ እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ቢወሰንልኝም በፍርድ ያገኘሁትን መብት በአፈጻጸም ሳገኝ ባለመቻሌ ይህም ሕገ መንግሥታዊ መብት የሆነውን አንቀጽ 37 ፍትሕ የማግኘት መብት የጣሰ ስለሆነ ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል።

አጣሪ ጉባዔው የአመልካችን አቤቱታ መርምሯል። እንደመረመረውም የክስ አቤቱታው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ እንደ ክሱ የተወሰነ መሆኑን፣ በስር ፍ/ቤት ተከሳሽ የነበሩት ተከራካሪ ወገኖች በጉዳዩ ላይ እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ቢከራከሩም ውሳኔው አልተለወጠም። በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች እንደ ፍርዱ እንዲፈጸምላቸው መጀመሪያ ጉዳዩን ላየው ፍ/ቤት አመልክተዋል።

ነገር ግን ፍ/ቤቱ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ፍርዱን እንዲያስፈጽም ለበላይ የዞን ከፍ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል። አመልካችም በአፈጻጸሙ ክስ ላይ እስከ ሰበር ቅሬታ ቢያቀርቡም ሊፈጸምላቸው ስላልቻለ ጉባኤው ጉዳዩን ዐይቶ የሕገ መንግሥት መብታቸውን ያስከብርላቸው ዘንድ ጠይቀዋል። አመልካች ስነ ሥርዓታዊና አስተዳደራዊ በሆነ መልኩ መብታቸው ይከበርላቸው ዘንድ ለፍ/ቤቶችና በየደረጃው ላሉ ፍ/ቤቶች ፕሬዝዳንቶች አቤቱታ ሲያቀርቡ የቆዩ መሆኑን መዝገቡ ጋር የተያያዙት ሰነዶች ያስረዳሉ።

አመልካች ፍ/ቤቶቹ እንደ ፍርዱ ሊፈጽሙላቸው ባለመቻላቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ፕሬዝዳንቱ በቀን 17/03/08 ዓ.ም በቁጥር 00372/08 ለጋምቤላ ከተማ አስተዳደር መጀ/ደ/ፍ/ቤት በጻፉት ደብዳቤ በስር ፍ/ቤት የተወሰነና እስከ ፌዴራል ሰበር

ሰሚ ችሎት የሰናው ውሳኔ በመመልከት እንደ ፍርዱ ማስፈጸም እየተቻለ፣ ጉዳዩን ለረጅም ዓመታት ማጓተት የሚያስከትልን አፋጣኝ ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውንና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች የሚጻረር መሆኑን ተገንዝበችሁ ይህ የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንደደረሳችሁ ከሚመለከታቸው የጋምቤላ ከተማ 05 ቀበሌ መስ/ጽ/ቤት የፀጥታ አካላት እንዲሁም ከጋምቤላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ጋር በመሆንና ትዕዛዝ በመስጠት ፍርዱን እንድታስፈጽሙ ጠ/ፍ/ቤት በጥብቅ አዝዟል በሚል ትዕዛዝ ያስተላለፉ ቢሆንም የስር ፍ/ቤቱና የሚመለከታቸው አካላት እንደ ትዕዛዙ ሊፈጽሙ አልቻሉም።

ይህም ሊፈጸም ባለመቻሉ አመልካች ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ማመልከቻ መሠረት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የካቲት 14/2008 ዓ.ም በቁጥር ጠ/1-6-1/14028 ለጋምቤላ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 102787 ግንቦት 18 ቀን 2007 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እስከአሁን ድረስ ያልተፈጸመበት ምክንያት በአፋጣኝ በኩል መግለጫ እንዲቀርብ አሳስባለሁ በማለት ጠይቋል።

በዚህም ጥያቄ መሠረት የተሰጠ መልስ መኖሩን የሚያሣይ መዝገቡ ጋር የተያያዘ ማስረጃ የለም። ከላይ ያለው ትዕዛዝ ሊፈጸም ባለመቻሉ የጋምቤላ ከተማ መስ/ምክር ቤት ለጋምቤላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በቀን 03/04/09 በቁጥር 403/09 በተጻፈ ደብዳቤ ትዕዛዙን በመፈፀም የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ እንዲያከብሩና የአመልካችንም መብት እንዲጠብቁ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም በዚሁ መሠረት የተፈጸመ ነገር የለም። አመልካች ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ ፍርዱ ሊፈጸምላቸው ስላልቻለ ጉባኤው በትርጉም ሕገ መንግሥታዊ ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን እንዲያስከብርላቸው ጠይቀዋል።





ንዑስ ጉባኤው ስለጉዳዩ እንዲጣራ ባዘዘው መሠረት ውሳኔው ለምን እንዳልተፈጸመ የጋምቤላ ከተማ ፍ/ቤትን ጠይቀን ፍ/ቤቱም በቀን 22/09/2011 በቁጥር ጋከፍ/67/2011 ደብዳቤ ልኳል። በዚህ ደብዳቤ መሠረት ፍ/ቤቱ መፈጸም ያልቻለው በፍ/ቤቶቹ ውሳኔ ተጠሪዎች ካሳ ብቻ እንዲከፍሉ የተወሰነ ከመሆኑ ውጭ መሬትን በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ አለመኖሩን ጠቅሷል። በተጨማሪም የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ለምን እንዳልፈጸመ ጠይቆ መልስ የተሰጠ መሆኑና የተከራካሪዎች መዝገብ ሙሉ በሙሉ ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ የተዛወረ በመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ምንም ዓይነት መዝገብ የሌለ መሆኑን በመጥቀስ ልኳል።

ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ የቀረበው ሌላው ማስረጃ የጋምቤላ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02359/2011 በቀን 09/08/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በደብዳቤ ለከፍተኛ ፍ/ቤት የተላከ ማስረጃ ይገኝበታል። በዚህ መሠረት የመጀመሪያ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንደሚያስረዳው በውል የተፈጸመው የቤት ሽያጭ መኖሩ ተረጋግጦ ተጠሪዎችም በዚህ ውል መሠረት እንዲፈጽሙና የያዙትን ቦታ እንዲለቁ መወሰኑን ነው።

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ቢጠየቅም ስለቤቱና ቦታው የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተለወጠም። በይግባኝ የተሻሻለው የውሳኔ ክፍል በይዞታውና ንብረቱ ላይ ባደረሱት ጉዳት የተወሰነው የገንዘብ የካሳ ክፍያ ብቻ ነው። በሌላ በኩል በአፈጻጸም ወቅትና በደብዳቤም እንደተገለጸው ፍ/ቤቶቹ ቦታው የማን እንደሆነ ስላልተወሰነ ለማስፈጸም ያልቻሉ መሆኑን የወረዳው ፍ/ቤት ገልጿል።

ሆኖም ግን በዋና ጉባኤው በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት የጋምቤላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሥራ ኃላፊዎችና የጋምቤላ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ወደ ጉባኤው ቀርበው እንዲያስረዱ ተደርጎ ለጉባኤውም ቀርበው ካስረዱ በኋላ

ይዞታውን በተመለከተ ለአመልካች እንደሚገባ የተወሰነ ውሳኔ የለም ቢሉም እጃችን ላይ ያለው የወረዳው ፍ/ቤት የወሰነውን ውሳኔ ስናነብላቸው ይህ ውሳኔ ካለ መፈጸም እንችላለን ብለው ከሄዱ በኋላ በጽሑፍ በላኩት ሪፖርት የአፈጻጸም ችሎቱ በመደበኛ ችሎት ይዞታውን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል የሚል ሪፖርት በስልክ እና በደብዳቤ ያሳወቁ ሲሆን ከዚህ በኋላ ንዑስ ጉባኤው ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ተደጋጋሚ የስልክ መደዋወሎች ወደ ወረዳው ፍ/ቤት ተደርጎ በዋና ክርክር የተወሰነ ውሳኔ በአፈጻጸም ችሎት ሊሻር እንደማይችል ተግባብተን ውሳኔውን ለመፈጸም ግን መሰናክል የሆነባቸው የጋምቤላ ከተማ ከፍ/ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሀሳቡን በተመለከተ አከራክረው ሲወስኑ ይዞታውን በተመለከተ ያለው ውሳኔ መፅናት፡ መሻሻል ወይም መሻርን የሚገልፅ ውሳኔ ይሁን ትእዛዝ ያላስፈሩ በመሆኑ እና የመ/ደ/ፍ/ቤቱ አከራክሮ የወሰነበት መዝገብ ሊገኝ ባለመቻሉ ውሳኔው ሊፈጸም እንዳልቻለ አሳውቀውናል።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ፍ/ቤቶች በሚፈጽሙት የአጻጻፍ ስህተት ምክንያት የዜጎች መብት ሊጣስና ሳይፈጸም ሊቀር አይገባም፡፡ ስለሆነም ይዞታውን በተመለከተ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 00639/99 ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲለቁ ተብሎ የተወሰነ ውሳኔ ስላልተሻሻለና ስላልተሻረ ውሳኔው ሊፈጸም የሚገባው ነው።

በፍሬ ጉዳይ ክርክር ጊዜ ይዞታው ለአመልካች እንዲመለስ የተወሰነው ውሳኔ ክፍል ሀንቶ ባለበት ሁኔታ በአፈጻጸም ክርክር የፍርዱን ይዘት ለመለወጥ መሞከር በሕግ ከተፈቀደው አሠራር ውጭ ነው። አመልካችም በፍርድ ያገኙትን መብት በዚህ መልኩ በማጓተት ፍትሕ እንዲነፈጉ ማድረግ ተገቢ ያልሆነና ሕገ መንግሥቱ የቆመለትን የሕግ የበላይነት መርህ የሚጥስ አሠራር ነው።





ይህ ዐይነቱ የፍርድ አፈጻጸም ችግር የሕግ ተርጓሚውን ሚና ዋጋ የሚያሳጣና ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤት ላይ ያለውን አመኔታ የሚቀንስ ነው። የፍርድ ቤት ውሳኔ በተለያዩ ምክንያቶች ማጓተት ብሎም አለመፈጸም የፍርድ ቤቶችን ተግባርና ሥራ የሚጎዳ ነው። የፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጻሚ ካልሆነ ሕግ ሊከበር አይችልም። ይህን መሰል ተግባር ሲከሰትም የሕገ መንግሥቱ ዓላማ የሆነው የሕግ የበላይነት መርህ በእጅጉ ይጎዳል።

የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37/1/ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ደንግጓል። የአሁን አመልካች ጉዳያቸውን ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔ ተሰጥቶበታል። ይህን ውሳኔ ለማስፈጸም ለሚመለከተው ፍ/ቤትና የተለያዩ አካላት በተደጋጋሚ ቢጠየቁም እንደ ፍርዱ ሊፈጸምላቸው አልቻለም። የፍ/ቤቱ ውሳኔ ሊፈጸም ካልቻለ የአመልካች ሕገ መንግሥታዊ ፍትሕ የማግኘት መብት ተከብሯል ለማለት አይቻልም። የውሳኔው ተፈጻሚ አለመሆን ደግሞ በሕገ መንግሥቱ የተደነገገውን ፍትሕ የማግኘት መብት በመንግሥት አካል በሆኑት ፍ/ቤትና አስፈፃሚ አካላት ቸልተኝነት ምክንያት ነው።

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 13/1/ ላይ እንደተደነገገው ማንኛውም ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚ እና ሕግ አስፈጻሚ አካል በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩትን መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት እንዳለባቸው ተጠቅሷል። ይህ አሠራር ደግሞ የሕገ መንግሥቱ የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት መወጣት አለመቻላቸውን ያሳያል። ስለዚህ የከተማው ፍ/ቤቱ፡ ማዘጋጃ ቤትና የቀበሌ አስተዳደር ተቋማት በሕገ መንግሥቱ የተጣለባቸውን ኃላፊነት እየተወጡ አይደለም።

በዚህም መሠረት የአፈጻጸም መዝገቡ ፍሬአልባ በመሆኑ የአመልካች ሕገ መንግሥታዊ ፍትሕ የማግኘት መብት ተጥሷል። ስለዚህ ውሳኔው የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ የወሰነ መሆኑን የቀረበው መዝገብ ያስረዳል።

እኛም የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ከሕገ መንግሥቱ እና ከፍርድ ቤቶች ውሳኔ ጋር በማጣመር ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም አመልካች በቀን 28/03/2009 ዓ.ም ለጋምቤላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በወ/ሮ ታደለች ታረቀኝ እና ጓደኞቻቸው ለማ ላይ በንብረቴ ላይ ጉዳት ስላደረሱብኝና ቤቴንም ስለወሰዱብኝ እንዲመልሱልኝ በማለት ለመሠረቱት ክስ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀረበው ማስረጃ መሠረት ተከሳሾች የወሰዱትን ይዞታ መሬት ለአመልካች እንዲመልሱ እንዲሁም በአመልካች ንብረት ላይ ላደረሱት ጉዳት፡ የሞራል ካሳና የክርክር ወጪ እንዲከፍሉ ወስኗል።

ይህም ውሳኔ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ተሻሽሎ በጠ/ፍ/ሰ/ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 202787 ፀንቷል። በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች እንደ ፍርዱ እንዲፈጸምላቸው መጀመሪያ ጉዳዩን ላየው ፍ/ቤት ያመለከቱ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ፍርዱን እንዲያስፈጽም ለበላይ የዞን ከፍ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል። የስር ፍ/ቤት ራሱ የወሰነውን ውሳኔ የበላይ ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም መመለሱ የሚያሳየው አሠራሩ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ጋር የሚቃረን መሆኑን ነው።

ባጠቃላይ ከላይ ከጉዳዩ አመጣጥ የተረዳነው አመልካች በስር በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተወሰነላቸው ውሳኔ እንደፍርዱ እንዲፈጸምላቸው በአስተዳደራዊ መልኩና በሕጉ መሠረት ለሚመለከታቸው አካላት አቅርበው ውሳኔ ወይም የመዳኘት ዕድል አለማግኘታቸውን ነው። ይህ የሚያሳየው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37/1/ ስር ማንኛውም ሰው በፍርድ





ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው በሚል የተደነገገውን ድንጋጌ የተጣሰ መሆኑን ነው።

ስለሆነም የፌዴሬሽን ምክር ቤት የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ በጥልቀት እና በስፋት መርምሮ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ አግባብ መሆኑን ተቀብሎ በሙሉ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ 4ኛ ዓመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

<u>የመ/ቁ. 63/10</u>

አመልካች፡- ወ/ሮ አሚና አብዱልቃድር

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ከድር መሃመድ

2ኛ. ወ/ሮ በድሪያ መሃመድ

3ኛ. ወ/ሮ ብርሃን መሃመድ

4ኛ. ወ/ሮ ፋጡማ መሃመድ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ ሰሙኃ ቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ የወላጅ አባቴ ወራሽ መሆኔ ተረጋግጦ በመቀሌ ከተማ 02 ቀበሌ የሚገኘውን ቤት ኪራይ እንድሰበስብ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ማህበራዊ ፍ/ቤቱም ወራሽነታቸውን አረጋግጦ የቤት ኪራይ እንዲሰበስቡ የሚል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሰሜን ወረዳ ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪ ቤቱ የእርሱ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቢጠየቅም ማስረጃ ባለማቅረቡ አመልካች የቤቱን ኪራይ ከቀን 1/06/2000 ዓ.ም ጀምሮ ከተከራዮች እንዲሰበስቡ በማለት የማህበራዊ ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የመቀሌ ከተማ ማዕከላዊ ፍ/ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ባለቤትነት የአመልካች መሆን አለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታና ተከራካሪ ወገኖች በቤቱ ላይ ምን አይነት መብት እንዳላቸው ሳይታወቅ በደፈናው የቤት ኪራይ ለወ/ሮ አሚና ይከፈል ተብሎ የተወሰነው አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት ክርክር የተነሳበት ቤትና ቦታ የአመልካች አባት የሆኑት የአቶ አብዱልቃድር መሀመድ መሆኑ ስለተረጋገጠና አመልካችም ወራሽ መሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት የቀበሌ ማ/ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ይህም ውሳኔ ለክልሉ ሰበር ችሎት ቀርቦ የተፈፀመ የህግ ስህተት አለመኖሩ ተገልጾ ፀንቷል፡፡

በሌላ በኩል ሌሎች ሰዎች በዚሁ ቤት ላይ በሰሜን ወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ክስ መስርተዋል፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት አላግባብ ይዘዋል የሚል ነው፡፡ በክርክሩም ከሳሾች ለራሳቸው ካስወሰኑ በኋላ አመልካች ይግባኝ እያሉ እስከ ሰበር ቢከራከሩም ውሳኔው ጸንቷል፡፡

አመልካች ለቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የአፈጻጸም ክስ መስርተው ማ/ፍ/ቤቱም ለአመልካች የተወሰነ ሊፈፀም የሚችል የጸና ውሳኔ የለም በማለት ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ በዚህም ምክንያት ለይግባኝ ፍ/ቤቶች ቀርቦ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ አመልካች ይህን የአፈጻጸም ክርክር ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው ችሎቱም አመልካች ለሁለተኛ ጊዜ በሌሎች ሰዎች ክስ ሲቀርብባቸው ጉዳዩ ቀድሞ ውሳኔ ያገኘ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 5 መሰረት ተቃውሞ ማቅረብ ሲኖርባቸው ይህን ሳላላደረጉ የሁለተኛው ውሳኔ ሊሻር አይገባውም በማለት ወስኗል፡፡ ውሳኔውም ለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ቢቀርብም የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም በማለት ተወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ለጉባዔው ያቀረቡት ጥያቄ ከተጠሪዎች ጋር በነበረኝ የንብረት ክርክር በፍ/ቤቶች ባለመብት መሆኔ ተወስኖልኝ ሳለ ፍርዱ ሳይሻር በአፈጻጸም ወቅት የሚፈፀም ውሳኔ የለም በማለት ያስተላለፉት ውሳኔ ህገ መንግስታዊ መብቱ የሆነውን አንቀጽ 13፣ 40 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 እና 37 ስለሚቃረን ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ክርክሮች ተካሂደዋል፡፡ በመጀመሪያው ክርክር አመልካች የቤቱ ባለቤት ለሆኑት አባታቸው ህጋዊ ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ የቤት ኪራይ እንዲሰበስቡ ተወስኖላቸዋል፡፡ ክርክር በተነሳበት ንብረት ላይ በአመልካች ላይ በተመሰረተ ሌላ ክስ አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር በመሆን ቤቱን ሸጠው እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡ ይህም ውሳኔ በቤቱ ላይ ሌሎች ሰዎች መብት ያላቸው ስለሆነ አመልካች ብቸኛ ባለመብት ያለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ ይህ ሁለተኛ ክስ በከሳሾቹ ይግባኝ ባይነት አመልካች ቀድሞ ተወስኖ ያደረ መሆኑን መቃወሚያ ባለማቅረባቸው ቤቱ ለእሳቸው አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

ጉዳዩ በጉባኤው ፅ/ቤት በኩል እንዲጣራ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት በሁለተኛው ክርክር ወቅት የክሱ ይዘት ምን እንደሆነ ለማወቅና ለመረዳት ማስረጃ እንዲቀርብ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትን ተጠይቆ የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሰሜን ምድብ ችሎት ውሳኔ ያሳለፈበትን የመዝገብ ግልባጭ ተልኳል፡፡ በዚህ መዝገብ ላይ እንደተገለፀው አመልካች አንደኛ የአፈጻጸም ተከሳሽ የነበሩና የክሱ ይዘትም በመቀሌ ከተማ 02 ቀበሌ የሚገኘውን በሟች አቶ አብዱልቃድር መሃመድ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት አመልካች የሟችና የባለቤታቸው ወ/ሮ ለምለም ቀጥታ ተወላጅ በመሆናቸው ቤቱን ከ2ኛ ተከሳሽ ከድር ሃጂ መሃመድ ጋር ለብቻቸው መያዛቸው አግባብ አይደለም፣ የአያቶቻችን ንብረት የሆነውን ቤት የድርሻችንን ለመውሰድ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የውርስ ሃብት የግራቀኙ በመሆኑና አመልካችም ከሳሾች የድርሻቸውን እንዲወስዱ የተስማሙ ስለሆነ፣ 2ኛ የአፈጻጸም ተከሳሽ አቶ ከድር ሐጂ መሃመድ ያላግባብ ቤቱን ወደ አባታቸው ወደ አብዱልቃድር

መሃመድ ማህራቸው አግባብ ስላልሆነ ቤቱ ለስምንቱ ወራሾች እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ መዝገብ መረዳት እንደሚቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የግራ ቀኙ የውርስ ሃብት መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ክርክር ይግባኝ ተጠይቆበት አመልካች በቤቱ ላይ መብት እንደሌላቸው ተወስኗል፡፡ በዚህ ክርክርና ውሳኔ አመልካች ቀድሞ የተወሰነላቸውን መብት አጥተዋል፡፡

በመጀመሪያው ክርክር በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት ቤቱ በአመልካች አባት ስም የተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም የአባታቸው ወራሽ መሆናቸውን በፍ/ቤት አስወስነዋል፡፡ ይህ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ በሁለተኛው መዝገብ አመልካች የወራሽነት መብታቸውን አጥተዋል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የአፈጻጸም ክስ ላይ በይግባኝ ለክልሉ ሰበር ችሎት ቀርቦ ችሎቱም ጉዳዩ ቀድሞ የተወሰነ መሆኑ በተቃውሞ መልክ ሁለተኛው ክርክር በአመልካች በኩል ስላልተጠየቀ በማለት አመልካች መብታቸውን እንዲያጡ ተደርጓል፡፡ በሁለቱም ክርክር ወቅት ያሉት ግራ ቀኝ ወገኖች ዘመዳሞች መሆናቸው ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ውሳኔዎቹ ላይ በግልጽ አይቀመጥ እንጅ መጀመሪያ በሌሎች ሰዎች እጅ የነበረን ንብረት በህግ ወራሽነት አስወስነው ቤቱን ይዘው በዚሁ ቤት ላይ ሌላ ክርክር ሲነሳ ወራሽነታቸውን ቀድመው በፍርድ ማስወሰናቸው በክርክር ጊዜ አልቀረበም የሚለው አሳማኝ ነጥብ አይደለም፡፡ የክርክሩም ይዘት አንድ አይነት በመሆኑ መቃወሚያው አልተጠየቀም ማለት አይቻልም፡፡

ጉዳዩን ይበልጥ ለማጣራት ግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ጉባኤው ላይ በመቅረብ እንዲያስረዱ በታዘዘው መሰረት አመልካች ቀርበው እንደገለፁት ክርክር የተነሳበት በመቀሌ ከተማ 02 ቀበሌ የሚገኝ ቤት የውርስ ሃብት መሆኑን አመልካችም ከ8 ልጆች ውስጥ እርሳቸው አንድ ወራሽ መሆናቸውንና ቀድሞም ለእርሳቸው ብቻ ተወስኖላቸው የነበረ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ አመልካች በሰጡት ቃል ቤቱ የውርስ ሃብት መሆኑን ከማመን በተጨማሪ ለሁሉም 8 ወራሾች ተጠሪዎችን ጨምሮ ለመከፋፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሰሜን ወረዳ ፍ/ቤት የቀረበው ክስና ውሳኔ እንደሚያስረዳው ቤቱ የውርስ ሃብት መሆኑን ሟችም አመልካችን ጨምሮ 8 ልጆች ያላቸውና ሁሉም ልጆች መከፋፈል ያለባቸው መሆኑን ይገልጻል፡፡

የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የአመልካች አባት የነበረና በአባታቸውም ሞት ምክንያት ሁሉም ተወላጆች ባላቸው ህጋዊ መብት ምክንያት የቤቱ ወራሽ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም አግባብ ፍ/ቤቱ ሁሉንም ተወላጆች የቤቱ የጋራ ወራሽ ማድረግ ሲገባውና እንዲሁም የፀና ውሳኔ እያለ አመልካችን ከውርስ ንብረት እንዲነቀሉ ማድረጉ የአመልካችን ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ ነው፡፡

ለሁለተኛ ጊዜ በተደረገው ክርክር ቀድሞ ለአመልካች የተወሰነውንና አመልካች የፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ቤት እንዲያጡ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች በህገ መንግስቱ የተከበረላቸው የንብረት መብታቸው በህግ ከተደነገገው ውጭ የተነፈገ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም

የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባኤው የውሳኔ ሃሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት ቋሚ ኮሚቴው የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና የምክር ቤቱ ባለሙያዎች ያቀረቡትን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውንና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የአመልካችን የንብረት ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤውና ቋሚ ኮሚቴው የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የፍርድ ቤቶች ውሳኔ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) እና (2) ድንጋጌን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሻሩን አውቀው የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያስፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ አመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የፋ/ቁ.78/12

አመልካች፡- ፶ አለቃ ግዛው ደንቤ ሳልልህ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ

ተጠሪ፡- 1/ ኮሚቴ ኦፍ ኢንተለጀንስ ኤንድ ሴኪዩሪቲ ሰርቪስ ኦፍ አፍሪካ (CISSA)

2/ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

አድራሻ፡- አዲስ አበባ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለዉን የውሳኔ ሃሳብ አቅርቧል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ ለህገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዝያ 03 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ ከስራ ቅጥር ውል ጋር የተያያዘ ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ 2ኛ የስራ ክርክር ችሎት አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን በክርክሩ ተካፋይ ሆኗል፡፡

የጉዳዩ ይዘትም ከየካቲት 13 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ 1ኛ ተጠሪ በጥበቃ ስራ በወር 1,633 የአሜሪካ ዶላር (አንድ ሽህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሶስት የአሜሪካ ዶላር) ደመወዝና ተያያዥ ክፍያዎች እየከፈለኝ እስከ ጥር 24 ቀን 2006 ዓ.ም ከሰራው በኋላ ካለምንም ምክንያት 1ኛ ተጠሪ በህገ ወጥ መንገድ የስራ ውል ሲያቋርጥ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን በ$1,192 (አንድ ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ሁለት የአሜሪካ ዶላር) የከፈለኝ ሲሆን ሊከፈለኝ የሚገባ ወይም ቀንሶ ያስቀረብኝ በአጠቃላይ ብር 1,945,600 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት ሽህ ስድስት መቶ ብር) እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ ገብ በመሆን ባቀረበው አቤቱታ በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ ደርሶት ከተመለከተ በኋላ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠውን ከለላ በመግለጽ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ላይ የሚጠይቁትን ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች መከፈሉን ቀሪ የሚጠይቁትን ገንዘብ በተመለከተ ደግሞ ክሱ ተዘግቶ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማስማሚያ ክፍል በድርድር እንዲያልቅ ፍቃደኛ መሆኑን በጽሁፍ እንዳሳወቃቸው በመግለጽ፤ 1ኛ ተጠሪ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ነሀሴ 14 ቀን

2006 ዓ.ም ባደረገው የአስተናጋጅ አገር ስምምነት አንቀጽ 4(1) መሰረት በተሰጠው ከለላ ያለመከሰስ መብት ስላለው ክሱ ተቋርጦ ጉዳዩ በስምምነት እንዲያልቅ ጠይቋል፡፡

2ኛ ተጠሪ የመንግስት አስፈጻሚ አካላትን ተግባርና ሃላፊነት ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 15(4) እና 10 መሰረት በስምምነቱ የተካተቱ መብቶች የማስከበርና መከበራቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቱ ክሱን የማየት ስልጣን የለውም፤ ክሱ ቢቀጥል ከለላ ባለመስጠት ሃላፊነት ስለሚያስከትልና 2ኛ ተጠሪ ጥበቃ ለመስጠት ያለመቻሉን ስለሚያመለክት ክሱ እንዲዘጋ ሲል ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካቹ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን ክስ ተከትሎ 2ኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ባቀረበው አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ባደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት አንቀጽ 4 ላይ የድርጅቱ ቅጥር ግቢ፣ የንብረቶቹ፣ ገንዘብና ሀብቱ ያለ መደፈር መብት ከለላ እንደተሰጠው አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አመልካች የስራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በማለት ገንዘብ እንዲከፈላቸው ቢያቀርቡም 1ኛው ተጠሪ ገንዘቡን እንዲከፍል ሊወሰንበት እንደማይገባ ከላይ በተጠቀሰው ውል ላይ ከለላ ስለተሰጠው ቢወሰንበትም ሊፈጸም የማይችል እና መብታቸው በማስረጃ ቢረጋገጥ እንኳን 1ኛ ተጠሪ ባለው ከለላ በፍ/ቤት ውሳኔ መብት ሊያቋቁሙበት አይችሉም በማለት የአመልካች ክስ የክስ ምክንያት የሌለው ነው ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አያስቀርብም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ለጉባኤው ባቀረቡት ዝርዝር ቅሬታ 1ኛ ተጠሪ ራሱ ያወጣውንና የአሰሪና ሰራተኞችን አዋጅ በመጣስ ሊከፈለኝ የሚገባውን ጥቅማጥቅም ስለከለከለኝ ለ2ኛ ተጠሪ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 142 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ጉዳዩን በግልግል ክፍል በድርድር እንዲያይልኝ ያሉኝን ማስረጃዎች ከማመልከቻ ጋር አቅርቤ እንዲጣራ ለዲፕሎማቲክና መብቶች ከለላ ዳይሬክቶሬት ክፍል ተመርቶ በባለሙያዎች ከተመረመረ በኋላ 1ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ሁለት ጊዜ ተጠይቆ ለመደራደር ፈቃደኛ ባለመሆኑ ጉዳዩ ከአቅማቸው በላይ መሆኑን በቀን 13/06/07 ዓ.ም ለክቡር ሚኒስትሩ ካቢኔ ጽ/ቤት ቀርቧል፡፡ ካቢኔ ጽ/ቤቱ ሁኔታውን በፕሮቶኮል ክፍሉ በኩል ተጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ

እንዲቀርብ ስላዘዘ እንደገና ያሉኝን ማስረጃዎችና ማመልከቻ በማቅረብ ለ1ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ መጻፉን ሰምቼ የሚሰጠውን መልስ ብጠባበቅም መፍትሄ አላገኘሁም፡፡

ስለዚህ በ2ኛ ተጠሪ ለሚጻፉ ደብዳቤዎች 1ኛ ተጠሪ መልስ ባለመስጠቱ ጉዳዩን ሊዳኝ ለሚችልና ፍትህ ከፍርድ ቤት እንደማገኝ በማመን ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ባቀርብም ፍ/ቤቶች ጉዳዩ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ጉዳዩን ዘግተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በሕግ አግባብ የሚገባኝን ክፍያ ሊከፍለኝ ባለመቻሉ ጉዳዩ በ2ኛ ተጠሪ አደራዳሪነት እንዲያልቅ ቢጠየቅም ሊያልቅ ካለመቻሉም በላይ ፍርድ ቤቶችም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ያለመቻላቸው የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ፍትህ የማግኘት፣ 79(1-3) የዳኝነት ስልጣን እና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ስምምነት አንቀጽ 86(1) እና (2) ላይ የተደነገገውን የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት መርሆዎችን የሚጥስ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በፍርድ ቤት ከተሰጠው ውሳኔና አመልካች ተጥሷል በማለት ከጠቀሷቸው የሕገ መንግስት ድንጋጌዎች ጋር በመመርመር የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የምክርቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ እና በምክርቤቱ ባለሙያዎች አስተያየት ላይ ከተወያየ በኋላ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክርቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ምክርቤቱም አቤቱታውን ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር በማጣመር መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት ይህ የአመልካች ጉዳይ በ2ኛ ተጠሪ አደራዳሪነት በድርድር ክፍሉ እንዲታይ ስለመጠየቁና እየታየ ከሆነ ጉዳዩ የደረሰበት ደረጃና ውጤት እንዲገለፅ በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ተጠይቆ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ጠሪሠ23/1/10 በቀን 13 መስከረም 2010 በተፃፈ ደብዳቤ መልስ ተሰጥቷል፡፡

ከዚህም ባሻገር ቀድሞ ጉባኤው ባደረገው ውይይት የለያቸው ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ 2ኛ ተጠሪ የሆነው የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጠይቆ በቁጥር IRO23/9/1/09 በቀን 04/05/09 ዓ.ም በተጻፈ የተያዘውን አይነት ጉዳይ በፕሮቶኮል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄነራል የዲፕሎማቲክ መብት፣ ጥበቃና ከለላ ዳይሬክቶሬት ስራ ክፍል የሚታዩ መሆናቸውን፤ አለመግባባታቸውን በስራ ውላቸው እና በተጠሪዎች መካከል በተደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት በድርድር ለመፍታት ጥረት ይደረጋል ሲል 1ኛ ተጠሪ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ያደረገውን ስምምነት የእንግሊዝኛ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ቅጅ በማያያዝ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ ያለውን የቅጥር ውላቸውን እንዲያቀርቡ ተጠይቀው የመጀመሪያው አምስት ዓመታት ቅጥር ውል በቃል ስለነበር ለዚህ የማቀርበው ማስረጃ የለም በማለት ነገር ግን ከየካቲት 13 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ስለመቀጠራቸው በስንብት ደብዳቤው መገለጹን ጠቅሰው አቅርበዋል፡፡

አመልካች በአስረጅነት ያቀረቡት ማስረጃ ባይኖርም አለመግባባቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የግልግል ክፍል እንዲፈታ ጥያቄ አቅርበው ተጠሪ በፈቃደኛነት መልስ ሊሰጥ ባለመቻሉ እና ለግልግል ክፍሉ ጉዳዩ ከአቅሙ በላይ መሆኑ ስለተረጋገጠና የተሰጣቸውም መፍትሄ ስለሌለ በአማራጭ ወደ ፍ/ቤት አምርተው ከላይ የተመለከተው ውሳኔ ስለመወሰኑ በአቤቱታቸው ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ለፍ/ቤት በሰጠው መልስ 1ኛ ተጠሪ የፍ/ቤቱ ክስ እንዲዘጋና የአመልካች ክስ በውጪ ጉዳይ ሚ/ር ማስማሚያ ክፍል በድርድር እንዲያልቅ መጠየቁን ገልጿል፡፡ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃም በ2ኛ ተጠሪ በኩል ተልኳል፡፡

አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ሚያዝያ 7/2006 ዓ.ም ያቀረቡትን አቤቱታ ተከትሎ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ በፃፈው ደብዳቤ በዝርዝር የአመልካች አቤቱታና ቅሬታ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት በደብዳቤ ቁጥር AU2-9/2/06 በቀን 13 ጁላይ 2014 (እ.ኤ.አ) በተፃፈ ደብዳቤ ተጠይቋል፡፡ 1ኛ ተጠሪም በቀረበለት ጥያቄ መሰረት በአመልካች ጉዳይ ላይ ለ2ኛ ተጠሪ በደብዳቤ ቁጥር CISSA/2/15/2015/34 በዝርዝር መልስ ሰቷል፡፡ አመልካች 1ኛ ተጠሪ የሰጠው መልስ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በፕሮቶኮል ክፍሉ በኩል ግልባጩ እንደደረሳቸው በመግለፅ እንደገና ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት በማድረግ 2ኛ ተጠሪ በድጋሚ ለ1ኛ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ማብራርያ እንዲሰጥበት ወይም ተወካይ እንዲልክ መጠየቁን የሚገልፅ የደብዳቤ ግልባጭ ቀርቧል፡፡

2ኛ ተጠሪ ለጉባኤው በፃፈው በመጨረሻው ደብዳቤ አመልካች ሚያዝያ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ለ2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት መስርያ ቤቱ 1ኛ ተጠሪን በጉዳዩ ላይ ማብራርያ እንዲሰጥበት እ.ኤ.አ. ሐምሌ 31/2014 (በኢ.ት. አቆጣጠር ሃምሌ 24/2006 ዓ.ም) የጠየቀ ሲሆን 1ኛ ተጠሪም በጉዳዩ ላይ እ.ኤ.አ. ጥር 15/2015 (በኢት. አቆጣጠር ጥር 7/2007) መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በድጋሚ ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ጉዳያቸው በድርድር እንዲታይ ለ2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት 2ኛ ተጠሪ በድጋሚ እ.ኤ.አ. ሃምሌ 30/2015 (በኢ.ትዮ. አቆጣጠር ሃምሌ 23/2007 ዓ.ም) ለ1ኛ ተጠሪ በፃፈው ደብዳቤ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት 1ኛ ተጠሪ ተወካይ ወደ ዳይሬክቶሬቱ እንዲልኩና በተለመደው አሰራር ጉዳዩን መፍታት እንዲቻል ተጠይቆ እያለ አመልካች በዚህ መሀል ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰዳቸው የድርድር ጥያቄው የተቋረጠ መሆኑን በመግለፅ ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ ያለና እልባት ያላገኘ እንደሆነ፡

በቀጣይ ጉዳዩን እንደገና በማንሳት ተጠሪውን ወደ ድርድር መድረክ እንዲቀርብ በማድረግ ጉዳዩን ለመፍታት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልጸአል፡፡

አመልካች ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ በኩል ወደ ድርድር እንዲቀርብ የቀረበለትን ጥያቄ ለመቀበል ፍላጎት የለውም በማለት ያቅርቡ እንጂ አመልካች ጉዳያቸው በድርድር እንዲያልቅ ግንቦት 25/2007 ዓ.ም ለ2ኛ ተጠሪ አቅርበው 2ኛ ተጠሪም ይህንኑ ጥያቄ ለ1ኛ ተጠሪ ሃምሌ 23 ቀን 2007 ዓ.ም 1ኛ ተጠሪን ወደ ድርድር ጋብዞ የ1ኛ ተጠሪ የድርድር አቋም ሳይታወቅ አመልካች የጀመሩትን የድርድር ጥያቄ አቋርጠው ሰኔ 30 2007 ዓ.ም በፍርድ ቤት ክስ እንደመሰረቱ፡ መረዳት በመቻሉ በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሃሳብ ከማቅረብ በፊት 2ኛ ተጠሪ በሃፊው ደብዳቤ አግባብ ጉዳዩን በድርድር መፍታት እንዲችል ጥረት መደረጉን ምክር ቤቱ ተረድቷል፡፡

በመሰረቱ በ1ኛ ተጠሪና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት የዜጎች መብት እንዳይጣስ እና አለመግባባት ከተከሰተም በድርድር ለመጨረስ የተደረገው ስምምነት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(3) እና በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተለየ ደንብ ወይም መመሪያ እስካላወጣ ድረስ ክርክሩ በኢትዮጵያ ህግ ሊዳኝ እንደሚገባ የተገለፀውን ተክቶ የሚሰራ ነው፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 85 እና 86 የኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነት እና የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎች የዜጎችን እና የሀገሪቱን ጥቅምና ሉዓላዊነት ብቻ ሳይሆን መንግስታትንና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በሚኖር ግንኙነት የጋራ ጥቅምን፣ እኩልነትንና መሰል ጉዳዮች እንዲያራምድ ያስገድዳል፡፡ ኢትዮጵያም በምታደርጋቸው መሰል ተግባሮች በተመሳሳይ ከለላ መብትና ጥቅም በማግኘት የሀገሪቱን እና የዜጎችን ጥቅም እያረጋገጠች በመስራት ላይ የምትገኝበት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ነው፡፡ የሁለትዮሽ ስምምነት የሀገሪቱን ጥቅምና ሉዓላዊነት እንዲጥስ የማይፈቅድ፣ እንዳይጣስ የሚያስጠነቅቅ እና ተጥሶ ሲገኝ መብቶችን በስምምነት ለማስመለስ ማካተቱ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 86(1) የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት መርህ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ነገር ግን ይህ ሕገ መንግስታዊ መሰረት ያለው የሁለትዮሽ ስምምነት በሚፈቅደው መሰረት መንግስት የዜጎች መብት እንዳይጣስ የማድረግና አለመግባባቶች በሚፈጠሩ ጊዜም ሃላፊነቱን ወስዶ የመፍታት ግዴታ አለበት፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለፍርዱ መሰረት ያደረገው አመልካች የውጪ ድርጅት የሆነውን ተከሳሽ በመክሰስ መብታቸውን በማስረጃ በማረጋገጥ መብት ሊያቋቁሙበት አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ተከሳሽ ያለመከሰስ መብት አላቸው በሚል ነው፡፡

የ1ኛ ተጠሪ ያለመከሰስ መብት የመነጨው ደግሞ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ከተገባው የሁለትዮሽ ስምምነት ነው፤ ነገር ግን የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ለፍርድ ቤቱም ሆነ ለጉባኤው



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

በሰጠው መልስ መሰረት ጉዳዩን በድርድር መጨረስ የማይችል ከሆነ አመልካች ጉዳያቸውን ለፍርድ አካል በማቅረብ ፍርድ ወይም ውሳኔ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት ይኖራቸዋል፡፡

ስለዚህ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ከኢትዮጵያ ጋር ባደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት አለመግባባቶችን በስምምነት (በድርድር) መጨረስ እንደ አንድ የሙግት መፍቻ መንገድ የተቀመጠ ቢሆንም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ጉባኤው ለውጭ ጉዳይ ሚ/ር (ለ2ኛ ተጠሪ) ማስማሚያ ክፍል ጉዳዩ በድርድር እንዲያልቅ አቅጣጫ ቢሰጥበትም በ2ኛ ተጠሪ በኩል ሊፈፀም አልቻለም፡፡ በተጨማሪም የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከተው ሚኒስቴር ዴኤታም በጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝተው ጉዳዩን በድርድር ለመጨረስ አንድ እድል ለክፍሉ እንዲሰጥ በመጠየቃቸው ጉባኤው በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሃሳብ ከመስጠቱ በፊት ይህንኑ እድል ቢሰጥም በዚህ መልክ ሊፈፀም አለመቻሉን ምክር ቤቱ ተገንዝቧል፡፡

በመሆኑም አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያላቸውን ሕጋዊ መብት 2ኛ ተጠሪ በገባው ውል መሰረት በድርድር ማግኘት ወይም ማረጋገጥ ካልቻሉ ጉዳያቸውን ለዳኝነት አካል (ለፍርድ ቤቶች) በማቅረብ መብታቸውን የማስከበር ሕገ መንግስታዊ መብታቸው ሊጠበቅላቸው ይገባል፡፡ ከዚህ ቀደም ጉዳዩ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶችም ከላይ የተጠቀሰውን የውጭ ፖሊሲ እና የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት በማድረግ የድርድር ውጤቱ ሳይታወቅና በተለመደው አሰራር 2ኛ ተጠሪ አመልካችን እና 1ኛ ተጠሪን ለማደራደር አለመቻሉን ሳያረጋግጡ ወይም 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ለመደራደር ፍቃደኛ አለመሆኑ ሳይረጋገጥ በተለይም 2ኛ ተጠሪ በጊዜው ግራ ቀኙን ለማደራደር ፍቃደኝነቱን እየገለፀ ባለበት ሁኔታ የአመልካች ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብታቸው መጣሱን ማረጋገጥ ባይቻልም አሁን ግን የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተቋረጠውን ድርድር በማስቀጠልና ግራ ቀኙን ወደ ድርድር ጋብዞ የጀመረውን የድርድር ሂደት በመቀጠል የደረሰበትን ውጤት ለጉባኤው እንዲያሳውቅ ጉባኤው በፃፈው ደብዳቤና በስብሰባው ላይ ከተገኙት የሚኒስቴሩ ኃላፊዎች ጋር ስምምነት ላይ ቢደረስም የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ለጉዳዩ እልባት ባለመስጠቱ አመልካች ፍትህ ማግኘት አለመቻላቸው ሊረጋገጥ ችሏል፡፡

በመሰረቱ 1ኛ ተጠሪ የውጪ ድርጅት ሆኖ ከአመልካች ጋር ያለው ክርክር ከዲፕሎማቲክ መብትና ድርጊት ጋር የሚያያዝ ሳይሆን ጉዳዩ መደበኛ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ በውጪ ሀገር ድርጅቶች ወይም ዲፕሎማቲክ አካላት ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች ከዲፕሎማቲክ ስራና መብት ጋር ያልተገናኘ ነገር ግን መደበኛ የአሰሪና ሰራተኛ መብትን ብቻ በሚመለከት ክርክር ሲነሳ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ከድርጅቶቹ ጋር በገባው የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት ጉዳዩን በድርድር መፍታት ካልቻለ እንዲህ ዓይነት የአሰሪና ሰራተኛ መደበኛ ክርክርን ብቻ የሚመለከቱ ጉዳዮችን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ለማየት የሚያግዳቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነት ካለመኖሩም በላይ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

በሃገሪቱ ሕገ መንግስት መሰረት ሕግን መሰረት አድርገው የዜጎችን ሕገ መንግስታዊ መብቶች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታቸውን መወጣት የሚጠበቅባቸውና የእለት ተግባራቸው ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ የሚጠይቁትን ሕጋዊ መብት 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በገባው የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት በድርድር ሊያስጠብቅላቸው ባለመቻሉ እንዲሁም ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩን ለማየት አንችልም በማለታቸው የአመልካች ሕገ መንግስታዊ ፍትህ የማግኘት መብት የተጣሰ ስለሆነ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በማየት ውሳኔ ሊሰጡ ይገባል በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ትእዛዝ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ በምክር ቤቱ ተፈጻሚ እንዳይሆን የተወሰነ መሆኑን አውቆ ተገቢውን እንዲፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የፌዴራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 6ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

የመ/ቁጥር 720/15

መስከረም 29 ቀን 2016 ዓ.ም

ባይግባኝ አመልካች፡- አቶ አለማየሁ መኮንን

ተጠሪ፡- የምስራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መቆጣጠሪያ ድርጅት

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ11/09/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም የምስራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መቆጣጠሪያ ድርጅት ሊከፍሉኝ የሚገባውን የተለያዩ የደሞዝ፣ ጥቅማጥቅም፣ ውሎ አበል እና የመሳሰሉ ክፍያዎች እንዲከፈለኝ ለሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም እንዲሰጥበት አመልክቼ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የተከበረው ም/ቤት ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሲሆን ተገቢው ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም እንዲከፈለኝ የሚል ነው፡፡ የሥር አመልካች የአሁን ይግባኝ ባይ በምስራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መከላከያ ድርጅት ውስጥ በኤርክራፍት ኢንጅነርነት ተቀጥሬ ላገለገልኩባቸው አመታት ያልተከፈለኝ ደሞወዝ፣ የአመት ዕረፍት ክፍያ፣ የተለያዩ አበሎች እና ወጭዎች ብር 909,657.80 (ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ ሺህ ስድስት ሃምሳ ሰባት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም) እንዲከፈለኝ በማለት ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ መስርተዋል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት መልስ ሰጪ መልስ እንዲሰጥ ታዞ ድርጅቱ በ1969 ዓ.ም ከመንግስት ጋር ባደረገው ስምምነት ያለመከሰስ መብት ያለው እና ይህውም ስምምነት በ14/111991 ዓ.ም በተጻፈ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ደብዳቤ ስምምነቱ አሁንም የጸና በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክስን የማየት ስልጣን የሌለው እና የአሁን ይግባኝ ባይ አመልካች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አደራዳሪነት በስምምነት 536.10 ዶላር (አምስት መቶ ሰላሳ

ስድስት ከአስር ዶላር) የወሰደ ስለሆነ በድርድር ያለቀ ጉዳይ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ሁለቱን መቃወሚያዎች ከተመለከተ በኋላ የድርጅቱ ያለመከሰስ መብት በስምምነቱ አንቀጽ 11 ትርጉም መሰረት በ3ቱ የመንግስት አካላት እንጂ በግለሰቦች አይደለም በማለት በስምምነቱ ተከሳሹ ድርጅት ከመንግስት ባገኘው ያለመከሰስ መብት ምክንያት ከሳሽ በሕገ መንግስት የተሰጣቸውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚያሳጣ ከሕገ መንግስት በላይ የሆነ ህግ ወይም ስምምነት መኖር የለበትም፡፡

ጉዳዩ በድርድር አልቋል ለሚለው መቃወሚያ የአሁን ይግባኝ ባይ አምኖበት ያልፈረመ ከመሆኑ በተጨማሪ የደብዳቤ መጻጻፎች እንጂ በመደበኛ አካሄድ የተፈጸመ ድርድር ባለመሆኑና ተከሳሽ ለከሳሽ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንዲወስዱ ተጋብዘዋል ከማለት ውጪ አመልካች የአሁን ይግባኝ ባይ ተስማምተው ገንዘብ መውሰዳቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

ፍ/ቤቱ ሁለቱንም መቃወሚያዎች ውድቅ ካደረገ በኋላ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ድርጅት በአማራጭነት የፍሬ ነገር መልስ ባለማቅረቡ መብቱን በፍቃዱ እንደተወ ተቆጥሮ ያለፍሬ ነገር ክርክር የሥር ፍ/ቤት አመልካች የአሁን ይግባኝ ባይ የጠየቀውን 909,657.80 (ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ ሺህ ስድስት ሃምሳ ሰባት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም) ብር እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ድርጅቱ በፍ/ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ያስቀርባል በማለት ድርጅቱ አለም አቀፍ ድጅት በመሆኑ መንግስት ያለመከሰስ መብት ሰጥቶታል በማለት የስምምነቱ አንቀጽ 11(1) ከ3 የተለያዩ ተርጓሚ አካላት በግራ ቀኙ ተተርጉሞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጠቷል፡፡ የስምምነቱ አንቀጽ 11(1) በእንግሊዘኛው፡-

"The organization shall enjoy immunity from the criminal jurisdiction of the government. It shall shall enjoy immunity from its civil and administrative jurisdiction except insofar as the counsel of the organization has unvalued the immunity".

የሚል ሲሆን ከሶስቱም ተርጓሚ አካላት የቀረበው ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን ትርጉሞቹም ድርጅቱ በመንግስት የዳኝነት ስርዓት በወንጀል ያለመከሰስ መብት

አለው፡፡ እንዲሁም ድርጅቱ ያለመከሰስ መብቱን እስካልተወ ድረስ በመንግስት የዳኝነት ስርዓት በፍታብሔርም ሆነ በአስተዳደር ያለ መከሰስ መብት አለው፡፡የሚል ይዘት እንዳላቸው ተገልጧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ፍ/ቤቱ ድርጅቱ በውሉ መሰረት በመንግስት የዳኝነት ስርዓት ውስጥ ክስ ሊቀርብበት እንደማይችል ይህም ያለመከሰስ መብት በግለሰብ እና በመንግስት አካላት መሆኑን በመጥቀስ ብይን በመስጠት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረም አመልክቶ አለማቀፍ ስምምቶች ፍ/ቤቶች ማየት አይችሉም በማለት የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በዚህም ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፤ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አጣርቶ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በዚህም ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደሬሽን ም/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር ድርጅቱ በ1969 ዓ.ም ከመንግስት ጋር ባደረገው ስምምነት ያለመከሰስ መብት ያለው እና ይህውም ስምምነት በ14/111991 ዓ.ም በተጻፈ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ደብዳቤ ስምምነቱ አሁንም የጸና በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን የማየት ስልጣን የሌለው እና የአሁን ይግባኝ ባይ አመልካች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አደራዳሪነት በስምምነት 536.10 ዶላር (አምስት መቶ ሰላሳ ስድስት ከአስር ዶላር) የወሰደ ስለሆነ በድርድር ያለቀ ጉዳይ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ እንደተከራከሩ፡፡

የድርጅቱ ያለመከሰስ መብት በስምምነቱ አንቀጽ 11 ትርጉም መሰረት በ3ቱ የመንግስት አካላት ማለትም በሕግ አውጭው፣ በሕግ አስፈጻሚው እና በዳኝነት አካሉ እንጂ ግለሰቦችን ሊመለከት የሚችል አይደለም፡፡

በስምምነቱም ተከሳሹ ድርጅት ከመንግስት ባገኘው ያለመከሰስ መብት ምክንያት ከሳሽ በሕገ መንግስት የተሰጣቸውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚያሳጣ ከሕገ መንግስት በላይ የሆነ ህግ ወይም የውል ስምምነት ሊኖር አይገባም፡፡

ጉዳዩ በድርድር አልቋል ለሚለው ክርክርም የአሁን ይግባኝ ባይ አምኖበት ያልፈረመ ከመሆኑ በተጨማሪ የደብዳቤ መጻጻፎች እንጂ በመደበኛ አካሄድ በጋራ ቁጭ ብለው ቃለጉባኤ ተይዞ የድርድሩ ፎርም (አካሄድ) እንዴት እንደተካሄደ የሚታወቅ ድርድር

ባለመሆኑ እና ተከሳሽ ለከሳሽ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንዲወስዱ ተጋብዘዋል ከማለት ውጪ ለመጋበዛቸውም ሆነ ተስማምተው ገንዘብ መውሰዳቸውን የሚገልጽ አንድም ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ተገቢ ድርድር ነበረ ማለት አይቻልም፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባደረገው ክርክር መቃወሚያውን ከፍሬ ነገር ጋር በአማራጭነት አቅር መከራከር ሲገባው መቃወሚያ ብቻ አቅርቦ ፍሬ ነገር አለማቅረቡ ጉዳዩን እንዳመነ ከሚያስቆጥር በስተቀር ተገቢ የሆነ ሥነ ሥርዓትን ተከትሎ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት ተከራክሯል ለማለት እንደማይቻል ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡

ይግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤት የአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 337/96 ንዑስ ቁጥር 3ን በመጥቀስ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት ጋር የምታደርጋቸውን ስምምነቶች የሚደነግግ ደንብ በሚኒስትሮች ም/ቤት ማውጣት እንደምትችል የሚደነግግ ቢሆንም ይህ ደንብ እስከሚወጣ ድረስ ግን የአሰሪ እና ሰራተኛ ሕግ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ፍርድ ቤቶች ማከራከር እንደሚችሉ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ስለሆነም ይግባኝ ባይም ሆነ የበታች ፍ/ቤት ይህንን የሕግ ድንጋጌ ጠቅሶ አከራክሮ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢነት ያለው ነበር፡፡

በሌላ በኩል ኢሚኒቲ ማለት ምን ማለት ነው ? ኢሚኒቲ በየትኛው ሕግ ላይ ተግባራዊ ይደረጋል? የሚሉ ነጥቦች በደንብ መፈተሽ አለባቸው ከዚህ በመነሳት ወደ ነጥቦች ስንገባ ኢሚኒቲ ለሕዝብ ተወካዮች እና ለዲፕሎማቲክ ኮሚኒቲ አባላት የሚሰጥ ሲሆን የሕዝብ ተወካዮች አባላት ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው ሲጠረጠሩ እጅ ከፍንጅ ካልተያዙ በስተቀር ምክር ቤቱ በፍትህ ሚኒስተር ጠያቂነት ሲቀርብ ኢሚኒቲቸውን ካላነሳ በስተቀር ምርመራ አይደረግባቸውም፤አይታሰሩም አይጠየቁም፡፡ ኢሚኒቲ የሚሰጠውም የሕዝብ ተወካይ የሆኑ አባላት ሙሉ ጊዜአቸውን በስራ ላይ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን እና እንደ ሕዝብ ተወካይነታቸው ክብራቸው እንዲጠበቅ እና እንዳይጉላሉ ለመጠበቅ ሲባል ነው፡፡

ይህም ቢሆን አንድ የሕዝብ ተወካይ አባል ኢሚኒቲው ሊከላከልለት የሚችለው ወንጀል ሲፈጽም እንጅ ከፍንጅ ካልተያዘ ብቻ ነው፡፡ ይህም ኢሚኢቲ ሊከላከልለት የሚችለው በወንጀል ጉዳይ እንጂ በፍትሐብሔር እንዲሁም በአስተዳደር ሊሆን አይችልም በሀገራችን ያለው ተሞክሮም የሚያሳየን ይህንኑ ነው፡፡

የድፕሎማቲክ ኮሚኒቲም ቢሆኑ ኢሚኒቲ የሚሰጠው በተመደቡበት ሀገር ሀገራቸውን ወክለው ስለሚቀርቡ የየሀገሩን ሉአላዊነት ለማክበር እና ለማስከበር ሲባል የሚሰጥ ሆኖ

ግለሰቦችን ሳይሆን የሚያገለግሉትን ሀገር ክብር እና መብት ለማስጠበቅ ሲባል የሚሰጥ ኢሚኒቲ እንጂ ለግለሰቦች የተሰጠ ኢሚኒቲ ተብሎ ሊቆጠር የሚችል አይደለም፡፡

ለአውሮፓ ሕብረትም ሆነ ለተባበሩት መንግስታት ሰራተኞች የሚሰጠው ኢሚኒቲም ቢሆን የድርጅቱን ስራ ሲሰሩ መጉላላት፣ ያላግባብ ፍተሻ እና እስርን ለመከላከል የሚሰጥ መብት እና ክብር ለማስጠበቅ እንዲሁም በሆነ ባልሆነው እንዳይመረመሩ እና እንዳይታሰሩ የተሰጠ ኢሚኒቲ እንጂ ለግለሰቦች የተሰጠ ኢሚኒቲ ነው ተብሎ ሊቆጠር አይገባም፡፡

ባጠቃላይ ኢሚኒቲ የሚሰጠው አንድ መንግስት ወይም ከአንድ መንግስት በላይ ጋር በሚያደርጉት ስምምነት የሚሰጥ ኢሚኒቲ እንጂ ለቀጣሪ እና ለተቀጣሪ ሰራተኛ ብሎም ለግለሰብ በወንጀል፣ በየፍትሐብሔር እና በአስተዳደር ሕግ ላለመጠየቅ የሚሰጥ ኢሚኒቲ ሊሆን አይገባም፡፡

ይግባኝ ባይ ድርጅቱን ከማቋቋም ጀምሮ እስከ ማሳደግ፣ ከትውስት ሰራተኛነት እስከ ቋሚ ሰራተኛ በመሆን አይር መንገድን ትተው እድሜ ልክ አገልግለው በጡሮታ ሲገለሉ ለአንድ ሰራተኛ ሊደረግለት የሚገባውን መብት በመንፈግ በማይመለከተው የኢትዮጵያ መንግስት እና የምስራቅ አፍሪካ አምበጣ መቆጣጠሪያ ድርጅት ባደረጉት የኢሚኒቲ ስጦታ ግለሰብ ተቀጣሪ ሰራተኛ መብቱን የሚያጣበት አንዳች ምክንያት የለውም፡፡

የምስራቅ አፍሪካ አምበጣ መቆጣጠሪያ ድርጅት እና ሰራተኛው ያላቸው ግንኙነት የአሰሪ እና ሰራተኛነት ቀጥር ግንኙነት መብት እንጂ ያለመከሰስ ኢሚኒቲ መብት አይደለም፡፡

ይግባኝ ባይ በውጭ ጉዳይ ሚኒስተር በኩል ለመደራደር በተለያዩ ጊዜያት አቤቱታ ለፕሮቶኮል ዳይሬክቶሬት አመልክተው ብዙ ጥረት ቢያድርጉም ሕጋዊ የድርድር ስርዓት ተዘርግቶ በኩልነት ደረጃ መደራደር አልቻሉም፡፡ይህውም በተለያዩ ጊዜያት የተጻጻፉባቸውን ሰነዶች ማጣራት አድርገን እንዲደራደሩ ጥረት አድርገው እንዳልተሳካላቸው መረዳት ችለናል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን አከራክሮ ኢሚኒቲው ከመንግስት ጋር የተደረገ ስምምነት እንጂ ግለሰቡን የሚመለከት አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መረታዊ እና ሕገ መንግስታዊ ፍትህ የማግኘት መብትን የረጋገጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የምስራቅ አፍሪካ አምበጣ መቆጣጠሪያ ድርጅት የ87 አመት አዛውንት እድሜአቸውን በሙሉ ያገለገሉ ግለሰብን በማይመለከታቸው ኢሚኒቲ ምክንያት ያቀረቡትን ደሞወዝ፣ የአመት ዕረፍት ክፍያ፣ የተለያዩ አበሎች እና ወጭዎች ብር 909,657.80 (ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ ሺህ ስድስት ሃምሳ ሰባት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም) ጥያቄ እና ሕጋዊ ያልሆነ ክርክር በማንሳት ለብዙ አመታት በማገላታት ወለድ እና ኪሳራቸውን በወቅቱ ገበያ መሰረት ተሰልቶ መክፈል እንዳለበት ታምኗል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይግባኝ ባይ በማይመለከተው የኢሚኒቲ ጉዳይ ይመለከተዋል በማለት ትርጉም አያስፈልገውም በሚል የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ተሽሯል፡፡

ስለሆነም ኢሚኒቲው መንግስትን እንጂ ግለሰብን የሚመለከት ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

## ትዕዛዝ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በምክር ቤቱ ቀርቦ የጸደቀ ሲሆን በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም አስታውቃለሁ፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ቀርቦ የተሻረ መሆኑን እንዲያውቀው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. አቶ አለማየሁ መኮንን በይግባኝ ያቀረቡት አቤቱታ በምክር ቤቱ ቀርቦ በሙሉ ድምጽ የፀደቀ ስለሆነ በውሳኔው መሰረት ተከታትለው እንዲየስፈጽሙ ውሳኔው ይድረሳቸው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ. 84/12

አመልካች፡- ፍቃደ ስላሴ ሕንፃ ተቋራጭ

ተጠሪ፡- አሚዳድ ኃላ/የተ/የግ ማህበር

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

### ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 26/03/2009 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.114645 በቀን 25/01/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩም የውል ክርክርን ይመለከታል፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች በቀን 23/11/2006 ዓ.ም ያቀረቡት የክስ አቤቱታ ተጠሪ በዱከም ከተማ የእንጨት እና የብረት ስራ ፋብሪካ ህንፃ ለማሰራት ተስማምተን ውል ተፈርሟል፡፡ በስምምነቱም መሰረት አመልካች የውል ግዴታውን ለመወጣት የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ከግሎባል ኢንሹራንስ ገዝቶ አቅርቦ ስራውን ለመጀመር የሚያስፈልገውን አሟልቶ የግንባታ ቦታውን (ሳይት) እንዲያስርክቡት ቢጠይቅም ተጠሪ ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸውና በውሉም ስራው በ10 ቀናት ውስጥ እንደሚጀምር ቢገለፅም ተከሳሽ ለማስጀመር ፈቃደኛ ባለመሆን ለ8 ወራት ስራውን በማዘግየት ውሉን አፍርሰዋል፡፡ ውሉም በመፍረሱ የብር 438,350.02 /አራት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺ ሶስት መቶ ሀምሳ ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ ኪሳራ ስለደረሰበት ይህንን እንዲከፍላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ባቀረቡት የክስ መልስ በውላችን አንቀጽ 2 (ሐ) ላይ የተጠቀሰውን እና የውላችን አካል የሆነው የከተማ ልማት ሚኒስቴር ያወጣው /General condition of the contract/ አንቀጽ 67 ማንኛውም አለመግባባት በፍ/ቤት ሳይሆን በሽምግልና ኢንጂነሩ እንዲፈታ እና በኢንጂነሩ ውሳኔ ይግባኝ ሊቀርብ የሚችለው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሆነ የተደነገገ በመሆኑ ክሱ ለፍ/ቤት ሊቀርብ አይገባም የሚል ነው፡፡ አመልካች በዚህ መቃወሚያ ላይ መልስ ሲያቀርቡ የውሉ አጠቃላይ ሁኔታ እ.ኤ.አ በ1994 በስራ እና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የወጣ ነው፡፡ ይህ ሚኒስቴር አሁን የለም፡፡ አሁን ያለው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በውስጡ ይህን የግልግል ስራ የሚሰራ አካል የለም በሚል የተጠረ መቃወሚያ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ መዝገቡን በመመርመር ጉዳዩ በሽምግልና መሀንዲስ ሊታይ ይገባል በማለት በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ አያስቀርብም በማለት ዘግቶታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህ የፍ/ቤት ውሳኔ የሕገ መንግስት ጥበቃ የተደረገበትን ፍትህ የማግኘት መብቴን ጥሷል በማለት የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ጉባኤውን የጠየቁ ሲሆን ጉባኤው ጉዳዩን መርምሮ የፍ/ቤት ውሳኔው የአመልካችን ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለምክር ቤቱ በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በዋናነት ያነሱት ቅሬታም እ.ኤ.አ. በ1994 በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የወጣው ስታንዳርድ ስምምነት የተሻረ እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም የሽምግልና ስራ የማይሰራ ሆኖ ሳለ፤ መሀንዲሱም ሆነ ይግባኝ ሰሚው የሚኒስቴሩ መስሪያ ቤት የግልግል ዳኝነት ስራዉን እንዲሰሩ በሚኒስቴሩ መመሪያ ያልተፈቀደ እና በውሉ መሰረት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው ኢንጂነር ያልተመደበ ሆኖ ሳለ በፍርድ ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት መብቴን ስለሚፃረር የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጠኝ የሚል ነው፡፡

ጉባዔው በጽ/ቤቱ በኩል በጻፈው ደብዳቤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይሄንን ተግባር የሚሰራ አካል መኖር አለመኖሩን እና ውላቸውም አስገዳጅ መሆን አለመሆኑ በጉባኤው በኩል ተጨማሪ ማጣራት ተደርጓል፡፡ በዚህም ማጣራት ለከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በተጠቀሰው ሰነድ መሰረት በተቋሙ ውስጥ የግልግል ስራ ሊሰራ የሚችል የሽምግልና ኢንጂነር መኖር አለመኖሩ በደብዳቤ ቁጥር 2015/08 በ29/01/2012 በተጻፈ ደብዳቤ የተጠየቀ ቢሆንም ጉዳዩ የማይመለከታቸው በመሆኑ መረጃ ሊሰጡን እንደማይችሉ ገልጸውልናል፡፡በተመሳሳይ ለኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ቁጥጥር ስራዎች ኮርፖሬሽን ስለ ጉዳዩ በደብዳቤ እና በስልክ ቢጠየቁም እንደማይመለከታቸው በቃል መልስ መስጠታቸው ተረጋግጧል፡፡

በኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 79(1) ስር በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/4 ላይ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም በሕግ ካልተገለፀ በስተቀር ክስን ተቀብሎ ለማከራከር ስልጣን ያለው ፍ/ቤት ብቻ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ግን በዚሁ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37(1) እና 78(4) ላይ እንደተመለከተው በሕግ የዳኝነት ስልጣን የሚሰጣቸው አካላት ሊቋቋሙ እንደሚችሉ ይገልፃል፡፡ ከዚህ የዳኝነት አካል አንዱ በሰዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ከፍ/ቤቶች ውጭ እልባት እንዲያገኙ በስምምነት የሚወሰኑበት አግባብ ሲሆን ከእነዚህ ስምምነቶች መካከል በፍ/ብ/ሕ/ቁ/3325 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት በዘመድ ዳኛ የመዳኘት መብት ይሰጣል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ተዋዋዮቹ የውላቸው አካል ባደረጉት ሰነድ አንቀጽ 67 መሰረት የግልግል ዳኝነት ተግባር እንዲያከናውን ተመርጦ የነበረው የስራ እና ከተማ ልማት ሚኒስቴርና የሽምግልና ኢንጂነሩ ነበሩ፡፡ ይሕ ተቋም የግልግል ስራን መስራት ካቆመ ተዋዋዮቹ ጉዳያቸውን የት አቅርበው ዳኝነት ማግኘት ይችላሉ የሚለውን በተመለከተ በፍትሐብሔር ሕጉ በዘመድ ዳኛ ስለመዳኘት በሚለው ስር የተቀመጡትን የሕግ ድንጋጌዎች በመተርጎም ሊመለስ የሚችል ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ የስራ እና ከተማ ልማት ሚኒስቴር መፍረሱን እና የግልግል ስራም እንደማይሰራ አጥብቀው ሲከራከሩ መምጣታቸውን የመዝገቡ ሒደት ያስረዳል፡፡

ጉባኤውም በመዝገቡ ላይ ተጨማሪ ማጣራት ባደረገበት ወቅት የተጠቀሰውን የግልግል ተግባር የሚያከናውን አካል ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ይኖረዋል ተብሎ የታሰበውን

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ቢጠየቅም ጉዳዩ የማይመለከታቸው መሆኑን ገልጸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በተዋዋዮች ስምምነት የተመረጠው የዘመድ ዳኛ ችሎታ ባጣ ጊዜ የሚመጣው ውጤት ምን ይሆናል የሚለው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 80722 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በፍታብሔር ሕጉ አንቀጽ 3337 መሰረት መልስ ሊያገኝ የሚገባ ስለመሆኑ እና በዚህም መሰረት ተዋዋይ ወገኖች የመረጡት የግልግል ዳኛ የግልግል ዳኝነት ተግባሩን ማከናወን ካቆመ በኃላ ሌላ የግልግል ዳኛ በስምምነት ሰይመው ጉዳያቸውን አቅርበው ማስወሰን የሚችሉ መሆኑን፣ ይሕን ለማድረግ ካልተስማሙ ግን ጉዳያቸውን ስልጣን ላለው መደበኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ሊያስወስኑ እንደሚችሉ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 37 በመጥቀስ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ጉዳያቸውን ሊያቀርቡ የሚችሉበት በውላቸው የተሰየመው የስራ እና ከተማ ልማት ሚኒስቴር መፍረሱ የሚታወቅ ሲሆን ይሕን ተቋም ተክቶ የግልግል ተግባሩን ሊያከናውን የሚችል አካል ስለመኖሩም ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በመዝገቡ ውስጥም በክርክር ሒደት በቀድሞው የሥራ እና ከተማ ልማት ሚኒስቴርም ሆነ አዲስ በተቋቋመው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ የግልግል ስራ ተክቶ የሚሰራ ተቋም አለ የሚል መከራከሪያ ስለመቅረቡ አያሳይም፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 መሰረት ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው በሚል ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ የመረጡት የግልግል ዳኝነት ተግባር የሚያከናውነው የስራ እና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የፈረሰ መሆኑ የሚታወቅ ስለሆነ ይሕም ማለት የግልግል ተግባሩን ማከናወን አቁሟል ማለት ነው፡፡ ተከራካሪዎቹም ሌላ የዘመድ ዳኛ በስምምነት መምረጣቸውን አልገለጹም፡፡ ስለሆነም አመልካች ጉዳያቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ዳኝነት የማግኘት መብት ያላቸው ሆኖ ሳለ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ስልጣኔ አይደለም በማለት መዝገቡን መዝጋቱ የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብት የሚጥስ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔው መዝገቡን በመመርመር ፣ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ከሚመለከታቸው ተቋማት በመጠየቅ አግባብነት ካላቸው የህገመንግስቱ ድንጋጌዎች እንዲሁም ሌሎች ህጎችና የሰበር ውሳኔዎችን አንፃር በመመርመር በፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብት የሚነካ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች አመልካቹ ያቀረቡትን ክስ ባለመቀበል የሰጡት ውሳኔ ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብታቸውን የጣሰ ስለሆነ ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ የሰጠ ስለሆነ ውሳኔውን አውቀው የአመልካቹን ክስ ተቀብለው ግራ ቀኙን አከራክረው እንዲወስኑ የምክር ቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ አምስተኛ ዓመት አንደኛ
መደበኛ ስብሰባ
መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ.ቁ. 60/10

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርቱኳን ኩማ ዘለቀ

ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ (2 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ይህ ጉዳይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 37 እና ዓንቀፅ 40(1) (2) የተደነገጉትን ፍትሕ የማግኘት እና የንብረት መብቶችን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሐሳብ በማቅረብ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የላከው ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች በግዥ ያገኙትን ቤት በተመለከተ (በአሁኑ ተጠሪዎች መካከል ይካሄድ በነበረው ክርክር) መብታቸውን ለማስከበር በመጀመሪያ ክርክሩን ላየው ለሰንዳፋ ወረዳ ፍርድ ቤት (አቤቱታ) ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በተጠሪዎች መካከል የነበረው የጋብቻ ክርክር ውሳኔ አላገኘም በሚል ምክንያት አቤቱታቸው ውድቅ በማድረጉ ክርክራቸውን ሊቀጥሉ እንዳልቻሉ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ይህንኑ ቤት በተመለከተ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንብረታቸውን ለማስመለስ በተጠሪዎች ላይ ለመሰረቱት የመፋለም ክስ ፍርድ ቤቱ አቤቱታቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ሊያዝ ወይም የንብረት ክርክሩን ከማየት ባሻገር የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች በተጠሪዎች መካከል በነበረው የባልና የሚስት ይረጋገጥልን ክስ ጣልቃ ገብተው ነበር በማለት ይህንኑ ውሳኔ ተቃውመው ሳያሽሩ አዲስ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ አመልካች ቤቱን በተመለከተ በፍርድ ቤቶች ተከራክረው መብታቸውን እንዳያስከብሩና ፍትሕን እንዳያገኙ ያደረገ ውሳኔዎች መሆናቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ...ስለዚህ በጉዳዩ ላይ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት ዓንቀፅ

37 ፍትሕ የማግኘት እና 40 ንኡስ ዓንቀፅ 1 እና 2 የንብረት መብቶች ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 84 ንኡስ ዓንቀፅ 1 እና በአዋጅ ቁጥር 798/2005 ዓንቀፅ 3 ንኡስ ዓንቀፅ 1 መሰረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሓሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት

አመልካች የመፋለም ክስ ያቀረቡት አስቀድሞ በተሰጠ ውሳኔ ለ1ኛ ተጠሪ በተላለፈ ቤት ነው፡፡ ቀድሞ ባደረጉት ክርክር አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብተው መከራከራቸውንና በተደረገውም ክርክር ጉዳዩ ውሳኔ አግኝቶ ፍርዱም መፈፀሙን አመልካች ገልፀዋል፡፡ አስቀድሞ ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ስልጣን ሳይኖረው የሰጠው ውሳኔ ነው የሚሉ ከሆነ አመልካች ሕጉ ባስቀመጠው አግባብ ስነ ስርዓቱን ተከትለው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረብ መብታቸውን ከሚያስከብሩ በቀር አስቀድሞ የተሰጠ ውሳኔ ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ክስ ማቅረብ የሕግም ሆነ የስነ ስርዓት ድጋፍ የለውም..." በማለት የፌ.መ.ደ. ፍ/ቤት የአመልካችን የመፋለም ክስ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ይህ ብይን/ውሳኔ በይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤቶች እንዲፀና ተደርጓል፡፡

ፍርድ ቤቱ የአመልካችን የመፋለም ክስ አቤቱታ ውድቅ ለማድረግ በምክንያትነት የጠቀሰው ክስ የቀረበበት ጉዳይ አስቀድሞ በተሰጠ ውሳኔ ፍፃሜ ያገኘ ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ አይቻልም በማለት ሲሆን ይህ አስቀድሞ የተሰጠ የተባለው በኦሮሚያ ክልል፣ በሰሜን ሸዋ ዞን፣ በሰንዳፋ/በረህ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 04956 በአሁኑ ተጠሪዎች መካከል በነበረውና የአሁኑ አመልካች በጣልቃ ገብነት ቀርበው በተከራከሩበት መዝገብ ቀን 18/04/2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠውና በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ

ቤት በመዝ/ቁጥር 16365 ቀን 26/07/2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እንዲፀና የተደረገው ብይን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡

በዚህ ብይን/ውሳኔ የወረዳ ፍርድ ቤቱ የአሁኑ አመልካች የንብረት መብታቸውን ለማስከበር ለወደፊቱ ሊኖራቸው የሚችለውን አቤቱታ የማቅረብ መብት በመጠበቅ ያቀረቡትን የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ሓተታ ዘምክንያት "...የጣልቃ ገቧ አቤቱታ ይህ ተከሳሽ (የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ አቶ መስፍን ገ/መድህን) ከከሳሿ (የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ) ጋር ያፈራውን ንብረት እንዲያካፍል ለማድረግ የቀረበ ክርክር መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳው ስለሆነ ጣልቃ ገቧን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 418(1) እና 419(1) በሚያዘው መሰረት ከጣልቃ ገብነት አውጥተን የባልና ሚስት ንብረት ሲካፈል መብቷን የሚጋፋ ከሆነ ልትቀርብ ትችላለች እንጂ የቤተሰብ ጉባኤ ሽማግሌዎች የዕርቅ ውጤት ታውቆ ትዳራቸው ሳይፈርስ ልትቀርብ አይገባትም ብለን ብይን ሰጥተናል፡፡..." በማለት ሲሆን ይህ ብይን የአሁኑ አመልካች በቀጣይ መብታቸውን ለማስከበር ያላቸውን አቤቱታ የማቅረብ መብት የተጠበቀ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በዚሁ መሰረትም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 25/88 ዓንቀፅ 5(2) እና በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁ. 9 እንደተደነገገው መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት እንዲሁም ለክርክር መነሻ የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚገኝበት ቦታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት በአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ያላግባብ ተያዞብኛ ያሉትና በአዲስ አበባ ከተማ፣ የካ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 10፣ ልዩ ስሙ አንቆርጫ በሚባለው ቦታ የሚገኘው የቤት ቁጥሩ አዲስ የሆነው ቤት እንዲለቀቅላቸው ለመጠየቅ በአሁኗ 1ኛ ተጠሪና 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት አቶ ደሱ ሐደራ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሄር ችሎት የመፋለም ክስ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ከሳሽ (የአሁኑ አመልካች) አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቶ ባለበት ሁኔታ በተከሳሾች ላይ ክስ ማቅረባቸው የሕግም ሆነ የስነ ስርዓት ድጋፍ የሌለው ነው በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን የሰጠ ሲሆን ብይኑ እስከ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች እንዲፀና ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በግዥ ያገኙትን ቤት በተመለከተ መብታቸውን ለማስከበር መጀመሪያ ክርክሩ መብቴን ሊነካ ይችላል ብለው ባሰቡትና በኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በአሁኑ ተጠሪዎች መካከል ይካሄድ በነበረው ክርክር ጣልቃ ገብተው ለመከራከር ቢያመለክቱ የተያዘው

ክርክር ካለቀ በኋላ ከምትቀርቢ በቀር አሁን ባልቃ ገብተሽ መከራከር አትችዪም ተብለው አቤቱታቸው ውድቅ ስለተደረገባቸው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅና በፍ/ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት አቤቱታቸውን ቢያቀርቡም የፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ከዚህ ቀደም በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች ታይቶ ውሳኔ ተሰጥቶበት ፍርዱ የተፈፀመ ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን አናስተናግድም (አያስከስስም) በማለት አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ መስጠታቸው አመልካች የግል ንብረታቸውን የሚመለከተው ጉዳይ ለፍርድ ቤቶች አቅርበውና ተከራክረው መብታቸውን እንዳያስከብሩና ፍትሕን እንዳያገኙ ተደርገዋል፡፡

በመሆኑም በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 37 እና ዓንቀፅ 40 ንኡስ ዓንቀፅ 1 እና 2 ከተደነገጉት ፍትሕ የማግኘትና የንብረት መብቶች ጋር የሚጋጭ ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1 መሰረት ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የጸናው እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም የተባለው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የፌዴራሉ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የምክር ቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ አመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የፋ/ቁ.67/11

አመልካች ፡-አቶ ክፍለ ጽዮን በርሄ ገ/ማርያም

ተጠሪዎች ፡-1. አቶ ተሾመ አባመጋል

2. ወ/ሮ አይዳ ታደሰ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ቀርቦ ሊታይ የቻለው አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ለጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ክርክሩ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የተገኘ ቤት በውክልና ተሸጧል የተባለበት ውል የጥቅም ግጭት አለበት የሚል ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል መባሉን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 07 ፊለገ ሰላም የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ በሚገኝ ቤት ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሚያዚያ 17 ቀን 1989 ዓ.ም ተፈፀመ የተባለው ውል በሌለሁበትና ፈቃዴን ሳልሰጥ ስለተደረገ፣ የሽያጭ ውል መኖሩን ያወኩት በ2005 ዓ.ም በመሆኑ ይፍረስልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግላቸው መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ውል መኖሩን ያወኩት በ2005 ዓ.ም ነው የሚለው ክርክራቸው በማስረጃ ስላልተደገፈ ተቀባይነት አላገኘም በማለት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ አቤቱታቸውን ያላቀረቡ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ሲል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 244(2) (ሠ) ጠቅሶ ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡

ብይኑ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክርክር ተደርጎበት ሲፀና፤ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለሰበር አያስቀርብም ተብሏል፡፡

ጉባኤውም የአመልካችን አቤቱታ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 እና 40 አንጻር መርምሮ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴበሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ እና የምክር ቤቱን ባለሙያዎች አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

በዚሁ መሰረት አመልካች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍ/ቤት ውሳኔ የሕገ መንግስት ጥሰት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡እንደመረመረውም የአመልካች ቅሬታ ከተጠሪዎች ጋር የተደረገውን ክርክር የተመለከተው ፍ/ቤት የሰጠው ብይን የሕገ መንግስት ጥሰት ስለተፈፀመበት ትርጉም እንዲሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ከአመልካች አቤቱታና ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ መገቢያ ላይ መረዳት የተቻለው አመልካች የውክልና ስልጣን በቀን 08/03/87 ዓ.ም ለ1ኛ ተጠሪ ሰጥቼ ንብረቱን እንዲያስተዳድርልኝ ወከልኩት እንጂ በቀጥታ ለ2ኛ ተጠሪ ያደረኩት ሽያጭ የለም፡፡ ተጠሪዎች ባልና ሚስት በመሆናቸው ውክልናውን ሰበብ በማድረግ ቤቱን ከመያዛቸው በቀር አመልካች ውክልና እንደሰጠሁ ወደ ኤርትራ በመሄዴ እና የኢትዮ-ኤርትራ ግጭት በመፈጠሩ ወደ ኢትዮጵያ ባለመመለሴ ምክንያት 1ኛ ተጠሪ በውክልና ስልጣኑ እንደ መልካም አባት ማስተዳደር ሲገባው በህገ ወጥ ተግባር ለባለቤቱ በመሸጥና እንደእማኝ በመፈረም ያለአግባብ ለመበልፀግና የንብረት ባለቤት ለመሆን ያደረገው ጥረት ነው፡፡

በሌላ በኩል የህብረት ስራ ማህበሩን በመክሰስ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 130494 በቀረበ ክስ ዝውውር ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ የካቲት 25 ቀን 2005 ዓ.ም ማወቁ፣ 2ኛ ተጠሪ ባለቤቷን መወከሌንና ኤርትራ መሄዴን እያወቀች አሰጥታብኝ የነበረው የመጥፋት ውሳኔ መሻሩን፣ የሽያጭ ውሉ ሀሰተኛ ሰነድ እንጂ በአመልካች የተፈፀመ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ የፎረንሲክ ምርመራ ቢታዘዝም በዳኛ መቀየር ምክንያት ውጤቱ ሳይታወቅ ሂደቱ ተቋርጦ መወሰኑ፣ ከህብረት ስራ ማህበሩ ማስረጃ ሳይጠየቅ እና ምስክሮች ሳይደመጡ በቀረበ መቃወሚያ ብቻ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት እንደሌለው እና ክሱ በይርጋ እንደማይታገድ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 43600 በማይንቀሳቀስ ንብረት

ላይ የሚደረግ ክርክር ይርጋ የለውም ሲል ከሰጠው ውሳኔ ጋር ስለሚቃረን በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት የሚል ዝርዝር ቅሬታ አቅርበዋል፡፡

በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመፋለም ክስ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43600 አስገዳጅ ውሳኔ መስጠቱ ይታወቃል፡፡ ይህ አስገዳጅ

ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ ፍ/ቤቱ የአመልካችን ሁኔታና ማስረጃ ሳይመረምር በጠቅላላ ህግ የተደነገገውን የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1845ን በመጥቀስ በይርጋ በብይን መዝጋቱ ተገቢነት የለውም፡፡

ተወካይ በተወከለበት ጉዳይ ላይ የወካዩን ጥቅምና ፍላጎት ማስከበር ያለበት መሆኑን የእንደራሴነት ህግ ይደነግጋል፡፡ በዚህም ላይ ተወካይ የጥቅም ግጭት የሚያስነሱ ሁኔታዎችን ማስወገድ ያለበት መሆኑን የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 32241 ቅጽ 5 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ተወካይ ሲሆኑ፤ ለ2ኛ ተጠሪ ደግሞ ባል በመሆናቸው ተወካይ ከቤተሰቡ ጋር የሚያደርጋቸው ውሎች እና ሌሎች ተግባሮች የወካዩን ጥቅም ስለሚጎዳና የጥቅም ግጭት ስለሚኖርበት ይህንንም ለወካዩ ማሳወቅ ሲኖርበት ባለማሳወቁ ከቤተሰቡ ጋር የሚያደርገው ተግባር ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህንንም ፍ/ቤቱ ማጣራት ሲገባው ማለፉ ፍትሀዊነትን ያዛባል፡፡

አመልካች ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ የሄዱት ሁለቱ ሀገሮች መልካም ግንኙነት እያላቸው እንጅ በጦርነቱ ወቅት ወይም ከጦርነቱ በኋላ አይደለም፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 /2/ መሰረት ማንኛውም ሰው በጉልበቱ፣ በእውቀቱ ወይም በገንዘቡ የግል ንብረት የማፍራት መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ንብረት ያፈራ ሰው ደግሞ በሕግ አግባብ በንብረቱ የመጠቀም እና የማስተላለፍ መብት እንዳለው በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ አንድ ሰው በሕግ አግባብ ያፈራው የግል ንብረት መብቱን ሊያጣ የሚችለው ሕግ በዘረጋው ስርዓት ብቻ መሆን እንዳለበት የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም፡፡ በፍርድ ቤት ደረጃ በሚደረገው ክርክር ደግሞ አንድ ሰው የንብረት መብቱን ሊያጣ የሚችለው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ሥር የተመለከተው ፍትሕ የማግኘት መብቱን ባስከበረ ሁኔታና በሕግ በተዘረጋው ስርዓት መከላከያ እና ተገቢ ክርክር በማቅረብ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ሕጋዊ ሂደት ውጪ ግን አንድ ሰው የንብረት መብቱን ያጣ እንደሆነ በሕገ መንግስቱም

ሆነ በዝርዝር ሕጎች የተመለከተውን የሚጥስና ሕግን ያልተከተለ ድርጊት በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡

ይህ የፍ/ቤት ብይን የአመልካችን አቤቱታ በፍሬ ነገር ላይ በጥልቀት ሳይመረምርና ሳያጣራ ጠቅላላ የይርጋ ህግን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተሰጠ ፍርድ የአመልካችን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገውን የመሰማትና ትክክለኛ ውሳኔ የማግኘት እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተደነገገውን የንብረት መብት በመቃረን የተወሰነ ነው፡፡

በመሆኑም የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ትእዛዝ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን በምክር ቤቱ መወሰኑን አውቀው በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የፌዴራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የስራ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

የፌ/ም/መ/ቁ.020/08

አመልካች፡- አቶ ነጋሽ ዱባለ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ-መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2006 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.22719 የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብቴን የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ለአጣሪ ጉባኤ በማመልከታቸው ነው፡፡

የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2006 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 22719 የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብቴን የሚቃረን በመሆኑ የሕገመንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአቤቱታውም ፍሬ ነገር በአጭሩ ሲታይ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 17 ቀበሌ 20 በካርታ ቁጥር 32221 እና የባለቤትነት ደብተር ቁጥር 17/31791 የተመዘገበ ቁጥራቸው 1304፣ 1305 እና 1306 የሆኑ በአንድ ጣሪያና ግድግዳ ተያይዘው የተሰሩ ቤቶች የቀበሌው ጽ/ቤት ቤቱን አለአግባብ ለሶስት



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

11

ግለሰቦች አከራይቷል በማለት አመልካች በቀበሌው ጽ/ቤትና በተከራዮቹ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ መስርተው የስራና ከተማ ልማት ቢሮም ጣልቃ ገብቶ ተከራክሮ ፍ/ቤቱም አመልካችን የቤቱ ባለቤት /ባለመብት/ በማድረግ ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ወስኗል፡፡

ውሳኔው እስከ ጠቅላይ ፍ/ቤት ስለፀና አመልካችም የፍርድ አፈጻጸም ከፍተውና ቤቱን ተረክበው በእድሳት ላይ እያሉ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የቤቶቹን ካርታና ደብተር እንዲመክን በማድረጉ በፍርድ አፈጻጸም ተገደው የወጡት ግለሰቦችም ቤቱን በኃይል እንዲይዙባቸው ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት አመልካች ካርታው አለአግባብ መምክን የለበትም በማለት የሰነዱ ሕጋዊነት እንዲቀጥልና ሶስቱም ግለሰቦች ቤቱን እንዲለቁ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ እና በሃይል ቤቱን በያዙት ግለሰቦች ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ መስርተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የቤት ማረጋገጫ ሰነድ ያለ በቂ ምክንያት ሊሰረዝ አይገባም፣ ቤቱም በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ለመወረሱ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ አመልካች ቤቱን በፍርድ አፈጻጸም ከተረከቡ በኋላ ሰነዱን ማምከኑ አላግባብ ነው፣ እንዲሁም አመልካች ሌላ ቤት ነበረው የሚባለው ክርክር በወቅቱ አዋጅ ቁጥር 47/67 ስራ ላይ ሲውል እንጂ አሁን አይደለም በማለት ያመከነውን የቤት ሰነድ ካርታ ቁጥር 32221 እና የደብተር ቁ. 17/31791 በቤት ቁጥር 1304፣ 1305 እና 1306 በሆኑት ላይ ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል ሲል ወስኗል፡፡የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔውን ያፀደቀ ሲሆን የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ መስጠት፣ መከልከልና መሰረዝ በሕግ የተሰጠው ሥልጣን ስለሆነ አመልካች ይህንን የባለቤትነት ማረጋገጫ በእጁ ሳያስገባ ለፍ/ቤት ክስ ማቅረቡ አላግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል፡፡አመልካችም በሕገመንግስቱ የተመለከተው የንብረት ባለቤትነት መብቴ ተጥሶ በፍርድ አፈጻጸም የተረከብኩትና በአዋጅ ቁ.47/67 ያልተወረሰ ቤቴን ግለሰቦች በኃይል ይዘው እየተጠቀሙበት ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካችን አቤቱታና የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ እንደመረመርነው አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ቤቶች በፍርድ ባለመብት ሆነው በአፈጻጸም ከተረከቡ በኋላ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩንና የቤቶቹን ካርታ ማምከኑ እንዲሁም በፍርድ አፈጻጸም ተገደው የወጡ ግለሰቦች እንደገና ተመልሰው ቤቱን በኃይል መያዛቸው ከቀረበው የውሳኔ



10

ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሰነዱን ለመሠረዝ ምክንያት ያደረገው አመልካች ከአሁኑ ቤት ሌላ የራሱ የሆነ ቤት የነበረው ስለሆነ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 በትርፍነት ተወርሷል በማለት ነው፡፡ ክርክር የተነሳበት ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ያልተወረሰ ነው በማለት በፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሳይሻር የስራና ከተማ ልማት የቤቱን ሰነድ የማምከኑን አግባብነት መመርመሩተ ገቢ ይሆናል፡፡

አመልካች በቀበሌ ጽ/ቤትና ቤቱን ያለአግባብ ይዘዋል ብለው በመሠረቱባቸው ክስ ላይ የሥራና ከተማ ልማት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር ቢያመለክትም እስከ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ጥያቄው ውድቅ ሆኖበታል፡፡ ቤቱም ለአመልካች እንዲመለስ ሲወሰን በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም እስከ መጨረሻው ውሳኔው ፀድቆ የፍርድ አፈጻጸም ተከፍቶ እንደ ፍርዱ ተፈጽሞ እያለ ሰነዱ መምከኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ የህግ የበላይነት ከሚረጋገጥባቸው መንገዶች አንዱ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች ሲከበሩና ሲፈፀሙ ነው፡፡ ተጠሪ ከዚህ በተቃራኒ ክርክሩ በፍ/ቤት ውድቅ ሲደረግበት ስልጣኑን በመጠቀም የቤቱን ሠነድ ማምከኑ ፍርዱ እንዳይከበርና ተፈፃሚነት እንዳይኖረው አድርጓል፡፡በሌላ በኩል አመልካች አቤቱታውን እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ የቤትና አፈር ግብር እየከፈሉበት መሆኑን እንደ ተጨማሪ ማስረጃ የተለያዩ ደረሰኞችን ከአቤቱታው ጋር አያይዘው አቅርበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

1ኛ. ከ1968 እስከ 1984 ዓ.ም የከፈሉበት፣
2ኛ. ከ1987 እስከ 1992 ዓ.ም የከፈሉበት፣
3ኛ. ከ1997 እስከ 2006 ዓ.ም የከፈሉበትን የቤትና የቦታ ግብር ደረሰኞች ለማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ጉባኤው ቤቱ ከሚገኝበት ቦሌ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት አስፈላጊው ማጣራት እንዲደረግ ለጽ/ቤቱ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት የጉባኤው ፅ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 646/01/07 በቀን 17/02/2007 እና አጠጉ /634-06-08 በቀን 17/06/08 ዓ.ም ለጉባኤ ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ለቦሌ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የቤቱ ማህደር ታይቶ አስፈላጊው መረጃ እንዲሰጥ ጠይቋል፡፡ለቦሌ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ቦ/ክ/ከ/7836/08 በቀን 01/09/2008 ዓ.ም ለጉባኤው ጽ/ቤት በሰጠው መልስ በአመልካች ስም የቤት ካርታና የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ የተሰጠበትን ጊዜ የሚመለከት በማህደሩ ውስጥ የሌለ መሆኑንና በቁ 17/31791 የተመዘገበ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሁም የ1988 ዓ.ም የገበሩበት የግብር ደረሰኝ በማህደሩ ውስጥ የሚገኝ



9

መሆኑን፤ በአሁኑ ሰዓት የማያገለግልና አዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሌለው መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔው እንዳተተው የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የቤትባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ የመስጠትም ሆነ የመሰረዝ ሥልጣን አለው ቢልም ቢሮው የአንድ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ መሠረዝ የሚችለው በበቂ ምክንያት እንጂ ከያዝነው ጉዳይ አንጻር አመልካች በፍርድ ባለመብት በሆኑበት ጉዳይ ላይ ሊሆን አይችልም፡፡ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ አለአግባብ ሊነጠቅ ወይም ሊሰረዝ አይገባም፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40(8) መሰረት የግል ንብረት ባለቤትነት መብት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት ለመወሰድ የሚችልበት አግባብበ ግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የተጠሪ ድርጊት ከዚህ የህገ መንግስት ድንጋጌ በተቃራኒ የአመልካች የንብረት ባለቤትነት መብትን ያሳጣ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸው በፍርድ ተረጋግጦ በአፈፃፀምም ከተረከቡ በኋላ ፍርዱ ሳይሻር የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዱን ማምከኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40 የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገመንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ አመልካች ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ቤት ላይ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ክርክር አካሒደው በመጨረሻም ባለቤት መሆናቸው በፍርድ ተረጋግጦ እያለና በአፈፃፀምም በፍርድ ኃይል ከተረከቡ በኋላ ፍርዱ ሳይሻር የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በክርክሩ ቢረታም የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዱን በእራሱ ውሳኔ ማምከኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ1 የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚቃረን መሆኑን ተረድቷል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ መስሪያ ቤት ካርታ የማምከን እርምጃ ከዚህ የሕገ-መንግስት ድንጋጌ በተቃረነ ሁኔታ የአመልካችን የንብረት ባለቤትነት መብት ያሳጣ ሆኖ እያለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በፍርድ ባለመብት ሆነው



8

እያለ የስራና ከተማ ልማት ቢሮው የአመልካችን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ መሰረዙ በአግባቡ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል በሚል የተደነገገውን የሚቃረን በመሆኑ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር በሰ.መ.ቁ.22719 በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን እንዲያውቀው የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ እንዲደርሰው ይደረግ፡፡
2. የፌዴራሉ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

1398/2007 (15/2008)

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣1ኛ ዓመት፣3ኛ መደበኛ ስብሰባ

ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ.ም

አመልካቾች 1ኛ/ አቶ ታጠቅ ኃይለማርያም

2ኛ/ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ

ተጠሪ፦ አቶ አየለ ኃብተስላሴ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካቾች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

<u>ውሳኔ</u>

የዚህ ጉዳይ መነሻ የመንግሥት የንግድ ቤት ኪራይን የሚመለከት ሲሆን የአሁኑ 2ኛ አመልካች የሆነው የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ ለአሁኑ ተጠሪ አቶ አየለ ኃብተስላሴ ባከራየው የንግድ ቤት ተጠሪው በንግድ ቤቱ የንግድ መደብር (Business) ስራ ሲያካሂድበት ከቆዩ በኋላ የንግድ መደብር ስራውን ለአሁኑ 1ኛ አመልካች አቶ ታጠቅ ኃይለማርያም ማከራየታቸውን ተከትሎ የአሁኑ 2ኛ አመልካች የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ ከተጠሪው አቶ አየለ ሃብተስላሴ ጋር የነበረውን የንግድ ቤት ኪራይ ውል በማቋረጥ የተጠቀሰው የንግድ ቤት ለአሁኑ 1ኛአመልካች አቶ ታጠቅ ኃይለማርያም አሳልፎ በመስጠት አዲስ የንግድ ቤት ኪራይ ውል በመፈፀሙ ተጠሪው የአሁኑ አመልካቾች ያደረጉት የንግድ ቤት ኪራይ ውል ተሽሮ ቀደም ሲል የነበረውና በአሁኑ 2ኛ አመልካች የመንግስት ቤቶቸ ኤጀንሲና በተጠሪ መካከል የነበረው የንግድ ቤት ኪራይ ውል እንዲቀጥል እንዲወሰንላቸው በመጠየቅ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻነት የተጀመረ ክርክር ነው፡፡በክርክሩም የአሁን አመልካቾች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ሕገመንግስታዊ መብታችንን ይነካል በሚል ለሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ አቅርበው

ጉባኤውም ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ለምክርቤቱ የውሳኔ ሀሳብ አቅቧል፡፡

የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 የቤት ቁጥር 102/01 የሆነው የንግድ ቤት ባለቤት መንግስት ሲሆን ይህንን የንግድ ቤት በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚያስተዳድረው 2ኛ አመልካች ነው፡፡ ተጠሪው የንግድ መደብር (business) ባለቤት ሲሆን የንግድ ስራውን የሚከናወነው ከ2ኛው አመልካች በተከራየው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ቤት ቁጥሩ 102/01 በሆነው የንግድ ቤት ነበር፡፡ ተጠሪው ባለቤት የሆነበትን በተጠቀሰው የንግድ ቤት የሚካሔደውን የንግድ መደብር ኪራይ ውል ለ1ኛ አመልካች አከራይቷል፡፡ ተጠሪው የንግድ መደብሩን ለ1ኛ አመልካች ከማከራየቱ በፊት የንግድ መደብሩን ለ1ኛው አመልካች የሚያከራይ መሆኑን በቅድሚያ ለ2ኛው አመልካች ለማሳወቅ በ2ኛው አመልካች እና በተጠሪው መካከል በተደረገው ውል አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀጽ 4 የገባውን ግዴታ አላከበረም፡፡

2ኛው አመልካች ከተጠሪው ጋር የነበረውን የንግድ ቤት ኪራይ ውል በማቋረጥ በንግድ ማከናወኛው ቤት ውስጥ የንግድ ስራውን ከተጠሪ ጋር በገባው የንግድ መደብር ኪራይ ውል ምክንያት በማከናወን ላይ ከሚገኘው 1ኛ አመልካች ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል በመፈፀም የንግድ ቤት ኪራዩን ከተጠሪው ወደ 1ኛ አመልካች አስተላልፏል፡፡

በዚህ ፍሬ ነገር መነሻነት ተጠሪው ከሌሎች የዳኝነት ጥያቄዎቹ በተጨማሪ ወይም በዋናነት 2ኛው አመልካች ከተጠሪው ጋር የነበረውን የንግድ ቤት ኪራይ ውል በማቋረጥ የንግድ ቤት ኪራይ ውሉን ወደ 1ኛው አመልካች ያስተላለፈው መመሪያ ቁጥር 4/2004ን ያለ አግባብ በመተርጎም በመሆኑና ተጠሪ ለ1ኛው አመልካች ያከራየሁት የንግድ ቤቱን ሳይሆን ባለቤት የሆንኩበትን የንግድ መደብር ስለሆነ 2ኛው አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የንግድ ቤት ኪራይ ውል ያቋረጠው ያለአግባብ ነው ተብሎ እንዲሻር እና የንግድ ቤት ኪራይ ውሉን ከተጠሪ ጋር እንዲቀጥል ይወሰንልኝ በማለት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ ይመሰርታል፡፡



3

2ኛው አመልካች ተጠሪው የንግድ መደብሩን ለ1ኛው አመልካች ከማከራየቱ በፊት ስለ ሁኔታው ለ2ኛው አመልካች የማሳወቅ የውል ግዴታ እያለበት ይህንን የውል ግዴታውን በመተላለፍ የንግድ መደብሩን ለ1ኛው አመልካች ሲያከራይ የንግድ መደብር ስራ የሚያከናውንበትንም 2ኛ አመልካች የማስተዳድረውን የንግድ ቤት ይዞታ ለ1ኛ አመልካች ያስተላለፈ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 መሠረት በማስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ላይ የውል ጥሰት ተፈፅሞ በተገኘ ጊዜ እርምጃ ለመውሰድ በተሰጠኝ ህጋዊ ስልጣን የተፈፀመና አግባብነት ያለው ስለሆነ የተጠሪው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

1ኛው አመልካች በበኩሉ ከተጠሪው ጋር የንግድ መደብሩን ለመግዛት ድርድር የነበረው መሆኑንና ተጠሪው ከ2ኛው አመልካች ጋር በገባው የውል ግዴታ መሰረት የማሳወቅ ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን እንዲሁም በሁለት ቼኮች የንግድ መደብሩን ለመግዛት ለተጠሪው ክፍያ የፈፀመ መሆኑን በመጥቀስ የሚፈለግብኝ ቀሪ ክፍያ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ውሣኔ ተጠሪው 2ኛ አመልካችን የማሳወቅ ግዴታውን በመተላለፍ የንግድ ቤቱን ለ1ኛው አመልካች በማስተላለፍ ህግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 ለ2ኛው አመልካች ስልጣን የሰጠበትን አላማና ህጋዊ ውጤት አልጣሰም እና የንግድ መደብሩ ኪራይ ውል በባህሪው፣ በይዘቱና በህጋዊ ውጤቱ ከንግድ ቤት ኪራይ ውል በእጅጉ የተለየ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 31264 እና በሌሎች መዛግብት አንድ የንግድ መደብር ባለሀብት ባለቤት የሆነበትን የንግድ መደብር ለሌላ ሰው በማከራየቱ ምክንያት የንግድ ቤቱ ባለቤት የንግድ ቤት ኪራይ ውሉን ማቋረጥ የለበትም በማለት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ 2ኛ አመልካች ከተጠሪው ጋር የነበረውን የንግድ ቤት ኪራይ ውል በተናጠል የመሰረዝ ህጋዊ ስልጣን አለኝ በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት የመጨረሻ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ የአብላጫ ድምፅ በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማው አነስተኛው ድምፅ በበኩሉ ህግ አውጪው በአዋጅ ቁጥ 555/2000 አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 የውል ግዴታቸውን ያልተወጡ

ተከራዮችን በተመለከተ 2ኛው አመልካች በራሱ ውሣኔ የመሰለውን እርምጃ እንዲወስድ ስልጣን የሰጠው በበቂ የፖሊሲ ምክንያት ነው ተብሎ ይገመታል፡፡

በ1952 ዓ.ም የወጣው የንግድ ህግ ቁጥር 145 ንኡስ ቁጥር 1 ንግድን የማቀላጠፍ ዓላማ ላይ ብቻ ተመስርቶ ማንኛውም የንግድ መደብር ባለህብት ባለቤት የሆነበት የንግድ መደብር በኪራይ ለሶስተኛ ወገን ሲተላለፍ የንግድ መደብሩ ስራውን በሚያከናውንበት የንግድ ቤት ባለቤቶች ፈቃድ በመጠየቅ ሂደት መጓተቶች እንዳይፈጠሩ የሚከለክል ቢሆንም አዋጅ ቁጥር 555/2000 በሚወጣበት ጊዜ የነበረው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ህጋዊ ሁኔታዎች ተለውጠዋል፡፡ በመሆኑም የንግድ ህጉ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች መተርጎም ያለባቸው አሁን ካለው የሕገ መንግሥት ማዕቀፍ እና ሕገ መንግስቱን ተከትለው ከወጡት ህጎች በማጣጣም ነው፡፡ በዚህ አግባብ 2ኛው አመልካች ከመንግስት በአነስተኛ ዋጋ ቤቶችን እየተከራዩ ለሌላ ሶስተኛ ወገን በከፍተኛ ዋጋ መልሰው በሚያከራዩ ወይም ህገወጥ ተግባር በሚፈፅሙ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለው የህግ መሰረት አለው፡፡ የንግድ ህጉ በ1952 ዓ.ም ሲወጣ የነበረው ነባራዊ ሁኔታ ከመለወጡ ባሻገር ይህ የንግድ ህግ ቁጥር 145 ንዑስ ቁጥር 1 ባለበት ህግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 555/2000 2ኛው አመልካች ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ሰጥቶታል፡፡

በመሆኑም 2ኛው አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 እና በመመሪያው አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በተጠሪ ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የህግ መሰረት እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ በንግድ ህጉ ቁጥር 145 ንኡስ ቁጥር 1 እና በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 መካከል ልዩነት የሚታይ ቢሆን እንኳ ህግ አውጪው ለ2ኛ አመልካች የሰጠው ስልጣን ከንግድ ህጉ ይልቅ የገዥነት ባህሪ አለው፡፡ ለ2ኛው አመልካች በህግ የተሰጠውን ስልጣን በማንኛውም ሁኔታ የሚሸረሽር የህግ አተረጓጎምን በመከተል የንግድ ህጉ በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ ከአዋጅ ቁጥር 555/2000 በላይ የገዥነት ሚና እንዳለው መውሰድ የአዋጁን ይዘትና ዓላማ የሚያሳካ የአተረጓጎም ስርዓት አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ህግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 555/2000 ሊያሳካ ያሰበውን ዓላማ ሊያሳካ አይችልም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ከአብላጫው ውሳኔ ተለይቻለሁ በማለት የልዩነት ሀሳባቸውን አስፍረዋል፡፡



29

አመልካቾች ለህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ.ም ግንቦት 17 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ህገመንግስታዊ መብታችንን ይቃረናል በማለት የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ በዚሁ መነሻነት ጉባኤው ጉዳዩን በመመርመር የሚከተለውን የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ጉባኤው ጉዳዩን በመመርመር ሂደት 2ኛው ተጠሪ የመንግስት ንብረት የሆነውን የንግድ ቤት የማስተዳደር ህጋዊ ስልጣን ያለው መሆኑን፣ ተጠሪው ክርክር ባስነሳው የንግድ ቤት የሚያከናውነው የንግድ መደብር ባለቤት መሆኑን እና ይህንኑ የንግድ መደብሩን በኪራይ ለ1ኛው አመልካች ሲያስተላልፍ የንግድ ቤቱንም ጨምሮ ማከራየቱን፣ ተጠሪው ይህንን ተግባር የፈፀመው ከ2ኛው አመልካች ጋር በገባው ውል አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 4 በገባው ግዴታ መሠረት 2ኛውን አመልካች ሳያሳውቅም ቢሆን 2ኛው አመልካች በንግድ ህግ ቁጥር 145 ንኡስ ቁጥር 1 መሠረት የንግድ ቤቱን ኪራይ ለ1ኛ አመልካች በማስተላለፍ ከዚሁ የንግድ መደብሩን ተከራይቶ 2ኛው አመልካች በሚያስተዳድረው የንግድ ቤት ውስጥ የንግድ ስራውን ከሚያከናውነው 1ኛ አመልካች ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል መፈፀሙም ሆነ 1ኛ አመልካች ለተጠሪው ሊከፍል የተስማማውን ኪራይ ዋጋ በቀጥታ እንዲከፍለው በፍ/ህ/ቁ 2962/2 መሠረት ባለው መብት መስራቱ ከንግድ ህጉ ቁጥር 145 ንኡስ ቁጥር 1 እና ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2962 አላማ ጋር የሚስማማ መሆኑን እና 2ኛው አመልካች የሚያስተዳድረውን የንግድ ቤት የንግድ መደብሩ ባለሃብት ከሆነው ተጠሪ ላይ በመከራየት እየተገለገለበት ካለው 1ኛ አመልካች ጋር ውል ሲፈጽም የንግድ ቤቱን በውል ግዴታው መሠረት ሳያሳውቀው ወደ 1ኛው አመልካች ካስተላለፈው ተጠሪ ጋር የነበረውን የንግድ ቤት ኪራይ ውል የማቋረጡን ፍሬ ነገሮች በመነሻ ወስዷል፡፡

1. 2ኛው አመልካች በሕግ በተሰጠው ስልጣን የሚያስተዳድረውን የንግድ ቤት ከሱ የተከራየው የንግድ መደብር ባለቤት በንግድ ቤት ኪራይ ውል አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 4 በተመለከተው ግዴታው መሠረት የንግድ መደብሩን ለ1ኛው አመልካች በኪራይ ሲያስተላልፍ የንግድ ቤቱንም ይዞታ ለ2ኛ አመልካች ሳያሳውቅ በማስተላለፉ የውል ግዴታውን ያላከበረ የንግድ መደብሩን ተከራይቶ 2ኛ አመልካች በሚያስተዳድረው የንግድ ቤት ውስጥ የንግድ ስራውን በማከናወን ላይ ከሚገኘው 1ኛ አመልካች ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል መፈፀሙ ከንግድ ሕጉ ቁጥ



28

145 ንኡስ ቁጥር 1 አላማ ጋር የሚስማማ እና በፍተሐብሔር ህግ ቁጥ 2962 ንኡስ ቁጥር 2 በተጠበቀለት መብት በስራ ላይ ከማዋል ያለፈ ተግባር ፈጽሟል የሚያስብል ምክንያት የለም፡፡

2. 2ኛው አመልካች ህግ አውጪው ቀልጣፋ የንግድ ዝውውርን ለማበረታታት አላማ በ1952 ዓ.ም የወጣውን የንግድ ህግ ቁጥር 145 ንኡስ ቁጥር 1 ያልተሸረ መሆኑን እያወቀ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6 ንኡስ ቁጥር 3 2ኛው አመልካች የሚያስተዳድራቸው የንግድ ቤቶች በአነስተኛ ዋጋ በመከራየት ምንም እሴት ሳይጨምሩ ለ3ኛ ወገናት በማከራየት ተገቢ ያልሆነ ጥቅምን የሚያገኙ ህገ ወጦችን ለመከላከል ለ2ኛ አመልካች የተሰጠውን ስልጣን አሁን ካለው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ሁኔታ ጋር የማይስማማ ይልቁንም የስርዓቱ ዋና አደጋ ነው ተብሎ በግልጽ የተለየውን ኪራይ ሰብሳቢነት ከመድፈቅ አስተሳሰብና ከአስተሳሰቡም በመነጪ ፖሊሲ የወጣ ህግ በመሆኑ በ1952 ዓ.ም ከወጣው የንግድ ህግ ቁጥር 145 ንኡስ ቁጥር 1 ጋር ይጋጫል የሚባልበት አንዳች ምክንያት ቢኖር እንኳን ገዥነት እና የበላይነት ሊኖረው የሚገባው አዋጅ ቁጥ 555/2000 በመሆኑ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አናሳ ድምጽ የሀሳብ ልዩነት እንደተመለከተው ይህ ጉዳይ ከሀገሪቱ ሕገ መንግስት እና ከመንግስት ፖሊሲ ጋር ተጣጥሞ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 555/2000 የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ሰጥቷቸዋል የሚባሉ አስገዳጅ የህግ አተረጓጎሞችንም ሆነ ከንግድ ህግ ቁጥር 145 ንኡስ ቁጥር 1 ጋር በይዘቱም ሆነ በአላማው የበላይነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

3. በፍ/ቤቶች ውሳኔ እንደተመለከተው የንግድ መደብር የሚንቀሳቀስ ንብረት ሲሆን የንግድ መደብሩ የሚከናወንበት የንግድ ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው፡፡ አከራካሪ በሆነ ጉዳይ የንግድ መደብሩ ባለቤት ተጠሪ ሲሆኑ የንግድ ቤት ባለቤት መንግስት ነው፡፡ የንግድ ህግ ቁጥር 145/1 ድንጋጌ የንግድ መደብር ሽያጭና ኪራዩን ከማቀላጠፍ አልፎ የንግድ ቤት ባለቤትነትን በንግድ ቤት ውስጥ ስራውን ወደሚያከናውነው የንግድ መደብር ባለቤት ሃብትነት የማስተላለፍ ውጤት ያለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም በህጋዊም ሆነ ህጋዊ ባልሆነ ምክንያት የንግድ መደብሩ ባለቤት ስራውን ከሚያከናውንበት የንግድ ቤት ባለቤት ጋር ያለው የንግድ ቤት



27

ኪራይ ውል ሲቋረጥ የሚንቀሳቀስ ንብረት የሆነውን የንግድ መደብሩን ይዞ ሌላ የንግድ ቤት በመከራየት ስራውን ለማከናወን መብቱ በህግ የተሰጠው ነው፡፡

በተመሳሳይ ከማንኛውም የንግድ ቤት ባለቤት በንግድ ቤት ውስጥ የሚከናወነው የንግድ ስራ ባለቤትነትም ሆነ ይዞታ በንግድ መደብር ሽያጭም ሆነ ኪራይ ውል ሲለወጥ ባለቤት የሆነበትን የንግድ ቤት ለማስተዳደር እና ለንግድ ቤቱ የሚከፈለውን የኪራይ ዋጋ ለመቀበል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2962 ንኡስ ቁጥር 2 በተጠበቀለት መብት እና በንግድ ህግ ቁጥር 145 ንኡስ ቁጥር 1 በተጣለበት ግዴታ መሠረት የንግድ መደብሩን በመግዛት በባለቤትነት ከሚይዘው ወይም በመከራየት ባለይዞታው ካደረገው ሰው ጋር የንግድ ቤት ኪራይ የመዋዋል መብትና ግዴታ አለው፡፡ በዚሁ አግባብ 2ኛ አመልካች ከተጠሪው ጋር ያደረገው ለአንድ አመት የሚፀና የንግድ ቤት ኪራይ ውል ተጠሪው የውል ግዴታውን ባለመወጣቱም ሆነ በሌላ በማንኛውም ምክንያት በማቋረጥ በእርግጥ የንግድ ቤቱንም በእጁ አድርጎ የንግድ ሥራ በማካሄድ ላይ ካለው 1ኛ አመልካች ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል መዋዋሉ ተገቢነት ያለው ነው፡፡

4. ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ውሳኔ መንግስት የንግድ ቤቶችን ከ2ኛ አመልካች በአነስተኛ ዋጋ በመከራየት ምንም ዓይነት እሴት ሳይጨምሩ በንግድ መደብር ኪራይ ሽፋን ለሶስተኛ ወገኖች በማስተላለፍ ያልተገባ ጥቅም በማግኘት ላይ ያሉ ህገ ወጦችን ለመግታት በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 እና በመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ከህገ ወጦች ጋር የነበረውን ውል በማቋረጥ የተከራይ ተከራይ ከሆኑትና በእርግጥ የንግድ ስራ እያከናወኑበት ከሚገኙ በርካታ ዜጎች ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል በስፋት እየተደረገ ባለበት ሁኔታ 1ኛ አመልካች የዚሁ የመንግስት ፖሊሲ ተጠቃሚ እንዳይሆን በፍርድ ቤቱ አብላጫ ድምጽ የተሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 25 የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡
5. በተጨማሪም ህግ አውጪው የመንግስትን ፖሊሲ ለማስፈጸም ያወጣው አዋጅ ቁጥር 555/2000 መኖሩን እያወቀ በ1952 ዓ.ም የወጣውን የንግድ ህግ ቁጥር 145 ንኡስ



26

ቁጥር 1 ህግን በመተርጎም ሰበብ ተፈጻሚ እንዳይን ማድረጉ ከውጤት አንጻር ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50 ንኡስ አንቀጽ 3 ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

6. በፍርድ ቤት አብላጫ ድምጽ የተሰጠው ውሳኔ ህግ አውጪው የንግድ ሕጉ ቁጥር 145 ንዑስ ቁጥር 1 መኖሩን እያወቀ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 ግልጽ ድንጋጌ ለ2ኛው አመልካች የተሰጠውን ህጋዊ ስልጣን ባለመቀበል በ1952 ዓ.ም በወጣው የንግድ ህግ ሽፋን የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 79 ንኡስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡
7. በመጨረሻም የፍርድ ቤቱ አብላጫ ድምጽ ውሳኔ 2ኛው አመልካች የመንግስት ንብረት የሆኑትን የንግድ ቤቶች ለማስተዳደር የተሰጠውን ህጋዊ ስልጣን ከግምት ያላስገባ ወይም ያለመቀበል ውጤት ያለው በመሆኑ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለዚህ ጉዳዩ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሁሉ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ ተስማምቶ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84 ንኡስ አንቀጽ 3 ፊደል 'ለ' መሠረት የውሳኔ ሃሳቡ ለመጨረሻ ውሳኔ ወደ ፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲላክ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 2፣3፣4 እና 8 ላይ የተጠቀሰን የጉባዔው አባላት ከአብላጫው ድምጽ የተለየን ሲሆን የልዩነት ሃሳባችንን እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

ከአመልካቾች አቤቱታና አያይዘው ካቀረቧቸው ሰነዶች መረዳት እንደተቻለው ክርክር የተነሳው በመንግስት የንግድ ቤት ኪራይ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በውሳኔው እንደገለጸው ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ያከራዩት ህንጻውን ሳይሆን የንግድ መደብሩን በመሆኑ የንግድ መደብር ለማከራየት የሚደረግ ውል በባህርይው፣በይዘቱና በህጋዊ ውጤቱ የንግድ ማከናወኛ ቤት ለማከራየት ከሚደረግ ውል የተለየ ነው፡፡ ችሎቱ በመዝገቡ ላይ ተጠሪ የንግድ መደብራቸውን ለአንደኛ አመልካች በማከራየታቸው ምክንያት ሁለተኛ አመልካች የኪራይ ውሉን የማቋረጥ መብት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ እኛም የሰበር ችሎቱን አቋም ሙሉ በሙሉ የምንጋራው ነው፡፡

በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል ክርክር ያስነሳው ጉዳይ የንግድ ህጉ አንቀጽ 145 በመንግስት የንግድ ቤቶች ላይ የሚኖረውን የተፈጻሚነት ወሰን የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም የንግድ ህጉን አንቀጽ 145 እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 555/2000 በንጽጽር ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ የንግድ ህጉ አንቀጽ 145 እንደሚከተለው ይደነግጋል *"የማይንቀሳቀስ ንብረት ተከራይ የንግድ መደብሩን ለገዛው ሰው የቤት ኪራይ ውሉን አያስተላልፍም ወይም የተከራይ ተከራይ አድርጎ አያከራይም ወይም የኪራይ ውሉን ለማስተላለፍ ወይም የተከራይ ተከራይ አድርጎ ለማከራየት የባለቤቱ ፈቃድ ያስፈልጋል የሚሉ የውል ቃሎች ሁሉ ፍርስና ዋጋ የሌላቸው ናቸው"*፡፡

በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6(3) ኤጀንሲው በገቡት ውል መሠረት ግዴታቸውን የማይወጡ ተከራዮችን በራሱ ውሳኔ ለማስለቀቅ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳው የሕግ ጥያቄ የኤጀንሲው መመሪያ የንግድ ሕጉን አንቀጽ 145 ንኡስ አንቀጽ 1 የመሻር ኃይል አለው ወይስ የለውም የሚለው ነው፡፡ የንግድ ሕጉ በግልና በመንግሥት የቤት ኪራይ ውሎች መካከል ልዩነት ሳያደርግ በንግድ መደብሮች ዙሪያ የሚደረጉ የማስተላለፍ ስምምነቶች የባለቤቱን እውቅና ሳያስፈልግ በነጻነትና በተቀላጠፈ አኳኋን እንዲከናወኑ ደንግጓል፡፡ አዋጅ ቁጥር 555/2000 ከንግድ ሕጉ ዓላማ ጋር የሚጋጭበትን ሁኔታ ልናገኝ አልቻልንም፡፡ ሁለቱም ሕጎች ተስማምተው የሚጓዙ ናቸው፡፡ ግጭት አለ ከተባለ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ባወጣው መመሪያና በንግድ ሕጉ መካከል ነው፡፡ መመሪያ ደግሞ ሕግን የመሸርሸር ኃይል አልተሰጠውም፡፡ በተጨማሪም ኤጀንሲው የተከራይ ተከራዮችን ማስወጣት እንደማይችል በቆየው የንግድ ሕግ ውስጥ በግልጽ ሰፍሮ እያለ ባወጣው መመሪያ መሠረት ውል አፍርሳችኋል በማለት በሕግ ያልተሰጠውን ስልጣን ሊፈጽም አይችልም፡፡

የአብዛኛው ድምጽ የውሳኔ ሃሳብ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስነሳል በማለት ጉዳዩን ለምክር ቤቱ ቢያቀርብም ጉዳዩ የሕግ አተረጓጎምና አፈፃፀም እንጂ ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ሊያስነሳ የሚችል ነጥብ የለውም፡፡ በሰበር የተሰጠው ውሳኔም የቆየውን የጠቅላይ ፍ/ቤት ልምድ ተከትሎ የተደረገና አዲስ ነገር ባለመሆኑ የአብዛኛው የውሳኔ ሃሳብ ሊተች የሚገባ ነው፡፡



24

የብዙሃን የውሳኔ ሃሳብ ተከራዮች የንግድ መደብራቸው ኤጀንሲውን ሳያሳውቁ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፋቸው ሁል ጊዜም ያልተገባ ጥቅምን ለማግኘት አድርጎ መውሰዱም የተሳሳተ ነው፡፡ ጉዳዩን ከኪራይ ሰብሳቢነት ጋር አያይዞ ሕገ መንግስታዊ ትርጉም እንደሚያስፈልገው ጭብጥ አድርጎ ማቅረቡንም አልተቀበልነውም፡፡

ጉዳዩ ሕገ መንግስታዊ ትርጉም የሚያስነሳ ቢሆንም እንኳ ኤጀንሲው ሳያውቅ የንግድ መደብራቸውን ማስተላለፍ ማስቀም የሚቻለው በመመሪያ ሳይሆን የንግድ ሕጉን አንቀጽ 145 በአዋጅ በማሻሻል ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 ሥር የንግድ ሕጉን አንቀጽ 145 የሚያሻሽል ድንጋጌ የለም፡፡

በአብዛኛው ድምጽ ከተራ ቁጥር 1-7 የተዘረዘሩት ማብራሪያዎች የሕግ ክርክሮች እንጂ የነገሩን ሕገ መንግስታዊ ጭብጥነት የሚያመላክቱ አይደሉም፡፡ ሕጋዊ ክርክሮቹ ደግሞ በፍርድ ቤቶች ያለቁና ለአጣሪ ጉባዔው የይግባኝ ይግባኝ ሆነው ሊቀርቡ የማይችሉ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

ስለሆነም እኛ ስማችን በተራ ቁ. 2፣3፣4 እና 8 ላይ የተዘረዘረው የጉባኤው አባላት አቤቱታው የሕገ መንግስታዊነት ትርጉም ጥያቄ የማያስነሳ ነው በማለት የልዩነት ሃሳባችንን አቅርበናል፡የሚል ነው

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው የጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ችሎት በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሳኔ መንግስት የንግድ ቤቶችን ከ2ኛ አመልካች በአነስተኛ ዋጋ በመከራየት ምንም ዓይነት እሴት ሳይጨምሩ በንግድ መደብር ኪራይ ሽፋን ለሶስተኛ ወገኖች በማስተላለፍ ያልተገባ ጥቅም በማግኘት ላይ ያሉ ህገ ወጦችን ለመግታት በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 እና በመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ከህገ ወጦች ጋር የነበረውን ውል በማቋረጥ የተከራይ ተከራይ ከሆኑትና በእርግጥ የንግድ ስራ እያከናወኑበት ከሚገኙ በርካታ ዜጎች ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል በስፋት እየተደረገ ባለበት ሁኔታ 1ኛ አመልካች የዚሁ የመንግስት ፖሊሲ

ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግ በመሆኑ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 25 የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪም ፍርድቤቱ ህግ አውጪው የመንግስትን ፖሊሲ ለማስፈጸም ያወጣው አዋጅ ቁጥር 555/2000 መኖሩን እያወቀ በ1952 ዓ.ም የወጣውን የንግድ ህግ ቁጥር 145 ንኡስ ቁጥር 1 ህግን በመተርጎም ሰበብ በኃላ በወጣው በመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ለኤጀንሲው የተሰጠው ሥልጣን ተፈጻሚ እንዳይን ማድረጉ ከውጤት አንጻር ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50 ንኡስ አንቀጽ 3 ጋር የሚቃረን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በመጨረሻም ፍርድቤቱ የሰጠው ውሳኔ 2ኛው አመልካች የመንግስት ንብረት የሆኑትን የንግድ ቤቶች ለማስተዳደር የተሰጠውን ህጋዊ ስልጣን ከግምት ያላስገባ ወይም ያለመቀበል ውጤት ያለው መሆኑን ምክርቤቱ የተረዳ በመሆኑ ውሳኔው የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የሚቃረን ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በመሆኑም ምክርቤቱ አጣሪ ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በሚል ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተቀብሎ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገ መሆኑን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት፣እንዲደርሰው ይደረግ፡፡

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡

የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአመልካቾችም ይሰጥ፡፡

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ. 92/13

አመልካቾች፡- 1. አቶ ደረጀ ዘሪሁን

2. ወ/ሮ ትዕግስት ዘሪሁን

አድራሻ፡ አዲስ አበባ

ተጠሪ፡- አቶ ንጉሴ ደጉ ጥላሁን

አድራሻ፡ አዲስ አበባ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

### ውሳኔ

ጉዳዩ ለህገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በቀን 23/09/2009 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩም አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተጀመረ የንብረት ክርክር ነው፡፡

አመልካቾች ለፍ/ቤቱ ጽፈው ባቀረቡት ክስ በአመልካቾች አውራሽ እና በተጠሪ መካከል ነሐሴ 16 ቀን 1985 ዓ.ም በተደረገው ውል በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 17 ቀበሌ 20 የቤት ቁጥር 1800 ከሚገኘው ስፋቱ 212 ካ.ሜ ይዞታ ላይ 100 ካ.ሜ በሚሆን ቦታ ተጠሪ ለንግድ ስራ ቤት ሰርተው ለ10 አመት እንዲጠቀሙበት እና በየወሩ 1000 ብር ለመክፈል መስማማታቸው፣ ተጠሪ የ10 ዓመት የውል ጊዜው ሲያልቅ የቤቱን ግምት ወስደው ለመልቀቅ መስማማታቸው እና ተጠሪ ለሰሩት ቤት በአቅም ማነስ ምክንያት የአመልካቾች አውራሽ ግምቱን መክፈል ካልቻሉ ተጠሪ ለተጨማሪ 10 ዓመት በይዞታው እንዲጠቀሙና በመጨረሻ የሰሩትን ቤት አስረክበው ይዞታው ሊለቁ የተስማሙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካቾች አውራሽ ከጥር ወር 1987 ዓ.ም በህመም ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ተጠሪ በየወሩ መክፈል የሚጠበቅባቸው ክፍያ ሳይፈጽሙ እስከ ነሐሴ 15 ቀን 2005

ዓ.ም ለ20 ዓመት በይዞታው በመጠቀማቸው የውል ጊዜው ተጠናቅቋል በማለት ተጠሪ ይዞታውና ቤቱ እንዲያስረክቡን ይወስንልን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ጽሬው ባቀረቡት መልስ አመልካቾች ከዚህ በፊት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 176327 መጋቢት 8 ቀን 2003 ዓ.ም ክስ አቅርበው ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት የአመልካቾች ክስ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል ሲል ውሳኔ መስጠቱን፣ አመልካቾች ለ2ኛ ጊዜ በመ/ቁ 194849 ክስ አቅርበው ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት ክሱ የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶ ያደረ ነው ሲል በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው መሆኑን፣ ለ3ኛ ጊዜም በመ/ቁ 10389 ክስ አቅርበው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 5 መሰረት ውድቅ የተደረገ መሆኑና ይህ ክስ ለ4ኛ ጊዜ የቀረበ በመሆኑ ወጪና ኪሳራ ተከፍሎኝ ክሱ በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ይደረግልኝ ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም አመልካቾች በተጠሪ ላይ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ክሶች ከዚህ በፊት ሶስት ጊዜ አቅርበው በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ ከቀረበው መዝገብ አረጋግጠናል ሲል አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ለአራተኛ ጊዜ የቀረበ ሆኖ ተመሳሳይ ይዘትና ጭብጥ ያለው ክስ በመሆኑ የቀረበው ክስ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 244(2ለ) እና 245(2) መሰረት በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ መዝገቡ ዘግቷል፡፡

አመልካቾች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም በየደረጃው ስልጣን ላላቸው ፍ/ቤቶች የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡

አመልካቾች ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ የስር ፍ/ቤት ያቀረብነው ክስ በመመርመር ውሳኔ መስጠት ሲገባው ጉዳዩ ከዚህ በፊት ታይቷል በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 244(2ለ) እና 245(2) መሰረት ውድቅ አድርጎ መዝገቡን መዝጋቱ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠልን ፍትህ የማግኘት መብት ይጥሳል፤ ክርክር የተነሳበትን ይዞታና ቤት ተጠሪ መያዝ የቻሉት ከአውራሻችን ጋር ነሐሴ 16 ቀን 1985 ዓ.ም ባደረጉት ውል መሰረት ሲሆን ይህንን ውል ተጠሪን የዘለቄታ ባለሀብት አያደርግም ሲሉ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠልን ንብረት የማፍራት መብት ይጥሳል በማለት የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤም ጉዳዩን መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካቾች መጋቢት 8 ቀን 2003 ዓ.ም በመ/ቁ 176327 ለፍ/ቤቱ ያቀረቡት ክስ ይዘት ተጠሪ ከአውራሻችን ጋር በ1985 ዓ.ም ባደረጉት ውል መሰረት በአውራሻችን ስር ከሚገኘው ይዞታ ውስጥ 100 ካ.ሜ ቦታ ተረክበው ለድርጅት የሚሆን ቤት

በራሳቸው ወጪ ሰርተው እንዲጠቀሙ ለዚህም በወር 1000 ብር እንዲከፍሉ ቢሆንም በየወሩ ለመክፈል የተስማሙትን ክፍያ በማቋረጣቸው ውሉ በተጠሪ ጥፋት ምክንያት ፈርሷል በማለት ፍ/ቤቱ ተጠሪ ያልከፈሉትን ውዝፍ ክፍያ እንዲከፍሉ እና በአመልካቾች አውራሽ ይዞታ የተሰራው ቤትና ይዞታው ለቀው እንዲወጡ ዳኝነት ይሰጥልን የሚል ነው፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ አመልካቾች ያቀረቡት የውዝፍ ክፍያ ጥያቄ እና ተጠሪ እንደ ውሉ ባለመፈጸማቸው ይዞታውን እና ቤቱ እንዲመለስላቸው የጠየቁበት ክስ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ እንደ ውሉ ክፍያ መፈጸም ካቋረጡበት ከጥር ወር 1987 ዓ.ም በኋላ 16 ዓመት ያለፈው በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845፣1846 እና 1847 ጣምራ ንባብ መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል ሲል በአመልካቾች የተጠየቀው ዳኝነት ውድቅ አድርጓል፡፡

ከዚህ ውሳኔ በኋላ አመልካቾች በመ/ቁ.194849 በድጋሚ ውሉ ይፍረስልን የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርበው ጉዳዩ ከዚህ በፊት ታይቷል ተብሎ በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ተደርጓል፡፡

በመቀጠል አመልካቾች ነሐሴ 24 ቀን 2005 ዓ.ም በመ/ቁ. 10388 ባቀረቡት ክስ ተጠሪ በውሉ መሰረት በይዞታችን ለ20 ዓመት በመጠቀማቸው ይዞታችንና በይዞታችን የገነቡት ቤት ለቀው ይውጡልን የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 176327 ውሉ መፍረስ የለበትም ሲል የሰጠው ውሳኔ ዋቢ በማድረግ ጉዳዩ ከዚህ በፊት ታይቷል ሲል አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 244(2ለ) እና 245(2) በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በመጨረሻ አመልካቾች በመ/ቁ. 171212 ተጠሪ በይዞታችን የመጠቀም መብታቸው በውሉ መሰረት የተጠናቀቀ በመሆኑ ይዞታችን እና ቤቱ ለቀው ይውጡልን የሚል ክስ አቅርበው አሁንም ክሳቸው በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ተደርጓል፡፡ አመልካቾች በየደረጃው ስልጣን ላላቸው ፍ/ቤቶች ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡

አመልካቾችም ለጉባኤው ያቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ይዘት ተጠሪ በይዞታችን ለመጠቀም በውል ያገኙት መብት ለ20 ዓመት ብቻ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት በተጠሪ የተያዘው ይዞታችንና ቤት እንዲያስለቅቅልን ያቀረብነው ክስ በፍሬ ነገር ደረጃ ሳይመረምር በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ መዝገቡ ዘግቶ ማሰናበቱ ተጠሪ በይዞታችን ከሕግ ውጭ እንዲጠቀሙ በማድረግ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠልን ንብረት የማፍራት መብት እና ፍትሕ የማግኘት መብት ጥሷል የሚል ነው፡፡

በተጠሪ እና በአመልካቾች አውራሽ መካከል በተደረገው ውል መሰረት ተጠሪ በአመልካቾች ይዞታ ለ10 አመት ከተጠቀሙ በኋላ ለገነቡት ቤትና ንብረት በአመልካቾች ግምታቸው ተሰጥቷቸው ለመልቀቅ መስማማታቸው፤ አመልካቾች በውሉ መሰረት ግምቱን መስጠት የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ውሉ ማሻሻል ሳያስፈልገው ተጠሪ ለተጨማሪ 10 ዓመት በይዞታው ከተጠቀሙ በኋላ ይዞታውና በይዞታው የገነቡት ቤት ለአመልካቾች ለመልቀቅ መስማማታቸው በግራ ቀኝ ተከራካሪዎች አልተካደም። በመሆኑም ተጠሪ በውሉ መሰረት በአከራካሪው ይዞታ ያለማቋረጥ ለ20 ዓመት ከተጠቀሙ በኋላ ይዞታውና በይዞታው ያረፈው ቤት የማስረከብ ግዴታ አላቸው ማለት ነው።

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1806 መሰረት በውል የተገባ ግዴታ ቀሪ ከሚሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ ውለታው በተደረገው ስምምነት መሰረት የተፈጸመ እንደሆነ ነው። በፍ/ሕ/ቁ. 1731(1) መሰረት በሕግ አግባብ የተቋቋመ ውል በተዋዋይ ወገኖች ላይ ሕግ ነው ይላል። ስለዚህ ተጠሪ ከአመልካቾች ጋር በገቡት ውል መሰረት በአመልካቾች ይዞታ የመጠቀም መብታቸው በ20 ዓመት የሚጠናቀቅ ሲሆን ውሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ተጠሪ በአመልካቾች ይዞታ የመጠቀም ህጋዊ መብት የላቸውም። በዚህ መሰረት ተጠሪ ከነሐሴ 15 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ያለማቋረጥ በአመልካቾች ይዞታ ለ20 ዓመት በመጠቀማቸው በውሉ መሰረት ይዞታውና ቤቱ ለአመልካቾች ለቀው ማስረከብ ይጠበቅባቸዋል። ይሁን እንጂ የስር ፍ/ቤት ሥነ ሥርዓታዊ በሆነ ምክንያት አመልካቾች በይዞታቸው የመገልገል መብታቸው በመጣስ ተጠሪ ምንም ኪራይ ሳይከፍሉ ለረዥም ግዜ በአመልካቾች ይዞታ እንዲጠቀሙ እና ህጋዊ መብት ሳይኖራቸው በይዞታው መጠቀም እንዲቀጥሉ ውሳኔ ማስተላለፉ አመልካቾች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 የተረጋገጠላቸው ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ ነው።

በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 5(1) መሰረት አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ተወስኗል ለማለት ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ ነገርና የተያዘው ጭብጥ አሁን ከቀረበው ክስ አንድ አይነት መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ለመገንዘብ እንደተቻለው አመልካቾች መጀመርያ ያቀረቡት ክስ ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ሲሆን የፍ/ቤቱ ውሳኔም ውሉ መፍረስ የለበትም ወይም እንደ ውሉ መፈጸም አለበት የሚል ነው። አመልካቾች ውሉ መፈጸሙን ምክንያት በማድረግ አሁን ያቀረቡት ክስ ደግሞ ተጠሪ በውሉ መሰረት በይዞታችን የመጠቀም መብታቸው በመጠናቀቁ ይዞታችን ለቀው ያስረክቡን የሚል ነው። አመልካቾች የውሉን መጠናቀቅ ወይም

ቀሪ መሆን የክስ ምክንያት በማድረግ ከዚህ በፊት ክስ አቅርበው ክርክር ያላደረጉ በመሆናቸው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) ክሱ ቀድሞ ታይቷል ሊባል አይችልም፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37(1) አመልካቾች በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ ለፍርድ ቤት የማቅረብና ውሳኔ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ አመልካቾች በተጠሪ የተያዘባቸው ይዞታና ቤት እንዲለቀቅላቸው ያቀረቡት ክስ በፍሬ ነገር ደረጃ ሳያከራክር ውድቅ ማድረጉ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37፣40 እና 79(3) የተደነገገውን የሚጥስ ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ውሳኔው የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው ፍ/ቤት አመልካቾች በመ/ቁ. 171212 ያቀረቡት ክስ በመቀበል አከራክሮ እንዲወስን አጣሪ ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በመጨረሻ ያቀረቡት ክስ ቀደም ሲል ካቀረቡት ክስ ጭብጡ ተመሳሳይ ባለመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን አከራክሮ እንዲወስን የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ አግባብ ስለሆነ ምክር ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 171212 የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ጉዳዩን እንደገና አይቶ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 176327 የሰጠው ውሳኔ የአመልካቾችን ፍትህ የማግኘትና ንብረት የማፍራት ሕገ መንግስታዊ መብትን የጣሰ ስለሆነ ጉዳዩን እንደገና አይቶ በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን ታዟል፡፡ የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዎች ይሰጥ፡፡

ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም

# የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የስራ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

የፌ/ም/መ/ቁ.022/08

አመልካች፡- ቄስ ወርቁ ዳዲሞስ

ተጠሪዎች፡- 1 ወ/ሮ ሰብለ ወንጌል ወርቁ

2. ወ/ሮ ማሚቴ ወሬራ

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ-መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካቾች የካቲት 04 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለጉባኤው ያቀረቡት ጥያቄ የደቡብ ክልል እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በእኔ ላይ ያስተላለፉት ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 የተረጋገጠልኝን የንብረት ባለቤትነት መብት ዋጋ የሚያሳጣ በመሆኑ ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ለአጣሪ ጉባኤው አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 04 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለጉባኤው ያቀረቡት ጥያቄ የደቡብ ክልል እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በእኔ ላይ ያስተላለፉት ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 40 የተረጋገጠልኝን የንብረት ባለቤትነት መብት ዋጋ የሚያሳጣ በመሆኑ ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ሲሆን ይዘቱም እናቴ ለሆኑት 2ኛ ተጠሪ ገንዘብ ከአውስትራሊያ በመላክ በሀዋሳ ከተማ ታቦር ክ/ከተማ ሂጣታ ቀበሌ በስማቸው ቤት ገዝተውልኝ እኔም በመመላለስ ስቤቱን ስሰራ ቆይቼ ቤቱን እና ሰነዱን

ሊያስረክቡኝ ስላልቻሉ በፍርድ ሀይል ያስረክቡኝ የሚል ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪም ቤቱ የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን አምነው መልሳቸውን የሰጡ ቢሆንም አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ በመግባት ቤቱ የተገዛው 2ኛ ተጠሪ እና እኔ በጋብቻ ወቅት ያፈራነው እና ከብር 1.2 ሚሊዮን ብር በላይ አውጥተን አሻሽለን በመስራት አከራይተን እየተጠቀምንበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አከራካሪው ቤት የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት የወሰነ ሲሆን የዚሁ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት 1ኛ ተጠሪ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው በመሆኑ ጉዳዩ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሚታይ ነው በማለት ጉዳዩን ሳይመለከተው ቀርቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ሰበር ችሎቱም ቤቱ የተሰራው በ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ መሆኑን በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን በመጥቀስ በፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሰረት የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ያለው ሰው የቤቱ ባለቤት እንደሆነ ግምት ቢወስድም በፍ/ሕ/ቁ 1196 መሰረት ግምቱ በማናቸውም ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት ወስኗል፡፡

ጉባዔውም የአመልካችን የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች በአቤቱታቸው ተጣሰብኝ በማለት የገለፁት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ በነበርንበት ወቅት ያፈራነውን የጋራ ንብረት ፍ/ቤቶች የ1ኛ ተጠሪ ንብረት ነው በማለት መወሰናቸው በሕገመንግስቱ አንቀፅ 40 ላይ የተረጋገጠልኝን የንብረት መብቴን ይጥሳል የሚል ነው፡፡

በአመልካችና ተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር በሚስት ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው ወይስ የ1ኛ ተጠሪ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካች በክርክር ወቅት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ከ1949 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ መቆየታቸውን፣ 1ኛ ተጠሪን ጨምሮ 11 ልጆች ማፍራታቸውን እና አሁን ክርክር ያስነሳውንና በሚስት ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት በጋራ ካገኘነው ገቢ የተገዛ በመሆኑ የጋራ ንብረት ነው በማለት ምስክሮችን ያቀረቡ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት ቤቱ የአመልካች ሚስት በሆኑት በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ ይገኝ እንጂ ቤቱ የተገዛውና ማሻሻያ የተደረገበት በ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ በመሆኑ አከራካሪ ውቤት የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ይህንን የፍ/ቤት ውሣኔ ሕገመንግስቱ በአንቀጽ 34(3) ላይ ለቤተሰብ ከሰጠው ከለላ እና ከአመልካች ሕገመንግስታዊ የንብረት መብት አንፃር በመመርመር የፍርድቤቱ ውሳኔ የሕገመንግስቱን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የተከተለ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ማየት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሠረት የሕገመንግስቱ አንቀጽ 34(3) ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ



8

መሰረታዊ መነሻ መሆኑን እና ከሕብረተሰቡና ከመንግስት ጥበቃ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ይህንን ድንጋጌ መሠረት አድርገው የወጡ የፌዴራልና የክልል የቤተሰብ ሕጎችንም ስንመለከት ለቤተሰብ ተገቢውን ጥበቃ እንደሚያደርጉ መረዳት ይቻላል፡፡የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 ላይም በአንደኛው ተጋቢ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ንብረት የግል ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ ካልተመዘገበ በስተቀር የጋራ ነው የሚል የሕግ ግምት ያስቀመጠበት ምክንያት ይህንኑ ሕገመንግስታዊ ከለላ ለማጠናከር ነው፡፡

የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች በተመሳሳይ መልኩ ቤቱ የተገዛውና ማስፋፊያ የተደረገበት በ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህም ውሳኔ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ የተቀመጠውን የሕሊና ግምት መነሻውን አድርጎ የ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች ይህንን የሕሊና ግምት ማስተባበል ያለማስተባበላቸውን ሳይመረመር መተላለፉ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን ሲመለከት በፍ/ሕ/ቁ 1195 ላይ ያለው የባለሀብት የህሊና ግምት ሊስተባበልባቸው የሚችሉባቸው ሁኔታዎች በፍ/ሕ/ቁ 1196 ላይ ተዘርዝረው ሳለ አንዱም ሁኔታ ሳይሟላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ማጽናቱ ተገቢ ካለመሆኑም በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠን ባለሀብትነት በምስክሮች ሊስተባበል የማይችል መሆኑን የሚደነግገውን የማስረጃ መርህ ከግምት ያስገባ አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አከራካሪው ቤት የተገዛው ተጠሪ ከአውስትራሊያ በላኩት ገንዘብ ቢሆን እንኳን የተላከው ገንዘብ እንደ ስጦታ ከሚቆጠር በስተቀር 2ኛ ተጠሪ የቤቱ ባለመብት መሆናቸውን ሊያስተባብል አይችልም፡፡ በአጠቃላይ ውሳኔው በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችም በጋብቻ ውስጥ የተፈራን የጋራ ንብረት ለማሸሽ ዕድል የሚፈጥር እና የሕብረተሰብ መሠረት መሆኑ እውቅናና ከለላ የተሰጠውን ቤተሰብ ህልውና የሚጎዳ ነው፡፡

ይህ ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ ላይ የተቀመጠው የሕሊና ግምት ባልተስተባበለበት ሁኔታ ከተጋቢዎች የአንደኛው የግል ንብረት ከመሆን አልፎ የሶስተኛ ወገን የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ፍርድቤቶች ያስተላለፉት ውሳኔ ሕገመንግስቱ ለቤተሰብ ከሰጠው ከለላ አንጻር የሚቃረን ሆኖ ስለተገኘ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክርቤት እንዲተላለፍ የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው የፌዴራልና የክልል የቤተሰብ ሕጎችም ለቤተሰብ ተገቢውን ጥበቃ እንደሚያደርጉ ግልጽ ሲሆን የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 ላይም



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

በአንደኛው ተጋቢ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ንብረት የግል ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ ካልተመዘገበ በስተቀር የጋራ ነው የሚል የሕግ ግምት ያስቀመጠበት ሁኔታ አለ፡፡

በተጨማሪም በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠን ባለሀብትነት በምስክሮች ሊስተባበል የማይችል መሆኑን የሚደነግገውን የማስረጃ ሕግ መርህ ከግምት ባለማስገባት በአጠቃላይ በቤተሰብ ሕጉ ላይ የተቀመጠው በአንደኛው ተጋቢ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ንብረት የግል ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ ካልተመዘገበ በስተቀር የጋራ ነው የሚል የሕግ የሕሊና ግምት በበቂ የምዝገባ ማስረጃ ባልተስተባበለበት ሁኔታ ከተጋቢዎች የአንደኛው የግል ንብረት ከመሆን አልፎ የሶስተኛ ወገን የሚሆንበት አግባብ ባለመኖሩ በየደረጃው የሚገኙ ፍርድቤቶች ያስተላለፉት ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ የንብረት መብት የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ከዚህም በላይ ሕገ-መንግስቱ ለቤተሰብ ከሰጠው ጥበቃና ከለላ በተቃራኒ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ በጉዳዩ ላይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶችና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**ትዕዛዝ**

1. በጉዳዩ ላይ የሀዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጸናውና ይህንኑ በማጽደቅ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.119937 በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን እንዲያውቀው የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲደርስ ይደረግ፡፡
2. የፌዴራሉ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡



6

## የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 15ኛ ወንጀል ችሎት ያቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ

የመ/ቁጥር 141356

11/3/2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አባሆይ ጓዴ

በሪሁ ተወልደብርሃን

ታደሰ አጥናፉ

ከሳሽ፣ የፌ/ስ/ም/ፀ/ሙ/ኮ/ዐ/ሕጎች አየለ ተሰማ፣ ጌታቸው አጋ ቀረቡ

ተከሳሾች፣ 1. መላኩ ፈንታ ቻይ ከጠበቆች ተሻገር ደሳለኝ ጋር ቀረቡ

2. ገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ ከጠበቆች ሚሊዮን አበራና ማርታ በቀለ ጋር ቀረቡ

3. አምኘ ታገለ ከጠበቆች ገዛኸኝ ፍቅሬ፣ አድያም ሰገድ አጥናፉ ሞላልኝ መለሰ ጋር ቀረቡ

4. ተመስገን ጉላል ከጠበቃ ሐጎስ አብርሃ ጋር ቀረቡ

5. አሸቱ ግረፍ ከጠበቃ ደግነቱ እንግዳወርቅ ጋር ቀረቡ

31. ገብረስላሴ ገብሬ ከጠበቆች ዶ/ር ዘውድነህ በየነና አሰፋ ጋር ቀረቡ

የሺ.ጥላ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው በፍርድ ቤቱ የቀረበው ጉዳይ ከማየት ስልጣን ጋር ተያይዞ በተነሳው ጭብጥ ላይ ብይንና ትእዛዝ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ብይንና ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ብይን

ፍርድ ቤቶች አንድ ክስ ከቀረበላቸው በኋላና በቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ማየትና ማረጋገጥ ያለባቸው ጉዳይ ክሱ የማየት ስልጣን ያላቸው መሆኑ ወይም አለመሆኑ ነው::

ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንዳለ ሳይረጋገጥ ወደ ስረ ነገር ክርክር መግባት አይቻልም:: አሁን ክስ በቀረበበት የእነ አቶ መላኩ ፈንታ የሙስና ጉዳይ (የወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352፣ 141354 እና 141356 የተከሰሱት ሰዎች በአጠቃላይ) በተለይም ከስረ-ነገር ስልጣን /Material Jurisdiction/ በየትኛው ፍርድ ቤት መታየት አለበት የሚለውን መሠረታዊ ጭብጥ እልባት ሳይሰጥበትና ከፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 ከነማሻሻያ አዋጆቹና በተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የስነ-ስርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 ከተደነገገው የስረ-ነገር ስልጣን /Material Jurisdiction/ የሚመለከት ድንጋጌ አንፃር ጉዳዩ ሳይመዘን መደበኛው ሂደት መቀጠል አይቻልም::

በዚህ ጉዳይ የስረ-ነገር ስልጣን /Material Jurisdiction/ አይቶ መወሰን አስፈላጊ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ዋነኛው አቶ መላኩ ፈንታ ቻይ ሚኒስትር ናቸው ወይስ አይደሉም፣ ሚኒስትር ከሆኑስ ጉዳዩ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን ያለው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት /ይሄው ችሎት/ ነው? ወይስ የሌላ የሚለው የግድ እልባት ማግኘት ያለበት ጉዳይ በመሆኑ ነው::

አቶ መላኩ ፈንታ ቻይ በዐ/ሕግ ክስና ማንነታቸው በሚረጋገጥበት ወቅት ዋና ዳይሬክተር መሆናቸው በግልፅ የሰፈረ ቢሆንም በተለያዩ ሰነዶች ዋና ዳይሬክተር በሚለው በወይም የተገለፀ ሚኒስትር መሆናቸው የሚያስረዳ





ከመሆኑም በተጨማሪ ህዳር 09 ቀን 2006 ዓ.ም. በዚሁ መነሻነት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር አቶ መላኩ ፈንታ ቻይ በሚኒስትር ማዕረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባል መሆናቸው ያስረዱ ሲሆን፣ ዐ/ሕግ በጉዳዩ ላይ በሰጠው አስተያየት ተጠቃሹ በሚኒስትር ማዕረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባል መሆናቸው ተቀብሎ ነገር ግን የሚመሩት መስሪያ ቤት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ባለመሆኑ፣ ተጠቃሹ ያላቸው የሚኒስትር ማዕረግነት ለጥቅማ ጥቅም ዓላማ ብቻ የሚያገለግል እንደሆነ፣ ክሱ ሲቀርብ የሌሎች ተከሳሾች ሙብት ጋር አብሮ በመመልከት ጉዳዩ የመረመረው መሆኑና የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት /ይሄው ችሎት/ ስልጣን አለው ሲል ገልጿል::

ፍርድ ቤቱ አቶ መላኩ ፈንታ በሚኒስትር ማዕረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባል መሆናቸው ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክርና የተለያዩ ሰነዶች አረጋግጧል:: ይህ ከሆነ ደግሞ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 8/1/ እና በተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 7/1/ መሠረት የፌደራል መንግስቱ ባለስልጣናት /ሚኒስትሮችን ጨምሮ/ በስራ ሃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ በሚሆኑባቸው ሙስና ጨምሮ ማናቸውም የወንጀል ጉዳዮች የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የስረ-ነገር ስልጣን /Material Jurisdiction/ የተሰጠው መሆኑ በግልፅ ስለደነገገ ጉዳዩ የማየት ስልጣን የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው ማለት ነው፤ ነገር ግን የነዚህ ሁለት አዋጆች ሁለት ንዑስ አንቀፆች ሕገ መንግስታዊ ናቸው? ወይስ አይደሉም? የሚለው ትርጉም የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው::

በተለይም አቶ መላኩ ፈንታ ጉዳያቸው በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢታይ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20/6/ የተከበረላቸውን መሠረታዊ ጉዳያቸውን በይግባኝ እንዲታይ የማቅረብ መብት በግልፅ የሚጋፋ በመሆኑ፣

አቶ መላኩ ፈንታ በዋና ወንጀል አድራጊነት ከሌሎች ሰዎች ጋር የተቋቋመ የወንጀል ክስ የቀረበባቸው በመሆኑና የሁሉም ተከሳሾች ጉዳይ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢታይ ሁሉም ተከሳሾች በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20/6/ የተከበረላቸውን መሠረታዊ ጉዳያቸውን በይግባኝ እንዲታይ የማቅረብ መብት በግልፅ የሚጋፋ ከመሆኑም ሌላ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሌሎች ከአቶ መላኩ ፈንታ ጋር የተከሰሱት ተከሳሾች ላይ በአቶ መላኩ ፈንታ ምክንያት የታችኛው ፍርድ ቤት ወይም የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የስረ ነገር ስልጣን /Material Jurisdiction/ እንዲያይ የሚያስገድደው በመሆኑ፣

የአቶ መላኩ ፈንታ ጉዳይ ብቻውን ተነጥሎ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከአቶ መላኩ ፈንታ ጋር የተከሰሱት ሌሎች ተከሳሾች በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለየፍርድ ቤቶቹ በሕጉ እንደተሰጣቸው የመጀመሪያ ደረጃ የስረ-ነገር ስልጣን /Material Jurisdiction/ መሠረት ተነጥሎ ይታይ ቢባል ደግሞ ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማናቸውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል ከሚለው የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 25 መሠረታዊ መርህ ጋር አብሮ የማይሄድና አቶ መላኩ ፈንታ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20/6/ የተከበረላቸውን መሠረታዊ ጉዳያቸውን በይግባኝ እንዲታይ የማቅረብ መብት እንዳይጠቀሙ በተቃራኒው ሌሎች ተከሳሾች የይግባኝ





መብት እንዲከበርላቸው በማድረግ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸው የሚያስቀር በመሆኑ፣

የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20/6/ እና አንቀፅ 25 የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች በመሆናቸውና የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ፣ ሰው ሰው ሆኖ እስካለ ድረስ ከሰውነቱ ተለይተው የማይታዩና ይህ መብት ለመጎናፀፍ ሰው መሆን ብቻ በቂ መሆኑ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 10 በመርህ ያስቀመጠው መሠረታዊ ድንጋጌ በመሆኑ፣

የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች የማክበር ብቻ ሳይሆን የማስከበርም ኃላፊነትና ግዴታ በግልፅ ለሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈፃሚውና የዳኝነት አካሉ የተጣለባቸው መሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 13/1/ በመደንገጉና ፍርድ ቤቱ ባለው ድንጋጌዎች የመተርጎምና ስራ ላይ የማዋል ኃላፊነት መብቶቹ ከዓለም አቀፍ ስምምነቶችና አገራዊ መርሆዎች ጋር ተጣጥመው መተርጎም ስላለባቸው፣

የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 8/1/ እና የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 7/1/ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20/6/፣ አንቀፅ 25፣ አንቀፅ 10 እና አንቀፅ 13/1/ የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9/1/ መሠረት የሁለቱም አዋጆች ሁለት ንዑስ ዓንቀፆች ተፈፃሚነት ሊኖራቸው ስለማይገባና፣

የሕገ መንግስታዊነት ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባ በመሆኑ፣ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሕገ መንግስታዊ ጉዳዮች የማጣራት ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑና የፌደራል

ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 8/1/ እና የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 7/1/ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20/6/፣ አንቀፅ 25፣ አንቀፅ 10 እና አንቀፅ 13/1/ ይቃረናሉ ወይስ አይቃረኑም? ለዚህ ትርጉም ምክንያት በሆነው ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ የስረ ነገር ስልጣን /Material Jurisdiction/ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው? ወይስ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው? የሚለው እንዲመረመርና ትርጉም እንዲሰጠው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ጉዳዩ ሊመረመር እንደሚገባው በማመን በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 83/1/ እና አንቀፅ 84/2 መሠረት የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት በሙሉ ድምፅ በይነናል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ አምስተኛ ዓመት አንደኛ መደበኛ ስብሰባ

መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ.ቁ. 49/10

አመልካች፡- ወ/ሮ አያልነሽ ሞገስ ደመቀ ጠበቃ አቶ አምሃ መኮንን

ተጠሪ፡- አመልማል አሳየ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 79 ለፍርድ ቤቶች የተሰጠ ሕግ የመተርጎም ስልጣን እና አንቀፅ 55 ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠውን ሕግ የማውጣት ስልጣን መሰረት አድርጎ የቀረበ የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ ነው፡፡ ለጥያቄው መሰረት የሆነው ክርክር የተጀመረው በአዲስ አበባ መስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተቃዋሚ ነበሩ፡፡

አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የአቶ አገኘሁ ፈንቴ ሚስት መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ጠይቀው ፍ/ቤቱም ሚስት ናቸው በማለት ወስኗል፡፡

ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ተጠሪ ባቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ አመልካች የሟች አቶ አገኘው ፈንቴ ሚስት አይደሉም፡፡ሟች እና አመልካች ልጆች የወለዱ መሆናቸው የማይካድ ቢሆንም በ1977 ዓ.ም ተጣልተው ከተለያዩ በኋላ አመልካች ወደ ሌላ አካባቢ በመሄድ ሌላ ባል አግብተው ብርሃኑ አበበ የተባለ ልጅ ወልደው የራሳቸውን ህይወት እየኖሩ ነበር፤ ሟች ደግሞ ከ1980 ዓ.ም ጀምረው ከእኔ ጋር በመጋባት እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ ሳንለያይ አብረን ኖረናል፡፡

አመልካች በዚህ 26 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሚስት ነኝ ብለው በሚች ላይም ሆነ በእኔ ላይ ክርክር አንስተው አያውቁም፤ የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት በክስ ካልተጠየቀ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ስለሰጠበት ውሳኔው ሊሻር ይገባል በማለት ጠይቀዋል።

አመልካች በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከሚች ጋር በ1977 ዓ.ም በተፈጠረ ችግር ምክንያት ከቤት ሸሽተው መውጣታቸውን እና ለብቻቸው በሚኖሩበት ጊዜ ከሌላ ሰው ልጅ መውለዳቸውን አምነው ልጅ መውለዴ ከሚች ጋር የነበረኝን ጋብቻ ስለማያፈርሰው ውሳኔው የሚሻርበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ተከራክረዋል።

የግራ ቀኙን ክርክር የሰማው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ፍርድ ቤት አመልካች ከሚች ጋር ተለያይተው የራሳቸውን ሕይወት መኖራቸውና ሚችም ተጠሪን ወ/ሮ አመልማል አሳየን በማግባት የራሳቸውን ሕይወት በመመስረት መኖራቸውን፤ አመልካችም ይህንኑ የሚያውቁ መሆኑ ከሚች ጋር የነበራቸው ጋብቻ ለመፍረሱ አስረጂዎች ናቸው። በመሆኑም ቀደም ሲል በ13/11/2002 ዓ.ም የተሰጠውን ውሳኔ ሰርዞ የአሁን አመልካች ወ/ሮ አያልነሽ ሞገስ የሚች አቶ አገኘው ሚስት አይደሉም በማለት ወስኗል። ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ በማጽናት ወስኗል። ጉዳዩን በመጨረሻ ያየው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቷል።

አመልካች ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ መተርጎም ሰበብ የሰጠው ውሳኔ ሕገ-መንግስታዊ አይደለም በማለት በርካታ መከራከሪያዎች በማቅረብ በየደረጃው ለሚገኙት ፍርድ ቤቶች አቤት ብልም ተቀባይነት አላገኘም በማለትና የአዲስ አበባ መስተዳድር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ የሰፈረው የልዩነት ሃሳብ ትኩረት የሚሻ ነው።

የልዩነት ሐሳቡ የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 20938 ባልና ሚስት ተለያይተው የሚኖሩና የየራሳቸው ሕይወት መስርተው ከተገኙ ፍቺ እንደፈጸሙ ይቆጠራል በማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79/1/ ለፍርድ ቤቶች ከተሰጠው ሕግን የመተርጎም ስልጣን ያለፈና በሕገመንግስቱ አንቀጽ 55 ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተለይቶ የተሰጠውን ሕግ የማውጣት ስልጣን የሚጋፋ ነው።

በመሆኑም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 75 መሰረት ጋብቻ የሚፈርሰው በሞት ወይም የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥ በጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን፣ እና

በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ ብቻ እንደሆነ ከተደነገገው የማያሻማ ግልጽ ድንጋጌ ውጪ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ/20938 እንዲሁም በዚህ ውሳኔ የሰጠውን "የሕግ ትርጉም መሰረት በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባልና ሚስት በአካል ተለያይተው ከኖሩና የየራሳቸውን ኑሮ ከመሰረቱ ጋብቻቸው ፈርሷል በማለት ለጋብቻ መፍረስ ብቸኛ ምክንያት ናቸው ተብለው በሕግ ከተደነገጉ ሶስት ምክንያቶች ውጪ አራተኛ ምክንያት በመፍጠር በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79 ለፍርድ ቤቶች ከተሰጠው ሕግ የመተርጎም ወይም የዳኝነት ስልጣን በላይ መስራቱን የሚያሳይ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.20938 ላይ የሰጠውን ውሳኔ ተከትለው አመልካች ከሚች አገኘሁ ፈንቴ ጋር የነበራቸው ጋብቻ ፈርሷል በማለት የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ መብቴን የሚጋፋ ስለሆነ ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ጉዳይ ለጉባኤው ቀርቦ በጉዳዩ ላይ ጥናት ተደርጎ እንዲቀርብ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በጉባኤው ፅ/ቤት በኩል ሰፊ ጊዜ የወሰደ ጥናት ተደርጎ በተደረገው ጥናት ላይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ውይይት እንዲያደርጉበት ከተደረገ በኂላ በተደረገው ጥናት መሰረት ጉባኤው ጉዳዩን መርምሮታል፡፡

አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ተያይዘው ከቀረቡትና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተካሄዱትን ክርክሮችና የተሰጡትን ውሳኔዎች ከሚያሳዩት ማስረጃዎች፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በእነ ሸዋዬ ተሰማ ጉዳይ በሰ/መ/ቁ. 20938 ሚያዝያ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሰጠው ውሳኔና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች በዋናነት ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ጋር በማገናዘብ ጉባኤው መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም ከቀረበው ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሕገመንግስታዊነቱ ላይ የቅሬታ አቤቱታ የቀረበበትና ለዚህ አቤቱታ መነሻ ለሆነው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደ/ፍ/ቤት ውሳኔው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ2 (4) በሚደነግገው መሰረት እንደማጣቀሻ የሕግ ትርጉም ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ይኸውም በእነ ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ ጉዳይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 20938 ሚያዝያ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሲሆን የዚህ ውሳኔ ጥቅል ይዘቱ" ተጋቢዎች ምንም እንኳ ቀደም ብሎ የተፈጸመ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም በመካከላቸው

በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት መቀጠል አለመቻላቸው እና ሁለቱ በየፊናቸው የራሳቸውን ሕይወት መጀመራቸው ተረጋግጦ እያለ ፍቺ መፈጸሙን አንደኛው ተጋቢ አላስረዳም በሚል ውሳኔ መስጠት ትክክለኛ የሕግ አተረጓጎም አይደለም በመሆኑም የአሁኗ መልስ ሰጪ ቀደም ሲል የፈጸሙትን ጋብቻ መሰረት በማድረግ ብቻ ሚስት ናቸዉ ብሎ መወሰኑ ትክክለኛ የሕግ አተረጓጎም አይደለም።" የሚል ነው።

ከዚህ በመነሳት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4) በተደነገገው መሰረት የስር ፍርድ ቤቶች እንደ አንድ የሕግ ድንጋጌ በመጥቀስ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እየሰጡበት ይገኛል።

ይህ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 79 ለፍርድ ቤቶች ከተሰጣቸው የዳኝነት ሕግን የመተርጐም ስልጣን በመውጣት ጋብቻ የሚፈርስበትን 4ኛ (አራተኛ) ምክንያት የሚያስቀምጥ ሕጋዊ ድንጋጌን የሚደነግግ ሲሆን ይህም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51 እና 55 ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠውን ሕግ የማውጣት ስልጣንና ተግባር የሚጋፋ ውሳኔ ነው።

ሕግ አውጪው አካል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 75 ላይ ጋብቻ የሚፈርስባቸውን ሶስት ምክንያቶች በመዘርዘሩና በተለይም በአንቀጽ 82 ላይ የጋብቻን ፍቺ የመወሰን እና የጋብቻው በፍቺ መፍረስ የሚያስከትለውን ውጤት የመወሰን ስልጣን የፍ/ቤት ብቻ ነው ብሎ መደንገጉ የራሱ ዓላማ ያለው ሲሆን ከዚህም ውስጥ በዋነኝነት ሊጠቀስ የሚችለው ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የተጋቢዎችን የንብረት ክፍፍልና የህፃናትን የአስተዳደግ ሁኔታ አገናዝቦ ውሳኔ መስጠት ያለበት ፍ/ቤት ነው ከሚል ምክንያት የተነሳ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ይህ በሕግ አውጪው እንደምክንያት የተወሰደው ጉዳይም በሕገመንግስቱ አንቀጽ 34 ላይ የሴቶችን እና የሕፃናትን ሕገመንግስታዊ መብት ለማስጠበቅ የጎላ ድርሻ ያለው ይህን መሰል ሕገመንግስታዊ መብት ወደ ጎን በመተው ከሕግ አውጭው ዓላማ ውጭ በሆነ መልኩ የባልና ሚስት ፍቺ በፍ/ቤት ሳይረጋገጥና ፍ/ቤት የሁለቱን ተጋቢዎች የንብረት ክፍፍል እና የህፃናት ጉዳይ አይቶ ተገቢውን ውሳኔ ሳይሰጥበት ተጋቢዎች ተለያይተው በመኖራቸው እና የራሳቸውን ሌላ ህይወት ጀምረዋል በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻው እንደፈረሰ መቁጠር የሕጉን ዓላማ የሳተ ይሆናል።

በሌላ መልኩ እንዲህ ዓይነት መደምደሚያ ተጋቢዎች በቸልተኝነት ጋብቻቸውን ከፍ/ቤት እውቅና ውጭ በፍቺ መልክ እንዲያቋርጡ መንገድ የሚከፍትና ሕገ ወጥነትን የሚያበረታታ ተግባር ነው። የቤተሰብ ሕጉን አንግቦ የተነሳውን ይህን መሰረታዊ መርህ ወደ ጎን በመተው ጋብቻ ከፍ/ቤት ውጭ በተጋቢዎቹ ተለያይተው መኖር ምክንያት ብቻ ሊፈርስ ይችላል የሚለው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት አቋም ሕገመንግስቱን እና ይህን ተከትሎ የወጣውን የቤተሰብ ሕጉን መሰረት ያላደረገ ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ በተሰጡት ምክንያቶች የአዲስ አበባ መስተዳደር የመጀመሪያ ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 2189/02 ላይ የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 64931 ላይ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ ከሕገመንግስቱ ጋር የሚቃረን ነው፡፡

ስለዚህ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 64931 ላይ በቀን 15/07/2003 የተሰጠውን ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 ላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር፣ በአንቀጽ 51 የፌዴራል መንግሥት ሥልጣንና ተግባር እና በአንቀጽ 79 ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ፤ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡ ከሚሉ ድንጋጌዎች ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(4) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም ሕግ ሆኖ በሃገሪቱ ባሉ ሁሉም ፍ/ቤቶች ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይ ግን ባልና ሚስት ጋብቻቸው በፍ/ቤት ሳይፈርስ ለ10 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ተለያይተው የየራሳቸውን ኑሮ እየኖሩ ከሆነ በሁኔታ እንደፈረሰ ይቆጠራል በሚል የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በቤተሰብ ሕጉ ላይ ከተቀመጡት እና ጋብቻ ከሚፈርስባቸው ምክንያቶች ውጪ ከመሆኑም በላይ ከጋብቻው መፍረስ ጋር ተያይዞ የሚመጡ የፍቺ ውጤቶችን ማለትም

1. የጋራ ልጆችን አስተዳደግ
2. በጋብቻ ወቅት የተፈሩ የጋራ ሃብት ክፍፍልን በሚመለከት ምን ሊሆን እንደሚገባ ባልተመለከተበት ሁኔታ እና

ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሕግ አውጪው አካል የወጣውን ሕግ የመተርጎም እንጅ በሕግ ላይ የሌለን ነገር በትርጉም ሰበብ ሕግ ማውጣት ከስልጣኑ ውጪ በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወስኖ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ የፀናውና በመጨረሻም በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም የተባለው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 5 አንቀጽ 55 እና 79 ንዑስ አንቀጽ 3 ጋር የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተፈፃሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወስኖ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ የፀናውና በመጨረሻም በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም የተባለው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያስፈጽም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የፌዴራሉ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የምክር ቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ አምስተኛ ዓመት አንደኛ

መደበኛ ስብሰባ

መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም

<u>የመ.ቁ. 50/10</u>

አመልካች፦ ወ/ሮ ቀለሚ ተፈራ

ተጠሪ፦ አቶ ፍስሀ ደምሴ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዝያ 5 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ባለቤታቸው ከነበሩት አቶ ፍሰሐ ደምሴ ጋር የነበራቸዉ ጋብቻ ፈርሶ በጋራ ያፈሩት ንብረት እንዲካፈሉ ያቀረቡት ጥያቄ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ማጣቱ ከሕገ መንግስት ጋር ይቃረናል በማለት ትርጉም ይሰጥልኝ ሲሉ በመጠየቃቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካች በ1965 ዓ.ም በፍ/ቤት ተጠሪ ከነበሩት አቶ ፍስሀ ደምሴ ጋር ጋብቻ መስርተን ልጆችን ወልደናል፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረትን አፍርተናል፡፡ ነገር ግን ባለቤቱ በፍ/ቤት የፀና ፍቺ ሳናደርግ ሌላ ጋብቻ የመሰረቱ ስለሆነ ጋብቻችን ይፍረስ በማለት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡

በፍ/ቤት ተጠሪ የነበሩትም ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በ1984 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ተቋርጦና ተለያይተው መኖር በመጀመራቸዉ ጋብቻቸው በተግባር የፈረስ ስለሆነ በፍ/ቤት የሚወሰን የፍቺ ውሳኔ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ካቀረቧቸው ማስረጃዎች ጋር በመመርመር አቶ ፍሰሀ ደምሴ ከአመልካች ጋር በ1965 ዓ.ም ጋብቻ የመሰረቱ ሲሆን በ1984 ዓ.ም በስራ ምክንያት ወደ አዲስ አበባ በመግባት ሌላ ሚስት አግብተው ልጅ የወለዱና ልጂቷም 20 አመት የሞላት መሆኑን፣ ከአመልካች ጋር ይኖሩ ለነበሩት ልጆችም ቀለብ ይቆርጡ የነበረ ሲሆን ከአመልካች ጋር የነበራቸዉ ግንኙነት የባልና የሚስት ሳይሆን ቤተሰባዊ በመሆኑ ለአንዳንድ ማህበራዊ ጉዳይ አመልካች የሚኖሩበት ጎባ ክፍለ ሀገር ይሄዱ የነበረና አመልካች ባለቤታቸው ሌላ ጋብቻ የመሰረቱ መሆኑን ያውቁ እንደነበር በመጥቀስ አመልካች ከአቶ ፍሰሀ ደምሴ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በሁኔታ የፈረሰ ነው በማለት ተመሳሳይ ትርጉም የተሰጠበትን የሰበር ውሳኔ ቅጽ በመጥቀስ የወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ያፀናው ሲሆን ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስሕተት አልተፈጸመበትም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች ፍ/ቤቱ ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል በማለት የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን መሆኑን በመጥቀስ ያቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ተመርምሯል፡፡

በዚሁ መሰረት ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት አመልካች ከአቶ ፍሰሀ ደምሴ ጋር ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ተለያይተው ስለቆዩ የነበራቸዉ ጋብቻ በሁኔታ የፈረሰ ስለሆነ በፍ/ቤት የሚወሰን የፍቺ ውሳኔ የለም በማለት ተመሳሳይ ትርጉም የተሰጠበትን የሰበር ውሳኔ ቅጽ በመጥቀስ የወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ሕግ አውጪው አካል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 75 ላይ ጋብቻ የሚፈርስባቸው 3 (ሦስት) ምክንያቶች መዘርዘሩንና በተለይም በአንቀጽ 82 ላይ የጋብቻን ፍቺ የመወሰን እና ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የሚያስከትለው ውጤት የመወሰን ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው ብሎ መደንገጉ የራሱ ዓላማ ያለው ሲሆን ከዚህም ውስጥ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ጋብቻ በፍች ሲፈርስ የተጋቢዎችን የንብረት ክፍፍልና የህፃናትን የአስተዳደግ ሁኔታ አገናዝቦ ውሳኔ መስጠት ያለበት ፍርድ ቤት ነዉ የሚል ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህ በሕግ አውጭው እንደምክንያት የተወሰደው ጉዳይም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34 ላይ የሴቶችን እና የሕጻናትን ሕገ መንግስታዊ መብት ለማስጠበቅ የጎላ ድርሻ ያለው ነው፡፡ ይህን

መሰል ሕገ መንግስታዊ መብት ወደ ጎን በመተው ከሕግ አውጭው ዓላማ ውጭ በሆነ መልኩ የባልና ሚስት ፍች በፍርድ ቤት ሳይረጋገጥና ፍርድ ቤት የሁለቱን ተጋቢዎች የንብረት ክፍፍል እና የህጻናት ጉዳይ አይቶ ተገቢውን ውሳኔ ሳይሰጥበት ተጋቢዎች ተለያይተው መኖራቸውን እና የራሳቸዉን ሌላ ህይወት ጀምረዋል በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻው እንደፈረሰ መቁጠር የህጉን አላማ የሳተ ነው፡፡

በሌላ መልኩ እንዲህ ዓይነት መደምደሚያ ተጋቢዎች በቸልተኝነት ጋብቻቸዉን ከፍርድ ቤት እውቅና ውጭ በፍቺ መልክ እንዲያቋርጡ መንገድ የሚከፍትና ሕገ ወጥነትን የሚያበረታታ ተግባር ነው፡፡

ስለዚህ አመልካች በዋነኛነት ባለቤታቸው ከሆኑት አቶ ፍስሀ ደምሴ ጋር ያላቸው ጋብቻ በፍ/ቤት በፍቺ እንዲፈርስ የጠየቁበት ምክንያት የጋብቻ መፍረስ ከሚያስከትለው ውጤት ጋር ተያይዞ የሚመጣው የንብረት ክፍፍል በመሆኑ ይህ እንዲወሰንላቸው ለመጠየቅ መሆኑ እየታወቀ ባልና ሚስት በሕግ የሚፀና ፍቺ መፈፀማቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ ባይኖርም በአካል ተለያይተው ከኖሩ ሁለቱ በየፊናቸው የየራሳቸውን ሕይወት መስርተው መኖር መጀመራቸው ከተረጋገጠ ጋብቻቸው እንደፈረሰ ይቆጠራል በማለት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመቁ/ 39874 ተወስኖ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመቁ/168154 የፀናውና በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 124235 አያስቀርብም የተባለው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 5 አንቀጽ 55 እና 79 ንዑስ አንቀጽ 3 ጋር የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት አመልካች ከአቶ ፍስሀ ደምሴ ጋር ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ተለያይተው ስለቆዩ የነበራቸዉ ጋብቻ በሁኔታ የፈረሰ ስለሆነ በፍ/ቤት የሚወሰን የፍቺ

ውሳኔ የለም በማለት ተመሳሳይ ትርጉም የተሰጠበትን የሰበር ውሳኔን በመጥቀስ የወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል።

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 75 ላይ ጋብቻ የሚፈርስባቸው ሦስት ምክንያቶች ተዘርዝረው ተቀምጠው እያለ ፍ/ቤት ሌላ መመዘኛ እየፈለገ ጋብቻን ማፍረሱ ተገቢነት አልነበረውም።

በተለይ በአንቀጽ 82 ላይ የጋብቻን ፍቺ የመወሰን እና ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የሚያስከትለው ውጤት የመወሰን ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው ብሎ መደንገጉ የራሱ ዓላማ ያለው ሲሆን ከዚህም ውስጥ በዋነኝነት ሊጠቀስ የሚችለው ጋብቻ በፍች ሲፈርስ የተጋቢዎችን የንብረት ክፍፍልና የህፃናትን የአስተዳደግ ሁኔታ አገናዝቦ ውሳኔ መስጠት ተገቢ እንደነበር ተረድተናል።

በመሆኑም በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ቉/ 39874 ተወስኖ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ቉/168154 የፀናውና በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 124235 አያስቀርብም የተባለው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 5 አንቀጽ 55 እና 79 ንዑስ አንቀጽ 3 ጋር የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተፈፃሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/቉/124235 የሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የፌዴራሉ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የምክር ቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ አመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የፋ/ቁ.77/12

አመልካች፡- ወ/ሮ ትሁኔ ጥሩነህ

አድራሻ፡- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማቻከል ወረዳ

ተጠሪ፡- አቶ እንዳለማው ጌታሁን

አድራሻ፡-በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማቻከል ወረዳ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 15 ቀን 2009 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ አቤቱታውም በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 131616 የተሰጠው ውሳኔ ላይ የተጠየቀ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲሆን ጉዳዩም የባልና ሚስት የንብረት ክርክርን ይመለከታል፡፡

የጉዳዩ ፍሬ ሀሳብ አመልካች በቀን 12/02/2008 ዓ.ም ተጠሪ ላይ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በማቻከል ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ህጋዊ ጋብቻ መስርተን ልጅ ወልደን አብረን ስንኖር በደረሰብኝ ህመም ምክንያት ወደ ጸበል እና ህክምና በመሄድ በሽታዬን በማስታመም ላይ ሳለሁ ተጠሪ እኔን መንከባከብ ሲገባው ጋብቻችን ሳይፈርስና ሀብት ንብረት ሳንከፋፈል በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመደረብ ሌላ ሴት በማግባት የጋራ ሀብቴን የእርሻ መሬቴንና መኖሪያ ቤቴን ከነጓሮ አትክልቱ በግላቸው ይዘው እየተጠቀሙ እኔ ግን በችግር እየተሰቃየሁ ቆይቼ ህመሜ ሲሻለኝ ጋብቻችን በፍ/ቤት መፍረሱ ተረጋግጦ የሀብቴን ድርሻ እንዲያካፍለኝ በመ/ቁ/13024 ጠይቄ ፍ/ቤቱም ጋብቻው መፍረሱ ተረጋግጦ የንብረት ጥያቄን በተመለከተ እንደገና ዘርዝሬ ለመጠየቅ እንድችል መብቴን ጠብቆልኝ ወስኗል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ 78 ዚንጎ ቆርቆሮ፣

አትክልት፣ ባህርዛፎች እና 10 የንብ ቀፎ ድርሻዬን እንዲያካፍሉኝ በማለት የንብረቱን መጠን እና አይነት በመዘርዘር ክሳቸውን ለፍ/ቤቱ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪም በሰጡት መልስ በወቅቱ ከአመልካች ጋር ስንለያይ ያለንን ንብረት ተካፍለን ስለ ተለያየን አመልካች የቀራቸው ምንም ሀብት የላቸውም፡፡ አለኝ ካሉም በወቅቱ መጠየቅ የነበረባቸው ሲሆን ጋብቻችን ፈርሶ ከተለያየን 18 አመት ስለሆነ ይህ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ እንዲሆንልኝ በማለት መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በበኩላቸው ባደረጉት የቃል ክርክር ከተጠሪ ጋር ከተለያየን 13 አመት ስለሆነ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ እንዲፈርስ እና ንብረት እንዲከፋፈሉ በዚህ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 13024 በተጠሪ ላይ ክስ አቅረበው ፍ/ቤቱም አመልካች እና ተጠሪ ከተለያዩ ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ ጋብቻው በሁኔታ ፈርሷል፡፡ አመልካች የንብረት ክርክርን በተመለከተ በሌላ ሁኔታ ተጠሪን መጠየቅ ይችላሉ በማለት ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካች በዚህ ችሎት የንብረት ክፍፍል ጥያቄን ቢያቀርቡም ነገር ግን አመልካች ከተጠሪ ጋር ከተለያየ 13 አመት መሆኑን ሲገልፁ ተጠሪ ደግሞ 18 አመት መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ሲሆን ይህ ደግሞ አመልካች እና ተጠሪ ከተለያዩ ከ10 አመት በላይ መሆኑን ስለሚያመላክት አመልካች ያቀረቡት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔም እስከ ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በትእዛዝ ፀንቷል፡፡

አመልካችም ይህ የፍ/ቤት ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ መብቴን ጥሷል በማለት ለጉባኤው ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት ያነሱት ቅሬታም፣ የጋራ ንብረት የሆነው መሬትና ንብረት ተጠሪ እጅ ሊቆይ የቻለው በከባድ ህመም ታምሜ ለፀበልና ህክምና ወደ ሩቅ ቦታ ሄጄ እያለ ፍ/ቤቶቹ ይህንን ሳያጣሩ ተጠሪ ያቀረቡትን ማስረጃ ብቻ መሰረት በማድረግ ጋብቻው በሁኔታ የፈረሰ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ውሳኔ መስጠታቸው የአመልካችን ከይዞታ ያለመነቀል፣ በመሬት የመጠቀም እና በጋብቻ ውስጥ የተፈራው ንብረት ከተጠሪ እኩል የመጠቀም ሕገ መንግስታዊ መብት የሆኑትንና በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 23፣ 35(2)(7) እና 40 የተደነገገውን የጣሰ በመሆኑ የፍ/ቤቱ ውሳኔ የሕገ መንግስት ትርጉም ተሰጥቶት እንዲታረምልኝ በማለት ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

አመልክተው ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡ ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴበሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ እና የምክር ቤቱን ባለሙያዎች አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሰረት አመልካች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍ/ቤት ውሳኔ የሕገ መንግስት ጥሰት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም፣ በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ በፍ/ቤት ፈርሶ የጋራ ንብረታቸውን እንዲካፈሉ በወረዳ ፍ/ቤት ክሳቸውን አቅርበው ነበር፡፡ ፍ/ቤቱም በመዝገብ ቁጥር 13024 ላይ ጉዳዩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በ10 ዓመት ግዜ ውስጥ በሁኔታ ስለፈረሰ ፍ/ቤቱ የሚያፈርሰው ጋብቻ የለም፣ ነገር ግን የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ አመልካች በሌላ ሁኔታ መጠየቅ ይችላሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚሁ መሰረት አመልካችም አሁን ቅሬታ የቀረበበትና በወረዳው ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 13725 ላይ ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ መፍረሱ በመዝገብ ቁጥር 13024 ላይ ስለተረጋገጠ አመልካች እና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩትን ንብረት ተጠሪ እንዲያካፍሏቸው የጠየቁ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግን አመልካች ያቀረቡት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ከተጠሪ ጋር ከተለያዩ ከ10 አመት በላይ በመሆኑ በ10 አመት ግዜ ውስጥ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ የወሰነ ሲሆን አመልካችም ይህ ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር ይቃረናል በማለት ለጉባኤው አቤቱታ ማቅረባቸውን ምክር ቤቱ ተረድቷል፡፡

በዚሁ መሰረት ፍ/ቤቱ በወረዳ ፍ/ቤት መዝገብ ቁጥር 13024 ላይ ጋብቻቸው በሁኔታ ፈርሷል በማለት መወሰኑ፣ አሁን ቅሬታ የቀረበበት መዝገብ ቁጥር 13725 ላይ ደግሞ አመልካች እና ተጠሪ ከተለያዩ ከ10 ዓመት በላይ ስለሆነ የአመልካች የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በይርጋ ይታገዳል በማለት መወሰኑ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ የንብረት መብታቸውን ይጥሳል ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ስንመለከት፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ የወረዳው ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 13024 ላይ አመልካች እና ተጠሪ ከ10 ዓመት በላይ ተለያይተው ስለቆዩ የነበራቸው ጋብቻ በሁኔታ የፈረሰ ስለሆነ በፍ/ቤት የሚወሰን ፍች የለም በማለት የወሰነው ውሳኔ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 20938፣ 17937፣ 32308 እና 31891 ላይ ተመሳሳይ የህግ ትርጉም በመስጠት ከወሰነው ውሳኔ ጋር በሚመሳሰል ሁኔታ የተወሰነ መሆኑን ቅሬታ ከቀረበበት እና በመጨረሻ ፀንቶ ካለው ውሳኔ ላይ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ ሕግ አውጪው አካል በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 75 እንዲሁም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 86 ስር እንደ ተቀመጠው ጋብቻ የሚፈርስባቸው 3 (ሶስት) ምክንያቶች ማለትም፣ 1ኛ ከተጋብዎቹ አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥ፣ 2ኛ ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በሕግ መሰረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን፣ 3ኛ የፍች ውሳኔ በፍ/ቤት ሲሰጥ እንደሆነ መዘርዘሩና በተለይም በክልሉ የቤተሰብ ሕግ ከአንቀፅ 89 እስከ 95 እና በፌደራሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀፅ 82 ላይ የጋብቻን ፍቺ የመወሰን እና ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የሚያስከትለውን ውጤት የመወሰን ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው ብሎ መደንገጉ የራሱ ዓላማ ያለው ሲሆን ከዚህም ውስጥ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የተጋቢዎችን የንብረት ክፍፍልና የህፃናትን የአስተዳደግ ሁኔታ አገናዝቦ ውሳኔ መስጠት ያለበት ፍርድ ቤት ነው ከሚል ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ ከህገ መንግስቱ ዓላማ ውጭ የባልና ሚስት ፍች በፍ/ቤት ሳይረጋገጥና ፍርድ ቤት የሁለቱን ተጋቢዎች የንብረት ክፍፍል እና የህፃናት ጉዳይ አይቶ ተገቢውን ውሳኔ ሳይሰጥበት ተጋቢዎች ተለያይተው በመኖራቸው እና የራሳቸውን ሌላ ህይወት ጀምረዋል በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻው እንደፈረሰ መቁጠር የህጉን ዓላማ የሳተ ነው፡፡

በሌላ መልኩ እንዲህ ዓይነት መደምደሚያ ተጋቢዎች በቸልተኝነት ጋብቻቸውን ከፍርድ ቤት እውቅና ውጭ በፍቺ መልክ እንዲያቋርጡ መንገድ የሚከፍትና ሕገ-ወጥነትን የሚያበረታታ ተግባርም ነው፡፡

ስለዚህም አመልካች በዋነኛነት ባለቤታቸው ከሆኑት ከአሁን ተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ በፍ/ቤት እንዲፈርስ የጠየቁበት ምክንያት የጋብቻ መፍረስ ከሚያስከትለው ውጤቱ ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ እንዲወሰንላቸው እና በጋብቻ ውስጥ

ያፈሩት የንብረት መብታቸው እንዲከበርላቸው ለመጠየቅ መሆኑ እየታወቀ ባልና ሚስት በሕግ የሚፀና ፍቺ መፈፀማቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ ባይኖርም በአካል ተለያይተው ከኖሩና ሁለቱ በየፊናቸው የየራሳቸው ሕይወት መስርተው መኖር መጀመራቸው ከተረጋገጠ ጋብቻቸው ከ10 ዓመት በኋላ እንደፈረሰ ይቆጠራል በማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በማቻከል ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 13024 ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 50(5)፣ አንቀፅ 55 እና 79(1) ጋር ይቃረናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የወረዳው ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር. 13725 ላይ የአመልካች የጋራ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ተወስኖ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፀናውን ውሳኔ በተመለከተ አመልካች በክርክራቸው ከ13 ዓመት በፊት ማለትም በ1995 ዓ.ም በከባድ ሁኔታ ታመው ከህመማቸው ለመዳን ጠበል እና ህክምና ከመሄድ በስተቀር አግብተው ሌላ ትዳር በመመስረት የግል ኑሮ መኖር እንዳልጀመሩ ከተጠሪ ጋር ለመለያዬትም ሀሳብ እንዳልነበራቸው እና በችግር ብቻ ተለያይተው እንደ ቆዩ ፍ/ቤቱን አስረድተው ተከራክረዋል፤ ነገር ግን ፍ/ቤቱ አመልካች እና ተጠሪ ከ10 ዓመት በላይ በችግርም ይሁን ያለችግር ስለ ተለያዩ ብቻ ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል፣ በጋብቻ ውስጥ የተፈራው የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ጥያቄ ደግሞ በይርጋ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ቀሪ ሆኗል በማለት በሕግ በግልፅ ያልተቀመጠውን ትርጉም በመስጠት መወሰኑ ሕገ መንግስታዊ የሆነውን የአመልካችን የንብረት መብት በሚያስቀር ሁኔታ የተወሰነ ውሳኔ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡

የዚህ ውሳኔ ውጤት ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ ጋብቻ የሚፈርስበት ከ3ቱ መስፈርቶች ሌላ 4ኛ መስፈርት ከመፍጠሩም ባሻገር አመልካች ከተጠሪ ጋር ባል እና ሚስት ሆነው በጉልበታቸው ከጋብቻ ቀን ጀምሮ እስከ ተለያዩበት ቀን ድረስ ያፈሩትን ንብረት እንዳይጠቀሙ የሚገድብ ውሳኔ በመሆኑ ህገ መንግስቱ በአንቀፅ 40 ስር ‹‹ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል፣ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው›› የሚለውን የሕገ መንግስቱን ድንጋጌ ይቃረናል፡፡ በተጨማሪም ፍ/ቤቱ አመልካች እና ተጠሪ ከተጋቡበት ቀን ጀምሮ ተለያይተው መኖር እስከጀመሩበት ቀን ድረስ በጋራ ያፈሩትን ንብረት አጣርቶ እኩል እንዲካፈሉ መወሰን ሲገባው በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም በማለት የአመልካችን

የጋራ የንብረት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ማድረጉ ከላይ የተጠቀሰውን ሕገ መንግስታዊ መብታቸውን ይቃረናል፡፡

በመሆኑም አመልካች ጋብቻ ከመሰረቱበት ቀን ጀምሮ ከተጠሪ ጋር እስከተለያዩበት ቀን ድረስ ያፈሩትን ንብረት ለመከፋፈል መብት እያላቸው ይህንን መብት በሚያስቀር ሁኔታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማቻከል ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 13024 እና 13725 ላይ ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል፣ የንብረት ጥያቄ ደግሞ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ስላልቀረበ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የተሰጠውና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 131616 የፀናው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 50(5)፣ አንቀፅ 55 እና 79(1) እንዲሁም ከአንቀፅ 40(1)(7) ጋር ስለሚቃረን ውሳኔው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትእዛዝ

1. በአማራ ክልል ማቻከል ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን በምክር ቤቱ የተወሰነ መሆኑን አውቀው ተገቢውን እንዲፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የፌዴራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ አምስተኛ ዓመት አንደኛ መደበኛ ስብሰባ

መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ.ቁ. 58/10

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ማሞ

ተጠሪ፡- አቶ ሽንኮሬ ኡጋሞ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

አመልካች በ20/04/2007 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.32308 የሰጠውና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የጸናው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ የተመለከተውን መብቱን የሚቃረን ስለሆነ ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦች፣ ህዝቦች ክልል ሲዳማ ዞን ዳሌ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ አቶ ሽንኮሬ ኡጋሞ ጋር ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ አብረን ስንኖር ሰባት ልጆች ወልደናል፣ በ1986 ዓ.ም የአሁን ተጠሪ አቶ ሽንኮሬ ኡጋሞ ከቤት አባሮኝ በመንገላታት ላይ ስለምገኝ ጋብቻው እንዲፈርስና የንብረት ክፍፍል ውሳኔ እንዲሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ከሀያ (20 ) አመት በፊት ልጆቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ጥለው በፈቃዳቸው የሄዱ ስለሆነ በፍታ/ብሄር ህግ ቁ. 1845 መሰረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ስለሚሆን ሊጠይቁ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤቱም የተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ግራ ቀኙን አከራክሮ ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስ እንዲሁም ባልና ሚስት የጋራ ሀብት ካላቸው የመከፋፈል መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለት በመ/ቁ. 06321 በ14/08/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ በወረዳ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻ አለ ወይስ የለም እንዲሁም አመልካች ጋብቻ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ በመደበኛው የፍታ/ብሄር ህግ ቁ.1845 መሰረት በይርጋ የሚቀር ነው ወይስ አይደለም

የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን የመረመረ ሲሆን አመልካች በእራሳቸው ፈቃድ ጋብቻውን ለሀያ አመት ጥለው የሄዱ በመሆኑ ጋብቻ በሁኔታ የፈረሰ ነው፤ ስለዚህም የሚፈርስ ጋብቻ የለም በማለት የወሰነ ሲሆን 2ኛውን ጭብጥ በተመለከተ የባልና ሚስት ጉዳይን በሚመለከት ይርጋ ባይኖርም ማንኛውም የፍታ/ብሄር ክርክር አለኝ የሚል ሰው ማግኘት አለብኝ ብሎ የሚገምተውን ንብረት በአስር አመት ውስጥ መጠየቅ ያለበት በመሆኑ የአመልካች ክስ በአስር አመት ውስጥ ስላልቀረበ በመደበኛ የክስ ይርጋ ጊዜ በፍታ/ብሄር ህግ ቁ. 1845 መሰረት ውድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢጠይቁም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠልም አመልካች የሰበር አቤቱታለክልሉና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች ያቀረቡ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም፣ ለሰበር አያስቀርብም በማለት ወስነዋል፡፡

የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔውም አመልካች እና ተጠሪ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ተለያይተው መኖራቸው በሁለቱም በኩል የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች የፍቺና የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት በ2006 ዓ.ም ሲሆን አመልካችና ተጠሪ ለሀያ አመታት ያህል ተለያይተው ኖረዋል ማለት ነው፡፡ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚፈርስ ጋብቻ የለም ወይም ጋብቻው በእራሱ ጊዜ የፈረሰ ነው የሚከፋፈል የጋራ ንብረት አይኖርም የሚል መደምደሚያ ላይ ከመድረሱ በፊት ቢያንስ አመልካችና ተጠሪ ከተለያዩበት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ የሚጸና የፍቺ ውሳኔ መስጠት ነበረበት፡፡ የጋብቻ ውጤትን በተመለከተ በዚሁ መሰረት አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ አብረው በኖሩበት ዘመን ያፈሯቸው የጋራ ንብረቶች ካሉ ይርጋ ስለማይመለከተው መፍትሄ ማግኘት እንዳለበት መወሰን ሲገባው በድፍኑ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ብሎ መዝጋቱ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብት የሚቃረን ውሳኔ ነው፡፡ ስለዚህ በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የጸናው ውሳኔ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34፣ 50/5፣ 55 እና 79/3 የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና

የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ከምክር ቤቱ ባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡

በዚሁ መሠረት የአሁን አመልካች ያቀረቡት የፍቺ ጥያቄ በዳሌ ወረዳ ፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቶ በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት ካለ የንብረት ክፍፍል የመጠየቅ መብታቸውን ጠብቆ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ከሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የዳሌ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ ጋብቻው በሁኔታ ፈርሷል የንብረት ክፍፍል ጥያቄውም በፍታ ብሄር ህግ ቁጥር 1845 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ውሳኔ መሰጠቱ አመልካች በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን መብት የሚጋፋ ነው፡፡ በመሆኑም በባልና ሚስት ጉዳይ ይርጋ ስላልተቀመጠ በሕግ በግልጽ ባልተመላከተ ሁኔታ ለሌላ ጉዳይ የተቀመጠን የይርጋ የጊዜ ገደብ በመጥቀስ የዳሌ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠውን መብት የጣሰ ስለሆነ እንዲሁም ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል በማለት በፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔም አጣሪ ጉባኤው በግልጽ እንዳስቀመጠው የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 50(5)፣ 55 እና 79(3) ድንጋጌዎችን የጣሰ በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባኤው ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሕግ አውጪው አካል የወጣውን ሕግ የመተርጎም እንጅ በሕግ ላይ የሌለን ነገር በትርጉም ሰበብ ሕግ ማውጣት ከስልጣኑ ውጪ በመሆኑ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.32308 የሰጠውና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የጸናው በመጨረሻም በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም የተባለው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 5 አንቀጽ 55 እና 79 ንዑስ አንቀጽ 3 ጋር የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተፈፃሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.32308 የሰጠውና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የጸናው እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም የተባለው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

89

ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡

2. የፌዴራሉ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የምክር ቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን

## 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሸዋዬ ሙላት

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አረጋሽ ባዲ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

### ውሳኔ

ጉዳዩ የመኖሪያ ቤት ባለቤትነትና የውርስ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በአሁን አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ ከባለቤቴ አቶ አለማየሁ ታደሰ ጋር በ1985 ዓ.ም ተጋብተን ስንኖር ሞግዚት የሆንኩላቸውን ልጆች ወልደን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥሩ አዲስ የሆነ ሰነድ አልባ ቤት ሰርተን እየኖርን እኔ ለስራ ወደ ውጭ ሀገር በመሄዴ ተከሳሽ ወይም የአሁን አመልካች በቤት ሰራተኝነት ተቀጥረው እየሰሩ እያለ ባለቤቴ ሞቷል፡፡ ተከሳሽ ይህን ቤት ይዘው ከሚጠቀሙበት በተጨማሪ እኔ የሟች አቶ አለማየሁ ሚስት እና የልጆች ሞግዚት መሆኔን በፍርድ ቤት ባቀረብኩት አቤቱታ ላይ ተቃዋሚ በመሆን ቀርበው ስንከራከር ከቆየን በኋላ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሚስት መሆኔን እና የልጆቹ አሳዳጊ መሆኔን በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በማፅናት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ ወይም የአሁን አመልካች ቤቱን እና በቤቱ ውስጥ የሚገኙትን ቁሳቁስ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ተከሳሽ በመሆን በሰጡት መልስ ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት ከሳሽ የሟች ንብረት መስሏቸው እንዲጣራላቸው ለውርስ አጣሪ አቅርበው ቤቱ የሟች እንዳልሆነ ተረጋግጧል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ የሚስትነት እና የልጆች ሞግዚትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ አቅርበው እኔም ይህንኑ በመቃወም ስንከራከር ቆይተን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ውሳኔው እኔ በሚስትነቴና በወለድኳት ልጅ ሞግዚትነት የማቀርበውን የመብት ጥያቄ የማያግድ መሆኑ ተወስኖልኛል፡፡ በተጨማሪም ይህ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት በግሌ ያፈራሁት

እንጂ የሟች አይደለም እንዲሁም የቤቱ አድራሻ በግልፅ ስላልተገለፀ ከሳሽ ለመጠየቅ መብት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የሰው ምስክር ከሰማና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የቀረቡት የከሳሽ ወይም የአሁን ተጠሪ ምስክሮች ከአሁን አመልካች ምስክሮች በበለጠ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ሟች እና ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) በጋራ የሰሩት ነው በማለት የአሁን አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እና ለሟች ሶስት ልጆች አመልካች ከሟች የወለደችውን ልጅ ጨምሮ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በተመሳሳይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ከማስረጃ ምዘናና ከፍሬ ነገር ክርክር ጋር የተያያዘ ስለሆነ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት ወስኗል፡፡

ይህ ውሳኔ የእኩልነት እና የንብረት ሕገ መንግስታዊ መብቴን የሚጋፋ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ ሲሉ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታም ከሟች አቶ አለማየሁ ታደሰ ጋር በሀገር ባህል በ1995 ዓ.ም ተጋብተን በጋራ ስንኖር አሁን ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት ቀድሞ የነበረውን ሶስት ክፍል ቤት አፍርሰን በጋራ አዲስ 8 (ስምንት) ክፍል ቤቶችን በመጨመር ሰርተን ስንጠቀም የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም መጀመሪያ ለፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ላይ አሁን ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት እኔ ለስራ ወደ ውጭ ሀገር ከሄድኩ በኋላ ተከሳሽ እኔ ሰርቼ የሄድኩትን ቤት አከራይተው በግላቸው ሌሎች ተጨማሪ ቤቶችን ገንብተዋል በማለት ቤቶቹን እኔ ከሟች ጋር መስራቴን አምነው እያለ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በክሳቸው ባላቀረቡት አዲስ ጭብጥ ላይ ማስረጃ በመስማት አዲስ የተሰሩት ቤቶች ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ የተሰራ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ አላግባብ ነው፡፡

ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ሲሰራ ከሟች ጋር በቤቱ ውስጥ ያለሁ መሆኑ በግራ ቀኛችን ያልተካደና በምስክሮች የተደገፈ ሆኖ ሳለ እኔ በአቀረብኩት ክርክር አግባብ ቤቱ የግሌ መሆኑ በምስክሮች ባይረጋገጥ እንኳን የሟች ሚስት መሆኔ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ በሚስትነቴ ማጣት የሌለብኝን ሕገ መንግስታዊ የእኩልነትና የንብረት መብት ፍርድ ቤቶች እንዳጣ ስላደረጉኝ በውሳኔው ላይ ትርጉም ይሠጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤው አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ከፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር የመረመረው ሲሆን አመልካችና ተጠሪ የሟች አቶ አለማየሁ ታደሰ ሚስቶች መሆናቸው በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ነገር ግን የንብረት ክፍፍልና የውርስ ሃብት ክፍፍልን በተመለከተ የአሁን አመልካች ምስክሮች አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የግላቸው መሆኑን በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡ ተጠሪ ወደ ውጭ ሀገር ከመሄዳቸው በፊት ከሟች ጋር ከሰሩት ቤቶች በተጨማሪ እርሳቸው ወደ ውጭ ከሄዱ በኋላ ተጨምረው የተሰሩት ሌሎች ክፍል ቤቶችም የተሰሩት በአመልካችና በሟች ሳይሆን ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ መሆኑ በተጠሪ ምስክሮች ስለተረጋገጠ የአሁን አመልካች ቤቱን መካፈል አይችሉም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በማፅናት ወስኗል፡፡

በዚህ ጉዳይ ውስጥ የአሁን አመልካች ለክርክር መነሻ የሆኑት ተጨማሪ ቤቶች ሲሰሩ ከሟች ጋር በቤት ውስጥ የነበሩ መሆኑና ለሟችም ሚስት መሆናቸው ባልተካደበት እና በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ ከሟች ጋር አብረው በሚስትነት ይኖሩበት ከነበረው ቤት ላይ ምንም ዓይነት መብት የላቸውም ወይም በቤቱ ስራ ውስጥ ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ አላደረጉም መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑ በዋና ጭብጥነት መታየት ያለበት ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 34 ንኡስ አንቀጽ 1 ሴቶች በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል በማለት የተደነገገ ሲሆን ይህም ንብረት በጉልበታቸው በመፍጠር በችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነ ዋጋ ያለው ውጤት ሊሆን እንደሚችል በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

አሁን በክርክር ላይ ባለው ጉዳይ አመልካች ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ከሟች ጋር ሟች እስከሞቱበት 2003 ዓ.ም ድረስ በባልና ሚስትነት አብረው ይኖሩ እንደነበረ ከፍርድ ቤቶች በተሰጣቸው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በተመሳሳይ ተጠሪ ደግሞ ከሟች ጋር በ1985 ዓ.ም ተጋብተው አብረው ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ ለስራ ወደ ውጭ ሃገር እንደሄዱና ሟች ከሞቱ በኋላ ሲመለሱ የአሁን አመልካችን በቤቱ ውስጥ እንዳገኙአቸው ከክርክራቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ ከሟች ጋር በጋብቻቸው ጊዜ እንደሰሩና ነገር ግን የአሁን አመልካችም በፊት ተሰርቶ የነበረው ቤት ላይ ተጨማሪ ቤቶችን በግላቸው የሰሩ መሆኑን ተጠሪ በክሳቸውም የጠቀሱትና ያልካዱት ጉዳይ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከተጠሪ ምስክሮች እንዳረጋገጠው ተጠሪ ወደ ውጭ ሀገር ከሄዱ በኋላ የተገነቡት ተጨማሪ ቤቶች የተሰሩት ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ ነው፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው አመልካች ባቀረቡት ክስ መሰረት ለክርክር ምክንያት ከሆነው ቤት ውስጥ የተወሰነውን አመልካች የሰሩት መሆኑን እና የተጠሪ ምስክሮች ባረጋገጡት አግባብ ደግሞ ተጠሪ ወደ ውጭ ከሄዱ በኋላ የተገነቡት ቤቶች ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ የተገነባ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል ይህንኑ እውነታ የሚያጠናክር ለክርክር ምክንያት ለሆነው ቤት የመብራት አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልካች ያመለከቱበትና ሌሎች መረጃዎችም ለፍርድ ቤቱ ቀርበው የነበሩ መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ፍርድ ቤቶች ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት ለአሁን ተጠሪ ለመወሰን መሰረት ያደረጉት ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ተጠሪ ከውጭ ሀገር በላኩት ገንዘብ የተሰራ ለመሆኑ ጉዳዩ በሰዎች ምስክር ስለተረጋገጠ ነው የሚል ሲሆን በሌላ በኩል የአሁን አመልካች የሰው ምስክሮች ግን አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የግላቸው ወይም በግል የሰሩት መሆኑን አላረጋገጡም በሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቶች አመልካች ካቀረቡት አቤቱታ አንፃር ቤቱ በግላቸው የተሰራ መሆኑ ባይረጋገጥም እንዲሁም ቤቱ ተጠሪ በላኩት ገንዘብ የተሰራ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳን አመልካች የሟች ሚስት ሆነው በቤት ውስጥ እየኖሩ ለተገነቡት ተጨማሪ ቤቶች የጉልበት ወይም የካፒታል አስተዋፅኦ የነበራቸው መሆን አለመሆኑን ግን በአግባቡ ያጣሩት ነገር አልነበረም፡፡ በተጨማሪም ከክርክር ሂደቱ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ እራሳቸው ባቀረቡት ክስ አመልካች ቀድሞ የተሰሩትን ቤቶች አከራይተው ተጨማሪ ክፍሎችን በግላቸው ያሰሩ መሆኑን መጥቀሳቸው በቤቱ ላይ የአመልካች የካፒታልና የጉልበት አስተዋፅኦ ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 63 ላይ በግልፅ ተደንግጎ እንደሚገኘው አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ያፈሩት ሀብት የጋራቸው እንደሆነ በሕጉ ግምት የሚወሰድ ነው፡፡ ይህ የሕጉ ግምት አንድ ባል ከአንድ በላይ ሚስቶች ስላሉት ብቻ ቀሪ የሚሆንበት አግባብ አይኖርም፡፡ አንድ ባል ከአንድ ሚስት በላይ ሲኖረው ብዙ

ጊዜ በሚኖሩበት ቦታ ያፈራው ንብረት ቀጥታ ተሳታፊ በሆነችው ሚስት እና በሌላኛዋ ሚስት መካከል መኖር ስለሚገባው የሀብት ክፍፍል ፍርድ ቤቶች ተገቢውን እና ሕጋዊ መፍትሄ ከመስጠት ባሻገር አንደኛዋ ሚስት በንብረት ማፍራት ሂደቱ ላይ አስተዋፅኦ አላበረከተችም በሚል ከሀብት ክፍፍሉ ውጭ ማድረግ የህጉን አላማ የሳተ ነው፡፡ ምክንያቱም በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት ከግል ንብረታቸው የሚያገኙአቸው ገቢዎች የጋራ ሀብታቸው እንደሚሆን በቤተሰብ ሕጉ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን አንድ ሚስት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተጠቀሰውን ንብረት ለማፍራት አስተዋፅኦ ስለማድረጓ አላስረዳችም ቢባልም በባሏ ጥረት በተፈራው ንብረት ላይ የጋራ ተጠቃሚ ለመሆን ሕጉ መብት ይሰጣታል፡፡ ከዚህም የሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው አመልካች ሚስት መሆናቸው እስካልተካደ እና ከባላቸው ጋር ይኖሩ እንደነበር ከተረጋገጠ የንብረት ክፍፍል ድርሻ ጥያቄያቸው ውድቅ መደረግ የለበትም፡፡

በዚህ መሰረት የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ሲሰራ በቤቱ ውስጥ ከሟች ጋር እንደነበሩ ያልተካደና በማስረጃም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠሪ እራሳቸው ባቀረቡት ክስ ላይ የአሁን አመልካች ቀድሞ እሳቸው የሰሩትን ቤት አከራይተው ከኪራይ ባገኙት ገንዘብ ተጨማሪ ቤቶችን የገነቡ መሆኑን የገለጹ ሲሆን እንዲሁም አመልካች ለቤቱ የመብራት አገልግሎት ለማግኘት ያመለከቱበት የፅሁፍ ማስረጃም በመዝገብ ውስጥ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ሁሉ መረዳት እንደሚቻለው ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ሲሰራ የአሁን አመልካች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋፅኦ ያደረጉ መሆኑን ነው፡፡

የአመልካች አስተዋፅኦ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ አልተመላከተም ቢባልም እንኳን ከላይ በተጠቀሰው አግባብ አመልካች በሟች ባለቤታቸው የተፈራውን የጋራ ሀብት የመካፈል ሕጋዊና ሕገ መንግስታዊ መብት ይኖራቸዋል፡፡

ሲጠቃለል የቤተሰብ ሕጉ ባልና ሚስት በትዳር አብረው በሚኖሩበት ጊዜ በጋራ ያፈሩት ሀብት የጋራ ሀብታቸው እንደሆነ ግምት መወሰድ እንዳለበት በግልፅ ከሚደነግገው መርህ ጋር ጉዳዩ ታይቶ ሁለቱም ሚስቶች (አመልካችና ተጠሪ) ከንብረቱ ላይ ማግኘት የሚገባቸውን ድርሻ እንዲያገኙ መወሰን ሲገባው ከሟች ጋር የነበሩት አመልካች ከቤቱ ላይ ምንም ዓይነት መብት የላቸውም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳያርመው መቅረቱ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብቶች የሚጥስ ነው፡፡

ስለዚህ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 135833 ላይ በቀን 27/11/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ጋር የሚጋጭ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 84 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በአዋጅ ቁጥር 798 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ በሕገመንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩ ታይቶ እንዲቀርብ መርቶት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ አመልካች ከሟች አቶ አለማየሁ ታደሰ ጋር በ1995 ዓ.ም በባህል ጋብቻ ተጋብተው አቶ አለማየሁ ታደሰ በሞት እስከተለዩበት 2003 ዓ.ም ድረስ አብረው መኖራቸው ያልተስተባበለ ሲሆን በጋብቻ ወቅት በጋራ ያፈሩት ንብረት ታስቦ የድርሻቸውን ተካፋይ መሆን ሲገባቸው የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በጋብቻ ወቅት ያፈሩትን ንብረት ጨምሮ ለወ/ሮ አረጋሽ ባዲ እና ለሟች ልጆች  እንዲያስረክቡ ሲሉ የሰጡት ውሳኔ ለአመልካች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 25፣ አንቀጽ 34 እና አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተረጋገጡላቸውን መብቶች የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት ምክር ቤቱ የሕገመንግስት ትርጉም በመስጠት ወስኗል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት አመልካች በጋብቻ ወቅት ያፈሩት ንብረት ታስቦ ድርሻቸውን እንዲያገኙ ምክር ቤቱ የወሰነ በመሆኑ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጸም የውሳኔው ግልባጭ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለባለጉዳዩ ይሰጥ፡፡
3. የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይላክ፡፡

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የ/መ/ቁ 99/13

አመልካች፡- ወ/ሮ የጅቴወርቅ ከ.ዳኔ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ሚሊዮን ቅጣው

2ኛ. ወ/ሪት አልማዝ ቅጣው

3ኛ. ወ/ሮ ወርቅነሽ ቅጣው

4ኛ. ወ/ሮ መንበረ ቅጣው

5ኛ. ወ/ሮ ሄለን ቅጣው

6ኛ. ወ/ሮ ዮዲት ቅጣው

7ኛ. ወ/ሮ ምስራቅ ቅጣው

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

### ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 12/10/2010 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ዕፊው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.144441 በቀን 28/09/10 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩም የንብረት ክርክርን ይመለከታል።

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው። አመልካች ባለቤታቸው አቶ ቅጣው መሸሻ ዶሪ በ2005ዓ.ም መሞታቸውን ተከትሎ የሟች ሚስት መሆናቸውንና በጋራ አንድ ልጅ መውለዳቸውን በፍ/ቤት ማረጋገጣቸውን ጠቅሰው ከሟች ጋር የነበራቸው የጋራ ሀብት ተጣርቶ የንብረት ክፍፍል እንዲደረግና የሟች የውርስ ሀብት እንዲጣራ ጠይቀዋል። ተጠሪዎችም

የሟች ልጆች እና ወራሾች መሆናቸው በፍ/ቤት ማረጋገጣቸውን ጠቅሰው የሟች አባታቸውን የውርስ ሃብት እንዲጣራላቸው እና ክፍፍል እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱ የውርስ አጣሪ በመሾም በውርስ አጣሪው በቀረበው ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡ አመልካችም በ1991 ዓ.ም ከሟች ጋር ባደረግነው የጋብቻ ውል መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ ቂ/ክ/ከ/ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 433 የሆነው ቤት የጋራ እንዲሆን በውል መስማማታቸውን ፣ቤቱም ከሟች ጋር ያፈሩትና በሁለቱም ስም ተመዝግቦ ካርታ የወጣለት መሆኑን ገልጸው ቤቱ የአመልካችና የሟች የጋራ ንብረት ተብሎ በውርስ አጣሪው የቀረበውን ሪፖርት እንዲፀድቅላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በአስተያየታቸው የቤትቁጥር 433 የሆነው ቤት ላይ በውርስ አጣሪው የቀረበውን ሪፖርት በመቃወም ቤቱ ሟች አባታቸው ከአመልካች ጋር ከመጋባታቸው በፊት በ1975 ዓ.ም ገዝተው ሲኖሩበት የነበረ የግል ንብረት እንደሆነ፣አመልካች ከተጠሪዎች አባት ጋር አደረጉት የተባለው የጋብቻ ውልም በፍ/ቤት ያልፀደቀና ውጤት የሌለው መሆኑን፣ ቤቱ የጋራ እንዲሆን ካርታ በጋራ እንዲሰጣቸው የተጠሪዎችአባት ሟች ጠየቁበት የተባለው ፊርማም የአባታቸው አለመሆኑን ጠቅሰው ቤቱ የአመልካችና የሟች የጋራ ንብረት ሳይሆን የሟች የግል ሃብት ነው ተብሎ ለተጠሪዎች እንዲወሰንላቸው ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ይህን አከራካሪውን መኖሪያ ቤት በሚመለከት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት፣ የግራ ቀኙን ክርክር፣ የጋብቻውን ውል እና ከክፍለ ከተማው መሬት አስተዳደር የቀረበለትን ማስረጃ መርምሮ ወስኗል፡፡ ፍ/ቤቱ ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲመቸው ባደረገው ማጣራት ሟች በህይወት እያሉ በስማቸው የነበረው ቤት የአመልካችን ስም አካቶ እንዲመዘገብ በቀን 13/12/02 ዓ.ም ለክፍለ ከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ፅ/ቤት በፃፉት ማመልከቻ መሰረት ቤቱ በካ.ቁ CK520/04/937/178/02 በሟችና አመልካች ስም ተመዝግቦና ካርታ ወጥቶለት እንደሚገኝ፣በቀን 17/12/2002 ዓ.ም ደግሞ በካርታው ጀርባና በሌላ ፎርም ላይ ፈርመው ካርታውን የወሰዱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች በቤቱ ካርታ ጀርባ ያለው ፊርማ የሟች አባታቸው አለመሆኑን ገልፀው ያቀረቡትን ክርክር ሲመረምር ፍ/ቤቱ ፊርማው በፎረንሲክ ምርመራ ውጤት የሟች እንዳልሆነ ቢገለፅም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 20890 (ቅፅ5) በባለ ስልጣን ፊት የተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ያሉ ፊርማዎችና የሰነዱን ይዘት ማስተባበል አይቻልም ሲል አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፣አመልካችና ሟች ስለቤትና ይዞታ ምዝገባ ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርበውና ፈርመው ካርታውን

መውሰዳቸው በጽ/ቤቱ በመረጋገጡ ፊርማው ሊስተባበል አይችልም ብሏል፡፡ ስለሆነም የፎረንሲክ ማስረጃ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተመዝኖ መስተባበል የሚችል በመሆኑ የቀረበው ውጤት በቂርቆስ ክ/ከ/የይ/አስ/የሽ/ገ/አ/ፐ/ጽ/ቤት የቀረበውን ካርታ ሊያስተባብል አይችልም በማለት አከራካሪው ቤት የአመልካችና ሟች የጋራ ንብረት ነው ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ባደረገው ማጣራት ቤቱ በ 2002 ዓ.ም በሟችና አመልካች ስም መመዝገቡና ካርታ የወጣለት መሆኑ ብቻ ቤቱን የጋራ አያደርገውም፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 633(1) እና የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 73 መሰረት ተጋቢዎች በጋብቻ ውስጥ ባሉበት ጊዜ የሚያደርጉትን ውል በፍ/ቤት ወይም በቤተ ዘመድ ማፀደቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በሟችና አመልካች መካከል የተደረገው የጋብቻ ውል ደግሞ ድንጋጌውን የተከተለ ስላልሆነ ውሉ ህጋዊ ውጤት የለውም ሲል ቤቱ የአመልካችና ሟች የጋራ ንብረት ሳይሆን የሟች ውርስ ሀብት ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ለተጠሪዎች ወስኗል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡

አመልካች ይህ የፍ/ቤት ውሳኔ የሕገ መንግስት ጥበቃ የተደረገበትን ንብረት የማፍራት፣የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት እንዲሁም በአንቀፅ 35(7) የተመለከተውን በጋብቻ ውስጥ ያገኘሁትን ንብረት የሚያሳጣኝ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ጉባኤውን ጠይቀዋል፡፡ጉባኤው ጉዳዩን መርምሮ የፍ/ቤት ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለምክር ቤቱ በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 34(2) እና (3) ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፍቃድ ላይ ብቻ እንደሚመሰረት የደነገገ ሲሆን በዚህ መሰረት የተመሰረተ ቤተሰብ የህብረተሰብ የተፈጥሮ መነሻ በመሆኑ በመንግስት ጥበቃ እንደሚደረግለት ተደንግጓል፡፡ የተሻሻለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የቤተሰብ ህግም ለግል ንብረት እውቅና የሚሰጥ ቢሆንም በአንቀፅ 63 ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም የጋራ ንብረት እንደሆነ የህሊና ግምት የሚወስድ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ባልና ሚስት የግል ንብረታቸው ለመሆኑ ማስረዳት ካልቻሉ ንብረቱ የጋራ ንብረት እንደሚሆን ነው፡፡ይህ የሚያሳየው የቤተሰብ ህጉ ከግል ንብረት ይልቅ

ስጋራ ንብረት የበለጠ እውቅና የሚሰጥና የሚያበረታታ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ባልና ሚስት በጋብቻ አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ግንኙነታቸው ንብረትን መሰረት ያደረገ እንዳይሆን እና ሕገ መንግስቱ ለጋብቻ የሰጠው ልዩ ጥበቃ ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን ያሳያል፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይም አመልካች ከሟች ጋር በጋብቻ አብረው ሲኖሩ በሟች ስም የሚታወቀውን ንብረት የጋራ ለማደረግ ስምምነት ስለማድረጋቸው በተጠሪዎች የተካደ አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 633(1) እና የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 73 መሰረት ተጋቢዎች በጋብቻ ውስጥ ባሉበት ወቅት የሚያደርጓቸው ውሎች በፍ/ቤት ቀርበው መፅደቅ አለባቸው የተባለበት ምክንያት ከቤተሰብ ህግ አጠቃላይ መንፈስና አላማ አንፃር መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በነዚህ ድብጋጌዎች መሰረት ተጋቢዎች በትዳር ውስጥ እያሉ በመካከላቸው የሚያደርጓቸው ውሎች የፍርድ ቤት ይሁንታን እንዲያገኙ የተፈለገበት ዋናው ምክንያት "ቤተሰብ" ለሚለው ተቋም ጥበቃ ለማድረግ ያለመ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔም የጋብቻን አላማ ፣በባልና ሚስት መካከል የሚኖረውን ግንኙነትና ሕገ መንግስቱ ለጋብቻ የሰጠውን ጥበቃ እንዲሁም ሴቶች በጋብቻ ውስጥ ያላቸውን የእኩልነት መብት ግምት ውስጥ ያስገባ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት ውሉን ውድቅ ሊያደርግ የቻለው ስምምነቱ ስለመኖሩ አረጋግጦ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሰረት ውሉ በፍርድ ቤት ቀርቦ አልፀደቀም በሚል ምክንያት ነው፡፡አመልካች ከሟች ጋር በነበራቸው ጋብቻ ሟች በህገ መንግስቱ በተረጋገጠላቸው በነፃነት እና በሙሉ ፍቃድ የመወሰን መብት ተጠቅመው ንብረቱ የጋራ እንዲሆን መወሰናቸውን የስር ፍ/ቤት ካደረገው የፍሬ ነገር ማጣራት ለመረዳት ይቻላል፡፡በመሆኑም ውሉ ውጤት የሌለውና በአመልካችና በሟች ላይ ምንም ህጋዊ ውጤት የማያስከትል ነው ቢባል እንኳን ሟች በህይወት እያሉ በራሳቸው ነፃፈቃድ ቤቱ በሁለቱም ስም ተሰርቶ በጋራ እንዲሰጣቸው ጠይቀውና ፈርመው መውሰዳቸውን ስናይ የውሉ ውጤት አልባነት ቤቱ የጋራ እንዳይሆን ሊከለክለው የሚችል አይደለም፡፡በሌላ በኩል በአመልካች እና ሟች መካከል ቤቱን የጋራ ለማድረግ ውል መፈጸሙን እና ውሉ በሟች ሙሉ ፈቃድ የተፈጸመ ስለመሆኑ በፍ/ቤቱ ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ ፍ/ቤቱ በቤተሰብ ህጉ በተሰጠው የጋብቻ ውልን የማፅደቅ ስልጣን መሰረት የቀረበለትን ውል መርምሮ በማፅደቅ ማለፍ ሲገባው ውሉ ተቀባይነት የለውም ሲል መወሰኑ ሕገ መንግስቱ ለቤተሰብ የሰጠውን ጥበቃ ግምት ውስጥ ያላስገባ እና የአመልካች ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

በመሆኑም ውሳኔው በህገ መንግስቱ ለቤተሰብ ሊደረግለት የሚገባውን ጥበቃ በመቃረን አመልካች በአከራካሪው ቤት ላይ ያላቸውን የንብረት መብት እንዲያጡ ያደረገ በመሆኑ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ34 (3) እና 40(1) ጋር የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን መረዳት ተችሏል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.144441 በቀን 28/09/10 ዓ.ም በአዲስ አበባ ቂ/ክ/ከ/ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 433 የሚገኘውን ቤት የአመልካችና ሟች የጋራ ንብረት አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 34(3) እና 40(1) የሚጥስ በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈፃሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ትእዛዝ

1. የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሄር ችሎት በመ.ቁ 08145 በቀን 26/08/09 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የጸና እንዲሆን፤ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ደግሞ በምክር ቤቱ ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን የተወሰነ መሆኑን አውቀው እንዲያስፈጽሙ የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የስራ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

የፌ/ም/መ/ቁ.015/08

አመልካች፡- ወ/ሮ አዜብ ቱፋ

ተጠሪ፡- አቶ አለማየሁ መንግስቱ

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ-መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

**ውሳኔ**

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች ከተጠሪ ጋር በጋብቻ እያለን የተሰራ በአዳማ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ በካርታ ቁጥር 4495/94 የተመዘገበ የ180 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤት የጋራችን ሆኖ እያለ ባግባቡ እንኳ ባለተሰሙ የሰው ማስረጃዎች በመመስረት ቤቱ የተጠሪ የግሉ ነው በማለት በፍ/ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች የሕገ- መንግሥቱን አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ(1) 25 እ 37 ይጥሳሉ በማለት ለሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ታህሳስ 5 ቀን 2008 ዓ.ም ለጉባኤው ፅፈው ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ሃሳብ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ እያለን ተጠሪ ከጋብቻችን በፊት ከመንግሥት ባገኘው ቦዶ ቦታ ላይ ከተጋባን በኃላ በጋራ ገንዘባችን የተሰራ በአዳማ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ በካርታ ቁጥር 4495/94 የተመዘገበ የ180 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤት የጋራችን ሆኖ ተጠሪም ይህን አውቆ በመንግሥት ሰራተኞች የሀብት ምዝገባ ወቅት በፌዴራሉ ስነ-ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አስመዝግቦ እያለ ባግባቡ እንኳ ባለተሰሙ የሰው ማስረጃዎች በመመስረት በፍ/ቤቶች የተሰጡ



የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ውሳኔዎች የሕገ- መንግሥቱን አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ(1) 25 እ 37 ይጥሳሉ ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ ከላይ በአመልካች ቅሬታ ላይ የተጠቀሰውን ቤት እና በሌላ በማይንቀሳቀስ እና በሚንቀሳቀሱ ሌሎች ንብረቶች ላይ ክፍፍል እንዲደረግ ባቀረበው አቤቱታ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ አመልካች አከራካሪውን ቤት በሚመለከት ባቀረቡት ክርክር ተጠሪ ቀደም ብሎ ባዶ መሬት የተረከበ ቢሆንም ለዚሁ የተሰጠው ማስረጃ ተሰርዞ በቀን 17/11/2005 ዓ.ም. ካርታ ተሰጥቶናል፣ ቤቱን በጋብቻችን ወቅት ነው ሰርተን ያጠናቀቅነው፣ ተጠሪም ይህን ስለሚያውቅ ነው በፌዴራሉ የፀረ ሙስና እና ስነ-ምግባር ኮሚሽን የጋራ ነው ሲል ያስመዘገበው በሚል ያቀረቡት ክርክር በመሆኑ የግሌ ነው በሚል ያቀረበውን ክርክር ሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ በቀረቡ የሰው ማስረጃዎች ጋብቻቸው በ1999 ዓ.ም የተመሰረተ መሆኑን በመለየት፣ አከራካሪው ቤት ከጋብቻ በፊት ተሰርቶ የተጠናቀቀ ሆኖ በጋብቻ ውስጥ ደግሞ ለሴቶች የውበት ሳሎን አገልግሎት የሚውል አንድ ክፍል መስራቱ ተረጋግጧል በማለት አከራካሪው ቤት የተጠሪ የግል ነው ብሏል፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተሰራውን አንድ ክፍል ቤት በተመለከተ ተገምቶ የግምቱን ግማሽ የገንዘብ መጠን ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ በተጨማሪ ንብረቱ በፌዴራሉ ስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን መመዝገቡ የጋራ አያስብለውም ሲል ወስኗል፡፡

በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደዚሁም የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን አስቀርበው ከመረመሩ በኋላ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማፅናት ወስነዋል፡፡በጉዳዩ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል ወስኗል፡፡

ጉባዔው በጽ/ቤቱ በኩል ለአዳማ ከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ጉዳዩን አስመልክቶ ደብዳቤ በመፃፍ ተጨማሪ ማጣራት አድርጓል፡፡ ኤጀንሲው በቁጥር 01/78/39 በቀን 29/06/2003 ዓ.ም ጉዳዩ ስለ ወ/ሮ አዜብ ቱፋ እና አቶ አለማየሁ መንግስቱ ይመለከታል በሚል ርእስ በፃፈው ደብዳቤ፡-

‹‹ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በደብዳቤ ቁጥር አጣገ 643/06/08 ቀን 25/06/2008 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ቀበሌ 01 በካርታ ቁጥር 4495/94 በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ አጣርተን እንድንገልፅላችሁ መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፤



12

በዚሁ መሰረት ከላይ የተጠቀሰው ካርታ ቁጥር በአቶ አለማየሁ መንግሥቱ በአዳማ ከተማ በካርታ ቁጥር 4495/94 በቀን 21/10/1994 ዓ.ም ከ01 ቀበሌ 180 ካሬ ሜትር የመኖሪያ ቤት ለመስራት መሬት የወሰዱ ሲሆን፣ የቤት ግንባታ ስራ ፈቃድ ቁጥር 1/01/135/18618 በቀን 21/10/1994 ዓ.ም ወስደው በ2005 ዓ.ም በቀን 17/12/2005 ዓ.ም የንብረት ካርታ ቁጥ 4495/1994 በሆነው ላይ ሶስት ቤት ሰርተው ጨርሰው ካርታና ፕላን አረጋግጠው የወሰዱ መሆናቸውን እና በስማቸው ተመዝግቦ መኖሩን እየገለጥን ለዚህ አስረጅ ሶስት ገጽ ሰነድን አባሪ በማድረግ አብረን የላክንላችሁ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡ ‹‹በሚል ምላሹን ሰጥቷል፡፡

ጉባኤው በተጨማሪ ባደረገው ማጣራት አከራካሪውን ቤት በሚመለከት የፌዴራል የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በቀን 10/06/2007 ዓ.ም በቁጥር 15/መብ4-አ44/1413 ለአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ ንብረቱ በአመልካች እና በተጠሪ የጋራ ንብረትነት መመዝገቡን በመጥቀስ መጻፉን እና አያይዞ በላከው 7 ገጽ የሀብት ምዝገባ ቅጽ ላይ ተጠሪ ንብረቱን የጋራ ነው ሲል ማስመዝገቡን መረዳት ተችሏል፡፡

የአመልካች ዋና ቅሬታ ተጠሪ አከራካሪውን ንብረት በተመለከተ በግልፅ አምኖ በፌዴራሉ ስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጋራ ነው ሲል አስመዝግቦ ፍ/ቤቶችም አረጋግጠው እያለ ንብረቱ የተጠሪ የግል ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ የሕገ-መንግስቱን አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ አንቀጽ 25 እና አንቀጽ 37 ይጥሳል የሚል ነው፡፡

የአንድ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ጥሰት የሌላውንም ተያያዥ መብት የሚነካ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ከጉዳዩ ጋር በቀጥታ አግባብነት ካላቸው የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ 35 ንዑስ አንቀጽ (7) እና 79 ንዑስ አንቀጽ (1) አንፃር ጉዳዩ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ በጋብቻ ተጣምረው ሲኖሩ የነበረ እና ባለመግባባታቸው ጋብቻቸውን በፍቺ አጠናቀው ፍቺውን ተከትሎ ወደ ንብረት ክርክር መግባታቸውን መረዳት የሚቻል ነው፡፡

ጉባኤው በጉዳዩ ላይ የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን ለመመዝገብ ስልጣን ካለው የአዳማ ከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ኤጀንሲ በደብዳቤ ካደረገው ማጣራት ባገኘው ምላሽ አመልካች በፍ/ቤት ካቀረቡት ክርክር ጋር በሚቀራረብ መልኩ ተጠሪ ቤት ለመስራት በቀን

21/10/1994 ዓ.ም መሬት ወስደው እንደዚሁም በዚሁ ቀን የቤት ግንባታ የሥራ ፈቃድ የወሰዱ ቢሆንም ቤት ሰርተው ጨርሰው ካርታና ፕላን አረጋግጠው የወሰዱት ግን ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ ፅንቶ ባለበት በቀን 17/12/2005 ዓ.ም መሆኑ ሲታይ ተጠሪ አከራካሪው ንብረት የጋራ ነው ሲሉ ያረጋገጡበትን ግልፅ ማስረጃ ይበልጥ የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪ በግራ ቀኙ በፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ተጠሪ አከራካሪው ንብረት ከአመልካች ጋር የጋራችን ነው ሲል ለፌደራሉ የስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማመን የሰጠው ማስረጃ ያስረዳልኛል በሚል አመልካች ባቀረባቸው ክርክር የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በትዕዛዙ ያስቀረበው ማስረጃ በግልፅ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ከአመልካች ጋር የጋራችን ነው ሲል በማመን ማስመዝገቡን መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ጉባኤውም የፌዴራሉ የስነ-ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ለአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ከአባሪ ጋር የፃፈውን ደብዳቤ አስቀርቦ ይህንኑ መረዳት ችሏል፡፡

በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀጽ (1) ሆነ በኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመሳሳይ ‹‹አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል›› በሚል የተደነገገ ሲሆን በዚሁ መሰረት ተጋቢዎች ከፍቺ በኋላ በአንድ ንብረት ላይ የግል በመሆኑ ላይ ክርክር የሚያነሱ ከሆነ በሕጉ የተቀመጠውን ግምት የሚያስተባብል ማስረጃ ሊያቀርቡ የሚገባ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ባቀረቡት ክርክር መነሻ የህጉን ግምት የሚያጠናክር የሰነድ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን፣ በፍ/ቤቶች የሕጉን ግምት ሊያስተባብሉ ችለዋል የተባሉ የሰው ማስረጃዎችም መቅረባቸውን መረዳት ተችሏል፡፤በማስረጃ አቀባበል ሕግ/መርህ/ መሰረት በሰነድ የቀረበ በሰዎች የማስረጃነት ቃል ሊስተባበል እንደማይችል በግልፅ የተደነገገ ነው፡፡

በመሆኑም ጉባኤው በተያዘው ጉዳይ ፍ/ቤቶች በግልፅ ይበልጥ ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ባለመቀበል ግልፅ ድንጋጌን በመጣስ የሰጡት ውሳኔ አመልካችን በፍቺ ጊዜ ያላቸውን የእኩል መብት የሚጥስ በመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ(1) ‹‹በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፡፡ በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና



10

ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፡፡›› በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፤

እንዲሁም ውሳኔው የአመልካችን ንብረት የማፍራት መብት የሚጋፋ በመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ (7) ‹‹ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይ መሬትን በመጠቀም በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡›› በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም በተያዘው ጉዳይ ፍ/ቤቶች በግልጽ ድንጋጌ ባለመመራት የሰጡት ውሳኔ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ (3) ‹‹ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ፡፡ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡›› በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፤በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ይኸው ጉዳዩ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ የተረዳው የአዳማ ከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ባረጋገጠው መሰረት አመልካች በፍ/ቤት ካቀረቡት ክርክር ጋር በሚቀራረብ መልኩ ተጠሪ ቤት ለመስራት በቀን 21/10/1994 ዓ.ም መሬት ወስደው እንደዚሁም በዚሁ ቀን የቤት ግንባታ የሥራ ፈቃድ የወሰዱ ቢሆንም ቤት ሰርተው ጨርሰው ካርታና ፕላን አረጋግጠው የወሰዱት ግን ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ ፅንቶ ባለበት በቀን 17/12/2005 ዓ.ም መሆኑን ነው፡፡

በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀጽ (1) ሆነ በኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመሳሳይ ‹‹አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል በሚል ተደንግጎ እያለ በፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ንብረት የማፍራት መብት የሚጋፋ ከመሆኑም በላይ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ (7) ‹‹ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣

የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይ መሬትን በመጠቀም በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በተጨማሪም በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ(1) ‹‹በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው›› በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፤

በመሆኑም አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ሆኖ ስለተገኘ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በየደረጃው ባሉ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠውና በየደረጃው ባሉ የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች እንዲሁም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.120149 እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲደርሳቸው ይደረግ፡፡

2. የፌዴራሉ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

3. የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ፡፡

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣5ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሀሊማ መሐመድ

ተጠሪ፡- አቶ አደም አብዲ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

በዚህ ጉዳይ የቀረበው የሕገመንግስት የትርጉም አቤቱታ መነሻ የገጠር መሬት የግል ባለይዞታነት እና የመውረስ መብትን የሚመለከት ሆኖ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ስምንት ቀርጥ መሬት ሕጋዊ የባለይዞታነት መብት ከመጀመሪያው ጀምሮ የአመልካችና የሟች ወራሾች የሆኑት ሶስቱ ህፃናት ልጆቻቸው በጋራ - ማለትም አራቱ ቀርጥ የአመልካች ቀሪው አራት ቀርጥ ደግሞ የሟች ወራሾች የሆኑት ህፃናት ልጆች መሆኑ፣የተጠሪ የባለይዞታነት መብት ያለው ደግሞ ከሌላኛው ትዳሩ ባለው መሬት ላይ መሆኑን በማረጋገጥ የጭናክሰን ወረዳ ፍርድ ቤት እና የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጠሪው በሃይል የያዘውን የአመልካችና የህፃናት ልጆቻቸው ይዞታ የሆነውን ስምንት ቀርጥ መሬት እንዲለቅ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

በሌላ በኩል የበታች ፍርድቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የገጠር መሬት እንደ ሌላ የግል ንብረት ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ነው ሊባል አይችልም በሚል ምክንያትና አተረጓጎም ተጠሪው በሌላ ቦታ ያለው የራሱ የመሬት ይዞታ እንዳለ ሆኖ የሟች ወራሾች የሆኑት ህፃናትን ድርሻ ጨምሮ ከስምንቱ ቀርጥ መሬት ግማሽ የመካፈል መብት አለው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ውድቅ የተደረገባቸው በመሆኑ ውሳኔው በጋብቻ ስም ከመሬት መንቀልና የልጆቹን የመውረስ መብት



16

የጣሰ ስለሆነ የሕገመንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ሲሉ ለሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ ማቅረባቸውን ምክርቤቱ ተረድቷል፡፡

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤም ጉዳዩን መርምሮ ክርክር ያስነሳው መሬት በአመልካች የቀድሞ ጋብቻ ጊዜ የተሰጠ እንጂ ከተጠሪ ጋር ከተጋቡ በኃላ የተሰጠ እንዳልሆነ የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ የክልሉም የገጠር መሬት ይዞታ አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 15/8/ እና /9/ እንዲሁም የክልሉ የቤተሰብ ሕግ ሰዎች የጋራና የግል የገጠር መሬት ይዞታ ሊይዙ እንደሚችሉ የሚያሳዩ ከመሆናቸውም በላይ የኢፌዴሪ የገጠር መሬት ይዞታ አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀጽ 6/4/ እና የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች የክልሉን ሕጎች የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

ይህ ሆኖ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪው ከሌላ ጋብቻ የግሉ የይዞታ መሬት እያለው የአመልካችን የግል የይዞታ መሬት እንደጋራ ይዞታ ተመልክቶ እኩል እንዲካፈሉ መወሰኑ ሴቶችን ከግል ይዞታቸው የሚነቅልን ተግባር የሚያበረታታ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 7 ሴቶች በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው እና በተለይ መሬትን በመጠቀም፣በማስተላለፍ፣በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው የሚለውን ያላጤነ ነው በማለት ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስልገዋል ሲል የውሳኔ ሀሳብ ለምክርቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የምክርቤቱ የሕገመንግስት እና የክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ እና በምክርቤቱ ባለሙያዎች አስተያየት ላይ ከተወያየ በኃላ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክርቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ምክርቤቱም አቤቱታውን ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር በማጣመር መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ስምንት ቀርጥ የገጠር የእርሻ መሬት አመልካቿ ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የሶስት ልጆቻቸው አባት ከሆነው ሟች ባለቤታቸው ጋር በጋራ ሲጠቀሙበትና ልጆቻቸውን ሲያሳድጉበት የነበረ መሬት መሆኑ፣ የአሁኑ ተጠሪ አመልካችን



15

በአካባቢው ባህል መሰረት በውርስ ሲያገባቸው አሁን ለክርክር መነሻ የሆነውን ስምንት ቀርጥ መሬት በይዞታቸው ይዘው እንደነበረ ፣የአሁኑ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ካለው የትዳር ግንኙነት በተጨማሪ ሌላ ትዳርና የመሬት ይዞታም እንዳለው ከስር ፍርድቤት መዝገቦች ከተያያዙ ሰነዶች መረዳት ችሏል፡፡

ይህ ሆኖ እያለ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ስምንት ቀርጥ መሬት ሕጋዊ የባለይዞታነት መብት ከመጀመሪያው ጀምሮ የአመልካችና የሟች ወራሾች የሆኑት ሶስቱ ህፃናት ልጆቻቸው በጋራ ማለትም አራቱ ቀርጥ የአመልካች ቀሪው አራት ቀርጥ ደግሞ የሟች ወራሾች የሆኑት ህፃናት ልጆች መሆኑ፣ የተጠሪ የባለይዞታነት መብት ያለው ደግሞ ከሌላኛው ትዳሩ ባለው መሬት ላይ መሆኑ ግልፅ በመሆኑ የጭናክሰን ወረዳ ፍርድ ቤት እና የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጠሪው በሃይል የያዘውን የአመልካችና የህፃናት ልጆቻቸው ይዞታ የሆነውን ስምንት ቀርጥ መሬት እንዲለቅ የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ... የገጠር መሬት እንደ ሌላ የግል ንብረት ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ነው ሊባል አይችልም... በሚል ምክንያት ተጠሪው በሌላ ቦታ የራሱ የመሬት ይዞታ ያለው መሆኑ እየታወቀ የሟች ወራሾች የሆኑት ህፃናትን ድርሻ ጨምሮ ከስምንቱ ቀርጥ መሬት ግማሽ የመካፈል መብት አለው... በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ ውሳኔ ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ..ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 35 (2) (7) ሴቶች ንብረት የማፍራት በተለይም መሬትን በመጠቀም፣በማስተላለፍ፣በማስተዳደር እና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፣በአንቀፅ 36/2/ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በፍርድቤቶች፣በአስተደደር ባለሥልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የሕጻናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት፣በአንቀፅ 40/4/የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው በማለት ሕገመንግስቱ ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎች በተለይም የአመልካችና ከሟች የወለዷቸው የህፃናት ልጆቻቸውን መብቶች የጣሰ እና በገጠር መሬት ይዞታቸው የመጠቀምና ያለመነቀል እንዲሁም የመውረስ መብታቸውን የሚጋፋ ውሳኔ መሆኑን ምክርቤቱ አምኖበታል፡፡

በመሆኑም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ

የአመልካችንና ከሟች የወለዷቸው የህፃናት ልጆቻቸውን መብቶች የጣሰ በመሆኑ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1.በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገውና የአመልካችንና የሕጻናት ልጆቻቸውን ሕገመንግስታዊ የመሬት ባለይዞታነት፣የተጠቃሚነት እና የመውረስ መብቶች የሚጻረረው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን አውቀው እንዲያስፈጽሙ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡

2.የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ፡፡

1352

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣1ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ራኒያ አህመድ ኢብራሂም

ተጠሪ፡- ዶ/ር ኢብራሂም መሀመድ ሀሰን

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 34 እና 35 የተደነገጉትን የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች እንዲሁም የሴቶች መብትን የሚመለከት ሲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው በመሆኑ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በሙሉ ድምጽ የውሳኔ ሐሳብ በመስጠት ለምክር ቤቱ በመላኩ ነው፡፡

የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 8 ቀን 2007 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረን ስንኖር የነበረ ሲሆን ተጠሪ እኔን ወደ አሜሪካን ሀገር ለእረፍት እንድሄድ ካደረጉ በኋላ ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት የፍቺ አቤቱታቸውን በማስገባት ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ለታህሳስ 2 ቀን 2006 ዓ.ም እንድቀርብ የሚገልጽ የጥሪ ማስታወቂያ በማውጣት በተንኮል ጥሪው እንዳይደርሰኝ በማድረግ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34 ንኡስ አንቀጽ 5 መሰረት በሀይማኖታዊ ፍ/ቤት ለመዳኘት ግልጽ ፈቃዴን መስጠት እየተገባኝ ፈቃዴን በግልጽ ባልሰጠሁበት፣ እንደዚሁም የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው



13

አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት በቅድሚያ መጥሪያው በአግባቡ እንደደረሰኝ መረጋገጥ ሲገባው ሳይረጋገጥ በዚሁም ምክንያት ፍ/ቤቱ ስልጣን ሳይኖረው ጉዳዩን በመመልከት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን አላግባብ በመጠቀም ታህሳስ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የፍቺ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በፍቺው ውጤት ላይ በቀጠለው የንብረት ክርክር በተጠሪው ለቀረበው ማመልከቻ ተቃውሞዬን ባቀርብም ተቃውሞዬ ታልፎ ክርክሩ ቢቀጥልም መስከረም 19 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ጉዳዩ ለሕገ መንግስታዊ ትርጉም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ እንዲላክ ብጠይቅም በአቤቱታዬ ላይ ትዕዛዝ ሳይሰጥ ጉዳዩ በመታየት ላይ ይገኛል፡፡በመሆኑም የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5፣ አንቀጽ 35 ንኡስ አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 2፣ አንቀጽ 35 ንኡስ አንቀጽ 4፣ አንቀጽ 35 ንኡስ አንቀጽ 7 እና 9 በፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተጣሱ በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ታህሳስ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም ከአመልካች ጋር የነበራቸውን አለመግባባት ለመፍታት ጥረት አድርገው ያልተሳካ በመሆኑ አመልካችን የፈቱ መሆኑን ገልጸው አመልካችም ከዚህ በኋላ በራሳቸው ፈቃድ ወደ ውጪ ሀገር ሄደዋል በማለት ፍቺው እንዲጸድቅላቸው የጠየቁ ሲሆን ፍ/ቤቱም ተጠሪ ያቀረቡትን የፍቺ አቤቱታ በመቀበል አመልካች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እትም ጥሪ እንዲተላለፍ በማድረግ በጥሪው መሰረት አመልካች ሊቀርቡ አልቻሉም በማለት አመልካች በሌሉበት የፍቺ ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡ ይህም የሼሪዓ ፍ/ቤቱ አመልካቿ ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይቅረብልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ባለመቀበል ጉዳዩን ማየት መቀጠሉን ያረጋግጣል፡፡

ፍ/ቤቱ በአመልካች እና በተጠሪ መሀል በቀጠለው የፍቺ ውጤት ክርክር የካቲት 18 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 አስተዳደር በቤት ቁጥር 427 የሚገኙ የቤት ቁሳቁሶችን ቆጥራችሁ እና ገምታችሁ ለግራ ቀኙ እንድታካፍሉ የሚል እንደዚሁም አመልካች ለተጠሪ የሚያስረክቧቸውን የንብረት ዝርዝር በመጥቀስ ትዕዛዙን ሰጥቷል፡፡ ውጤቱንም ለመጋቢት 8 ቀን 2007 ዓ.ም ለመጠባበቅ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡



12

የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት በማየት ላይ ባለው ጉዳይ ቀደም ብሎ ታህሳስ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው የፍቺ ውሳኔ ላይ የተከተለውን የሕግ አግባብ ስንመለከት ፍ/ቤቱ የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ ውሳኔውን የሰጠ መሆኑን ከአጠቃላይ የውሳኔው አሰጣጥ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ የድንጋጌዎቹን ይዘት መመርመሩ ተገቢ ሆኖ ይታያል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 "ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት አቤቱታ ሲያቀርብ ጉዳዩ የቀረበለት የሸሪዓ ፍቤት ሌላው ተከራካሪ ወገን በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ፍቃደኛ መሆን አለመሆኑን ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ቅጽ መሰረት ቀርቦ እንዲያረጋግጥ መጥሪያ ይልክለታል፡፡" የሚል ሲሆን፣ የአዋጁ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 2 ደግሞ "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሰረት የፍ/ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው የተደረገ ተከራካሪ ወገን ተቃውሞውን ወይም ፈቃደኛነቱን ለፍ/ቤቱ ሬጅስትራር ቀርቦ ካላረጋገጠ ተቃውሞ ለማቅረብ እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ጉዳዩ በሌለበት ይታያል፡፡" የሚል ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም ፍ/ቤቱ ታህሳስ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው የፍቺ ውሳኔ "ተጠሪ (የአሁን አመልካች) ለቀረበባቸው ክስ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ በማለት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ 73ኛ ዓመት ቁጥር 80፣ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም ዕትም ገፅ 19 ላይ ግልጽ የሆነ ጥሪ ቢያደርግም ተጠሪ ሊቀርቡ አልቻሉም" በማለት አመልካች በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ፈቃዳቸው እንደሆነ በመውሰድ ውሳኔውን መስጠቱን መረዳት ተችሏል፡፡

በኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 34 ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ "ይህ ሕገ መንግስት የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" በሚል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ከላይ የተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ፈቃዱን ሰጥቷል ተብሎ የሚገመተው ወገን በአግባቡ መጥሪያው ሊደርሰው እንደሚገባ ያስረዳል፡፡ ድንጋጌው መጥሪያው ባግባቡ መድረስ እንዳለበት ሲያስቀምጥ በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት መሆን እንዳለበት የደነገገ በመሆኑ ከዚሁ ንዑስ አንቀጽ ይዘት አንጻር አግባብነቱ ሲታይ መጥሪያው ከአዋጁ ጋር ተያይዞ ከሚገኘው ቅጽ ጋር ለተጠሪው ተከራካሪ ወገን ደርሶት ፈቃደኛ መሆን አለመሆኑን ሊገልጽ እንደሚገባ የሚያስቀምጥ

በመሆኑ በዚሁ መሰረት መጥሪያው ባግባቡ ደርሷል ለማለት አያስችልም፡፡ አግባብነቱ ከፍታብሔር ሥነ ሥዓት ሕጉ አንጻር ቢፈተሽ እንኳ ተጠሪ ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም የፍቺ አቤቱታቸውን አቅርበው ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በጋዜጣ የጥሪው ማስታወቂያ እንዲወጣ መደረጉን ስናይ አመልካች በውጪ የሚገኙ መሆኑ በተጠሪ እየተጠቀሰ በቂ ጊዜ እንኳ አለመሰጠቱ አስፈላጊው ጥረት ተደርጎ መጥሪያው በአግባቡ ለአመልካች ደርሷቸዋል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡በድንጋጌው የተቀመጠው በአግባቡ መጥሪያው የመድረስ ፍሬ ነገር መረጋገጥ የአንደኛውን ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት የመፍቀድን ህገ መንግስታዊ መብት ፍሬ ነገር የማረጋገጥ ውጤት ያለው በመሆኑ ፍ/ቤቱ በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ትጋት የፍሬ ነገሩን መሟላት ማረጋገጥ እንዳለበት በቀላሉ መረዳት የሚቻል ነው፡፡

በመጨረሻም የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34 ንኡስ አንቀጽ 5 የተከራካሪዎች በኃይማኖታዊ ፍ/ቤት የመዳኘት ፍላጎት መረጋገጥ እንዳለበት ከሚያስቀምጠው አስገዳጅ ሁኔታ አንጻር መጥሪያ አላላኩ እንደ መደበኛው የፍትሐብሔር ክርክር የመሰማት መብትን ለማስከበር ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ የተከራካሪ ወገኖችን ፍላጎት የማግኘት ዓላማውን የማሳካት ተደራቢ ግብ መሆኑን ጭምር መረዳት ያስፈልጋል፡፡በመሆኑም በሸሪዓ ፍ/ቤቱ አንደኛው ወገን በሀይማኖቱ ሕግ የመዳኘት ፍላጎት እንዳለው በአግባቡ ሳይረጋገጥ የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ጥሰት ያለው በመሆኑ ጉባዔው በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ሊሰጥበት ይገባል በሚል በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ የውሣኔ ሃሳቡ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ በቀረበለት የጋብቻ ፍቺ አቤቱታ ክስ ላይ ተከሳሽ (የአሁኗ አመልካች) በሌሉበት ጉዳዩን በማየት ውሳኔ የሰጠበት አግባብ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 34 ንኡስ አንቀፅ 5 "ይህ ሕገ መንግስት የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" ተብሎ የተደነገገውንና ይህን ተከትሎ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁጥር



10

188/92 አንቀፅ 4 ንኡስ አንቀፅ 2 እንዲሁም አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሰረት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖች በእስልምናው ሃይማኖት ስርዓት ለመዳኘት ግልፅ በሆነ መንገድ በፈቃዳቸው መርጠው የቀረቡ ከሆነ ብቻ እንደሆነ፣ ጉዳዩ የቀረበለት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሌላው ተከራካሪ ወገን በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆን አለመሆኑን ቀርቦ እንዲያረጋግጥ መጥሪያ ሊልክለት እንደሚገባና የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት... የተደነገገውን የተከተለ/ያከበረ ውሳኔ አለመሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም የአሁኑ ተጠሪ የፍቺ አቤቱታውን ያቀረቡት ሕዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ሲሆን የአሁኗ አመልካች ወደ ውጭ አገር (አሜሪካ) መሄዳቸው እየታወቀ ለቀረበባቸው ክስ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ... የሚለው የፍርድ ቤቱ የጥሪ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ የተደረገው ከ4 (አራት) ቀን በኋላ ሕዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ መሆኑ ሲታይ ሌላው ተከራካሪ ወገን የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑ መረጋገጥ እንዳለበት በሕግ የተደነገገውን ስርዓት እንኳ ያከበረ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ፍርድቤቱ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 35 ድንጋጌዎች መሰረት ሕገ መንግስቱ ባረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድና በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላትን የአሁኑዋን አመልካች መብት ለማስጠበቅ - ወደ ውጭ አገር መሄዷ እየታወቀ ተመልሳ መጥታ በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆን አለመሆኗ ቀርባ እንድታረጋግጥ ብሎም ለቀረበባት ክስ መልስ ለመስጠት የሚያስችላት በቂ ጊዜ እንድታገኝ የሚያስችላት ረዘም ያለ ቀጠሮ መስጠት ሲገባው ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በሕግ የተሰጠውን ስልጣን የአንዱን ተከራካሪ ወገን መብት ለማስከበር ብቻ ከቅን ልቦና ውጪ ያለአግባብ የተጠቀመበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሆኑም የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የአመልካችን እና የተጠሪን ጉዳይ በተመለከተ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 34 እና 35 የተደነገጉትን የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች እንዲሁም የሴቶች መብት ድንጋጌዎችን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪዐ ፍርድቤት የሰጠው ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገ መሆኑን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ እንዲደርሰው ይደረግ፡፡

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡

የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋም ይሰጥ፡፡

ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም

## የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የስራ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

የፌ/ም/መ/ቁ/ 021/08

አመልካች፡- አቶ ብርሃኑ ረጋሳ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መስከረም ምትኩ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ-መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የዚህ ጉዳይ መነሻ የሕጻን የሞግዚትነት ሥልጣንን በተመለከተ አመልካች የሸሪዓ ፍ/ቤት የተጠሪን የሞግዚትነት ጥያቄ ተቀብሎ በማጽደቁ ሕፃን ሪያንን ለመረከብ የአፈፃፀም ፋይል አስከፍተው መጥሪያ ሲደርሰኝ ጉዳዩን ያወቅኩ በመሆኑ ፍ/ቤት ቀርቤ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፍቃዴን ባልሰጠሁበት እና ባልተከራከርኩበት የተሰጠው ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 31፣ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የሚቃረን ነው በማለት የሕገመንግስት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ ለአጣሪ ጉባኤ ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡

የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 24 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ ማመልከቻ ለጉባኤው አቅርበዋል፡፡ በማመልከቻቸውም እኔ የክርስትና እምነት ተከታይ የሆንኩ የሙስሊም እምነት ተከታይ ከነበረችው ወ/ሮ ሲሀም መሐመድ ጋር ተጋብተን አሁን እድሜዋ 1 ዓመት ከ4 ወር የሆናት ሕፃን ሪያንን ወልደናል፡፡ ባለቤቴ ከሞተች በኋላ ተጠሪ የሆኑት የባለቤቴ እናት እና የሕፃን ሪያን አያት የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጣቸው በፌ/የመ/ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ጥያቄአቸውን አቅርበው ሞግዚትነታቸውን አፀድቀዋል፡፡



12

ፍ/ቤቱም የተጠሪን የሞግዚትነት ጥያቄ ተቀብሎ ካፀደቀላቸው በኋላ ሕፃን ሪያንን ለመረከብ የአፈፃፀም ፋይል አስከፍተው መጥሪያ ሲደርሰኝ ጉዳዩን ያወኩ በመሆኑ ፍ/ቤት ቀርቤ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፍቃዴን ባልሰጠሁበት እና ባልተከራከርኩበት የተሰጠው ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4፣ አንቀጽ 13፣ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/እና ንዑስ አንቀጽ 2 ጋር የሚቃረን ነው በማለት የሕገመንግስት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች አሁን በሕይወት ከሌሉት ባለቤታቸው ለወለዷት ሕፃን ሪያን ተጠሪ የሆኑት የሕፃነዋ አያት የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጣቸው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ጥያቄአቸውን አቅርበው የሞግዚትነት ስልጣን ከተሰጣቸው በኋላ ባስከፈቱት የአፈፃፀም ፋይል አመልካች መጥሪያ ሲደርሳቸው ሸሪዓ ፍ/ቤት በመቅረብ መቃወሚያቸውን አቅርበዋል፡፡

በመቃወሚያቸውም የሕፃን ሪያን አባት የሆነው እያለ በሌሉበት ቦታ የሕፃኗ አያት የሆኑት ተጠሪ ሞግዚት ሆነው መሾማቸው አግባብ አይደለም በማለት ለተጠሪ የተሰጠው የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የአመልካችን አቤቱታ ከሰማ በኋላ ተጠሪን አስቀርቦ ያከራከረ ሲሆን ተጠሪ የአመልካች ባለቤት የሆኑት የሕፃኗ እናት ስትሞት ሕፃን ልጁን አባት የሆነው አመልካች ራሱ ተንከባክቦ ማሳደግ ሲገባቸው ሻሸመኒ የምትኖር እህቱ ጋር እንድታድግ የላኩ በመሆናቸው ሕፃኗ እኔ አያቷ ዘንድ ሆና ብታድግ የተሸለ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በሸሪዓ ሕግ በኪታብ ሙቅኒል ሙህታጅ 3ኛ ክፍል ከገጽ 452-455 የሕፃኗ እናት ከሞተች ሕጻኗን የማሳደግ ስልጣን የሚሰጠው ለእናት እናት (ለአያት) እንጅ ለአክስት ባለመሆኑ አመልካች ያቀረቡትን ተቃውሞ ውድቅ በማድረግ ለተጠሪ የተሰጠው የሞግዚትነት ስልጣን የፀደቀ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ጉባኤው የአመልካችን ጥያቄ አያይዞ ካቀረቧቸው የፍ/ቤት ውሳኔዎች እና ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 /ሐ/ እና ንዑስ አንቀጽ 2 ጋር የሚቃረን መሆን ያለመሆኑን መርምሯል፡፡

በአንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ ሕገመንግስቱ የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሐይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን

አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ተብሎ የተደነገገ ሲሆን በሕገመንግስቱ አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሐይማኖትና የባሕል ፍ/ቤቶችን ሊያቋቁሙ ይችላሉ ተብሎ ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሰረት የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነው ሕብረተሰብ የሚዳኝበት የሸሪዓ ፍ/ቤት በአዋጅ የተቋቋመ ሲሆን የፌደራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 4/ሀ/ ማናቸውም የጋብቻ፤ የቀለብ አወሳሰን፤ አካለመጠን ያልደረሱ ሕፃናት ሞግዚትነት እና በቤተሰብ ተዛምዶ ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ላይ ባለጉዳዮች በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት ፈቅደው እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከላይ በተገለጹት ጉዳዮች ላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖቹ በእስልምና ሐይማኖት ስርዓት ለመዳኘት ግልጽ በሆነ መንገድ በፈቃዳቸው መርጠው የቀረቡ ከሆነ ብቻ ነው ተብሎ ተደንግጓል፡፡

ይህ የአዋጅ ድንጋጌም በሐይማኖታዊ ፍ/ቤት ለመዳኘት ግልፅ በሆነ መንገድ በፈቃድ መርጦ መቅረብን እንደዋና መስፈርት ያስቀመጠ እንጅ የሌላ እምነት ተከታይ የሆነ ሰው በእስልምና ሐይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት የሚከለክል ያለመሆኑን ከአዋጁ መረዳት ተችሏል፡፡

አመልካች በአቤቱታቸው ላይ ፍ/ቤቱ የሕፃን ልጃቸው ሞግዚትነት ጉዳይ ላይ ተጠሪ ቀርበው የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አባት ፍ/ቤት ቀርበው ባለተከራከሩበት ቦታ መታየቱ እና የሌላ እምነት ተከታይ ሆነው በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃዳቸውን ባልሰጡበት ሁኔታ የተሰጠው ውሳኔ ከሕገመንግስቱ ጋር ይቃረናል በማለት አቤቱታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ተጠሪ ለአመልካች ሕፃን ልጅ በሸሪዓ ፍ/ቤት ሞግዚት ሆነው ከተሾሙ በኋላ አመልካች ሕፃን ልጃቸውን እንዲያስረክቡ የአፈፃፀም መጥሪያ ሲደርሳቸው ሸሪዓ ፍ/ቤት በመቅረብ ተጠሪ የሆኑት የሕፃን ልጃቸው አያት በሸሪዓ ፍ/ቤት በተሰጣቸው የሞግዚትነት ስልጣን ሣይገኙ እና ሳይከራከሩ እንዲሁም የሕፃን ልጃቸው አባት የሆኑት ራሳቸው እያሉ የሞግዚትነት ስልጣን ለአያት መሰጠቱ አግባብ ያለመሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ይህም አመልካች በመጀመሪያ መጥሪያ ቢደርሳቸው ሊያነሱ የሚችሉትን ክርክር በማንሳትና ተቃውሟቸውን በማቅረብ የተከራከሩ፤ ተጠሪም የአመልካች ተቃውሞ ላይ መልሳቸውን በመስጠት ከአመልካች ጋር የተከራከሩ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት የሚቻል ስለሆነ አመልካች



10

ከፈቃድ መስጠት ጋር አያይዘው ያቀረቡት የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ ከላይ የፌደራል የሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር ከወጣው አዋጅ አንፃር በሕገመንግስቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሐይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም ከሚለው ድንጋጌ ጋር የማይቃረን መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 /ሐ/ ማንኛውም ሕፃን ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱን እንክብካቤ የማግኘት፤ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰኑበት ጊዜ የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት ተብሎ ከተደነገገው ድንጋጌ አንፃር መርምረናል፡፡

ተጠሪ የሆኑት የሕፃኗ አያት ለፍ/ቤት ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት የሞግዚትነት ስልጣኑ ሊሰጣቸው የቻለው የሕፃንዋ አባት የሆነው አመልካች ሕጻን ልጃቸውን ራሳቸው ተንከባክበው ማሳደግ ሲገባቸው ከምትኖርበት ድሬዳዋ ከተማ ሻሸመኒ የምትኖረው እህታቸው ጋር እንድታድግ በመስጠታቸው መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ፍ/ቤቱም በሕገመንግስቱ ላይ የሕፃኗን መብት ለማስጠበቅ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ለሕጻኗ መልካም አስተዳደግ ሲባል መጣራት ያለባቸው ነጥቦች ሳይጣሩ የተወሰነ በመሆኑ ጉባኤው በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል መጣራት የሚገባቸው ነጥቦች ተጣርተው እንዲቀርቡ ከጽ/ቤቱ ለሕፃናት ፕሮጀክት ፅ/ቤት ደብዳቤ ተፅፏል፡፡

የሕፃናት ፕሮጀክት ጽ/ቤትም ግንቦት 8 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሃ/4-39/16019 በተፃፈ ደብዳቤ ለአመልካች ሕፃን ልጅ መልካም አስተዳደግ ሲባል ሕፃኗ አሁን በምትገኝበት አክስትን ጨምሮ በፍ/ቤት ተከራካሪ የነበሩት የሕፃኗ አባትና የሕፃኗ አያት የሚገኙበት አካባቢ በመሄድ ቤት ለቤት ጉብኝት እና ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቃለ ምልልስ በማድረግ ለሕፃኗ መልካም አስተዳደግ ሲባል በቀጣይ ሕፃኗን የማሳደግ መብት ለወላጅ አባት ቢሰጥና ሕፃኗ ባለችበት አክስቷ ዘንድ እንድትቆይ ቢደረግ፤ ተጠሪም በሁለት ወር አንድ ጊዜ ሕጻኗን እንዲያዩዋት የጉብኝት ሁኔታ ቢመቻችላቸውና አመልካች በስራ ምክንያት ከሻሸመኒ ድሬዳዋ ስለሚመላለሱ ሕፃንዋን ድሬዳዋ ይዘው መጥተው ለተጠሪ እንዲያስጎበኙ ቢደረግ መልካም መሆኑን፤ በውይይቱ ጊዜ ተጠሪም ሕፃኗ ድሬዳዋ ከተማ የአመልካች እናት ጋር

ማደግ ከቻለችና እርሳቸው በቅርብ መኖብኘት ከቻሉ ሕፃኗ ወላጅ አባቷ ጋር ብታድግ ቅሬታ እንደሌላቸው በሕፃኗም እድገት ዙሪያ ቅር የሚላቸው ነገር እንደሌለ መግለፃቸውን በመጥቀስ ሙያዊ አስተያየታቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ በየደረጃው ቀርቦላቸው የተመለከቱት ፍ/ቤቶች በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 /ሐ/ እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፤ በፍ/ቤቶች፤ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት መብትን በቀደምትነት በማሰብ (the best interest of the child) ሕፃኗ ማን ዘንድ ብታድግ በተሻለ ሁኔታ መብቷ ይጠበቃል የሚለውን አጣርተው መወሰን ሲገባቸው ‹‹የሕፃኗ እናት ከሞተች ሕፃኗን የማሳደግ ስልጣን የሚኖራቸው አያት እንጅ የአባት እህት ወይም አክስት አይደሉም፡፡›› በማለት የወሰኑት ውሳኔ አመልካች ከጠቀሱት የሕገመንግስቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 /ሐ/ እና ንዑስ አንቀጽ 2 ጋር የሚቃረን መሆኑን ጉባኤው በሙሉ ድምጽ የተስማማበት ስለሆነ ይህ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል፡የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው ክርክር በተነሳበት የጎጃን አሳዲገነት ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ሕፃኗን የማሳደግ ስልጣን የሚሰጠው ለአያት ስለሆነ ተጠሪ የሕፃን ሪያን የሞግዚትነት ስልጣን አላቸው በማለት የወሰነው ውሳኔ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 /ሐ/ መሰረት ማንኛውም ሕፃን ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱን እንክብካቤ የማግኘት መብት አለው፣ እንዲሁም በአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን ማለትም ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፤ በፍ/ቤቶች፤ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት የሚለውን ድንጋጌ የጣሰ ከመሆኑም በላይ የሕፃኗን ደህንነትና ጥቅም ሊጠብቅ የሚችል ማን ነው የሚለውን ሳይረጋገጥ የሕጻኑዋ አባት እያለ ለአያት የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጥ የሰጠው ውሳኔ አጣሪ ጉባኤው በአግባቡ እንደዘረዘረው ከላይ ከተጠቀሰው ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ነው፡፡



90

በመሆኑም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪዓ ፍርድቤት እና በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ ከላይ የተጠቀሱትን ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች የሚቃረን በመሆኑ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1.የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች በሕጻናት አስተዳደግ ላይ የሰጡት እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.111047 እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን እንዲያውቁት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ እንዲደርሳቸው ይደረግ፡፡

2.የሞግዚትነት ስልጣኑ ለኀጻኗ አባት ሊሰጥ ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡

3.የፌዴራሉ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

4.የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት 6ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ጉባኤ

የ/መ/ቁ. 104/13

ሀምሌ 8 ቀን 2014 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳራ ገ/ስላሴ

ተጠሪ፡- አቶ አክመል ኑር ኡርጋ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 05/05/2013 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/199991 የሰጠው ውሳኔ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ስለጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ አቤቱታ አቅራቢ አመልካች ደግሞ መልስ ሰጪ ነበሩ፡፡ ጉዳዩ ሞግዚትነትን ይመለከታል፡፡

ተጠሪ ህዳር 8 ቀን 2013ዓ.ም የተሻሻለ አቤቱታ ለፌ/መ/ደ/ ሸሪዓ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ አመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ ሲፈርስ በፍቺ ወቅት የጋራ ልጃቸውን ሕፃን መግፈራ አክመል እናቷ ጋር እንድታድግና አባቷ በየወሩ 2500 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ) ብር ለቀለብ ተቆራጭ እንዲያደርግ ተወስኖ ነበር፡፡ ነገር ግን እናቷ ስታሳድጋት የልጅቱን እምነት እንደማይቀየር እና አመልካች የእስልምና ተከታይ ነበረች፡፡ በአሁን ወቅት ግን አመልካች ልጃችንን የክርስትና እምነት ተከታይ እንድትሆን እያደረገቻት ስለሆነ ያለፈቃዴ ይህ መደረጉ አግባብ ስላልሆነ ልጄ ከኔ ጋር እንድትሆንና እኔ እንዳሳድጋት ትዕዛዝ እንዲሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አመልካች ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጡ ቀጠሮ ሲሰጣት ያልቀረበች በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቷ ታልፏል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ተጠሪ አቤቱታቸውን ከማሻሻላቸው በፊት በቀረበው ክስ ላይ በቀን 20/11/2012 በሰጡት መልስ የባልና ሚስት ፍቺ ክርክር በሚደረግበት ጊዜ ሙስሊም የነበረች እና ከተፋቱ በኋላ ወደ ክርስትና እምነት እንደተመለሰች በመግለፅ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆኗን ገልፃ መልስ በመስጠቷ አመልካች አሁን የክርስትና እምነት ተከታይ መሆኗን ለመረዳት ችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ፍ/ቤቱም በሸሪዓዊው ህግ የልጆች አሳዳጊ የሆነ ወገን

ሊያሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም አንደኛው ልጅ አሳዳጊው ወገን በእምነቱ የፀና መሆን ሲሆን ከዚህ አኳያ አመልካች ይህንን ባሟላ መልኩ ህፃኗን የማሳደግ ብቃት አላት የላትም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ አመልካች በተደጋጋሚ እምነቷን እንደምትቀይርና በአንድ እምነት የማትፀና መሆኑን ከቀረበው ማስረጃና ከአመልካች መልስ አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አመልካች ከሸሪዓ ህጉ አኳያ የህፃኗ ሞግዚት ለመሆን መስፈርቱን ያላሟላች ሆኖ ፍ/ቤቱ ስላገኘው በቀን 14/5/2011 ዓ.ም የሰጠውን የሞግዚትነት ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ ልጁን ወስዶ እንዲያሳድግ እንዲሁም አመልካች ልጅቷን ለተጠሪ እንድታስረክብ እና ልጅቷን በየ8 ቀኑ እንድትጎበኝ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ የሸሪዓ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል ፡፡ በመቀጠል ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት አያስቀርብም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ጥር 5 ቀን 2013 ዓ.ም ፅፈው ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ በአመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በሸሪዓ ፍ/ቤት በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የልጅ ቀለብና የልጅ ሞግዚትነት የሚመለከቱ ጉዳዮች በውሳኔ እልባት አግኝቷል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ቀድሞ የነበረው ውሳኔ በይግባኝ ሳይሻር በተመሳሳይ ጉዳይ አዲስ ክስ በማቅረብ አመልካች ሀይማኖቷን የቀየረች በመሆኑ የልጅቷ ሞግዚት መሆን አትችልም በማለት አቤቱታ ለሸሪዓ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ አመልካችም ከፍቺ ውሳኔ በኋላ ሀይማኖቴን የቀየርኩ በመሆኑ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፍላጎት እንደሌለኝ በመግለፅ መቃወሚያዬን አቅርቤ የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በመጀመሪያ ክስ ላይ ያቀረብኩትን በሀይማኖት ህግ ያለመዳኘት መቃወሚያ በማለፍ የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 9(1)፣34(5)፣35(1) እና (2)፣ 27(1) እና(3) ፣36(2) የሚጥስ ነው፡፡

በተጨማሪም የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች ከድጃ በሽር ጉዳይ ላይ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም እና በተመሳሳይ በአመልካች ራንያ አህመድ ጉዳይ ላይ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ የተከራካሪዎች ፍቃድ ሳይገኝ  በሀይማኖት ህግ ዳኝነት መስጠቱ የሕገ መንግስታዊ መብት ጥሰት መሆኑን ወስኗል፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ከላይ የተጠቀሱትን የሕገ መንግስት ድንጋጌዎች የሚጥስ በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤው አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ከፍ/ቤቶች ውሳኔ ፣አግባብነት ካላቸው ሕጎችና ከሕገመንግስቱ አንፃር መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ውስጥ በዋነኝነት መፍትሄ ማግኘት የሚገባው ነጥብ የልጅ ሞግዚትነት ለመወሰን በፍ/ቤቶች በቀደምትነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ ምን መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡

ከላይ ከጉዳዩ አመጣጥ እንደተገነዘብነው አመልካች እና ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት የፍቺ አቤቱታ በተጠሪ አቅራቢነት ቀርቦ የፍቺ ውሳኔ እና በቀለብና በልጅ አስተዳደግ ላይ ውሳኔ አግኝቶ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የነበረ መሆኑ ከፍ/ቤቶች ውሳኔ መረዳት ይቻላል፡፡ በውሳኔውም ተጠሪ ለልጁ ቀለብ ብር 2500 እንዲከፍል እና ህፃኗ አመልካች(እናቷ) ጋር እንድታድግ ተወስኖ ነበር፡፡

ተጠሪ በድጋሚ በአመልካች ላይ ባቀረቡት አቤቱታ አመልካች እምነቷን የቀየረች ስለሆነ የልጅቷ አሳዳጊ ልትሆን አትችልም በማለት ለሸሪዓ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ፍ/ቤቱ አመልካች እምነቷን ለመቀየሯ ተረጋግጧል በማለት ልጅቷን ለተጠሪ ታስረክብ በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊነት እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 36(2) ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል በጎ አድራጎት ተቋሞች፣በፍርድ ቤቶች፣በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህ ማለት አመልካችና ተጠሪ መካከል ያለው ክርክር ከህፃንሞግዚትነት ጋር የተያያዘ ሲሆን የልጅነት ሞግዚትነትን ለአሁን አመልካች በሸሪዓ ፍ/ቤት ተወስኖላት የነበረ መሆኑ፣ነገር ግን የአሁን ተጠሪ የልጅቷን ሞግዚትነት ከአመልካች ለመውሰድ የአመልካችን እምነት መቀየር እንደ መከራከሪያ አድርጎ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን ለአቤቱታው መልስ እንድትሰጥ ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር፡፡በዚሁ መሰረት አመልካች ለፍ/ቤቱ በሰጠችው መልስ ቀደም ሲል በሀይማኖት ፍ/ቤቱ ቀርባ የተዳኘችው የሀይማኖቱ ተከታይ በመሆኗ ነገር ግን ከፍቺ ውሳኔ በኋላ እምነቷን ወደ ክርስትና የቀየረች መሆኑን ፣በሸሪዓ ሕጉ ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆኗን፣ሀይማኖት መቀየር ሞግዚትነትን እንደማያስነጥቅ እና መብቷ መሆኑን፣እንዲሁም ይህ የሚታለፍ ከሆነ ሸሪዓ ፍ/ቤቱ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ እንዲታይ እንዲወስንላትና ሞግዚትነትም ክርክሩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ከህፃናት መብትና ጥቅም አንፃር ለህፃኗ መብት ቀደምትነት ባማከለ መልኩ እንዲወሰን መቃወሚያና አማራጭ መልስ መስጠቷን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 36(2) የተረጋገጠው የህፃናት ጥቅም የማስጠበቅ ግዴታ አስመልክቶ ከዚህ በፊት በአመልካች ብርሀኑ ረጋሳ እና ተጠሪ ወ/ሮ መስከረም ምትኩ በተመሳሳይ የሞግዚትነት ጉዳይ እና የህፃናትን አስተዳደግ ከመወሰን ጋር ተያይዞ በፌዴሬሽን ምክር ቤቱ መዝገብ ቁጥር 021/08 ፀድቆ አስገዳጅ ውሳኔ ሆኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ፍ/ቤቶች የህፃናት ሞግዚትነት ክርክር አስመልክቶ ውሳኔ በሚሰጡበት ግዜ በዋናነት ታሳቢ ማድረግ ያለባቸው በሕገ መንግስቱ የተደነገገው የህፃናትን ጥቅም በቀደምትነት ማስጠበቅ መሆን እንዳለበት ተወስኗል፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በሸሪዓ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከህፃኗ አስተዳደግ ጋር በተያያዘ በተሰጠው ድምዳሜ መሰረት ጉዳዩን በየደረጃው ቀርበላቸው የተመለከቱት ፍ/ቤቶች በተለይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሸሪዓ ፍ/ቤት የደረሰበትን ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 36(2) መሰረት

የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ከህፃኗ እድሜ አንፃር ማን ዘንድ ብታድግ የተሻለ ይሆናል? ለህፃኗ ትምህርት፣ጤና፣እድገት በተለይም
በማህበራዊ ሳይንስ እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች በሚሰጡት ምክር ተደግፎና ተጣርቶ
መወሰን ሲገባው ሸሪዓ ፍ/ቤቱ ቀድሞ ለአመልካች የተሰጠውም የሞግዚትነት ስልጣን አመልካች
ሀይማኖቷን መቀየሯን ብቻ መሰረት በማድረግ በመሰረዝ የሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል
ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 36
ንኡስ አንቀፅ 1(ሐ) እና ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት ህፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ
በመንግስታዊ ወይም በግል በጎ አድራጎት ተቋሞች፣በፍርድ ቤቶች፣በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም
በህግ አውጪ አካላት የህፃናት መብትን( the best interest of the child) በቀደምትነት ማሰብ አለባቸው
የሚለውን መርህ የተከተለ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ህፃኗን የማሳደግ ስልጣን በመሰረዝ
ተጠሪ እንዲያሳድግ በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 36 ንኡስ አንቀፅ 1(ሐ) እና ንኡስ
አንቀፅ 2 ጋር የሚቃረን ነው፡፡

ሌላው የሸሪዓ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣንን ሕገ መንግስታዊነት እንደሚከተለው
መርምሯል፡፡እንደመረመረውም የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 34(5) ሕገ መንግስቱ የግልና የቤተሰብ ህግን
በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖታቸው ወይም በባህላዊ ህጎች መዳኘትን አይከለክልም፡፡
የዳኝነት ስልጣን የመደበኛ ፍ/ቤቶች ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ነው፡፡በህግ
የተቋቋሙት እነዚህ ተቋማት የዳኝነት ስልጣን አስገዳጅ ነው፡፡ በመሆኑም የሀይማኖት ወይም የባህል
ተቋማት የዳኝነት ስልጣን በተከራካሪ ወገን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ፈቃድ ከሌለ የዳኝነት
ስልጣን አይኖረውም፡፡ ሕገ መንግስቱን ተከትሎ የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን ለማጠናከር በወጣው አዋጅ
ቁጥር 188/92 አንቀፅ 4(2) በተመሳሳይ ሁኔታ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 34(5) በተገለጸው መሰረት
ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖች በእስልምና ኃይማኖት ስርአት ለመዳኘት
ግልፅ በሆነ መንገድ በፈቃዳቸው መርጠው የቀረቡ ከሆነ ብቻ ሲሆን የኃይማኖት ፍ/ቤቶች የዳኝነት
ስልጣን ከመተግበራቸው በፊት ባለጉዳዮች ፈቃደኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዳለባቸው በግልፅ
ተደንግጓል፡፡ ተከራካሪዎች ፈቃደኛነታቸውን መግለፅ የሚችሉት እንደነገሩ ሁኔታ ክስ በመሰረቱት
ወይም በክሱ መልስ እንዲሰጡ በተጠየቁበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚሆነው ለቀረበው ክስ ተከሳሹ
መልስ በሚሰጥበት ቀን ነው፡፡

የፌዴሬሽን ም/ቤት በከድጃ በሽር ጉዳይ ላይ በግል እና በቤተሰብ ጉዳይ ላይ በሃይማኖት ወይም በባህል
ሊዳኙ የሚችሉት በተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ ብቻ መሆኑን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 34(5) በተደነገገው
መሰረት የተከራካሪዎች ፈቃድ ሳይገኝ በሃይማኖት ሕግ ዳኝነት መስጠት ሕገ መንግስታዊ ጥሰት ነው
በማለት ወስኗል፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች ከአሁን ተጠሪ ነሀሴ 1 ቀን 2012 ዓ.ም ለቀረበው አቤቱታ (ክስ) ምላሽ
በምትሰጥበት ወቅት ማለትም ነሀሴ 20 ቀን 2012 ዓ.ም ወደ ክርስትና እምነት የተመለሰች መሆኑን



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

በመግለፅ በሸሪዓው ፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆኗን በመቃወሚያ ላይ ያቀረበች መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ ተጠቅሷል። ለፍርድ ቤቱ ያቀረበችው መልስ ዝርዝር ከ መዝገቡ ጋር ተያይዟል። ነገር ግን የሸሪዓ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በድጋሚ አመልካች ህዳር 8 ቀን 2013 ዓ.ም አሻሽለው አቅርበዋል ለተባለው ክስ አቤቱታ የአሁን አመልካች የተሻሻለ መልስ ያልሰጠች ቢሆንም በቃል ቀርባ ባስረዳችው መሰረት ከፍቺ በኂላ ወደ ክርስትና እምነት የተመለሰች መሆኑ በመግለጽ በሸሪዓው ህግ እንደማትዳኝና ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲታይ እየጠየቀች መቃወሚያውን በመተው በሸሪዓው ህጉ መሰረት በመዳኘት ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 34(5) እና አንቀፅ 9 እንዲሁም አንቀፅ 27(1) እና (3) የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል።

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ የሸሪዓ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 19866 በቀን 07/04/2013 ዓ.ም አመልካች ሃይማኖቷን በመቀየሯ ምክንያት የህፃኗ ሞግዚት መሆን አትችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 199991 ውሳኔውን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 36(2) የሚጥስ ስለሆነ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 9(1) መሰረት ተፈፃሚነት የለውም።
2. አመልካች የህፃን መግፈፉ አክመል ሞግዚት መሆኗ ቀድሞ በሸሪዓ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የፀና እንዲሆን የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን መረዳት ተችሏል።
3. የሕገ መንግስት ትርጉምና የውሳኔ አፈጻጸም ክትትል ቋሚ ኮሚቴ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ከሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል። በዚሁ መሰረት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚነቀፍበት ምክንያት ባለመኖሩ ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ ተቀብሎ እንዲያጸድቀው በማለት ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።
4. ስለሆነም ምክር ቤቱ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 19866 በቀን 07/04/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 199991 በቀን 30/04/2013 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 34 (5) እና አንቀጽ 36 (2) ድንጋጌዎችን ስለሚቃረን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ወስኗል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

## ትእዛዝ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 19866 በቀን 07/04/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ስለሚቃረን ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ የሰጠ ስለሆነ የምክር ቤቱን ውሳኔ አውቆ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽም የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 199991 በቀን 30/04/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ስለሚቃረን ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ የወሰነ መሆኑን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለባለጉዳዩ ይሰጥ፡፡
4. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

8ቁ6/05

# የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣1ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም

አመልካች፡- የህፃን ሱራፌል ዘውዱ እናት እሙሃይ ገ/ኢየሱስ

ተጠሪ፡-አቶ ዘውዱ መርሻ

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች መጋቢት 14 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 36 የተመለከተው የሕፃናት መብትና ኢትዮጵያ ያፀደቀችውን የዓለም አቀፍ የሕፃናት መብት ስምነትን የሚጥስ የፍርድ ቤት ውሳኔ በልጄ በሕፃን ሱራፌል ዘውዱ ላይ ስለተላለፈ ይህ እንዲታረም በማለት የሕገ-መንግሥት ትርጉም እንዲሰጣቸው አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገመንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

የጉዳዩም ፍሬ ሃሳብ አመልካች ወ/ሮ እሙሃይ ገ/እየሱስና አቶ ዘውዱ መርሻ በተባለው ግለሰብ መካከል በተደረገው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት ሕፃን ሱራፌል ዘውዱ ስለተወለደ የተጠሪ አባትነት ይረጋገጥልኝ በማለት አመልካች በሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱ ሲሆን ተጠሪም ክሱን ስለካደ አመልካች የሰው ምስክር አቅርባ ምስክሮቹ ከተጠሪ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸውና በኋላም ሕፃኑ የተወለደ መሆኑን መስክረዋል፡፡ተጠሪም በራሱ በኩል የሰው ማስረጃ አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ምስክሮቹም ተጠሪና አመልካች ጎረቤታሞች እንደነበሩና ብር 1000(አንድ ሺ ብር) በስጦታ መስጠቱን እንደሚያውቁ እንጂ ሌላ ግንኙነት መኖሩን እንደማያውቁና ግን የልጁን አባትነት አለመቀበሉን መስክረዋል፡፡



9

የከፍተኛው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን በዚህ ሁኔታ ካከራከረ በኋላ የአመልካችን አቤቱታ በመቀበል ተጠሪ የልጁ አባት ነው ብሎ ወስኗል፡፡ ተጠሪም በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ጠይቆ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም የተጠሪ አባትነት በማስረጃ አልተረጋገጠም ሲል የከፍተኛውን ፍ/ቤት ሽሮ ተጠሪን በነፃ አሰናብቷል፡፡ አመልካቿም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ ብታቀርብም በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ቅሬታዋን አላቀረበችም በማለት አቤቱታውን አልተቀበለውም፡፡ በመቀጠል ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ ብታቀርብም የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት አቤቱታዋ ውድቅ ሆኗል፡፡

የአመልካች ቅሬታም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በሚያይበት ጊዜ ተጠሪው በሀሰት አመልካች በአካባቢው የለችም በማለት እኔ በሌለሁበት ጉዳዩ እንዲታይ አድርጎ ማስወሰኑን፡ ተጠሪ በከፍተኛ ፍ/ቤት መልስ ሲሰጥ የዘረ-መል (DNA) ምርመራ እንዲደረግ ሲያመለክት እኔም ተስማምቼ አያለሁ ፍ/ቤቱ አላግባብ ይህን ጥያቄ ማለፉ፡ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ይህንን ሳያጣራ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻሩ፡ እንዲሁም የተሰጠው ውሳኔ ‹‹In the best interest of the child” የሕፃኑን መሰረታዊ መብትና ጥቅም የሚለውን ዓለም አቀፋዊ መርህ›› የሚቃረንና የሕፃኑን ወላጆቹን የማወቅና ከእነሱም እንክብካቤ የማግኘት መብት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን የሚፃረር ነው የሚል ነው፡፡

ፍሬ ሃሳቡ ከዚህ በላይ እንደተዘረዘረው ሲሆን ‹‹ተጠሪ አገባሻለሁ ብሎኝ የግብረ ስጋ ግንኙነት አድርገን ከዚሁ የተነሳ ሕፃን ሱራፌል ስለተወለደ የልጁ አባትነት ይታወቅልኝ›› ስትል አመልካች ክስ የመሰረተች ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይህን ክዷል፡፡ ሆኖም አመልካች ከወለደች በኋላ ተጠሪው ብር 1000 በቅንነት ሰጥቻታለሁ፤ የእኔና የልጁ ደም ተወስዶ የዘር-መል ምርመራ እንዲደረግልኝ›› ሲል በከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን የተመለከተው የአማራ ክልል የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች በኩል የቀረበው የሰው ምስክር በቂ ነው በማለት የዘረ-መል ምርመራውን ሳያዝ የልጁ አባት ነው ብሎ ወስኗል፡፡ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤትም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበውን ማስረጃ በቂ አይደለም ብሎ ውሳኔውን ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ በቅሬታው ባመለከተው መሰረት የዘረ-መል(DNA) ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡



8

ውሳኔው በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተውን ማንኛውም ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች ሲወሰዱ በመንግሥታዊ ወይም በግል በጎ አድራት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጭው አካላት የሕፃናት ደኅንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት የሚለውን ድንጋጌ እንዲሁም ኢትዮጵያ ባጸደቀቸው የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 4 መሠረት በስምምነቱ ዕውቅና ያገኙትን የሕፃናት መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ የሕግ የአስተዳደርና ሌሎች ዕርምጃዎችን ሁሉ ተዋዋይ አገራት መውሰድ ያለባቸው የሚለውን በሚቃረን መልክ የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚም የአመልካች አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል ብሎ አቤቱታውን ውድቅ ማድረጉ በሞግዚቷ ስህተትና በሥነ-ሥርዓታዊ ጉዳይ የሕፃኑን ሕገ-መንግሥታዊ መብት የሚጥስ ውሳኔ መስጠቱ የሕፃኑን መሰረታዊ መብትና ጥቅም የሚጎዱና በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል(ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን ሕፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅና ከእነሱም እንክብካቤ የማግኘት መብት የሚጥስ ስለሆነ ጉዳዩ የልጁን ሕገ-መንግሥታዊ መብት በሚያስጠብቅ መልኩ ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ስለሚገባ የሕገ-መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ጉዳዩ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል የሚል ነው

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገመንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው የሕጻን ሱራፌል ወላጅ እናት ሕጻኑ ከአቶ ዘውዱ የተወለደ በመሆኑ አባትነቱ እንዲረጋገጥለት በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት ክስ ካቀረበች በኃላ ፍርድቤቱ በአመልካች በኩል የቀረበው የሰው ምስክር በቂ ነው በማለት ተከሳሹ የልጁ አባት ነው ብሎ ቢወስንም ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበው ማስረጃ በቂ አይደለም ብሎ ውሳኔውን ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ በቅሬታው ባመለከተው መሰረት የዘረ-መል(DNA) ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡አመልካቿም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ ብታቀርብም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቅሬታዋን አላቀረበችም በማለት አቤቱታውን አልተቀበለውም፡፡

ይሁን እንጂ የሕጻናትን ጉዳይ በተመለከተ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 36 ድንጋጌዎች መሰረት ፍርድ ቤቶችም ሆነ ሌሎች የመንግስት አካላት ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወስዱበት ጊዜ የሕጻናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ እንዳለበት በአስገዳጅ ሁኔታ ተመልክቶ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሕጻኑ አባት አይደለም በማለት ሲወስንና የሰበር ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ በጊዜ ገደብ ምክንያት ውድቅ ማድረጉ የሕፃኑን ሕገ-መንግሥታዊ መብት የሚጥስ እና የሕፃኑን መሰረታዊ መብትና ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በሕጻን ሱራፌል ጉዳይ ላይ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት የተሰጠው ውሳኔ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል(ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን ሕፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅና ከእነሱም እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው የሚለውን ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

## ትዕዛዝ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ ሕገ-መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው የተደረገ መሆኑን አውቆ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት የሕጻኑን መሰረታዊ መብትና ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ እንዲወስን የውሳኔው ግልባጭ እንዲደርሰው ይደረግ፡፡

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡

የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ፡፡

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የ/መ/ቁ 94/13

አመልካች፡- ወ/ሮ ትዕግስት መንግስቱ

ተጠሪ፡- አሚላ አለምነው

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 07/11/2009 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ ሲሆን፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.138440 በቀን 20/10/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በአ/ብ/ክ/መንግስት በደቡብ ወሎ ዞን ደላንታ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡

የክሱ ይዘትም ከአሁን አመልካች ጋር ከየካቲት 13/2016 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ አብረን ስንኖር የነበረ ቢሆንም ተጋብተን በሶስተኛው ወር ግንቦት ወር 2006 ዓ.ም ላይ የተወለደው ልጅ ሕፃን በፍቃዱ የእኔ ልጅ ስላልሆነ በሳይንሳዊ የዘረ መል (DNA) ምርመራ ተረጋግጦ የኔ ልጅ አለመሆኑ ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ተከሳሽ በመሆን በሰጡት መልስ በዚህ ጉዳይ ላይ ከዚህ ቀደም በፍርድ ቤት በነበረው የጋብቻ ፍቺና የንብረት ክርክር ወቅት ልጅ በፍቃዱ የራሱ የአሁን ተጠሪ ልጅ መሆኑ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ በመሆኑ ዳግም ሊታይ አይገባም፡፡ልጁ የተጠሪ ለመሆኑ በሳይንሳዊ የዘረ መል ምርመራ እንዲረጋገጥ ለማስመርመር ፍቃደኛ አይደለሁም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በአሁን አመልካች የተነሳው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ አባትነትን ለመካድ ሌላ ክስ ለማቅረብ የሚከለክለው ሕግ የለም ።ነገር ግን ለክርክር ምክንያት የሆነው ልጅ የተጠሪ ነው ወይስ አይደለም ፍሬ ነገር በማስረጃ ለማረጋገጥ የአሁን አመልካች ህፃን በፍቃዱን ለማስመርመር ፍቃደኛ አይደሉም ።በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የህግ ግምት በመውሰድ ህፃን በፍቃዱ የተጠሪ ልጅ አይደለም በማለት ወስኗል።

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ህፃን በፍቃዱን እንዲያስመረምሩ ብዙ ቀጠሮ ቢሰጣቸውም ለማስመርመር ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ፍርድ ቤቱ በህግ በተቀመጠው አግባብ ውሳኔ መስጠቱ ትክክል ነው በማለት የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በማፅናት ወስኗል።

ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎቶች ቀርቦ በጉዳዩ ላይ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል።

አመልካች ከተጠሪ ጋር በአ/ብ/ክ/መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀፅ 1 መሰረት ቅድመ ጋብቻ ትጭጭት ፈፅመንና በቃልኪዳን ተሳስረን በነበርንበት ወቅት የግብረ ስጋ ግንኙነት በማድረጋችን ልጁ የተጸነሰ መሆኑን በመግለፅ ይህ የፍ/ቤት ውሳኔ የሕገ መንግስት ጥበቃ የተደረገበትን የህፃናት መብት እና ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው ዓለማቀፍ የሴቶችና ሕፃናት መብት ስምምነቶች በግልፅ የሚጥስ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ጉባኤውን የጠየቁ ሲሆን ጉባኤው ጉዳዩን መርምሮ የፍ/ቤቶች ውሳኔው ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለምክር ቤቱ በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

ጉባኤው ባቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ትንታኔ ላይ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 36 እና ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው ዓለማቀፍ የሕፃናት መብት ስምምነቶች አንፃር የመረመረ ሲሆን ጉዳዩን ለመመርመር ሶስት ጭብጦችን የለየ ሲሆን እነሱም፦

1ኛ. በፍርድ ቤቶች በነበረው ክርክር ህፃን በፍቃዱ የአሁን ተጠሪ ልጅ መሆኑ ቀድሞ በሌላ ፍ/ቤት ውሳኔ ማግኘቱ አሁን ከቀረበው ክርክር ጋር እንዴት ይታያል?

2ኛ. ተጠሪ አባት አለመሆኑን የመካድ አቤቱታ ማቅረብ የሚችልበትን ጊዜ የክልሉ የቤተሰብ ህግ ድንጋጌ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 36 አንፃር መተርጎም የለበትም ወይ?

3ኛ. ህፃናት አባታቸውን ለማወቅ የህፃኑ ቤተሰቦች በሚያደርጉት ክርክር ውስጥ ከቤተሰቦቻቸው እኩል ሳይንሳዊ የደም ምርመራዎችን የማድረግ ህጋዊ ግዴታ አለባቸው ወይ? ምርመራ ለማድረግ ግዴታ ካለባቸውስ በህግ የተቀመጠው የማስረጃው ውጤት በእነርሱ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ወይ? የሚሉት ናቸው፡፡

የኢ..ፌ..ዴ..ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 36 ስር ከተደነገጉት የህፃናት መብቶች ውስጥ አንዱ የህፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅ ሕገ መንግስታዊ መብት ነው፡፡ ከሕገ መንግስታዊ ድንጋጌው በተጨማሪ ስለ ህፃናት መብት የሚደነግጉ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለማቀፍ ስምምነቶችን ማየት ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ ህዳር 29 ቀን 1984 ዓ.ም እና ጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የጸደቁትን የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽንስ አንቀፅ 3(1) እና የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀፅ 4(1) መሰረት ፍርድ ቤቶችም ሆኑ ሌሎች አካላት ህፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሲሰጡ የህፃናቱን ጥቅምና ደህንነት በዋነኝነት ማስጠበቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በሕገ መንግስታችን አንቀፅ 9(4) መሰረት ደግሞ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለማቀፍ ስምምነቶችን የሀገሪቱ ሕግ አካል እንደሆኑ ተደንግጓል፡፡

የኢ..ፌ..ዴ..ሪ ሕገ መንግስትና አለም አቀፍ ስምምነቶች ስለ ህፃናት መብትና ጥቅም ከላይ የደነገጉትን መሰረት በማድረግ በዚህ ጉዳይ ወደ ተያዘው የመጀመሪያ ጭብጥ ስንመለከት የአሁን አመልካች የህፃን በፍቃዱ እናት ሲሆኑ ከአሁን ተጠሪ ጋር በጋብቻ አብረው የነበሩ መሆኑን እና ጋብቻቸው በፍቺ መፍረሱን በፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ግራ ቀኙ የጋብቻቸውን ፍች በሚመለከት በፍርድ ቤት በነበራቸው ክርክር ወቅት የአሁን ተጠሪ ህፃን በፍቃዱ የኔ ልጅ አይደለም የሚል ክርክር አንስተው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 147 እና 155 መሰረት በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው እንደሆነ ስለሚደነግግ ተጠሪ የህፃኑ አባት ነው ብሎ ወስኗል፡፡ በተጨማሪም ፍ/ቤቱ ይህንን መሰረት በማድረግም የአሁን ተጠሪ ለአሁን አመልካች በወር 300ብር ለህፃኑ ቀለብ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡ ከዚህ ውሳኔ መረዳት የሚቻለው ህፃን በፍቃዱ የአሁን ተጠሪ ህጋዊ ልጅ መሆኑ በፍርድ ቤቶች ውሳኔ አግኝቶ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ይህ ውሳኔ በፍርድ ቤት ያልተሻረ እና በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ መሰረት ለአሁን አመልካች ህፃን በፍቃዱ ቀለብ ሲከፍል ከቆየ በኋላ አሁን ለሕገ መንግስት ትርጉም ምክንያት የሆነውን የልጁን አባትነት ለመካድ በክልሉ የቤተሰብ ህግ

መሰረት ሌላ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡የክልሉ የቤተሰብ ህግ ይህንን አቤቱታ ማቅረብ እንደሚቻል ቢደነግግም አፈፃፀሙ እንዴት እንደሚሆን፣ ቀድሞ ተሰጥቶ ከነበረው ውሳኔና ማስረጃ አንፃር እንዴት እንደሚታይ እና አጠቃላይ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ በፍ/ቤቶች በአግባቡ ሊጤንና ከሕገ መንግስቱ የህፃናት መብት አንፃር መታየት ያለበት ነው፡፡

በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 187(1) መሰረት የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ ማቅረብ የሚቻለው የልጁ መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ በ180 ቀናት ውስጥ መሆን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ ህፃን በፍቃዱ ከተወለደ ከአንድ አመት በኂላ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የአሁን ተጠሪ ልጁ የኔ አይደለም በማለት እንደተከራከረ እና የግራ ቀኙ ፍቺ በፍርድ ቤት ከተወሰነ በኂላም የልጁን ቀለብ ሲከፍል ቆይቶ አዲስ ክስ የከፈተ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይህ በሕጉ የተደነገገው የመካድ ክስ የማቅረቢያ ግዜም ከሌሎች የይርጋ ግዜዎች ጋር በአንድነት መታየት የሌለበት እና ህገ መንግስታዊ የህፃናትን መብትና ጥቅምን ለማስጠበቅ ሲባል እንዲህ አይነት የይርጋ ግዜ በተከራካሪ ወገኖች ባይነሱም ፍ/ቤቶች ሊመረምሩአቸው የሚገቡ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ፍ/ቤቱ ተጠሪ ያቀረቡትን አባትነትን የመካድ ክርክር በማስረጃ ለማረጋገጥ ህፃን በፍቃዱ የሳይንሣዊ የዘረ መል ምርመራ እንዲያደርግ ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር ፡፡ ነገር ግን አመልካች የልጁን የዘረ መል ምርመራ ለማድረግ ፍቃደኛ አልሆኑም ፡፡ፍ/ቤቱም ይህንንም መሰረት በማድረግ ብቻ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በመሰረቱ ህፃናት እንደየ እድሜ መጠናቸው ሊሰጣቸው የሚገቡ ጠቃሚ ህክምናዎች ቢኖሩም ለሌላ አላማ የሚውሉ ለምሳሌ በያዝነው ጉዳይ ለፍርድ ቤት ማስረጃነት የሚውሉ የህክምና ምርመራዎችን ለማድረግ መገደድ አይኖርባቸውም፡፡ ባለመገደዳቸውም ለዚሁ አላማ በህጉ የተደነገገው የህግ ግምትም በህፃናት ላይ ተፈፃሚ ሊሆን አይገባውም፡፡

ይልቁንም ፍ/ቤቶች በማስረጃ አሰማም ሆነ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 36(2) የተደነገገውን የህፃናት ህገ መንግስታዊ መብት መሰረት በማድረግ በህፃኑ ላይ ከሚደረገው ምርመራ ይልቅ ጉዳዩን በማናቸውም ማስረጃዎች በማጣራት፣ በጉዳዩ ላይ ቀድሞ ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት ነበረባቸው፡፡ በተለይም የህገ መንግስቱን መርህ መሰረት አድርጎ የተቀረጸውና አባትነትን ለመካድ በጠባቡ ያስቀመጠውን የቤተሰብ ህጉን ድንጋጌዎች በመከተል ውሳኔ መስጠት ነበረባቸው፡፡ ነገር ግን ተጠሪ

የጠየቀውንና በህፃኑ ላይ የሚደረገው የዘረ መል ሳይንሳዊ ምርመራ ባለመደረጉ ብቻ ውሳኔ መስጠት በሕገ መንግስቱ የተደነገገውን የህፃኑን መብት የሚጥስ ነው፡፡

በመሆኑም ፍርድ ቤቶች የቤተሰብ ህጉና ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌው በሚቃረን መልኩ የህፃን በፍቃዱ አባት ተጠሪ እንደሆነ መጀመሪያ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔን ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ በተጠሪ የቀረበውን በህፃኑ ላይ መደረግ አለበት ባሉት የዘረ መል ምርመራ አለመደረግ ብቻ እንደ በቂ እና የመጨረሻ ማስረጃ በመውሰድ የሰጡት ውሳኔ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 36(1) ሐ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም በአ/ብ/ክ/መንግስት በደቡብ ወሎ ዞን ደላንታ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 28294 ላይ ክርክር ተጀምሮ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 13440 ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሠጠበት ጉዳይ ከ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 36(ሐ) ጋር ይቃረናል በማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 84(1) መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን መረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሕገ መንግስቱ ጥበቃ የተደረገለትን የህፃናት መብት እና ጥበቃ ከግምት ያላስገባ በመሆኑ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ትእዛዝ

1. በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች በዚህ መዝገብ የሰጡትና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፀናው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን እንዲያውቀው ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች በዚህ መዝገብ የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ስለሚቃረን ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ የሰጠ ስለሆነ ፍርድ ቤቶቹ ውሳኔውን አውቀው ተገቢውን እንዲፈጽሙ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ፡፡

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ. 96/13

አመልካች፡- ህፃን ኖህሚ ታሪኩ ብርሀኑ /ሞግዚት እና አስተዳዳሪ ወ/ሮ አረጋሽ አባተ ወኪል አቶ አባተ ዳዲ/

አድራሻ፡- አ.አ ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤ/ቁ 955

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ ወ/ሪት አማረች ብርሀኑ

2ኛ/ ወ/ሮ አለምነሽ ብርሀኑ

3ኛ/ አቶ ጌታመሳይ ብርሀኑ

አድራሻ፡- አ.አ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤ/ቁ 1697/1698

የኢፌዴሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

### ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ11/12/2012 ዓ.ም ለጉባኤው ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ሲሆን ጉዳዩም ልጅነት ይረጋገጥልኝ የሚል ክርክርን የተመለከተ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት መጋቢት 11 ቀን 2009 ዓ.ም በመ.ቁ 68524 ባቀረቡት ክስ የተጠሪዎች ወንድም የሆነው አቶ ታሪኩ ብርሃኑ ከወ/ሮ አረጋሽ አባተ ጋር ህዳር 27 ቀን 2005 ዓ.ም ጋብቻ የፈፀሙ መሆኑን ገልጸው ጋብቻ ከተፈፀመ በኋላ በ4 ወራቸው ህጻን ኖህሚ ታሪኩ መወለዷን እና አቶ ታሪኩ ብርሃኑ በደማቸው ኤች አይ ቪ ቫይረስ ተገኝቶባቸው ለረዥም ጊዜ ታመው የካቲት 24/2007 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው ህጻንዋ ከቫይረሱ ነፃ መሆኗን፣ የህፃኗ እናት ከሟች ጋር ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት አቶ ጌድዮን ከተባሉ ግለሰብ ጋር በፍቅር ግንኙነት በአንድ ቤት አብረው ሲኖሩ ስለነበር ህፃኗ በጋብቻ ወቅት የተወለደች ከመሆኗ ውጭ የሟች ልጅ ልትሆን የምትችልበት አግባብ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የለም በሚል ህፃን ኖህሚ ታሪኩ የወንድማችን የአብራክ ክፍያ ልጅ አይደለችም የሚል ዳኝነት ይሰጠን ሲሉ የልጅነት መካድ ክስ አቅርበዋል፡፡

አመልካችም የተጠሪዎች አቤቱታ ደርሷቸው መልስ ያቀረቡ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ህፃን ኖህሚ ታሪኩ ሟችና አመልካች ጋብቻ ውስጥ ሆነው ጋብቻው ተፈጽሞ ከ4 ወር በኋላ መወለዷን አምነው የቀረበው የመካድ ክስ ህፃኗ ከ4 ዓመት ዕድሜ በላይ ከሆናት እና የተጠሪዎች ወንድም ከሞቱ 2 ዓመት በላይ ከሆነ በኋላ የቀረበ በመሆኑ ተጠሪዎች ወንድማቸውን ተክተው ክስ ለማቅረብ የልጅቷን መወለድ ካወቁበት ወይም ማወቅ ከሚገባቸው ቀን ጀምሮ በ180 ቀናት ውስጥ ክሱን ባለማቅረባቸው የመካድ ክስ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ ክሱ ተዘግቶ በቂ ኪሳራ እንዲወሰንላቸው መልስ አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ህፃኗ በጋብቻ ወቅት የተወለደችና ሟች አባቷ በህይወት እያሉ ለህጻኗ የሚገባትን እንክብካቤ ሲያደርጉላት የነበረ ከመሆኑም ባሻገር በተወለደች በ180 ቀናት ጊዜ ውስጥ ልጄ አይደለችም በሚል የመካድ ክስ ባለማቅረባቸው የህጻኗን አባትነት ተቀብለው ማረፋቸውን ገልጸዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ባደረገው ማጣራት በተጠሪዎች የቀረበው የመካድ ክስ ሊቀርብ የቻለው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 167፣174፣176 (1) እና 177 ድንጋጌዎች የተመለከተው የ180 ቀናት የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነው በማለት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ሲል ወስኗል፡፡

ፍ/ቤቱም በውሳኔው ላይ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 176 መሰረት በአባትነት በኩል ያለውን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ መሆኑንና ክሱም መቅረብ ያለበት የልጅቷ አባት ነህ የሚባለው ሰው ህፃኗ መወለዷን ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ በ180 ቀን ውስጥ ማቅረብ የሚቻል መሆኑን እንዲሁም በአንቀጽ 177 በሕግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞተ ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ችሎታውን ያጣ ከሆነ ከተወላጆቹ አንዱ በርሱ ፋንታ ሆኖ የመካድ ክሱን ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት በተለይም ከህጻኗ መብት አኳያ ማንኛውም ሰው በማንኛውም ጊዜ እየቀረበ የመካድ ክስ በማቅረብ ልጆች አባት አልባ እንዳይሆኑ ለማድረግ ታስቦ የተደነገገ መሆኑን ከቤተሰብ ህጉ አጠቃላይ አላማ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ በመሆኑም በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ክሱን ያቀረቡት ህጻን ኖህሚ ከተወለደች 4 ዓመት ከ6 ወራት ካለፈና ሟች ከሞቱ 2 አመት ከ4 ወራት ካለፈ በኋላ በመሆኑ የመካድ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው ያለፈ ነው በማለት የቀረበውን ክስና መቃወሚያ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244

ንኡስ አንቀጽ 2 (መ) እና 245 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ውድቅ በማድረግ ግራ ቀኙን አሰናብቷል፡፡

የአሁን አመልካች ሐምሌ 25 ቀን 2009 ዓ.ም በመ/ቁ. 255537 ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ህፃን ኖሀሚ ታሪኩን ከአቶ ታሪኩ ብርሃኑ ጋር ከሰኔ 2004 ዓ.ም ጀምሮ ከጋብቻ በፊት እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ በነበራቸው ግንኙነት መውለዳቸውን በመጥቀስ ህፃን ኖሀሚ ታሪኩ የሟች አቶ ታሪኩ ብርሃኑ ልጅ ናት ተብሎ እንዲወሰንላቸውና የልጅነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱም የህፃን ኖሀሚ ታሪኩ ወላጅ አባት አቶ ታሪኩ ብርሃኑ ናቸው በማለት የልጅነት ማረጋገጫ ሰጥቷቸዋል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ቀደም ሲል ለህጻን ኖሀሚ በመ/ቁ 255537 የተሰጠውን የልጅነት ማስረጃ በመቃወም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት የመቃወም አመልካች በመሆን ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት የመቃወም ማመልከቻ ይዘትም ወንድማችን የሆነው አቶ ታሪኩ ብርሃኑ ከመቃወም ተጠሪ (ከአሁን አመልካች) ጋራ ጋብቻ ፈፅመው በትዳር አብረው ይኖሩ የነበረ ቢሆንም ልጅ አልወለዱም፣ ሕፃን ኖሀሚ ታሪኩ የሟች ወንድማችን ልጅ መሆንዋ በዲ.ኤን.ኤ ሳይመረመር ለህጻኗ የተሰጣት የልጅነት ማስረጃ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 360 መሰረት እንዲሰረዝልን የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ክሱ ደርሷቸው ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም የተጻፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪዎች የመቃወም ህጋዊ መብት የላቸውም፤ የመቃወም መብት አላቸው ከተባለም አባትነትን ለመካድ በህግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ አልፏል በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፍሬ ነገር ደረጃ የማስረዳት ግዴታ ያለባቸው የአሁን ተጠሪዎች በመሆናቸው በተጠሪዎች ወጪ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረግ፣ ሟች ህጻን ኖሀሚ ልጃቸው መሆኗ እና ልጅ መውለዳቸውን አምነው ሁለት አመት ልጃቸውን ሲንከባከቧትና ሲያሳድጓት ቆይተዋል ሲሉ ህጻን ኖሀሚ የሟች ልጅ ነች ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት በአመልካች የቀረበውን መቃወሚያ በማለፍ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ በተጠሪዎች እንዲደረግ የታዘዘ ቢሆንም አመልካች የተለያዩ ምክንያቶች በማቅረብ ሕፃኗን የምርመራው ቦታ መውሰድ አልቻሉም በማለት የማስረዳት ግዴታውን ወደ አመልካች በማዞር የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራው ወጪ በአመልካች እንዲሸፈን ከተወሰነ በኋላ አመልካች የገንዘብ አቅም

የለኝም በማለት ለማስመርመር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ትዕዛዙ ያስከተለውን ውጤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 199 መሰረት ታልፏል ሲል ብይን ሰጥቷል። ቀጥሎም ፍ/ቤቱ አመልካች ሕፃን ኖህሚ ታሪኩ የሚች ታሪኩ ብርሃኑ ልጅ መሆኗን በማስረጃ ማስረዳት ያልቻሉ በመሆኑ ከዚህ በፊት በዚሁ መዝገብ ላይ ሕዳር 27 ቀን 2010 ዓ.ም ይህ ፍ/ቤት በዋለው ችሎት የሰጠው የልጅነት ማስረጃ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁጥር 360(2) መሰረት ተሰርዟል ሲል ወስኗል።

አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው በትዕዛዝ ተዘግቷል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ቀርቦለት አያስቀርብም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል።

አመልካች ለጉባኤው ጽሬው ባቀረቡት አቤቱታ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠውን ልጆች ወላጆቻቸውን የማወቅ መብት በመጣስ ህጻን ኖህሚ ታሪኩን ወላጅ አልባ የሚያደርግ ውሳኔ በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት የሚል ጥያቄ አቅርበዋል።

የአመልካች አቤቱታ ከህገ መንግስቱ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች አንጻር በተለይም ከአንቀፅ 36 እና ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው ዓለም ዓቀፍ የህፃናት መብት ስምምነቶች አንፃር ተመርምሯል።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 36 ስር ከተደነገጉት የህፃናት መብቶች ዋናው የህፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅ ሕገ መንግስታዊ መብት ሲሆን የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 36 ንኡስ አንቀጽ 1 ፊደል 'ሐ' ሲነበብ *"ማንኛውም ህፃን ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት"* መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። የዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 ደግሞ *"ህፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች በፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት"* በማለት ይደነግጋል።

ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ስንመለከት ህዳር 29 ቀን 1984 ዓ.ም እና ጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የፀደቁት የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ፍርድ ቤቶችና ሌሎች አካላት ህፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሲሰጡ የህፃናቱን ጥቅምና ደህንነት በዋነኛነት ማስጠበቅና ቅድሚያ መስጠት እንዳለባቸው ይደነግጋል። ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 አንፃር ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ



የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የሕግ አካል ናቸው። ከላይ የተጠቀሱት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው በመሆኑ የሀገሪቱ የሕግ አካል ናቸው።

ከዚህ አንጻር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት የአሁን አመልካች የህፃን ኖህሚ ታሪኩ እናት ሲሆኑ ከሚች ጋር በጋብቻ አብረው የነበሩ መሆኑን እና ጋብቻቸው በሞት መፍረሱ በፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። የቤተሰብ ሕጉ በሕገ መንግስቱ የተደነገጉትን የህፃናት መብቶች መሰረት አድርጎ የወጣ እንደመሆኑ ፍርድ ቤቶችም ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ይህንኑ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። በሕገ መንግስቱ የተደነገገውን ህፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅ መብት ለመጠበቅ ሲባል በቤተሰብ ሕጉ የተደነገገው አባትነትን መካድ ሂደትም በልዩ ሁኔታ ብቻ ሊቀርብ እና ሊስተናገድ እንደሚገባ ለዚህ ጉዳይ ከተደነገጉት ህጎች መረዳት ይቻላል። በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ልጅ አይደለም በሚል የመካድ ክስ ማቅረብ የሚቻለው የልጁ መወለድ ከታወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ በ180 ቀናት ውስጥ መሆን እንዳለበት በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል። በተያዘው ጉዳይ ህፃን ኖህሚ ታሪኩ ከተወለደች 2 አመት ከ6 ወር በኋላ የህጻኗ ወላጆች ጋብቻ በሞት ሲፈርስ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ህጻኗ የወንድማችን ልጅ አይደለችም በማለት የመካድ ክስ አቅረበው የህጻኗ የአባትነት ማስረጃ መሰረዙ ከፍ/ቤት ውሳኔዎች መረዳት ተችሏል።

ፍርድ ቤቶች በህፃናት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጡ የሕገ መንግስቱን መሠረታዊ መርሆዎች እና ህጻናትን የሚመለከቱ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችንና ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን አለም አቀፋዊ ስምምነቶች መሰረት አድርገው ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው የልጅቷን አባትነት በሚመለከት ተጠሪዎች ባቀረቡት የመቃወም ክስ ቀደም ሲል የተሰጠውን የአባትነት ማስረጃ በመሰረዝ ውሳኔ ላይ መድረሳቸው ከላይ የተጠቀሰውን የሕገ መንግስት ድንጋጌ የሚጥስ ነው።

በመሆኑም የህፃን ኖህሚ ታሪኩ አባት ሚች ታሪኩ ብርሃኑ እንደሆነ መጀመሪያ ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ በመሰረዝ የህፃኗን የዘረመል ምርመራ ማድረግ አለመቻል ብቻ እንደ በቂ እና የመጨረሻ አሳማኝ ማስረጃ በመውሰድ የሰጡት ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል 'ሐ' የሚጥስ ስለሆነ ውሳኔው የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረቡን መረዳት ተችሏል።

ስለሆነም አመልካች በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ምርመራውን ባለማድረጋቸው ቀደም ሲል ለህጻኗ የተሠጠውን የአባትነት ማስረጃ መሰረዙ የህጻኗን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 36(1)(ሀ)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የተደነገገውን ሕገ መንግስታዊ መብት የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ውሳኔው ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል።

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የህጻን ኑሀሚ አባት አቶ ታሪኩ ብርሀኑ ነው በማለት በመ/ቁ.255537 የሰጠውን ውሳኔ የመቃወም አመልካቾችን አቤቱታ ተቀብሎ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 360(2) መሰረት መሰረዙ ኢሕገመንግስታዊ በመሆኑ ውሳኔው ተፈጻሚነት የለውም ተብሎ በምክር ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ ደርሶት በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽም ታዟል። የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይድረሳቸው።
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት።
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዋ ይሰጥ።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ አመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የፋ/ቁ.80/12

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ብርሃኔ ዮሴፍ

አድራሻ.፡- ኦሮሚያ ክልል አቦምሳ ከተማ

2. ዬሚዬ ዋቁማ /ተወካይ ወ/ሮ ብርሃኔ ዮሴፍ/

አድራሻ.፡- ኦሮሚያ ክልል አቦምሳ ከተማ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የውብዳር ከበደ

አድራሻ.፡- አዲስ አበባ የካ/ክ/ከተማ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካቾች የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሚያዝያ 03 ቀን 2009 ዓ.ም ለጉባኤው ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩም የውርስና የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተጀመረ ክርክር ነው፡፡

አንደኛ አመልካች ለፍ/ቤቱ ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከሟች አቶ ዋቁማ በረደድ ጋር ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው በመኖር ህፃን ዬሚዬ ዋቁማ የወለዱ መሆኑን በመግለጽ አቶ ዋቁማ ግንቦት 9 ቀን 2006 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ በመሆናቸው፣ ህፃኗ የወላጅ አባቷ ንብረት ወራሽ በመሆኗ የሟች ድርሻ እንዲወሰንላት፤ አመልካች ከሟች ጋር የጋራ ንብረታችን ነው ያሉትን በየካ ክፍለ ከተማ የቤት ቁጥር 670 የሚገኝ መኖሪያ ቤት ፣የሠሌዳ ቁጥር 2-71506 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ በኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ የተቀመጠ ገንዘብ እና በኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ በሟች ስም ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/145 መሰረት ፍ/ቤቱ በትእዛዝ ማስረጃውን በማቅረብ አጣርቶ እንዲያካፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአሁን ተጠሪ ከላይ የተገለጸው

ቤትና መኪና ምንም መብት ሳይኖራቸው የያዙ በመሆናቸው እንዲያስረክቧቸው ፍ/ቤቱ ትእዛዝ እንዲሰጣቸው ዳኘነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ለፍ/ቤቱ ጽፈው ባቀረቡት መልስ ህፃን ዬሚዬ የሟች ልጅ አይደለችም፤ ሟችም ከአመልካች ጋር እንደ ባልና ሚስት አብረው አልኖሩም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ከጥቅምት 27 ቀን 1989 ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት አብረው መቆየታቸው እና ከ2000 ዓ.ም በኋላ ህጋዊ ጋብቻ መስርተው ባልና ሚስት ሁነው መኖራቸው ገልጸዋል፡፡ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰው መኖሪያ ቤትም የወላጆቹ ነው በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት አመልካች በተለያዩ ባንኮች ገንዘብ መቀመጡን የሚያስረዳው ሰነድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 145 መሠረት በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲቀርብላቸው የጠየቁትን ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት አልፎታል፡፡ አመልካች ከሟች ጋር የጋራ ንብረታችን ነው በማለት ፍ/ቤቱ እንዲያስረክባቸው የጠየቁት በየካ ክ/ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤትም የተጠሪ ወላጆች ነው ሲል ወስኗል፡፡ በክርክር ያለው መኪና በተመለከተ ተጠሪ ንብረቱ የሟች አይደለም በማለት በግልፅ ያልካዱ በመሆኑ እና ህፃን ዬምዬ የሟች ልጅ መሆኗ ከዚህ በፊት በፍ/ቤት በመረጋገጡ፣ አመልካችም ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት ከ3 ዓመት በላይ መኖራቸው በማስረጃ ያረጋገጡ በመሆኑ፣ ተጠሪም የሟች ሚስት መሆናቸው በጋብቻ ምስክር ወረቀት የተረጋገጠ በመሆኑ መኪናው ለሶስቱ ተከራካሪዎች ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካችና ተጠሪ በፍ/ቤቱ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ውሳኔው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፀንቷል፡፡ አሁንም አመልካችና ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ባለመስማማት የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ችሎቱ በስር ፍ/ቤት የተሰጡ ውሳኔዎችን በመመርመር የግራ ቀኙን የህግ ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በሟች ስም በባንክ የተቀመጠ ገንዘብና የአክሲዮን ድርሻ የሚመለከት ማስረጃ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 145 መሰረት በፍ/ቤቱ በኩል በትእዛዝ እንዲቀርብላቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱ ጥያቄቸው ሳይቀበል በማለፍ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል በማለት የስር ፍ/ቤት ማስረጃው አስቀርቦ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት መልሶታል፡፡ እንዲሁም አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት አብረን ነበርን ያሉት ከ1986 እስከ 1993 ዓ.ም በመሆኑና ተሸከርካሪው በ2000 አ.ም አመልካች ከሟች ጋር የነበራቸው ግንኙነት ተቋርጦ በነበረበት ወቅት የተፈራ ስለሆነ፣ አመልካች

በተሸከርካሪው ላይ ድርሻ አላቸው በማለት የስር ፍ/ቤት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል ሲል ተሽከርካሪው ለህጻን የሚዬ እና ለተጠሪ ብቻ ለሁለት እኩል ሊካፈል ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በማሻሻል ችሎቱ ወስኗል፡፡ ችሎቱ ክርክር ያስነሳው ቤት በተመለከተ የተጠሪ ወላጆች ነው መባሉ የሚነቀፍ አይደለም ሲል በዚህ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡ ጉዳዩን የያዘው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በባንክ የተቀመጠውን ገንዘብ እና የአክስዮን ድርሻ በተመለከተ አጣርቶ እንዲወስን በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 145 አስፈላጊውን ትእዛዝ በመስጠት ያለውን ገንዘብ እና የአክስዮን ድርሻ አጣርቶ ገንዘቡ እና አክስዮኑ ለተጠሪ እና ለህፃን ዬሚዬ እኩል እንዲካፈል ወስኗል፡፡

አመልካቾች ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ 1/ በኦሮሚያ ክልል የመርቲ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ሟች እስከ አረፉበት ግንቦት 9 ቀን 2006 ዓ.ም የሟች ሚስት መሆኔን በሁኔታ አረጋግጦ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተጀመረውን የንብረት ክርክር በመጨረሻ የተመለከተው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት በጋራ የቆዩት ከ1986 እስከ 1993 ዓ.ም ነው በማለት ከሟች ጋር ከ1993 ዓ.ም በኋላ ያፈራናቸው ንብረቶች እንዳልካፈል መወሰኑ የአመልካች በህገ መንግስቱ የተረጋገጠውን ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ በመሆኑ 2/ በክርክር ያለው ቤት ሟች ከተጠሪ ወላጆች የገዙት መሆኑን እና በሟች ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ከየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት የጽሁፍ ማስረጃ ቀርቦ እያለ ፍ/ቤቱ መኖርያ ቤቱ የተጠሪ ወላጆች ነው ማለቱ የህጻኗን ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ በመሆኑ የህገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልን በማለት ጠይቀዋል፡፡ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤም ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴበሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ እና የምክር ቤቱን ባለሙያዎች አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኋላ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

በዚሁ መሰረት አመልካቾች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍ/ቤት ውሳኔ የሕገ መንግስት ጥሰት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም፣

1/ አመልካች በኦሮሚያ ክልል የመርቲ ወረዳ ፍ/ቤት ከ1986 ኢ.ም ጀምሮ ሟች እስከ
አረፉበት ግንቦት 9 ቀን 2006 ኢ.ም የሟች ሚስት መሆኔን በሁኔታ አረጋግጦ ውሳኔ የሰጠ
ቢሆንም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተጀመረውን የንብረት ክርክር በመጨረሻ የተመለከተው
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት በጋራ የቆዩት

ከ1986 እስከ 1993 ዓ.ም ነው በማለት ከሟች ጋር ከ1993 ዓ.ም በኋላ ያፈራናቸው
ንብረቶች እንዳልካፈል መወሰኑ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠልኝ ንብረት የማፍራት መብት
የሚጥስ ነው በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በተመለከተ፤

አመልካች አያይዘው ባቀረቡት ማስረጃ በኦሮሚያ ክልል የመርቲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ
15013 ሰኔ 23 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መሰረት ከሟች ጋር ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ
ሟች እስከ አረፉበት ግንቦት 9 ቀን 2006 ዓ.ም በጋብቻ አብረው የቆዩ መሆናቸው በሁኔታ
አስረድቷል ሲል መወሰኑ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የንብረት ክርክሩ
ለተመለከተው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ዳኝነት እንዲሰጥበት የጠየቁት ከሟች ጋር ከ1986 እስከ
1993 ዓ.ም ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብረው መኖራቸውን ብቻ የሚመለከት እንጂ
የሟች ሚስት መሆናቸውን በመግለጽ አይደለም በማለት ፍ/ቤቱ አመልካች እንዲሰጣቸው
በጠየቁት ዳኝነት መሰረት ውሳኔ መስጠቱን አትቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በኦሮሚያ
ክልል መርቲ ወረዳ ፍ/ቤት ቀርበው የሟች ሚስት የነበሩ መሆናቸውን በሁኔታ ያስረዱ
ቢሆንም የንብረት ክርክር ባደረጉበት ፍ/ቤት የጠየቁት ዳኝነት ከሟች ጋር ከ1986 እስከ
1993 ዓ.ም ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት መኖራቸውን በመግለጽ በጋራ ያፈሩት ንብረት
ክፍፍል እንዲደረግ በመሆኑ እና ፍ/ቤቱም አመልካች እንዲሰጣቸው በጠየቁት ዳኝነት
መሰረት ህግንና ማስረጃን መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ውሳኔው የአመልካችን
በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸው መብት የሚጥስ አይደለም፡፡

2/ ክርክር የተነሳበት መኖሪያ ቤት ሟች ከተጠሪ ወላጆች የገዙት መሆኑን እና በሟች ስም
ተመዝግቦ እንደሚገኝ ከየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት
የጽሁፍ ማስረጃ ቀርቦ እያለ ፍ/ቤቱ መኖርያ ቤቱ የተጠሪ ወላጆች ነው ማለቱ የህጻኗን
ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ ስለመሆኑ የቀረበው ጥያቄ በተመለከተ፤

በአመልካቾች ከቀረበው መዝገብ መረዳት እንደተቻለው በክርክር ላይ ያለው መኖሪያ ቤት ሟች ከተጠሪ ወላጆች በጥር 23 ቀን 1998 ዓ.ም የገዙት መሆኑንና የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤትም የቤ/ቁ 670 የሆነ ይዞታ በሟች ባለቤትነት ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ለፍ/ቤቱ ማረጋገጫ ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት መኖሪያ ቤቱ በሟች ባለቤትነት ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ማረጋገጫ የቀረበለት ቢሆንም መኖሪያ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ተከሳሽ ወይም ጣልቃ ገብ በመሆን በመኖሪያ ቤቱ ላይ የባለቤትነት ክርክር በማንሳት ዳኝነት ላልጠየቁት ለተጠሪ ወላጆች ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ፍ/ቤቱ በመኖሪያ ቤቱ ላይ የሰጠው ውሳኔ ህጻን ዬምዬ በህገ መንግስቱ እና ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው የህጻናትን መብት የሚመለከቱ አለም አቀፍ ስምምነቶች አንጻር ያለው እንደምታ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በአለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 24 መሰረት ህጻናት አካለ መጠን ባለመድረሳቸው ምክንያት የሚያጋጥማቸው የመብት ጥሰት ለመከላከል በቤተሰባቸው፣በማህበረሰቡ እና በመንግስት አስፈላጊ ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ ኢትዮጵያ ካጸደቀቻቸው ስምምነቶች መካከል አንዱ የሆነውን የአለም አቀፍ የህጻናት መብቶች ስምምነት በመግቢያው ላይ ህጻናት በአካል እና አእምሮ ያልበሰሉ በመሆናቸው ምክንያት ልዩ ጥበቃ እና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ያስገድዳል፡፡ በአንቀጽ 3/1/ መሰረትም የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች ህጻናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች በህግ አውጪው፣ ህግ አስፈጻሚው እንዲሁም በፍርድ ቤት የሚወሰዱ እርምጃዎች የህጻናትን ጥቅም ቅድሚያ ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን እንደሚጠበቅባቸው ተደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአፍሪካ ህጻናት መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች የህጻናትን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስፈልጉ እርምጃዎች ለመውሰድ ግዴታ ገብተዋል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 36 መሰረትም የመንግስት ተቋማት ፍ/ቤትን ጨምሮ ህጻናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች እርምጃ በሚወስዱበት ጊዜ የህጻናት ጥቅም በቅድሚያ ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡ ህገ መንግስቱ በአንቀጽ 41/5/ መንግስት የህጻናትን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አቅም በፈቀደ ደረጃ እንክብካቤ ማድረግ እንደሚጠበቅበትም ያስገድዳል፡፡ ውርስ ህጻናት ንብረት ከሚያፈሩበት መንገዶች አንዱ በመሆኑም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 መሰረት ጥበቃ የሚደረግለት

ነው፡፡ በመሆኑም ከህገ መንግስቱ እና ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ለመረዳት የሚቻለው የህጻናት መብት እና ጥቅም ማስከበር በሚመለከት ጉዳዩ ለሞግዚቶቻቸው ብቻ የሚተው ሳይሆን መንግስትን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚመለከታቸው መሆኑን ነው፡፡ በተለይ ፍ/ቤቶች የህጻናትን ጉዳይ የሚመለከት ክርክር የሚያስተናግዱ እና ውሳኔ የሚሰጡ በመሆናቸው በሚሰጡት ውሳኔ የህጻናትን ጥቅም እንዲጠበቅ የተቻላቸውን ማድረግ እንደሚገባቸው መረዳት ይቻላል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ መኖሪያ ቤቱ በህጻን ዬምዬ አባት ባለቤትነት ስም የተመዘገበ መሆኑን የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት የገለጸ በመሆኑ፣ በሟች እና በተጠሪ ወላጆች መካከል የቤት ሽያጭ ውል መደረጉ የሚያሳይ የውል ስምምነት በመኖሩ፣ የተጠሪ ወላጆችም በክርክሩ ተካፋይ በመሆን በመኖሪያ ቤቱ ላይየባለቤትነት ክርክር በማንሳት ዳኝነት ሳይጠይቁና በአመልካቾች በኩል የቀረበውን ማስረጃ ሳያስተባብሉ ፍ/ቤቱ የተጠሪ ወላጆች የመኖሪያ ቤቱ ባለቤት ናቸው በማለት መወሰኑ ህገ መንግስቱ የህጻኗን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር ለፍ/ቤቱ የሰጠውን ሚና ግምት ውስጥ ያላስገባና ህጻኗ በመኖሪያ ቤቱ ከሟች ሚስት የነበሩት ከተጠሪ ጋር ሟችን በመተካት ድርሻዋን እንዳትካፈል በመከልከል ተጠቃሚነትዋ የሚያስቀር በመሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 36፣ 40፤41/5/፣79/3/ ጋር የሚቃረን ውሳኔ ነው፡፡

በመሆኑም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት መኖሪያ ቤቱ የተጠሪ ወላጆች ነው የሚለው የውሳኔው ክፍል ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ትእዛዝ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር የተነሳበት መኖሪያ ቤት የተጠሪ ወላጆች ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተፈጻሚ እንዳይሆን በምክር ቤቱ መወሰኑን አውቆ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው
2. የፌዴራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዎች ይሰጥ

ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የስራ ዘመን፣2ኛ ዓመት፣1ኛ መደበኛ ስብሰባ

የፌ/ም/መ/ቁ.019/08

1.አመልካች፡-1ኛ አቶ ወሰን አለሙ

2ኛ. አቶ ዳዊት አትቾ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ተቋም

2ኛ. የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካቾች የቀረበውን የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ-መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

<u>ውሳኔ</u>

የዚህ አቤቱታ መነሻ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 41/2/ እና አንቀፅ 25 የተደነገጉትን የኢኮኖሚና የእኩልነት መብቶችን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው በመሆኑ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት የውሳኔ ሐሳብ በማቅረቡ ነው፡፡

የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉደዩ ላይ ለምክርቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካቾች ሚያዚያ 8 ቀን 2007 ዓ.ም.ለጉባኤው ዕፈው ያቀረቡት ማመልከቻ ፍሬ ሀሳብ ቀደም ብሎ በነበረ ልማድ 1ኛ ተጠሪ የሚያስለጥናቸውን የሕግ ባለሙያዎች በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት ለማሰራት ዕጣ በማስወጣት ሰልጣኞች የሚሰማሩበትን ዘርፍ እንዲመርጡ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን በዚህ ሂደት ግን ማየት የተሳናቸውን ሰልጣኞች በተመለከተ ዕጣ በማስወጣት ሳይሆን በዳኝነት መስራት አይችሉም በሚል ልማድ በቀጥታ በዐቃቤ ሕግነት የሚመደብ በመሆኑ አመልካቾች በመረጥነው የሥራ ዘርፍ መሰማራት መብታችን መሆኑን



14

በመጥቀስ በዕጣ ውስጥ እንድንካተት ብንጠይቅም 1ኛ. ተጠሪ ጥያቄው አዲስ የሆነበት መሆኑን በመጥቀስ ከማሰልጠን ውጪ ማየት የተሳነው ሰው ዳኛ መሆን ይችላል አይችልም በሚለው ላይ መወሰን እንደማይችል የገለፀልን ሲሆን መልሱንም በጽሁፍ አድርጎ ሊሰጠን አልቻለም፡፡ ጥያቄያችንን ለ1ኛ ተጠሪ ቦርድ ብናቀርብም በቀን 23/05/07 ባደረገው ስበሰባ ምንም መነሻ ሳይኖር ማየት የተሳናቸውን ዳኛ አድርጎ መመልመል የሚከብድ እንደሆነ እና በጠቅላይ ፍ/ቤት የበላይ ተቆጣጣሪነት የባህርዳር ዩኒቨርስቲ በጉዳዩ ላይ ጥናት እንዲያደርግ መፍትሔ መቀመጡን የ1ኛ ተጠሪ ዳይሬክተር እና የቦርዱ ሰብሳቢ ገልፀውልናል፡፡ በተሰጠው መልስ ላይ ቅሬታችንን ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ብናቀርብም ጉባኤው ከጠቅላይ ፍ/ቤት ካልተመራልኝ ጉዳዩን አላይም በማለት ምላሹን ሰጥቶናል፡፡ በመቀጠል ቅሬታችንን ለክልሉ ም/ቤት አፈ-ጉባኤ፣ ለም/ቤቱ የሕግ ቋሚ ኮሚቴ እና ለክልሉ አሰተዳደር ቅሬታ ክፍል ብናቀርብም ጥያቄያችን ምላሽ አላገኘም፡፡ በመሆኑም በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 41(2) የተቀመጠው በመረጥነው ሙያ የመሰማራት መብታችን ቀጥሏል ሲሉ ቅሬታቸወን አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች ቅሬታቸውን ለአ/ብ/ክ/መንግሥት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ተቋም ለአ/ብ/ክ/መ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ተቋም ቦርድ፤ለአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለአ/ብ/ክ/መ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ፤ ለአ/ብ/ክ/ ም/ቤት የሕግ ቋሚ ኮሚቴ እና ለአ/ብ/ክ/መ የሕዝብ ቅሬታ ሰሚ ጽ/ቤት ማቅረባቸውን የሚያሳይ የማመልከቻውን ቀሪ ኮፒ በማድረግ አያይዘው አቅርበዋል፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቁ አጣጉ/335/02/08 እና አጣጉ 335/02/08 በቀን 02/02/2008 ለ1ኛ እና ለ2ኛ ተጠሪዎች እንደቅደም ተከተላቸው በተፃፈ ደብዳቤ ባደረገው ማጣራት፡-

1ኛ ተጠሪ፡- የአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት በደንብ ቁጥር 74/2003 መሰረት ሲቋቋም ከተሰጠው ስልጣን አንዱ በዩኒቨርስቲ የሕግ ዲግሪ ያላቸውን ተመራቂዎች በቅድመ ስራ ሰልጣኝነት መልምሎ በማስገባት በእውቀት፣ በክህሎት በአመለካከትና በስነ-ምግባር በማብቃት ሕገ-መንግሥታዊ ስርዓቱን በማክበርና በማስከበር የተጀመረውን ልማትና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጾኦ በማበርከት የፍትሕ ስርዓቱ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ባለሙያ በማፍራት ወደ ፍትህ ስርዓቱ እንዲቀላቀሉ ማድረግ ነው፡፡ስለሆነም ሰልጥነው የሚመረቁ ሰልጣኞች የሚመደቡት በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት ሲሆን ዕጣ እንዲያወጡ የምናደርገው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና

በፍትህ ቢሮ በኩል በዕጣ ለይተን እንድንሰጣቸው ሲስማሙ እንጂ የኢንስቲትዩት ኃላፊነቱ ሆኖ አይደለም፡፡ስለዚህ ዕጣ በምናወጣበት ጊዜ ማየት የተሳናቸው ሰልጣኞች ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ከስራው ባህሪ አንፃር ዳኛ እንዲሆኑ ያልተፈቀደላቸው ስለሆነ በቀጥታ ዐቃቤ ሕግ ሆነው እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ለክልሉ ም/ቤት አቅርበው የስራው ባህሪ ግምት ውስጥ ገብቶ ዐቃቤ ሕግ እንዲሆኑ ተደርጓል እንጅ በእኛ በኩል የተደረገ ክልከላ የሌለ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ በሚል ምላሹን ሰጥቷል፡፡

2ኛ. ተጠሪ በበኩሉ፡ ቅሬታቸውን ለጉባኤ ጽ/ቤቱ አቅርበው ነበር፡ በእኛ በኩል በወቅቱ የተሰጣቸው ምላሽ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተን ስላልሆነ ማሰልጠኛ ት/ቤቱንና ቦርዱን እንዲጠይቁ ምላሽ ሰጥተናቸው እንደነበር እናስታውሳለን፡፡

በክልላችን ውስጥ በመሰረቱ የዳኞችና የአቃቢ ሕጎች ምልመላና ስልጠና የሚካሄደው በፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም አማካኝነት ነው፡፡ ስልጠናቸውን አጠናቀው ሲጨርሱ በዕጣ ወደ ፍርድ ቤት እና ወደ ዐቃቢ ሕግነት የሚገቡትን ለይቶ እንድንመድባቸው ይልክልናል፡፡ በዚህ ሂደት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤም ይሁን ጽ/ቤታችን ያለው ሚና ስልጠናቸውን አጠናቀው የተመደቡለትን በረዳት ዳኝነት መድቦ ሲከታተል ከቆየ በኋላ ለዳኝነት ብቁ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ለክልል ም/ቤቱ ቀርበው እንዲሾሙ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በእኛ በኩል ወደ ዳኝነት ወይም ወደ ዐ/ሕግነት ይግቡ የሚለውን የመወሰን ስልጣንና ኃላፊነት የሌለን በመሆኑ ሙሉ ምላሽ ለመስጠት እንቸገራለን፡፡ ይሁን እንጂ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም በቦርድ የሚመራ በመሆኑና የጠ/ፍ/ቤቱም የቦርዱ አባል በመሆኑ ከቦርዱ ሰብሳቢና ከማሰልጠኛ ተቋሙ ጠይቀን እንደተረዳነው አሁን ቅሬታ ያቀረቡት ሰዎች በወቅቱ ለማሰልጠኛ ተቋሙ ቦርድ አቅርበው እንደነበር ተገልፆልናል፡፡

ቦርዱም ያቀረቡትን ቅሬታ በአግባቡ እንደመረመረ፣ በምርመራ ሂደቱ ወቅት የዳኝነት ስራ በአካል ምስክሮችን ማየትና ማስረጃውን ማረጋገጥ የሚጠይቅ መሆኑን በዚህ ረገድ በዓለም ላይም ይሁን በሀገራችን ማየት የተሳናቸውን በዳኝነት መደብ የማሰራት ልምድ እንደሌለና እንደተቸገረ በዚህ ምክንያት የተሻለው የስራ ስምሪት ዐ/ሕግ መሆኑን ተገንዝቦ ወደ ዐ/ሕግነት የመደባቸው መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም ከዓለም ዓቀፍም ይሁን ከሀገር አቀፍ ልምድ አንፃር ሲታይ የዳኝነት ስራ ከአለው አስቸጋሪነት አንፃር ማየት የተሳናቸውን መድቦ ማሰራት ሊፈጥር የሚችለውን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት ለእነሱ አመች ወደሆነው የስራ ስምሪት የመደባቸው መሆኑን እንደተገለፀልን እና በእኛ በኩልም የቦርዱ ይሁን የማሰልጠኛ ተቋሙ አሰራር ተቀባይነት ያለው መሆኑን እንገልፃለን፣ በማለት ምላሹን ሰጥቷል፡፡ ጉባኤው የተጠሪ ተቋማት ኃላፊዎችን ጠርቶ ቢያናግርም የተለየ ምላሽ ሊያገኝ አልቻልም፡፡

የአመልካቾች ቅሬታ በተጠሪዎች በተያዘ የአሰራር ልማድ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 41/2// የተረጋገጠልን በመረጥነው ሙያ የመሰማራት መብታችን ተጥሷል በሚል ነጥብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ተጠሪዎች ከሰጡት ይፋዊ ምላሽ፣ በተጠሪዎች ዘንድ ማየት የተሳናቸው ሰልጣኞች በዳኝነት ስራ ለመሰማራት የስራው ፀባይ አይፈቅድላቸውም ከሚል መነሻ ማየት የተሳናቸውን ሰልጣኞችን በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት የስራ ዘርፍ ለማሰማራት በሚደረገው የዕጣ ማስወጣት ሂደት አሳታፊ ያለማድረግ የአሰራር ልማድ እንዳለ መረዳት ተችሏል፡፡ኢትዮጵያ ተቀብላ በአዋጅ ቁጥር 676/2002 ያፀደቀችው የአካል ጉዳተኞች መብት ኮንቬንሽን አንቀጽ 27 ሥራና ቅጥር በሚል ርእስ፡-

1«የተዋዋይ መንግሥታት አካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር በእኩልነት የመስራት መብት ያላቸው መሆኑን ያውቃሉ፡፡ ይህም ለአካል ጉዳተኞች ክፍት፣ አካታችና ተደራሽ በሆነ፣ በነፃነት በተመረጠና ወይም በሰራተኛ ገበያና የስራ አካባቢ ተቀባይነት ባገኘ ቦታ ውስጥ በመስራት ኑሮን ለመምራት ዕድል የማግኘት መብቱን ይጨምራል፡፡ ተዋዋይ መንግሥታት ተቀጥረው በመስራት ሂደት ውስጥ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ጨምሮ የመስራት መብታቸውን ያስጠብቃል፤ ያበረታታል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ሕግ መደንገግን የጨመረ ሆኖ ከሌሎች ነገሮች መካከል የሚከተሉትን እውን ለማድረግ ነው፡፡

ሀ. ምልመላ፣ ቅጥር፣ ስራን የመያዝ፣ የቅጥር ቀጣይነት: ሙያን ማሳደግና አደጋ- የለሽና

ጤናማ የስራ ሁኔታዎችን የተመለከቱትን ጨምሮ ከሁሉም የቅጥር ዓይነቶች በተያያዙ ጉዳዮች በአካል ጉድለት ምክንያት የሚደርሱ አድልዎን መከላከል፣...›› የሚል ድንጋጌ ተካቶ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ እና በመላ ስምምነቱ ኢትዮጵያ በአካል ጉዳተኞች ላይ የስራ ምልመላን ጨምሮ በተለያየ መልኩ አድልኦ እንዳይፈፀም ኃላፊነትን ወስዳለች፡፡እንደዚሁም በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በወጣው የአካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁጥር (568/2000) አንቀጽ 4 የአካል ጉዳተኞችን የስራ ስምሪት መብት ስለመጠበቅ በሚል ርዕስ፡-



11

1. የሰራው ጠባይ የማይፈቅድ ካልሆነ በስተቀር የተፈላጊ ችሎታ መመዘኛዎችን አሟልቶ የተገኘና በውድድር ውጤቱ ብልጫ ነጥብ ያገኘ ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ በምንም ዓይነት መልኩ መድሎ ሳይደረግበት፣

ሀ. በማንኛውም መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ የሚገኝ ክፍት የሰራ ቦታን በቅጥር፣በዕድገት በድልድል ወይም በዝውውር ለመያዝ ወይም

ለ. በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በሚሰጥ የስልጠና ፕሮግራም ለመሳተፍ መብት አለው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተፈላጊ ችሎታ መመዘኛዎችን አሟልቶ የተገኘና ለወድድር ውጤት እኩል ወይም ተቀራራቢ ነጥብ ያገኘ ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ በምንም ዓይነት መልኩ መድልዎ ሳይደረግበት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ሀ/ እና /ለ/ ለተመለከቱት መብቶች ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

3. በስራው ጠባይ አስገዳጅነት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የመወዳደሪያ መስፈርት በተወደዳሪው ላይ ያለውን ጉዳዩ የሚመለከት መሆን የለበትም፡፡

በሚል የተደነገገ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የተፈላጊ ችሎታ መመዘኛዎችን አሟልተው ነገር ግን ውድድር ባለመኖሩ በውድድር ባይሳተፉም በሚከናወነው የዕጣ ስምሪት ግን እንዳይሳተፉ መከልከሉ ድንጋጌውን ያከበረ አይደለም፡፡ድንጋጌው የስራው ፀባይ የማይፈቅድ ካልሆነ በቀር.. በሚል ዓረፍተ ነገር የሚጀመር ሲሆን ለዚህ ዓረፍተ ነገር በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 8 ‹‹የሰራው ፀባይ የማይፈቅድ›› ማለት ተፈላጊውን ችሎታ የሚያሟላ የአካል ጉዳተኛ ተመጣጣኝ ማመቻቸት ተደርጎለትም ቢሆን ሊያከናውነው የማይችል ስራን ያመለክታል›› በሚል የተተረጎመ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህም በመነሳት አመልካቾች ተመጣጣኝ ማመቻቸት ቢደረግላቸው ስራውን ሊያከናውኑ እንደማይችሉ በተጠሪዎች የቀረበ አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡

የሕገመንግሥቱ አንቀጽ 41/2/ ‹‹ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው፡፡ በሚል ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡

መብቱ ፍፁም ያልሆነ እና ሊገደብ የሚችል ቢሆንም የአንድ ስራ ተፈጥሯዊ ባህሪ አንዱን ከሌላው መለያ ሊሆን የሚችለው ስራው ከተፈጥሯዊ ባህሪው የሚጠይቀው ቅድመ ሁኔታ በድንገት ወይም በምርጫ የሚጠይቅ ሳይሆን የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከስራው ባህሪ በሚል መነሻ በአሰራር የተጣለው ገድብ ከላይ ኢትዮጵያ ከተቀበለችው



10

ዓለም አቀፍ ስምምነትም ሆነ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ከወጣው አዋጅ በተለይ በሌሎች ሀገራት ካለው ተሞክሮ አንፃር በበቂ ጥናት ወይም ምክንያት ላይ የተመሰረተ እና የግድ አስፈላጊ በሆነ ቅድመ ሁኔታ ላይ መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ያሰራር ልማዱ ከላይ የተጠቀሰውን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ የሚያጣብብ ነው፡፡ እንደዚሁም አመልካቾች በአሰራር ልማዱ ልዩነት የተደረገባቸው በመሆኑ የተያዘው ልማድ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 25 ‹‹ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው በመካከለቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡ በሚል የሰፈረውን የእኩልነት መብት የሚጋፋ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ- መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ የሚል ነው፡፡

ምክርቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክርቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት ምክርቤቱ እንደተረዳው አመልካቾች የዳኝነት ይሁን የዓቃቤ ሕግነት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ስራ ለመስራት የሚያስፈልገውን የሕግ ትምህርት ተምረው እና ለዚሁ ተግባራዊ ስራ ብቁ የሚያደርጋቸውን በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የሚሰጠውን የቅድመ ስራ ስልጠና ወስደው በማጠናቀቅ ተመርቀው እያሉ 1ኛ ተጠሪ አመልካቾችን አብረዋቸው እንደሰለጠኑት ሌሎቹ ሰልጣኞች እኩል ጥበቃ በማድረግ በዳኝነት ወይም በዓቃቤ ሕግነት ተመድበው እንዲሰሩ ለመወሰን ዕጣ እንዲያወጡ ማድረግ ሲገባው ይህንን ወደ ጎን በመተው ማየት የተሳናቸው በመሆናቸው ብቻ በሕግ ያልተደነገገን "ማየት የተሳናቸው የዳኝነት ስራን መስራት አይችሉም" የሚል ልማዳዊ አሰራርን በመከተል አመልካቾችን ከዕጣ ድልድል ውጪ በማድረግ በዓቃቤ ሕግነት እንዲመደቡ አድርጓል፡፡

ምክርቤቱ እንደተገነዘበው አመልካቾች በዳኝነት እንዳይሰማሩ የሚከለክል ሕግ ካለመኖሩም በላይ በአጣሪ ጉባኤው የውሳኔ ሓሳብ በዝርዝር እንደተገለፀው ተጠሪዎች የሰጡት ውሳኔ በአካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት መብት ሕግ - አዋጅ ቁጥር 568/2000 እና አገራችን ኢትዮጵያ በአዋጅ ቁጥር 676/2002 ባፀደቀችው ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች መብት ኮንቬንሽን ድንጋጌዎች መሰረት የስራው ጠባይ የማይፈቅድ ካልሆነ በስተቀር ተፈላጊው የችሎታ



9

መመዘኛዎችን የሚያሟሉ አካል ጉዳተኞችን በአካል ጉዳታቸው ምክንያት መድልዎ እንዳይደረግባቸውና ተመጣጣኝ ማመቻቸት ተደርጎላቸው ጭምር ሊያከናውኑት በሚችሉት በመረጡት የስራ ዘርፍ እንዲሰማሩ ያላቸውን መብት የሚጋፋ አሰራርና ውሳኔ ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪዎች ተቀባይነት በሌለው ልማዳዊ አሰራር መሰረት የሰጡት ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 41/2/ ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ሥራውን እና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው በሚል የተደነገገውን እንዲሁም በአንቀፅ 25 የተደነገውን የአመልካቾች ሕገ-መንግስታዊ የእኩልነት መብት የሚጋፋ በመሆኑ የተጠሪዎች የልማድ አሰራር እና ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9/1/ መሰረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1. ተጠሪዎች 1ኛ የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ተቋም 2ኛ የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አመልካቾች በዳኝነት ስራ እንዳይሰማሩ ልምድን መሰረት አድርገው የሰጡት ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍላቸው፡፡

2. አመልካቾች በመረጡት የዳኝነት የሙያ መስክ የመሰማራት ሕገ-መንግስታዊ መብት አላቸው በማለት ምክርቤቱ ወስኗል፡፡

3. የፌዴራሉ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

4. የምክርቤቱ የውሳኔ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢዎች ይሰጥ፡፡

## የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ም/ቤት የ5ኛው የፓርላማ ዘመን አምስተኛ ዓመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

### የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ም/ቤት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ባቀረበው የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ ላይ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ የሚከተለውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ሕገመንግስት በአብዛኛው የዓለማችን አገራት የፖለቲካ ስርዓቱን መልክ ከማስያዝ በተጨማሪ በመንግስትና በዜጎች መካከል የሚኖረውን መስተጋብር የሚደነግግ ሰነድ ነው፡፡ሕገ መንግሥት የፖለቲካ ሥርዓቱን ቅርፅ በማስያዝ ሂደት ተቋሞችን ይፈጥራል፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የፌዴሬሽን ም/ቤትም ሕገመንግስቱ ከፈጠራቸው ተቋማት መካከል አንዱ ሲሆን ይህንኑ የፌዴራልሕገ መንግሥት የመተርጎም ስልጣን በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 62(1) ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ተሰጥቷል፡፡

በዚህ መሠረት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በአገራችን የተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝና ወረርሽኙን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ተጽዕኖውን ለመቀነስ በታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ምክንያት 6ኛውን ዙር አገራዊ ምርጫ ማካሄድ ባለመቻሉ ምክንያት አሁን በሥራ ላይ ያሉት ምክር ቤቶችና የአስፈጻሚው አካል ስልጣንና የሥራ ዘመንን አስመልክቶ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 54/1/፣ 58/3/ እና 93 ከሕገ መንግስቱ አላማ እና ግቦች እንዲሁም መሰረታዊ መርሆች ጋር በማስተሳሰርና በማገናዘብ ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የቀረበውን ጥያቄ ጉባኤው መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ለተከበረው የፌዴሬሽን ም/ቤት ልኳል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ም/ቤትም የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም ባደረገው መደበኛ ስብሰባው መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ 28 ቀን 2012 ዓ.ም ከላይ በተጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች ላይ የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሊቀርብ የቻለው በኢትዮጵያ ምርጫ በሚደረግበት የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰትና ወረርሽኙን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጅ የተገደደችበት ወቅት ሲሆን ስልጣን ላይ ያሉት የመንግስት አካላት ሚና እና ሀላፊነት በቀጣይ ምን ይሆናል? ምርጫውስ መቼ መካሄድ ይኖርበታል? የሚሉትን ጥያቄዎች ሕገ መንግሥቱ በግልጽ ባለመደንገጉ ምክንያት ነው፡፡

የቀረበው የሕገ-መንግስት ትርጉም ጥያቄ ይዘት በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ምርጫ ማካሄድ ስላልተቻለ ሕገ መንግሥቱ ደግሞ የዋና ዋና የመንግስት ስልጣን አካላት (ሕግ አውጪ እና ሕግ አስፈጻሚ) በየአምስት አመቱ በሚደረግ ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ምርጫ መሰረት በሚካሄድ የስልጣን ርክክብ ላይ የሚመሰረት በመሆኑ፣ አሁን ሀገሪቱን በመምራት ላይ የሚገኙት የመንግስት አካላት የስልጣን ዘመን ላይ ሁኔታው ምን እንድምታ አለው የሚልና ኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና ለሕዝብ ጤና ስጋት መሆን ካቆመበት ጊዜ ጀምሮ ምርጫው መከናወን ያለበት በምንያክል ጊዜ ውስጥ ነው የሚል ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔው ጉዳዩን መመርመር ከመጀመሩ አስቀድሞ ጉዳዩን ተቀብሎ የማየት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የኢ.ፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጉዳዩን ለጉባዔው መላክ ይችላል ወይስ አይችልም? በሚሉት ነጥቦች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ጉባኤው ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት እንዲቻል ሁለት ጭብጦችን ለይቷል፡፡ የለያቸው ጭብጦች የኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከሰትና ወረርሽኙን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ተጽእኖውን ለመቀነስ በታወጀው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ምክንያት የምክር ቤቶቹ እና የአስፈጻሚው አካል ስልጣን የስራ ዘመንን አስመልክቶ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበውን ጥያቄ ለመመለስ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 54 (1) ፣ 58(3) እና 93 እንዴት ይተረጎማሉ? የኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከሰትና ወረርሽኙን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ተጽእኖውን ለመቀነስ በታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ምክንያት ምርጫ የሚደረግበትን ጊዜ አስመልክቶ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበውን ጥያቄ ለመመለስ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 54(1) ፣ 58(3) እና 93 እንዴት ይተረጎማሉ? የሚሉ ሲሆን በእነዚህ ጭብጦች ላይ ምርመራ አካሂዷል ፡፡

በዚህም መሰረት በአንቀጽ 84(1) መሠረት ጉዳዩን ተቀብሎ የመመርመር ስልጣን ያለው መሆኑን ስምምነት ላይ የደረሰ ሲሆን ጉባዔው ሕገ መንግሥቱን መሠረት በማድረግ የፍርድ ቤት ክርክርን አስታከው የሚመጡ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን ወይንም ሕገ መንግሥቱን የሚጋፉ አዋጆችን መመልከት ብቻ ሳይሆን ሕገ መንግሥታዊ የትርጉም ስርዓትን ሊያሰፉ የሚችሉ አንኳር ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ትንታኔ እና የውሳኔ ሀሳብ በመስጠት ጉባዔውም ሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ ሕገ መንግሥቱ ቀድሞ ታሳቢ እንዳደረገው የሕገ መንግሥት ትርጉም ስርዓትን የማሳደግ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ጭምር ከግምት ያስገባ ነው፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የትርጉም ጥያቄውን ማቅረብ የሚችል መሆኑን በተመለከተም በሕገመንግስቱ አንቀጽ 84(1) እና በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አዋጅ ቁ.798/2005 አንቀጽ 3(2)(ሐ) መሰረት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄውን ለማቅረብ ይችላል የሚል ብይን ሰጥቷል፡፡

ጉባዔው ለቀረበለት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የውሳኔ ሀሳብ ከመስጠቱ በፊት ከግለሰቦችና ተቋማት 34 የሙያ አስተያየቶች በጽሁፍ ተቀብሎ ጽሁፎቹን በመዳሰስ በግባዓትነት ተጠቅሟል፡፡ በተጨማሪም ሶስት መድረኮችን በተለያዩ ጊዜያት በማዘጋጀት ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎችና ጠበቆች ማህበር፣10 የሕገ መንግሥት ከፍተኛ ባለሙያዎች፤ ሕገ መንግሥቱ በሚረቀቅበትና በሚፀድቅበት ጊዜ ተሳትፎ ከነበራቸው 4 ሰዎች፣ ከብሄራዊ ምርጫ ቦርድ፤ከጤና ሚኒስቴር፤ከህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት፣ ከጤና ባለሙያዎች ማህበርና ከኮቪድ- 19 የሳይንስ አማካሪ ካውንስል የመስማት /Hearing/ ሂደት ስለማከናወኑ የተላከልን ሰነድ በማስረጃነት ያመላክታል፡፡ሂደቱም በልዩ ልዩ ሚዲያዎች ቀጥታ ስርጭት የሀገራችን ህዝቦች እንዲከታተሉት ተደርጓል፡፡ሂደቱ በሀገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያ ፊር ቀዳጅና ታሪካዊ ሊባል የሚችል ሲሆን ጉባዔው ለፈጠረው ግልጽና አሳታፊ መድረክ ከፍተኛ ምስጋና ሊቸረው የሚገባ መሆኑን፣ እንዲሁም ጉባዔው ቀጣይ ተመሳሳይ ጉዳዮች ሲቀርብለት ይበልጥ አሳታፊ በሆነ መልኩ ባለድርሻ አካላትን በስፋት የማሳተፍ ስራውን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ብሎ ምክር ቤቱ ያምናል፡፡

እንደሚታወቀው 6ኛው ዙር ሀገራዊ ምርጫ በያዝነው በጀት ዓመት በተያዘለት ፕሮግራም መሰረት መካሄድ እንዳለበት መንግሥት ቁርጠኝነቱን በተደጋጋሚ በልዩ ልዩ መድረኮች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ማለትም ለህዝብ፣ ለተፎካካሪ ፓርቲዎችና ለሌሎች አካላት ጭምር አስቀድሞ ግልጽ በማድረግ መግባባት ላይ መድረሱ ይታወሳል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድም ምርጫውን ለማስፈፀም የቅድመ ምርጫ ዝግጅት ስራዎችን ሲያከናውን ከቆየ በኋላ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳውን ይፋ ማድረጉ ይታወቃል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ማንም ቀድሞ ባላሰበውና ባልገመተው ሁኔታ በሀገራችንና በአለም ላይ የኮሮና ቫይረስ በሽታ ተከስቶ በርካታ ህዝብን እየገደለና የስርጭት አድማሱን እያሰፋ ይገኛል፡፡ከዚሁ የወረርሽኝ ስጋት የተነሳ 53 ሀገራት ምርጫን ጨምሮ መንግስታዊ እቅዶቻቸውን በማቋረጥ የህዝባቸውን ህይወት ለመታደግ እና ወረርሽኙን ለመከላከል ዘመቻ ከፍተዋል፣ ከ100 በላይ የሚሆኑ አገሮች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጣት ተገደዋል፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥትም የሕዝቡን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወረርሽኝ በመከሰቱ ወረርሽኙን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ተፅዕኖውን

ለመቀነስ ሲል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012ን አውጇል፡፡አዋጁ በሕገ መንግሥቱ ከሰፈሩት አንቀጽ 1፣18፣25 እና 39 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በስተቀር ለህዝቡ ደህንነት ሲባል የተወሰኑ የዴሞክራሲ መብቶችን ይገድባል፡፡በዚህ ሁኔታ ጉባዔው የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የሕገ መንግሥቱን ዓላማና ግብ እንዲሁም መርሆዎች መሠረት በማድረግ መርምሯል፡፡ጉባዔው የተከተለው የሕገ መንግሥት አተረጓጎም መርሆዎች የጉባኤው አባላት የቀረበውን ጥያቄ ለመመርመር የተሻለ ሆኖ ያገኙትን የሕገ መንግሥት አተረጓጎም ዘዴ ኣላማ ተኮር እና መዋቅራዊ (purposive/structural) የሚባለውን የትርጉም ዘዴ ሲሆን የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔውም የሚከተለውን የውሳኔ ሀሳብ አቀርቧል፡፡

1. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 54(1)፣ 58(3)፣ 67(1) እና 72(3) ላይ የተደነገገው የአምስት አመት የስራ ዘመን ከአንቀጽ 93 እንዲሁም ከሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች፣ ኣላማዎችና ግቦች ጋር በማገናዘብ የኮቪድ-19 ወረርሺኝ የህዝብ ጤና ስጋት ሆኖ ባለበትና የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ፀንቶ በሚቆይባቸው ጊዜያትና ከተነሳም በኋላ አዲስ ምርጫ ተካሂዶ የስልጣን ርክክብ እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የክልል ም/ቤቶች እና የፌዴራልና የክልል አስፈፃሚ አካላት የስራ ዘመን እንዲቀጥል በማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84(1) መሠረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ .ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት፣

2. የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 እንዲታወጅ ምክንያት የሆነው ወረርሺኝ አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የጤና ድርጅቶች የሚያወጡትን መረጃ መሠረት በማድረግ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጤና ሚኒስቴር እንዲሁም የህብረተሰብ ጤና ኢኒስቲትዩት እና የሳይንስ ማህበረሰብ አካላት ወረርሺኙ የህዝብ ጤና ስጋት አለመሆኑን ካረጋገጡበትና ይህም በህዝብ ተወካዮችምክር ቤት ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ከዘጠኝ ወር እስከ አንድ አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ምርጫው እንዲካሄድ በማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ84(1) መሰረት የኢ.ፌ.ድ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻውን ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡ ቋሚ ኮሚቴውም ከም/ቤቱ አፈ ጉባዔ ከላይ የተጠቀሰው ጉዳይ ተመርቶለት በጥልቀት የመረመረ ሲሆን አራት የአጣሪ ጉባኤ አባላት በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ሰኔ 1 ቀን 2012 ዓ.ም በአስረጅነት ተገኝተው

ከቋሚ ኮሚቴ አባላት ለተነሱ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች በቂ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን ቋሚ ኮሚቴውም ያጣሪ ጉባዔውን የውሳኔ ሀሳብ በመደገፍ የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

በመሆኑም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሕገ መንግሥቱን አጠቃላይ መርሆዎችና አላማዎችን በመፈተሽ በሕገ መንግስቱ ላይ ግልጽ የሆነ ድንጋጌ ባለመኖሩ የምርጫውን ጊዜ ለማራዘም ባለመቻሉ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበውን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ በበቂ ትንተና እና አሳማኝ ምክንያቶች ላይ ተመስርቶ ተገቢውን ጊዜ ወስዶ በጥልቀት መርምሮ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ምክር ቤቱ በሚገባ ተወያይቶበት ባብላጫ ድምፅ ተቀብሎ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀረባው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ተመርምሮ የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ም/ቤት ተወያይቶበት በአብላጫ ድምጽ ያፀደቀው ስለሆነ ውሳኔው ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፣ ለክልል ምክር ቤቶች እንዲሁም ለአስፈፃሚው አካላት ደርሷቸው በውሳኔው መሠረት እንዲፈፀሙ ይደረግ፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በምክር ቤቱ የፀደቀ በመሆኑ በግልባጭ እንዲያውቀው ውሳኔው ይላክለት፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን ፣ 5ኛ ዓመት አንደኛ አስቸኳይ ስብሰባ

ነሐሴ 30 ቀን 2012 ዓ.ም

የመ/ቁ. 87/12

አመልካች ፦ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት.ዴ.ፓ)

ተጠሪ ፦ የለም

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ-መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 20/12/2012 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ዕጩ ባቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መነሻነት ነው። የጥያቄው ይዘትም፦

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 62/1/ ሕገ መንግስትን የመተርጎም ስልጣን የተሰጠው የፌዴሬሽን ምክር ቤት 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተውና በከፍተኛ ደረጃ እየተዛመተ፣ ገዳይነቱ እየጨመረ በመጣው ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ምርጫውን ማድረግ ስለማይቻል በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሪፖርት ላይ ተመስርቶ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ካቀረበ በኋላ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት ምርጫው እንዲራዘም ሕገ መንግስታዊ ትርጉም መስጠቱ ይታወቃል።

ይሁንና ለሕዝብ ጤና ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት ወረርሽኙ በሕዝብ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስና ስርጭቱንም ለመከላከል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁ እየታወቀ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድም ምርጫውን በጊዜው ማካሄድ እንደማይችል በገለፀበት፣ የምርጫውን ሁሉ አቀፍነት በእኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን የሚገልፅበትና ለምርጫው ዋስትና የሚሰጥ ሕገ መንግስታዊ ተቋም በማይሳተፍበት ፣ በወረርሽኙ ምክንያት መራጩ ሕዝብ በነጻነት ተንቀሳቅሶ ምርጫውን ለማካሄድ በማይችልበትና የፖለቲካ ድርጅቶችም በነጻነት ተንቀሳቅሰው የፓርቲያቸውን ፖሊሲና ፕሮግራም ለመራጩ ሕዝብ ማስተዋወቅ አዳጋች በሆነበት ወቅት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 6ኛውን ዙር ምርጫ በክልሉ ለማካሄድ በመወሰንና ክልላዊ የምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም የምርጫ እንቅስቃሴ ጀምሯል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደሆነና ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ከተቃረነ ተፈጻሚነት እንደሌለው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) ተደንግጓል። በተጨማሪም በዚሁ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(2) ማንኛውም ዜጋ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ሕገ መንግስቱን የማስከበርና ለሕገ መንግስቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት እንዳለባቸው ተደንግጓል። በተያያዘም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50(8) መሠረት ለፌዴራል መንግሥት የተሰጠው ሥልጣን በክልሎች መከበር ያለበት መሆኑ እና የሕገ መንግስት የበላይነት የሚደነግገው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ማንኛውም ሕግ ወይም የመንግስት አካል ውሣኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው በግልጽ ተደንግጓል።

ስለሆነም እኛ በትግራይ ክልል የምንቀሳቀስ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት.ዴ.ፓ) በትግራይ ክልል ምርጫ ላይ ለመሳተፍ እቅድና ዝግጅትም የነበረን ቢሆንም ምርጫው በሕገ መንግስቱ ስልጣን በተሰጠው አካል በመራዘሙ ሕገ መንግስቱን በማክበር በህገ ወጡ የትግራይ ክልል ምርጫ ላለመሳተፍ ወስነናል።

የፌዴራል መንግስትም የሕገ መንግስቱን የበላይነት ለማስከበር ተገቢውን እርምጃ መውሰድና በሕወሓት መሪነት እየተካሄደ ያለው ሕገ መንግስቱንና የምርጫ ህጉን የጣሰ የምርጫ እንቅስቃሴ እንዲቆም መደረግ አለበት።

ስለሆነም የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም የተሰጠውን ሕገ መንግስታዊ ትርጉምና የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ሕገ መንግስታዊ ስልጣን በመጋፋት ከህግ ውጭ ምርጫን ለማካሄድ ወስኖ እየተንቀሳቀሰ ስለሆነ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምርጫ ለማካሄድ የወሰነው ውሳኔ፣ ያቋቋመው ክልላዊ የምርጫ ኮሚሽን እና እያደረገ ያለው የምርጫ እንቅስቃሴ ኢ-ህገ መንግስታዊ መሆናቸው በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ተጣርቶ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳብ እንዲተላለፍ የሚል ነው።"

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤውም የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሯል። ጉባኤው ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን እና አመልካች የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት.ዴ.ፓ) ባለጉዳይ ሆኖ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ማቅረብ የሚችል መሆን አለመሆኑን ጉባኤው ወደ ዋናው ጉዳይ ገብቶ ከማየቱ በፊት እነዚህን ነጥቦች መርምሯል። እንደመረመረውም፣ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዮችን ተቀብሎ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ለመመርመር ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን በሚመለከት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 84(1) እንደሚከተለው ይነበባል፤

"የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሕገ መንግስታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል። በሚያደርገው ማጣራት መሰረት ሕገ መንግስቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል" ይላል።

ከላይ ከተገለጸው ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ጉባኤው ማንኛውንም ሕገ መንግስታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ስልጣን ያለው መሆኑን ነው። አመልካች ያቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምርጫ ለማድረግ ወስኖ የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 351/2012 በማውጣት እና የምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም እያደረገ ያለው የምርጫ ዝግጅትና እንቅስቃሴ ከሕገ መንግስቱ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል ነው። ይህም የሚያሳየው አመልካች ያቀረበው ጥያቄ ምርጫን በሚመለከት የፌዴራል መንግስት እና ክልሎች ያላቸው ስልጣን ከሕገ መንግስቱ አንጻር በመመርመር ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ በመሆኑ ሕገ መንግስታዊ ጉዳይ ነው። በዚህ መሰረት ጉባኤው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 84 መሰረት ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ ስልጣን አለው።

የአመልካች የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የማቅረብ መብትን አስመልክቶ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 84(2) ስር ተደንግጓል። ድንጋጌውም እንደሚከተለው ይነበባል፤

"በፌዴራል መንግስትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጎች ከዚህ ሕገ መንግስት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩም በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳይ ሲቀርብለት (ጉባኤው ጉዳዩን) መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽኑን ምክር ቤት ያቀርባል።"

በተመሳሳይ ሁኔታ የአጣሪ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 5 ከፍርድ ቤት ውጭ የሚቀርቡ የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄዎች የሚመለከት ሲሆን በንኡስ አንቀጽ 3 ስር በፌዴራል መንግስትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጎች ከሕገ መንግስቱ ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በባለጉዳዩ ለጉባኤው ሊቀርብ እንደሚችል ተደንግጓል።

ከላይ ከተገለጸው የሕገ መንግስቱ እና የአዋጁ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው የሕግ ሕገ መንግስታዊነት ትርጉም ጥያቄ በፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዩ መቅረብ እንደሚችል ነው። በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 84(2) እና በአዋጁ አንቀጽ 5(3) የተገለጸው "ባለጉዳይ" የሚለው አገላለጽ አመልካችን የሚመለከት መሆን እና አለመሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ማቅረብ አንዱ የፍትህ ማግኘት መብት ነው። በመሆኑም ለዚህ ጉዳይ አወሳሰን የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 37 ፍትህ የማግኘት መብትን ከጉዳዩ ጋር አያይዞ መመልከት ተገቢነት አለው። በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37(1) መሰረት "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው" በማለት ተደንግጓል። በዚሁ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 2 ስር ደግሞ "በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ውሳኔ ወይም ፍርድ፦

ሀ) ማንኛውም ማሕበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል

ለ) ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው" ይላል።

ከዚህ የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው በሕገ መንግስቱ ከተረጋገጠው ፍትሕ የማግኘት መብት ለመጠቀም የጉዳዩ አቅራቢ የሆነው ሰው ውሳኔ ወይም ፍርድ እንዲሰጥበት በሚጠይቅበት ጉዳይ ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆን እንዳለበት ነው።

ወደ ቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ስንመለስ ጥያቄ አቅራቢው በምርጫ ተወዳድሮ በክልል ስልጣን ለመያዝ የፖለቲካ አላማ ይዞ በትግራይ ክልል የሚንቀሳቀስና ሥልጣን ላይ ካለው መንግስት ጋር ተወዳድሮ ሥልጣን ለመያዝ ተፎካካሪ ፓርቲ ሆኖ እያለ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ ባልቻለበት ሁኔታ ምርጫው ቢደረግ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን የመመረጥ መብት የሚያሳጣው በመሆኑ አመልካች መብት ወይም ጥቅም አለው። በዚህ መሰረት ጥያቄ አቅራቢው በክልሉ የወጣው የምርጫ ሕግ፣ የተቋቋመው የምርጫ ኮሚሽን እና አጠቃላይ የምርጫ ሂደቱን በመቃወም የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ለማቅረብ መብት አለው።

በአጠቃላይ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 84 መሰረት ጥያቄ አቅራቢው ባለጉዳይ ሆኖ የመቅረብ መብት ያለው መሆኑ እና ጉባኤውም ጉዳዩን ተቀብሎ ለመመርመር ሕገ መንግስታዊ ስልጣን ያለው መሆኑ ተረጋግጧል።

ከዚህ በተጨማሪ ጉዳዩ በጉባኤው ሊታይ የቻለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከዚህ ቀደም 6ኛው ሀገራዊ ጠቅላላ ምርጫ በተመለከተ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ላይ የመጨረሻ የሕገ መንግስት ትርጉም ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም አሁን በዚህ መዝገብ የቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በክልሉ ምርጫ ለማካሄድ የምርጫ ሕግ ማውጣቱ፣ የምርጫ ኮሚሽን ማቋቋሙ እና ሌሎች የምርጫ

እንቅስቃሴዎች ማድረጉን የተመለከተ ተጨማሪ ዝርዝር ጥያቄዎችን የያዘና ጥያቄውም የቀረበው በሌላ አካል በመሆኑ ነው።

**በቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ላይ በጉባኤው የተለዩ ዋና ዋና ጭብጦች እና ትንታኔዎች**

ከጥያቄ አቅራቢው አቤቱታ ለመረዳት እንደተቻለው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም የተሰጠውን ሕገ መንግስታዊ ትርጉም ባለማክበር እና የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ሕገ መንግስታዊ ስልጣን በመጋፋት ከህግ ውጭ ምርጫን ለማካሄድ የወሰነው ውሳኔ፣ ያቋቋመው ክልላዊ የምርጫ ኮሚሽን እና እያደረገ ያለው የምርጫ እንቅስቃሴ ከሕገ መንግስቱ ጋር ይቃረናል የሚል ነው። በዚሁ መሰረት ጉባኤው የሚከተሉትን ሁለት ዐበይት ጭብጦችን የለየ ሲሆን ጭብጦቹም፤

ሀ) በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት የምርጫ ሕግን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው ለማን ነው?

ለ) በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት መሰረት ጠቅላላ ምርጫን የማስፈጸምና የምርጫ ቦርድ የማቋቋም ስልጣን የማን ነው? የሚሉት ናቸው።

ጉባኤውም ከላይ በተለዩት ሁለት ዐበይት ጭብጦች ስር ለውሳኔ ሀሳብ አሰጣጥ እንዲመች ሌሎች ንዑስ ጭብጦችን ለይቶ ቀጥሎ ባለው አግባብ ተንትኗል።

**የምርጫ ሕግ የማውጣት ስልጣን በተመለከተ፣**

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 1 መሰረት ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ እና ዴሞክራሲያዊ የሆነ የመንግስት አወቃቀር እንዳላት ተደንግጓል። የፌደራል ስርአቱ ዝርዝር መገለጫዎች በሕገ መንግስቱ የመግቢያ ክፍል እና አንቀጽ 50 እስከ 52 ላይ ተደንግጓል። በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግስት እና በክልሎች ተዋቅሯል።

በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 39(1) እና (3) መሰረት ደግሞ ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፤ ብሔረሰብ፤ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን፤ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው። ይህ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት የሚመለከት ነው። ክልሎች ይህንን መብት ተግባራዊ የሚያደርጉት በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡትን የፌዴራልና የክልል ሥልጣን ክፍፍል ባከበረ መልኩ መሆን ይገባዋል።

በክልል እና በፌዴራል መንግስት መካከል ከተደረገው የስልጣን ክፍፍሎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ሕግን የማውጣት የስልጣን ክፍፍልን የሚመለከት ነው። የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ከሚወስኑበት አንዱ በመረጡአቸው

የፌደሬሽን ምክር ቤት

ተመራጮች መተዳደር ነው፡፡ ይህን የስልጣን ምንጭ የሆነውን ምርጫ የሚፈፀመውና የሚተገበረው በምርጫ ሕግ ነው፡፡ ይህን የምርጫን ሕግ የማውጣት ስልጣን በሕገ መንግስቱ ተደንግጓል፡፡

በክልል እና በፌዴራል መንግስት መካከል የሚደረግ ሕገ መንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል በሶስት መንገድ እንደተቀመጠ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 51፣ 52፣ 55 እና ከሌሎችም መረዳት ይቻላል፡፡ ለፌዴራሉ መንግስት በግልፅና በዝርዝር የተሰጡ ስልጣኖች ያሉ ሲሆን ለክልሎች ደግሞ በግልፅ የተሰጡ ስልጣኖች እንዲሁም በጋራ ለፌዴራሉ መንግስትና ለክልሎች የተሰጡ ያሉ ሲሆን በግልጽ ለፌዴራል መንግስት እና ለክልሎች ያልተሰጡ ስልጣኖች የክልሎች ስልጣን እንደሆኑ ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሰረት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 51 እና 55 ስር የተዘረዘሩት ስልጣንና ሃላፊነቶች በጥቅሉ ለፌዴራል መንግስት ማለትም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዝርዝር የተሰጡ ስልጣኖች ናቸው፡፡ እነዚህ ስልጣኖች ለፌዴራሉ መንግስት በግልፅና ለብቻው የተሰጡት በመሆናቸው ክልሎች በእነዚህ ዝርዝር ስልጣኖች ላይ ምንም ዓይነት ስልጣን የላቸውም፡፡

በሕገመንግስቱአንቀጽ 51(15) እንደተደነገገው የፌዴራሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ካሉት ስልጣንና ሃላፊነቶች ውስጥ አንዱ ምርጫን የሚመለከት ሕግ የማውጣት ሲሆን ድንጋጌው እንደሚከተለው ይነበባል፤

"በሕገ መንግስቱ የተረጋገጡትን የፖለቲካ መብቶች ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን እንዲሁም ምርጫን በሚመለከት ሕጎችን ያወጣል" ይላል፡፡ በሌላ በኩል የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 55(2) (መ) ደግሞ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት "በዚህ ሕገ መንግስት የተደነገጉትን የፖለቲካ መብቶች አፈፃፀምን እንዲሁም ምርጫን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ያወጣል" በማለት ተደንግጓል፡፡

ከእነዚህ ሁለት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ምርጫን በሚመለከት ሕግ የማውጣት ሕገ መንግስታዊ ስልጣንና ሃላፊነት በፌዴራል መንግስት ውስጥ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡ ይህ ምርጫን በሚመለከት ሕግ የማውጣት ስልጣን በሕገ መንግስቱ በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ ለፌዴራሉ መንግስት በዝርዝር ከተሰጠው ስልጣን ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ምርጫን በሚመለከት የክልል መንግስታት ወይም የክልል ምክር ቤቶች ሕግ ማውጣት አይችሉም፡፡

የኢትዮጵያ የፌዴራል ስርዓት በመከባበር ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ስርዓት መሆኑን በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 50 (8) ላይ ተደንግጓል፡፡ ድንጋጌውም ሲነበብ፡-

“የፌዴራሉ መንግስት እና የክልሎች ስልጣን በሕገ መንግስቱ የተወሰነ መሆኑን፤ ለፌዴራሉ መንግስት የተሰጠው ስልጣን በክልሎች መከበር አለበት፡፡ ለክልሎች የተሰጠው ስልጣን በፌዴራሉ መንግስት መከበር አለበት” በማለት ይደነግጋል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው በግልፅ እና በዝርዝር ለፌዴራሉ መንግስት የተሰጡትን ስልጣኖች ክልሎች ሊያከብሩት እንደሚገባና በሕገ መንግስቱ ለክልሎች በአንቀፅ 52 መሰረት የተሰጡት እና የተተውትን ስልጣኖችን የፌዴራሉ መንግስት ሊያከብራቸው ይገባል፡፡

በሕገ መንግስቱ በክልሎችና በፌዴራል መንግስቱ መካከል የስልጣን ክፍፍል ቢደረግም እንዲሁም አንዱ የአንዱን ስልጣን የማክበር ሃላፊነት ቢኖርባቸውም በሁለቱ መካከል ስልጣንን በሚመለከት ክርክር ወይም አለመግባባት ሊነሳ እንደሚችል ይገመታል፡፡ ለዚህም ሲባል ሕገ መንግስቱ እንዲህ ዓይነት አለመግባባቶችና ክርክሮች ሲነሱ ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሚቀርብበትንና የፌዴሬሽን ምክር ቤትም በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥበትን ስርአት የዘረጋው፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 9(1) መሰረት ሕገ መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደሆነና ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት እንደሌለው ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ሕገ መንግስቱን የማስከበር ለሕገመንግስቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህንኑ የሕገ መንግስቱን ድንጋጌ በመቃረን የሚወጣ ሕግን መርምሮ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የማድረግ ስልጣንና ሃላፊነትም የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡

የክልሉ ምክር ቤት ይህን የሕገ መንግስቱን ድንጋጌ በግልፅ በሚቃረን መልኩ በክልሉ ተፈፃሚነት የሚኖረው የምርጫ ሕግ ማውጣቱ በሕገ መንግስቱ በፌዴራል እና በክልል መንግስታት መካከል የተደረገውን ሕግ የማውጣት ሕገ መንግስታዊ የስልጣንን ክፍፍል የሚቃረን ነው፡፡ ስለዚህም አሁን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የቀረበበት እና በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት የወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012 በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ለፌዴራል መንግስት ብቻ በዝርዝር የተሰጠውን የምርጫ ሕግን የማውጣት ስልጣን ባለማክበር የወጣ በመሆኑ ሕገ መንግስቱን ይጥሳል፡፡

**ምርጫን የማስፈጸም ስልጣንን በተመለከተ**

በመቀጠል መመርመር ያለበት ሁለተኛው ጭብጥ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት መሰረት ምርጫን የማስፈጸም ስልጣን የማን ነው? የሚለው ነው፡፡

ከላይ በጭብጥ አንድ ስር እንደተመለከተው ምርጫን የተመለከተ ሕግ የማውጣት ስልጣን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51(15) እና 55(2(መ) መሰረት የፌዴራል መንግስቱ ስልጣን ሲሆን የምርጫ ቦርድን የማቋቋም እና ምርጫን የማስተዳደር ስልጣንም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 102 ስር በተደነገገው መሰረት የሚመራ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 102 በግልጽ እንደተደነገገው በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻ እና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሄድ ከማንኛውም ተጽዕኖ ነጻ የሆነ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ተቋቁሟል፡፡

በዚህ የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ መሰረት ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነው የምርጫ ቦርድ እንደ ሌሎቹ ሕገ መንግስታዊ ተቋማት ራሱን ችሎ ነጻነቱ ተጠብቆ በሕገ መንግስቱ በመቋቋሙ የተነሳ ምርጫን የተመለከቱ ጉዳዮችንም የማስተዳደር ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 103 (5) ስር የፌዴሬሽን ምክር ቤት የምርጫ ክልሎችን ለመወሰን መሰረት የሚያደርገው በሕገ መንግስቱ የተቋቋመው የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ ተመስርቶ መሆኑ ምርጫን ከማስተዳደር አኳያ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የምርጫ ቦርዱን አባላት አሰያየም በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 102(2) ላይ መደንገጉ የምርጫ ቦርድ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ ሀገራዊ ተቋም እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ሃገራዊ ተቋም የተመሰረተው በሃገሪቱ የሚካሄደው አጠቃላይ ሃገራዊ ምርጫ በቦታ ያልተገደበና በመላሃገሪቱበተመሳሳይጊዜ ወይም ወቅት ለማካሄድ ነው፡፡

የምርጫ ቦርድን ማቋቋም ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ዋናው ጉዳይ ክልሎች በዚህ ረገድ በሕገ መንግስቱ ያላቸውን ስልጣን የተመለከተ ነው፡፡ ከላይ ስለ ስልጣን በተመለከተው ክፍል እንደተገለጸው ምርጫን የተመለከተ ህግ የማውጣት ስልጣን የፌዴራል መንግስቱ መሆኑ በግልጽ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51(15) እና 55(2(መ)) ላይ የተደነገገ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 52 ስለ ክልሎች ስልጣን በተደነገገበት አንቀጽ ስር ምርጫን የተመለከተ በክልል ደረጃ ሊቋቋም የሚችል አካል ስለመኖሩ ስልጣን ያልተሰጠ እና ለክልሎች ያልተተወ ነው፡፡ ስለዚህ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 102 መሰረት ከተቋቋመው የምርጫ ቦርድ ሌላ ክልሎች በሌላቸው ስልጣን በክልል ደረጃ የምርጫ ቦርድም ሆነ የምርጫ ኮሚሽን የማቋቋም ሕገ መንግስታዊ መሰረት የላቸውም፡፡ ስለሆነም የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012ን በማውጣት በክልል የምርጫ ኮሚሽን ማቋቋሙ ሕገ መንግስቱን ይጥሳል፡፡

በዚህ ጭብጥ ስር ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ሌላው ጉዳይ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምርጫ ለማካሄድ መወሰኑና የምርጫ እንቅስቃሴ የመጀመሩን ሕገ መንግስታዊነት የተመለከተ



የፌደሬሽን ምክር ቤት

ነው። ከላይ በጭብጥ አንድ ስር እንደተገለጸው የምርጫ ህግን የማውጣት ስልጣን የፌዴራል መንግስቱ መሆኑንና ምርጫን የማስፈጸም ስልጣንም የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በመሆኑ በክልሉ የወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012ን መሰረት በማድረግ ክልሉ የሚያከናውናቸው ምርጫን የተመለከቱ ውሳኔዎች እና እንቅስቃሴዎችም ሕገ መንግስታዊ አይደሉም።

ከዚህ በተጨማሪ ከዚህ ቀደም የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም 6ኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ አስመልክቶ ያሳለፈውን የሕገ መንግስት ትርጉም ውሳኔ ማየቱ ተገቢ ይሆናል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ 6ኛውን ሀገራዊ ጠቅላላ ምርጫ ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በማከናወን ላይ ባለበት ሁኔታ በአለም አቀፍና በሀገራችን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በመከሰቱ ምርጫውን ባወጣው መርሃ ግብር መሰረት ማካሄድ የማይችል መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔ እንዲተላለፍ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው መሰረት ምክር ቤቱም በጉዳዩ ላይ ስልጣን ለተሰጠው ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ አቅርቧል። በቀረበው የትርጉም ጥያቄ ላይ አጣሪ ጉባኤውም ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ተቀብሎ የሕገ መንግስት ትርጉም ውሳኔ ሰጥቶበታል። በውሳኔውም የኮቪድ-19 አለም አቀፍ ወረርሽኝ የሕብረተሰብ ጤና ስጋት አለመሆኑ በሚመለከታቸው አካላት ከተረጋገጠ ጀምሮ ምርጫው ከ9 (ዘጠኝ) ወር እስከ 12 (አስራ ሁለት) ወር ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲካሄድ ውሳኔ ሰጥቷል። በተጨማሪም ምርጫ ተደርጎ የስልጣን ርክክብ እስከሚደረግ ድረስ የፌዴራል እና የክልል ምክር ቤቶች እና አስፈጻሚ አካላት ስልጣናቸውን ይዘው እንዲቀጥሉ ወስኗል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ይህንን የሕገ መንግስት ትርጉም ውሳኔ ለመስጠት ያስገደደው ምክንያት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሃገሪቱ መከሰቱ እና ይህን ተከትሎ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመታወጁ ምክንያት ነው። የውሳኔው ዋና አላማም የሕዝብን ጤንነት በመጠበቅ በሕገ መንግስቱ የተደነገጉ የምርጫ መስፈርቶችን ማለትም ሁሉ አቀፍ፣ ነጻ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በሚስጥር የሚሰጥበት ስርዓት የሚያሟላ ምርጫ ማካሄድ እንዲቻል ነው።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ አጠቃላይ ውጤት የሚኖረው መሆኑና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ውሳኔውን የማክበርና የመፈጸም ግዴታ እንዳለባቸው በአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 11 (1) እና 56(2) ተደንግጓል። በተጨማሪም ይህ የምክር ቤቱ ውሳኔ የአስገዳጅነት ውጤት ያለው እና በማናቸውም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ላይ ተፈፃሚ ነው። ሆኖም የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከላይ የተጠቀሰውን የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ መንግስት ትርጉም አስገዳጅ ውሳኔ የማክበር እና የመፈጸም ግዴታ ያለበት ቢሆንም በሕገ መንግስቱ ሕግ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

የማውጣትም ሆነ የማስፈጸም ስልጣን ሳይኖረው የምርጫ ጉዳይ ላይ ምርጫ ለማካሄድ መወሰኑና የምርጫ እንቅስቃሴ መጀመሩ ሕገ መንግስታዊ እና ሕጋዊ መሰረት የለውም።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ከሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር መርምሮ የሚከተሉትን የውሳኔ ሀሳቦች በሙሉ ድምጽ አቅርቧል።

1) የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ያወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012 ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51(15) እና 55(2)(መ) ጋር ይቃረናል በማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 84 መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

2) የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/20012ን መሰረት አድርጎ የምርጫ ኮሚሽን ማቋቋሙ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 102 ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጠውን ስልጣን ይጥሳል በማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 84 መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

3) የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት፣ አስፈጻሚ አካላት እና የምርጫኮሚሽን ምርጫን በሚመለከት ያወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012 ያሳለፏቸው ውሳኔዎች እና የፈጸሟቸው ተግባራት ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረኑ በመሆናቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት እንዳልተደረጉ የሚቆጠሩ፣የማይፀኑ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው ናቸው በማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 84 መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ የሕገ መንግስት ትርጉምና ማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ ከሕገ መንግሥቱና ሕገ መንግስቱን ተከትለው ከወጡ አዋጆች ጋር በማገናዘብ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ጉዳዩን በመምራቱ ቋሚ ኮሚቴው በጉዳዩ ላይ በጥልቀት ከተወያየበት በኋላ ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳቡን አቅርቧል። በዚሁ መሰረት ምክር ቤቱ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ ሰፊ ውይይት በማድረግ የትግራይ ክልል ያወጣው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 351/2012፤የምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም የሚያደርገው የምርጫ እንቅስቃሴ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 51 (15) ፣ 55 (2) (መ) እና 102 ድንጋጌዎችን የሚቃረን ሆኖ አግኝቶታል። በመሆኑም ምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ በመቀበል በሙሉ ድምፅ ወስኗል።



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

## ትእዛዝ

- የሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል ተቋማት የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲውቁት የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው።
- የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት።
- የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ።

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 6ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

የመ/ቁ. 91/13

አመልካች፡- አቶ ኡስማን ሰይድ

አድራሻ፡- አማራ ክልል

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ

አድራሻ፡- አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ መዝገብ የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 116251 የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ይቃረናል ሲሉ በ14/11/2009 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩም የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በአማራ ክልል መስተዳድር ደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 90 ፊደል 'ለ' ድንጋጌን በመተላለፍ ጌትነት ታምራት የተባለ አስመጪ በዲክላራሲዮን አሳውቆ ወደ አገር ውስጥ ለሚያስገባቸው ዕቃዎች ለጉምሩክ ቁጥጥር ዓላማ በሚደረግ አካላዊ ፍተሻ አመልካች በፍተሻ ኦፊሰርነት ስራቸው በአካል የመጡት ከዲክላራሲዮን ጋር በአባሪነት ከሚያያዝ ስታንዳርድ ዝርዝር የዕቃዎች መግለጫ ሰነድ ጋር በዓይነትና በብዛት አንድ ዓይነት መሆን አለመሆናቸውን በማረጋገጥ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍል በልዩነት መግለጫ ላይ ሪፖርት ማቅረብ ሲገባቸው አስመጭው ግለሰብ ለመንግስት መክፈል የነበረበትን ብር 346,127.42 /ሦስት መቶ አርባ ሥድስት ሺህ አንድ መቶ ሐያ ሰባት ብር ከአርባ ሁለት ሣንቲም/ እንዳይከፍል ስላደረጉ የማይገባቸውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለአስመጪው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ያለአግባብ የተገለገሉ በመሆኑ ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካችም ድርጊቱን አለመፈጸማቸውን ገልፀው አሉኝ የሚሏቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች አቅርበው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን የሰውና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች የሴቶች ፓንትና ማርከር ፈትሾ የብዛት ልዩነት የለበትም በማለት ቅጽ ሞልቶ ሪፖርት ስለማቅረቡ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ተጠሪ ቻርጀብል ባትሪን በተመለከተ የአገላለጽ ልዩነት እንዳለው ሪፖርት ያደረገበት ብቻ ነው፡፡ በዕቃ ፍተሻ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 40/2002 ዓ/ም አንቀጽ 2(5) መሠረት ልዩነት ማለት በተፈጸመው የጉምሩክ ወንጀል የተያዘው ዕቃ በተከፈለው እና በትክክል ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ መካከል ያለው የገንዘብ መጠን ስለሆነ በቻርጀብል ባትሪ ላይ የተገኘው የአገላለጽ ልዩነት በመንግሥት ገቢ ላይ ያስከተለው የገንዘብ መጠን ለውጥ አለመኖሩን የጉምሩክ የሥራ ሒደት ለዓቃቤ ሕግ የሥራ ሂደት በጻፈው ደብዳቤ አረጋግጦ በደንቡ ላይ ባገኙት ስልጠናም ሆነ በተግባር የሚታየው አሰራር የጭነቱ 20% እንደሚፈተሽ እንጂ የእያንዳንዱ ዕቃ 20% እንደሚፈተሽ አያመለክትም በማለት አመልካችን ከቀረበበት ክስ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 149(2) መሰረት በነጻ አሰናብቷል፡፡

የአሁን ተጠሪ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቀርቦለት ችሎቱ ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መርምሮ አመልካች የተከሰሰበት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ተሽሮ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 የተተካና የተጠሪ ድርጊት በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 መሰረት የጉምሩክ ወንጀሎች ተብለው በተጠቀሱት ድንጋጌዎች ሥር የማይሸፈን መሆኑን ገልጾ የአመልካች ድርጊት በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 ፊደል 'ሀ' ድንጋጌ መሠረት ወንጀል መሆኑ አልቀረም ብሏል፡፡ ስለሆነም አመልካች የፈጸሙት ድርጊት በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ወንጀልነቱ በዝምታ የታለፈ ስለሆነ የወንጀል ኃላፊነት የለም የሚለውን መከራከሪያ ባለመቀበል የወንጀል ተጠያቂነቱን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113(2) መሰረት ቀይሮ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ዓ/ም አንቀጽ 9(1)(ሀ) ሥር ጥፋተኛ ነው ሲል የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ የደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት አመልካች ጥፋተኛ የተባሉ መሆኑን አውቆ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ የቅጣት ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት ለስር ፍ/ቤት መልሷል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለጉባኤው ባቀረቡት አቤቱታ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ችሎት በስር ፍ/ቤቶች በነፃ ተሰናብቼ እያለሁ ውሳኔውን በመሻር ድርጊቱ ተፈፅሟል በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ ያልነበረውን አዋጅ በመጥቀስ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም። ክስ በተመሰረተበት ጊዜ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/07 በስራ ላይ አልነበረም። እንዲሁም የተከሰስኩበት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/01 በተሻረበት ሁኔታ ችሎቱ በጊዜው ያልነበረውን አዋጅ በመጥቀስና በሕገ መንግስቱ በአንቀፅ 22 እና 9(1) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ አይደለም በማለት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል።

ጉባኤውም አመልካች የጉምሩክ አዋጅ ቁ. 622/2001 ጸንቶ ባለበት የፈጸሙት ድርጊት ወንጀል በመሆኑ ተከሰው ክሱ በሂደት ላይ እያለ ይህ አዋጅ በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 859/2006 የተተካ መሆኑን እና በዚህ አዋጅ የአመልካች ድርጊት ወንጀል መሆኑ በመቅረቱ ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው ፍ/ቤት አመልካች በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 9(1)(ሀ) ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱን ለመገንዘብ ችሏል።

በአመልካች ላይ የቀረበው ክስ አመልካች የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 90(ለ) ማለትም የተሰጠውን ስልጣን በግልጽ ተግባር ወይም በግድፈት ያለአግባብ የተገለገለ እንደሆነ ከሶስት እስከ አስር አመት በሚደርስ እስራት በሚያስቀጣው አንቀጽ ስር መከሰሳቸው መዝገቡ ያስረዳል። ክሱ በሂደት ላይ እያለ የጉምሩክ አዋጅ ቁ. 622/2001 ተሽሮ በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 859/2006 መተካቱንና በጉምሩክ አዋጅ 622/2001 መሰረት ወንጀል የነበሩ ድርጊቶች አዲሱ አዋጅ በዝምታ ያለፈው ስለመሆኑ ለመረዳት ተችሏል። ስለዚህ አመልካች የተከሰሱበት አዋጅና ህግ ተፈፃሚ ሳይሆን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ባልተከሰሱበት የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 9(1)(ሀ) ማለትም "የተሰጠውን ሹመት፣ ስልጣን ወይም ኃላፊነት በግልጽ ተግባር ወይም በግድፈት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከስራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ስልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሰራበት እንደሆነ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ አመት በማያንስ ቀላል እስራትና ከሶስት ሺ.ህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአስር አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአስር ሺ.ህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል" በሚለው የአዋጅ ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱን ተመልክተናል።

የወንጀል ህጉ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሆኖ ይህንን የሚያደርገው በተለያዩ አይነት ያሉ ድርጊቶችን በድንጋጌ በመከልከል ወንጀል አድራጊዎች ቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

እንዲቀጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙና ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈጽሙ ማስቻል በመሆኑ በፍ/ቤቶችም የሚሰጡ ውሳኔዎች አስተማሪና ተገማች ሆኖ ክስ በቀረበበት ህግ ስር ተከሳሾችን በቀረበው ማስረጃ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ በህጉ አግባብ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠት ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ከላይ በተገለፀው መሰረት በአመልካች ላይ የቀረበው ክስ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 90(ለ) ሲሆን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9(1)(ሀ) ስር በመውሰድ ክስ የቀረበበትን አንቀጽ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 113(2) በመለወጥ ነው፡፡

የወ/ሥ/ሥ/ህ.ቁ.113 አፈጻጸም የሚመለከተው በተለይ የተፈጸመው ወንጀል ዐይነት የሚያጠራጥር በሆነ ጊዜ መሆኑ አንቀጹ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 113(2) መሰረት "የቀረበው ማስረጃ ተከሳሹ በተጨማሪ የሚያስከስሰው ወንጀል ከሆነና ፍ/ቤቱም ወንጀሉን ለማየት ስልጣን ያለው ከሆነ ክስ ባይቀርብበትም በዚሁ ወንጀል በተከሳሹ ላይ መፍረድ ይቻላል፡፡ ይሄውም ተጨማሪ ከክሱ ውስጥ ያለውን ወንጀል አነስተኛ ወንጀል ሆኖ ሲገኝ ነው " ይላል፡፡ አመልካች ክስ ሲቀርብባቸው በሙስና ወንጀል ያልተከሰሱ ሲሆን በሙስና ወንጀል ጉዳይ ማስረጃቸው አቅርበው የመከራከር እድል አልተሰጣቸውም፡፡ አመልካች በተከሰሱበት የጉምሩክ ወንጀል እንዲከላከሉ በተሰጣቸው እድል መሰረት በቂ ማስረጃ አቅርበው ከክሱ ነጻ የተባሉ በመሆናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣን ያለው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የማስረጃ ምዘና ውስጥ በመግባት አመልካች ባልተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት እና ድርጊቱ ሲፈጸም በስራ ላይ ባልነበረው አዋጅ ጥፋተኛ ናቸው ማለቱ ከሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 20 እና 21 ለተያዙ እና ለተከሰሱ ሰዎች ካረጋገጣቸው መብቶች ጋር የሚቃረን ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ፈጸሙ የተባለው ድርጊት የጉምሩክ አዋጅ ቁ. 622/001 ጸንቶ እያለ ሲሆን ጉዳዩ ውሳኔ ያገኘው ይህ አዋጅ በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 859/2006 ተተክቶ ባለበት በመሆኑ የፌዴራል ሰበር ችሎት ጸንቶ ያለውን የጉምሩክ አዋጅ ወደጎን በመተው አመልካች ባልተከሰሱበትና የመከራከር እድል ባላገኙበት በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 9(1)(ለ) ስር በተደነገገው አመልካች ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከህገ መንግስት አንቀጽ 22 ጋር ስንመለከት ህጋዊነቱ ቀሪ ያልሆነውን የጉምሩክ አዋጅ ቁ. 859/2006 ተፈጻሚ ማድረግ ሲገባው በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 9(1)(ሀ) በተደነገገው ድንጋጌ አመልካችን ለድርጊቱ ሀላፊ ማድረጉ ከሕገ መንግስቱ ጋር

የሚቃረን ሆኖ በመገኘቱ ውሳኔው የህገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረቡን መረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 859/2006 በዝምታ የታለፈ በመሆኑ ባልተከሰሱበት የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁ. 881/2007 ጥፋተኛ ሊባሉ አይገባም በማለት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ አግባብነት ያለው ሆኖ ስለተገኘ ምክር ቤቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 116251 ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22ን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተፈጻሚነት አይኖረውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ትእዛዝ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 116251 ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ስለሚቃረን ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ ውሳኔ የሰጠ ስለሆነ ይህንኑ አውቆ የምክር ቤቱ ውሳኔ ተግባራዊ እንዲያደርግ የምክር ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በምክር ቤቱ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፤ 4ኛ ዓመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ
ሰኔ 02 ቀን 2011 ዓ.ም

የመ/ቁ. 66/11

አመልካች፡- አቶ ንጉሴ ሀድጎ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል አቃቤ ሕግ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

አመልካች ነሀሴ 5 ቀን 2008 ዓ.ም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤው ያቀረቡት አቤቱታ ከአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን የጅምላ ንግድ ፍቃድ እያለኝ ቅርንጫፍ መ/ቤት ስትከፍት ለዞኑ ንግድ መምሪያ ሳታሳውቅ ፤የንግድ ፈቃድ ኮፒ፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ኮፒ ሳትሰጥና ፈቃድ ሳትጠይቅ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በቄለም ወለጋ ዞን ዳሌ ወበራ ወረዳ አካባቢ በርበሬ ገዝተሀል በማለት በወንጀል ተከስሼ የንግድ ፈቃዴን አሳይቼ እያለ ፍ/ቤቶች ጥፋተኛ በማለት በሰጡት ውሳኔ 3 አመት እስራትና የብር 30,000(ሰላሳ ሺህ ብር ) የገንዘብ መቀጮ እንዲሁም የጫንኩት 169 ኪሻ ሚጥሚጣ እንዲወረስ የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን በህገ መንግስቱ የተሰጠኝን ተዘዋውሮ የመስራት መብት የሚጥስ ስለሆነ የህገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥልኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ክሳሽ አቃቤ ህግ ሆኖ አመልካች የወንጀል ህጉን አንቀፅ 32(1) ሀ እና የንግድ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6(4) እና 60(3) በመተላለፍ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በቄለም ወለጋ ዞን ዳሌ ወበራ ወረዳ ቂሬሞ መንደር 11 እና 12 ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ለወረዳው ንግድ ጽ/ቤት ማሳወቅ እያለበት ሳያሳውቅ 169 ኩንታል ሚጥሚጣ ግምቱ ብር 82,000(ሰማንያ ሁለት ሺህ ብር) ገዝቶ ጭኖ ሊወጣ ሲል የተያዘ ሲሆን ለሚመለከተው አካል ሳያሳውቅ ቅርንጫፍ በመክፈት የንግድ ስራ ላይ የመሰማራት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካችም ለዚሁ የወንጀል ክስ ባቀረበው የመከላከያ መልስ አመልካች ቅርንጫፍ አልከፈትኩም፣ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ወሎ ዞን የሰጠኝ የንግድ ፍቃድ ግገርውን ለመፈጸም በቂ ነው ሌላ ፍቃድ ማውጣት አይጠበቅብኝም፣ ሽያጭ አልፈጸምኩም በማለት የተከሳሽነት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡ አመልካችን ጨምሮ በዐቃቤ ሕግ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የበርበሬ ግገርውን መፈጸሙን ለፍ/ቤት

አሳውቀዋል፡፡ በተጨማሪም ከወረዳው ንግድ ጽ/ቤት በተጻፈ የጽሁፍ ማስረጃ አመልካች ቅርንጫፍ የመክፈት ንግድ ፈቃድ የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ገልጸዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች እና የጽሁፍ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ በአማራ ክልል የተሰጠው የንግድ ፍቃድ አመልካችን ከዚህ የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት ሊያድነው ይችላል ወይስ አይችልም? ይህ የወረዳ ንግድ ጽ/ቤት ለአመልካች ፈቃድ ስለከለከለው ያለፈቃድ መግባት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉትን ሁለት ጭብጦች ይዞ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች አሁን ንግድ እያካሄደ ያለው በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ውስጥ በመሆኑ ቅርንጫፍ ለመክፈቱ ለጽ/ቤቱ ማሳወቅ ነበረበት፣ ያለፈቃድ መግባት አይችልም በማለት በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6(4) መሰረት አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በ3 ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

ተጠሪ ለኦሮሚያ ክልል ለቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ጠይቆ አመልካች የጫነው 169 ኪሻ ሚጥሚጣ ከወንጀል ፍሬ የተገኘ ነው በማለት እንዲወረስ ተወስኗል፡፡አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡በመጨረሻ ጉዳዩን የተመለከቱት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች የማስፈቀጃ ማመልከቻውን ከመረመረ በኋላ አያስቀርብም ሲሉ መዝገቡን ዘግተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በእጄ ላይ የንግድ ፍቃድ እያለ ከሌላ ክልል የገዛሁት በርበሬ ፍቃድ ሳትጠይቅ መግባትህ ወንጀል ነው ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱ እኔ አመልካች ሀገር አቀፍ የንግድ ፍቃድ ኖሮኝ እያለ በህገ መንግስቱ ላይ በተቀመጠው መሰረት ተዘዋውሬ የመስራት መብቴን የሚጥስ ነው የሚል ነው፡፡

አጣሪ ጉባኤው የአመልካችን አቤቱታ አያይዘው ካቀረቧቸው የፍርድ ቤቶች ውሳኔ ፣ ከአዋጅ ቁጥር 686/2002 አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ከህገ መንግስቱ አንጻር መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም ጉዳዩን በድጋሚ የተመለከተው የዳሌ ወበራ ወረዳ ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት አመልካች በተጠሪ የተከሰሱት አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6(4) እና 60(3) እንዲሁም የወንጀል ህጉን አንቀጽ 32(1)ሀ በመተላለፋቸው ነው የሚል ሲሆን አመልካችም የበርበሬ ግዢ ፈጽምኩ እንጂ አልሸጥኩም፣ለመግባት ፍቃድ አያስፈልገኝም፣ የጅምላ ነጋዴ ስለመሆኔ የንግድ ፈቃድ መያዜን በመግለጽ በርበሬ ገዝቼ ብሸጥ ኖሮ ቅርንጫፍ መክፈት ያስፈልገኝ ነበር አሁን ግን ግዢ ብቻ ስለሆነ ቅርንጫፍ መክፈት አያስፈልገኝም የሚል ነው፡፡ በፍ/ቤቱ ውሳኔ ውስጥ የተካተተው ለጉዳዩ የዳሌ ወበራ ወረዳ ንግድ እና ገበያ ልማት ጽ/ቤት በቁጥር 334 በቀን 26/07/2006ዓ.ም የሰጠው የጽሁፍ ማስረጃ አመልካች የንግድ ፍቃድ የሌለው መሆኑን ይገልጻል፡፡

አመልካች ከአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን ተሰጠኝ በማለት ያቀረቡት የንግድ ፈቃድ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 መሰረት የተሰጠ የበርበሬ ጅምላ ንግድ ፍቃድ ሲሆን በዚሁ አዋጅ

የጅምላ ሻጭ ማለት የንግድ እቃዎችን ከአምራች ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለቸርቻሪ የሚሸጥ ሲሆን አመልካች በዚሁ መሰረት ተመዝግቦ የበርበሬ ጅምላ ንግድ ለመነገድ የንግድ ፈቃዱን የወሰደ መሆኑን እንረዳለን ፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት መግቢያ ላይ እንደተገለጸው አንድ አይነት ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ ዜጎች በሀገራቸው ውስጥ በማናቸውም ሁኔታ ተዘዋውሮ የመስራት፣የመንቀሳቀስ እና ንብረት የማፍራት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

አመልካች ግኘ በመፈጸም የተከሰሰበት አዋጅ የወጣበት ዋነኛው አላማ የንግዱ ዘርፍ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚደግፍበትን ሁኔታ በማጠናከር የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን በአግባቡ በማደራጀት የንግዱን ዘርፍ ጎጂና ተገቢ ካልሆነ እንቅስቃሴ የመከላከል፣በንግዱ ዘርፍ መንግስት ሊኖረው የሚገባውን መረጃ በአግባቡ ለመያዝ የሚያስችል ሁኔታ ለማመቻቸትና ለንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6 መሰረት ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ የሚመዘገበው ዋናው መስሪያ ቤት ባለበት ስፍራ ነው፡፡በተለያዩ ክልሎች የተለያዩ የንግድ ስራ ቢሰራም በንግድ መዝገብ የሚመዘገበው አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑንና ይህም የሚሆነው በዋናው መ/ቤት ባለበት ስፍራ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ነገር ግን በዚሁ አዋጅ ቁጥር 6(4) በብዙ ስፍራዎች ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት የሚከፍት ማንኛውም ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት ቅርንጫፍ መ/ቤቱ በሚገኝበት ስፍራ ላለው መዝጋቢ መስሪያ ቤት አግባብነት ያለውን ማመልከቻ ቅጽ በመሙላትና የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ በማያያዝ የቅርንጫፍ መስሪያ ቤቱን አድራሻ እና ልዩ የምዝገባ መለያ ቁጥሩን ሊያሳውቅ እንደሚገባ አስቀምጧል፡፡

አመልካች የተከሰሰበት ቅርንጫፍ መ/ቤት ለመክፈት ሳያሳውቁ የንግድ ስራ ሰርተዋል በማለት የአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6(4) በመተላለፉቸው የተመሰረተባቸውን ክስ መሰረት በማድረግ በዚሁ አንቀጽ 6(4) እና 60(3) መሰረት ጥፋተኛ የሚል ሲሆን አጣሪ ጉባኤው አመልካች በክሱ ላይ የተጠቀሰውን አንቀጾች በመተላለፍ የተሰራ ወንጀል አለ በማለት ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ ነው አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምሯል::

የዳሌ ወበራ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች ለተከሰሱበት ቅርንጫፍ ሳይከፍቱ ግገር መፈጸም ክስ አመልካችን ጥፋተኛ የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስቻለው አመልካችን ጨምሮ በዐቃቤ ሕግ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የበርበሬ ግገሩን መፈጸሙን ለፍ/ቤት በሰጡት ምስክርነት ነው፡፡ በተጨማሪም በወረዳው ንግድ ጽ/ቤት የተጻፈው የጽሁፍ ማስረጃ አመልካች ቅርንጫፍ ከፍቶ የመስራት ንግድ ፈቃድ የሌለው መሆኑን ጠቅሰው የጻፉትን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

በሕገ መንግስቱ፡ አንቀጽ 22(1) ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ እና አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡

አመልካች በኦሮሚያ ክልል ዳሌ ወበራ ወረዳ በርበሬ ግገር መፈጸማቸውን እሳቸውም አምነው የሰጡትን ቃል የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም ግገርውን ተዘዋውረው ሲፈጽሙ ማየታቸውን እንጂ ሲሸጡ እንዳላዩ መስክረዋል፡፡ አመልካች ነጋዴ ለመሆናቸው ከአማራ ክልል የተሰጠ የንግድ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን አሳውቀዋል፡፡ አመልካች በተከሰሱበት የአዋጁ ድንጋጌዎች የንግድ ስራ ለመስራት ቅርንጫፍ ለመክፈት የሚፈልግ ነጋዴ ቅርንጫፍ ሊከፍት በሚፈልግበት ቦታ ለሚገኝ የንግድ ጽ/ቤት ስራውን ከመጀመሩ በፊት  የንግድ ፍቃዱንና ቲን ኮፒ በማቅረብ ማሳወቅ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡

ሆኖም የአመልካች ድርጊት ግገር ሲሆን በተከሰሱበት አዋጅ ድንጋጌ ላይ የሚወድቅ የወንጀል ድርጊት አይደለም፡፡የአመልካችን ድርጊት ስንመረምር ከኦሮሚያ ክልል ግገርውን መፈጸሙ የወንጀል ድርጊት ለመሆኑ በአዋጁ/በሕግ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡

ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የፍ/ቤቶች ውሳኔ በህገ መንግስቱ፡ አንቀጽ 22 እና 32 የተደነገጉትን ማንም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት ድርጊቱ፡ በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም የሚለውን ድንጋጌ እንደዚሁም የአመልካችን ተዘዋውሮ የመስራት ነጻነት ሕገ መንግስታዊ መብት የሚጋፋ በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው ለምክር ቤቱ፡ የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ለሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶለት ቋሚ ኮሚቴው የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብና የምክር ቤቱ፡ ባለሙያዎች የሰጡትን አስተያየት በማጣመር የውሳኔ ሀሳቡን ለምክር ቤቱ፡ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን እና የቋሚ ኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ በማጣመር መርምሯል፡፡በዚህም መሰረት የዳሌ ወበራ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች ለተከሰሱበት ቅርንጫፍ ሳይከፍቱ፡ ግገር መፈጸም ክስ አመልካችን ጥፋተኛ የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስቻለው አመልካችን ጨምሮ በዐቃቤ ሕግ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የበርበሬ ግገርውን መፈጸሙን ለፍ/ቤት በሰጡት ምስክርነት ነው፡፡ በተጨማሪም በወረዳው ንግድ ጽ/ቤት የተጻፈው የጽሁፍ ማስረጃ አመልካች ቅርንጫፍ ከፍቶ የመስራት ንግድ ፈቃድ የሌለው መሆኑን ጠቅሰው የጻፉትን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

በሕገ መንግስቱ፡ አንቀጽ 22(1) ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ እና አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡

አመልካች በኦሮሚያ ክልል ዳሌ ወበራ ወረዳ በርበሬ ግገር መፈጸማቸውን እሳቸውም አምነው የሰጡትን ቃል የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም ግገርውን ተዘዋውረው ሲፈጽሙ ማየታቸውን እንጂ ሲሸጡ እንዳላዩ መስክረዋል፡፡ አመልካች ነጋዴ ለመሆናቸው ከአማራ ክልል የተሰጠ የንግድ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን አሳውቀዋል፡፡ አመልካች በተከሰሱበት የአዋጁ ድንጋጌዎች የንግድ ስራ ለመስራት ቅርንጫፍ ለመክፈት የሚፈልግ ነጋዴ ቅርንጫፍ ሊከፍት በሚፈልግበት ቦታ ለሚገኝ የንግድ ጽ/ቤት ስራውን ከመጀመሩ በፊት የንግድ ፍቃዱንና ቲን ኮፒ በማቅረብ ማሳወቅ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡

ሆኖም የአመልካች ድርጊት ግገር ሲሆን በተከሰሱበት አዋጅ ድንጋጌ ላይ የሚወድቅ የወንጀል ድርጊት አይደለም፡፡ የአመልካች ድርጊት ሲመረመር ከኦሮሚያ ክልል ግገርውን መፈጸሙ የወንጀል ድርጊት ለመሆኑ በአዋጁ/በሕግ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡

ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የፍ/ቤቶች ውሳኔ በሕገ መንግስቱ፡ አንቀጽ 22 እና 32 የተደነገጉትን ማንም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት ድርጊቱ፡ በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም የሚለውን ድንጋጌ እንደዚሁም የአመልካችን ተዘዋውሮ የመስራት ነጻነት ሕገ መንግስታዊ መብት የሚጋፋ በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አጣሪ ጉባኤውና ቋሚ ኮሚቴው ያቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 እና 32 ድንጋጌዎችን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግስቱ፡ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ፡ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና በየደረጃው ያሉ የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ውሳኔ በምክር ቤቱ፡ ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቀው እንዲያስፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. አጣሪ ጉባኤው ለምክር ቤቱ፡ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአመልካቹ ይሰጥ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ አመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሰኔ 3 ቀን 2012 ዓ.ም

የፋ/ቁ.73/11

አመልካች፡- አቶ እሸቱ ውብሸት

አድራሻ፡ አልተጠቀሰም

ተጠሪ፡- ዐቃቤ ሕግ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበለትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

ውሳኔ

አመልካች መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ.ም ለሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ ፅፈው ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ሃሣብ ከወ/ሮ ፍጹም ክብረት ጋር የእህት እና የወንድም ግንኙነት ያለን ሲሆን ግለሰቧ ከአረብ ሀገር ቆይታዋ በ1995 ዓ.ም ስትመለስ በነበረባት የገንዘብ እጥረት ከቀረጥ ነፃ መኪና ገዝቶ የማስገባት መብቷን መጠቀም ያልቻለች በመሆኑ ውክልና ሰጥታኝ በ1996 ዓ.ም ወደ ዱባይ ሄጀ በራሴ ገንዘብ ሌሎችንም ወጪዎች ሸፍኜ አሁን የታርጋ ቁጥሩ 2-51205 የሆነ የቤት መኪና ገዝቼ ነበር። ገቢዎችና ጉሙሩክ በ3ኛ ወገን መኪና ያስገባን ሰዎች የመንግስት ታክስ እንድንከፍል ባስገደደንም መሰረት ተገቢውን ታክስና ቅጣት ከፍዬ ስጨርስ ተጠሪ መኪናውን እንዳስረክባት የጠየቀችኝ ሲሆን እኔም ያወጣሁትን ወጪ ከፍለሽ ውሰጂ ብላትም ፍቃደኛ ሣትሆን ቀርታ የፍ/ብሔር ክስ መስርታብኝ ክርክር ላይ እያለን በክርክሩ ወጪዬን እንደምትከፍል ስታውቅ የወንጀል ክስ መሰረተችብኝ። በወንጀል ክሱ ጉዳዩን አይቶ ውሣኔውን የሰጠው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የፍታብሔር ጉዳይ ሆኖ ሣለ እንደዚሁም በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 2224 መሰረት ወካይ ለተወካይ ሊከፍለው የሚገባውን ገንዘብ ጨርሶ እስከሚከፍለው ድረስ ተወካይ ከተረከበው ንብረት ውስጥ ተመጣጣኙን በእጁ ለማቆየት የሚችል መሆኑ ተደንግጎ እያለ በዚሁ መሰረት የያዝኩትን መኪና እንደ እምነት ማጉደል ድርጊት በመቁጠር ውሣኔውን ሰጥቷል። በመሆኑም ወንጀል ባልሆነ ጉዳይ መቀጣቴ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 22 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ኢትዮጵያ ተቀብላ ያፀደቀቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶችን ይጥሣል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

ጉዳዩን በዐ/ሕግ ክስ አቅራቢነት በመጀመሪያ የተመለከተው የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በሰጠው ውሣኔ አመልካች የቀረበበት ክስ ተነቦለት ከተረዳ በኋላ ሲጠየቅ ውክልና መውሰዴ እውነት ነው፣ ይሁን እንጂ እምነት ማጉደል የለብኝም፣ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ሙሉ በሙሉ ክዷል በማለት የግራ ቀኙን የሰነድ እና የሰው ምስክሮች ማየቱን እና መስማቱን በመጥቀስ አመልካች በዐ/ሕግ በቀረበበት ማስረጃ የተመሰከረበት መሆኑ ተጠቅሶ እንዲከላከል መባሉን ጠቅሷል፡፡ በመጨረሻም የዐ/ሕግ ምስክሮች በክሱ መሰረት አመልካች በውክልና ምክንያት ከውጭ ሀገር ያስገባውን መኪና በግል ተበዳይ ገንዘብ የተገዛ መሆኑን በሰው እና በፅሁፍ ማስረጃ ማረጋገጡን በመጥቀስ በሌላ በኩል አመልካች ባቀረባቸው የመከላከያ ማስረጃዎች ማስተባበል አለመቻሉን በመጥቀስ በወንጀል ህግ አንቀፅ 676/2/ መሠረት ጥፋተኛ በማድረግ በ2 ዓመት ከ6 ወር እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አያስቀርብም ሲል ወስኗል፡፡

በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አመልካች በውክልና ውል መሰረት በእጁ የገባውን መኪና ከከለከለ የግል ተበዳይ በሕግ በመካከላቸው ባለው የውክልና ውል ላይ በመመስረት በፍታብሔር ክርክር ከምትጠይቀው በቀር የውል ግዴታውን አልተወጣም በሚል በእምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቅበት ሕግ ስለሌለ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 23/2/ ስር የተደነገገው መስፈርት አልተሟላም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመሻር ውሣኔውን ሰጥቷል፡፡

በጉዳዩ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል ወስኗል፡፡

በመጨረሻ በጉዳዩ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስቀርቦ መርምሯል፡፡ በምርመራውም አመልካች ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ ክርክር ያስነሣው መኪና በተጠሪ እጅ የገባው በውክልና መሰረት መሆኑን አልካዱም መኪናው በግል ተበዳይ ስም ቢሆንም አመልካች መኪናውን በግል ገንዘቤ ገዝቼ መኪናውን ወደ ሀገር ውስጥ አስገብቻለሁ፣ ይህ ስለመሆኑ ስር ፍ/ቤት አስረድቻለሁ በማለት ያቀረቡት የመከራከሪያ ነጥብ ማስረጃ ምዘናን የሚመለከት በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕገ መንግስቱ መሰረታዊ የህግ ስህተትን ለማረም ከተሰጠው ስልጣን ስር የሚሸፍን አይደለም ሲል ጠቅሷል፡፡ በመቀጠልም የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 676/2/ /ሀ/ን በመጥቀስ የእምነት ማጉደል ወንጀል በተወካይ (በውክልና መሰረት) ሲፈፀም ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል እንደሚሆን በማተት



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራሽን ምክር ቤት

እንደዚሁም ቀደም ሲል በሌላ መዝገብ የሰጠውን ተመሣሣይ ውሣኔ በማስታወስ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ አመልካች የፌ.ጠ. ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 22(1) የተደነገገውን የሚጥስ ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ይስጥልኝ በማለት ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ጉባኤውም ጉዳዩን መርምሮ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የሕገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ እና የምክር ቤቱን ባለሙያዎች አስተያየት በማጣመር ከተወያየበት በኂላ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሰረት አመልካች ቅሬታ ያቀረቡበት የፍ/ቤት ውሳኔ የሕገ መንግስት ጥሰት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች ዋነኛ ቅሬታ የወንጀል ድርጊት ባልሆነ ተግባር እንደወንጀል ተቆጥሮ መቀጣቴ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 22/1/ ይጥሣል የሚል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ በተደረጉ ክርክሮች ግራ ቀኙን የሚያከራክራቸው ነጥብ አከራካሪው መኪና በማን ገንዘብ ተገዛ በሚለው ነጥብ ላይ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር የውክልና ግንኙነት የነበራቸው መሆኑ ያልተካደ ነው፡፡ የአመልካች ክርክር አከራካሪውን መኪና በተሰጠኝ ውክልና ከውጭ ሀገር ሳስገባ መኪናው የተገዛበት እና ሌሎች ወጪዎችን ስላወጣሁ ወካዩ /የግል ተበዳይ/ ትክፈል የሚል መሆኑን መረዳት የሚቻል ነው፡፡

"የእምነት ማጎደል ወንጀል /Criminal Breach of trust/ በወንጀል ሕጉ 676/2/ /ሀ/ መሰረት የእምነት ማጉደል ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት የሚቻለው በቀዳሚነት ገንዘብ ወይም ዕቃ ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት በአደራ የተቀበለ ሰው በሕግ ወይም በውል ስምምነት በእምነት የተረከበውን ይህን ገንዘብ ወይም ዕቃ ወይም ሌላ ዓይነት ንብረት ለግል ጥቅሙ ወይም ለሦስተኛ ሰው ጥቅም ያዋለ እንደሆነ ነው፡፡" በማለት ተደንግጓል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ አንደኛ አደራ ሰጪው በአደራ ተቀባዩ ላይ እምነቱን በመጣል ለተወሰነ ጊዜ ንብረቱን እንዲያቆይለትና በጠየቀው ጊዜ እንዲመልስለት በማሰብ አደራ ማለቱን፣ ሁለተኛ አደራ ተቀባይ የአደራ ጠባቂነቱን ኃላፊነት ለመወጣት መስማማቱን፣ ሦስተኛ አደራ ተቀባዩ ከአቅሙ በላይ በሆነ

ችግር ምክንያት አደራውን ለመወጣት ባይችል ሁኔታውን ወዲያውኑ ለአደራ ሰጭው ሲያስታውቀው ግዴታ እንዳለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

የእምነት ማጉደል ወንጀል በአደራ የተሰጠውን ገንዘብ ወይም ንብረት የአደራ ሰጭውን /የግል ተበዳዩን/ ጥቅም መጉዳት ብቻ ሳይሆን ድርጊቱ ከእምነት ማጉደል የመነጨ፣ ይኸውም ከክፉ ልቦና የመነጨ መሆን እንዳለበት በተጨማሪ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ንብረቱ ከአያያዝ ጉደለት፣ ከሙቀት ወይም ከቅዝቃዜ ተፅዕኖ ወይም በቅድሚያ የጠፉበት እንደሆነ አደራ ተቀባዩ ለንብረቱ በፍትሐብሔር ተጠያቂ ከሚሆን በቀር በእምነት ማጉደል ወንጀል ድንጋጌ የሚጠየቅበት መንገድ ዝግ ነው፡፡ እንደዚሁም አደራ ተቀባዩ በአደራ የተቀበለው ገንዘብ ወይም ንብረት ለአደራ ሰጭው ጥቅም ያዋለው እንደሆነ ለምሳሌ የአደራ ሰጭውን ዕዳ ለመክፈል ሲል ይህ ድርጊት ከአደራ ሰጭው ፈቃድ ውጭ ሆኖ የፍትሐብሔር ጉዳይ ከሚያስነሳ በቀር በእምነት አጉዳይነት የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅበት ሁኔታ የለም፡፡ በተመሳሳይ የእምነት ማጉደል ወንጀል ከፍትሐብሔር የውል ማፍረስ ድርጊት ለመለየት ልንመለከተው የሚገባ ድንጋጌ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2/ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 676/2//ሀ/ የሚወድቅ የእምነት ማጉደል ወንጀል ድርጊት አድራጊው የተጣለበትን አደራ በማፍረስ ገንዘቡን፣ ዕቃውን ወይም የተረከበውን ሌላ ንብረት ለግል ጥቅሙ ለማዋል ግልጽ ዓላማ (criminal intention) ይዞ የተነሳ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

በአደራ የተረከበውን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለግል ጥቅሙ ማዋል (embezzlement)፣ የተረከበውን ዕቃ ሳይሰረቅ ተሰርቋል ማለት፣ ትክክለኛውን ንብረት በተመሳሰለ ዕቃ ቀይሮ መመለስ /ማጭበርበር/፣ ንብረቱን መረከቡን መካድ በአንቀጽ 676/2/ /ሀ/ ስር ተጠያቂነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ እነዚህና መሰል ሁኔታዎች የወንጀል ድርጊቱን ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታ (mensrea) የሚያሟሉ ናቸው፡፡ በማናቸውም ሁኔታ ግን ለእምነት ማጉደል ወንጀል ተጠያቂነት አንድን ንብረት በአደራ መስጠትን እንደ ቅድመ ሁኔታ ታሳቢ ያደርጋል፡፡ የእምነት ማጉደል ድርጊት ከስርቆት የሚለይበትም ዋናው መሰረቱ ይኸው ንብረትን በአደራ የመስጠት ሁኔታ ነው፡፡

አሁን ከያዝነው ጉዳይ አኳያ ዘርዘር ተደርጎ መመርመር ያለበት የውል ስምምነቱ በተለይ የውክልና ውል ኃላፊነት ከእምነት ማጉደል ተጠያቂነት ጋር ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ ነው፡፡ የአለመግባባቱ ምክንያት እንደአመልካች ክርክር ገንዘቤ እስኪሰጠኝ ድረስ መኪናውን አላስረክብም የሚል ነው፡፡ ጎልቶ መውጣት ያለበት ጭብጥ ከውል ጋር በተያያዘ አንደኛው

ተዋዋይ ወገን ግዴታውን ባለመፈጸሙ ሁለተኛው ተዋዋይ ወገን የአንደኛውን ተዋዋይ እምቢተኛነት ተንተርሶ እሱም በተራው እምቢተኛ ከሆነ ክርክሩ መሰማት ያለበት በፍትሐብሔር ሕጉ መሰረት ነው ወይስ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 676/2/ /ሀ/ የሚለው ይሆናል፡፡

ከመዝገቡ እንደምንረዳው ተከሳሽ መኪናውን በግል ተበዳይ ስም እና ለግል ተበዳይ ጥቅም ከውጭ አገር አለማስመጣታቸውን በመካድ የተከራከሩበት ጊዜ የለም፡፡ ክርክራቸው መኪናውን እንዳስረክብ የመኪናው ዋጋ በቅድሚያ ይከፈለኝ የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ የሕጉ መሰረቶች ሦስት ናቸው፡፡ አንደኛ ጥሬ ገንዘብ ወይም ዕቃ በአደራ መቀበል፣ ሁለተኛ ዕቃውን ለመመለስ እምቢተኛ መሆን እና ሦስተኛ ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሀሳብ ናቸው፡፡

ተከሳሽ በአንደኛ እና በሁለተኛ ነጥብ ላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ይመለከታቸዋል፣ መኪናውን ገዝተዋል፣ ወደ አገር ውስጥም አስገብተዋል፡፡ ንብረቱ በግል ተበዳይ ስም እና ለግል ተበዳዩ ጥቅም እንዲውል አስበው የገዙት በመሆኑ በአደራ እንደተረከቡት አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ሆኖም ሦስተኛውን የወንጀሉ አቋቋሚ ጉዳይ በተመለከተ በፍ/ቤቶቹ የጥፋተኝነት ውሳኔ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675/3/ ተጠቅሷል፡፡ ድንጋጌው እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

"ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሃሳብ እንዳለው ይቆጠራል፡፡" በሚል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ድንጋጌው ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሀሳብ እንዳለ ግምት የሚወሰድበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን ከድንጋጌው ዝርዝር ውስጥ አንድ ሰው በእጁ በገባው ንብረት ላይ መብት አለኝ በሚል የሚያነሳው ሕጋዊ ክርክር ያላግባብ የመበልጸግን ሀሳብ እንደሚያሳይ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም ሦስተኛውን የወንጀል አቋቋሚ በተመለከተ፣ የአመልካች ክርክር ከመነሻው ጀምሮ ለአከራካሪው መኪና ያወጣውት ወጪ ይከፈለኝ የሚል መሆኑን ስንመለከት፣ የክርክሩ ውጤት በፍትሐብሔር ክርክር ከሚወሰን በቀር ሦስተኛው የወንጀል አቋቋሚ አመልካችን ይመለከታቸዋል ለማለት የወንጀል ሕጉን ከሚገባው በላይ በማስፋት ወይም በመለጠጥ መተርጎም ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የወንጀል ሕግ በጠባቡ ይተርጎም ከሚለው እንደዚሁም አንድን ተከሳሽ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የወንጀል ድርጊቱ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ መንገድ መረጋገጥ ይገባዋል ከሚለው መርህ ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ከመሆኑም በተጨማሪ

በሕገ መንግስታችን አንቀፅ 22/1/ “ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም።...” በሚል የተደነገገውን መብት የሚቃረን ነው። በመሆኑም የፌዴራል ጠቅለላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስቱን ስለሚቃረን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

<u>ትእዛዝ</u>

1. በኦሮሚያ ክልል አዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን በምክር ቤቱ መወሰኑን አውቀው በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽሙ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
2. የፌዴራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መጽደቁን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ 37/09

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣
መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም

አመልካች፡- እነ ውዱ ተስፋሁን (3 ሰዎች)

ተጠሪ፡- አቶ ለገሰ በላይ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ፣

ጉዳዩ የተጀመረው በትግራይ ክልል፣ ምእራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የስር ከሳሾች እነ ውዱ ተስፋሁን (3 ሰዎች) በወልቃይት ወረዳ ዓዲ ረመጽ ከተማ የሚገኘውን የመሬት ይዞታችንና ቤታችንን አቶ ለገሰ በላይ ይዞ ስለሚገኝ እንዲለቅልን ይወሰንልን ሲሉ ክስ በማቅረባቸው ሲሆን ከሳሾች የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ስለሆኑ በአዋጅ ቁ.25/1988 አንቀጽ 5(2) መሠረት መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ የፍትሀ ብሔር ክርክሮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን መሆኑ የተደነገገ ስለሆነና የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የፌዴራሉን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን ደርበው እንደሚሰሩ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(4) የተደነገገ በመሆኑ የትግራይ ክልል ምእራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና ምስክሮቻቸውን ሰምቶ የመሬት

ይዞታውና ቤቱ የእነ ወ/ሮ ውዴ ተስፋሁን (3 ሰዎች) ነው በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የስር ተከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) አቶ ለገሰ በላይ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የምእራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የመሬት ይዞታውና ቤቱ የአሁን ተጠሪ የአቶ ለገሰ በላይ ነው በማለት ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የአሁን አመልካቾች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረብ እንደማይችል በመግለጽ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በመቀጠል የአሁን አመልካቾች እነ ውዴ ተስፋሁን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን የሚያቀርቡበት ጊዜ ጠቅላይ ስላለፈባቸው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርበው ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ማስፈቀጃውን ተቀብሎ ይግባኛቸውን በአስር ቀናት ውስጥ እንዲያቀርቡ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመቅረቡና ሰበር ሰሚ ችሎቱም ጉዳዩ መታየት የሚገባው በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በመሆኑም ለሁለተኛ ጊዜ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት በማጣቱ ሬጅስትራሩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ በመሆኑ የአመልካቾች የይግባኝ መብት፣ ፍትህ የማግኘትና የመሰማት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው መጣሱን ገልጸው የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የአመልካቾችን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 የተደነገገውን

ፍትህ የማግኘት መብትን ይቃረናል፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡